ትግላችን

የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ

ቅፅ ሁለት

ሌ/ኮሎኔል
መንግሥቱ ኃይለ ማርያም

ትግላችን

የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ

ቅፅ ሁለት

ሌተና ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

ታኅሳስ 2008 ዓ.ም
መጋቢት 2008 ዓ.ም

ማውጫ

ምስጋና..5

መግቢያ..6

ክፍል አሥራ አንድ

አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከትግል ወደ ድል ከድል ወደ ትግል የኢትዮጵያ አብዮተኞች የ17 ዓመታት አብዮታዊ ገዞ..9

ክፍል አስራ ሁለት

ዘመቻ ላሽ..19

ክፍል አሥራ ሦስት

የፐሬዝዳንት ዚያድ ባሬ መንግሥት ውድቀት አገማሚያና መቃረቢያ.......52

ክፍል አስራ አራት

ኤርትራ..66

ክፍል አስራ አምስት

የኤርትራ ክልል ህዝብ ፌደሬሽኑን ለማፍረስ የወሰነው ፌደሬሽኑ ከመቋቋሙ በፊት ነው................94

ክፍል አስራ ስድስት

በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ የተቋቋመውና በአገራችን ሰሜን ምሥራቅና ደቡብ አረቦች ያወጁብንን የእጅ አዙር ጦርነት ግልፅ ወረራ ለመከላከል እጣው የሆነው የመከላከያ ሠራዊታችን አጭር ታሪክ........................135

ክፍል አሥራ ሰባት

ለኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክልል ድንበርና ለህዝቡ ማህበራዊ ደህንነት ጥበቃ የተሰማራው ሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር ከገንጣዮች ጋር ያደረገው ፍልሚያ..149

ክፍል አሥራ ስምንት

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ ማህበራዊ አብዮት መፈንዳት፣ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በአገሪቱ ምሥራቅና ደቡባዊ ክልል ጠረፎች ከተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጋር ለውጊያ መፋጠጥ፣መላዋ ኢትዮጵያ በአብ ዮት ማዕበል መናወጥ፣ የኤርትራ ገንጣዮች መናጠጥና ረዥሙ የእርስ በርስ ጦርነት መጧጧፍ ጅምር................................168

ክፍል አስራ ዘጠኝ

ገንጣዮች የውጊያ ስልታቸውን በመለወጥ ደረጃ በደረጃ በሠራዊታችን ላይ ተከታታይ ጥቃት መሰንዘርና ብለውም የክፍለ ሃገሩን ርዕሰ ከተማ አስመራን መክበብ..201

ክፍል ሃያ

ከተሰነይና ከናቅፋ ውድቀት በኂላ ሁለቱም ገንጣይ ድርጅቶች በተለያየ ጊዜና በፈረቃ ባሬንቱን ለመቆጣጠር ያደረጉት ያልተሳካ ጥረት፣ የአቆርዳትና የከረን መያዝ...219

ክፍል ሃያ አንድ

ድል አድራጊው ሃያሉ አብዮታዊ ሠራዊታችን ፊቱን ወደ ሰሜን ያዞራል በምሥራቅ የተገኘው ድል በሰሜንም ይደገማል 245

ክፍል ሃያ ሁለት

አብዮታዊ የጦር ኃይሎችና የሲቪል መከላከያ ድርጅት ከአገር መከላከያ ኢንዱስትሪዎች ጋር ለማቋቋም የታቀደ እቅድ.................................278

ክፍል ሃያ ሦስት

ብሄራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻ.......................................312

ክፍል ሃያ አራት

ከጦርሜዳ ወታደራዊ ድል በኂላ ከውስጥና ከውጭ ጠላቶቻችን ጋር የተደረገ አዲስ የሰላም ጥረትና ሠላምን ፍለጋ ወደካርቱም ጉዞ...........346

የቃላቶች ትርጉም...395

ዋቢ መፃህፍት...398

ምስጋና

የኢትዮጵያን ህዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ አንድን ስፅፍ እንደ አደረጉልኝ ሁሉ ይህንንም ቅፅ ሁለትን ሳዘጋጅ፣ ወዳጄ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል አምባሳደር ፍሰሀ ገዳ እና ከቤተሰቦቼም ልጆቼና ባለቤቴ ለሰጡኝ ድጋፍና ትብብር፣ በእጅ ጽሁፍ ያዘጋጀሁትን የመጽሃፉን ረቂቅ በኮምፒውተር በመተየብ ለረዳችን ለወ/ት ማህደር አየለ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ።

መግቢያ

በብርቱ ጥንቃቄ በታላቅ ትዕግሥትና በረቀቀ የትግል ሥልት የተመራውን ታላቁን የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮት ፍፁም በማያስፈልግ ደም የበከለው ራሱን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢ.ሕ.አ.ፓ) ብሎ የሚጠራው የፖለቲካ ድርጅት የአመራር አካላትና አባላት ቅሪት የሆኑ፣ ከታሪክ የማይማሩ፣ ጊዜና እድሜ የማይለውጣቸው፣ የጥፋት መልዕክተኞች በሰሜን አሜሪካ ያሳተምኩትን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ አንድ የመጀመሪያ ህትመት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተሰራጭቶ እንዳይነበብ ብለው በአከናወኑት አሳዛኝና አሳፋሪ ሻጥር ምክንያት ከመጀመሪያው ህትመት አንድ አራተኛው እንኳን ለአንባቢ ባለመዳረሱና አሳታሚው ድርጅት በደረሰበት ከፍተኛ የገንዘብ ኪሣራ ምክንያት ሁለተኛ ህትመት ማሳተም አልቻለም።

ብዙ የደከምኩበት የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ አንድ አብዛኛው አንባቢ እጅ ሳይደርስ ከንቱ በመባከኑ ወይንም በመውድሙ በእጅጉ እያዘንኩ የመጽሐፉን የተሟላ ይዘት ባያካትት ወይንም ባይተካም የመጽሐፉ ዋና ዋና ትኩረቶች የሆኑትን ማለትም የመጀመሪያውን አምስት ዓመታት አብዮታዊ የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል ሂደት፣ የተቀዳጀናቸውን አኩሪ ድሎችና ለድሎቹ ግኝት የኢትዮጵያ ሕዝብ የከፈላቸውን መስዋዕትነቶች መጽሐፉን አግኝተው ለማንበብ ላልቻሉ አንባቢዎች የተወሰነ ሃሳብ ወይንም ግንዛቤ ሊሰጥ ይችል ይሆናል ብዬ በማሰብ በቅፅ ሁለት እንደ መቅድምና መግቢያ በማድረግ የቅፅ አንድን መቅድምና መግቢያ ከመጀመሪያው የአብዮቱ የአምስት ዓመታት ታሪክ እንደ ታሪኩ የአቀራረብ ቅደም ተከተል ከክፍል አንድ እስከ ክፍል አስር ያሉትን ዋና ዋና ክፍለ አርዕስቶች መልሼ ከዚህ እንደሚከተለው ለአንባቢ አቅርቤአለሁ።

ሀ) የታሪኩ መግቢያ ከሆኑት ፍሬ ነገሮች፡-

1ኛ ስለ ጥንታዊት ኢትዮጵያ፣ ስለ አክሱም መንግሥት አነሳስና ሥልጣኔ፣ በመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ሁኔታዎች፣ የአክሱማዊያን መንግሥት ፍፃሜና የዛጉዌ ነገሥታት አነሳስ፣ ከዛጉዌ ነገሥታት ውድቀት በኋላ የመጡ የሸዋ ነገሥታትን የጠበቁዋቸውን ሥራዎችና የገጠሟቸውን ፈተናዎች፣ የኢማም አህመድ ግራኝ ኢትዮጵያን የእስልምና እምነት ተከታይ ሕዝብ ብቻ አገር ለማድረግ የመራውን አመፅ፣ የኦሮሞ ማህበረሰብን ፈለሳና ብሎም ወረራ፣የሥርዓተ አልበኛ መሳፍንቶች ዘመን፤

2ኛ) የዘመነ ኢምፔሪያሊዝምን ሁኔታዎች፣ የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎችና የአካባቢያችን ባዕዳን ተስፋፊዎች በኢትዮጵያ ላይ ያደረጓቸውን ከበባዎችና ወረራዎች በድህረ ፋሽስት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት የኢትዮጵያ ሁኔታ የኢትዮጵያዊያን ጀግንነትና አይበገሬ አርበኝነት፤

ለ) ወደ አብዮቱ ታሪክ በመግባት

1ኛ በታሪኩ ክፍል አንድ፤

የታላቁን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት መቃረቢያ፣ ዋዜማና አጥቢያ፤ በጉልታዊት ኢትዮጵያ ትምህርትና ተማሪው እንዲሁም አዲሱ ምሁር፣ በአብዮቱ መቃረቢያ የጊዜ ክልል ውስጥ የነበረውን የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች፣ የአብዮቱን ዋዜማና አጥቢያ፤

2ኛ በክፍል ሁለት፤

የአብዮቱን ማግሥት፤ ስለደርግና የልጅ እንዳልካቸው መንግሥት፣ ደርግ ከልጅ ሚካኤል እምሩ መንግሥት ጋር ያደረገው ቆይታ፣ ዘውዱን ለመገርሰስ የደርጉ የመጨረሻ ዝግጅቶች፣ ደርግና ሌ/ጀነራል አማን ሚካኤል አንዶም፣ ደርግና የደርጉ ምክትል ሊቀመንበር የነበረው ሌ/ኮሎኔል አጥናፉ አባተ፣ ደርግና አፄ ኃይለሥላሴ፣ የጉልታዊውን ሥርዓተ ማህበር ላዕላይና ታህታይ መዋቅር ስለማፈራረስ፤

3ኛ በክፍል ሦስት፤

መሬት ለአራሹ የገጠሩን የእርሻ መሬት የአርሶ አደሩ ይዞታ የሚያደርገው አዋጅ ጥናትና መሰናዶ፣ የእድገት በህብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ፣ የመጀመሪያውን የኢትዮጵያ ገበሬዎች፣ የቀበሌ ማህበር ወደ ከፍተኛ ንቃት፣ ድርጅት፣ ምርትና ማህበራዊ ይዞታ የማሸጋገር እመርታ፤

4ኛ በክፍል አራት፤

የሠራተኛው መደብና የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ አደረጃጀት፣ የኢትዮጵያ ሠራተኞች መተዳደሪያ ህግ፣ የሠራተኛው ማህበርና የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ አደረጃጀት፣ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ የዕደ ጥበቡ ኢንዱስትሪ፤

5ኛ በክፍል አምስት፤

በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ለሠላም የተደረጉ ጥረቶች፣ አብዮታዊት ኢትዮጵያን ለማዳን አማራጭ የሌለው መድሃኒት፣ በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ የሠላም ጥረት በኢትዮጵያዊያን መካከል ስለ ኤርትራ ክፍለ ሃገር ችግር ሠላማዊ መፍትሄ ለማግኘት የተደረጉ ጥረቶች፣ ከሱማሌ ተስፋፊ መንግሥት ጋር ወደ ጦርነት ላለመሄድ በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ የተደረጉ የሠላም ጥረቶች፤

6ኛ በክፍል ስድስት፤

የውጭ ጥቃቶች፣ ከውጭ የተሰነዘሩብን ጥቃቶች አብዛኛዎቹ በጠላቶቻችን ብርታት ወይንም ጥንካሬ ሳይሆን በኛ ድክመትና የዋህነት ነው፣ በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት፣ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት፣ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት፤

7ኛ በክፍል ሰባት፤

ሃገርንና አብዮትን የማዳን ጦርነት ዝግጅት፣ የታጠቅ የጦር ሠፈር ምስረታ ወይንም ግንባታ፣ የኢትዮጵያ ህዝባዊ ሠራዊት አመሰራረት ወይንም መቋቋም፣ ህዝባዊ ሠራዊታችንን ለማስታጠቅ የተደረጉ ጥረቶች፣ የአብዮታዊው የመከላከያ ሠራዊት አደረጃጀት፣ ዓለምን ያስደነቀው የኢትዮጵያ አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊት አገሩንና አብዮቱን ከወራሪዎች ለመከላከል ወደ የጦር ግንባሩ ከመሰማራቱ በፊት ያሳየው የጀግኖች ሠልፍ፤

8ኛ በክፍል ስምንት፤ አገርንና አብዮትን የማዳን ፍልሚያ የሱማሌን መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጥቃት ለመከላከል በምሥራቅና በደቡብ ግንባሮች አብዮታዊ ሠራዊታችን ያደረገው ትግል፣ በሐረርጌ፣ በባሌና በሲዳሞ ክፍለ ሃገራት ደጋማ አውራጃዎች ለሰባት ወራት የተደረገ የመከላከል ትግል፣ በኔ የተመራው የኢትዮጵያ ልዑካን ከሞስኮ ሲመለ በአዲስ አበባ የጠበቀን የኢ.ሕ.አ.ፓ ነጭ ሽብር ዝግጅት፣ የኢ.ሕ. አ.ፓ አደገኛ ሴራ በቆሬ የጦር ግንባር፣ የኢትዮጵያ አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊት በደቡብና በምሥራቅ የጦር ግንባር ከመከላከል የሱማሌን መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ወደ ማጥቃት እርምጃ መሸጋገር፣ ለመልሶ ማጥቃቱ የተደረጉ መሰናዶዎች፣ ወራሪው የሱማሌ መንግሥት የጦር ኃይል ሐረርጌን ለመያዝ ያደረገው የመጨረሻ ጥረት፤

9ኛ በክፍል ዘጠኝ፤

ከመከላከል ወደ ማጥቃት፣ ለመልሶ ማጥቃት ውጊያ የተደረጉ መሰናዶዎች፤

10ኛ በክፍል አስር፤

ማጠቃለያ- ያሸነፈው አብዮት ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ አንድ የያዘው የአብዮታችንን የመጀመሪያውን የአምስት ዓመታት የትግል ሂደት ሲሆን በአስር ዋና ዋና ክፍሎችና በአርባ ምዕራፎች ተጠቃሏል::

ይህ ሁለተኛው ቅፅ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ የሁለተኛውን አምስት ዓመታት አብዮታዊ የትግል ታሪክ ዝርዝር በመጽሐፉ መግለጫ አምድ በአግባቡ የተገለፀ ስለሆነ አንባቢ አንብቦ መረዳት እንደሚችለው ቅፅ ሁለት 14 ዋና ዋና ክፍሎችንና 60 ምዕራፎችን ይዟል::

ትግላችን

ክፍል አሥራ አንድ

አብዮታዊትኢትዮጵያ ከትግል ወደ ድል፤ ከድል ወደ ትግል የኢትዮጵያ አብዮተኞች የ17 ዓመታት አብዮታዊ ጉዞ

ምዕራፍ አንድ

የተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት በአብዮታዊው የኢትዮጵያ ሠራዊት መልሶ ማጥቃት ሲመታ የምዕራቡ ዓለምና የአረብ አድህሮት ኃይላት ያሰሙት ጩኸት።

በኢትዮጵያና በሱማሌ መንግሥት የጦር ኃይሎች መካከል ለሰባት ወራት የተካሄደው ውጊያ በኛ አብዮታዊ ሠራዊት አሸናፊነት ወደ መጠናቀቁ ቢተቃረበበት ወቅት የተሸናፊውን የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ሽንፈትና ሽሽት የተመለከቱና የሰሙ የአረቡና የምዕራቡ ዓለም በአጠቃላይ፣ የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት በተለይ በመሸሽ ላይ ያለውን ወራሪ የሱማሌ መንግሥት ሠራዊት የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት እግር በእግር ተከታትሎ በማሳደድ ወደ ሱማሌ መንግሥት ግዛት በመግባት አፀፋ የበቀል ወረራ ያደርጋል ብለው በማመን በፀረ ኢትዮጵያና በፀረ ሶቪየት የአንድነት ግንባር ፈጥረው በጦርነቱ ጊዜ ለተስፋፊው የሱማሌ መንግሥትና ለወራሪ ሠራዊቱ ማበረታቻ የፖለቲካ፣ የፕሮፖጋንዳ፣ የሞራልና የቁሳቁስ ድጋፍ ከመስጠት ባሻገር ኢትዮጵያ አበቃች አለቀላት በማለት ሲያሟርቱ የነበሩት መንግሥታት ሁሉ ታላቅ የፕሮፖጋንዳና የፖለቲካ ዘመቻ በማድረግ ከጣራ በላይ መጮህ ጀመሩ።

አሜሪካኖች ለተወሰነ ጊዜ ማቀዝቀዝ ብቻ ሳይሆን ረስተውት የነበረውን ዴታንት (detente) ማለትም የካፒታሊስቱና የሶሻሊስቱ ዓለም ተቻችሎ በሰላም የመኖርና የመሣሪያ ቅነሳ (disarmament) ውሎች ተከታታይ ድርድር በአስቸኳይ እንዲቀጥል ከመጠየቅ ባሻገር የኢትዮጵያ ሠራዊት በመልሶ አጥቂነት ወይንም ወራሪነት ሱማሌ መንግሥት ግዛት ውስጥ ቢገባ በሁለቱ ኃያላን መንግሥታት መካከል እስከዚያ ጊዜ ድረስ የተደረጉትን የሰላም ውሎች ሊያፈርስ የሚችል ታላቅ መዘዝ እንደሚያስከትል በመግለፅ ዛቻና ማስጠንቀቂያዎችን ለሶቪየት ህብረት መንግሥትና ለወዳጆቹ ሁሉ ሲፅፉ ለእኛም ለየትና ጠለቅ ያለ ትዕዛዝ መሰል ማስፈራሪያ ደብዳቤ ደረሰን።

የኢምፔሪያሊስቱ ዓለምና አረቦች ያሰሙት ጩኸት እነሱ ቀደም ብለው የሱማሌን መንግሥት በመገፋፋት የፈፀሙት ዓለም አቀፍ ወንጀል ስጋት ላይ ስለጣላቸው እንጂ ስለእኛ የበቀል ወረራ ዕቅድ ያገኙት መረጃ ኖሮአቸው አልነበረም።

አቋም በተመለከተ እንደሚታወቀው የቆምንለት ሕዝባዊ ዓላማ አገርንና አብዮትን የማዳን እንጂ አንድነታችንንና አብዮታችንን ለባስ አደጋ ለሚዳርግ ጀብደኛ እርምጃ የተገበዘን አልነበርንም:: አንባቢ እንደሚያስታውሰው አብዛኛው የኤርትራ ክፍለ ሃገር ምድር በጀብሐና በሻዕቢያ ቁጥጥር ሥር ውሎ የአስመራ፣ የምፅዋና የባሬንቱ ከተሞች ከአንድ ዓመት በላይ ከመከበባቸው ሌላ-

1ኛ የአገራችን ሰሜን ምዕራብ ክልሎች የተወሰኑ ክፍሎች ራሱን «የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ህብረት» (ኢዲዩ) ብሎ በሚጠራው ተስፋ ለዘውድ የፊውዳሎች ጥርቅም ድርጅት ተወሯል::

2ኛ በአብዛኛው የመሀል አገር ክፍለ ሃገሮች ውስጥ በወታደራዊ የውጊያ ሥርዓትና ሥልት ባይሆንም ራሱን « የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ» ብሎ በሚጠራው ድርጅት የሚያካሂደውን ነጭ ሽብር ሙሉ በሙሉ ለመግታት አልተቻለንም ነበር::

3ኛ የሰሜን ምስራቁ ክልል በአጠቃላይ የአሰብ ወደብ አካባቢና አሰብን ከአዲስ አበባ የሚያገናኘው አስፋልት አውራ ጎዳና ወትሮ ከሚሰጠው በላይ የላቀ አገልግሎት መስጠት ብቻ ሳይሆን በጦርነቱ ምክንያት የወሳኝነትም ባህሬ ያለው ሆኖ ሳለ በአፋር ፀረ-አብዮተኞችና በወያኔዎች ተፅእኖ ሥር ነበር ማለት ይቻላል::

4ኛ በአገሪቱ ምዕራብና ደቡባዊ ክልሎች ራሳቸውን የኦሮሞ፣ የሲዳማ፣ የጌዴዎ ወዘተ ነፃ አውጭ እያሉ ከሚጠሩና ከታጠቁ የቀድሞ የመሬት ከበርቴ ፊውዳሎች ጋር ሕዝቡና አብዮታዊ ሠራዊታችን ይታገሉ ነበር::

5ኛ በሲዳሞ፣ በባሌና በሐረርጌ ክፍለ ሃገሮች ከወራሪው የሱማሌ ሠራዊት ጋር አብረው የሚወጉን ምንደኞች ወራሪው የሱማሌ መንግሥት ሠራዊት ሲፈረጥጥ በየክፍለ አገራቸው ከተሞችና ገጠሮች በደፈጣ ውጊያ ከኋላ ሲያጠቁን የተቀሩት መሣሪያቸውን በመሸሸግ ሰላማዊ ዜጎች መስለው ከህዝቡ ጋር በመቀላቀል ሌላ አመቺ ጊዜና ሁኔታዎችን ሲጠብቁ የነበሩት ከህዲዎች ቁጥር ቀላል አልነበረም::

አገርንና አብዮትን ማዳን በተሰኘው የትግል መርሆአችን መሰረት ከምሥራቁ ድል በኋላ የኛ ቀዳሚ ትኩረትና ተከታዩ የውጊያ ስትራቴጂ በአስቸኳይ ፊታችንን ወደነዚህ የጉያ እሳት ወደ ሆኑብን የውስጥ ጠላቶች ማዞር ነበር:: ዋናው ወዳጅ የሶቪየት ህብረት መንግሥትና የተቀሩትም መላው ህብረተሰብአዊ አገሮች ራሳችንን ከመከላከል ሌላ ጎረቤት አገርን እንድንወር ፍፁም እንደማይተባበሩንም እናውቅ ነበር::

በምስራቁ ውጊያ ከጎናችን ተሰልፈው ከተዋጉት የኩባ የጦር ክፍሎች ውስጥ አንድ ወጣት መኮንንና ለሠራዊታችን የህክምና አገልግሎት ሲሰጡልን ከነበሩ የሶቪየት ህብረት ዜጎች መካከል አራት ሐኪሞችን የኦሮሞ ነፃ አውጭ ነን ባዮች ከሐረር

ከተማ አፍነው ወደ ሞቃዲሾ ወሰዷቸው። ከዚህ በተጨማሪ ስድስት የሱማሌን ተዋጊ ሚግ አውሮፕላኖች የጣለው የህብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ብሄራዊ ጀግና ሻምበል ለገሰ (በኋላ ብ/ጀነራል) በሞቃዲሾ ብቸኛና ልዩ ጨለማ ወህኒ ቤት ከኩባው መኮንን ጋር ተዘግቶባቸው በመሰቃየት የአእምሮ ህሙማን ሆነዋል የሚል መረጃ ደርሶናል።

ከጦርነቱ በፊት በኦጋዴን ክልል በተለያዩ የመንግሥት ስራዎች በተለይም በህክምና ስራ፣ በመምህርነት፣ በተለያዩ የግል ሥራዎችና በንግድ ተዳዳሪ የነበሩና ሱማሊኛ ቋንቋ ተናጋሪ ያልሆኑ በሺህ የሚቆጠሩ ዜጎቻችንን ወራሪው ሠራዊት በኃይል አስገድዶ ወደ ሱማሌ ርዕሰ ከተማ ሞቃዲሾ በመውሰድ ለየመንግሥቱ ባለሥልጣኖች በባርነት የቤት አገልጋይ ከማድረግ ሌላ የተለያዩ ከባድና የግዴታ የጉልበት ሥራ እየሰሩ በግፍ አገዛዝ ለሚሰቃዩት ወገኖቻችን ቅድሚያውን በመስጠት በዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ትብብርና እንዲሁም በምርኮ ልውውጥ ሕግ ነፃ የማውጣት ዓላማ ስለነበረን ከወታደራዊ ድላችን በኋላ ከሱማሌዎች ጋር ሌላ ውጊያ ሳያሻን የሰላም ውይይት የመጀመር እቅድ ነበረን።

ምዕራፍ ሁለት

የሱማሌ መንግሥት አመራር አካላት ዳግም መሳሳትና ፀብ አጫሪነት

ከኢትዮጵያ ህዝብ ታሪካዊና የመደብ ጠላቶች ጋር ወግነው አገራቸውንና ወገናቸውን የሚወጉት ገንጣይ አስገንጣዮችና አድህሮት «የጠላቴ ጠላት» በማለት ተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ስለ ኢትዮጵያ ማወቅ የሚፈለገውን ማናቸውንም የአገር ገበናና በተለይም በአገራችን ውስጣዊ የፀጥታ ችግር ላይ ያተኮረ ወታደራዊ መረጃ ስለሚያቀርቡለት በዚህ ረገድ ለጠላት በእጅጉ የተጋለጥን ነበርን ማለት ይቻላል::

በሱማሌ ወራሪ ሠራዊት ላይ ከተቀዳጀነው የተሟላ ወታደራዊ ድላችን ማግሥት ብዙዎች እንደ ገመቱትና እንደ ጠበቁት ወራሪውን የጠላት ሠራዊት እያሳደድን ወደ ሱማሌ ግዛት ጠልቀን በመግባት ከመበቀል ፋንታ እርቅና ሰላም እንዲወርድና የምርኮኞች ልውውጥ እንዲደረግ የመሞከር ሰላማዊ ጥረታችንን በድክመት በመገመት ሠራዊታቸው ሸሽቶ ከአገራችን ከወጣ በኂላ እንደተለመደው ጨርቅ የለበሱ ልዩ የደፈጣ ተዋጊዎችን አስርገ በማስገባት ዳግም የኦጋዴን ክልል ነዋሪ የሆኑትን ዜጎቻችንን ሰላም መንሳት፣ ማሸበርና መዝረፍ ተጀመረ::

በተለይ አብዮታዊ ሠራዊታችን ፊቱን ወደ ሰሜን ካዞረበት ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ የሰሜኑን ገንጣይና አስገንጣይ አጋሮቻቸውን በተራቸው ለመርዳት ይመስላል በኦጋዴን ክልል ተጨማሪ ኃይል አስርገ በማስገባት የየብስ መገናኛ መንገዶች ላይ ፀረ-ሰውና ፀረ-ተሽከርካሪ ፈንጂዎችን በመቅበር ጦርነቱ ያወደመውን የኢኮኖሚና የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን መልሰን ለመገንባት የምናደርገውን ጥረት ገቱት::

የክልሉን ማለትም የአንደኛውን አብዮታዊ ሠራዊታችንን ሰላማዊ ንቅናቄ ከመግታት ባሻገር በተለይ በ1972 እና በ19 73 ዓ.ም ከጅጅጋ እስከ ሙስታሂል አውራጃ ድረስ ያለውን የዕደላ መስመራችንን እየዘጉ በብርቱ አወኩን::

የደፈጣ ተዋጊዎቻቸው ሁለቱን አገሮች በሚያዋስኑ የጠረፍ አውራጃዎች ውስጥ ያለውን ህዝባችንን የማሸበር ተግባራቸውን ሲያካሂዱ መንግሥታቸው ዳግም ፀረ-ኢትዮጵያ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ በመጀመር አረቦች ህፃናት ልጆቻቸውን «እባቡን ትተህ ሐበሻን ግደል»

እያሉ እንደሚያስተምሩ ሁሉ አቅማቸውን ሳይመዝኑ በግብዝነት የሰነዘሩት ወረራ በሠራዊታቸው፣ በህዝቡና በጠቅላላ በአገራቸው ላይ ያስከተለውን ጥፋት ሕዝቡን ያስረሱ መስሏቸው የሱማሊኛ ቋንቋ ለሚናገረው የህብረተሰብ ክፍል በሙሉ «ከደጋው፣ ከለሙና ከለምለሙ መሬትህ ገፍትሮ እዚህ ደረቅ በረሃማ መሬት ላይ

በመጣል፣ ለውሃ ጥምና ለረሀብ እንዲሁም ለዘላለም ድህነት የዳረገህ የሐበሻ ኢምፔሪያሊዝም ነው።

ሐበሻ የተፈጥሮ ጠላትህ ስለሆነ ሳታመነታና ሳትሰንፍ ታገለው፣ ባገኝህበት ጊዜና ቦታም ግደለው» በማለት ከባህላዊ ሙዚቃና ቀረርቶ ጋር ቅስቀሳ ማድረግን የየዕለቱን ተግባራቸው አደረጉት።

የጀነራል ዚያድ ባሬ መንግሥት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያካሄደው ጀብደኛ ወረራና በውጤቱም የሱማሌ መከላከያ ሠራዊትና ሕዝቡ የከፈሉት መስዋዕትና ለሱማሌ ህዝብ ታላቅነት ሲባል የተከፈለ ህጋዊና የተቀደሰ መስዋዕትነት አድርጎ በማቅረብ የህዝቡን ብሶትና ቁጣ ለማቀዝቀዝና ብሎም ለማስረሳት ቢሞክርም የሕዝቡ ቁስል እንዲህ በቀላሉና በአጭር ጊዜ የሚሽርና ጉዳቱም የሚረሳ ሳይሆን እያመረቀዘ ለዘመናት የሚቆይና የአገሪቱን አመራር አካላት ከሚያራምዱት የፖለቲካ ሥርዓት ጋር ገዝግዞ በመቁረጥ የሚጥል ነው የሆነው።

የሱማሌ ሕዝብ መሪዎች ያልተገነዘቡት የሕዝቡን ሰቆቃና በመንግሥቱ ላይ ያደረበትን መሪር ጥላቻ ብቻ ሳይሆን የእኛንም ጥንካሬ ነው።

ጦርነቱ ከተጀመረበትና በእነሱ ሽንፈትና ውድቀት እስከ አከተመበት ጊዜ ድረስና ከዚያም በኋላ በመላው ሱማሌ የደረሰውን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማህበራዊ ቀውስ የሕዝቡን ሰቆቃና ጩኸት ጦርነቱ ባስከተለው ጉዳትና ውድመት ሞራላቸው የዳሸቀውና ሥርዓት አልባ የሆኑት የአገሪቱ የጦር ኃይሎች በመሪና በጭፍራ በመለዮና በጎሳ ተከፋፍለው በመንግሥቱ ላይ የሚያካሂዱትን አመፅ ከስትራቴጂካዊ የመረጃ ምንጫችን ብቻ ሳይሆን በየቀኑ መንግሥታቸውን እየከዱ ወደ እኛ ከሚመጡት አያሌ የጦር መኮንኖች አስተማማኝ መረጃ እናገኛለን።

በጦር ኃይሎች አባሎች ብቻ ሳይሆን በሕዝቡም ላይ እጅግ የከፋ የሞራል ውድቀትና በመንግሥቱ ላይ መሪር ጥላቻ እንዲያድርበት ካደረጉት ምክንያቶች በጣም ጥቂቱን ብቻ እገልፃለሁ።

ሠራዊቱን ብቻ ሳይሆን ሕዝቡን ያስገረመውና በእጅጉ ያሳዘነው «ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር ሲዋጉ የቆሰሉ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮች፣ የበታች ሹማምንትና መኮንኖች ሱማሌ ስፍራ ስለሌላት እዚያው በኢትዮጵያ ምድር ይረሸኑ» ብሎ ከጦር ኃይሎች ከፍተኛ የአመራር አካላት በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት መላው የጦር ሜዳ ቁስለኞች ጠረፍ ላይ መገደላቸው ነው።

ወራሪውን የሱማሌ መንግሥት ጦር አባሮ የጅጅጋን ከተማ የተቆጣጠረው የደርግ አባል በሻምበል ኃይሌ መለስ (በኋላ ብ/ጀነራል)ና የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የተመራው 69ኛው የሕዝባዊ ሠራዊት ብርጌድ ጠላት

ከኢትዮጵያ ምድር ጠቅልሎ መውጣቱን ለማረጋገጥ በጅጅጋ ግንባር ያለውን ድንበር በቃኘበት ጊዜ በራሳቸው ሠራዊት የተረሸኑት የሱማሌ የጦር ሜዳ ቁስለኞች አፈር ያልለበሰ የሬሳ ክምር ማገኘቱን አመልክቶናል።

ከተለያዩ የሱማሌ የጦር ክፍሎች በተለያዩ አቅጣጫና ጊዜ መንግሥታቸውን ከድተው የመጡት የጦር መኮንኖችም በጅጅጋ ግንባር ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ሥፍራዎች አያሌ የጦር ሜዳ ቁስለኞች በተመሳሳይ ሁኔታ መረሸናቸውን በምሬት ገልፀውልናል።

በኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት ድል ከተመታው የሱማሌ ሠራዊት መኮንኖች መካከል ከበላይ አካል የተሰጣቸውን የውጊያ ትዕዛዝ ተግባራዊ አላደረጉም፣ የሚያዙትን ሠራዊት በሚገባ አልመሩም፣ በታላቅ መስዋትነት ከኢትዮጵያ ሠራዊት በውጊያ የተወሰዱ ከተሞችን፣ በወታደራዊ ጠቀሜታቸው ወሳኝነት የነበራቸውን ወታደራዊ መሬቶች እስከ መጨረሻው ሰውና ጥይት ሳይከላከሉ በመሸሽ መልሰው ለጠላት አስረክበዋል ወዘተ በሚል ክስ የተወነጀሉ፣ ያለ ፍርድ የታሰሩ፣ ከማዕረግ ደረጃቸው ዝቅ ያሉና ከሠራዊቱ የተወገዱ ብዙ ናቸው።

በሰፊው የሱማሌ ሕዝብ ላይ ጦርነቱ ያደረሰበት ጉዳት በመለዮ ለባሹ ላይ ካደረሰው የከፋ እንጂ የተሻለ አልነበረም። ከኢትዮጵያ ጋር የሚዋሰኑ የደቡብ ሱማሌ ክልሎችና ሰሜኑ በሙሉ ማለት ይቻላል ለአንድ ዓመት ያህል የጦር አውድማ ወይንም የአየር ኃይላችን ዒላማ ነበሩ።

ተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት የአገራችንን ድንበር በመጣስ ሰባት መቶ ኪ/ሜትር ያህል ርቀት አስገብቶ መላውን ወራሪ ሠራዊት ከነትጥቁና መሳሪያው ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው ለውጊያው የሚያስፈልጉትን ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችና ስንቁን ወዘተ ለማጓጓዝ የሚበቃ ወታደራዊ የየብስ መጓጓዣ ወይንም ተሽከርካሪዎች አልነበሩትም።

ታላቋን ሱማሌ ለመፍጠር በምናካሂደው ታሪካዊ ትግል እያንዳንዱ ሱማሌ የበኩሉን አስተዋፅኦ የማድረግ ብሔራዊ ግዴታ አለበት በሚል አዋጅ የተለያዩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ንብረትና መተዳደሪያ የሆኑ ማናቸውንም ጠጣር ጭነት የሚጭኑ ተሽከርካሪዎችን ነዳጅና ቅባት የመሳሰሉ ፈሳሽ ነገሮችን የሚያጓጉዙ ቦቴዎችን የጫኑትን ኢትዮጵያ ምድር ካራገፉ በኋላ ይመለሱላችኋል የሚል ቃል በመግባት በንግድና በየብስ መጓጓዣ መስክ የተሰማሩትን የህብረተሰብ ክፍሎች መተዳደሪያ በመንጠቅ ለከፋ ድህነት ዳርጓቸዋል።

የጀነራል ዚያድ ባሬ መንግሥት ተሽከርካሪዎቻችሁ የጫኑትን ኢትዮጵያ ካደረሱ በኋላ ይመለሱላችኋል ብሎ ለሕዝቡ ቃል ቢገባም በውጊያው ሂደት አብዛኛው ተሽከርካሪዎች ሲጋዩና ሲወድሙ የተረፉትም ጥቂቶቹ በመለዋወጫ ዕቃ እጥረትና

በጥገና እጦት በየመንገዱ ቆመው ስለቀሩ ለባለንብረቶች እንዳችም ተሽከርካሪ አልተመለሰም፡፡

ሰላማዊው የሱማሌ ሕዝብ ሞትን መድማትንና መቁሰልን ከመለዩ ለባሹ ጋር ከመካፈል ባሻገር በታላቋ ሱማሌ ግንባታ አስተዋፅኦ ማድረግ ብሄራዊ ግዴታህ ነው እየተባለ ለከፋ ድህነት ተዳርጎ የጀነራል ዚያድ ባሬ መንግሥት አመራር አካላት ራሳቸው በቁምና በቀን እየቃዡ ሕዝቡን የሕልም ዳቦ ሲመግቡት የኖሩ የጥፋት መልዕክተኞች መሆናቸውን ከጦርነቱ ውጤት በመረዳቱ በመሪዎቹ ላይ የመረረ ጥላቻ አድሮበታል፡፡

ምዕራፍ ሦስት

ከጦርነቱ በኋላ ሌላ ጥፋት እንዳይደገም በኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት በኩል የተደረገ የሰላም ጥረት

በምዕራፍ ሁለት እንደተገለፀው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሠላም አንድነትና አብዮት ፀር የሆኑት የውስጥ ጠላቶቻችን «የጠላቴ ጠላት» በማለት የሌለውን ነገር እየፈጠሩና ያለውን እያጋነኑ የሚያቀርቡለትን መረጃ ሁሉ እውነት ነው ብሎ በመቀበል የሱማሌ መንግሥት በኛ ችግሮችና ጊዜያዊ ድክመቶች ለመጠቀም ያላደረገው ጥረት የለም።

አለኝታዬ ነው የሚለውን አንድ አምስተኛ የኢትዮጵያ መሬት በጦር ኃይል ወሮ ጥፋት ከማድረሱ በፊት ቀደም ብሎና ከሱዳን መንግሥት ቀጥሎ ራሳቸውን «የኤርትራ ነፃ አውጭ» ብለው የሚጠሩትንና «ጀብሐና ሻዕቢያ» በመባል የሚታወቁትን አገር ገንጣዮች ከአረቡ ዓለምና ከምስራቁ ዓለም ጋር በፀረ ኢትዮጵያ ግንባር አስተባባሪና አገናኝ በመሆን የትጥቅ፣ የገንዘብ፣ የአልባሳት የስንቅና የመድሃኒት ወዘተ እርዳታ አሰባሳቢ ሆኖ ኢትዮጵያን በማድማትና በማዳከም የፈፀመው ደባ ያነሰ ይምስል ከጦርነቱ ፍፃሜም በኋላ ከሰሜኑ፣ ከሰሜን ምዕራቡ፣ ከሰሜን ምስራቁ፣ ከምስራቁና ከደቡቡ ሌላ በተጨማሪ በትግራይ ስድስተኛ የውጊያ ግንባር በመክፈት የወያኔ ዋና አደራጅና መሣሪያ አቀራቢ ሆነ።

የሠላም ድርድር ጀምረን በሱማሌ ውስጥ በባርነት የሚሰቃዩትን ወገኖቻችንን ነፃ የማውጣት ዕቅዳችንንና በአፍሪካ ቀንድ ሰላም መልሶ እንዲያንሰራራ የማድረግ ፍላጎታችንንም ፍፁም እንደማይጋራ በጣም ግልፅ ሆነ።

በእብሪትና በህገ ወጥነት በኢትዮጵያ ላይ ጠቅላላ ወታደራዊ ወረራ በመሰንዘር እጅግ ከፍ ያለ አውዳሚ ጉዳት በሁለቱም ሕዝቦች ላይ ካደረሰ በኋላ በአገራችን የውስጥ ጉዳይ ገብቶ ወያኔን እስታጣቂ መሆኑን በትዕግስት ለመመልከት ፍፁም የማይቻል በመሆኑ የሱማሌ መንግሥት በሚገባው ቋንቋ ዳግም ወታደራዊ እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት ዳግም ውጊያ ቢጀመር የውጊያው ሰለባ ለሚሆነው የሱማሌ ሕዝብ በማሳወቅ የመንግሥቱን ፀብ አጫሪነትና የጥፋት መልክተኛነት በመልሶ ማጥቃት ፕሮፖጋንዳ ማጋለጥ ይገባል ብለን ወሰንን።

ከጦርነቱ በኋላ የሱማሌ መንግሥት ብዙሃን ማሰራጫዎች በአዲስ መልክ የጀመሩትን በሐሰት የፈጠራ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ሠላም ፕሮፖጋንዳ በመልሶ ማጥቃት ፕሮፖጋንዳ በመምታትና በማጋለጥ ለሱማሌ ሕዝብ የመሪዎቹን አጭበርባሪነት፣ ጀብደኘነት፣ የጦር ወንጀለኛነትንና የጥፋት መልዕክተኘነት ለማሳወቅ ያቀድነው የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ከአቀፋቸው ዝርዝሮች ጥቂቶቹና ዋና ዋናዎቹ ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ-

የኢትዮጵያና የሱማሌ ህዝቦች በባህል በመልክአ ምድር፣ በኢኮኖሚና በአጠቃላይ በተፈጥሮ ካላቸው ትስስር ሌላ የስዊዝ ቦይ ከመከፈቱና የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች የአፍሪካን ቀንድ ከመውረራቸው በፊት ሁለቱ ሕዝቦች በአንድ ሰንደቅ ዓላማ ጥላ ስርና በአንድ ሉአላዊ መንግሥት አመራር ስር የኖሩ የአንድ ሕዝብነት ህልውናና አንድ የጋራ ታሪክ የነበራቸው ስለመሆናቸው ከሱማሌ ሕዝብ ነፃነት በኋላ በፖለቲካ ሥልጣን ማማ ላይ የተፈራረቁት የዶክተር አብዱል ረሺድ አሊ ሼርማርኬና የጀነራል ዚያድ ባሬ መንግሥታት እውነቱንና የጥንቱን የአፍሪካ ቀንድ ታሪክ ለህዝቡ ከማስረዳትና አዲሱንም ትውልድ ከማስተማር ፋንታ «ሐበሻ የተፈጥሮ ጠላትህ ነው» በሚል ጥላቻ ከመመረዝ በላይ በኢትዮጵያ፣ በኬንያና በጅቡቲ ህዝቦች ኪሳራ ታላቋን ሱማሌ እንፈጥርልሀለን በማለት ሲያታልሉትና የሕልም ዳቦ ሲመግቡት ስለመኖራ ቸው፣

በሐሰት የፈጠራ ታሪክ በጀብደኝነትና በመስፋፋት ምኞት ራሳቸውን ያስከሩ መሪዎቹ እሱ ባልጠየቀውና ባልደገፈው ጦርነት ውስጥ ስለመማገዳቸው፣

በከንቱ የጦርነቱ ጭዳ የሆኑትን የኢትዮጵያና የሱማሌ ሕዝብ ልጆች ብዛትና ጦርነቱ በሁለቱም አገሮች ላይ ያስከተለውን ውድመት፣

በግፍና ወደር በሌለው ጭካኔ «ሱማሌ ለእናንተ ሥፍራ የላትም» ተብለው በኢትዮጵያ ምድር በጀነራል ዚያድ ባሬ ታማኝ የክብር ዘቦች ስለተረሸኑት የጦር ሜዳ ቁስለኞች፣

የተስፋፊው መንግሥት የጦር ኃይል አባላት ኢትዮጵያን የወረርነው አንተን ከሐበሻ ቅኝነት ነፃ ለማውጣት ነው ያሉትን በኦጋዴን ክልል በከብት እርባታ የሚኖር ሱማሊኛ ተናጋሪ የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረት የሆኑትን አብዛኛውን ግመሎች የዳልጋና የቀንድ ከብቶች አርደው ስለመብላታቸውና የተረፋቸውንም በጦር ሜዳ በውጊያ ተረተው ሲሸሹ ጠራርገው ወደ ሱማሌ መንዳታቸውን፣ «ከብቶቻችንን አርዳችሁ መብላታችሁ ያነሰ ይመስል የቀሩትን እንዴት ነድታችሁ ትወስዳላችሁ» ብሎ በመጠየቅ የተቃወማቸውን ሕዝብ በግፍና በገፍ ስለመፍጀታቸው፣

በመጨረሻም የመንግሥት መገልገያ የነበሩትን ጠቅላላውን በኦጋዴን የነበሩ ሕንፃዎችና የጦር ሰፈሮችን ወዘተ ብቻ ሳይሆን ሆስፒታሎችን፣ ትምህርት ቤቶችን፣ የግለሰቦችንና የድርጅቶች መገልገያ የነበሩ ማናቸውንም ተቋማትና የሕዝቡን መኖሪያ ጎጆዎች ጭምር በማፈራረስ የቆርቆሮ ክዳን ሳይቀር ነቃቅለው ወደ ሱማሌ መውሰዳቸውን፣

አንዱ በሙስታሂል ከተማ የፋሽስት ኢጣሊያ ስሪት የነበረ ሌላው በጎዴ ከተማ በፈረንሳይ መሐንዲሶች የኢትዮጵያ መንግሥት ያሰራውን ሁለት የዋቢ ሸበሌን ወንዝ

ታላላቅ የብረት ድልድዮች ከማፈራረስ ሌላ የጎዴን ዘመናዊ የአውሮፕላን ሜዳ በትራክተር ማረስን ወዘተ ስለመሳሰሉት የዚያድ ባሬ መንግሥት የጥፋት ተልዕኮ፣

የጥፋት መልዕክተኛው ወራሪ የሱማሌ መንግሥት ሠራዊት በኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት ድባቅ ተመትቶ ሲፈረጥጥ እያሳደድን እስከ ሞቃዲሾ ድረስ በመግባት ለመበቀል ብንፈልግ መክቶ ሊያቆመን የሚችል ምንም ዓይነት ኃይል እንዳልነበረ እያወቅን ለመበቀል ያልፈለግነው ጀብደኛ፣ የጦር ወንጀለኛና የጥፋት መልዕክተኛ ብለን የምናወግዘውን የጀኔራል ዚያድ ባሬን መንግሥት ተግባር እኛም በመድገም የሱማሌን ሕዝብ ዳግም ለመጉዳትና ስቃዩን ለማብዛት ባለመፈለጋችን ብቻ መሆኑን የሚገልፁ ማስገንዘቢያዎች ነበሩ።

እነዚህ ከዚህ በላይ የገለፅኳቸውን ለሱማሌ ሕዝብ ንቃትና ግንዛቤ የሚበጁ የፕሮፖጋንዳ ፋይዳዎችን በራዲዮ ፕሮግራም ከማሰራጨት በተጨማሪ በራሪ ጽሑፎች በብዛት እየተዘጋጁ ለሳምንታት ያህል በሁለቱ አገሮች የጋራ ድንበሮች አቅራቢያና እንዲሁም ወደ መሀል ሱማሌ ጠልቀን በመግባት በገጠርና በከተሞች እንዲሁም በየጦር ሰፈሮች ላይ በአውሮፕላን እንዲበተኑ በማድረጋችን የዚያድ ባሬን መንግሥት እየከዱ ወደኛ የመጡት የዚያድ ባሬ ተቃዋሚ የሲቪል ፖለቲከኞችና የጦር መኮንኖች በሙሉ በዚህ ጥሪ መሰረት ነው የመጣነው በማለት በራሪ ጽሑ ፎችን እንደ ማለፊያ ሰነድ በመጠቀም እያንዳንዳቸው ከአንድ በላይ ሁለትና ሦስት በራሪ ጽሁፎችን እየያዙ ነው የመጡት።

ክፍል አስራ ሁለት

ምዕራፍ አራት

ዘመቻ ላሽ

ከጦርነቱ በኋላ በእኛ በኩል የበቀል ወረራ ሳያምረን በድንበራችን ላይ ቆመን በአፍሪካ ቀንድ ሠላም ለመፍጠር ሁለቱ እህትማማች አገሮች ከመዋጋት ፈንታ በሠላም፣ በመተሳሰብና በመረዳዳት በመልካም ጉርብትና በጋራ የሚጥሩበትን መንገድ በመፈለግ ለዘላቂ እርቅ ብለን የምናቀርባቸውን የሠላም ሀሳቦች ተስፋፊው የሱማሌ መንግ ሥት በድክመት በመገመት ከፀረ ኢትዮጵያና ከፀረ ሠላም የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ባሻገር ወደ ዳግም ጦርነት የሚወስደንን ፀብ አጫሪነትና የሽብር ተግባሩን ማስፋፋት ስለቀጠለ ከጀመርነው የመልሶ ማጥቃት የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ጋር በተቀናጀ ሁኔታ ዳግም አቅሙን እንዲያውቅ የሚያደርገውና ከጭፍን ጀብደኝነት የሚገታው «ዘመቻ ላሽ» በተሰኘ መጠሪያ ጠጠር ያለ የመሣሪያ ፕሮፖጋንዳ ማለትም ኃይልን የማሳየት እርምጃ ወደመውሰዱ አመራን።

በሱማሌ ወራሪ ሠራዊት ላይ ካገኘነው ወታደራዊ ድል በኋላ በእረፍትና በመዘናናት ላይ የነበሩትን የምሥራቁን አንደኛ አብዮታዊ ሠራዊትና የደቡቡን ኮር ተዋጊ ክፍሎች በሙሉ አንቀሳቀስን።

ከአንቀሳቀስነው ሰፊ ሠራዊት ከፊሉ የጠላት አድፋጭ ተዋጊዎች የሚገቡባቸውንና የሚወጡባቸውን መተላለፊያ በሮች እንዲዘጋ በማድረግ የሽብር ተግባራቸውን አዘወትረው የሚያካሂዱባቸውን የጠረፍ ወረዳዎችና አወራጃዎች በተቀረው መጠነ ሰፊ እግረኛና ብረት ለበስ ጦር አስከብበን በተዋጊ ሄሊኮፕተሮች በተረዳ አሰሳና ሃያ ቀናት ያህል በወሰደ የአፈና ውጊያ አብዛኛውን የጠላት አድፋጮች ለመደምሰስ ተችሎ በጣም ጥቂቶች ነበሩ ለማምለጥ የቻሉት።

ሁለቱም ጦሮቻችን ያመለጡትን የጠላት አድፋጭ ሰርጎ ገቦች የሽሽት ዱካ እየተከተሉ ተጠግተው በሱማሌ መንግሥት የአስተዳደር ክልል ውስጥ በጠረፉ ዳርቻ ለጠረፍ ጥበቃ በቋሚነት የሰፈሩትን የሱማሌ መደበኛ የጦር ክፍሎችና የፖሊስ ሠራዊት አካላትን ከነሰፈራቸው በመደምሰስ አልፈው በሦስት ቀጠናና አቅጣጫ ማለትም በሰሜን፣ በመሀከላዊና ደቡብ ሱማሌ ክልል ውስጥ በመጥለቅ ከ30 እስከ 40 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኙ ጠቃሚ ስፍራዎችንና ለመከላከል የሚያመቹ ወታደራዊ መሬቶችን ይዘው እንዲቀመጡ አደረግን።

በመሀከላዊው የሱማሌ ግዛት ውስጥ «የኢትዮጵያ ጩቤ» በማለት የሱማሌ መንግሥት በሚጠራው የአፍሪካ ቀንድ ጫፍ ባለበት ክልል የገባው ጦራችን የደቡብንና የሰሜኑን ሱማሌ ወይም የሞቃዲሾንና የሐርጌሳን ከተማ የሚያገናኘውን

ብቸኛ አውራ የአስፋልት መንገድ በቁጥጥሩ ስር አድርጎ በመንገዱ ተገልጋይ የሆኑ ማናቸውንም ተሽከርካሪዎች እንዳይንቀሳቀሱ በማገዱ በሞቃዲሾና በሐርጌሳ ከተሞች ሽብር ተፈጠረ።

የጀነራል ዚያድ ባሬን አመራር የሚቃወሙ የተለያዩ የማዕረግ ደረጃ ያላቸውና ከተለያዩ የጦር ክፍሎች የተወጣጡ የጦር መኮንኖችና እንዲሁ ከተለያዩ ክልሎችና የጎሳ ማህበራት የተወጣጡ ሲቪል ፖለቲከኞች የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት የፈጠረላቸውን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም በሱማሌ ግዛት ውስጥ በአውሮፕላን የበተነውን በራሪ ጽሁፍና የሠላም ምልክት የሆነ ነጭ ጨርቅ በዘንግ ብጤ እንጨት እያንጠለጠሉ በመምጣት ለጦራችን በብዛት እጃቸውን በመስጠት ተደራጅተው የዚያድ ባሬን መንግሥት ለመጣል የሚያስችላቸውን ድጋፍ የጠየቁን በዚህ ጊዜ ነበር።

የሞቃዲሾ መንግሥት የኢትዮጵያ የጦር ኃይል አገሬን ወሯል በማለት ከተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ጀምሮ ለተለያዩ አህጉራዊ ድርጅቶችና እንዲሁም መንግሥታት ቢያመለክትም በወረራ መልክ የኢትዮጵያ የጦር ኃይል በሱማሌ ግዛት ውስጥ መግባቱን የሚያመለክት ነገር ባለመታየቱና ከሌላ ምንጭ አንድም ፍንጭ ባለመሰማቱ ክሱን ያስተጋባ አንድም አገርና ድርጅት አልነበረም።

በጦርነቱ ጊዜ የሱማሌ መንግሥት በየዕለቱ ጣልኳቸው ያላቸው የኢትዮጵያ ተዋጊ አይሮፕላኖችና ገደልኳቸው ያላቸው ወታደሮች ቁጥር በጦርነቱ መገባደጃ ጊዜ ጠቅላላ ድምራቸው ሲሰላ የአውሮፕላኖቹ ቁጥር ከሁለት መቶ በላይ የታንኮቹ ቁጥር በሺህና ገደልኩ ያለው የኢትዮጵያ ወታደሮች ቁጥር ወደ ሃምሳ ሺህ መድረሳቸውን ዴይሊ ኔሽንና ዘጋርዲያን የተባሉ ሁለት የእንግሊዝ ጋዜጦችና እንዲሁም ለሞንድ የተባለው የፈረንሳይ ጋዜጣ በማጋለጥ ለዓለም ሕዝብ ትዝብት ስለዳረጉት ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የሱማሌ መንግሥት የሚያቀርባቸውን ክሶችና ዜናዎች እውነት ነው ብለው የሚቀበሉ መንግሥታትና ድርጅቶች ብዙ አልነበሩም።

የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊና የፀጥታው ምክር ቤት አንድ የመንግሥታቱ ማህበር አባል አገር መንግሥት አገሬ ተወረረ ብሎ ክስ ሲያቀርብ ዝም ሊሉ ስለማይችሉ እንዲሁም የኢትዮጵያ ጦር በሱማሌ መንግሥት ግዛት ውስጥ አለመግባቱን በሳተላይት ካሜራ አማካኝነት ስለተገነዘቡ ይመስላል የሱማሌ መንግሥት ላቀረበው ክስ የኢትዮጵያ መንግሥት መልስ ወይም ማብራሪያ እንዲሰጥ በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ተጠየቅን። ለቀረበልን ጥያቄ የሰጠነው መልስ ባጭሩ ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

"የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ብቻ ሳይሆን የመንግሥታቱ ሸንጎና መላው አባላት እንደሚያውቁት ተስፋፊውና ጦረኛው የጀነራል ዚያድ ባሬ መንግሥት አለኝታዬ ነው የሚለው የኢትዮጵያን አንድ አምስተኛውን መሬት

ከመሆኑ ባሻገር ይህንንም ፍላጎቱን በኃይል ተግባራዊ ለማድረግ እንደወረረን ዓለም የሚያውቀው ነው ።

ተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት የሁለቱ አገሮቻችን ድንበር ነው ብሎ የሚያውቀው አዋሽ በመባል የሚጠራው የአገራችን ታላቅ ወንዝ የሚያቋርጠውን መስመር ነው።

የተከበረው የፀጥታው ምክር ቤት በካርታ ላይ ተመልክቶ ለመረዳት እንደሚችለው የአዋሽ ወንዝ በኢትዮጵያና በሱማሌ ግዛት ክልል መሀል ያለ ወንዝ ሳይሆን ሁለቱን አገሮች ከሚያዋስነውና ዓለም አቀፍ እውቅና ካለው ድንበር ሰባት መቶ ኪ/ሜትር ርቀት ላይና የኢትዮጵያ ርዕሰ ከተማ ከሆነው ከአዲስ አበባ አንድ መቶ ሃምሳ ኪ/ሜትር ብቻ ርቆ የሚገኝ ነው።

የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት የተለመደ የሱማሌን መንግሥት ክስ በማዳመጥ ብቻ ለኛ ጥያቄ ከማቅረቡ በፊት በኢትዮጵያ የጦር ኃይል ተጣሰ የተባለው ድንበር የቱ እንደሆነ የተጣሰው መቼና እንዴት እንደ ሆነና የሱማሌ መንግሥት ተይዞብኛል የሚለውን ስፍራ ስምና ካርታ ጥቅስ እንዲያቀርብ ተጠይቆ ለኛም ለፀጥታው ምክር ቤትም ሊያብራራ የሚገባ መሆኑን እያሳሰብን የኢትዮጵያ አብዮታዊ የጦር ኃይል ወራሪውን የሱማሌ መንግሥት ሠራዊት ረግጦ ካስወጣ በኋላ ሰፍሮ የሚገኘው በአገሩ ምድር ላይ እንጂ በሱማሌ ምድር ያለመሆኑን በትህትና እንገልፃለን "የሚል ነበር።

የኢትዮጵያ መንግሥት የሰጠውን የፅሁፍ መልስ ቅጂ አባሪ በማድረግ በተጠየቀው መሰረት ያብራሩ ዘንድ የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ለሱማሌ መንግሥት ጻፈለት።

የሱማሌ መንግሥት የኢትዮጵያ መንግሥት ለፀጥታው ምክር ቤት የጻፈውን ቅጂ ሲመለከት የሱማሌ መንግሥት ያብራራ ተብሎ የተጠየቀው ጥያቄ ዓላማ ስለገባውና ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ደብዳቤ መልስ መስጠቱ አስቸጋሪ ይዘት ስለነበረው በበኩሉ መፍትሄ ይሆናል ብሎ የገመተውን ሌላ አማራጭ እርምጃ ለመውሰድ ወሰነ።

ታላቋን ሱማሌ የመፍጠር ምኞቱ ህልም እንደሆነ የተረዳ ቢሆንም በሰረፀበት ፊውዳላዊ ግብዝነት ምክንያት ዓለም የተቀበለውንና አማራጭ የሌለውን የሁለቱን አገሮች ህጋዊ ድንበር አምኖ መቀበሉ የማይዋጥ መራራ ኪኒን ሆኖበታል።

ኩራቱን ለማሳየት ሲል ብቻ ለአንዴና ለመጨረሻ ከጦርነቱ የተረፈ ሠራዊቱን በማሰባሰብ ደቡብን ሱማሌ ከሰሜኑ የሚያገናኘውን አውራ ጎዳና ይዞ ቀንዱ ላይ የተቀመጠውን የኢትዮጵያ ጦር ወግቶ ለማስወጣት አቀደ።

በአብዮታዊ ሠራዊታችን ተቀጥቅጦ ከኢትዮጵያ የተባረረው ሠራዊት የውጊያ ፍላጎቱና ወታደራዊ ሞራሉ የወደቀ፣ የኢትዮጵያን ሠራዊት አሸንፋለሁ ብሎ የማያምን አልፎም ጀነራል ዚያድ ባሬን ከሥልጣን ለማውረድ የሚያደባ ፀረ-መንግሥት ስለነበረ የሱማሌ መንግሥት በዚህ ዓይነቱ ሠራዊት ሊያስፈፅም ያቀደው ውጊያ ፍፁም ስሕተት ነበር።

በዚህ ወቅት አብዛኛዎቹ የሱማሌ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች የተከፉና እምነት የሚጣልባቸው ስለአልነበሩ ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ አማቹና የሪፐብሊኩ ጋርድ አዛዥ የነበረውን ሜ/ጀነራል ሞርጋንን ሌ/ጀነራልና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማጆር ሹም በማድረግና እሱ ይታመናሉ ያላቸውን መኮንኖች በዕዙ ስር ያሰባሰበ አንድ ግብረ ኃይል (Task Force) አዘጋጅቶ ቀንዱን የያዘውን የኢትዮጵያን አብዮታዊ ጦር ወግቶ ለማስለቀቅ የሰነዘረው ጥቃት ውጤት ሽንፈት ነበር ከማለት አሳዛኝ እልቂት ነበር ማለት ነው የሚሻለው።

እንደሚታወቀው የሱማሌ ተዋጊ አውሮፕላኖች በጦርነቱ አልቀው ስለነበር አየር ኃይሉ ከውጊያ አገልግሎት ውጭ ነበር ማለት ይቻላል።

ወራሪው ሠራዊት ወደ ኢትዮጵያ ክልል ሲገባ ይዟቸው የመጣው የተለያዩ ከባድ መሣሪያዎች አብዛኛዎቹ በጦ ርነቱ ሂደት የወደሙ ከመሆናቸው በላይ ከተረፉትም አብዛኛዎቹን ጦሩ በሚሸሽበት ጊዜ በኢትዮጵያ ምድር ጥሏቸው ነው የሄደው።

ጀነራል ሞርጋን የመራውን አጥቂ ግብረኃይል የውጊያ እቅድ፣ የሠራዊቱን መጠንና ዓይነት፣ የሚያጠቃበትን አቅጣጫና ጊዜ በሚገባ እናውቅ ነበር።

አጥቂው የጠላት ጦር ጥቃት ለመሰንዘር በተካበተበት የመሰብሰቢያ ወረዳ ላይ እንዳለ ነው አየር ኃይላችን ጦሩን ብቻ ሳይሆን አብዛኛውን ከጦሩ ኋላ የነበሩትን አጋዥ መሣሪያዎች ከውጊያው በፊት ያወደማቸው።

ይህም ሆኖ ጠላት ከአየር በቦምብና በሮኬት ከምድር በወገን የተለያዩ ከባድ መሣሪያዎች ስብስብ ተኩስ እየተደበደበ ወደፊት በመንቀሳቀስ ወደ ጨበጣ መስመሩ በተቃረበበት ጊዜ ለመከላከል ባመቸ ወታደራዊ መሬት ላይ ጥሩ መከታና ከለላ ባለው ምሽግ ውስጥ ምላጩን ጨብጦ ይጠባበቅ የነበረው የወገን ጦር በራሱ ላይ አንዳችም ጉዳት ሳይደርስበት የጠላትን እግረኛ ጦር ፈጀው።

የሱማሌ ግብረ ኃይል የሰነዘረው ማጥቃት ውጤት ሽንፈት ነበር ከማለት ይልቅ አሳዛኝ እልቂት ነበር ለማለት የተገደድኩበት ምክንያት ኤታማዦሩ ጀነራል ሞርጋን ለጀነራል ዚያድ ባሬ ታማኝነቱን ለመግለፅና ቢቻለውም ለማስደሰት ብሎ የመዋጋት ፍላጎት የሌለውን ጦር አስገድዶ ወደ ቄራ እንደሚነዳ ከብት በመንዳት ስለአስፈጀው ነው።

ጀነራል ሞርጋን ጦሩን ያለአግባብ በከንቱ በማስፈጀቱ ሳይቀጣ ወይንም ሳይወቀስ እንዳውም መልካም ስራ እንደሰራ የተቆጠረለት ይመስላል ከውጊያው በኂላ የአገር መከላከያ ሚኒስትር ሆኖ ተሾመ።

የጀነራል ዚያድ ባሬ መንግሥት በድጋሚ የደረሰበትን ወታደራዊ ውድቀት ከሱማሌ ሕዝብና ከዓለም ለመሰወር ቢሞክርም በአገር ውስጥ ተቃዋሚዎችና ሞቃዲሾ በሚኖሩ ባዕዳን ዲፕሎማቶች አማካኝነት የውጊያው ይዘትና የሠራዊቱ እልቂት ተጋኖ ተወራ።

ወሬው ከአፍሪካና ከመካከላዊው ምሥራቅ አልፎ እስከ ኒው ዮርክ ተዛምቶ የተባበሩት መንግሥታት ጽህፈት ቤት ደረሰ።

ምዕራፍ አምስት

የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ኩርት ቫልደሃይም ኢትዮጵያንና ሱማሌን ለማስታረቅ ያደረጉት ጥረት

የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ የነበሩት የኦስትሪያው ተወላጅ ኩርት ቫልደሃይም በተባበሩት መንግሥታት የሱማሌ መንግሥት አምባሳደርን ተገናኝተው ለሱማሌው መሪ ለፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ከዚህ የሚከተለውን የቃል መልእክት በወዳጃዊ ምክር መልክ እንዲያቀርብላቸው ይጠይቁታል።

«ከጥቂት ዓመታትበፊት አገርዎና ኢትዮጵያ ወደለየለት ጦርነት ውስጥ ለመግባት ከመዛዛት አልፋችሁ ጦርነቱን ለመጀመር በምትዘጋጁበት ጊዜ ሊቀመንበር መንግሥቱን በአፍሪካ መሪዎች ስብሰባላይ ጋቦን ተገናኝቻቸው ጦርነት የሰውን ሕይወት ያለ ጊዜው ቀሳፊና አገር አውዳሚ ነው ሁለቱ ታዳጊ አገሮቻችሁ ከጦርነት ይልቅ ልታተኩሪባቸውና አስቸኳይ መፍትሄ ልትፈልጉላቸው የሚገቡ አያሌ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ችግሮች አሉባችሁ ብዬ አስባለሁ።

በአገሮቻችሁ መካከል ያሉትን ቅራኔዎች በመፍታት ከጦርነት የተሻለ ሰላማዊ አማራጭ ልትፈልጉ አትችሉም ወይ?» ብዬ በጠየቅኳቸው ጊዜ የሰጡኝ መልስ ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

«ያቀረቡልኝ ጥያቄ ትክክልና የሰጡትም አስተያየት እውነት ነው። አገሬ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተመሰረተበትን አጠቃላይ መንፈስና ቻርተሩ ከአቀፋቸው አያሌ ቁምነገሮች አንዱና ዋናም ብዬ የማስበው የድርጅቱ አባል አገሮች ሁሉ ማለትም ከቅኝግዛት ኃይሎች መዳፍ ተላቀው ነፃ የሆኑትና ወደፊትም የሚሆኑት ቅኝ ገዥዎቻቸው ያስረከቧቸውን የአገር ድንበር ተቀብለውና አክብረው መኖር አለባቸው የሚለውን ሕግ ወይንም ውሳኔ ታከብራለች።

ይህንን ውሳኔ የምታከብረው ከራሷ ጥቅምና ሰላምን ከመፈለግ አኳያ ብቻ ሳይሆን አፍሪካዊያን ይህንን ባለመቀበል ከቅኝ ግዛት በፊት የነበረውን ታሪካቸውንና ድንበራቸውን በማደስ እያንዳንዱ አገር የየራሱን የፖለቲካ ካርታ ለመሳል ከተነሳ አፍሪካን የሚያጠፋ መሆኑን በማመን ነው።

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተቋቋመውና የድርጅቱ አባል አገር መሪዎች ቻርተሩን በፊርማቸው ያፀደቁት አዲስ አበባ ስለሆነ ኢትዮጵያ ቻርተሩን ማክበር ብቻ ሳይሆን የማስከበርና የመጠበቅ ኃላፊነትም አለብኝ ብላ የምታምን አገር ነች።

ኢትዮጵያ ከጎረቤቶቿ በአጠቃላይ ከሱማሌ በተለይ አንዲት አጥቅ መሬት አትሻም፣ የመስፋፋት ዓላማም የላትም። እዚህ ጦርነት ውስጥ የምንገባው በሱማሌ መንግሥት አስገዳጅነት አገራችንንና አብዮታችንን ለመከላከል ብለን ነው» ነው ያሉኝ።

ከዚህ በኋላ በሁለቱ አገሮች መካከል ስለሆነው አሳዛኝ ነገር መልሼ ለማውሳት አልፈልግም። በሁለቱ አገሮቻችሁ መካከል ያለው መሠረታዊ ችግር ምክንያት የወሰን ጉዳይ ነው ብዬ አስባለሁ።

እንደ ሊቀመንበር መንግሥቱ አነጋገር ሁላችንም ከምናውቀው የኢትዮጵያ አቋም አንፃርና በተለይም በቅርቡ የክቡርነትዎ መንግሥት «አገሬ በኢትዮጵያ የጦር ኃይል ተወሯል» ብሎ ባቀረበው ክስ ከኢትዮጵያ መንግሥት የተሰጠው አስተያየት የሚጠቁመን «የክብርነትዎ መንግሥት የአፍሪካና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅቶች የተቀበሉትን ድንበር ይቀበል የሚል ስለሆነና ይህንን መቀበል አሁን ጊዜው ከመሆኑ ሌላ ለተፈጠረውም ችግር አማራጭ የሌለው መፍትሄ ይመስለኛል የምለው በወንድማዊ ስሜት ነው።

ይህ መልዕክት የተባበሩት መንግሥታት ጽሕፈት ቤት መልዕክት ሳይሆን የኔ የግል ወንድማዊ ሃሳብ ነው» የሚል ነው።

በማዕከላዊው የሱማሌ መንግሥት የአስተዳደር ክልል ቀንዱን የተቆጣጠረውን ጦራችንን አጥቅቶ ለማስለቀቅ የሞከረው የጠላት ጦር በደረሰበት ውድቀት ከተበታተኑት አባላት መካከል ጥቂቱ የሰላም ምልክት የሆነ ነጭ ጨርቅ እያሳዩ በመምጣት ለኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት እጃቸውን መስጠትን እንደቀጠሉ ነበር።

የአፍሪካ ቀንድ ሁኔታ ይህንን በመሰለበት በ1974 ዓ.ም ሐምሌ ወር ከሰሜን ሱማሌ የመጡ የጀነራል ዚያድ ባሬ መንግሥት ተቃዋሚ የጦር መኮንኖችና የሲቪል ፖለቲከኞችን ያካተተና በኮሎኔል ጃማ አብዲ የሚመራ ቡድን አዲስ አበባ መጥቶ የሰሜን ሱማሌ ክልል ህዝብ ከጎሰኛውና ከጥፋት መልዕክተኛው የዚያድ ባሬ የጭቆና አገዛዝ ነፃ የሚያወጣ መሪ የፖለቲካ ድርጅትና በእሱም የሚመራ ነፃ አውጭ ተዋጊ ኃይል አቋቁመን እንድንታገል አብዮታዊው የኢትዮጵያ መንግሥት ይረዳን ዘንድ እንለምናለን የሚል ጥያቄ አቀረበ።

ቡድኑን ተቀብለን ወንድማዊ መስተንግዶ በማድረግ ላቀረበው ጥያቄ የይሁንታ መልስ ስለሰጠነው በሚያስገርም ፍጥነት «የሱማሌ ብሄራዊ ንቅናቄ» (Somali National Movement) የተሰኘውን ድርጅት አስኪል አቋቁመው ከሰሜኑ ሕዝብ ተዋጊ የሰው ኃይል መመልመል ጀመሩ።

የሰሜን ሱማሌ ሕዝብ ተወካይ ነን የሚሉት ተቃዋሚዎች ለትግል መደራጀታቸውን የተመለከቱና የሱማሌን መሀከላዊ ክልል ህዝብ እንወክላለን የሚሉ

ሲቪልና የጦር መኮንኖች ቅምር ቡድን በኮሎኔል አብዱላሂ ዩሱፍ እየተመራ ሰሜኖች በተቋቋሙ ሦስተኛው ወር ላይ በመስከረም ወር 1975 ዓ.ም መጥቶ የሰሜኑ ቡድን ካቀረበው የድጋፍ ጥያቄ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ጥያቄ ስለአቀረበና በእኛም በኩል የጠየቀው ስለተፈቀደለት እንደ ሰሜኖቹ በተፋጠነ ሁኔታ «የሱማሌ መድህን ዲሞክራሲያዊ ግንባር» (Somali Salvation Democratic Front) የተሰኘ የፖለቲካ ድርጅት አስኳል አዋቅሮ ከመሀከላዊው የሱማሌ ክልል ነዋሪ ህዝብ መካከል ተዋጊ ኃይል መመልመል ጀመረ።

እነዚህ ሁለት ድርጅቶች ያለብዙ ችግር ከዚያድ ባሬ መንግሥት የመከላከያ ሠራዊት ወታደር የማሰልጠንና የውጊያ ልምድ ያላቸውን የጦር መኮንኖች ከነጭፍሮቻቸውና ከሰላማዊው ህዝብም መካከል በቂ የሰው ኃይል በአመዛኙ ከመንግሥት መደበኛ ሠራዊት ከመሆኑ ባሻገር ከሰላማዊው ሕዝብም መካከል የተመለመሉ ወጣቶች የተዋጊነት ባህል ያላቸው ነበሩ።

የሁለቱ ድርጅቶች አመራር በውትድርና የበሰለውን የሰው ኃይል ከጥሬው ጋር በመበወዝ አደራጅተው አጭር ሥልጠና በመስጠት በአጭር ጊዜ ውስጥ አስታጥቀው ለውጊያ ማሰማራት በኛ በኩል ለሁለቱም ድርጅቶች የተሰጠው የሞራል፣ የስንቅና የትጥቅ ድጋፍ የተሟላ ስለነበር ሁለቱም ድርጅቶች በሰሜንና በመሀከላዊው ክልሎች ሰፍሮ የሚገኘውን የመንግሥቱን ሠራዊት በአስደንጋጭ ሁኔታ ያምሱት ጀመር።

ይህንን የተመለከቱና ደቡባዊውን የሱማሌ ህዝብ እንወክላለን የሚሉ ሲቪሎችና የጦር መኮንኖች ቡድን በኮሎኔል ኡመር ጀሲ እየተመራ በዚያው ዓመት በጥቅምት ወር አዲስ አበባ መጥቶ ለሁለቱ ድርጅቶች ከተሰጠው ድጋፍ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ጥያቄ አቅርቦ ስለተፈቀደለት «የደቡብ ሱማሌ ብሄራዊ ንቅናቄ» (Southern Somali National Movement) በተሰኘ የፖለቲካ ድርጅት አመራር የደቡብን ክልል ህዝብ ከዚያድ ባሬ አገዛዝ የሚያላቅቅ የደፈጣ ተዋጊ ጦር ተቋቋመና ኪሱማዩ በመባል በሚጠራው የሱማሌ ሦስተኛውና ደቡባዊ የወደብ ከተማ አቅጣጫ ውጊያ ጀመሩ።

ሦስቱም የጀነራል ዚያድ ባሬ መንግሥት ተቃዋሚ ድርጅቶች ውጊያ ከጀመሩ በኋላ በየፊናቸው የሚዋጉበትን ዓላማ፣ ከህዝቡ የሚጠይቁትን ትብብርና እንዲሁም ህዝቡን ሊያሳውቁት የሚፈልጉትን ማናቸውም ነገር የሚያስ ተላልፉበት ለእያንዳንዳቸው በፈረቃ በቀን አንድ ሰዓት የራዲዮ አገልግሎት ስለፈቀድንላቸው መንግሥቱን ተቃዋሚ ለሆኑት የሱማሌ ልዩልዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና በጠቅላላውም በጀነራል ዚያድ ባሬ ላይ ጥላቻ ላደረባቸው ወገኖች የሚያስደስት ዜና ሲሆን ለመንግሥትና ለደጋፊዎቹ በጣም አስደንጋጭ መርዶ ነበር ለማለት ይቻላል።

ምዕራፍ ስድስት

ወሰኑን እንዳውቅ ከፈለግህ ወሰኑን ልቀቅልኝ

የፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ መንግሥት ከአካባቢው አድህሮት፣ ከውስጥ ፀረ አንድነትና ፀረ አብዮት ኃይላት ጋር ሆኖ በቅንጅት ውጊያ እንደ አላሰቃየን ሁሉ በተራው የእሱም ተቃዋሚ ኃይሎች የኢትዮጵያ አብዮታዊ ጦሮች ሱማሌ መንግሥት የአስተዳደር ክልል ውስጥ ጠልቀው በመግባት ከተቆጣጠሯቸው የሰሜን፣ የመሀልና የደቡብ ክልል ጠረፎች እየተንደረደሩ የመከላከያ ሠራዊቱንና ፀጥታ አስከባሪ ፖሊሶችን ማተራመስ ሲጀምሩ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሱማሌን መንግሥት በሚወክለው አምባሳደር አማካኝነት ጀነራል ዚያድ ባሬ ከዚህ የሚከተለውን የቃል መልዕክት ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሃፊ ለኩርት ቫልዳሃይም ላኩ።

ኩርት ቫልዳሃይም ከፕሬዝዳንት ዚያድ የተላከልኝ የቃል መልዕክት ብለው የነገሩኝን እጠቅሳለሁ። «በእኛና በኢትዮጵያዊያን መካከል ለረጅም ጊዜ የሰላም ጠንቅ ሆኖ የቆየውን የድንበር ጉዳይ በተመለከተ ለላኩልኝ ወንድማዊ ምክርና ማሳሰቢያ ባለውለታ ነኝ።

እርሶ እንደአሉትም ከብዙ ዘመናት ትግሎች፣ ወታደራዊ ግጭቶችና ብሎም ከፍ ያለ ጦርነት በኋላ ከጎረቤታችን ጋር ተቀራርቦ በመወያየት ዘላቂ የሆነ የሰላም መፍትሄ ከመፈለግ በስተቀር ሌላ አማራጭ አይኖርም።

ከሊቀ መንበር መንግሥቱ ጋር በማናቸውም እሱ በመረጠው ጊዜና ቦታ ከጠራኝም እስከ አዲስ አበባ ድረስ ሄጄ ልገናኘው ዝግጁ መሆኔን በክቡርነትዎ አማካኝነት እንዲያውቅ ሆኖ እሱ ዓለም ተቀብሎታል የሚለውን የሁለቱን አገሮቻችንን ሕጋዊ ድንበር ወይንም ወሰን አድርጌ እንድቀበል ከፈለግህ ወሰኑን ልቀቅልኝ ብሎሀል ብለው እንዲነግሩልኝ ላስቸግርዎት ተገድጃለሁ» የሚል ነበር።

በዚህ ጊዜ ውስጥ ተመሳሳይ የሆነና በተለይም ሊቀ መንበር መንግሥቱ አሁን ያለውን ወይንም ከቅኝ ገዥዎች የተረከብነውን የሁለቱን አገሮቻችንን ወሰን እንድቀበል ከፈለገ በጦር ኃይል የያዘውን መሬት ለቆ እንዲወጣና በሁለቱ አገሮቻችን መካከል እርቅ እንዲፈጠር እርዳኝ የሚል የቃል መልዕክት ለዲሞክራቲክ የመን ፕሬዝዳንት አሊ ናስርና ለጅቡቲው ፕሬዝዳንት ለሐሰን ጉሌድም ልኳል።

የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ኩርት ቫልዳሃይም መልዕክቱ እንደደረሳቸው የመልዕክቱን ይዘት ሳይገልፁ በደፈናው በዚያው ዓመትና ወራት ኬኒያ ናይሮቢ ላይ በሚደረገው የአፍሪካ መሪዎች ዓመታዊ ስብሰባ ላይ ስለሚገኙ ለብርቱ ጉዳይ ሊያነጋግሩኝ የሚፈልጉ መሆናቸውን ስለገለጡልኝ ናይሮቢ ለመገናኘት ተቃጠርን።

ናይሮቢ ላይ በተደረገው የአፍሪካ መሪዎች ስብሰባ ፕሬዝዳንት ዚያድም ተገኝቷል። ስብሰባው በተከፈተ ማግሥት ከቀትር በኋላ በግምት ወደ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ ከዋናው ስብሰባ አዳራሽ ጋር ተያይዞ በተሰራ ሰፊና ምቹ የእንግዶች ማረፊያ አዳራሽ ውስጥ ከኩርት ቫልደሃይም ጋር ተገናኝቼ ከዚህ በላይ የገለፅኩትን ከፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ የተላከላቸውን የቃል መልዕክት ነገሩኝ።

ፕሬዝዳንት ሀሰን ጉሌድና አሊ ናስር ቀደም ብለው አስታውቀውኝ ስለነበር ለተነገረኝ መልዕክት ባዕድ አልነበርኩም። ስለበጎ የሰላም ጥረታቸው ኩርት ቫልደሃይምን ከአመሰገንኩ በኋላ እውነት ከሆነ በፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ሀሳብ የምስማማ መሆኔን ገልጬ በእሱ በኩል ያቀረበውን መፍትሔ ምስጢር ሳያደርገው ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጽሕፈት ቤትና ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት በይፋ በጽሑፍ እንዲገልፀው ይነግሩት ዘንድ አሳስቤያቸው እሳቸውም ጥያቄዎ አግባብና ትክክል ነው ብለውኝ በሌሎች ጉዳዮች ላይ መወያየት ጀመርን።

በዚህ ጊዜ ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ከስብሰባው አዳራሽ ወጥቶ አጃቢዎቹን በማስከተል ወደ እኛ አምርቶ አጠገባችን ሲደርስ የኔ አጃቢዎች ፈጥነው በመጋረድ ወደኔ እንዳይቀርብ ሲከለክሉት የእሱ አጃቢዎች ደግሞ መሪያችንን ልትገፉ አትችሉም በማለት ከኔ አጃቢዎች ጋር በፈጠሩት ግርግር የተደናገጡት ኩርት ቫልደሃይም ሳይሰናበቱኝ ጥለውኝ ሸሹ።

ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ የፈጠረው ሁኔታ ያልጠበቅሁት በመሆኑ ጥቂት ግር ቢለኝም የኔን አጃቢዎች እንዳይነኩት በመገሰፅ ከመቀመጫዬ ስነሳ እሱም ወደኔ ጠጋ ብሎ ለመጨበጥ ሁለት እጁን ዘረጋልኝ።

ሰውዬው እኔን ሊወልድ የሚችል አዛውንት ነው። ኤደን ላይ ላልተሳካው የሠላም ውይይት በተገናኘን ጊዜ አብሮት የነበረውና ከብዙ ልጆቹ ሁለተኛው ነው የተባለው ግለሰብ የመሰለ ሽማግሌ ነበር።

ጠላትም ቢሆን በሽምግልናው ከበደኝና በሁለት እጆቻችን ተጨባብጠን እንደቆምን «መንግሥቱ! እኔና አንተ ተፈጥሮ ያስተሳሰረን ጎረቤቶች ከመሆናችን ሌላ አፍሪካዊ ወንድማማቾችም ነን።

ጎረቤትና ወንድምማማቾችም በተለያዩ ምክንያቶች መጋጨት ያለነው የሁለቱ እህትማማቾች አገሮች ግጭት የመጀመሪያ አይደለም። ስለሆነም ለዘላለም ጠላቶች ሆነን መኖር አለብን ብዬ አላምንም ይቅርታ አድርግልኝና እንታረቅ» አለኝ።

አሁንም እጄን ያለመልቀቅ አጥብቆ ይዟል። ሁለታችንም ለከበቡን ጋዜጠኞችና ካሜራዎች የተመቻቸን ቋሚ ዒላማ ሆነናል።

እኔም "እውነት ነው የሁለቱ አገሮቻችን ትስስር ከጎረቤትነትም በላይ የላቀ ነው ብዬ አስባለሁ እንዳልከውም ለዘላለም ጠላት ሆነን መኖር የለብንም በበኩሌ ያለፈውን ይቅር ብያለሁ።

ያለፈውን ለታሪክ ትተን ወደፊት እንራመድ ስለው በጣም አመስግኖ በተፈነቀለ ስሜት በሁለት እጆቹ ሲያቅፈኝ ለሚመለከቱን ሁሉ ትርዒቱ አስገራሚ ነበር።

ትርዒቱ በዚህ ሁኔታ አለቀና ወደ ስብሰባው አዳራሽ ስመለስ ወደ አዳራሹ በሚያስገባው በር አቅራቢያ ከጉባዔው ፊትለፊት በስተቀኝ የኬኒያ መንግሥት ከጋበዛቸው እንግዶች ጋር ተቀምጠው የነበሩትን ቫልዳሃይምን አግኝቼ ከተሳሳቅን በኋላ የተደረገው ጠለፋ (Hijack) ሁለታችሁ በጋራ ያቀዳችሁት ነው እንዴ? ብዬ ብጠይቃቸው «ሊቀ መንበር እውነት ነው የምልዎት ስለዚህ ጉዳይ የማውቀው ነገር የለም። እኔም ፍፁም ያልጠበኩትና ያላሰብኩትን ነገር ነው የተመለከትኩት» አሉኝና ወደ መቀመጫዬ አመራሁ።

የፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ መንግሥት ተቃዋሚዎች በሱማሌ ግዛት ውስጥ የጀመሩት ትግል ከመሳሪያና ከራዲዮ ፕሮፖጋንዳነት ደረጃ ልቆ ወደ መደበኛ ፍልሚያ አድጎ በመላው ሱማሌ ህዝብ ዘንድ ትኩረትና ድጋፍ ማግኘት ብቻ ሳይሆን በተጋነነ ሁኔታ ይወራለትም ጀመር።

በዚህም ምክንያት ከመንግሥቱ መደበኛ የመከላከያ ሠራዊትና ከሕዝቡም መካከል ለትግል ተቃዋሚዎቹን ለመቀላቀል የሚመጡ ወጣቶች ቁጥር እየጨመረ በመሄዱ ከአንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለሦስቱም ድርጅቶች በአጠቃላይ 60,000 ስልሳ ሺህ ተዋጊዎችን በተሟላ ሁኔታ አስታጥቀን ማሰማራት ተቻለ።

ተሳስበንና ተከባብረን በሰላምና በመልካም ጉርብትና አብረን እንኑር ብለን መጠየቅ ብቻ ሳይሆን ብንለምናቸውም የሠላም ፍላጎታችንን እንደ ፍርሃትና ድክመት በመገመት ሲወጉንና ሲያስወጉን የኖሩት ጎረቤቶቻችን የየእጃቸውን እንዲያገኙ ማድረግ የጀመርነው በደቡብና በምሥራቅ ግንባሮች ብቻ ሳይሆን በምዕራብም ነበር።

የተስፋፊውንና የጦረኛውን የሱማሌ መንግሥት ተቃዋሚዎች ከማደራጀታችን በፊት ጥቂት ዓመታት ቀደም ብለን የሱዳን ህዝብ ነፃ አውጭ ንቅናቄ የተሰኘ የፖለቲካ ድርጅት (Sudan People Liberation Army) የተሰኘ ቁጥሩ 80,000 ሰማኒያ ሺህ የሆነ ተዋጊ ኃይል አሰልጥነን አስታጥቀንና አደራጅተን በመላ የሱዳን ደቡባዊ ክልሎች አሰማርተናል።

ለደቡብ ሱዳን ጭቁን ህዝብ በኢትዮጵያ አቅም ይህንን ያህል ከፍያለ ድጋፍ መስጠት ያስፈለገበት ምክንያት የመነጨው የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮት ለሰው ልጅ

መብት መከበር፣ ነፃነትና እኩልነት ካለው እምነትና ከወዝ አደራዊ ዓለም አቀፋዊነት አቋሙ ነው።

የደቡብ ሱዳን ህዝብ ችግር የሱማሌ መሪዎች የመስፋፋት ፍላጎት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ከፈጠረው ችግር በጣም የተለየና ፍፁም የማይገጣጠም የፍትህና የዲሞክራሲ ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ መብት የእኩልነትና የነፃነት መሰረታዊ ጥያቄ ነው።

በሰባተኛው ምዕተ ዓመት በአረቦች የጦር ጫሪነት የተመራው የእስልምና እምነት አራማጅ ኃይሎች ንቅናቄ ከፊል እስያን አውሮፓንና ሰሜን አፍሪካን ወረው የአካባቢውን ህዝቦች በሰይፍ እስላምና አረብ ካደረጉ በኋላ ከግብፅ እየተንደረደሩ ጥንታዊቷን ሱዳን ወረው የኑባን ዘውዳዊ መንግሥት በመሰሉ የተለያዩ ክርስቲያናዊ ሥርወ ነገ ሥታት የተገነቡ አፍሪካዊ ሥልጣኔዎችን አውድመው የመንግሥታቱን ሉአላዊነትና የህዝቡን ነፃነት ገፈው በጊዜ ሂደት እስላማዊነትንና አረባዊነትን ከማስፋፋት ጀምሮ አፍሪካዊያኑን ህዝብ በዘር መድሎ መጨቆን ብቻ ሳይሆን ለለየለት ባርነት መዳረጋቸው የዓለም ታሪክ ከዘገባቸው የሰው ልጆች ሰቆቃዎች ሁሉ ወደር የሌለው አሳዛኝ ታሪክ ነው።

ይህ በሰው ልጅ ክብርና ስብዕና ላይ ለአያሌ ዘመናት ሲፈፀም የቆየ ወንጀል በ18ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ላይ ከአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች ግንባር ቀደም በሆነው የብሪታኒያ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ጣልቃ ገብነት ምክንያት በመጠኑ ተገትቶ የነበረ ቢሆንም ከነፃነት በኋላ በሱዳን የፖለቲካ ሥልጣን ማማ ላይ በመተካት የተፈ ራረቁ ገዥ መደቦች በአፍሪካዊው የደቡብ ህዝብ ላይ ፀረ ህዝብ ሥርዓታቸውን እንደገና መልሰው ጫኑበት። እብሪተኛና ግፈኛ የአረብ ፊውዳሎች የኢትዮጵያንም ህዝብ ለአያሌ ዘመናት በተደጋጋሚ ተፈታትነውታል።

በዚህ ታሪክ መግቢያ አምድ ላይ እንደተገለፀው በአስራ አምስተኛው ምዕተ ዓመት የኢትዮጵያን ክርስቲያናዊ ህዝብና ክርስትናን ለማጥፋት ለአስራ አምስት ዓመታት ያህል በእጅ አዙር ጦርነት ወግተውናል።

በአስራ ስምንተኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ላይ ኢትዮጵያን ቅኛቸው አድርገው አባይን ከምንጩ ለመቆጣጠር በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብና በምሥራቅ ወረራ ሰንዝረውብናል።

በአስራ ዘጠነኛውኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ላይ የአረብ ሊግ የተባለ ድርጅታቸውን ሲያቋቁሙ ከአንድ ሺህ ኖቲካል ማይልስ በላይ የቀይ ባሕር ድንበርተኛ የሆነችውን አገራችንን እንደሌለች በመቁጠር ቀይ ባህርን የአረብ ባሕር ብለው ሰይመዋል።

በዚህ ጊዜ ውስጥ የኤርትራን ሕዝብ አረባዊ ሕዝብ ነው በማለት የሚኖርበትን ክልል በሀሳብ ከኢትዮጵያ ገንጥለው የአረብ ዓለም ብለው ባዘጋጁት የፖለቲካ ካርታ ቀለም መቀባት ሳይበቃቸው አፍሪካን በሚያጠቃልለው ካርታቸው ውስጥ የሳሏት ኢትዮጵያ የኤርትራ ክፍለ ሃገር የሌለበት ራሷን የተቆረጠች ኢትዮጵያን ነበር።

በኢትዮጵያ ላይ እስላማዊነትንና አረብነትን ለማስፋፋት ብቻ ሳይሆን የለም አፈር ችግራቸውንና የጣፋጭ ውሃ ጥማታቸውን በኢትዮጵያ ኪሳራ ለመለቃት ያስችላቸው ዘንድ በ1953 ዓ.ም ካይሮ ላይ ጀብሀ በማለት የሚጠሩትን ገንጣይ ድርጅት አደራጅተውና አስታጥቀው ካዘመቱብን በኋላ በተከታታይ ሻዕቢያ የሚሉትን ሌላውን ገንጣይ ድርጅት አደራጅተው ከሰላሳ ዓመታት በላይ እልህ አስጨራሽ የሆነ የእጅ አዙር ጦርነት ማካሄዳቸው ኤርትራን መገንጠል ስለአላስቻላቸው በመጨረሻው ወያኔ የተባለውን አስገንጣይ ድርጅት በማቋቋም የረጅም ዘመን ምኞታቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ችለዋል።

የነፃ አውጭውን ሠራዊት ቁጥር የማስፋታችንና የትጥቁንም ጥራት ከፍ የማድረጋችን ምክንያት ደቡባዊያን የሚታገሉት አረቦች ነን ከሚሉት ሰሜን ሱዳናዊያን ጋር ብቻ ሳይሆን ከነዳጅ ዘይት አምራች አረባዊ መንግሥታት ጋር ሁሉ ከመሆኑ ሌላ ነፃ ማውጣት ያለባቸው ክልል በጣም ሰፊ በመሆኑ ነው።

አብዮታዊት ኢትዮጵያ ራሷ ከውጭ ወራሪዎችና ከውስጥ ፀረ ህዝብና ዐረ አንድነት አድህሮት ጋር እየተዋጋች የትጥቅና የተለያዩ ቁሳቁስ እርዳታ ትሰጥ የነበረው ድንበርተኞቻችን ለሆኑት ለሱማሌና ለሱዳን ጭቁን ህዝቦች ብቻ ሳይሆን ከአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች ጋር ለነፃነታቸው ሲታገሉ ለነበሩት፣ ለዚምባብዌና ለናሚቢያ ህዝቦችም ጭምር ነበር።

ለናሚቢያ የነፃነት ታጋዮች በአገራችን የንግድ አውሮፕላን አብራሪነትና መካኒክነት፣ የባንክና የተለያዩ የሕክምና ሞያ ትምህርቶችን ስንሰጥና በየጊዜው የገንዘብ እርዳታም ስናደርግ ለዚምባብዌ ነፃ አውጭ አርበኞች ግንባር (Patriotic Front) ማለትም በጓድ ጆሽዋ ኢንኮሞና በጓድ ሮበርት ገብርኤል ሙጋቤ ለሚመሩት ሁለት ድርጅት በአብዮታዊ ሠራዊታችን ደረጃ ለአምስት ሺህ የደፈጣ ተዋጊ ሠራዊት ሥልጠና በመስጠት፣ ዘመናዊ የውጊያ ልብስ በማልበስና ዘመናዊ የሆነ መሳሪያ በማስታጠቅ የአየር መንገዳችን ለተወሰነ ጊዜ የውጭ በረራውን አቁሞ ተዋጊዎቹን ወደ ዛምቢያ ርዕሰ ከተማ ሉሳካና ወደ ሞዛምቢክ ርዕሰ ከተማ ማፑቶ እንዲያጓጉዝ አድርገናል።

ከፖርቱጋል ቅኝ ገዥ መንግሥት አውሮፓዊ ሠራዊትጋር ታግሎ ድል በመቀዳጀት ነፃነቱን ያገኘውና በታወቀው አፍሪካዊ አብዮተኛ በጓድ ሳሞራ ማሼል የሚመራውን አብዮታዊ መንግሥት ለመጣል ሲባል በደቡብ አፍሪካ ዘረኛ መንግሥት እየተረዳ አገሩን የሚወጋው ሬናሞ ከተባለው ምንደኛ ድርጅት ጋር በሚዋጋ ጊዜ ለአስር ሺህ የመንግሥቱ ሠራዊት የሚሆን ትጥቅና አልባሳት ረድተናል።

አብዮታችንን ደጋፊ ከነበሩት አፍሪካዊ አገሮች የመጀመሪያዋ የነበረችውን ታንዛኒያን የዩጋንዳው መሪ ኢዲ አሚን በወረረበት ጊዜ ራሷን ትከላከል ዘንድ አምስት ሚሊዮን የአሜሪካን ብር የሚያወጡ ቀላል መሳሪያዎች፣ መድፎች፣ ፀረ-ታንክና ፀረ-አውሮፕላን ሚሳይል ወንጫፊዎች ወዘተ ከበቂ የተለያዩ ጥይቶች ጋር ዳሬሰላም ከተማ ድረስ በኢትዮጵያ አየር መንገድ አቅርበናል።

ጁሊየስ ኔሬሬ ከምንደኞች ጋር የሚዋጋውን የሞዛምቢክን መንግሥት ጦር ለመርዳት ፈልገው ጦሩን የሚያጓጉዙላቸው የአየር መጓጓዣ ጠይቀውን አንድ እግረኛ ብርጌድ ወይንም 2,500 ጦር የአየር ኃይላችን በአንቶኖቭ መጓጓዣ አውሮፕላኖች ከዳሬሰላም እስከ ማፑቶ ድረስ አጓጉዞንላቸዋል።

ከዚህ በላይ እንደተባለው ለተለያዩ ታጋይ ድርጅቶችና ወዳጅ አገሮች በተሰጧቸው እርዳታዎች የቱን ያህል እንደተጠቀሙ በአጠቃላይ፣ በኮሎኔል ዶክተር ጆን ጋራንግ ቆራጥና የበሰለ አመራር የደቡብ ሱዳን ህዝብ ነፃ አውጭ ንቅናቄ ያከናወናቸውን ተግባሮች በተለይ ወደፊት በዚሁ በቅፅ ሁለት ለጉዳዩ አግባብ ባለው ክፍል በተለያዩ ምዕራፎች በስፋትና በዝርዝር ይገለፃል።

ተስፋፊውን የሱማሌ መንግሥትና የፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ደጋፊ የሆነውን የመከላከያ ሠራዊት ለአንድ ዓመት ያህል በተፋለሙት በሦስቱ ተቃዋሚ ድርጅቶች ውስጥ አንዳንድ እንግዳ ነገሮች ተከስተዋል።

የሱማሌን ሦስተኛ ከተማ ኪሱማዩን የመጀመሪያ ግቡ አድርጎ የሚዋጋው የደቡብ ንቅናቄ መሪ ኮሎኔል ኡመር ጄሲ ድርጅቱ ሜ/ጀነራል አድርጎ ሾሞኛልና ማንነቴን እወቁልኝ ሲል በጽሑፍ አሳወቀን።

ርዕሰ ከተማዋን ሞቃዲሾን ግቡ አድርጎ የሚፋለመው ግንባር መሪ ኮሎኔል አብዱላሂ የሱፍ ከአብዛኛው የግንባሩ አባላትና በተለይም ከከፍተኛ የአመራር አካላት ጋር ቅራኔ ውስጥ በመግባቱ የተነሳ በተፈጠረው የአመራር ጉድለት ግንባሩ በመዳከሙ ተዋጊው ሠራዊት የሚከፍለው መስዋዕትነት ውጤት አልባ ይሆን ጀመር።

የሰሜኑን የሱማሌ ህዝብ እወክላለሁ የሚለውና የመጀመሪያ ግቡን የአገሪቱን ሁለተኛ ከተማ ሐርጌሳን አድርጎ የሚዋጋው ንቅናቄ ከተቀሩት ከሁለቱ ድርጅቶች በጥቂት ወራት ቀደም ብሎ የተቋቋመና ትግል የጀመረ ከመሆኑ ሌላ የሰሜኑ ክልል ሕዝብ በፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ላይ ባለው የከረረ ጥላቻ ምክንያት ለንቅናቄው ትግል መሳካት ሲል፣ የሞራል፣ የሰው ኃይል፣ የገንዘብ፣ የስንቅና የተለያዩ የቁሳቁስ ድጋፎችን በማበርከቱ ፍልሚያው በተሳካ ሁኔታ እየተካሄደ እያለ መሪው ኮሎኔል ጃማ አብዲ በፍልሚያው ላይ ተሰዋ። ኮሎኔል ጃማ በንቅናቄው ሠራዊት ብቻ ሳይሆን በሰሜኑ ህዝብ የተወደደና ችሎታ ያለው ብቁ መሪና ጀግናም ነበር።

በትግሉ አፍላ የተቀጨበት ምክንያት የዚያድ ባሬ መንግሥት ቅጥረኛና የአረቦች መሳሪያ ሆኖ ምሥራቅ ኢትዮጵያን ሲያሸብርና የንፁሀንን ደም ሲያፈስ የነበረውን የኦሮሞ እስላማዊ ጦር በቅድሚያ ለማጥፋት በገባልኝ ቃል መሰረት በልዩ ሁኔታ ያሰለጠነውን ኮማንዶ ጦሩን ራሱ እየመራ በሱማሌ ግዛት ውስጥ ጠልቆ በመግባት ከደመሰሰ በኋላ ከመንግሥቱ ጦር በተሰነዘረበት መልሶ ማጥቃት ነው ከብዙ ተከታዩቹ ጋር የተሰዋው።

በኮሎኔል ጃማ አብዲ ምትክ የንቅናቄውን መሪ ለመምረጥ የተጠራው አስቸኳይ ሸንጎ በፖለቲካና በወታደራዊ ሳይንስ ጥምር እውቀት ያለው ሁለገብና በሳል ሌላ የጦር መኮንን ለጊዜው በመታጣቱ የንቅናቄውን የፖለቲካ መሪና የወታደራዊ ክንፍ አመራር ከፋፍሎ ለሁለት ሰዎች በመስጠት የንቅናቄው መሪ ያደረገው መሐመድ ኢጋል የተባለ ምሁርና በሳል የፖለቲካ ሰው ነበር።

የኢጋል ቤተሰቦች በሰሜን ሱማሊያ መልካም ስም ያላቸው የታወቁና የሰሜኑን ክልል ከብሪታኒያ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ቅኝነት ነፃ ለማውጣት በተደረገው ትግል ታላቅ አስተዋፆ ማድረጋቸው የሚነገርላቸው ናቸው።

በቅፅ አንድ እንደገለፅኩት የሱማሌ ህዝብ ከብሪታኒያና ከኢጣሊያ ቅኝነት ታግሎ ነፃ በመውጣት ሁለቱን ሱማሌዎች ማለትም ሰሜኑንና ደቡቡን አንድ አድርጎ የመጀመሪያ መንግሥታዊ ህልውናውን በመሰረተ ጊዜ የደቡቡ ተወላጅ ዶክተር አብዱል ረሺድ አሊ ሸርማርኪ ፕሬዝዳንት የሰሜኑ ተወላጅ ኢብራሂም ኢጋል ጠቅላይ ሚኒስትር መሆናቸው በአንባቢ ዘንድ ይታወሳል።

በዚሁ ጊዜ ውስጥ የመንግሥቱን የጦር ኃይሎች እንዲመራ ጠቅላይ ኤታማጆር ሹም ሆኖ የተሾመው ኮሎኔል ዚያድ ባሬ በኋላ ጀነራል ብሎም ፕሬዝዳንት መንግሥት ሲገለብጥና መላውን ነባር የሱማሌ አንጋፋ ፖለቲከኞች ሰብስቦ ዘብጥያ ሲጥል አብሮ የተጣለውና በመሰቃየት ላይ የነበረው የጠቅላይ ሚኒስትር ኢብራሂም ኢጋል ታናሽ ወንድም ስለሆነ በእኛም በኩል ድጋፍ የነበረው ሰው ነው።

የወታደራዊው ክንፍ አመራር ለአንድ ከፍተኛ የጦር መኮንን ተሰጠና ንቅናቄው የአመራር ችግር ሳይገጥመው ትግሉ ቀጠለ።

የሰሜኑ ንቅናቄ ያለማሳለስ በየቀኑ በመንግሥቱ የመከላከያ ሠራዊት ላይ የሚያስመዘግበው ወታደራዊ ድል እየሰፋና እየጠነከረ በመሄዱ የመከላከያ ሚኒስትሩ ጀነራል ሞርጋን ሐርጌሳ ላይ የዕዝ መምሪያውን በማቋቋም ውጊያውን ራሱ ለመምራት ተገደደ።

ምዕራፍ ሰባት

የሞቃዲሾን ከተማ ግቡ አድርጎ በማዕከላዊው ሱማሌ ክልል የሚዋጋው

የሱማሌ መድህን ዲሞክራሲያዊ ግንባር የገጠመው ችግር

ጀነራል ኡመር ጂሲ የሚመራው የደቡቡ ንቅናቄ የሰሜኑን ያህል ባይሆንም በጥሩ ሁኔታ ይዋጋ የነበረ ሲሆን ድል መከጀል ቀርቶ ህልውናውም አሳሳቢ የሆነው በኮሎኔል አብዱላሂ የሱፍ የሚመራው የሱማሌ መድህን ዲሞክራሲያዊ ግንባር ነበር።

ከተከፋፈሉትና በቅራኔ ከተሳሰሩት ከግንባሩ አመራር አካላት ከተራዎቹ አባላትና ከኢትዮጵያዊያን ታዛቢዎች በየግዜው በሚደርሱን ሪፖርቶች፣ አቤቱታዎችና ብሶቶች እንደ ተረዳነው ችግሮቹ የተለያዩና ብዙም ሲሆኑ ጥቂቶቹና ዋና ዋናዎቹ ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ።

1ኛ ኮሌኔል አብዱላሂ ዩሱፍ ጠለቅ ያለ የፖለቲካ እውቀት ወይም ልምድ ያለው ሳይሆን አመራሩን ለከፍተኛዎቹ የአመራር አካላት ሳያጋራ ብቻውን በመያዝ ግንባሩ እንዳይራመድ ሰንክሎ ይዞታል።

2ኛ የትጥቅ ትግሉ በሚካሄድበት የውጊያ ግንባር እየተገኘ አመራር ከመስጠት ይልቅ በየጊዜው ሊቀመንበር መንግሥቱ ጠርተውኛል፣ ለሥራ ጉዳይ ይፈልጉኛል ወዘተ በማለት አብዛኛውን ጊዜውን የሚያሳልፈው በድሬዳዋና በአዲስ አበባ ከተሞች በመዝናናት ስለሆነ ግንባሩ መሪ አልባ ነው ለማለት ይቻላል።

3ኛ ወደ ተለያዩ ወዳጅ አገሮች እየሄድኩ እርዳታ ማሰባሰብ አለብኝ በማለት እስከ ዛሬ ብቻውን አዘውትሮ የሚሄደው ሊቢያ ብቻ ሲሆን ሄዶም በቶሎ ሳይመለስ ለወራት ስለሚቆይ የግንባሩ ከፍተኛ የአመራር አካላት አንዳንድ ውሳኔዎችን በተገቢው ጊዜ መወሰን ስለሚሳናቸው ድርጅቱ በመዳከም ላይ ይገኛል።

4ኛ ለድጋፍ ማሰባሰብ ሄድኩ እያለ ከውጭም ሆነ ከኢትዮጵያ መንግሥት በየጊዜው ለግንባሩ በገንዘብ የሚሰ ጠውን ድጋፍ ለተዋጊው ሠራዊት ቀርቶ ለከፍተኛው የአመራር አካላትም የማይገለጥና የማይታወቅ የግል ምስጢሩ ነው።

5ኛ ቀደም ብሎ በዚያድ ባሬ ሠራዊት ውስጥ የሚያውቃቸውን የጦር መኮንኖች ብቻ በህቡዕ እየሰበሰበ አንጃ ድርጅት ፈጥሮ የግንባሩን ሠራዊትና የአመራር አካላት ከፋፍሏል።

6ኛ ፀረ-ምሁር ነው፣ የግንባሩ ከፍተኛ የአመራር አካል የሆኑትን ሲቪል ምሁራን ከመኮንኖቹ ጋር እያጋጨ እንድንገለል ብቻ ሳይሆን እንድንፈራም አድርጎናል፣

በፍልስፍናና በፖለቲካ ሳይንስ የዶክትሬት ድግሪ ያለውን በእውቀቱና በሥራ ልምዱ ከሁላችንም የላቀና የበሰለ አባላችን በስራ አስኪያጅ ኮሚቴያችን ላይ እንደሰሜኑ ንቅናቄ የኛም ግንባር መዋቅራዊ ለውጥ ቢያደርግ ይበጀዋል ብሎ በማሳሰቡ የግል ጠላቱ አድርጎ ይመለከተዋል ወዘተ የሚሉ ናቸው።

እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የግንባሩ አባላትና የአመራር አካላት የቅራኔ ምንጮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፉና እየተባባሱ ከቁጥጥር ውጪ ሆነው ድርጅቱን ከማፍረሳቸው በፊት ግንባሩን አስተናጋጅና ከመንግሥት ጋር አገናኝ ሆነው ሁላችንንም ይረዱን የነበሩት እነፊታውራሪ ደምሴ ተፈራ፣ ጀነራል ምህረተ አብ ተድላና ጀነራል ክንፈ ቅራኔዎቹን ለማለዘብ ያደረጉት ጥረት አልተሳካም።

ሌሎች ለግንባሩ ደህንነትና ትግሉ ግቡን ለመምታቱ ልዩና ከፍተኛ ኃላፊነት ያላቸው፣ የ1ኛው አብዮታዊ ሠራዊት አዛዥ የነበረው ሜ/ጀነራል አበራ አበበና የአገር ደህንነት ሚኒስትራችን ጓድ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ወዘተ በየበኩላቸው ከተሰማቸው ስጋት የተነሳ በኔ ደረጃ መፍትሄ ይፈለግ ዘንድ በመጠየቅ እነሱም መፍትሄ ይሆናሉ የሚሏቸ ውን ሃሳባቸውን አካፈሉኝ።

በተጠየቅሁት መሰረት የበኩሌን መፍትሔ ለመሻት በቅድሚያ መስማት የፈለግሁት ኮሎኔል አብዱላሂ ሊመራን የሚችል ሰው ስለ አልሆነ በአስቸኳይ ከሥልጣኑ ይነሳ የሚሉትን ወገኖች ክስ ነበር።

ያዳመጥኳቸው የግንባሩ አመራር ከፍተኛ አካል አባላት በኮለኔል አብዱላሂ ላይ በጣም የከረረ ጥላቻ ያደረባቸውና በእሱ አመራር ፍፁም ተስፋ የቆረጡ መሆናቸውን ተገነዘብኩ። በእነሱና በኮለኔል አብዱላሂ መካከል ያለውን የከረረ ቅራኔ የኔ ሽንገላ ያግባባቸዋል ብዬ በማስበው ምክር ለማለዘብ ብሞክር ለችግሩ መፍትሄ ሊሆን እንደ ማይችልም ተረዳሁ።

ስለሆነም ኮለኔል አብዱላሂ ከሥልጣኑ ቢነሳ እሱን ተክቶ ከዚህ ውስብስብ ችግር በማውጣት ወደ ድል ይመራናል ብላችሁ የምታምኑበት ሰው አላችሁ ወይ? ወይንም አዘጋጅታችኋል ብዬ መጠየቅ ነበረብኝ።

ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ሁሉም በሕብረት የሰጡኝ መልስ «በሕንድ አገር የዚያድ ባሬ መንግሥት ተወካይ አምባሳደር ሆኖ የሚሰራው ብ/ጀነራል ፋራህ አይዲድ የኛ ሰው ነው።

ከፍ ያለ ወታደራዊና ፖለቲካዊ እውቀት ከልምድ ጋር አጣምሮ የያዘ የአመራር ብቃት ያለው በኛ ብቻ ሳይሆን በሱማሌ ሕዝብም የሚታወቅና የሚታመን ሰው ስለሆነ ኮለኔል አብደላሂን ተክቶ ይመራን ዘንድ እሱን ከሕንድ በመጥራትና

የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ረገድ መንግሥትዎ እንዲረዳን እንለምናለን» የሚል ጥያቄ ነው ያቀረቡልኝ።

ባቀረቡት ሃሳብ ከተስማማሁ በኋላ ኮሎኔል አብዱላሂ የግምባሩ መሪ የሆነው በግንባሩ ሸንጎ ብያኔ ስለሆነ አሁንም ከሥልጣኑ የሚወርደውና ጀነራል ፋራህ የሚተካው በሸንጎው ውሳኔ ነውና በእናንተ በኩል ከእንግዲህ ወዲያ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የሸንጎውን ስብሰባ ጠርታችሁ ግለሰቦችን የመለዋወጥ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ችግሮቻችሁን ሳትሸፋፍኑ በግልፅነትና በዲሞክራሲያዊ መንፈስ ፍርጥርጥ አድርጋችሁ በመወያየት ዘላቂ መፍትሄ ለማግኘት የሚቻላችሁን ሁሉ ማድረግ አለባችሁ ብዬ አስባለሁ።

ለሸንጎው ጥሪ ብቻ ሳይሆን ግንባሩ ወደማይቀረው ድል እንዲያመራ የተለመደው ሁለገብ ድጋፋችን አይለያችሁም በማለት አሰናበትኳቸው።

ከዚህ በኋላ ኮሎኔል አብዱላሂን ጠርቼ ማነጋገር ነበረብኝ። የግንባሩን ከፍተኛ የአመራር አካል አባላት ለመጀመሪያ ጊዜ ከእሱ ነጥዬ ማነጋገር በእሱ ዘንድ ያልተጠበቀና በእጅጉ የሚያሳስበው ብቻ ሳይሆን ሊያደናግረውም የሚችል ሁኔታ መፈጠሩ ግልፅ ነው።

ወደፊት የሱ ከግንባሩ መሪነት መነሳት በሸንጎው ውሳኔ ተግባራዊ እስኪሆን ድረስ በኔ በኩል እሱን ላለማሳዘንና ስሜቱን ላለመጉዳት ጥንቃቄ ማድረግ ነበረብኝ።

አዲስ አበባ አስጠርቼው በጽህፈት ቤቱ ውስጥ በተገናኘን ጊዜ በፈገግታና ወትሮም በማደርገው ወንድማዊ አቀባበል ተቀብየውና ሻይ ጋብዤው ነው ውይይት የጀመርነው።

እሱ በተከሰሰባቸው ሐተታዎች ላይ ሳይሆን የሱን ስጋትና ፍርሀት ፍፁም በሚያረጋጉና በሚያዝናኑ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ነበር መወያየት የጀመርነው።

በዚህም ምክንያት ስንገናኝ ከነበረው የጨፈገገ ገፅታው በተነጋገርን ቁጥር እየተለወጠ መሄዱን ለመመልከት ችያለሁ በመጨረሻም ያልኩት ከዚህ በፊት በተገናኘንባቸው ጊዜያቶች በአመራርህ ላይ የገጠሙህን አንዳንድ ችግሮች እንደ አስረዳኸኝ ሁሉ በምትመራቸው የግንባሩ ከፍተኛ የአመራር አካላትም ዘንድ አንዳንድ ቅሬታዎች መኖራቸውን አንተም አትስተውም።

ለችግሮቹ ተገቢውን ትኩረት ሰጥተን ስር ከመስደዳቸው በፊት በጋራ መፍትሄ መሻት ተገቢ መስሎ ስለታየኝና የሁሉንም ወገን ችግር መረዳት ደግሞ እኔን ከራሴ የህሊና ወቀሳ ስለሚያድነኝ ጓዶችህን ከአንተ ለይቼ በመጥራት የእነሱንም ቅሬታና እንዲሁም ሃሳብ ለማዳመጥ ሞክሬአያለሁ። ከአንተም ከእነሱም ባገኘሁት ግንዛቤ

ችግሮቹ ግንባሩን የሚያፈርሱ ናቸው ተብለው ሊጋነኑ የሚገባቸው ባይሆኑም የሚናቁ ያለመሆናቸውን ግን ልሰውርህ አልፈልግም።

ከተነገሩኝ ቅሬታዎች አንዱና ዋናው በመሃከላችሁ አንዳንድ ቅራኔዎች ሲፈጠሩ በውይይት የምትፈቱበትን፣ ለማናቸውም ችግሮች መፍትሄ የምትፈልጉበትን፣ የትግላችሁን የእድገት ደረጃ ወይንም ድክመት ገምግማችሁ ተገቢ የትግል ስልትና ስትራቴጂ የምትቀይሱበት መድረክ የሆነው የግንባሩ ዓመታዊ የሸንጎ ስብሰባ ሳይጠራ ጊዜው መተላለፉ ስለሆነ ሸንጎው አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እንደሚሰበሰብ በአንተስም ቃል ገብቼ በመሰናዶውም አስፈላጊ የሆኑት ድጋፎች እንደተለመደው በኛ በኩል የማይጓደሉ ስለመሆናቸው አስረድቼ ያሰናበትኳቸው መሆኔን ልገልፅልህ ነው የጠራሁህ አልኩት።

ውይይታችንን አብቅተን ሳሰናብተው በፊቱ ገፅታ ላይ የተመለከትኩት ተቃዋሚዎቼ እውን የሸንጎውን ስብሰባ አዘገየ ብለው ብቻ ነው የከሰሱኝ ይህ ሰው በእርግጥ ይህንን ብቻ ሊነግረኝ ነው ያስጠራኝ? ይህንን ማድረግ ምን ይገደኛል ብሎ ራሱን የሚያነጋግር መስሎ ነው የታየኝ።

እንደገመትኩትም «በኔ በኩል ሸንጎውን የመጥራት ችግር የለብኝም እንደተባለው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲጠራ አደርጋለሁ። ይህንን ያህል በማስቸገራችንና የእርስዎን እጅግ የተጨናነቀ ወርቃማ የስራ ጊዜ በማባከናችን ይቅርታ እየጠየቅሁ የክቡርነትዎ ፈቃድ ቢሆን በየጊዜው በአእምሮዬ የሚመላለሰውን አንድ ጥያቄ ላቀርብ እፈልጋለሁ» አለኝ።

ምንድን ነው ጥያቄህ ስለው «እነዚህ የግንባሩ ከፍተኛ የአመራር አካላት የምንላቸው ግለሰቦች እያንዳንዳቸው ባላቸው የግል ፍላጎትና አመለካከት በሚፈጠሩ ቅራኔዎች በመተሳሰራችን ግንባሩ ግቡን ይመታል የሚለው እምነቴ ከጊዜ ወደጊዜ እየተዳከመ ነው።

ከዚህ ሁሉ ችግር ረጅም ጊዜ በመውሰድ እኛ በደምና በህይወት እናንተ በገንዘብና በቁሳቁስ ከፍ ያለ መስዋዕትነትን ከምንከፍል እንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት በጦርነቱ የተመናመነውን፣ የተዳከመውንና ሞራሉ የወደቀውን የዚያድ ባሬን ጦር እየጠረገ በመሄድ እኛን ሞቃዲሾ ለማድረስ የአንድ ሳምንት ጊዜ እንደማይወስድበት እርግጠኛ ነኝ» አለኝ።

በሚመራው ግንባር ውስጥ ያለውን ችግር በውል ያላወቀ ብቻ ሳይሆን አብዮታዊት ኢትዮጵያ ራሷ በአገር ውስጥ ጠላቶቿ በሚያካያሂዱት ሽብርና ባወጁባት ጦርነት በሰው ህይወት፣ በገንዘብና በቁሳቁስ የቱን ያህል መስዋዕት እንደምትከፍል ጨርሶ የተገነዘበ ሰው አልነበረም።

ራሳችን እጅግ ከፍተኛ ችግሮች ውስጥ ሆነን እንደምንረዳቸው ያለመገንዘብ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ የጦር ኃይል እነሱን መቃዲሾ ወስዶ ሥልጣን ላይ ለማስቀመጥ በሱማሌ ላይ ወታደራዊ ወረራ ብንሰነዝር ሊነሳ የሚችለውን ዓለም አቀፍ የፖለቲካ አቧራም ለመገመት የሚችል ራስ እንደሌለው በመረዳቴ የምለው ቢቸግረኝ እየሳቅሁ ጥሩ ቀልደኛ መሆንህን አላውቅም ነበር አልኩት።

«ጓድ መንግሥቱ የተናገርኩት ለቀልድ አይደለም ከምሬ ነው ፕሬዝዳንት ጁልየስ ኔሬሬ ኢዲ ኢሚንን ከካምፓላ አባረው ፕሬዝዳንት ሚልተን ኦቡቴን ሥልጣን ላይ ያስቀመጡ ስለሆነ እርስዎ ይህንን ማድረግ ይሳንዎታል ብዬ ስለማላምን ነው ይህንን ጥያቄ ያቀረብኩት» አለኝ።

እሱ ያቀረበውን ጥያቄ ተግባራዊ ማድረግ ቀርቶ በኔ በኩል ሊታሰብም እንደማይችል አስረድቼው ካሰናበትኩት በኋላ በሳምንቱ እሱና የስራ ጓዶቹ በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ለመረዳት ድሬዳዋ ቤተ መንግሥት በተሰበሰብንበት ጊዜም በርካታ ሱማሌዎችና ኢትዮጵያዊያን በተገኙበት መድረክ ያነኑ ጥያቄ በድጋሚ ስለአቀረበ ለእሱ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ሱማሌን ለመውረር እንደማንፈልግ ዘርዝሬ ማስረዳት ነበረብኝ።

የደቡቡ ግንባር የአስተዳደርና የሎጀስቲክ መምሪያውና የከፍተኛ አመራር አካላት መኖሪያና መስሪያ የኋላ ጠቅላይ ሰፈር በሲዳሞ ክፍለ ሃገር በቦረና አውራጃ ከተማ ነገሌ ከደቡቡ አብዮታዊ ጦር መምሪያ አቅራቢያ ሲገኝ በዚህ ጊዜ መንግሥታችንን ወክሎ ግንባሩን የሚያስተናግደውና በማናቸውም ረገድ የሚረዳው የደቡቡ ኮር አዛዥ የደርግ አባልና የሠራተኛው ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ጀነራል ጌታቸው ሺበሺ ነበር።

የሰሜኑና የመሀከላዊው ሱማሌ ክልል ተቃዋሚዎች የአመራር አካላት የአስተዳደርና የሎጀስቲክ ማዕከል መሥሪያና መኖሪያ የኋላ ጠቅላይ ሰፈር ድሬዳዋ ከተማ ውስጥ የሐረርጌ ክፍለ ሃገር ፖሊስ ሠራዊት ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት በነበረ ወታደራዊ ሰፈር ውስጥ ነበር።

የሱማሌ መንግሥት አስርገ የሚልካቸው ሰርጎ ገቦች አደጋ እንዳይጥሉባቸው ሁለቱም ጠቅላይ ሰፈሮች በኢትዮጵያ ፖሊስ ኮማንዶዎች ከመጠበቃቸው በተጨማሪ የየድርጅቱ አመራር አካላትም የየራሳቸው የታጠቁ አጃቢዎች ነበሯቸው። ኮለኔል አብዱላሂ አዲስ አበባ በጠራሁትና ኋላም ድሬዳዋ በተገናኘን ጊዜ የገባልኝን ቃል ለመለወጥ ምን እንደአስገደደው ለኔ ግልፅ አይደለም።

የሱማሌ መድህን ዲሞክራሲያዊ ግንባር ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የሆነውንና ሥልጣኔን ይነጥቀኛል በማለት በእጅጉ የሚጠላውን ምሁር በድሬደዋ መኖሪያ ጠቅላይ ሰፈራቸው ዛሬ ቀኑን በማላስታውሰው ቀን ከድሬዳዋው ስብሰባችን አንድ

ሳምንት በኋላ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ገደማ እየተዘዋወረ አየር ሲቀበል በክላሽኒኮቭ አውቶማቲክ ጠብመንጃ ተኩስ አስገደለው።

መሸሹ ይሁን ወይንም እንዳላወቀ ሰው ማደናገሩ እንደሆነ አይታወቅም በበነጋታው ወደ ጦር ግንባር ሄጃለሁ በማለት ብቻውን ከአጃቢዎቹ ጋር ወደ ኦጋዴን በየብስ ተሽከርካሪ ይሄዳል። በኦጋዴን ክልል በዋርዴር አውራጃ በገላዲን ወረዳ የግንባሩ ሠራዊት የኋላ ማዘዣ በኢትዮጵያ ክልል ውስጥ ከአብዮታዊ ሠራዊታችን መምሪያ አጠገብ ነው።

የአንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት አዛዥ ጀነራል አበራ አበበ ከሐረር ገላዲን ለሚገኘው የአብዮታዊ ጦራችን አዛዥ በወታደራዊ የርቀት መገናኛ ራዲዮ መልዕክት «ኮሎኔል አብዱላሂ ድሬዳዋ በሚገኘው ጠቅላይ ሰፈር ውስጥ ዶክተር ዩሱፍ አደምን በምሽት አስገድሎ በበነጋታው ማለዳ ወደ ኦጋዴን በየብስ ተሽከርካሪ የሚጓዘው ወደ ግንባሩ የፊት ጠቅላይ ሰፈር ማዘዣ ነው ብለን ስለምንገምት ገላዲን ሲደርስ እጁን ሳትይዙ እንቅስቃሴውንና የሚያደርገውን ሁሉ በጥብቅ እንድትከታተሉት» የሚል ትዕዛዝ ይሰጣል። ጀነራል አበራ እጁን ሳትይዙ ያለበት ምክንያት አንደኛ የኮሎኔል አብዱላሂን እጅ ለመያዝ ከበላይ ሥልጣን ማግኘት ከማስፈለጉም በላይ የዶክተር ዩሱፍ አሟሟት ምርመራ ስለአልተጠናቀቀ ነው።

ኮሎኔል አብዱላሂ ቀኑን በሙሉ ሲጓዝ ውሎ ገላዲን ከተማ ከመሸ በኋላ በመግባቱ በበነጋታው የግንባሩ ተዋጊ ጦር አለበት ስፍራ ሄዶ «መላው የግንባሩ ከፍተኛ አመራር አካላት ግንባሩ የተቋቋመበትን ዓላማ በመሳትና የገቡትን ቃል ኪዳን በማፍረስ ድርጅታችንን ስለአፈረሱት ከዛሬ ጀምሮ እናንተም ፈርሳችኋል። ከዛሬ በኋላ ከንቱ መስዋትነት መክፈል ስለሌለባችሁ መሳሪያችሁን እንደያዛችሁ በመሄድ ከሱማሌ መንግሥት ሠራዊት ጋር ተቀላቀሉ። እስከ ዛሬ አለቆቻችን አሳስተውን አገራችንን በመውጋታችን ተፀፅተን ተመልሰናል ብትሉ ጦሩ እጃችሁን ስሞ ነው የሚቀበላችሁ ሂዱ» ይላቸዋል።

ይህንን በጣም አስደንጋጭ መርዶ ከሰማው ተዋጊ መካከል ጥቂት ችኩሎች እውነት ነው ብለው በማመን «ተሽከርካሪዎቻችን ነዳጅ ስለሌላቸው ከባድ መሳሪያዎቻችንን ማንቀሳቀስ አንችልምና ነዳጅ ሊያገኙልን ይችላሉ ወይ?» የሚል ጥያቄ ለኮሎኔል አብዱላሂ ያቀርባሉ።

የነቁና የሰከኑት የጦር አዛገሮች ሰብሰብ ብለው ወደ ኮሎኔል አብዱላሂ በመቅረብ «ከሁሉ በፊት ያለወትሮህ አንተ ብቻህን እንዴት መጣህ? ግንባሩ ለተቋቋመበት ዓላማ ታማኝ አንተ ብቻ ስለሆንክ ነው? የግንባሩ ከፍተኛ የአመራር አካላት ያንተን አመራርነው የነቀፉት ወይንስ ድርጅታቸውን ነው የከዱት?

በኛ በኩል የምናውቀው አንተ አዲስ አበባ በነበርክበት ጊዜ ድሬዳዋ ያሉት የግንባሩ ከፍተኛ የአመራር አካላት በቅርብ ጊዜ ውስጥ ለሚጠራው የሸንጎ ስብሰባ ሠራዊቱን የሚወክሉ አባላትን እንድንመርጥ ትዕዛዝ ከመስጠታቸው ሌላ ሸንጎውን ለመጥራት በመሰናዶ ላይ መሆናቸውን ነው።» እያሉ በሚያነጋግሩበት ጊዜ የክልሉ የኢትዮጵያ አብዮታዊ ጦር አዛዥ ሁኔታውን በወታደራዊ የራዲዮ መገናኛ ለበላይ አካል በማሳወቁ ኮለኔል አብዱላሂ በቁጥጥር ስር ሆኖ ግንቦት 7 ቀን 1976 ዓ.ም ወደ ሐረር እንዲላክ ተወሰነ።

ምዕራፍ ስምንት

የኮለኔል አብዱላሂ ዩሱፍ ከሱማሌ መድህን ዲሞክራሲያዊ ግንባር መሪነት መነሳትና ብ/ጀነራል ፋራህ አይዲድ መተካት

በዚህ ጊዜ እኔ አሥመራ ስለነበርኩ የአገር ደህንነት ሚኒስትራችን ጓድ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ሁኔታውን በስልክ ስለአስረዳኝ ኮለኔል አብዱላሂ ከሐረር ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ለፍርድ እንዲቀርብ አዘዝኩ።

ከአሥመራ እንደተመለስኩ ጀነራል ፋራህ አይደዲ ከሕንድ አገር እንዲመጣ አድርገን ወደተፈለገበት ተግባር ከመሰማራቱ በፊት ግንቦት 20 ቀን 1976 ዓ.ም በጽሕፈት ቤቴ ተቀብየ በሰፊው አነጋገርኩት። ጀነራል ፋራህ እንደ አብዛኛው የሱማሌ ህዝብ ጠይም መካከለኛ ከብደትና ቁመት ያለው እድሜው ከ45 እስከ 50 ዓመት የሚገመት ራሰ በራና ሽበት የጀመረው ሰው ነው።

ለመሪነት በመረጡት እድምተኞቹ እንደተነገረኝ በእርግጥም ጨዋ አስተዋይና ለተመረጠበት ኃላፊነት የሚመጥን በሳል መኮንን ሆኖ ነው ያገኘሁት።

አገሩ ሱማሌ ያለችበትን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ አብጠልጥሎ አስረዳኝ። ሱማሌን ከገጠሟት ውስብስብ ችግሮች ለማውጣት በእሱ በኩል መፍትሄ ናቸው የሚላቸውን ሃሳቦቹን እንዲገልዕልኝ ጠየቅሁት።

«ችግሮቻችን ረጅም እድሜ ያላቸውና ውስብስቦች ብቻ ሳይሆኑ በዓይነትና በመጠንም ብዙዎች ስለሆኑ ለሁሉም በአጭር ጊዜ መፍትሄ ይገኝላቸዋል የሚል እምነት የለኝም። ቢሆንም መፍትሄ መሻቱን ግን መጀመር አለብን። እድሜ ለኢትዮጵያ ህዝብ አብዮትና ለመሪው ለመንግሥቱ መፍትሄው ተጀምሯል።

በቅድሚያ ዚያድ ባሬ የሚያራምደውን ጠባብ ኋላ ቀርና ጨቋኝ የጎሳ ፖለቲካ ሥርዓት ማስወገድና በመላው ሱማሌ ህዝብ ፍላጎትና ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ ዲሞክራሲያዊ አመራር መፍጠር ያስፈልጋል።

ይህ እጅግ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ቢፈጠር የሱማሌን ህዝብ ባለብዙ ፈርጅ ውስብስብ ችግሮች ተራ በተራ ደረጃ በደረጃ ለማስወገድ የሚያስፈልገንና ሌላው ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ሰላም ነው።

ሰላም በሌለበት አገር ልማትና እድገት የለም። ሰላም በሱማሌ ህዝብ መካከል፣ ሰላም በአፍሪካ ቀንድ፣ ሰላም በተለይም በትልቋ ጎረቤታችን በኢትዮጵያ ህዝብና በሱማሌ ህዝብ መካከል ሊቀመንበር እኔ ታላቋ ሱማሊ እያሉ የሚቃዡ ሱማሊዎችን ሃሳብ ተጋሪ አይደለሁም። ታላቋን ሱማሌ እንፈጥራለን በሚል ቅዠት ዚያድ ባሬ

ከግብረ አበሮቹ ጋር ጦርነት ሲደግስ በድፍረት ከተቃወሙት ጥቂት ሱማሌዎች አንዱ ነኝ።

ኢትዮጵያ በሱማሌ ላይ ትስፋፋለች፣ ሐበሻ የተፈጥሮ ጠላትህ ነው፣ ሐበሻ ይበላሀል ወዘተ እየተባለ የሱማሌ ህዝብ በሚጋተው ፕሮፖጋንዳ ብዙዎቻችን ስናዝን ኖርን።

ዛሬ በማንም ሳይሆን በኢትዮጵያ አብዮታዊያን አርቆ አስተዋይነት የዚያድ ባሬና የግብረ አበሮቹ ፕሮፖጋንዳ እንዲህ እርቃኑን በመቅረቱ ደግሞ ግምቴና እምነቴ ትክክል በመሆኑ እኮራለሁ።

የሁለቱን አገሮች ወንድማማች ህዝቦች ሲያጋጭና ሲያጋድል የኖረው ሰው ሰራሽ (Artifical) የድንበር ችግር በዚሁ በተያያዝነው የትግል ሂደት ውስጥ ዘላቂ መፍትሄ አግኝቶ ሁለቱ ሕዝቦች ኑሮአቸውን ለማሻሻል በሚያስችላቸው በልማትና ግንባታ ተግባርላይ ማትኮር መቻል አለባቸው የሚል ምኞት አለኝ» አለ።

አነጋገሩ ልባዊ ወይም ለማስመሰል መሆኑን የሚገልፀው ጊዜ ቢሆንም ለአፍሪካ ቀንድ ያለው የሰላም ምኞት ከእምነቴና ከምኞቴ ጋር የሚገጥም ነው።

የሱማሌ መድህን ዲሞክራሲያዊ ግንባር የሚሰጥህ ኃላፊነት የተቃና እንዲሆን ከልብ ስለምመኝ ከጎንህ መቆሜን በማረጋገጥ እለይሃለሁ። መልካም ትግል ብዬ አሰናበትኩት።

የሱማሌ መድህን ዲሞክራሲያዊ ግንባር በ1977 ዓ.ም መባቻ ላይ በገላዲን ከተማ ውስጥ ባደረገው ሦስተኛው ጠቅላላ ጉባዔ ካከናወናቸው አበይት ተግባሮች ትልቁና ዋናው በኮለኔል አብዱላሂ ዩሱፍ ምትክ ብ/ጀነራል ፋራህ አይዲድን የግንባሩ መሪ አድርጎ መሾሙ ነበር።

ጀነራል ፋራህ የሱማሌ መድህን ዲሞክራሲያዊ ግንባር መሪ ከሆነ በኂላ በድርጅቱ ውስጥ የነበሩ ችግሮች በመወገዳቸውና ተዋጊው ኃይል የተሻለ አመራር በማግኘቱ ግንባሩ በጥሩ ሁኔታ መንቀሳቀስ ጀመረ።

ሦስቱም የሱማሌ መንግሥት ተቃዋሚ ድርጅቶች በየፊናቸውና በየክልላቸው የመንግሥቱን የመከላከያ ሠራዊት፣ የአገሪቱን የፀጥታ አስከባሪ ኃይሎችና አስተዳዳሪዎች አባረው መንግሥታዊውን የአስተዳደር ተቋማት በማፍረስና ሰፋፊ መሬቶችን በመቆጣጠር መንግሥትን ተክተው ማስተዳደር ጀመሩ።

በፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ጥያቄና በደቡብ የመን ፕሬዝዳንት አስተናጋጅነት እኔና ፕሬዝዳንት ዚያድ በ1977 ዓ. ም በሕዳር ወር ላይ ለእርቅና ሰላም ውይይት ኤደን ከተማ ላይ ተገናኘን። በውይይቱ ላይ ሌላ ሰው ሳይቀላቀል ከአንድ አስተርጓሚያችን

ጋር እኔና እሱ ብቻ ነበርን። የሁለታችንም አስተርጓሚ የጂጂጋ ክልል ተወላጅ በጡረታ ላይ ይገኙ የነበሩና ጥሩ ሱማሊኛ የሚናገሩ ኢትዮጵያዊ መኮንን ኮሎኔል ኃብተ ሚካኤል ይባላሉ።

እኝህ መኮንን ከአስተርጓሚነት ሌላ ሦስቱንም የሱማሌ መንግሥት ተቃዋሚ ድርጅቶች ተቀብሎ በማስተናገድ፣ በማስተዳደርና በማደራጀት ብሎም በማሰማራት ተግባር ይረዱን ከነበሩ ሰዎች አንዱና በዚህ ረገድ ለአገራቸው ባለውለታ ናቸው።

ከፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ጋር በደቡብ የመን ቤተመንግሥት አንዲት ክፍል ውስጥ ተገናኝተን ከተጨባበጥንና ሰላምታ ከተለዋወጥን በኂላ ውይይቱ የተጀመረው በእሱ ቀዳሚነት ነበር።

ለውይይታችን መግቢያ ወይም መንደርደሪያ ያደረገው ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሃፊ በኩርት ቫልደሃይም አማካይነት የተለዋወጥናቸውን ነገሮችና ኬኒያ ናይሮቢ ላይ የጠየቅሁትን እርቀ ሠላም ተቀብለህልና ከዚህ ወዴት? በሚለው በእሱ ጥያቄ ነው ውይይቱ የተጀመረው።

በውይይታችን ሂደት የሱማሌው መሪ ያቀረበው መሠረታዊ ጉዳይ አዲስ ሳይሆን በኩርት ቫልዳሃይም አማካይነት ያቀረበውን ጥያቄ በመድገም ለሁለቱ አገሮችና ሕዝቦች ወደ እርቅ ጉዞና ብሎም ለመልካም ጉርብትና ከቅኝ ገዥዎች የተረከብነውን ድንበር ቋሚና ሕጋዊ አድርጌ እቀበል ዘንድ በጦር ኃይል የያዝከውን ድንበር ልቀቅልኝ የሚል ነው።

ይህንን ጥያቄ በገፅ ተገናኝተን ለኔ ሲያቀርብ ለመጀመሪያ ጊዜ ቢሆንም በኩርት ቫልደሂም አማካኝነት ከቅኝ ገዥዎች የተረከብነውን ድንበር መቀበልህን ምስጢር ሳታደርገው ለተባበሩትመንግሥታት ማህበር ጽህፈት ቤትና ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት በጽሁፍ በማስታወቅ ይፋ አድርገው ብዬ የሰጠሁትን መልስ እንደ አልሰማና በኩርት ቫልደሃይም እንዳልተነገረው አድርጎ ነው የጠየቀኝ።

ሰውየው ሊያግባባኝና የሱን ፍላጎት እንድፈፅም ቢሞክርም የኔ መልስ ቀደምብዬ ከሰጠሁት የተለየ ሊሆን ስላልቻለ ልንግባባ አልቻልንም።

የእሱን ሁኔታና አቀራረብ እንደገመትኩት ከኔ ጋር ለመተዋወቅና ማንነቴን ለመፈተን እንጂ በዚያ የመጀመሪያ ግንኙነት የጠየቀው ይፈፀምልኛል ብሎ ያሰበ አይመስለኝም።

ሆኖም አንባቢ እንደሚያስታውሰው መጠነ ሰፊ ሜካናይዝድ የሱማሌ ሠራዊት ሲወረን በኦጋዴን ክልል በተለያዩ የስራ መስኮች ተሰማርተው ይተዳደሩ የነበሩና የሱማሊኛ ቋንቋ ተናጋሪ ያልሆኑ የመሀል ኢትዮጵያ ተወላጆችን ከየቤታቸው በኃይል

አስገድዶ የወሰዳቸው ዜጎቻችን ከአስር ዓመት በላይ በግዞትና በባርነት በመሰቃየት ላይ ናቸው።

ስለሆነም ሁለተኛ ለመገናኘት በሚያስችልና እሱን ተስፋ በማያስቆርጥ ሁኔታ እንዲፈጠር ስለፈለግሁ ትዕግሥትና እውነት የእርቅ ፍላጎት በሁለታችንም ዘንድ ካለ ይህንን ቀርቶ ከዚህም በላቁ ሌሎች ጉዳዮች ሁሉ ልንስማማ እንችላለን በሚል ቃል በሩን ገርበብ ካደረግሁ በኋላ ወደ እርቀ ሠላም የሚወስደን ቀዳሚ ቁልፍ ነገር ወይም የበጎ ፈቃድ ምልክት በጦርነቱ ጊዜ ተማርከውና በተለያዩ ሁኔታዎች ተግዘው በየአገሮቻችን የሚገኙ ዜጎቻችን ነፃነታቸውን ሰጥተን ወደየአገራቸው እንዲመለሱ ማድረግ ነው ብዬ አስባለሁ።

በአንተ በኩል ይህንን ለማድረግ ዝግጁ ነህ? ብዬ ላቀረብኩለት ጥያቄ ዝግጁ መሆን ብቻ ሳይሆን በሀሳብህም እስማማለሁ ስለአለ በቅርቡ እዚያው የመን ወይም ሌላ ቦታ ተገናኝተን ይህንንና ሌላውንም የሚያስፈፅምልን አንድ የጋራ የሚኒስትሮች ኮሚቴ ለማቋቋም ተስማምተን ተለያየን።

እንደ አጋጣሚ ሆኖ ከአንድ ወር በኋላ በታህሳስ ወር 1977 ዓ.ም የምስራቅ አፍሪካ ማለትም የኬኒያ፣ የሱዳን፣ የዩጋንዳ፣ የሱማሌ፣ የጅቡቲና የኢትዮጵያ መሪዎች በአገሮቻቸው መካከል የጋራ ልማትና የክልላቸውን የአየር ንብረት ደህንነት ጥበቃ ሕብረት ሲያቋቁሙ የማህበሩን ጽሕፈት ቤት ጅቡቲ እንዲሆን በተስማማንበት መሰረት ጅቡቲ ላይ ስለምንሰበሰብ ከፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ጋር ዳግም ለመገናኘት ተቃጠርን።

የጅቡቲው ግንኙነታችንና ውይይቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮቻችንን የጨመረ ሲሆን በዚህ ጊዜ የጋራ አስተርጓሚያችን ፊታውራሪ ደምሴ ተፈራ ነበሩ።

ፊታውራሪ ደምሴ ተፈራ የሐረርጌ ክልል ተወላጅና በክፍለ ሃገሩ ውስጥ ለረጅም ጊዜ በተለያዩ የሥራ ደረጃዎች ከመስራት ሌላ የሱማሌ ጉዳይና እንዲሁም የሱማሊኛ ቋንቋ ጠበብት ወይም (Expert) የምንላቸውና በፖለቲካም በሳል አገር ወዳድ አዛውንት ናቸው።

በረጅም ጊዜ ሁለገብ የስራ ልምዳቸው በቀልጣፋና ቅን አስተዳዳሪነታቸውና በፖለቲካ ብስለታቸው አብዮታችን እንደፈነዳ ልጅ እንዳልካቸው አቶ አክሊሉን ተክተው የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው በንጉሡ በተሾሙ ጊዜ በሚኒስትር ዴኤታ ማዕረግ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ሹም ወይም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ እንዲሆኑ የተመረጡ ሰው ናቸው።

ልጅ እንዳልካቸው ከተሻሩም በኋላ ከጠቅላይ ሚኒስትር ሚካኤል እምሩና ከጀነራል አማን ሚካኤል አንዶም ጋር በተፈላጊነታቸው ሰርተዋል።

በትግላችን ቅፅ አንድ ላይ የገለፅኩትን አንባቢ እንደሚያስታውሰው ከጀነራል አማን አደገኛ ሴራ አገራቸውንና አብዮታቸውን አድነዋል። የሱማሌ መንግሥት ባለሥልጣኖች ስለሚያውቋቸው አንጀት ጉበታችንን የሚያውቅ ጠንቀኛ ሐበሻ በማለት ይጠሏቸዋል።

በጅቡቲ የተሰበሰብንበት ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ ሌሎች የስብሰባው ተካፋይ መሪዎች ወደ የአገራቸው ሲመለሱ ሱማሌዎችና እኛ ብቻ ቀርተን በጅቡቲ ከተማ የተዋበ የስብሰባ አዳራሽ አካል በሆነች አንዲት ክፍል ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ከፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ጋር ተገናኘን።

በዚህ ጊዜ ውይይቱን የጀመርኩት እኔ ነበርኩ። ኤደን ላይ ሁለታችን ብቻ ስንወያይ ሁለቱ አገሮቻችን በመሀከላቸው መተማመንን ሊገነባ የሚችል እርምጃ መውሰድ አለብን ብለን ከተስማማንበት ማለትም ስለ ምርኮኖች ልውውጥ ተወያይተን ለተግባራዊነቱም ማስፈፀሚያ ዘዴ (Mechanism) እንዲፈጠር የሚል ሃሳብ አቀረብኩ።

በዚህ ጊዜ ውስጥ ሦስቱም የሱማሌ መንግሥት ተቃዋሚ ድርጅት ተዋጊ ኃይሎች በመላው ሱማሌ ማለት ይቻላል ብርቱ ጥቃት እያደረሱ ስለነበር የሱማሌ መንግሥት በታሪኩ ገጥሞት የማያውቀው አደገኛ ውጥረት ላይ ነበር።

የውጥረቱ ነፀብራቅ ከፕሬዝዳንቱ ጀምሮ አብረውን በነበሩት ሱማሌዎች ፊት ላይ ይነበብ ነበር። በኔ አቀራረብ ፕሬዝዳንት ዚያድ መበሳጨቱም በገሃድ ይታይ ነበር።

ፍርጥምና ቅጭም ብሎ «ምርኮኛ የመለዋወጡን ጉዳይ ኤደን ላይ ተስማምተናል። አፈፃፀሙም ብዙ ውይይት የማይጠይቅ በጣም ቀላል ነገር ስለሆነ ዛሬ የውይይታችን ቀዳሚና ዋና አጀንዳ መሆን አይገባውም።

ምርኮኞችን የመለዋወጡ ተግባራዊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ዛሬ ልንወያይባቸው ከሚገቡ መሰረታዊ ጉዳዩች የመጀመሪያው አገራችንን የያዘው የጦር ኃይላችሁ በአስቸኳይ ስለሚወጣበት ሲሆን፣

ሁለተኛው፣ ዛሬ በሐበሻ ወታደር ሳይሆን ከሱማሌ በቀጠራችኋቸው ምንደኞቻችሁ አገራችንን መውረራችሁ የማይደበቅ የአደባባይ ምስጢር ስለሆነ ምንደኞቻችሁ የሽብር ተግባራቸውን አቁመውና ትጥቃቸውን ተገፈው ወደ አገራቸው ስለሚመለሱበት ሁኔታ መሆን አለበት» አለ።

ከአነጋገሩ መረዳት እንደሚቻለው፣ ኤደን ላይ በተገናኘንበት ጊዜ ድንበሩን ልቀቅልኝና ድንበሩን ልወቅ ከሚለው ጥያቄው ሌላ አንድ ደረጃ ተራምዶ ድንበሩን የማውቀው የሚወጉኝን ተቃዋሚዎች ትጥቅ አስፈትታችሁ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ስታደርጉ ነው የሚል ጥያቄ መጨመሩን ነው።

በእኛም በኩል በኤደኑ ውይይታችን ባየሁት አዝማሚያ በጅቡቲው ግንኙነታችን ይሄ ጥያቄ ሊነሳ እንደሚችል ገምተን ነበር።

የእርቀ ሠላሙን ግንኙነት ለመጀመር ምክንያት በሆነው በኩርት ቫልድሃይም አማካኝነት ያቀረብከው ጥያቄ ቅኝ ገዥዎች ያስረከቡንን ድንበር በማወቅ ህጋዊ ወሰን አድርጌ እንድቀበል ጦርህን ከድንበሩ ላይ አንሳልኝ የሚል ነበር።

በበኩሌ ያቀረብከውን ጥያቄ በመቀበል ጦሬን ለማንሳት ተስማምቼ እስከአሁን ተግባራዊ ያልሆነበት ምክንያት በአንተ በኩል ድንበሩን ማወቅህን ለተባበሩት መንግሥታት ማህበር ጽሕፈት ቤትና ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት በጽሑፍ ለማሳወቅ ባለመፈለግህ ብቻ ነው።

በዛሬው ግንኙነታችንግን በአንተ በኩል ድንበሩን እንድታውቅ በኛ በኩል የእናንተን ተቃዋሚ ድርጅቶች ትጥቅ አስፈትተን ወደ አገራቸው እንድንመልስ ሌላ ጥያቄ ማቅረብህ ኤደን ላይ የተስማማንበትን ውል መሻር መሆኑን የሚገልፅ ነው አልኩ።

«ሁለተኛው ጥያቄ የኔን የመጀመሪያውን አቋሜን የሚሽር ወይንም የሚለውጥ አይደለም። የኔን መንግሥት ከመቃወም ባሻገር አገሬን ለመገነጣጠል የሱማሌን ህዝብ ደም በሚያፈሱ ቅጥረኞች ተክተህ የኢትዮጵያን ወታደሮች ብታወጣ ለኔ ምንም ትርጉም የለውም።

በሁለቱ አገሮቻችን ህዝቦች መካከል እውነተኛና ዘላቂ ሠላም የሚፈለግ ከሆነ ቅጥረኞችህንም ማስወጣት አለብህ» አለ።

ይህ ውይይት ፍሬ አፍርቶ በሁለቱ አገሮቻችን መካከል እርቅና ብሎም ዘላቂ ሠላም እንዲፈጠር ባለን ዕኑ ፍላጎት ምክንያት ሳናነሳ የተውነውን የቅጥረኞች ጉዳይ በእናንተ ብሶ ካነሳችሁት ላለፉት ሃያ ዓመታት የኢትዮጵያን አንድነት ለማፍረስና የኢትዮጵያዊያንን ደም ለማፍሰስ ከኢትዮጵያ መልምላችሁ፣ አሰልጥናችሁና አስታጥቃችሁ ያስማራችሁብንን ቅጥረኞች በሙሉ ትጥቃቸውን ገፋችሁ እጃቸውን አስረክቡን ማለት ያለብን እኛ ነበርን።

ለመሆኑ ይህንን ጥያቄ ብናቀርብላችሁ ተግባራዊ የሆነ መልስ ልትሰጡን ትችላላችሁ? የሚል ጥያቄ አቀረብኩ። ጥያቄዬ በሐሰት ፈጠራ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን እውነተኛና እነሱም ለመካድ የማይቻላቸው ነገር ስለሆነ መልስ ጠፋና እርስ በእርሳቸው መነጋገር ያስፈለጋቸው ይመስላል ውይይቱ ቆሞ እረፍት እንድናደርግ እነሱ ጠይቀው እረፍት ሆነ።

ከተሰበሰብንበት ክፍል ከወጣን በኋላ ሁላችንም አንዳችን ከሌላው ፈንጠር ብለን በመሰባሰብ እርስ በእርሳችን መወያየት ጀመርን።

የሱማሌው ልዑካን በሙሉ ከፕሬዝዳንታቸው ዙሪያ ተሰብስበው ሲወያዩ የተስማሙ አይመስልም። የጥል ያህል በኃላ ድምፅ ሲጨቃጨቁ ይሰማል።

በእኛ በኩል የውይይቱ አካሄድና በመጨረሻም የደረስንበትን ሁኔታ ስንገመግም መፍትሔ አልባ ወደሆነ የከረረ ሁኔታ እያመራን መሆናችንን በመገንዘባችን እንደተለመደው የውይይቱን በር ሳንዘጋና ሳንከፍትም ገርበብ አድርገን በመቅረብ ቢያንስ በዚያ መድረክ ላይ የምርኮኞችን ልውውጥ በተመለከተ የተስማማንበትን ጉዳይ በተግባር የሙተርጎም ስምምነት ላይ ለመድረስና ስለተቀሩት ጉዳዮች በሌላ ጊዜ ልንመለስባቸው የሚያስችል ቀጠሮ ለማድረግ ያስችላል ብለን አንድ አስማሚ ሃሳብ ለማቅረብ ወሰንን።

ውሳኔውም በኛ በኩል የቅጥረኞችን ትጥቅ አስፈትታችሁ እጃቸውን ስጡን ማለቱን ሳንገፋበት በእነሱ በኩል ለቀረበው ጥያቄ ግን ፕሬዝዳንት ዚያድ እንደ አለው ትጥቅን አስፈትተን በማስገደድ ወደ ሱማሌ መንዳት ሳይሆን የሱማሌ መንግሥት ከተቃዋሚዎቹ ጋር ተገናኝቶ በመወያየት ችግሩን በሰላም ይፈታ ዘንድ ልንረዳ ዝግጁ መሆናችንን መግለፅ ነበር።

ከእረፍት ተመልሰን በመሰብሰቢያ ክፍላችን ውስጥ እንደተገናኘን በፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ በኩል ኢትዮጵያዊያን በጦር ኃይል አገራችንን ይዛችሁና በተጨማሪ ቅጥረኞች አሰልጥናችሁ በማስማራት የሱማሌን መንግሥትና ሕዝብ እየወጋችሁ ሰላምና መልካም ጉርብትና መፍጠር ይቻላል በተሰኘ ተስፋ ለውይይት መቅረባችንን ተገቢውን ግምት አልሰጣችሁትም የሚል ክስ አቀረበ።

ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ባቀረበ ውክስ ከራሱ ባልደረቦች ጋር በጋራ የመከረበት ጉዳይ ስለአልነበረ የሱማሌ ልዑካን በአጠቃላይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በተለይ የሚስማሙ አይመስልም። ከሁኔታው መመልከት እንደተቻለው ውጥረት ይታይባቸዋል።

በኔ በኩል በሁለቱ አገሮቻችን መካከል የቆየውን ችግር የፈጠረና ብሎም ወደ አውዳሚ ጦርነት የወሰደን የሱማሌ መንግሥት የመስፋፋት ፍላጎት መሆኑን ከገለፅኩ በኋላ ለመስፋፋት ስትሉም ቅጥረኞችን በማሰማራት ብቻ ሳትቆጠቡ በጦር ኃይል የወረራችሁን እናንተ ናችሁ።

በወረራው ለደረሰብን ጉዳትና ጥፋት ካሳ ሳንጠይቃችሁ ወይንም በመልሶ ማጠቃት ሳንበቀላችሁ ባለፈው የፈፀማችሁትን ጥፋት ለታሪክ ትተን ወደፊት እንራመድ ብለን ለእርቅና ሠላም የቀረብን እኛ እንጂ እናንተ አይደላችሁም።

ለእርቅና ለሠላም በምናደርገው ውይይት እኛ ያቀረብንላችሁ ጥያቄ እጅግ ቀላል የሆነ አንድ ነገር ብቻ ነው። ይሄውም እናንተ ራሳችሁ ከቅኝ ገዥዎች የተረከብነውን

ድንበር ለመቀበል ዝግጁ ነን ስለአላችሁ መቀበላችሁን የተባበሩት መንግሥታት ማህበር ጽህፈት ቤትና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲያውቁት ይፋ አድርጉት የሚል ነው።

እኛ ለዘላቂ ሠላምና ለመልካም ጉርብትና ቆመናል። መንግሥታችሁን የሚቃወሙት ኃይሎች እናንተ እንደ ምትሉት እኛ የጠራናቸው ወይንም የቀጠርናቸው ሳይሆኑ በጦርነቱ የተሸነፍነው እናንተ ሠራዊቱን በትክክል ባትመሩትና ለመዋጋት ባለመፈለጋችሁ ነው ተብለው በጅምላ ከመታሰርና ብሎም ከመረሸን ሸሽተው የመጡ የሱማሌ መንግሥት የጦር መኮንኖች ሲሆኑ ወታደሮቹና የተቀሩትም ሰላማዊ ፖለቲከኞች በእኛ ሳይሆን በመኮንኖች ጥሪና በራሳቸው አነሳሽነት የመጡ ናቸው።

መንግሥታችን በእነኝህ ሰዎች ላይ ሥልጣንና ቁጥጥር የለውም። ወንድሞቻችን ስለሆኑ ሞትን ሸሽተው በመምጣታቸው ተቀብለን ወንድማዊ መስተንግዶ ማድረጋችንን አንክድም። የእነኝህን ሰዎች እጅ መስጠት ማለት በፍፁም አግባብነት ያለው ሃሳብና መፍትሄም ካለመሆኑ በላይ ልናደርገውም አንችልም።

በመሀከላችሁ ማንም ባእድ ጣልቃ ሳይገባ ከተቃዋሚዎቹ ድርጅቶች ከእያንዳንዱ ጋር በግል ወይንም ከሁሉም ጋር በወል ተገናኝታችሁ ችግራችሁን በሰላማዊ መንገድ ትፈቱ ዘንድ ለመርዳት ዝግጁ ነን ብዬ ስናገር ከፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ጀምሮ የሁሉም ሱማሌዎች ውጥረት ሲረግብና የፊታቸው ፀዳል ሲለወጥ ይታያል።

ከኔ ንግግር በኋላ አሁንም እረፍት ጠይቀው ሁላችንም ለረፍት ወጣን። አሁንም ሱማሌዎች በፕሬዝዳንታቸው ዙሪያ ተኮልኩለው ከተመካከሩ በኋላ ወደ ስብሰባው ክፍል ሁላችንም ተመለስን። እኛ ላቀረብነው ሠላማዊ የመፍትሄ ሀሳብ መልስ የሚጠበቀው ከእነሱ ነው።

ስለሆነም በዚህ ጊዜ ውይይቱን የጀመረው ፕሬዝዳንት ዚያድ ሳይሆን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ነበር። ፈገግ ባለ ገፅታ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ «ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ያቀረቡትን ሃሳብ መሰረት በማድረግ በዚህ መድረክ ላይ በተነሱት መሰረታዊ ጉዳዮች ማለትም ስለ ምርኮኞች መለዋወጥ የሁለቱን አገሮች ድንበር በተመለከተ የኢትዮጵያ ጦር የሱማሌን ምድር ለቆ ስለሚወጣበትና በመጨረሻም ዛሬ አገራቸውንና መንግሥታቸውን በመውጋት ላይ ስለአሉት ድርጅቶች ደረጃ በደረጃ መፍትሄ ስለሚገኝበት ሁኔታ እያጠናና እየመከረ ለመሪዎቹ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ ከሁለቱ አገሮች የውጭ ጉዳይ፣ የደህንነትና የአገር መከላከያ ሚኒስትሮችን ያቃመረ ኮሚቴ ሰይመን ስራውን እንድንሰራ በመወሰን በዚህ መድረክ ስለአተኮርንባቸው ጉዳዮች፣ ስለደረስንባቸው ስምምነቶችና ወደፊትም ደረጃ በደረጃ ስለምናከናውናቸው ተግባሮች የጋራ መግለጫ እናዘጋጅ ዘንድ የሁለታችሁን መሪዎቻችንን ፈቃድ እጠይቃለሁ ብሎ ያቀረበውን ሃሳብ ቤቱ በጭብጨባ ተቀበለው።

ለጊዜው እዚያ የተገኙት የሁለቱ አገሮች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮችና ረዳቶቻቸው መሪዎች ከተስማማንበት የምርኮኞች መለዋወጥ በተጨማሪ የተዘጉት የኤምባሲ ጽሕፈት ቤቶች እንደገና ስለሚከፈቱበትና ብሎም አምባሳደሮች ከምርኮኞች ልውውጥ ቀድመው በፍጥነት ስለሚላኩበት በጋራ አሰናድተው ያቀረቡት የጋራ መግለጫ በውይይቱ የተነሱትን የሁለቱን አገሮች ያለፉ አሳዛኝ ገጠመኞች ወደኋላ ለታሪክ ትተው ወደፊት እየተራመዱ ችግሮቻቸውን በማስወገድ በመልካም ጉርብትና በመተሳሰብና በሰላም አብሮ ለመኖር ሁለቱ መሪዎች መስማማታቸውን የሚገልፅ የጋራ መግለጫ ነበር ያዘጋጁት።

በዚህ ሁኔታ የሰላሙ ውይይት አብቅቶና ተሰነባብተን ወደየአገራችን ስንመለስ ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ በአገሩ ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰና አሳሳቢ እየሆነ የመጣውን የፖለቲካ ችግር በዚህም ምክንያት የተፈጠረውንው ጥረት ያረግብልናል በሚል ግምት ይመስላል በጅቡቲ ያደረግነውን ውይይት፣ የደረስንባቸውን ስምምነቶችና በመጨረሻም በጋራ ያወጣነውን መግለጫ ከዚህ እንደሚከተለው ለፕሮፖጋንዳ ጥቅም አዋሉት።

እንባቢ እንደሚያስታውሰው በኬኒያ ናይሮቢ የእንግዶች ማረፊያ አዳራሽ ውስጥ ጀነራል ዚያድ ባሬ እኔን አቅፎ በመቆም የተነሳነውን ፎቶ ግራፎች በከፍተኛ መጠን አሰርተው በህዝባዊ ሰልፍ ላይ በጎላ ሁኔታና በብዛት በማሳየትና ጅቡቲ ላይ ያወጣነውን የጋራ መግለጫ በማስተጋባት ከኢትዮጵያ ጋር እርቅና ሰላም ተመሰረተ በሚል የራሳቸውን መግለጫ አሰራጩ።

ይህንንም የሚያደርጉት በመደበኛው የብዙሃን ማሰራጫዎች ማለትም በራዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በጋዜጦች አማካኝነት ብቻ ሳይሆን ከጅቡቲ ከተማ በየብስ ተሽከርካሪዎች በመጓጓዝ የአገሪቱ ሁለተኛ ከተማ ከሆነው ከሐርጌሳ ጀምረው ለቀናት እየዋሉና እያደሩ በመንገዳቸው ላይ በየክፍለ ሀገሩ እስከ ርዕሰ ከተማቸው እስከ ሞቃዲሾ ድረስ ህዝብ በተሰበሰበበት በድምፅ ማጉያ በመለፈፍ ነበር።

በዚህ ብቻ አላበቃም በአገሪቱ የብዙሃን ማሰራጫዎች የጋራ መግለጫውን ማጋነን ብቻ ሳይሆን የእነሱንም ፈጠራ እየጨመሩ «ከኢትዮጵያ ምድር እየተንደረደራችሁ አገራችሁን የምትወጉ ምንደኞች ወዮላችሁ ከእንግዲህ ወዲያ አበቃላችሁ እየተባለ» ነበር።

ይህንን ፕሮፖጋንዳ ካዳመጡትና ካስተዋሉት የህብረተሰቡ ልዩ ልዩ ክፍሎች መካከል የመንግሥት ደጋፊ የሆኑት ታላቅ የድል ብስራት አድርገው ሲቀበሉት የመንግሥቱ ተቃዋሚዎችና በኢትዮጵያ ውስጥ በተደራጁት ኃይሎች ሰፈር ሽብር ተፈጠረ።

በኛ በኩል የሱማሌ ልዑካን እንደዚያ ያለ የውሸትና የፈጠራ ተግባር ያከናውናል ብለን ባናስብም ለፕሮፖጋንዳ ጥቅም እንደሚያውሉት ግን እናውቅ ስለነበር ከጅቡቲ እንደተመለስን ድሬዳዋ በመሄድ እያንዳንዱን የሱማሌ መንግሥት ተቃዋሚ ድርጅት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እየጠራን በፈረቃ እኔና ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ እንዴት መገናኘት እንደቻልን ከአንድም ሁለት ጊዜ ተገናኝተን ስለተወያየንባቸው ጉዳዩችና ጅቡቲ ላይ በጦርነቱ ጊዜ ተማርከውና በተለያዩ ምክንያቶች ተግዘው በኢትዮጵያና በሱማሌ የሚገኙት ዜጎቻችን ነፃነታቸውን አግኝተው ወደየአገሮቻቸው እንዲመለሱ ማድረግ ፖለቲካዊ ብቻ ሳይሆን በአመዛኙ ጎኑ ሰብአዊ በመሆኑ ከመስማማታችን በስተቀር የሱማሌ ሚዲያ እንደሚያሰራጨው ፕሮፖጋንዳ የተስማማንበት አንዳችም ነገር እንደሌለ በሐቅና በዝርዝር ከማስረዳት ባሻገር ይህንኑ የኔን ንግግር እንደ ኦፊሲሊያዊ መግለጫ አድርገው በየራሳቸው የራዲዮ ሰዓቶች ለሱማሌ ህዝብ ያስረዱ ዘንድ መመሪያ በመስጠት ማረጋጋት ነበረብኝ።

በጅቡቲው ስምምነት መሰረት ከሁለቱ አገሮች የተወጣጡና በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች የሚመሩ የፖለቲካ፣ የመከላከያና ደህንነት ጉዳይ ባለሞያዎች ኮሚቴ ተቋቁሞ ባቀረበው ሃሳብና ባዘጋጀው የአፈፃፀም ፕሮግራም በ1977 ዓ.ም ጥር ወር የምርኮኞች ልውውጥ አደረግን።

የምርኮኞች ልውውጡን በኛ በኩል ከውይይቱ የተገኘ ፍሬ ወይንም መልካም ውጤት አድርገን በመውሰድ የመንግሥታችን አመራር ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ በጣም የተደሰተበት ጉዳይ ነበር።

ምክንያቱም በሺህዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን በአሰቃቂ ግዞትና ባርነት እጅግ የተሰቃዩበት ብቻ ሳይሆን ብዙዎች ሕይወታቸውንም ያጡበት ስለነበረ ነው።

ለስሙ የምርኮኞች ልውውጥ ይባል እንጂ እኛ ለሰባት ወራት ወረራውን ተከላካይ ስለነበርን የማረክነው ጠላት አልነበረም ማለት ይቻላል።

በመልሶ ማጥቃት ጊዜ ሰው ቀርቶ አንድ መሳሪያ ወደ ሱማሌ እንዳይመለስ ማድረግ ያስችለን ዘንድ ታቅዶ የነበረው የከበባና የአፈና ውጊያ እቅዳችን ተግባራዊ ሳይሆን ወራሪው ሠራዊት ሸሽቶ ወደ ሱማሌ ስለተመለሰ የተማ ረኩት 1785 ብቻ ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ አብዛኛዎቹ መሸሽ የተሳናቸው ቁስለኞች ነበሩ።

በሱማሌ በኩል በጦርነቱ ከኢትዮጵያ ተማረኩ የሚሏቸውና እኛ ቁጥራቸውን በውል የማናውቀው ከዓለም ቀይ መስቀል ግምታዊ መረጃ ያገኘነው አህዝ ከሁለት ሺህ በላይ ሲሆን ሁሉም ከጦርነቱ በፊት በኦጋዴን ክልል በልዩ ልዩ የስራ መስክ ተሰማርተው ይኖሩ የነበሩ ሰላማዊ ዜጎቻችን እንጂ ለውጊያ የተሰማሩ የጦር ሰዎች ወይም ወታደሮች አልነበሩም።

እኛ ዘንድ የነበሩ 1785 ምርኮኞች ወደ ሞቃዲሾ የተወሰዱትና ሞቃዲሾ የነበሩት ከሁለት ሺህ በላይየሆኑ ኢትዮጵያዊያን ግዞተኞች ወደ ድሬደዋ ከተማ የተጓጓዙት በኢትዮጵያ አየር መንገድ በኢትዮጵያ መንግሥት ወጪ ነው እኛ ዘንድ የነበሩት ምርኮኞች ያልተራቡ፣ ያልተራቆቱና በጠቅላላው ሳይጎሳቆሉ በደህና ጤንነት ላይ ይገኙ የነበሩ ከመሆናቸው ባሻገር ሲመለሱ አስፈላጊው የጤና ምርመራ ተደርጎላቸውና ታክመው በአዲስ አልባሳት የተዋቡ ነበሩ።

ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት የሱማሌ መንግሥት ምርኮኞች የሚላቸውን ኢትዮጵያዊያን ከጦር ሜዳ የተማረኩ ወታደሮች ሳይሆኑ ከየቤታቸው እየተጎተቱ በኃይል ወደ ሱማሌ የተጋዙ ሰላማዊ ሰዎች በመሆናቸው የሱማሌ መንግሥት እንደደንቡ ስማቸውንና ቁጥራቸውን ለማሳወቅ ፈቃደኛ ስለአልነበረ አገራቸው እስኪገቡ ድረስ ቁጥራቸውን በውል ለማወቅ አልተቻለም።

በመቶዎች የሚቆጠሩ በጤና መታወክ፣ በምግብ እጥረትና ከአቅማቸው በላይ የሆነ የጉልበት ሥራ በግዴታ በመስራት ተጎድተው መሞታቸውን ያወቅነው ወደአገራቸው ከተመለሱ በኂላ ከእነሱው አንደበት ነው። ወደ አገራቸው ለመመለስ ከበቁትም መካከል አብዛኛዎቹ በፅኑ የታመሙ በሽተኞች፣ በምግብ እጥረት እጅግ የተበሳቆሉ ደካሞችና ሴቶቹም ሆኑ ወንዶቹ እጅግ በጣም የወሰከና የተበጣጠሰ ጨርቅ እንደ ሱማሌዎቹ የአለባበስ ባህል አገልድመው ከወገባቸው በላይ እርቃናቸውን ነበሩ።

ብዙዎቹ በአካል የተጎዱ ብቻ ሳይሆን የአእምሮ መታወክም ችግር የነበረባቸው ስለነበሩ ከፊሎቹን በድሬደዋ ከተማ አቅራቢያ ባለውና ሁርሶ በመባል በሚታወቀው ሰፊና ዘመናዊ ማሰልጠኛ የጦር ሰፈር ውስጥ አሳርፈን ልብስ በማልበስ ገንቢ ምግብ በመመገብና የጤና እንክብካቤ በማድረግ እንዲያገግሙ ስናደርግ በባሰ ሁኔታላይ የነበሩትን ሕሙማን ሐረርና ድሬዳዋ ከተሞች ውስጥ ባሉ ሆስፒታሎች ሁሉ በማስተኛት ማሳከምና ማስታመም ነበረብን። ከጠቅላላው ተመላሽ መካከል ምርኮኛ ማለት የሚቻለው አንዱን የኩባ መንግሥት ዜጋና የኩባ መከላከያ ሠራዊት አባል የሆነ ወጣትና መኮንን፣ አንድ የኢትዮጵያ አየር ኃይል አባልና የሕብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጀግና የሆነ አብራሪ መኮንን ብቻ ነበሩ። ከሐረር ከተማ ራሱን ኦሮሞ እስላማዊ ብሎ በሚጠራ የሱማሌ መንግሥት ምንደኛ ወንበዴ ታፍነው ወደ ሱማሌ የተወሰዱትን የሶቪየት ህብረት ዜጋ የሆኑ አራት ሐኪሞች እኛ በማናውቀው ሁኔታ ብዙ ቀደም ብለው ወደአገራቸው መመለሳቸው የተነገረን በምርኮ ልውውጡ ጊዜ በሱማሌዎቹ ነው።

ክፍል አሥራ ሦስት

ምዕራፍ ዘጠኝ

የፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ መንግሥት ውድቀት አገዛማሚያና መቃረቢያ

የሱማሌ መንግሥት የአመራር አካላት የጅቡቲን የሠላም ውይይትና ያወጣነውን የጋራ መግለጫ ከማጋነን ባሻገር ይዘቱንም በመለወጥ የራሳቸውን ፈጠራ ጨምረው ለፕሮፖጋንዳ መጠቀሚያ ማድረጋቸው ከሰጣቸው ጥቅም ያስከተለው ጉዳት በጣም የላቀ ሆነ::

ሦስቱም የትጥቅ ትግል በማካሄድ ላይ ያሉት የመንግሥቱ ተቃዋሚ ድርጅቶች በሱማሌ መንግሥት የሐሰት ፕሮፖጋንዳ እንዳይሸበሩ በኔ በኩል እውነቱን በማስረዳት ለማረጋጋት ቢሞክርም በሁለቱ አገሮች አመራር መካከል በተፈጠረው ግንኙነትና የሠላም ውይይት መጀመሩ፣ ምርኮኞችን መለዋወጡና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታችንን እንደገና ማደሱ ያልጠበቁት ታላቅ ስጋት ነው የፈጠረባቸው::

ሦስቱም ድርጅቶች ለመጀመሪያ ጊዜ ስብሰባ አድርገው በኢትዮጵያና በሱማሌ መንግሥታት አመራር መካከል በተፈጠረው ግንኙነት፣ የሠላም ውይይትና የጋራ መግለጫ፣ የጋራ ጠላታችን የሚሉት የፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ መንግሥት የተጠቀመበት ፕሮፖጋንዳ በእነሱና ደጋፊያቸው በሆነው የሱማሊያ ህዝብ ላይ የፈጠረውን ውዥንብር በጋራ ገመገሙ::

ዚያድ ባሬ በደረሰበት የፖለቲካ ውጥረት ተገዶ የማይፈለገውን ከኢትዮጵያ ጋር ሠላም ቢፈልግም በሱማሌ ውስጥ ሠላም አግኝቶ የአገዛዝ ዘመኑን እንዳያራዝም ኃይላቸውን አስተባብረውና የውጊያ ሥልታቸውን አቀነባብረው እስከዚያ ጊዜ ድረስ ካደረጓቸው ጥረቶች በላቀና በተፋጠነ ሁኔታ በህብረት በመውጋት ህልውናውን ለማሳጠር ተስማሙ::

ሦስቱም ድርጅቶች በህብረትና በተመሳሳይ ጊዜ በየፊናቸውና በየክልላቸው ያለማቋረጥ በተከታታይ የሰነዘሩት መጠነሰፊ ጥቃት የመንግሥቱን መከላከያ ሠራዊት ሦስት ላይ ክፍሎ ስራ ስለአበዛበትና በሦስቱም ግንባር በብቃትና በፅናት መከላከል ስለተሳነው ከደቡብና ከሰሜን ግንባር በርካታ ጦር በመቀነስ የአገሪቱ ርዕሰ ከተማና የአመራር ማዕከል የሆነውን የሞቃዲሾን ከተማ ለመከላከል ቅድሚያ ወይም የበለጠ ትኩረት በመስጠቱ በደቡብና በሰሜን የሚከላከሉትን የጦር ክፍሎች ማሳሳት ያልተጠበቀ ውጥረትና ታላቅ ስጋት ፈጠረ::

በዚህ ጊዜ ነበር ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ወደ ደቡብ የመን በመሄድ ለፕሬዝዳንቱ «እስከዛሬ ለሱማሌና ለኢትዮጵያ ህዝቦች የሰላም ጠንቅ ሆኖ የቆየውን ችግር ለአንዴና

ለመጨረሻ ጊዜ የሚያስወግድ መፍትሔ ስለአለኝ ከሊ.ቀ መንበር መንግሥቱ ጋር በአስቸኳይ መገናኘት እፈልጋለሁ» ሲል የጠየቀው።

የየመኑ ፕሬዝዳንት የተነገረውን ነገር ለማመን የተሳነው ቢሆንም ፕሬዝዳንት ዚያድ እጅግ ከፍተኛ ችግርና ጭንቀት ላይ እንዳለ በመገንዘብ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ለኔ የቃል መልዕክት እንዲያደርስ ወደ አዲስ አበባ ላከው

የተላከልኝ የቃል መልዕክት ይዘት ከዚህ እንደሚከተለው ነበር። "ወንድማችን ዚያድ ባሬ አንድ ለማመን የሚያስቸር ነገር ነግሮኝ ከአንተ ጋር በአስቸኳይ እንዳገናኘው ጠይቆኛል።

የነገረኝን ነገር እንድትሰማው የምፈልገው ከኔ ሳይሆን ከሱ ከራሱ አንደበት ነው። መልስህ በአስቸኳይ ይድረሰኝ" የሚል መልዕክት ነበር በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አማካኝነት የተነገረኝ።

የሱማሌዎች ሁሉ ልማድ ወይንም ፀባይ ነው ለማለት ባልደፍርም አብዛኛው ፖለቲከኞቻቸው መዋሸት፣ ማስመሰል፣ ማታለል (dispation) ብልህነት ወይንም የፖለቲካ ጥበብ ነው ብለው የሚያምኑ ይመስለኛል።

ማፈርና ይሉኝታ ብሎ ነገር በእነሱ ዘንድ አይታወቅም። የሚያስገርም ድፍረትና ሀሰትን የመፍጠር ስጦታ አላቸው ማለት ይቻላል።

በትግላችን ቅፅ አንድ ላይ የገለፅኩትን አንባቢ እንደሚያስታውሰው፣ የፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬን መልዕክት ይዤ የመጣሁ መልዕክተኛ ነኝ በማለት ከሁለት ቀን በላይ ያነጋገርኩት ዶክተር አደም ያሲን ያደረገውን ያጤኗል።

የፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬን ጥያቄ በፓርቲያችን ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽህፈት ቤትና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውስጥ ለጉዳዩ አግባብ ያላቸውን ጓዶች ጠርቼ የሱማሌዎች መሪ በአስቸኳይ እንድንገናኝ ያቀረበውን ጥያቄ፣ የየመኑ መሪ የሰማውን ነገር ለማመን የሚያስቸግር ነው። እንድትሰማው የምፈልገው ከኔ ሳይሆን ከሱ ከራሱ አንደበትነው ያለበት ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል ወዘተ በሚል ጥያቄ ተወያየን።

የውይይቱ ይዘት ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ምን አዲስ ሃሳብ ሊያቀርብ አስቦ ይሆን? ይህንን ወይም ያንን ቢል የኛ መልስ ምን መሆን አለበት? በጥያቄው መሰረት እንቀበለው ወይስ ችላ እንበለው? ልንቀበለው ከወሰንን ደግሞ የት? መቼና እንዴት እንቀበለው የሚል ነበር።

በዚህጊዜ በሱ ጥያቄ መሰረት እኔ ኤደን መሄድ ሳይኖርብኝ እሱን አዲስ አበባ ለመጥራት ወሰንን። መቼ ለሚለው ጥያቄ የኢትዮጵያን ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከመሰረተው ጉባዔ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1981 ዓ.ም መባቻ ላይ

ማለትም በጳጉሜ አንድ በሚጠራው ዓመታዊ ጉባዔ መሰብሰቢያ ጊዜ እንዲሆን ተስማማን::

ይህንን ለማድረግ የተፈለገበት አንደኛው ምክንያት እንደሚታወቀው ቅኝ ገዥዎች የተውልንን ወሰን እንድንቀበል ከፈለግህ በጦር ኃይል የያዝከውን ወሰን ልቀቅልኝ ብሎ ጥያቄ ካቀረበ በኂላ ውሳኔውን ይፋ እንዲያደርግ ቢጠየቅ ፈቃደኛ አልሆነም::

በእርግጥ ቅኝ ገዥዎች የተዉልንን ወሰን ለመቀበል ወስኖ እንደሆነ ለመፈተን ሸንጎው ስብሰባላይ እንዲገኝ ጋብዘን ንግግር እንዲያደርግ በማድረግ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ልናጋፍጠው በማሰብ ሲሆን፣

ሁለተኛው ምክንያት እኛ እንደ ሱማሌ መሪዎች የድብብቆሽ ጨዋታ የምንጫወት ሳይሆን ለእርቀ ሠላሙ ድርድርና ብሎም ለመልካም ጉርብትና ያለንን ፍላጎት ልባዊ መሆን ለሱማሌ ህዝብና እንዲሁም ለዓለም ለማሳወቅ ብለን ነበር በዚህ እቅድና ውሳኔ መሰረት አዲስ አበባ ላይ ተገናኝተን እንወያይ ዘንድ ሞቃዲሾ ባለው አምባሳደራችን አማካኝነት ጥሪ አቀረብንለት::

እንደሚታወቀው ይህ አጋጣሚ ከጅቡቲውም የተሻለ የፕሮፖጋንዳ ጠቀሜታ አለው ብሎ ስለአመነ መሆኑ አያጠያይቅም የተደረገለትን ጥሪ በደስታ እንደተቀበለና በተባለው ቀን አዲስ አበባ እንደሚገኝ ሞቃዲሾ ባለው አምባሳደራችን አማካኝነት አሳወቀን::

አዲስ አበባ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ በቀይ ሥጋጃ ምንጣፍና በክብር ዘብ ሰላምታ ተቀብለን በኢትዮጵያ ህዝብ ቤተመንግሥት አሳርፈን ለእሱና አብረውት ለነበሩ ልዑካን ተገቢውን መስተንግዶ አደረግን::

በማግሥቱ ጧት በሪፐብሊኩ ሸንጎ መድረክ ላይ በሰላምና በመልካም የጉርብትና ፍላጎት መርሆ ላይ የተመሰረተ ወንድማዊ ንግግር በማድረግ ለጉባዔው ከአስተዋወቅሁት በኂላ ከጉባዔው አባላት መካከል እኛ ያላዘጋጀናቸውና በተፈጠረው መልካም ነገር የተደሰቱ አንዳንድ ሰዎች በራሳቸው አነሳሽነት መድረክ እየጠየቁ ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬንና ጠቅላላው የሱማሌ ልዑካን መካከላችን መገኘት ምክንያት በማድረግ አጫጭር ገንቢ ንግግሮችን አደረጉ::

በታቀደው መሰረት እንግዳው የሱማሌ ፕሬዝዳንት የመልስ ንግግር ያደርግ እንደሆነ ቢጠየቅ ስለመጣሁበት ጉዳይ ከፕሬዝዳንት መንግሥቱ ጋር ከመነጋገሬ በፊት እዚህ ንግግር ለማድረግ አልተዘጋጀሁም በማለት ያለመናገሩ ሸንጎውንና የኢትዮጵያን ህዝብ ብቻ ሳይሆን ተመልካች የነበሩትን ዲፕሎማት ሁሉ ያስገረመ ነገር ሆነ::

እሱ በአዲስ አበባ ከተማና በዙሪያዋ አንዳንድ ጉብኝቶችን እያደረገ እኔ ጉባዔውን አስተናግጄ ካሰናበትሁ በኋላ ከአዲስ አበባ ከተማ 120 ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ በሚገኘው ትንሽ ግን የተዋበና ቤተ ሰልሆም በተሰኘ ስም በሚጠራው ቤተመንግሥት ውስጥ በኢትዮጵያ ባህል ሁለተኛና ጥሩ የራት ግብዣ አደረግንላቸው፡፡

ፕሬዝዳንቱን አጅበው የመጡት የሱማሌ መንግሥት ልዑካን በርካታ ሲሆኑ ከወንድ ልጆቹ አንዱና አማቹ የመከላከያ ሚኒስትሩ አብረውት ነበሩ፡፡

በበነጋታው ከቀትር በኋላ እኔና ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ከኢትዮጵያዊው ሱማሊኛ አስተርጓሚያችን ጋር ተገናኝተን እሱ የመጣበትን ጉዳይ ከመነጋገራችን በፊት ስለጥንት የኢትዮጵያ ትዝታው አንስቶ «በፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያ ተወራ በነበረችበት ጊዜ የኢጣሊያ ወታደር (ባንዳ) ሆኖ በሐረርጌ፣ በአርሲና በሸዋ የሰራ ከመሆኑ በላይ በጐንደር በጀነራል ናዚ ዕዝ ውስጥ እንደተዋጋና ከኢትዮጵያ ተባረው ሲወጡ የወጣው በምፅዋ ወደብ ስለነበረ ኤርትራን ስለማየቱ ካወጋኝ በኋላ ኢትዮጵያን የማውቃት ከአንተ መወለድ በፊት ነው» አለኝ፡፡

ሰምተኸው እንደሆነ አላውቅም በምስራቅ አፍሪካ ክልል የሚኖሩ ህዝቦች በሙሉ ማለት ይቻላል «ሱማሌዎች ሰዎቹም ሆኑ ግመሎቻቸው በአንድ አጋጣሚ የረገጡትን መሬት አገራችን ወይም አለኝታችን ነው ስለሚሉ ተጠንቀቁ» የሚል አባባል አላቸው፡፡

በዚህ መሰረት ድንበራችን እስከ ጐንደር ነው ባለማለትህ አመሰግንሃለሁ ብለው «እንዲህ ያለው ፈጠራ የማንም ሳይሆን የሐበሾች ብቻ ነው» ብሎኝ ተሳሳቅንና እሱ ወደ መጣበት ጉዳይ አመራን፡፡

በእሱ ቀደምትነት ውይይቱ ተጀመረና ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ለማስፈፀም ያቀደውን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ሲል እሱና አገሩ ስለአሉበት እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ እኔን ለማሳዘን፣ ለማሳመንና ቢችልም ለመጠምዘዝ በሚያስችለው ሁኔታ ስለ ሱማሌ ሲገልፅልኝ የሚጠቀምባቸው ቃላቶችና በአቀራረብ ስልቱ አንድ የፊልም ተዋናይ መስሎ ነው የታየኝ፡፡

በጣም እየተገረምኩ አንዳንዴም ለመሳቅ እየዳዳኝ ራሴን ተቆጣጥሬ በትዕግሥት ሳዳምጠው ከቆየሁ በኋላ «አሁን እዚህ መልስ እንድትሰጠኝ ሳይሆን ጊዜ ወስደህ አስብበትና ምናልባትም አስፈላጊ ቢመስልህ ከምታምናቸውና ምስጢር ከሚጠብቁ ጓዶችህ ጋር መክረህበት ለምትሰጠኝ መልስ የማቀርበው ሃሳብ ሁለቱን አገሮቻችንን በፌዴሬሽን ወይም በኮንፌደሬሽን እናንተ በፈለጋችሁት ዓይነት ለማስተሳሰር በበኩሌ ከጓዶቼ ጋር ለብዙ ጊዜ መክረንበት የተስማማንበት ብቻ ሳይሆን ፍፁም ያመንበት ሃሳብ ስለሆነ የእናንተን ሃሳብ ለመጠየቅ ነው የመጣሁት፡፡

እኛ የሁለቱ አገር መሪዎችና የአመራር አካላት ተወያይተን ውሳኔ ሃሳብ ላይ ከመድረሳችን በፊት እዚህ ከኔ ጋር አብረውኝ ላሉትም ይሁን ለማንም የሱማሌ ዜጋ ጆሮ እንዲገባ አልፈልግም » አለኝ።

በዚህ ጊዜ ይህንን ከማለት ሌላ ወትሮ እንደሚለውና እኔም እጠብቅ እንደነበረው የያዝከውን መሬት ልቀቅ፣ ያሰማራሃቸውን ሽብር ፈጣሪ ምንደኞች አስወጣ ወዘተ የሚል ጥያቄ አላቀረበም።

በኔ በኩል በአቀራረብ ስልቱ ምን ዓይነት አክተር ነው? ብዬ ከመገረሜ በላይ በመደነቅ ካቀረበው ሃሳብ ለመገንዘብ የቻልኩት የኢትዮጵያን ጦር ከሱማሌ ምድር ለማስወጣትና የሦስቱን ተቃዋሚ ድርጅቶች ትጥቅ አስፈትቶ አመፃቸውን በማኮላሸት ከገጠመኝ የሲቪል ጦርነትና የፖለቲካ ውጥረት ሊያወጣኝ ይችላል ብሎ በማሰብ ቅኝ ገዥዎች ያስረከቡንን ድንበር እቀበላለሁ ብሎ ያቀረበው መፍትሄ ስለአልሰራለት ወይም ፈጣን ውጤት ስለአላስገኘለት ሁለቱን አገሮች በፌደሬሽን ወይም በኮንፌደሬሽን ቋጠሮ አንድ አገር እናድርጋቸው ካለ ኢትዮጵያዊያን አምነውና ተደስተው ከገጠመኝ ችግር ሊያወጡኝ ፈቃደኞች ይሆናሉ በሚል ሃሳብ ላይ የተመሰረተ የስልት ለውጥ ማድረጉን ነው። ሌላ አንድ ምሽት እዚያው ቤተ ስሊሆም ከአሳለፍን በኋላ በበነጋታው ሁላችንም ወደ አዲስ አበባ ተመለስን።

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ህዝብ ቤተ መንግሥት ስንደርስ ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ቀኑን እረፍት በማድረግ ለማሳለፍ ሲጠይቅ የተቀሩት የልዑካኑ አባላት ደግሞ እረፍት ከሆነ ጫት ደግሱልን ብለው በመጠየቃቸው ተደግሶላቸው ሁሉም ያንን ቀን በቤተ መንግሥቱ ውስጥ እረፍት አድርገው ዋሉ።

የፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ አዲስ አበባ መገኘት እጅግ ያሳሰባቸውና ያስቆጣቸው ተቃዋሚዎች ሁሉም በአንድ ጊዜ የተቀነባበረ ከፍተኛ ማጥቃት ሰንዝረው የመንግሥቱ ሠራዊት ሊመክታቸው ስለአልቻለ በደቡብ ቀጣና ጀነራል ኡመር ጆሲ የሚመራው ጦር ወደ ኪሱማዩ ከተማ ተቃረበ።

በማዕከላዊው ሱማሌ ቀጣና የሚዋጋውና በጀነራል ፋራህ አይዲድ የሚመራው ጦር አሻባይዳዋ የተባለውን ከተማ ለመያዝ ተቃረበ።

ባይዳዋ የአውሮፕላን ማረፊያ፣ በርካታ ሠራዊትና ብዙ ህዝብ ያለበት ትልቅ ከተማ ከመሆኑ በላይ ለሞቃዲሾ ም በጣም ቅርብ ነው።

ምዕራፍ አስር

የታላቋ ሱማሌ ተስፈኞችና የዚያድ ባሬ መንግሥት ፍፃሜ

«የሱማሌ ህዝብ ብሄራዊ ንቅናቄ» በመባል የሚታወቀው ንቅናቄ ጦር ሐርጌሳ ያለውን የመንግሥቱን ሠራዊት ደምስሶ ከተማውን መቆጣጠሩን የሚገልፅ መልዕክት በዚያ ቀን ሌሊት ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ከሞቃዲሾ ስለደረሰው በመጡበት አውሮፕላን የመከላከያ ሚኒስትሩን መልሶ ወደ ሞቃዲሾ በላከበት ሌሊት አዲስ አበባ ሆነው የግንባሩን ዜና የሚያሰራጩት የሱማሌ ብሄራዊ ንቅናቄ ሰዎች በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ራዲዮ የሰማሌን መንግሥት የመከላከያ ሠራዊት ደምስሰው የሐርጌሳን ከተማ መቆጣጠራቸውን ለሱማሌ ህዝብ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ቋንቋዎች ለዓለም ሲያበስሩ በአዲስ አበባ በኢትዮጵያ ህዝብ ቤተመንግሥት በመስተናገድ ላይ ያሉትም እንግዶቻችን ይሰማሉ።

በዚያ ጊዜ ውስጥ ተቃዋሚዎች ይህንን ያደርጋሉ የሚል ግምት በእኛ በኩል ያልነበረ ብቻ ሳይሆን የሰነዘሩትም ጥቃት ከኛ የተሰወረ ነበር።

ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ይህንን ጥቃት አዘጋጅተን እንደጠራነው ማመኑ የሚያጠያይቅ ስለአልነበረ ተደናግጠናል። ኤደን ላይ እንድንገናኝ ያቀረብነውን ጥያቄ ባለመቀበል አዲስ አበባ የጠሩን ለውይይት ሳይሆን ለኛ ውድቀት ደግሰውልን ነው ማለታቸው ግልፅ ስለነበር በኔ በኩል በበነጋታው ፕሬዝዳንቱን ማየትና ማነጋገር አስቸጋሪ ቢሆንም እንግዳዬና የአንድ ጎረቤት አገር መሪ ስለሆነ ምርጫ የለኝምና ጧት ስገናኛቸው ምንም ነገር እንደ አልተፈጠረ ሁሉ «በሰሜን ሱማሌ ያንተ ቅጥረኞች ትንሽ ችግር ፈጥረው ስለነበር ሌሊት ጀነራል ሞርጋንን ልኬው ሁሉንም ነገር በቁጥጥር ስር አድርጓል። አውሮፕላኑ ተመልሶ ስለመጣልን እኔም አሁን ወደ ሞቃዲሾ ለመመለስ ወስኛለሁ»አለኝ።

ይህንን ከማለት ሌላ አስፀህበትና ከጓዶችህ ጋር መክረኽበት መልስ ትሰጠኛለህ ስለአለው ጉዳይና ከዚያ በኋላ የት መቼ? እንደምንገናኝ ያነሳው ነገር አልነበረም። ያ ግንኙነታችንም የመጨረሻ ነበር።

በእርግጥም ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ እንዳለው ጀነራል ሞርጋን ከሞቃዲሾ የአገሪቱን ስትራቴጂካዊ ተጠባባቂ ጦር (Reserve) አነቃንቆ ወደ ሰሜን በመውሰድ በመልሶ ማጥቃት ውጊያ ከሐርጌሳ ከተማ ተቃዋሚውን ኃይል በማስወጣት መልሶ ለመቆጣጠር ችሎ ነበር።

የመንግሥቱ ስትራቴጂካዊ ተጠባባቂ ወይም ብሄራዊ ደጀን ጦር ከሞቃዲሾ መራቁን የተመለከተው የሱማሌ መድህን ዲሞክራሲያዊ ግንባር የመንግሥቱን ጦር አስለቅቆ አይሻ ባይዳዋን መቆጣጠር ቻለ። ባይዳዋ በኢትዮጵያና በሞቃዲሾ ከተማ

መካከል ያለ በትግላችን ቅፅ አንድ እንደተገለፀው በጦርነቱ ጊዜ የወራሪው ሠራዊት ደቡባዊ እዝ ማዕከል የነበረ ትልቅ ከተማ ነው።

የቀድሞው የብሪታኒያ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ቅኝ የነበረው የሰሜን ሱማሌ ርዕሰ ከተማ ሐርጌሳ ከደቡብ ወይም ከአገሪቱ ርዕሰ ከተማ ከሞቃዲሾ ከሺህ ኪሎ ሜትር በላይ የራቀ ሲሆን ባይዳዋ ከመቃዲሾ የሚርቀው ወደ ሁለት መቶ ኪሎ ሜትር ያህል ብቻ ነው።

በጀነራል ፋራህ አይዲድ የሚመራው የሱማሌ መድህን ዲሞክራሲያዊ ግንባር ሠራዊት ከባይዳዋ ተወርውሮ የሞቃዲሾን ከተማ እንዳይዝ የሰጋው ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ የሐርጌሳን ከተማ ይከላከል የነበረው ሠራዊት ለጊዜው የሐርጌሳን ከተማ መከላከሉን ትቶ የአገሪቱን ርዕሰ ከተማ ሞቃዲሾን ይከላከል ዘንድ በአስቸኳይ እንዲመለስ የመከላከያ ሚኒስትሩን አዘዘው።

ጀነራል ሞርጋን በሁለት ቀን ውስጥ ሠራዊቱ በሐርጌሳ ከተማ ውስጥ አሉ የተባሉትን ዘመናዊ ሕንፃዎች ማለትም የመንግሥትና የግል ድርጅቶች፣ መስሪያ ቤቶችና ትምህርት ቤቶችን፣ ሆስፒታሎችንና የተለያዩ የጤና አገልግሎት መስጫዎችን፣ የህዝቡን መኖሪያ ቤቶች ወዘተ በፈንጂ እንዲያፈርስ፣ የስልክና የኤሌክትሪክ ገመዶችን እንዲበጥስ፣ የሐርጌሳ የሲቪል አቪየሽን ጠቅላላ ተቋም እንዲሁ ከማፈራረስ በላይ የአውሮፕላን ሜዳዋን በትራክተር እንዲያርስ የከተማውን ዘመናዊ የውሃ ማደያ ቧንቧዎች ከመነቃቀል ባሻገር ህዝቡ የሚጠቀምባቸውን አያሌ የውሃ ጉድጓዶች በስሜንቶ እንዲደፍን በማድረግ በወታደራዊ ሥልት ወደ ሞቃዲሾ ሊያፈገፍግ ሲሞክር ተቃዋሚው ጎሬላ ሠራዊት መንገድ ላይ አድፍጦ በመጠበቅ፣ በከበባና በቆረጣ ውጊያ ስልት ባደረሰበት ወከባና ጥቃት የዘረፏቸውን የተለያዩ ቁሳቁሶችና ተሽከርካሪዎች ብቻ ሳይሆን የሚዋጉበትን ከባድ መሳሪያ ጭምር ጥለው በተዝረከረከ ሁኔታ ስለሸሹ የሐርጌሳ ከተማ እንደገና በተቃዋሚው ኃይል እጅ ስለገባች የሱማሌ ህዝብ ብሄራዊ ንቅናቄ (SN M) የሱማሌን ሰሜናዊ ክልል ህዝብ ከዚያድ ባሬ የጭቆና አገዛዝ ነፃ ማውጣቱን ለሱማሌና ለመላው የዓለም ህዝብ ከአዲስ አበባ በኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የዜና ማሰራጫ ራዲዮ አበሰረ። እኔ ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬን ከሸኘሁ በኋላ ለስራ ጉዳይ የተወሰኑ ሚኒስትሮችንና የፓርቲያችንን ማዕከላዊ ኮሚቴ የልዩ ልዩ መምሪያና የዘርፍ ሃላፊዎች ይዤ ወደ ወለጋ አስተዳደር ሄጄ ነበር።

የሱማሌ ብሔራዊ ንቅናቄ መሪ የተወሰኑ የንቅናቄውን ከፍተኛ የአመራር አካላት አባላት ይዞ ወለጋ ክልል አስተዳደር ርዕሰ ከተማ ለቀምት በመምጣት « ሰሜን ሱማሌን ከዚያድ ባሬ የጭቆና አገዛዝ ነፃ አውጥተናል ከተማውን ሐርጌሳን ከተቆጣጠርንበት ጊዜ ጀምሮ ነፃዋን አገራችንን ሱማሌ ላንድ ወይንም የሱማሌ ምድር የተሰኘ ስም ሰጥተናታል በማለት ድልና ደስታውን አበሰረልን።

እንኳን ደስ ያላችሁ በማለት በሻይና በቡና ግብዣ ከተቀበልናቸው በኋላ በአንድ ክፍል ቤት ውስጥ እነሱና ጥቂት ኢትዮጵያዊያን ሆነን ስለውጊያውና ከውጊያ በኋላ የሰሜኑ ክልል በጠቅላላ ከተማው ሐርጌሳ በተለይ በምን ሁኔታ እንደአሉ ገለፃ አድርገውልን ለምሳና በተቀረውም ጊዜ እረፍት እንዲያደርጉ ወደ ሆቴላቸው አሰናበትናቸው::

በበነጋታው ከእንግዲህ ከዚህ ወዴት በሚል ርእስ ላይ ስንወያይ ቀደም ብለው እዚያው ሐርጌሳ ያዘጋጁትንና ከኛ የሚፈልጉትን የእርዳታ ዝርዝር አቀረቡ::

«እስከዛሬ በእናንተ ያልተቆጠበ እርዳታ የዚያድ ባሬን አስተዳደርና የመከላከያ ሠራዊት ተቋም ለማፈራረስ ነበር ስንታገል የነበረው::

እድሜ ለኢትዮጵያ ትግሉን በማያዳግም ድል ተወጥተነዋል ዛሬ አገርና ህዝብ እንዲሁም ሠራዊት መምራትና ማስተዳደርን የመሰለ ሃላፊነት ነው የተረከብነው::

የሰሜን ሱማሌን ህዝብ በጠቅላላ፣ የሐርጌሳ ከተማ ነዋሪ ህዝብ በተለይ ጀነራል ሞርጋንና ሠራዊቱ በቁም ቀብረውት ነው የሄዱት» በማለት ቀደም ብዬ የዘረዘርኳቸውን ጥፋቶች አስረዱን::

መሪው መሐመድ ኢጋል «የሚያሳዝነው ዛሬም እናንተን ማስቸገራችንና ከእናንተ ትከሻ ለመውረድ ያለመቻላችን ነው::

ከፀሀይ የምንከለልበት፣ ከዝናብ የምንጠለልበት አንድ ቤት እንኳ በሐርጌሳ ከተማ የለም:: አገሩን በሙሉ ፈንጂ ዘርተውበት ስለሄዱ ህዝቡም እንስሳውም በየእለቱ በፈንጂ አደጋ እየሞቱ ነው:: የዚያድ ባሬን አገዛዝ ታግሎ የጣለው ህዝብ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ላይ ስለወደቀ ዛሬም የእናንተን የተለመደ ድጋፍ ለመጠየቅ ተገድደናል» በማለት ከዚህ የሚከተለውን የጥያቄያቸውን ዝርዝር አቀረበልኝ::

1ኛ. ፈንጂዎችን ከተቀበሩበት የሚያወጣልን ወታደራዊ መሃንዲስ ቡድን፣

2ኛ. በሲሚንቶ የተደፈኑትን የህዝቡን የውሃ ጉድጓዶች ማፅዳት በጣም አዳጋችና ጊዜም የሚፈጅ መስሎ ስለ ታየን ዘመናዊዎቹን የውሃ ማደያ መስመሮች የሚያድስልንና ለህዝቡ አዲስ የውሃ ጉድጓዶች የሚቆፍርልን የውሃ ልማት ባለሞያዎች ቡድን ከነመሳሪያው፣

3ኛ. የኤሌክትሪክና የስልክ መስመሮችን የሚጠግንልን የቴክኒሺያን ቡድን፣

4ኛ. ጥቂት የመንግሥት መስሪያ ቤቶችን፣ ባንኮችን፣ መኖሪያ ቤቶችን፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎት መስጫ ዎችን፣ ከሲቪል አቪዬሽኑ ድርጅትና

ከአውሮፕላን ማረፊያው ሜዳ ጋር መልሶ የሚጠግንልን የኮንስትራክሽን ባለ ሙያዎች ቡድን ከነመሳሪያው፣

5ኛ. ከእንግዲህ ወዲያ አገር የምንመራ መንግሥት ሆነን ግን ገንዘብ የለንም። የሞቃዲሾን መንግሥት ገንዘብ ህዝባችን ለማየት የማይፈልግ ከመሆኑ ሌላ ህጋዊ ያልሆነ የሱማሌ ብር በውጭ አገር እየታተመ በብዛት አገር ውስጥ በመግባቱ ዛሬ የሱማሌ ገንዘብ ፋይዳ ቢስ በመሆኑ የሚቀበለው የለም።

የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገራችን ይሰራ ዘንድ ባንኩን በኢትዮጵያ ገንዘብና በኢትዮጵያ ባለሙያዎች መልሶ የሚያቋቁምልን ቡድን፣

6ኛ. ሠራዊታችን ከሰላማዊው ህዝብ መካከል የወጣ የደፈጣ ተዋጊ ሠራዊት ስለሆነ ወደ መደበኛ የመከላከያ ሠራዊት የሚለውጥልንና የፖሊስ ሠራዊት የሚያደራጅልን አንድ የመለዮ ለባሽ ቡድን እንዲሰጡን እንለምናለን የሚል ነበር ጥያቄያቸው።

በመጨረሻም የሶቪየት ህብረት መንግሥት በርበራ ላይ የገነባው ዘመናዊ ወደብ፣ የአውሮፕላን ማረፊያ፣ የነዳጅ ማከማቻ ዴፖ ወዘተ ከዛሬ ጀምሮ ኢትዮጵያ እንድትጠቀምበትና ክብርነትዎ እንዲያዙበት እኛ የአመራር አካላት ብቻ ሳንሆን ሕዝባችንም ለኢትዮጵያ ስጡ ሲል ከአዘዘን በኂላ ከእንግዲህ ወዲያ ከደቡቦች ጋር እንቀላቀል ማለት ቀርቶ ፊታችንንም ወደ ደቡብ ማዞር አንፈልግም። ካስፈለገ ከኢትዮጵያ ጋር መኖርን እንመርጣለን ብሎናል በማለት ገለፃውን ጨረሰ። ያቀረቡት ጥያቄ የበዛ ቢመስልም እነሱ ካሉበት ወቅታዊ ሁኔታ አንፃር ስንመለከተው አግባብና የሚያስፈልጋቸው ስለሆነ በእኛ በኩል የመረዳት ፍላጎት ብቻ ሳይሆን የጠየቁንን ለማድረግ አቅሙና ልምዱም ነበረን።

የተጠየቅነውን የተለያዩ የባለሞያ ቡድኖች በሚኒስትሮች ምክር ቤት የባህል፣ የማህበራዊና የሰራተኞች ጉዳይ ዘርፍ ሃላፊና ም/ጠቅላይ ምኒስትር በነበረው በጓድ ሽመልስ አዱኛ በሚመራ አንድ አጠቃላይ ግብረ ኃይል ስር አደራጅተን ለመላክ አቅደን ሳለ «ኤስ.ኤን.ኤም» የሐርጌሳን ከተማ አጥቅቶ በያዘበት ጊዜ መላው የከተማውና የአካባቢው ነዋሪ ህዝብ ማለት ይቻላል ከፍተኛና ሁለገብ ድጋፉን ከመስጠት ባሻገር የታጠቀው ወገን በውጊያውም ተካፋይ ስለነበር የመንግሥቱ ሠራዊት ከደቡብ በተላከለት አጠናካሪ ጦር ተረድቶ በመልሶ ማጥቃት የከተማውን ህዝብ በበቀል ያለ ርህራሄ በገፍ ፈጀው።

በብዙ ሺህ የሚቆጠር ህዝብ ህይወቱን ለማዳን ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ተሰዶ በአሰቃቂ ችግር ላይ ወድቆ ስለነበር ቅድሚያ በመስጠት በተቻለ መጠንና ፍጥነት ለስደተኛው መጠለያ በመስራት፣ ውሃ ምግብና የጤና አገልግሎት ወዘተ ማቋቋምና ማቅረብ ስለነበረብን በነፍስ አድኑ ዘመቻ ላይ አትኩረን ብዙ ርህብተኞችን ብቻ ሳይሆን ቁስለኞችንም ለማትረፍ የሚቻለንን አደረግን።

ከዚህ በኋላ የፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ መንግሥት ሌላ ጦር ወደ ሰሜን ለመላክ አልፈለገም። ቢፈልግም በዚህ ጊዜ የሚልከው ጦር ስለአልነበረው እስከ መጨረሻው ጊዜ ድረስ ያተኮረው የጀነራል ፋራህ አይዲድና የጀነራል ኡመር ጀሲ ጦሮች የአገሪቱን ርዕሰ ከተማ ሞቃዲሾን እንዳይዙ መከላከሉ ላይ ብቻ ነበር።

የቀድሞው የእንግሊዝ ሱማሌ ላንድ ይባል የነበረው ክልል ሱማሌ ላንድ በተሰኘ ስም መንግሥቱን ሰይሞ ነፃነቱን በማወጅ ከደቡብ ሱማሌ መነጠሉን ካስታወቀ በኋላ ጀነራል ፋራህ አይዲድ በተለያዩ ጊዜያቶች አዲስ አበባና ድሬ ደዋ ከተማ እየመጣ ተገናኝተናል።

በተገናኘን ቁጥር ያስረዳኝ የነበረው ስጋቶቹ ሁለት ነበሩ። አንደኛው፣ መላው የሱማሌ መንግሥት የጦር ኃይል ብቻ ሳይሆን ዚያድ ባሬ የሚወለድበት የሐውያ ጎሳና ከሱ ጋር ያበሩ ሌሎች የጎሳ ማህበራት ታጣቂዎች ጭምር የሞቃዲሾን ከተማና አካባቢውን በርቀትና በብርቱ መሽገው የሚከላከሉ ከመሆናቸው በላይ የመንግሥቱ ሠራዊት በግንባሩ የደፈጣ ተዋጊ ሠራዊት ላይ ባለው ከፍተኛ የመሳሪያ የበላይነት ምክንያት ውጊያው በጣም እየጠጠረና እየከፋ ስለመሄዱ፣

ሁለተኛ ስጋቱ፣ የእሱ ፅኑ ፍላጎትና ዓላማ የሱማሌን ህዝብ ከዚያድ ባሬ አገዛዝ አላቆ የሁሉም የሆነ ብሄራዊና ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለማቋቋም ሆኖ ሳለ ሰሜኖቹ ተነጥለው የራሳቸውን ነፃነት ማወጃቸው ዚያድ ባሬ ካደረሰብን ውድቀት ወደ ባሰ አዘማሚያ የሚወስድ እንጂ ለሱማሌ ህዝብ የሚበጅ አይደለም የሚል ነበር።

በኔ በኩል ምንም እንኳን የታላቋ ሱማሌ ተስፈኞች በኢትዮጵያ ላይ ለመስፋፋት በጦር ኃይል ወረው ከፍ ያለ ጉዳት ቢያደርሱብንም ፍርድ እንደ እራስ ነው እንዲሉ እኛ ከሰሜን ገንጣዮች ጋር ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት እየተዋጋን የሱማሌን ህዝብ መከፋፈል ወይንም መገነጣጠል በመርህ ደረጃ የሚደገፍ ካለመሆኑ በላይ እሱም እንደተናገረው፣ መበታተን ወይንም መገነጣጠል ለአንድ አገር ህዝብ ነፃነት፣ የህልውና ጥንካሬና የእድገት ፀር ሆኖ የሚያዳክም የሚያስንቅና የሚያስደፍር እንጂ የሚበጅ ስለአይደል እኔም የስጋቱ ተጋሪ መሆኔን እገልፅለት ነበር።

በዚህ የመነጣጠል ችግር ምክንያት የዚያድ ባሬ አገዛዝ ያመጣው ችግር ብቻ ሳይሆን እናንተም ከዚያድ ባሬ መንግሥት በኋላ ስለሚሆነው በጋራ መክራችሁ ለአንድ ዓላማና ተግባር የተሰለፋችሁ ሳትሆኑ በመነጣጠል የተለያዩ ክልሎችንና የጎሳ ማህበራትን እንወክላለን በማለት በየፊናችሁ መደራጀታችሁ ያስከተለው መዘዝ ጭምር ይመስለኛል በማለትም አስተያየቴን በግልፅነት እነግረው ነበር።

ከዚህ ሌላ ምናልባትም የችግሩ ዋናምክንያት የሰሜኑ ህዝብ የንቅናቄውን መሪዎች ከደቡቦችጋር መቀላቀል ቀርቶ ፊታችንንም እንኳን ወደ ደቡብ አዙሩ እንዳትሉን እስከማለት የከፋ ጥላቻ ያሳደረባቸው ጀነራል ሞርጋን የፈፀመው ተግባር ይመስለኛል።

ዛሬ የሰሜኑ ህዝብ እጅግ የተጎዳ፣ ያዘነና በደቡብ ህዝብ ላይ ታላቅ ጥላቻ ያደረበት ስለሆነ እስኪረጋጋና እስኪረሳው በትዕግሥት መጠበቅና አንዱ ግንባር ወይም ንቅናቄ ከሌላው ጋር እስከ ዛሬ ያለውን መልካም ግንኙነትና የትግል አጋርነት ይበልጥ ማጠናከር ነው ለወሳኙ ድልና ብሎም ሱማሌን አንድ ለማድረግ የሚያስችላችሁ ስለው «እኛን ለዚህ በጎ ዓላማ ለማስተባበርና የሱማሌን ህዝብ አንድነት መልሶ ለመገንባት ይረዱናል ብየ ተስፋ ያደረግሁት እርሶን ነው» አለ፡፡

ከአዲስ አበባ በጣም ሩቅ በሆነው በደቡብ ሱማሌ የሚዋጋው ንቅናቄ ከመንግሥቱ ሠራዊት ጋር ያለፋታ የሚዋጋና አንዳንዴም የመንግሥቱ ጦር እያየለ ንቅናቄው ከኛ አብዮታዊ ሠራዊት ጋር ያለውን መገናኛና የእደላ መስመሩን ይቆርጡበት ስለነበርና እንደልብ መገናኘት አዳጋች በመሆኑ ከጀነራል ኡመር ጀሲ ጋር የተገናኘሁት ሦስት ጊዜ ብቻ ነበር፡፡

አንደኛው፣ የንቅናቄው መስራቾች የኢትዮጵያን ድጋፍ ለመጠየቅ በመጡበት የመጀመሪያው ጊዜ፣ ሁለተኛው ድርጅቱን ስናቋቁምና በመጨረሻም እኔ ራሴ የንቅናቄውን የበላይ አመራር አካላት ለመጎብኘት ነገሌ ቦረና በሄድኩበት ጊዜ ነበር፡፡

መንግሥታችንን፣ ፓርቲያችንንና እንዲሁም እኔን በመወከል ከደቡብ ንቅናቄ አመራር አካላት ጋር የሚገናኘውና በማናቸውም ረገድ ይረዳ የነበረው፣ የደርግ አባል የፓርቲያችን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና የደቡብ አብዮታዊ ጦር አዛዥ የነበረው ጓድ ጌታቸው ሺበሺ ነበር፡፡

ጀነራል ፋራህ አይዲድ «የመንግሥቱ ሠራዊት በርቀትና በፅናት እንዲሁም ባለው የመሳሪያ የበላይነት ስለሚከላከል ውጊያው በጣም ጠጥሮብናል» ብሎ ለነገረኝ ችግር ከባድ መሳሪያዎችን በመስጠት ከጀነራል ኡመር ጋር ግንባር ፈጥረው በህብረት እንዲዋጉ መክሬው ነበር፡፡

በ1980 ዓ.ም አጋማሽ አዲስ አበባ መጥቶ ተጨማሪ ገንዘብ፣ መሳሪያና ጥይቶች እንዲሁም ጠቅላላ የተለያዩ የሎጀስቲክ ጥያቄዎችን ባቀረበ ጊዜ ውጊያውን በተመለከተ ስለአለበት ሁኔታ ጠይቄው ከጀነራል ኡመር ጀሲ ጋር በሚያስደስት ሁኔታ ወታደራዊ ህብረት ፈጥረው እንደሚዋጉና በሞቃዲሾ ከተማ አቅራቢያ ከሚከላከሉት የመንግሥቱ ጦር አባላት መካከል በማይናቅ መጠን ከነትጥቃቸው እየመጡ ከግምባሩ ጋር የሚቀላቀሉት እንደ አጠናከሩት ገልፆልኛል፡፡

ግቡን የሱማሌን መንግሥት ርዕሰ ከተማ ሞቃዲሾን አድርጎ የሚዋጋው የሱማሌ ህዝብ መድህን ዲሞክራሲያዊ ግንባር (S.S.D.F) የሰሜኑ ንቅናቄ ሐርጌሳን ከያዘ በኋላ ሞቃዲሾን ለመያዝ አንድ ዓመት ፈጅቶበት የፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬን ተከላካይ ጦር ለመርታት የቻለው በ1981 ዓ.ም መገባደጃ በሰኔ ወር ላይ ነበር፡፡

ምዕራፍ አስራ አንድ

የሱማሌ መንግሥት ርዕሰ ከተማ ሞቃዲሾ በተቃዋሚ ድርጅቶች እጅ መውደቅ

ከፊሉ የግንባሩ ኮሚቴ አባላት በጀነራል ፋራህ እየተመሩ አዲስ አበባ መጥተው በፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ መንግሥትና የመከላከያ ሠራዊቱ ላይ የማያዳግም ድል መቀዳጀታቸውን ባበሰሩልን ጊዜ፣ ከአምስት ዓመት በላይ የታገላችሁበትን የሞቃዲሾን ከተማ ይዛችኋል ከእንግዲህ ወዲያ ከፋኖነት ወደ መንግሥት ደረጃ አድጋችኋል:: ከዚህ ደግሞ ወዴት? ብዬ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ መሪው ጀነራል ፋራህ የሰጠኝ መልስ ከዚህ እንደሚከተለው ነበር::

«ከሁሉ በፊት ለዚህ ድል ላበቃችን ኢትዮጵያና ለአመራሯ ምስጋና ለማቅረብ ቃላቶች ያጥሩኛል:: ውለታችሁ በእጅጉ ከብዶናል:: አላህ የኢትዮጵያን አብዮት ይጠብቅ ከማለት ሌላ ምን ማለት ይቻላል?» በማለት ምስጋና አቀረበ::

ንግግሩን በመቀጠል «የሞቃዲሾን ከተማ ከዚያድ ባሬ እጅ ፈልቅቀን በማውጣት እሱን ከነዘር ማንዘሩ ከሱማሌ ምድር ከአባረርን በኋላ ወደ ቤተመንግሥት አልገባንም::

የሱማሌን ህዝብ ከዚያድ ባሬ አገዛዝ ነፃ አውጥተንህል ከእንግዲህ ወዲያ የሚበጅህን መንግሥት ማቋቋምና የምትፈልገውን መሪ መምረጥ ያንተ ፋንታ ነው አልነው እንጂ ሥልጣን ይዘናል መሪዎችህ እኛ ነን አላልነውም::

ጠቅላላውን ጦራችንን ከሞቃዲሾ ከተማ አውጥተን ለፀጥታ ማስከበር ስንል በከተማው ጠርዝ ደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብና ደቡብ ምሥራቅ አስፍረን ዳሮር ለምንለው የሱማሌ ህዝብ የጎሳ ማህበራት ከፍተኛ መማክርት ተሰብስቦ አዲስ መንግሥት ያቋቁም ዘንድ አስቸኳይ ጥሪ አቅርበናል::

ያለዳሮር መማክርት ፈቃድና ውሳኔ ጦራችንን ወደ ከተማው አናስገባም:: ያለዳሮር መማክርት ውሳኔና ትዕዛዝ ምንም ዓይነት እርምጃ አንወስድም:: የአገራችንን የቆየ አኩሪ ባህል፣ የህዝባችንን ፍላጎትና ብያኔ ድምፅ የምናከብርና የምንታዘዝነን» አለኝ::

በሱማሌ ህዝብ ባህልና የቆየ ጥንታዊ የፖለቲካ ዘይቤ በሰሜኑ ክልል «አሮር» በተሰኘ ስም በደቡብ ክልል «ዳሮር» በተሰኘ ስም የሚጠሩ የየክልሉ አያሌ ጎሳዎች ማዕከል በእነሱ አጠራር የጎሳ ግንድ የሚሏቸው እንደአሉ የሰማሁ ቢሆንም ጀነራል ፋራህ በገለፀልኝ ዓይነት በሱማሌ ህዝብ ላይ ፍፁም የሆነ የፖለቲካ ሥልጣን ያላቸው የጎሳዎች መማክርት ስለመኖራቸው እኛ የምናውቀው ነገር አልነበረም::

የዳሮር መማክርቶች ተሰብስበው አዲስ መንግሥት እስኪያቋቁሙ ድረስ ለአገሪቱ ደህንነት ያላችኂት ኃይል እናንተ ብቻ ከመሆናችሁ ባሻገር የሽግግሩን ሰላማዊ ሂደት ማደናቀፍ የሚችሉ የዚያድ ባሬ ደጋፊ የሆኑ ጎሳዎች ከመኖራቸውም ሌላ የተበተኑትም የዚያድ ባሬ መንግሥት የመከላከያ ሠራዊት አባላት ጊዜ ካገኙና አመቺ ሁኔታ ከተፈጠረላቸው ሊሰባሰቡና ሊደራጁ ስለሚችሉ ጦራችሁ ከተማውን በአጠቃላይ የዜና ማሰራጫዎችን፣ ባንኮችን፣ የተለያዩ የኢኮኖሚና የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ወደቦችንና የአውሮፕላን ሜዳዎችን ወዘተ በጥብቅ መቆጣጠርና ለምታደርጉት ነገር ሁሉ ከፍ ያለ ጥንቃቄ፣ ፍጥነትና ወሳኝነት ያላችሁ መሆን ያለባችሁ ይመስለኛል በማለት ሃሳብ አቀረብኩ።

«ክቡር ፕሬዝዳንት! ያሉት ፍፁም ትክክል ነው። ሆኖም የዚህንም አስፈላጊነት የዳሮር ሽማግሌዎች ተገንዝበው እስኪፈቅዱልን ድረስ መጠበቅ እንገደዳለን።

ይህንን የምናደርግበት ምክንያት የሱማሌ ህዝብ መድህን ዲሞክራሲያዊ ግንባር ከዚያድ ባሬ ጋር የተዋጋው መንግሥት ለመገልበጥ ያለመሆኑን ለሱማሌ ህዝብ ከማስገንዘብ በላይ ዛሬ ሰሜኑና ደቡቡ ህዝባችን መከፋፈሉ እጅግ ሲያሳዝነን ደቡቡ ደግሞ እንዳይከፋፈል የምናደርገው ጥረት አካል መሆኑን ይገንዘቡልን» ስለአሉ ውይይቱ በዚሁ አብቅቶ የደስታቸው ተካፋይ መሆናችንን በሚገልፅ ሁኔታ አስተናግደን አሰናበትናቸው።

ጀነራል ፋራህና ሌሎቹም ጓዶቹ በአስረዱን መሰረት የዳሮር መማክርት ሽማግሌዎች የግንባሩ አመራር ባደረገላቸው ጥሪ መሰረት በሱማሌ ፓርላማ አዳራሽ ቢሰበሰቡም ሽማግሌዎቹ አንድ ወጥ ድርጅት ሆነው ለአንድ ዓላማና ተግባር የቆሙ ሳይሆኑ የተለያዩ የጎሳ ማህበራት አመራር አካላት ጥንቅር፣ በፖለቲካ አመለካከታቸው፣ በማህበራዊ ስፍራቸው፣ በሥልጣን ጥምና በተለያዩ ጥቅማጥቅሞችና በመደብ ጀርባቸው የተለያዩ ከመሆናቸው በላይ የፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ መንግሥት አገዛዝ ተጠቃሚዎችና ደጋፊዎች በተቃራኒ ተከፊዎችና ተቃዋሚዎች የነበሩበት ስብስብ ነበር።

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ልዩነቶችና ቅራኔዎች የተመረዙ ብቻ ሳይሆኑ ብዙዎች እጅግ የሸመገሉና በማህበራዊ ንቃታቸውም እጅግ ዝቅ ያሉ ስለነበሩ፣ መግባባት ቀርቶ መደማመጥ ተስኖአቸው የተጠሩበትን ክቡር ህዝባዊ አገልግሎት ለመስጠት የሚመጥኑ ባለመሆናቸው በጭቅጭቅና በቀውስ በባከነው ጊዜ የተጠቀመና የታጠቀ፣ የሱማሌ ህዝብ መድህን ግንባር ተቃዋሚ የሆነ አንጃ ግንባር ተፈጥሮ በከተማውና በአካባቢው ከፍ ያለ ፀረ ፋራህ አይዲድ ቅስቀሳና የትጥቅ ፕሮፖጋንዳ ስለጀመረ ሞቃዲሾ የውጊያ አውድማ ሆነች።

በጀነራል ፋራህ አይዲድ የሚመራውና ራሱን «የሱማሌ ህዝብ መድህን ዲሞክራሲያዊ ግንባር» ብሎ የሚጠራው ድርጅት የሱማሌ ህዝብ መድህን ሳይሆን

የሱማሌ ህዝብ አንድነት፣ ሠላምና እድገት ፀር ነው። ያደራጁት፣ ያስታጠቁትና ያሰማሩብን የኢትዮጵያ ኮሚኒስቶች ናቸው። ጀነራል ፋራህ አይዲድ በኢትዮጵያ የተገዛ መሳሪያ ነው።

በጀነራል አይዲድ መሳሪያነት የኢትዮጵያ ኮሚኒስቶች ሱማሊያ ተመልሳ በሶቪየት ህብረት መዳፍ ውስጥ እንድትገባ ከማድረጋቸው በፊት የምዕራቡ ዓለም በአጠቃላይ አሜሪካ በተለይ በአጣዳፊ ሊረዱን ይገባል" በማለት የአሜሪካንን ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት ጋብዘው በተጀመረው የሲቪል ጦርነት ጀነራል ፋራህ አይዲድና ብዙዎቹ የግንባሩ አመራር አካላት ከነሠራዊታቸው ለዓላማቸው በጀግንነት ተፋልመው ስለተሰዉ ሱማሌ እስከዛሬ መንግሥትና ሥርዓት አልባ አገር ሆናለች።

ጀነራል ፋራህ አይዲድ በሱማሌ ህዝብ ዘንድ በጣም የተወደደ መሪ ብቻ ይሆን የማከብረው ጀግና መኮንን ነበር። ታዲያ ምን ያደርጋል በመጨረሻ ጊዜ በታላቅ ተጋድሎና መስዋዕትነት የተቀዳጀውን ድል የብዙ ጀግኖችና የራሱንም ህይወት ለጠላቶቹ አሳልፎ በመስጠት የጅል ስራ ሰራ።

ክፍል አስራ አራት

ምዕራፍ አስራ ሁለት

ኤርትራ

ከሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጋር የተደረገውን የትጥቅ ትግል ከመተረኬ በፊት የሱማሌ ህዝብ ከጥንድ የአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች ማለትም፣ ከብሪታኒያ ኢምፔሪያሊስት መንግሥትና ከፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት ነፃነቱን መልሶ ከወሰደ በኋላ በሁለቱ የአውሮፓ ቅኝገዥዎች ተከፋፍለው ይገዙ የነበሩ የሰሜኑና የደቡቡ ክልል ነዋሪዎች መልሰው አንድነታቸውን በመፍጠር መንግሥታቸውን እንደአቋቋሙና ከዚያም አልፈው ታላቋን ሱማሊያ እንገነባለን በሚል የመስፋፋት ዓላማ የአፍሪካን ቀንድ ሰላም ከማወክና ከማደፍረስም አልፈው የመስፋፋት ምኞታቸውን በጦር ኃይል ተግባራዊ ለማድረግ ስለአከናወኑት ወረራ ከመተረኬ በፊት የሱማሌን ህዝብ በጎሳ ማህበር ላይ የተመሰረተ ባህላዊና ፖለቲካዊ ታሪክ፣ የአገሪቱን የኢኮኖሚ ሁኔታና የተፈጥሮ ሀብት፣ ስለህብረተሰቡ ጥንት ጥንታዊ የወል የመሬት ይዞታ ወዘተ ጋር ዘርዘር አድርጌ እንደ መግለፄ ሁሉ ስለ ኤርትራ ታሪክ ቢያንስ የሱማሌን ያህል ለምን አልተረከም የሚሉ ኢትዮጵያዊያን ይኖራሉ ብዬ እገምታለሁ።

በትግላችን ቅፅ አንድ መቅድምና መግቢያ ለኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ መንደርደሪያ ብዬ ከጥንታዊ የኢትዮጵያ ህዝብ ማለትም ከኩሻይት ኢትዮጵያ ዘመነ መንግሥት ጀምሬ እስከ ዘመነ ኢምፔሪያሊዝምና የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ እስከሆነው ዘመን ወያኔ ድረስ የረጅም ጊዜ አንኳር አንኳር ታሪኮቻችንንና በጠቅላላው በረጅሙ የታሪካችን ሂደት በአፍራሽና በገንቢ ወሳኝ ተፅእኖ የነበራቸውን ክስተቶች አጠርና ጠቅለል ባለ ሁኔታ አቅርቤያለሁ።

ያቀረብኩት ታሪክ በሙሉ ኤርትራ የሚባለውን ክልል ህዝብ ያካተተ ነው። ከሃምሳ ዓመቱ የኢጣሊያን ጣልቃ ገብነት በስተቀር። የኤርትራ ክፍለ ሃገር ህዝብ ከተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ የተለየና የራሱ ብቻ የሆነ ታሪክ የለውም። የኢትዮጵያ ታሪክ የኤርትራ ታሪክ ነው። የኤርትራ ታሪክም የኢትዮጵያ ታሪክ ነው።

ዛሬ ኤርትራ በመባል የሚጠራው ክልል የሰው ልጅ ታሪኩን ለመፃፍ ከመቻሉ ወይም ከመጀመሩ በፊት በቅድመ ታሪክ ጊዜ የነበረች ጥንታዊት አገራችን ከሦስት ሺህ ዓመታት በላይ ከፑንት እስከ የአክሱም መንግሥት ውድቀት ድረስ በፖለቲካ ሥልጣን ማማ ላይ የተፈራረቁ ቁጥራቸው ከአንድ መቶ ሃምሳ በላይ የሆነ ነገሥታት መንበረ መንግሥት ወይም የመናገሻ ቅጥር የነበረ ክልል ነው።

እነኝህ ነገሥታት ከውጭው ዓለም ጋር በፖለቲካ፣ በንግድ፣ በባህልና በደህንነት ጉዳይ ሲገናኙበት የነበረ የኢትዮጵያዊያን መግቢያና መውጫ የባህር በራችን ነው።

በዚያን ጊዜ ቀይ ባህርን ተሻግረን እኛም የተሰናዘርንበትና ስንዳከም ደግሞ በአመዛኙ የውጭ ጠላቶች እየገቡ ጥቃት ሲሰነዝሩብን የኖሩት በዚሁ የባህር በራችንና በኤርትራ ምድር ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ በአመዛኙ የትግልና የጦርነት ታሪክ ነው ሲባል የትግልና የጦርነቱ አውድማ ወይም የጦር ሜዳው ደግሞ በአመዛኙ ዛሬ ኤርትራ ብለን የምንጠራው ምድር ነው።

ሮማዊያን ሦስት ጊዜ፣ ቱርኮች ሁለት ጊዜ፣ ግብፆች ሁለት ጊዜ በፈረቃና እየተመላለሱ ሲወሩን አገራችንን፣ ነፃነታችንንና አንድነታችንን ለማዳን የተፋለምነው በኤርትራና በትግራይ ምድር ነው።

ኢጣሊያኖች፣ ቱርኮች፣ ግብፆች ወዘተ ዓለም አቀፍ ወደባችንን ምፅዋን በመቆናጠጥ የኤርትራን ክፍለ ሃገር የተወሰነ ምድር ከተቆጣጠሩ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ልብ ጠልቀው ለመግባት ሲያጠቁን እኛ ስንከላከል እያንዳንዳቸው እየተመላለሱ ከ30 እስከ 50 ዓመታት በፈረቃ ወግተውናል።

ረጅሙንና የጥንቱን ትተን የቅርቡን ጊዜ ማለትም ከመሀከለኛው ዘመን ወዲህ ብቻ ከ15ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ እስከ 19ኛው ምዕተ ዓመት መገባደጃ ድረስ የተሰነዘሩብንን ጥቃቶችና ወረራዎችን ብንመለከት ለ500 ዓመታት አላቋረጡም።

ከዚህ ከ500 ዓመታት ካላቋረጠ የውጭ ወረራና በየዘመኑ በውስጥ የተደረጉትን ካለፈው የ30 ዓመት የእርስ በርስ ጦርነት ጋር የኢትዮጵያ ህዝብ ያደረጋቸውን ፍልሚያዎች ስናስባቸው የኤርትራ ምድር እልፍ አእላፍ የኢትዮጵያን ህዝብ ልጆች ደም የጠጣ ምድር ነው።

የኤርትራን ታሪክ ማለትም የኢትዮጵያን ታሪክ መፃፍ ዓላማዬ ካለመሆኑ በላይ በኔ አቅም ሊደረግ የማይቻለውን ነገር ለማድረግ ከመሞከር ይልቅ ማድረግ የሚገባኝና ተገቢም የሚሆነው ኤርትራን ለመጎብኘትና ህዝቡ መካከል ለመገኘት ወይም ስለኤርትራ አንብበው ለመረዳት ላልቻሉ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቼ የኤርትራን ምድርና ህዝቡን ማስተዋወቅ ነው።

የአገራችን ሰሜናዊ ጠረፍ ወይም የባህር ዳርቻ ክልል ኤርትራ የተሰኘ ስም ያገኘው ፋሽስት ኢጣሊያ ክልሉን በጦር ኃይል ወራ ከተቆጣጠረች በኋላ በ18ኛው ምዕተ ዓመት መገባደጃና በ19ኛው ምዕተ ዓመት መባቻ ላይ ኤርትራ ብላ ስለሰየመችው ነው።

ከፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ በፊት ይህ ኤርትራ የተባለ ቃል ወይም ስም የሚታወቀው ጥንታዊ ግሪኮች ቀይ ባህርን ባህረ ኤርትራ ብለው ሲጠሩ እንጂ ዛሬ ኤርትራ በምንለው ክልል ኤርትራ በመባል የሚታወቅ ምድር፣ ስፍራ፣ መንደር

ወይም ኤርትራዊ በመባል የሚጠራ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብና ብሔረሰብ የለም። በታሪክም አይታወቅም።

ዛሬ ኤርትራ በመባል የሚታወቀው ክልል ከጥንት ጀምሮ ለረጅም ምዕተ ዓመታት የተለየ ክልላዊ ደረጃና ስም ሳይሰጠው እስከ የአክሱም መንግሥት ውድቀት ድረስ የነገሥታቱ መንበረ መንግሥት ወይም መናገሻ ቅጥር ክልል ነበር።

ከአክሱም መንግሥት ውድቀት ማለትም ከዘጠነኛው ምዕተ ዓመት በኋላ በዛጉዌ፣ በጉንደርና በሸዋ ነገሥታት፣ ሐማሴን፣ ምድረ ባህሪ፣ ባህረ ነጋሽ ወዘተ እየተባለ ሲጠራ ቆይቶ በመጨረሻም እስከ ፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ድረስ ከትግራይ ክፍለ ሃገር ጋር ተቀላቅሎ አንድ ክልል በመሆን በትግራይ መሳፍንቶች ፈረቃ ይመራ ስለነበረ ትግሬ በመባል ሲጠራ ቆይቷል።

በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ የአስር ዓመት የልማትና የግንባታ እቅድ ለመንደፍና የኢትዮጵያን ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ለመመስረት ቅድመ ሁኔታ ወይም ቅድመ ዝግጅት በመሆኑ ተደርጎ በነበረው የህዝብ ቆጠራ ጊዜ ገንጣይ አስገንጣዮች በሚያካሂዱት ሽብርና ጦርነት ምክንያት የኤርትራን ክልል ነዋሪ ህዝብ በገፅ ከቤት ወደቤት በመዘዋወር ለመቁጠር ባለመቻሉ በተወሰደው የናሙና የ(Sample) ቆጠራ ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በማፈን ስትራቴጂዋ ከኤርትራ ክፍለ ሃገር ጋር የቀላቀለውን የአፋር አስተዳደር ክልልና ህዝብ ሳይጨመሩ የኤርትራ ክፍለ ሃገር ነዋሪ ህዝብ ቁጥር 3,000,000 ሦስት ሚሊዮን እንደሆነ ተገምቷል።

እዚህ የህዝብ ቁጥር ላይ የተደረሰው በጊዜው ማለትም በጦርነቱ ምክንያት የተፈናቀለውን፣ ወደተቀሩት የኢትዮጵያ ክልሎችና እንዲሁም ከኢትዮጵያ ውጭ የተሰደዱትን ሁሉ በማስላትና ግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

ከዚህ በላይ እንደገለፅኩት የአፋር ክልል ሲነጠል የኤርትራ ክልል ምድር ወይም የመሬት ቆዳ ስፋት 64,000 ስልሳ አራት ሺህ ካሬ ኪ/ሜትር ነው።

በኢትዮጵያችን ብሔር፣ ብሔረሰብና ማህበረሰብ ወዘተ የተባሉ የህብረተሰብ እድገት እርከኖችና በጠቅላላውም የህብረተሰብ እድገት ህግጋቶች በሁሉም ዘንድ በወል የሚታወቁና በዚህ ረገድ የጋራ ግንዛቤ ያለን አይመስልም።

በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ ዘመናዊ የሚባለውን የመንግሥት ትምህርት ቤትና ባህላዊ የምንለውን የቄስ ትምህርት ቤት ደጃፍ የረገጡ ኢትዮጵያዊያን እንደ ሚያስታውሱት በህፃንነታችን በመጀመሪያው ቀን ወይም ክፍል ፊደል ቆጠራ ስንጀምር የአማርኛ ሆሄያትን ቅርፅና ድምፅ የምንማርበትን የፊደል ሰሌዳ የጻፉልን አቶ ተስፋ ገብረሥላሴ የሚባሉ ግለሰብ ከሆሄያቱ ግርጌ ጸሐፊ ወይም ደራሲነታቸውን ለማሳወቅ «ተስፋ ገብረሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ» እያሉ ይጽፉ ነበር።

የእሳቸውን የደራሲነት መብት ማወቅ የትምህርቱ አካልና የኛም የመማር ግዴታ ሆኖ ከፊደል ቆጠራ እስከምንወጣ ድረስ በጎላ ድምፅ እየደጋገምን እናነበው ነበር። ቡልጋ በሰሜን ሸዋ የሚገኝ አንድ አውራጃ ሆኖ ሳለ አስፈላጊ ከመሰላቸው ከዚህ አውራጃ መወለዳቸውን መግለፅ ሲበቃ የቡልጋ ብሔር አባልነታቸውን ገልፀዋል።

በአብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ እስከ አብዮታችን ፍንዳታ ድረስ የብሔርና የብሔረሰብ ወዘተ እድገት ህግጋትና የእድገታቸው እርከን ትርጉም በእጅጉ የተምታታ ነበር። ዛሬም በአብዛኛው ኢትዮጵያዊያን ዘንድ የተሟላ ግንዛቤ እንደሌለ ግልፅ ነው።

በኢትዮጵያችን ሰላምና መረጋጋት ሰፍኖ ጠንካራ የህዝብ አንድነት፣ እኩልነትና የተፈጠነ ማህበራዊ እድገት እንዲገኝ ህዝቡን በፖለቲካ ዓላማ ላይ የተመሰረተ አመለካከቱና ፍላጎቱ እንዲደራጅ ከመርዳት ፋንታ ወያኔ በጎሳ ፖለቲካ አደንቁረህና ከፋፍለህ ግዛ መርህ እያስገደደ በቋንቋ ልዩነት ያደራጃቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ገንጣይና አስገንጣዮችን ጨምሮ በፖለቲካ ፕሮግራማቸውና በየልሳኖቻቸው ራሳቸውን ብሔር እያሉ ሲጠሩ ይሰማል ይነበባልም።

በድህረ አብዮት ያቋቋምነው የብሔረሰቦችን ጉዳይ የሚያጠናውና የሚመራመረው ተቋም አጥንቶ ባቀረበልን ጥናት መሰረት በኢትዮጵያ የእድገት ደረጃ ያሉት የህብረተሰቦች እድገትና የአደረጃጀት እርከኖች፣ ግለሰብ፣ ቤተሰብ፣ ቤተዘመድ፣ መንደር ወይም ጎጥና እነዚህ በብርካቴ የተካተቱበት ማህበረሰብና እንዲሁም በርካታ ማህበረሰቦች የተካተቱበት ብሄረሰብ እንጂ አንድ ብሔር ማሟላት ያለበትን የታሪክ፣ የባህል፣ የምጣኔ ሀብት፣ የፖለቲካና የአስተዳደር ወዘተ መስፈርት የሚያሟሉ ብሄሮች (Nation) በኢትዮጵያችን በየትኛውም ክልል የሉም።

ብሔር (Nation) የህብረተሰብ እድገትና አደረጃጀት ታላቁና የመጨረሻው እርከን ነው። የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ከብሄር የእድገት ደረጃ ወደ ኋላ የቀረን ብቻ ሳንሆን በእጅጉ እሩቅ ነን። ብሔር ማለት የዘር ወይም የጎሳ መጠሪያ ስም ብቻ አይደለም። አንድ ቋንቋ መናገር የሰው ብዛትና የመሬት ቆዳ ስፋት ብቻቸውን ብሄር አያደርጉም።

ብሔር የዝማኔ ወይም የሥልጣኔ፣ የሰው ልማትና በአጠቃላይም የምርትና የምርት ኃይሎች ግንባታ ሁለንተናዊ እድገትና የኑሮ ደረጃ መመዘኛ እርከን ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ አንድ ሉአላዊና ነፃ ህዝብ በመኖር ባለፈበት ታሪካዊ የትግል ጎዳና አያሌ ዉጣ ውረዶች፣ ጭቆችና ጦርነቶች በተለያዩ አያሌ ምክንያቶች ባደረጋቸው ንቅናቄዎች ስደትና ፈለሳ አንዱ ማህበረሰብ ከሌላው ጋር በመወራረስ ዛሬ ባለንበት የእድገት ደረጃ ላይ ያሉ ማህበረሰቦችና ብሔረሰቦች አንዳቸውም አንድ ወጥ ዘር ሳይሆኑ የብዙ ማህበረሰብ ጥንቅርና የቋንቋ ቤተሰቦች ሆነዋል።

መወራረስን በተመለከተ ለአብነት ያህል የአንድን ወቅት ክስተት ብቻ ብንወስድ የኦሮሞ ማህበረሰብ ከአፍሪካ ቀንድ ጠርዝ ተነስቶ በገዳ ሥርዓት ግፊት እስከ ጐንደር ያደረገውን ፈለሳ ስናስብ በመንገዱ ላይ ስንቱን ጥንታዊ ወይም ነባርና የተለያዩ አናሳ ማህበረሰቦችን ውጦ እንደ አበጠ መገንዘብ ይቻላል።

በተጨማሪ ደግሞ ከሰሜኑ የአገራችን ክልሎች ሁለት ብሄረሰቦችን ብቻ ለምሳሌ ያህል ብንወስድ ከመረብ ወዲያና ከመረብ ወዲህ ያሉት ትግሪኛ ተናጋሪ የህብረተሰብ ክፍልና አማራው ዛሬ አሉበት የብሄረሰብ እድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ አያሌና የተለያዩ ነባር ማህበረሰቦችን በየጊዜያቸውና በየፊናቸው ጨፍልቀው የመጡ የብዙ ማህበረሰቦች ጥንቅር ግን ሁለት የቋንቋ ቤተሰቦች እንደሆኑ በውል ይታወቃል።

በታሪክ ሂደትና በህብረተሰብ እድገት ህግጋት ላይ ተመስርቶ አንዴ በአብዮታችን አፍላ ወቅት ዶክተር ሐጎስ ገብረክርስቶስ ሲናገር «ከሰሜን ወደ ደቡብ፣ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ የኢትዮጵያ ማዕዘናት ሄዳችሁ በየትኛውም ክልል ያሉትን የኢትዮጵያ ህብረተሰቦች በወንፊት ብትነፏቸው እንኳን በሚናገሩት ቋንቋ እንጂ በዘር ልትለዩአቸው አትችሉም» ነው ያለው።

ጓድ ሐጎስ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ጉልታዊውን የፖለቲካ ሥርዓተ ማህበርና የሥርዓቱን አራማጅ ገዥ መደብ ብቻ ሳይሆን የሥርዓቱ ውጤት የሆኑትን ጠባብ ብሄርተኛና ሥርዓተ አልበኞች በፅኑ የታገለ ታዋቂ ኢትዮጵያዊ አብዮተኛ ነው።

ጓድ ሐጎስ ትግሪኛ ከሚናገረው የህብረተሰብ አብራክ የተገኘ ይህንን በተናገረበት ወቅት በካናዳ አንድ ትልቅ ዩንቨርስቲ ውስጥ መምህር የነበረ የታሪክ ሊቅ ነው።

በህብረተሰብ የእድገት ህግጋት መሰረት የኢትዮጵያን ህዝብ የየዘመናቱን የታሪክ ገጠመኞችና እንዲሁም ክስተቶች ስናወሳ ዛሬ ኤርትራ የሚባለውን ክልል ነዋሪ ህዝብ የረጅም ጊዜ ታሪክ ትተን ከመካከለኛው ዘመን ወዲህ ብቻ ከአምስት መቶ ዓመታት በላይ በተራዘመ የውጭ ኃይሎች ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ ጣልቃ ገብነትና ወረራ ስንመለከት ከተቀሩት የኢትዮጵያ ክልሎች ነዋሪ ከሆነው ህዝብ ሁሉ በታሪክ የተጓዘባቸው መንገዶችና የገጠሙት ገጠመኞች በባሰ ሁኔታ ውስብስቦች ናቸው።

ከሁሉ በፊት በጥንታዊው የኩሻይት ኢትዮጵያ ዘመነ መንግሥት ከአባይ ሸለቆ ክልል፣ ከሰሜን አፍሪካ፣ ከመካከለኛው ምስራቅና ከእስያ አህጉር በተለያዩ ጊዜያቶች ከአገራቸው እየተፈናቀሉ ለምለምና ነፋሻ ወደሆነችው አገራችን ኢትዮጵያ የመጡት አያሌ ነገዶች በቀይ ባህር በራችን እንደገቡና በኤርትራ ምድር እንደሰፈሩ የታወቀ ነው።

ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ባለበት የእድገት ደረጃ በእነዚያ የተለያዩ አያሌ ነገዶች አባልነት የሚታወቁ በስማቸው የሚጠሩና በቋንቋቸው የሚናገሩ የህብረተሰብ ክፍሎች አይገኙም። ምክንያቱም በጊዜ ሂደትና በህብረተሰብ እድገት ከስመዋልና።

ለብዙ ሺህ ዓመታት በተለያዩ ጊዜያቶች ከውጭ ከፈለሱት የተለያዩ ነገዶች ሌላ ከውስጥ ማለትም ከደቡብ ወደ ኤርትራ ምድር በየጊዜው የፈለሱት የትግራይ፣ የአገው፣ የአማራ፣ የአፋር ወዘተና እንዲሁም ከምዕራብ ማለትም ዛሬ ሱዳን ከሚባለው ምድር ወደ ኢትዮጵያ የፈለሱት ማህበረሰቦች የአካባቢውን ጥንታዊ ወይም ነባር የህብረተሰብ ክፍሎች ዘር ብቻ ሳይሆን ቋንቋቸውን፣ ባህልና መንፈሳዊ እምነታቸውን ጭምር በመደጋገም በርዘውታል፣ በውዘውታል፣ ለውጠውታል። በአጠቃላይ አነጋገር ሁሉም ተወራርሰው ዛሬ የእነዚህ ጥንቅሮች የሆኑ አዳዲስ የቋንቋ ቤተሰቦች ተፈጥረዋል።

ዛሬ ኤርትራ በቋንቋ ፣ በባህል፣ በሃይማኖት፣ በሰው ቁጥርና በሰፈሩበት የመሬት መጠን በማህበራዊ የእድገት ደረጃቸው የተለያዩ የትግሬ፣ የቤጃ፣ የቤንአምር፣ የአፋር፣ የሳሆ፣ የኩናማ፣ የናራ፣ የትግረና የቢለን ማህበረሰቦችና ብሄረሰቦች አባልና አካል የሆኑ በርካታ የቋንቋ ቤተሰቦች የሚኖሩበት በህርታዊ ክልል ነው።

የኤርትራ ክፍለ ሃገር በሁለት የአየር ንብረት ማለትም በደጋና በቆላ የተከፈለና ሦስት ዓይነት የመልክአ ምድር ገፅታ ያለው ክልል ነው።

ከሱዳን የሚያዋስነን የሳህል አውራጃ ከአፋቤት ወረዳ ጀምሮ ወደ ላይ ያለው ሰሜናዊው ምድር በበርካታ የተራራ ሰንሰለቶች የተሸፈነ፣ ነፋሻ የአየር ንብረት ያለው ወይና ደጋማ ክልል ሆኖ ከከፍተኛ መሬትነት ወይንም ከተራራ ማነት በላይ አካባቢው በጠቅላላ ማለት ይቻላል እርዳማ ወይንም አራዳ ዘበጣዘበጥና ገደላ ገደል በመሆኑና ተራሮቹም ድንጋያማ ተራሮች በመሆናቸው ለእርሻ ተግባር ጨርሶ የሚያመች አካባቢ አይደለም።

በአሳዛኙ የእርስ በእርስ ጦርነት ለገንጣዮችና ለአስገንጣዮች በአጠቃላይ ሻቢያ ብሎ ራሱን ለሚጠራው ገንጣይ ድርጅት በተለይ የተፈጥሮ ምሽግ ሆኖ የወጋን መሬት ነው።

ይህ በድንጋያማ ተራሮች የተሸፈነው የሳህል አውራጃ ከጠቅላላው የክፍለ ሃገሩ የመሬት ቆዳ ስፋት በግምት አስራ አምስት በመቶ ይሆናል።

በክፍለ ሃገሩ ምዕራብ ከሳህልና ከከረን አውራጃ ተራሮች ወይንም ከፍተኛ መሬቶች ግርጌና መካከል የሚገኙትና በአጠቃላይ ምዕራባዊ ቆላ በመባል የሚጠሩት ሰፋፊዎቹ የጋሽና የባርካ አውራጃዎች የመልክአ ምድር ገፅታ በሙሉ ማለት ይቻላል ሜዳማ ፣ የአየር ንብረታቸው በጣም ሞቃታማ ወይንም ቆላማ ሆኖ ከደቡቡና ከሰሜኑ ከፍተኛ

ደጋማ መሬቶች ዝናብ እያጠበ በሚያመጣው ለም አፈር የተሸፈኑ ሆነው ሳለ የዝናብ እጥረት በመኖሩ ለእርሻ ተግባር ተስማሚ አይደሉም።

የመሬቱ ተፈጥሮ ለዘመናዊ እርሻ እጅግ አመቺ ሆኖ ሳለ በቆላማዎቹ ክልሎች ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው በኤርትራ ኃይል ያላቸውና ክረምት ከበጋ የሚፈሱ ወንዞች ስለሌሉ ክልሉ በግብርና ኢኮኖሚ እድገት በኩል ያለው እድል በጣም ውስን ነው።

እነኝህ ምዕራባዊ ቆላ የሚባሉት የጋሽና የባርካ አውራጃዎች ከጠቅላላ የክፍለ ሃገሩ የመሬት ቆዳ በግምት ሃያ አምስት በመቶ ይሆናሉ።

በአመዛኙ ህዝበ ክርስቲያኑ የሚኖርባቸውና የኤርትራ ደጋማ ክልል የሚባሉት ብዙ ሰው የተሸከሙ ወይንም የሰፈረባቸው የከረን የአካለጉዛይ የሰራዬና የሐማሴን አውራጃዎች ናቸው።

እነዚህ አራት ደጋማ አውራጃዎች ከቆላማው ምድርና ከባህሩ ወለል በግምት ሦስት መቶ ሜትር በላይ የመሬት ከፍታ ላይ የሚገኙ ናቸው የሚባሉት ለሰው ህይወት የተስማማ ነፋሻ የአየር ንብረት ያላቸውና የሚያገኙት አመታዊ የዝናብ መጠንና ሥርጭት ለግብርና ተስማሚ ቢሆንም የመልክአ ምድራቸውን አቀማመጥና ተፈጥሮአዊ ገፅታ በተመለከተ ከሐማሴንና ከሰራዬ አውራጃዎች በስተቀር የአካለ ጉዛይና የከረን አውራጃዎች በከፊል ለእርሻ በማያመቹ፣ ዘብጥና ገደሎች የሚበዙባቸው ከመሆናቸው ሌላ በድንጋያማ ተራሮች የተሸፈኑ ናቸው።

የኤርትራ ክፍለ ሃገር ምሥራቃዊ ቆላ በመባል የሚታወቀው ከምፅዋ አውራጃ ጀምሮ እስከ ቃሮራ ወይንም ከራስ ካሳር እስከ ራስዱሜራ ድረስ ያለው የቀይ ባህር ዳርቻ እረጅም ወሽመጥ ያለው ሰፊ ምድር ለምንም ጥቅም የማይውል የፀሀይ ንዳድ የሚያጠቃው ፍፁም በረሐማ ክልል ሲሆን መሬቱም ሙሉ በሙሉ አሸዋማ ነው።

የዚህ የኤርትራ ክፍለ ሃገር ምሥራቃዊ ቆላ ወይንም የቀይ ባህር ዳርቻ መሬት ከጠቅላላው የክፍለ ሃገሩ የመሬት ቆዳ በግምት ሃያ በመቶ ይሆናል።

ከሳህል አውራጃ ደቡባዊውን ክልል ከጋሽና ሰቲት አውራጃ ምሥራቃዊውን ክልል መሬቶች የተወሰኑ ክፍሎችን አካቶ የአንሳባ ወንዝ የሚፈስበት የባርካ አውራጃ ለም አፈር አልፎ አልፎ በሚያገኘው ከባድ ዝናብና እንዲሁም አልፎ አልፎ በክረምቱ ወቅት በሚዘንበው ካፊያ የሚበቅለው ሳርና ቁጥቋጦ ከብቶችን በሚገባ ለመመገብ በመቻሉ የማይናቅ የግመል የቀንድና የዳልጋ ከብቶች ክምችት ያለው ነው።

የባርካ የሥጋና የወተት ከብቶች በብዛታቸው ብቻ ሳይሆን በነዶአቸው ወይንም በጥራታቸው ከፎገራ፣ ከቦረና ከኦጋዴ የሥጋና የወተት ከብቶች ጋር የሚወዳደሩ ናቸው።

በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚና በተፈጥሮ መሀከል ባለው የመተሳሰር እውነታ ላይ ተመስርተን ከዓመት ዓመት እድገት የማይታይበትን የግብርና ምርት መጠን በአፋጣኝ በማደግ ላይ ከነበረው የህዝብ ቁጥር ጋር ስናሰላው የምናገኘው ውጤት አሉታዊ ነው::

የኤርትራ ክፍለ ሃገር ህዝብ አብዛኛው ማለት ይቻላል የስራ ክቡርነትን የሚያውቅ ስራ ወዳድ ሲሆን አብዛኛው ከተሜ ልዩ ልዩ የዕደ ጥበብና የእጅ ሞያ እውቀት ያለው ገጠሬው ገበሬ ብርቱ ሠራተኛና ታታሪ ነው:: ነገር ግን አምራች ነው ተብሎ የሚነገርለት ገበሬ፣ ደገኛው በእርሻ መሬት እጥረት፣ ቆለኛው በዝናብ እጦት ምክንያት ከራሱ ፍጆት አልፎ የክፍለ ሃገሩን ህዝብ ፍላጎትና ፍጆት ለመሸፈን ከከፊል በላይ አምርቶ አያውቅም::

የኤርትራ ክፍለ ሃገር ህዝብ በእህል በኩል ያለበትን እጥረት የሚያሟላው ከትግራይ፣ ከወሎና ከጐንደር ገበሬዎች በመሸመት ነበር::

ነበር ነበር እያልኩ የምገልፅበት ምክንያት አንባቢ እንደሚያውቀውና ወይንም ለመገመት እንደሚችለው የእርስ በርስ ጦርነቱ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮ ያመጣቸው ችግሮች ተነባብረውና ተደራርበው የኤርትራን በጎና የተሻሉ ሁኔታዎች ሁሉ በአሳዛኝና አፍራሽ ሁኔታ ስለለዋወጧቸው ነው::

ጦርነቱ እጅግ በከፋበትና የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት በገንዘብ የገዛቸውና የኢትዮጵያ ነፃ መኮንኖች የፖለቲካ ድርጅት ብሎ ለአብዮት ቅልበሳ በአደራጃቸው ከሐዲና አድሐሪ ጀነራል መኰንኖች ጋር የተመሳጠሩት ሻዕቢያና ወያኔ በህብረት ኤርትራን ከመሀሉ አገር ትግራይ ላይ ቆርጠው የምፅዋን የባሕር በር በዘጉበት ጊዜ የኤርትራን ክፍለ ሃገር ህዝብና መላውን መለዮ ለባሽ አብዮታዊው መንግሥት እንዴት እንደመገባቸው በትግላችን ቅፅ አንድ በዝርዝር የገለፅኩ ስለሆነ እዚህ ላይ መድገም አስፈላጊ አይመስለኝም::

ፋሽስት ኢጣሊያ እንደተቀሩት የአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት በአፍሪካ አህጉር በጦር ኃይል ተስፋፍታ የቅኝ ግዛት አገሮች ባለቤት ለመሆን ያካሄደቺው ወረራ በቀላሉ የተሳካለት ሳይሆን ከፍያለ የገንዘብና የአያሌ ኢጣሊያዊያንን ህይወት እንዳስከፈላት ይታወቃል::

በጦር ኃይል ወርራ ቅኝ ግዛቷ የምታደርጋቸውን አገሮች የተፈጥሮ ሀብትና የሰው ጉልበት በመመዝበር ለመበልፀግ በነበራት ገደብ አልባ ምኞት ከአቅሟ በላይ ብዙ ስለናጠጠች ብዙ ዋጋ ከፍላለች::

በዚህ ረገድ በሊቢያና በሶማሊያ የገጠማትን ትቼ በኢትዮጵያ፣ ራስ አሉላ በዶጋሌ፣ ምኒልክ በአድዋ ያገኙትን ድሎች አስፋፍተው የኢጣሊያን ሠራዊት ለአንዴና

ለመጨረሻ ከኤርትራ ረግጠው ማስወጣት ሲቻላቸው ያለ ማድረጋቸው ከኢትዮጵያ አሳዛኝ ታሪክ አንዱ ቢሆንም በኢጣሊያ ጦር ላይ ያስመዘገቡትን ወታደራዊ ድሎች ማስታወስ ይበቃል።

ኢጣሊያ ለዘመናት ከተቆራኛት የኢኮኖሚ ችግርና የአገር ውስጥ የፖለቲካ ቀውስ ሳትወጣና ሳትሽር ነበር በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከጀርመን ጋር ወግና ታላቅ ዓለም አቀፍ ቀውስ ውስጥ የተዘፈቀቺው።

ዱቼ ሞሶሊኒ ከሂትለር ወግኖ የተሰለፈበት የዓለም ጦርነት ዳግም በብዙ መቶ ሺህ ኢጣሊያዊያን ላይ የከፋ የህይወት አደጋ ብቻ ሳይሆን በቀላሉ የማይወጡት ታላቅና ሁለገብ ማህበራዊ ምስቅልቅል ውስጥ ነው የከተታቸው በጦርነቱ የአሰላለፍ ጎራ ከጀርመን፣ ከኢጣሊያና ከጃፓኖች በተቃራኒ ለውጊያ ያበሩት ሰሜን አሜሪካና የአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት የጦር ኃይሎች በአፀፋ የመልሶ ማጥቃት ውጊያ ከመሰንዘራቸው በፊት ነው የኢጣሊያ ኮሚኒስቶች የሂትለርን የጦር ጓደኛ ዱቼ ሞሶሊኒን በሮም አደባባይ ዘቅዝቀው የሰቀሉት።

የኢጣሊያ ፋሽስቶች ኃይል ፍፁም ስለተንኮታኮተ ኢጣሊያ መንግሥትና ሥርዓት አልባ ቀውስ ውስጥ በወደቀችበትና ቅኝ ግዛቶቿን ለማስተዳደር ቀርቶ የኢጣሊያንን መሀከል የሚመራ የአመራር አካል ስላልነበረ የተነባበረ የቀውስ ማጥ ውስጥ ሰምጣ ነበር ማለት ይቻላል።

በአፍሪካ ቀንድ በተለይም በሰፊዋና በለሚ ኢትዮጵያላይ ተስፋፍታ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩና የኢጣሊያ ዜጎች የሆኑ ሥራ አጦችና በዘኔዎችን በማስፈር የመበዝበዝ እቅዷ በአጭሩ ተቀጨና ከሰፊዋ ኢትዮጵያ ለም ምድር ተረግጣ በመውጣት ለጊዜው በኤርትራ ክፍለ ሃገር ብቻ ተወስና ለመኖር ተገደደች።

ኢትዮጵያን ለመውረር ለፈለጉና ለሞከሩ ባዕዳንሁሉ ኤርትራ የባሕር በር በመሆኑ ወደ ኢትዮጵያ ልብ ጠልቆ ለመግባት ይጠቀሙበት እንጂ በብዝበዛ ለመበልፀግ የወረራ ዓላማቸው ኤርትራ ግባቸው እንዳልሆነ ማስረጃው በአደዋ ውጊያ ከደረሰባቸው ሽንፈት በኋላ ለአርባ ዓመታት ተዘጋጅተው ዳግም መመለሳቸው ብቻ ሳይሆን ከእነጁሴፔ ሳፔቶ የስለላ ጥናቶች ጀምሮ አያሌ ማስረጃዎች አሉ።

ኢጣሊያኖች በኤርትራ ውስጥ በቆዩበት ረጅም ጊዜ በተቻላቸው መጠን የጦር ኃይላቸውንና ሲቪል ዜጎቻቸውን ለመመገብና ይህንንም ለማድረግ የሚያስችላቸውን ወይንም ኤርትራ እስከአሉ ድረስ ብቻ የሚያገለግሏቸውን ጥቂት መሰረተ ልማቶች፣ ጥቂት የኢኮኖሚ አገልግሎት ተቋሞችን ለራሳቸው ብቻ ለመገንባት ካደረጉት ሙከራ ያለፈ ለኤርትራ ህዝብ ብለው ያደረጉት ነገር የለም።

ዛሬም ወደፊትም በጠቅላላው ለዘላለም የኢትዮጵያ ህዝብ በፅኑ ማሰብ ያለበት የኤርትራ ክፍለ ሃገር ህዝብ በደሙ በዘሩ በባህሉና በታሪኩ ወዘተ ፍፁም ኢትዮጵያዊ ህዝብ ሆኖ ሳለ በጠላቶቻችን ሴራ ከወገኑ ከተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ መለየቱን ብቻ ሳይሆን ጠላቶቻችን የኤርትራን ምድርና የቀይ ባህርን በር ለሌላ ወረራ ያዘጋጁ ስለሆነ በጠቅላላ ደህንነታችን፣ ነፃነታችንና ህልውናችን ለዳግም የወረራ አደጋ የተዳረጉ መሆናቸውን ነው::

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መገባደጃ ላይ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1940 ዓ.ም መጀመሪያ በእርዳታ ስም ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ኢጣሊያኖችን ወግቶ ኤርትራን በጦር ኃይል የተቆጣጠረው ሌላው ቅኝ ገዥ የኢምፔሪያሊስት ብሪታኒያ ወታደራዊ መንግሥት ኤርትራ በቆየባቸው አሥር ዓመታት ያከናወነው ግንባታ ወይንም ልማት ሳይሆን የኢጣሊያ ቅሪት የሆኑትን ማናቸውንም ጠቃሚነታቸው ያላቸውን ንብረቶችና በተለይም የማምረቻ መሣሪያዎችን በመነቃቀል ወደ ሱማሌ፣ የመንና ሕንድ ከማጓጓዝ ባሻገር የተቀሩትንና ለማጓጓዝ ያልተቻለውን በማፈራረስ ማውደምን ነው::

የኤርትራ ህዝብ ከወገኑ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር መልሶ በፌደሬሽን ከተዋሀደ በኋላ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግሥት የተረከበው በቅኝግዛት ቀንበር ውስጥ ታስሮ ነፃነቱንና ሰብአዊ መብቱን የተገፈፈ ህዝብ፣ ኃብት ንብረቱን የተዘረፈ፣ በስራ አጥና በቦዘኔ ዜጎች የተጨናነቀ አገር ነው::

በዝናብ እጥረትና በእርሻ መሬት ጥበት ምክንያት የኤርትራ የግብርናው ኢኮኖሚ ያለበትን ድክመት ለማካካስ እንግሊዞች ለፈጠሯቸው የክፍለ ሃገሩ ስራ አጥና ቦዘኔ ዜጎች ስራ ለመፍጠርና የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር የአመራር አካላት ፀረ አንድነቶችን ወደ አንድነት ጎራ ለመሳብ ወይንም ለማስገባት ሲሉ «ከወገናችን ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር መልሰን ብንዋሀድ ከምናገኘው የታሪክና የመንፈስ ፋይዳ ሌላ ትልቋ፣ ለሟና ሀብታሟ አገራችን ኢትዮጵያ ቁሳዊ ፍላጎታችንን በማርካት በልማትና በግንባታው ብዙ ታደርግልናለች» በማለት ለህዝቡ የገቡትን ቃል በተግባር ለመተርጎምና ህዝቡን ለማስደሰት ሲባል ማዕከላዊ መንግሥት ከተቀሩት የኢትዮጵያ ክፍለ ሃገራት እየወሰደ በአጭር ጊዜ ውስጥ በኤርትራ በኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚው በኩል ያደረገው ግንባታ ያለማጋነን ከዚያ በፊት ብቻ ሳይሆን ከዚያም በኋላ በኢትዮጵያ ታሪክ የትምና መቼም ተደርጎ የማይታወቅ ነው::

ዛሬ በኤርትራ የሚገኙት የጨርቃጨርቅ፣ የቆዳ፣ የጆኒያ፣ የጠርሙሶችና በጠቅላላው የሴራሚክስ ማምረቻዎች የተለያዩ የቀዝቃዛና የአልኮሆል መጠጥ ማምረቻዎች የተለያዩ የምግብ ማምረቻ ወዘተ ኢንዱስትሪዎች የተቋቋሙት በፌደሬሽን ውህደት ከተደረገ በኋላ አስር ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነው

ከፌደሬሽኑ መመሥረት በኋላ የስራ አጡን ቁጥር ለማቃለል በመሀል አገር በየመንግሥቱ መስሪያ ቤቶች በትዕዛዝ የተቀጠሩትንና በጦር ኃይሉ ውስጥ

በውትድርና የተካተቱን በብዙ ሺህ ከሚቆጠሩ ኤርትራዊያን ሌላ በተለያዩ መሰረታዊ ልማቶች በትምህርትና በጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የተደረጉትን ግንባታዎች በትግላችን ቅፅ አንድ የገለፅኩ ስለሆነ እዚህ ላይ መደገሙ አስፈላጊ አይሆንም።

ገንጣዮቹ የሚያካሂዱት ሽብርና ጦርነት የልማቱንና የግንባታውን ሂደት እስካገደው ድረስ የኢንዱስትሪው ግንባታ እንደቀጠለ ነበር።

ለማስረጃ ያህል በምፅዋ የወደብ ከተማ የተቋቋመው የበረዶ ማምረቻ፣ በደቀመሐሪ ከተማ የተቋቋሙት ልዩ ልዩ የምግብ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ወዘተ በሙሉ የተገነቡት በድህረ አብዮት በአብዮታዊው መንግሥት የአመራር ዘመን ነው።

በፌደሬሽን ውህደት ከመደረጉ በፊት የኢጣሊያ ስሪትና ቅሪት በሆኑት የምፅዋ የሲሚንቶ ማምረቻ ፋብሪካ፣ ከምፅዋ ጀምሮ እስከ አቆርዳት ከተማ ድረስ ይንቀሳቀስ በነበረው የምድር ባቡርና በአስመራ ከተማ ውስጥ በነበሩ የተለያዩ የቴክኒክ አገልግሎት መስጫ ድርጅቶች ውስጥ ይሰሩ የነበሩ ሠራተኞች ብዛት 11,000 አስራ አንድ ሺህ የነበረ ሲሆን ከፌደሬሽኑ በኋላ አብዮታችን እስከተቀለበሰበት ጊዜ ድረስ የኤርትራ ክልል ሠራተኞች ቁጥር ከ40,000 አርባ ሺህ በላይ ነበር።

ይህ የሠራተኞች ቁጥር አዲስ ወይንም በፌደሬሽኑ ጊዜ በተገነቡት የተለያዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተሰማሩትን መምህራን፣ የህክምና ባለሞያዎችን፣ የአየር መንገድንና የሲቪል አቪዬሽንን፣ የቴሌኮሚኒኬሽንን፣ የባንኮችን ወዘተ ሠራተኞች ሳይጨምር ከማምረት ተግባር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን የአምራች ወዝ አደሮችን ቁጥር ብቻ ነው የገለፅኩት።

የኤርትራን ስራ አጥና የቦዘኔ ቁጥር ለማቃለልና የህዝቡን ኑሮ ለማሻሻል ሲባል ይህ ሁሉ እየተደረገ የኤርትራ ጠባቦችና ገንጣዮች ውህደቱ ያስገኘልን አንዳችም ፋይዳ የሌለ ከመሆኑ ሌላ አገራችን በአማሮች እየተበዘበዘ ነው። ለኛ የሚበጀን መገንጠሉ ነው እያሉ ነበር ለህዝቡ የሚነግሩት።

ወደ ኢንዱስትሪው ግንባታ ልመለስና ከአቀረብኳቸው የኢንዱስትሪ ዓይነቶች አንባቢ ለመረዳት እንደሚችለው አብዛኛዎቹ አግሮ ኢንዱስትሪዎች ናቸው። አግሮ ኢንዱስትሪ ማለት የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የሚያቀርብላቸውን ጥሬ ምርት የሚጠቀሙ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ጥገኞች ናቸው።

የኤርትራ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ጥሬ ምርት የማቅረብ አቅም ስለሌለው ለመጠጥ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ስኳሩን፣ ጌሾውን፣ ገብሱን፣ ብቅሉን ወዘተ ለምግብ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች እህሉን ወዘተ በጠቅላላ ለኢንዱስትሪ ግብአት የሚሆኑት ጥሬ ምርቶች የሚያቀርበው የመሐሉ አገር የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ነው።

ምዕራፍ አስራ ሦስት

ሁለተኛው የፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ

የፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት በ1878 ዓ.ም የምፅዋን ወደብ በመቆጣጠርና ብሎም በመስፋፋት ግልፅ ወታደራዊ ወረራ ለመሰንዘር የቻለው በ1852 ዓ.ም በንግድና በልማት አሳቦ የአፋር ብሄረሰብ ባላባቶችን በገንዘብ በመደለል ዛሬ የአሰብ ወደብ ያለበትን የባህር ዳርቻ የመሬት ቁራጭ በመግዛት የአሰብን ወደብ በአንድ የንግድ ኩባንያ ስም ከሰራ በኂላ ነው።

ከአሰብ ወደብ በቀጥታ ወደ ምፅዋ ወይም ወደ ኤርትራ ከመራመዱ በፊት ለ16 ዓመታት ኢትዮጵያን ሲያጠናና ሲሰልል ከኖረ በኂላ የንግድ ተቋም ናቸው ያላቸውን ወደቡንና የመርከቡን ድርጅት ወደ ወታደራዊ ተቋም ከለወጠም በኂላ እያደባ ቀይቶ አንድም የኢትዮጵያ መንግሥት ወገን ወይም ባለሥልጣን ለመቃወም ቀርቶ የተመለከተውም ስላልነበረ ከአሰብ ወደ ቤሉል እና ወደ ምፅዋ ደረጃ በደረጃ በመንቀሳቀስ ነው።

የምፅዋን ወደብ ከተቆጣጠረም በኂላ በቀጥታ ወደ አስመራ ለመንደርደር ሳይቃጣ በቅድሚያ በምፅዋና በአካባቢው በመስፋፋት ከተቆናጠጠ በኂላ እንዲሁ ደረጃ በደረጃ እያደባ ሲንቀሳቀስ ዶጋሌ ላይ የራስ አሉላ አባነጋ ጦር ድባቅ ስለመታው አንድ እግረኛ ሻለቃ ጦሩን እንዳለ በሙሉ በማጣት ነው በምፅዋ ክልል ብቻ ተገትቶ የቆየው።

ጥንት ደባሩዋ በመባል የሚታወቀውን የክልሉን ርዕሰ ከተማ የዛሬውን አስመራ በመያዝ ብሎም በሙሉ የሰሜኑን የአገራችን ክልል በመቆጣጠር ኤርትራ የተሰኘ ስም ለመስጠት የተዳፈረውም አፄ ዮሐንስ ራስ አሉላን ከክልሉ አስተዳዳሪነትና ከጦር አዛዥነት ሽረውና ከኢጣሊያ ፋሽሽት ሠራዊት ጋር የተፋጠጠውን የኢትዮጵያ ሠራዊት ከምፅዋ ግንባር አንስተው ወደ ጐንደር በማዝመታቸው ኢጣሊያኖች ያለአንዳች ላብና ደም በሰላም ኤርትራን ተቆጣጥረው ለ50 ዓመታት በቅኝ ገዥነት የክልሉን ህዝብ ረግጠው በማሰቃየት ኖሩ።

የኢጣሊያ ፋሽስቶች በኤርትራ ክፍለ ሃገር ህዝብ ላይ ሲፈጽሟቸው የነበሩት በደሎች ገደብ አልባና ፍፁም ኢ - ሰብአዊ ነበሩ። የኢትዮጵያ መንግሥት ሉአላዊነትና የህዝቡ ነፃነት በማንም ሳይደፈር ታፍሮና ተከብሮ የኖረ አገር ፋሽስት ኢጣሊያ ወራ ቅኝ ግዛቷ በማድረግ በኤርትራ ክፍለ ሃገር ህዝብ ላይ የፈፀመችውን ግፍና በደል መዘርዘር ስለሚያዳግት ከፈፀመቻቸው ቅጥ አልባ ሰቆቃዎች ጥቂቱን ብቻ ከዚህ እንደሚከተለው ለአብነት ያህል ለመግለፅ እሞክራለሁ።

የኢትዮጵያዊያን መኖርያ ሰፈሮችና ቤቶች ከኢጣሊያዊያን መኖሪያ ሰፈሮችና ቤቶች በዘር መድሎና ጭቆና መርህ መሰረት የተራራቁና በይዘትም እጅግ የተለያዩ ነበሩ።

ኢትዮጵያዊያን ምንም ዓይነት ችሎታና ሞያ እንዲሁም የስራ ብቃት ቢኖራቸው ከኢጣሊያኖች ጋር በእኩልነት የመስራት መብት የሌላቸው ብቻ ሳይሆን ለተመሳሳይ ስራ ተመሳሳይ ክፍያ አይከፈላቸውም።

ይህም ሆኖ ለኢትዮጵያዊያን የሚሰጣቸው ስራ በአመዛኙ ውትድርና፣ ዘበኝነት ወይም የጥበቃ ስራዎች ሲሆኑ ከእነዚህ በተረፈ ለኢትዮጵያዊያን የሚሰጡ የቀሩት ስራዎች በጠቅላላ ማለት ይቻላል ማናቸውም የጉልበት ስራዎች በእሽከርናና በግርድና ወዘተ በቤት ውስጥ አገልግሎት የመስጠት ስራዎች ናቸው።

የኢጣሊያ ፋሽሽቶች በ1877 ዓ.ም የምፅዋን ወደብ ከግብፆች ተረክበው ከተቆጣጠሩና ብለውም ኤርትራ ብለው የሰየሙትን ክልል ነዋሪ ህዝብ ከወረሩ በኋላ ከኤርትራ እየተንደረደሩ መላዋን ኢትዮጵያ ቅኝግዛታቸው ለማድረግ በሰነዘሩብን ሁለት አውደ ጥቃቶች ማለትም በአድዋና በማይጨው ውጊያዎች የክልሉን ወጣቶችና ጎልማሶች በውትድርና እየመለመሉ የአጥቂ ሠራዊታቸው ዋና ኃይል ወይም የሠራዊታቸው የጀርባ አጥንት አድርገው በማስታጠቅና በማደራጀት ከወገናቸው ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ደም አቃብተዋቸዋል።

በአፍሪካ ቀንድ ሌላው ቅኝ ግዛታቸው የሆነችውን ሱማሌን የወረሩት ከኤርትራ በመለመሉት ኢትዮጵያዊ ሠራዊት ከመሆኑ ባሻገር የብሪታኒያ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ሰሜን ሱማሌን ከእነሱ ነጥቆ ለመውሰድ የሰነዘረባቸውን ብርቱ ጥቃት ለመከላከል ጦርነቱ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በኢጣሊያዊያኑ ሽንፈት እስከ አበቃበት ጊዜ ድረስ በመማገድ ያስፈጁት ኢትዮጵያዊያኑን ነው።

ከሰሜን አፍሪካ ቅኝ ግዛታቸው ያደረጉት የሊቢያ ህዝብ በአጠቃላይና የአርነት ተዋጊ አርበኞቹ በተለይ ለነፃነታቸው ያደረጉትን ረጂምና ታላቅ የትጥቅ ትግል ለማኮላሸት የወራሪ ሠራዊታቸው አበይት ኃይል አድርገው ያጋፈጡት ኢትዮጵያዊያንን ነው።

ይህንንና ሌላውንም ግፍናጭቆና ላለመቀበል ያመፁ ኢትዮጵያዊያንን ቀይ ባህር ውስጥ ካሉን አያሌ ደሴቶች አንዱ በሆነው በናኩራ ደሴት ላይ በሰሩት ኢትዮጵያዊያንን ማሰቃያ ዓለም በቃኝ ወህኒ ያለፍርድና ያለ ጊዜ ገደብ አጉረው ከ40 ዲግሪ ሴ.ግሬድ በላይ በሚፈጅ የፀሀይ ሃሩርና በክረምቱ ወቅት የውቂያኖሱ የአየር ንብረት በሚፈጥረው አጥንት የሚሰብር ቀዝቃዛ ንፋስና ከዜሮ ዲግሪ በታች በሆነ ከባድ ቅዝቃዜ ወይም ከባድ ቁርና አመዳይ፣ በርሀብ፣ በበሽታ፣ እነዚህም ሰቆቃዎች አንሰው በዱላ ድብደባ ወዘተ በሃምሳ ዓመታት የጊዜ ክልል ውስጥ ያለቁትን ኤርትራዊያን ቁጥር ለመገመት ያስቸግራል።

ኢጣሊያኖቹም ሆኑ የሌላ አውሮፓዊ አገር ዜጋ የሆኑ ነጮች በሚመገቡበት ሆቴል ወይም ሬስቶራንት፣ በሚጠጡበት የመሸታ ወይም የቡና ቤት፣ በሚዝናኑበት የቴያትር ወይም ሲኒማ ቤት ወዘተ ኢትዮጵያዊያን እንዳይገቡ በህግ የተከለከለ ነው።

ፋሽስቶች ኤርትራን በተቆጣጠሩበት የመጀመሪያው አፍላ ዘመን አንድ ኢትዮጵያዊት ወይም ኢትዮጵያዊ ከነጭ ሰው ጋር በአንድ ተሽከርካሪ ውስጥ ሆኖ መንዝ በጥብቅ የተከለከለ ነበር።

ሆኖም በሂደት ወይም በጊዜ ርዝመት የመጓጓዣ እጥረትና ብሶት በፈጠረው የስራዎች መታወክ ምክንያት ህጉን በጥቂቱ አሻሽለው የህዝብ መጓጓዣ በሚሏቸው አውቶብሶች ውስጥ ኢትዮጵያዊያን ነጮች ከተቀመጡበት ኋላ መቀመጫ በሌለበት የተሽከርካሪው ወለል ላይ ተቀምጠው እንዲጓዙ ለመፍቀድ ተገድደዋል።

አንዲት ወይም አንድ ኢትዮጵያዊ በሚሰሩትስራ ዓይነት ወይም በሚሰጡት አገልግሎት ምክንያት ቋሚ ወይም እለታዊ የማለፊያ ፈቃደ ካልያዙ በስተቀር በነጮች መኖሪያ ሰፈርና ከተማ ከቀኑ 12 ሰዓት በኂላ መዘዋወር በህግ የተከለከለ ነው።

በአንዳች ምክንያት ተገድደው ወይም ያለማወቅ በምሽት ሲዘዋወሩ በተገኙ ኢትዮጵያዊያን ላይ ፖሊሶች ወይም የእለት ፀጥታ አስከባሪ ኃይሎች ተኩሰው ቢያቆስሏቸው ወይም ቢገድሏቸው ደማቸው ደመ ከልብ ይባላል።

አንዲት ወይም አንድ ኢትዮጵያዊ አንድ ነጭ ባደረሰበት ውርደት፣ ድብደባ ወይም በደል ደሙ ፈልቶ ኃይል ለመጠቀም ቢሞክር ነጩን ቢሰድብ ወይም ቢዘልፍ ነጩ አይጠየቅም። ኢትዮጵያዊው ግን የነጮችን ዘር በመድፈሩ በጅራፍ መገረፍ ቋሚ ደንብ ነው።

በአጭሩ ወይም በጥቂቱ ከዚህ በላይ የጠቃቀስኳቸውን ኢ-ሰብአዊ እብሪትና የግፍ ተግባሮች ክርስቲያኖች ነን፣ ሰጥነናል፣ የሰው ልጅ መብትና የዲሞክራሲ ጠበቃ ነን እያሉ በሚያደነቁሩን ከሰሜን አሜሪካ እስከ ደቡብ አፍሪካ ያሉ ዘረኞች ቋሚ ተግባራቸው አድርገው ሲፈፅሙት ያየነውና የምናውቀው ሲሆን የኢጣሊያ ፋሽስቶችን ከሌሎች የሚያብሷቸው በማናቸውም ጊዜ የስራ ቀን ሆነ ወይም በዓል ቀን ሆነ ሌሊት አንዲት ወይም አንድ ኢትዮጵያዊ ወደ አንድ የነጮች መስሪያ ቤት፣ ሱቅ ወይም መኖሪያ ቤት ወዘተ ሲገቡ ጫማቸውን አውልቀው እውጭ በመተው እንዲገቡ መደንገጋቸውና ሌሎች ዘረኞች ለአገልጋዮቻቸው ውራጅ ልብሶቻቸውን ሲለግሱ የራሳቸው ስሪት የሆነውን ኢትዮጵያዊ የባህል ልብስ ብቻ እንጂ ውራጅም እንኳ ቢሆን የአውሮፓ ስሪት ልብሶችን እንዳይለብሱ በህግ መከልከላቸው ነው።

በኤርትራ ለትምህርት ገበታ የደረሱ ኢትዮጵያዊያን ህፃናትና ጎልማሶች እንዲማሩባቸው ተብሎ ለግብር ይውጣ የተቋቋሙት የ1ኛ ደረጃ ዝቅተኛ ትምህርት

ቤቶች ሥርጭት ከህዝቡ መጠንና ፍላጎት ጋር የማይቀራረቡ ከመሆናቸው በላይ የፋሽስት ኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ መርህ ወይም (Policy) አካል የሆነው ሥርዓተ ትምህርት ኢትዮጵያዊያን ከ4ኛ ክፍል በላይ እንዲማሩ አይፈቅድም።

የፋሽስቶቹ የቅኝ አገዛዝ መመሪያ መርህ ረግጠህና አደንቁረህ ግዛ ስለሆነ የሥርዓተ ትምህርቱ ዓላማም አደንቁሮ ለመግዛት ሲሆን እስከ 4ኛ ክፍል ድረስ እንዲማሩ የተፈቀደው ለኢትዮጵያኑ ታስቦ ሳይሆን ኢጣሊያዊ ጌቶችና አሰሪዎች የሚሰጧቸውን ትዕዛዝ እንዲያዳምጡና አራት መደብ ሂሳብ ለማስላት እንዲችሉ ብቻ ተብሎ የተነደፈ ሥርዓተ ትምህርት ነው።

ለሃምሳ ዓመታት የኤርትራ ክፍለ ሃገር ህዝብ በዚህ ሁኔታ የትምህርት እድል በተነፈገበት ጊዜ ወጣቶች ከ4ኛ ክፍል በላይ የ1ኛና የ2ኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች በተለያዩ ከፍተኛ የሞያ ማሰልጠኛ ተቋማት ከፍተኛ ትምህርት መማር የቻሉት ከመረብ ወዲህ ባለቺው ሰፊዋ እናት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው።

ኢጣሊያኖች በብሪታኒያ የጦር ኃይልና በኢትዮጵያ አርበኞች በጦር ሜዳ ድል ተመትተው ከተባረሩም በኂላ ከእብሪታቸውና ከግፍ ተግባራቸው አልታቀቡም።

ጀርመኖች ድል ሆነው ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከቆመ በኂላ ድል አድራጊዎቹ የሦስቱ ኃያላን አገሮች ማለትም የሶቪየት ህብረት፣ የሰሜን አሜሪካና የብሪታኒያ መሪዎች ጀርመንውስጥ ፖስትዳም ተብላ በምትጠራዋ ትንሽ ከተማ ተሰብስበው ካሳለፏቸው ታላላቅ ውሳኔዎች አንዱ ከጀርመን ጋር ወግነው ጦርነቱ ውስጥ ከገቡት ፋሽስታዊ የአውሮፓ አገሮችጋር የእርቅ ስምምነት ስለሚደረጉበት ሁኔታዎችና አውሮፓን መልሶ ስለማረጋጋት ጉዳይ ነበር።

ከጀርመን ጋር ካበሩት ፋሽስታዊ የአውሮፓ አገሮች ዋናና ቀንደኛዋ አገር ፋሽስት ኢጣሊያ ስትሆን የቀሩት ፊላንድ፣ ሐንጋሪ፣ ሩማኒያና ቡልጋሪያ ነበሩ።

ከእነኝህ አምስት ፋሽስታዊ የአውሮፓ አገሮችጋር በሚደረጉ ስምምነቶችና በአጠቃላይም አውሮፓን በማረጋጋቱ የሠላም ጉዳይ ውስጥ አብይስፍራ የያዘው ኢትዮጵያንም የሚመለከተው የኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ ነበር።

በኂላ ፈረንሳይን የጨመሩት አራቱ ኃያላን መንግሥታት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች የእርቁንና አውሮፓን መልሶ የማረጋጋቱን ጉዳይ በወል ወይም በጋራ ለመምራት እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በመስከረም ወር 1945 ዓ.ም ለንደን ላይ ተሰብስበው የምክር ቤታቸውን ካቋቋሙና ስራ ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ በነደፉት መመሪያና የስራ ፕሮግራም መሰረት የቅኝ ግዛቶች ጉዳይ በቅድሚያ ውሳኔ ማግኘት ነበረበት።

የሂትለር ግብረ አበሮች በመሆን ከጀርመን ሠራዊት ጋር ተሰልፈው ሁለተኛውን የዓለም ጦርነት በመቀስቀስ በዓለም ላይ ለደረሰው ጥፋትና ለሰባ ሚሊዮን ህዝብ ሞት ምክንያት ከሆኑት አምስቱ አገሮች ጋር የሚደረገውን የእርቅ ስምምነት ሂደት ኢትዮጵያን ጨምሮ ሃያ አገሮች የተካፈሉበት የሰላም ጉባዔ በፈረንሳይ ዋና ከተማ በፓሪስ በተከፈተበት ጊዜ የጥፋት መልዕክተኞቹ የኢጣሊያ ፋሽስቶች «ፋሽስቶች በዓለም ላይ የፈፀሙትን ጥፋትና ወንጀል አጥብቀን የምንኮንንና ሰላም ወዳዱን የኢጣሊያ ህዝብ የምንወክል አዲስ ሪፓብሊካን ነን» በማለት ቀረቡ። እነዚህ አስመሳይ ግፈኞች ነን የሚሉትን ናቸው ብሎ በከፊልም ቢሆን ዓለም ሳያምናቸው አልቀረም።

እንደ እውነቱ ግን ኢጣሊያኖችነን የሚሉትን አልነበሩም። እነዚያው የታወቁት ወንጀለኛ ፋሽስቶች ማስክ ለብሰው ነው የቀረቡት።

በኤርትራ ህዝብ ላይ ለሃምሳ ዓመታት ሲፈፅሚቸው ከነበሩት አሰቃቂ ግፍና በደሎች ባሻገር በ1928 ዓ.ም ከኤርትራ በመንደርደር መላዋን ኢትዮጵያ በመውረር መከላከያ የሌለውን ህዝብ ለ40 ዓመታት ባዘጋጁት ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎች ማለትም በጊዜው ለዓለም እንግዳ በሆነ የአውሮፕላን ቦምብ ከመደብደብ በላይ ዓለም አቀፍ ህግ በሚከለክለው የመርዝ ጋዝ የወጉትን፣ ለእናት ሀገሩ ባለው ፅኑ ፍቅር፣ ለነፃነቱ ባለው ቀናኢነትና የተፈጥሮ የታጋይነት ወኔው ጥቃታቸውን ተጋትሮ ስለመከታቸው ግንድ አስደግፈው አንገቱን በፋስ መጥረቢያ የቀሉትን፣ እግርና እጁን አስረው አውሮፕላን ላይ በመጫን ከሰማይ ወደ ምድር የወረወሩትንና በህይወት እያለ ከአንገቱ በታች መሬት ውስጥ ቀብረው ጌኛ የነዱበትን ህዝብ አፍረውና ተፀፅተው በእርቁ ሸንጎ ላይ ይቅርታ ይጠይቁታል ተብሎ ሲታሰብ ያለአንዳች ሀፍረትና ይሉኝታ የኤርትራን ህዝብ ነፃነትና ከእናት ኢትዮጵያ ጋር መልሶ ለመዋሀድ ያለውን ፍላጎት ቀንደኛ ተፃራሪ ሆነው ቆሙ።

የአራቱ ኃያላን አገሮች ተወካይ የሆኑት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ለመጀመሪያ ጊዜ በለንደን ከተሰበሰቡበት ጊዜ ጀምሮ ኤርትራ ነፃ ሆና ከእናቷ ከኢትዮጵያ ጋር ተመልሳ በፌዴሬሽን እንድትዋሀድ የተባበሩት መንግሥታት 5ኛ ጉባዔ ሕዳር 23 ቀን 1943 ዓ.ም እስከወሰነበት ታሪካዊ እለት ድረስ የኢጣሊያ ፋሽሽቶች አረቦችንና የላቲን አሜሪካ አገሮችን በሙሉ ማለት ይቻላል በፀረ ኢትዮጵያ ግንባር አሰልፈው ታገሉ።

የቆሙለት ፀረ-ኢትዮጵያ እኩይ ዓላማቸው ስኬታማ ይሆን ዘንድ የተለመደና በሀሰት ላይ የተመሰረተ ፀረ-ኢትዮጵያ ፕሮፓጋንዳ ከማካሄድ ባሻገር ለቀድሞው ባህረ ነጋሽ ለሚባለው የኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍለ ሃገር ኤርትራ የተሰኘ ስም እንደመስጠታቸው ሁሉ ዳግም ስለ ኤርትራ ህዝብ ማንነትና ምንነት ራሳቸው የፈጠሩትን አስገራሚ ታሪክ ብጤ መጽሃፍ አዘጋጅተው ለተባበሩት መንግሥታት አባል አገሮች በመበተን ዓለምን ለማሳሳት ሞከሩ።

እውነት ትከሳለች እንጂ አትሞትም እንዲሉ ፋሽስቶች በጦር ሜዳ በሰፈሩት ቂና ከመሰፈራቸው በላይ ኤርትራን ከእናቷ ከኢትዮጵያ ጋር መልሶ ለማዋሀድ በተደረገው የፖለቲካ ትግልም ዳግም የኢትዮጵያ ህዝብ አሸነፈ።

ስለኢጣሊያኖች ማንነትና ምንነት ለመግለፅ ከተፈለገ አንድ ትልቅ መፅሀፍ ለመፃፍ ሲቻል ዓላማዬ የእነሱን በወንጀል የታጀለ ፋሽስታዊ ታሪክ ለመተረክ ስለአልሆነ ማንነታቸውን ለአዲሱ ትውልድ ለማሳወቅ ያህል ይበቃል።

ምዕራፍ አስራ አራት

የኢትዮጵያን አርበኞች የነፃነት ተጋድሎ አግዛለሁ ብሎ የመጣው የብሪታኒያ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ሠራዊት እንደ ቅኝ ገዥ ኢጣሊያኖችን ተክቶ በኤርትራ በቆየባቸው አስር ዓመታት ውስጥ የፈጠራቸው ችግሮች።

የብሪታኒያ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት እንደ ቅኝ ገዥ በኤርትራ ለአስር ዓመታት የተከለው ወታደራዊ አስተዳደር የኤርትራ ክፍለ ሃገር ህዝብ በነፃነት ከእናት ኢትዮጵያ ጋር መልሶ ለመዋሀድ የሚያደርገውን ትግል ለማዳከምና ብሎም ለማክሸፍ የፈጠረው ችግር ከፋሽስት ኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ የከፋ እንጂ የሚሻል አልነበረም።

የብሪታኒያ መንግሥት እንደ ቅኝ ገዥ በኤርትራ በቆየበት የአስር ዓመታት ጊዜ ክልል ያከናወናቸውን እኩይ ተግባሮች ወደ መተረኩ ከማምራቴ በፊት አሁንም የኢትዮጵያ አዲስ ትውልድ ያውቀው ዘንድ የብሪታኒያ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ከ18ኛው ምዕተ ዓመታት አጋማሽ ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ መንግሥትና ህዝብ ህልውና፣ ታሪክና ደህንነት ላይ የፈፀማቸውን ክህደቶች፣ ሻጥሮችና ሸፍጦች አጠርና ጠቅለል ባለ ሁኔታ ለማስታወስ እወዳለሁ።

በትግላችን ቅፅ አንድ እንደተገለፀውና አንባቢም እንደሚያስታውሰው በኢጣሊያ ህዝብ የፖለቲካሥልጣን ማማ ላይ ሲፈራረቁ የነበሩ ፋሽስታዊገዥ መደቦች የአፍሪካን ቀንድ በአጠቃላይና ኢትዮጵያን በተለይ ቅኝ ግዛታቸው ለማድረግ በመመኘት ለዘጠና ዓመታት ያህል ሲያጠኑን ሲሰልሉንና ለወረራም ሲዘጋጁ ቢኖሩም በአውሮፓ የብሪታኒያ መንግሥት ዋና ተፎካካሪ ወይም ተቀናቃኝ የሆነው የፈረንሳይ መንግሥት በአፍሪካ ቀንድ ተስፋፍቶ እንዳይጋፋው የኢጣሊያንን መንግሥት ገፋፍቶና ስቦ ለወረራ ያነሳሳው ብቻ ሳይሆን ግብፃችን አነሳስቶ የምፅዋን ወደብ እንዲቆናጠጥ ያደረገው የብሪታኒያ መንግሥት ነው ካልኩ በኋላ የብሪታኒያ መንግሥት በክህደትና በሸፍጥ መርህ (ፖሊሲ) ላይ የተመሰረቱ ተለዋዋጭ አቋሞቹን ከዚህ እንደሚከተለው በአጭሩ ለመግለፅ እሞክራለሁ።

ፋሽስት ኢጣሊያን ገፋፍቶ ካስወረረን በኋላ ቤንቶ ሙሶሎኒ በ1928 ዓ.ም ሠራዊቱ አዲስ አበባን በተቆጣጠረ ማግሥት ከዛሬ ጀምሮ ኢትዮጵያ የሮም ቄሳራዊ መንግሥት ቅኝ ግዛት መሆኗን ለዓለም እናስታውቃለን ብሎ በደነፋ ጊዜ ወረራውን በመደገፍ ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት መሆኗን ካወቁት መንግሥታት የመጀመሪያው ነበር።

ወረራው ከመደረጉ በፊትና በወረራው ሂደት ውስጥ ተጠቂዋ ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት ሊግ ውልና ህግ መሰረት በተባበሩት መንግሥታት ሊግ አባልነቷ ማህበሩ ሊሰጣት የሚገባውን ፍርድና እንዲሁም ድጋፍ ብቻ ሳይሆን ራሷን ለመከላከል የጦር መሳሪያ አምራች የሆኑ የአውሮፓ መንግሥታትና ሰሜን አሜሪካ መሳሪያ እንዲሸጡላት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ያቀረበውን ጥያቄ

ለፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት ወግነው የመሳሪያ ማዕቀብ ካደረጉት አገሮች አሁንም የመጀመሪያው ነበር።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መቃረቢያ በብሪታኒያ መንግሥት ባለሥልጣኖች ዘንድ እንደ ትልቅ ወዳጅ ይታይ የነበረው የፋሽስት ኢጣሊያ መሪ ቤንቶ ሞሶሊኒ ከድቶ ከሂትለር ጋር በመሰለፉ በአውሮፓ አገሮች ላይ ጦርነት አውጆ ውጊያው በሚካሄድበት እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1940 ዓ.ም መባቻ ላይ ፋሽስት ኢጣሊያን ለመበቀል የኢትዮጵያን ፀረ-ፋሽስት አርበኞች የትጥቅ ትግል ለመደገፍ የብሪታኒያ መንግሥት ከወሰነ በኋላ የኢትዮጵያን ነፃነትና ሉአላዊነት አስመልክቶ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አንቶኒ ኤደን በዚያው ዓመት በየካቲት ወር በብሪታኒያ ህዝብ ምክር ቤት የተናገረውን ከዚህ እንደሚከተለው እገልፃለሁ።

«የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መንግሥት የኢትዮጵያን እንደገና ነፃ መንግሥት መሆን ይቀበላል። የአፄ ኃይለ ሥላሴንም ወደ ዙፋናቸው መመለስ ያከብራል። ንጉሠ ነገሥቱም የውጭ አገር እርዳታና ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው የኔ ሚኒስትር ለግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መንግሥት አስታውቋል።

የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መንግሥት ያመነበትና የፈቀደው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ወዘተ ድጋፍ ከጦርነቱ በኋላ በዓለም አቀፍ ስምምነት እንዲሆን ይደረጋል።

የግርማዊ ንጉሠ መንግሥት በኢትዮጵያ የግዛት ፍላጎት የሌለው መሆኑን ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት እንደገና ያረጋግጣል» የሚል ነበር።

የብሪታኒያ መንግሥት የፋሽስት ኢጣሊያን ወራሪ ሠራዊት ከአፍሪካ ቀንድ ወግቶ ለማስወጣት ካዘመተው 325 000 ሦስት መቶ ሃያ አምስት ሺህ ሠራዊት የሕንድና የፓኪስታን ዜጎች መሳውን ያሉበት የእንግሊዝ ዜጋ የሆኑት ወታደሮች ወደ አንድ መቶ ሺህ ሲገመቱ 225,000 ሁለት መቶ ሃያ አምስት ሺዎቹ ሱማሌዎችን ጨምሮ ከቅኝ ግዛት አገሮች የተመለመሉ አፍሪካዊያን ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል በሁሉቱም ተፋላሚ ጎራዎች የተሰለፉት ኢትዮጵያዊያን ቁጥር በጣም ያመዝን የነበረው ዋናውን ተዋጊ ኃይል የኢትዮጵያን ፀረ ፋሽስት የአርበኞች ጎራ ሳይጨምር ነው።

የሠራዊቱ የኃይል ሚዛን ይህንን የመሰለ በመሆኑና የብሪታኒያ የጦር ኃይል አዛገሮች ዘመቻው ስኬታማ እንዲሆን ያቀዱት በአብዛኛው ኢትዮጵያዊያን ደም ስለነበረ በዘመቻው ጊዜ ማለትም እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ከ1940 ዓ.ም እስከ 1941 ድረስ በነበረው የጊዜ ክልል ውስጥ በተለያዩ ዘዴዎችና በተለይም ከተዋጊ አውሮፕላኖች በሚበተኑ ወይም በሚረጩ በራሪ ጽሁፎች ለኢትዮጵያ ህዝብና መንግሥት የፈነጠቁትን ተስፋና የገቡትን ቃል ከዚህ እንደሚከተለው እገልፃለሁ።

በኢጣሊያ ሱማሌ ላንድና በኤርትራ በፋሽስቶች የቅኝ አገዛዝ ቀንበር ውስጥ ለነበሩት ህዝቦች በስደተኛው በአፄ ኃይለሥላሴ ስምና መንግሥታዊ አርማ ከብሪታኒያ የጦር አይሮፕላኖች በብዛትና በስፋት ለወራት የተበተነውን አዋጅ እጠቅሳለሁ፣ «ከመረብ ወዲያና ወዲህ ያላችሁ ሁሉ ከወንድሞቻችሁ ከኢትዮጵያዊያን ጋር ተባበሩ። ከእንግዲህ ወዲህ አንዳችሁም የጠላታችሁ የፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥትና የግፈኛው ወራሪ ሠራዊት መሳሪያ አትሁኑ።

ኢትዮጵያን እናታችሁንና ወዳጃችንን የብሪታኒያ መንግሥት ሠራዊት አትውጉ። የልባችሁን ምኞት አውቃለሁ። የእናንተ ምኞት የኢትዮጵያ ህዝብ ምኞት ነው። እድላችሁም ከተቀረው ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በፅኑ የተሳሰረ ነው በሚል አንድን አገር ወይም መላዋን ኢትዮጵያ ነፃ ለማውጣትና ብሎም ለህዝቦቿ አንድነት የተደረገ ቅስቀሳና የትግል ጥሪ ነበር የብሪታኒያ ባለሥልጣኖች በአዋጅ የለፈፉት።

የእንግሊዝ የጦር ባለሥልጣኖች በኤርትራ ውስጥ ከፋሽስት ኢጣሊያ ሠራዊትና ለኢጣሊያ መንግሥት ካደሩት ኢትዮጵያዊያን ጋር በሚዋጉበት ጊዜ ደግሞ ለኤርትራ ክፍለ ሃገር ህዝብ በተለይ ያደረጉትን ቅስቀሳ፣ የትግል ጥሪ፣ ለኢትዮጵያ የተሟላ ነፃነትና አንድነቷ የፈነጠቁትን ተስፋና የቃል ዋስትና ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት፣

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በመጋቢት ወር 1941 ዓ.ም ከረን ላይ ኢጣሊያኖች የመጨረሻውን ብርቱ የመከላከል ውጊያ በሚያደርጉበት ጊዜ የእንግሊዝ የጦር አዛዦች ለኤርትራ ክፍለ ሃገር ህዝብ ያሉትን እጠቅሳለሁ።

«የኤርትራ ህዝብ ሆይ! የራሳችሁ ሰንደቅ ዓላማ ሊኖራችሁ ይገባል። የጦር መኮንኖች ልትሆኑ ይገባችኋል። ኢጣሊያኖች ካሸከሟችሁ በበለጠና ጥራት ባለው የጦር መሳሪያ ልትዋጉ ይገባችኋል።

የተሸነፉትን ኢጣሊያኖች ጠላቶቻችሁን እየተዋችሁ ወደ እኛ ብትመጡ እኛ እነዚህን የምትመኟቸውንና የምትፈልጓቸውን ሁሉ እንሰጣችኋለን። ሁልጊዜ በኢጣሊያኖች ጦርና መትረየሶች ፊት ከመሄድ ይልቅ የራስን አገርና ህዝብ አገልጋይ መሆንና የኔ መንግሥት ብሎ መጥራት ከኢጣሊያ ባርነት ነፃ መውጣት፣ የራሳችሁ የጦር ሠራዊት አዛዥ መሆን፣ በራሳችሁ የመከላከያ ሠራዊት ውስጥ የታንክ ነጂና የጦር አውሮፕላኖች አብራሪ መሆን ለኤርትራዊያን ኩራት፣ የከበረ ስምና ህይወት ነው» ነበር ያሉት።

በእነዚህ እስከ አሁን በገለፅኳቸው የብሪታኒያ መንግሥት፣ የሲቪልና የጦር ባለሥልጣኖች በተለያዩ ጊዜያትና በመደጋገም በሰጡት ተስፋና በገቡት ቃል መሰረት ኤርትራን ብቻ ሳይሆን ሱማሌንም ጭምር ከእናታቸው ከኢትዮጵያ ጋር በነፃነት

ተመልሰው እንዲዋሀዱ ይደረጋል በማለት ንጉሡን ጨምሮ ብዙ ኢትዮጵያዊያን ትልቅ ተስፋ አድሮባቸው ነበር።

ሆኖም በሱማሌዎች፣ በኤርትራ ክልል ነዋሪ ህዝብ፣ በኢትዮጵያ ፀረ- ፋሽስት አርበኞችና በኋላም ከብሪታኒያ ሠራዊት ጋር አገራቸውን ነፃ ለማውጣት በተሰለፉ ወደ ዘማቾች ኢትዮጵያዊያን ህብረትና ደም የብሪታኒያ የጦር መኮንኖች ውጊያውን አሸንፈው ደቡብ ሱማሌንና ኤርትራን ከተቆጣጠሩ በኋላ የኦጋዴንም ክልል በመጨመር ደቡብ ሱማሌን ቀደም ብለው ቅኝ ግዛታቸው ካደረጉት ከሰሜኑ ሱማሌ ጋር ቀላቅለው ሲይዙ ኤርትራንም ከኢትዮጵያ ነጥለው ቅኝ ግዛታቸው በማድረግ ወታደራዊ አስተዳደር መሰረቱ።

ይህንን አስመልክቶ የኢትዮጵያ መንግሥት ላቀረበው ጥያቄ የተሰጠው መልስ ከዚህ እንደሚከተለው ነበር። እጠቅሳለሁ

«በህግ ረገድ ዛሬም ቢሆን ኤርትራ የኢጣሊያ መንግሥት ቅኝ ግዛት ነች። በ1896 ዓ.ም በንጉሥ ምንሊክና በኢጣሊያ መንግሥት መካከል በተደረገው ውል ኤርትራ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት መሆኗን ኢትዮጵያ ተቀብላለች።

ከእንግዲህ ወዲህ የኤርትራ ህዝብ እድል የሚወሰነው ከዓለም ጦርነት ፍፃሜ በኋላ የጦርነቱ አሸናፊ የሆኑት አራቱ ኃያላን መንግሥታት የኢጣሊያ ቅኝ ለነበሩት አገሮች ሁሉ የሚሰጡት አጠቃላይ ውሳኔ እስከሚገኝበት ጊዜ ድረስ ኤርትራ በታላቋ ብሪታኒያ ወታደራዊ አስተዳደር ሥር ትተዳደራለች» የሚል ነው።

ኤርትራ በነበረው ፋሽስት ኢጣሊያ ሠራዊት ላይ የብሪታኒያ ወታደራዊ ግብረ ኃይል ድልን ተቀዳጅቶ ኤርትራን ከተቆጣጠረ በኋላ ለሠራዊቱ መኖሪያ የኢጣሊያንን የጦር ሰፈሮች ለወታደራዊው መንግሥት የአመራር አካላትና ከፍተኛ መኮንኖች የፋሽስት ኢጣሊያ የአመራር አካላት ይዞታ የነበሩትን መኖሪያዎች ከመስሪያ ህንፃዎች ጋር የፖለቲካውን ላእላይ መዋቅር ወይም አመራር በመረከብ ታህታይ መዋቅሩን በሙሉ ለኢጣሊያኖች ነው የተወላቸው።

መሬት፣ ማዕድን፣ ኢንዱስትሪ፣ ግብርናው ወዘተ ጠቅላላው የኢኮኖሚና የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት በኢጣሊያኖች ሥልጣንና ይዞታ ስር እንዳሉ ሆነው የሚጠቀሙባቸው፣ የሚያስተዳድሯቸውና እንደተለመደውም በኢትዮጵያዊያኑ ላይ አዛዥና ናዛዦች ኢጣሊያኖች ነበሩ።

ኢጣሊያኖች ሲፈፅሟቸው የነበሩት ግፍና በደሎች የብሪታኒያ መንግሥት በኤርትራ ህዝብ ላይ የቅኝ ገዥነት ሥልጣን የተሰጠው ወታደራዊ መንግሥት ጊዜም መለወጥ ቀርቶ ሳይሻሻሉ እንደቀጠሉ ነበሩ።

ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጋር የመጣው የብሪታኒያ መንግሥት ሠራዊት ኢትዮጵያዊነታችንን ሊያስመልስልን የመጣ ነፃ አውጭ ወዳጅ አድርጎ መመልከት ብቻ ሳይሆን አብሮ ተዋግቶ፣ ደምቶና ሞቶ በደስታ ከተቀበለው በኋላ ከፋሽስት ኢጣሊያ ጋር አብሮ ጭቆናና ረገጣውን በመቀጠሉ እጅግ ያዘነውና የተከፋው የኤርትራ ክፍለሃገር ህዝብ አዲስና ሌላ የትግል ምዕራፍ ውስጥ እንደገባ በመገንዘቡ ወዲያው በሚያዚያ ወር 1941 ዓ.ም መላውን የኤርትራ ህዝብ አሰባስቦና አስተባብሮ ትግሉን የሚመራ የኢትዮጵያ ህዝቦች አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር የተሰኘ የፖለቲካ ድርጅት አቋቋመ።

ምዕራፍ አስራ አምስት

የኢትዮጵያ ህዝቦች አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር

«ኢትዮጵያ ወይም ሞት» በተሰኘ ዓላማ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በኤርትራ የተቋቋመ የፖለቲካ ድርጅት ያለ አንዳች ገደብ ወይም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ ከእናት ኢትዮጵያ ጋር መልሰን እንዋሀድ በማለት የእንግሊዝንና የኢጣሊያኖችን ጥምር ቅኝ አገዛዝ በፅኑ የሚቃወምና ሁለቱም በአስቸኳይ ከኤርትራ እንዲወጡ የሚጠይቅ ሌላ አቻ ወይም አንጻ የሌለውና የመላውን ኤርትራ ህዝብ ድጋፍ ያገኘ ብቸኛ የፖለቲካ ድርጅት ነበር።

እዚህ ላይ መታወስ ያለበት ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛቱ እንዲያደርግ ስለረዳሁት ከጀርመኖች ተነጥሎ ከጎኔ ይሰለፋል ብሎ ያመነው ቤንቶ ሞሶሊኒ ከድቶት ከዋና ጠላቱ ከጀርመን ጋር በመሰለፍ የወጋውን የኢጣሊያ መንግሥት በመበቀል ከአፍሪካ የቅኝ ግዛቱ ለማባረር የብሪታኒያ መንግሥት ሲወስን ውሳኔውን በተግባር የሚያስፈፅሙት የጦር መኮንኖች ደግሞ በበኩላቸው ኤርትራንና ሱማሌን ጨምረው መላውን የአፍሪካ ቀንድ ከምስራቅ አፍሪካ የብሪታኒያ ቅኝ ግዛት አገሮች ጋር በመጠቅለል አንድ ለምና ሰፊ ኩታ ገጠም መንደላቀቂያ የቅኝ ግዛት ክልል የመፍጠር ስውር ዓላማ ስለነበራቸው ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያንን መከፋፈልና ማዳከም ነበረባቸው።

ስለሆነም «ኢትዮጵያ ወይም ሞት» ብሎ በማምረር ሊታገላቸው የተነሳው የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር ዓላማ ግቡን እንዳይመታ በበኩላቸውም አምርረው መታገል የጀመሩት የአንድነት ማህበሩ ከተቋቋመበት እለት ጀምሮ ነው።

ሆኖም ፋሽስት ኢጣሊያ በሃምሳ ዓመታት ግፍና እብሪት በተሞላው የቅኝ አገዛዝ ሥርዓቱ የኤርትራን ህዝብ አንድነት፣ ኢትዮጵያዊነት፣ ኢትዮጵያዊ ባህል፣ ቋንቋ፣ ልዩ ልዩ ወግና ልማዶቹን፣ ሥነ ልቦናውን፣ ታሪኩንና ማህበራዊ መሰረቱን ለመናድና ለመለወጥ እንዳለመቻሉ ሁሉ የብሪታኒያ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት በኤርትራ ህዝብ ላይ የመሰረተው ወታደራዊ ቅኝ አስተዳደር የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር ንቅናቄ ሊገታ አልቻለም።

የአንድነት ማህበሩ እንደ ፖለቲካ ድርጅት ህልውናው በኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ የመጀመሪያ ብቻ ሳይሆን የኤርትራን ክፍለ ሃገር ህዝብ ከተቀረው ወገኑ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር መልሶ እንዲዋሀድ በመቀስቀስ፣ በማንቃትና በማደራጀት ረገድ ያከናወነው ተግባርም እንዲሁ በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ አዲስና ታሪካዊ ክስተት ነበር።

የማህበሩ አመራር አካላት የክልሉ ህዝብ ወትሮም የነበረውን የሃገር ፍቅር ስሜት ከመቀስቀስና ከማዳበር በላይ ህዝቡን አክራሪ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኛ አድርገውት ነበር።

የኤርትራ ህዝብ ለአንድነት ባደረገው ትግል «ኢትዮጵያ ወይም ሞት» የሚል መፈክሩን በመፈክር ደረጃ ብቻ አላቆመም።

በቀብር ሥርዓት ጊዜ የሙታን አፅም ወይም አስከሬን የሚለብሰው የኢትዮጵያን አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ቀለም ሰንደቅ ዓላማ ነበር።

በሀዘንም ጊዜ ሆነ በደስታ፣ በሠርግም ሆነ በተስካር ወዘተ ቤቶች፣ መሰብሰቢያ ዳሶችና ድንኳኖች የሚዋቡት በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ነበር።

በፖለቲካም ይሁን በባህላዊ በዓላት ቀናት መላው የኤርትራ ህዝብ መኖሪያ ወይም መጠለያ ቤቶችና ጎጆዎች በራፍ፣ ደጃፍና ወይም ከቤቱ ፊት ግድግዳ ላይ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተተክሎ ወይም ተሰቅሎ ይውለበለባል።

አንባቢ እንደሚያስታውሰው በከረን ጦርነት ጊዜ እጠቅሳለሁ «ኤርትራዊያን ሆይ! የራሳችሁ ሰንደቅ ዓላማ ሊኖራችሁ ይገባል፣ ሁልጊዜ በኢጣሊያኖች መትረየስ ፊት ከመሄድ ይልቅ የራስን አገርና ህዝብ ማገልገል፣ የኔ መንግሥት ብሎ መጥራት፣ ከኢጣሊያን ባርነት ነፃ መውጣት» ወዘተ ሲሉ የነበሩት የእንግሊዝ ወታደራዊ ባለሥልጣኖች በምንገዛው ቅኝ አገር እንዴት የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ሲተከል፣ ሲንጠለጠልና ሲውለበለብ እናያለን በማለት ባደረባቸው ፅኑ ጥላቻና ቁጣ ለወታደሩ በሰጡት ትዕዛዝ መሰረት ፖሊስና ወታደሮች በየቤቱ ደጃፍና በራፍ የተተከሉትን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማዎች እየነቀሉ ለመጣል ያደረጉትን ሙከራና ያሳዩትን ድፍረት በደም ፍላት የተቃወሙ ኢትዮጵያዊያን በፈጠሩት አመፅ በየጊዜው ህይወታቸውን ያጡ ጥቂት እንዳይደሉ ይነገራል።

በማናቸውም ፖለቲካዊና ባህላዊ በዓል ቀናት ብቻ ሳይሆን ስፖርቶችን በመሰሉ ህዝብን በሚያሰባስቡ ምክንያቶች በተለይም የፖለቲካ ይዘት ባላቸው ህዝባዊ ሰልፎች ወዘተ ወንዶች በኢትዮጵያ ባህላዊ እጀ ጠባብ ልብሳቸው ላይ የሚያደርጏቸው ኩታዎች፣ ሴቶች የሚለብሷቸው ቀሚሶችና የሚደርቧቸው ነጠላ ወይንም ኩታዎች በሙሉ ማለት ይቻላል አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ቀለማት ጥለቶች የተሸመኑ ናቸው።

ወታደራዊ ቅኝ ገዥዎቹ የብሪታኒያ ባለሥልጣኖች በህዝቡ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት በመበሳጨት የአንድነት ፓርቲው ጠላትና ፀሩ ሆኑ።

ኤርትራ የዘመተውን ወታደራዊ ግብረ ኃይል የመሩና በፋሽስት ኢጣሊያ ሠራዊት ላይ ድልን የተቀዳጁት የብሪታኒያ መኮንኖች በኤርትራ ወታደራዊ ቅኝ አገዛዝ አስተዳደር ሲመሰርቱ እንዲህ ያለ በኢትዮጵያዊ ብሄራዊ ስሜት ልቡ የነደደ ታጋይና አይበገሬ ህዝብ ያጋጥመናል ብለው አልገመቱም።

ኢትዮጵያዊ ስሜቱንና እምነቱን ለማዳከም የሚቻል መስሏቸው በኤርትራ ምድር የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ እንዳይውለበለብ ብቻ ሳይሆን አንድም ኤርትራዊ በማናቸውም ጊዜ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ይዞም ሆነ ለብሶ እንዳይታይ የሚከለክል ህግ አወጁ።

ከመረብ ወንዝ ወዲያም ወዲህም ነዋሪዎች አንድ ህዝብ ከመሆናቸው ባሻገር ብዙዎቹ በስጋ ዝምድናና በጋብቻ የተሳሰሩ ቤተሰብም በመሆናቸው ሲያደርጓቸው የነበሩትን ማናቸውንም ግንኙነቶች በህግ ከማገዳቸው ሌላ የኢትዮጵያ መንግሥት በአስመራ የህዝብና የመንግሥት ግንኙነት ጽህፈት ቤት ለመክፈት ቢጠይቅም ከለከሉ።

ይህንና ይህንን የመሳሰሉትን ጭቆናዎችና የመብት ረገጣዎች አንቀበልም በማለት የተቃወሙና የታገሉ ኤርትራዊያንን በአጠቃላይ፣ የአንድነት ፓርቲ አባላትንና የአመራር አካላትን በተለይ ማዋከብ፣ ማሰርና አልፎ አልፎም መግደል ሲጀምሩ አፄ ኃይለሥላሴ እንደተመኙት እንግሊዞች በሰላም ከኤርትራ ለመውጣት ፈቃደኛ ያለመሆናቸው በመታመኑ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር ራሱንና ህዝቡን ከጥቃት ለመከላከል በትግራይና በጐንደር ወታደራዊ ክንፍ ማደራጀት ጀመረ።

ምዕራፍ አስራ ስድስት

በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ የመሃል አገሩ ሁኔታ

በኤርትራ የብሪታኒያ ወታደራዊ ቅኝ አገዛዝ ከተመሰረተ ጀምሮ የመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት ሁኔታው ይህንን በመሰለ የቅራኔ ደረጃ ሲገኝ በመሀል ኢትዮጵያም ያለው ሁኔታ ከኤርትራ የሚሻል አልነበረም ማለት ይቻላል።

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ከ1941 እስከ 1944 ዓ.ም ድረስ የብሪታኒያ መንግሥት በኢትዮጵያ ከተከለው ወታደራዊ ቅኝ አገዛዝ ነፃ ለመውጣት የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በትግል ላይ ነበር።

በዚህ ጊዜ ውስጥ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት አልተጠናቀቀም፣ አዲሱ የዓለም መንግሥታት ማህበር ጽሕፈት ቤት በመደራጀት ላይ ነበር እንጂ የማህበሩ ጉባዔ ተጠርቶ ማህበሩ በይፋ አልተቋቋሙም።

የፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት ቅኝ የነበሩትን አገሮች ጉዳይ ኤርትራንና ሱማሌን ጨምሮ የወደፊት እድላቸውን ይወስናሉ ተብለው በሚጠበቁት የጦርነቱ አሸናፊ በሆኑት በአራቱ ኃያላን መንግሥታት ኮሚቴ ነው።

ይህም በመሆኑ የብሪታኒያ መንግሥት ብቻ ሳይሆን ኤርትራም ያሉት ወታደራዊ ቅኝ ገዥዎች የኢጣሊያ ቅኝ የነበሩትን አገሮች ጉዳይ ከእነሱ ብሄራዊ ጥቅም አኳያ ከአሜሪካና ከፈረንሳይ ጋር እየመከርን እንዳሻን እናደርገዋለን የሚል እምነት ነበራቸው።

በዚህ ጊዜ ማለትም በመጀመሪያው አምስት ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር በኤርትራ አንድም የፖለቲካ ተቀናቃኝ ወይም ተወዳዳሪ አንጃ የሌለበት ብቸኛ የፖለቲካ ድርጅት ከመሆኑ ሌላ ቆለኛና ደገኛ በተሰኘ የአካባቢ ስሜት እስላምና ክርስቲያን በተሰኘ የሃይማኖት ልዩነት ሳይከፋፈል መላው የኤርትራ ክልል ህዝብ ማለት ይቻላል በአንድ ፓርቲ ድርጅት ውስጥ ተካቶ ከአንድ ፓርቲ አመራር የሚያገኝ ነበር።

የኢጣሊያን ቅኝ ግዛት አገሮች በተመለከተ የብሪታኒያ መንግሥት የአብዛኛው ኃያላን መንግሥታት ይሆናል ብሎ የገመተው አቋምና አመለካከት እንደጠበቀው ሳይሆን ቀርቶ የፈረንሳይ መንግሥት ጉዳዩን ከራሱ የቅኝ ግዛቶች ጉዳይ ጋር እያነፃፀረ ከሶቪየት ህብረት መንግሥት ጋር ከመቆሙ ሌላ የአሜሪካን መንግሥትም ከመረጃ እጥረትና ከልምድ ውሱንነት የተነሳ መፍትሄ ብሎ የሚያቀርባቸው ሃሳቦች ከብሪታኒያ መንግሥት እቅድና ፍላጎት ጋር የሚገጥሙ አልነበሩም።

የኢጣሊያ ቅኝ በነበሩ አገሮች ጉዳይ ላይ ተወያይተው የጋራ ውሳኔ መስጠት ያለባቸው ኃያላን መንግሥታት በቅድሚያ የኤርትራን ህዝብ አቋምና ፍላጎት መርምሮ የሚያቀርብላቸው መርማሪ ኮሚሽን ወደ ኤርትራ ለመላክ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር የካቲት 15 ቀን 1947 ዓ.ም ፓሪስ ላይ በተደረገው ጉባዔ ላይ በወሰኑ ጊዜ ነው በኤርትራ ያለው ወታደራዊ አስተዳደር የኤርትራንና የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት ብቻ ሳይሆን የኤርትራን ህዝብም አንድነት ማፈራረስ የጀመረው።

የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር መስራችና የአመራር አካላት የሆኑ አንዳንድ ግለሰቦችን እያሳሳቱ ከማህበሩ በማስኮብለል፣

1ኛ. የኤርትራ ህዝብ ከተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ለመዋሀድ ያለውን ፍላጎት በመቃወም በእንግሊዝ መንግሥት የሞግዚት አስተዳደር ስር እንቆይ በሚሉና በሃይማኖት ልዩነት ራሳቸውን ከአንድነት ፓርቲው ለማግለል የእስልምና እምነት ተከታይ የሆነውን የኤርትራ ምዕራባዊ ቆላ ነዋሪ ህዝብ በከፊልም ቢሆን «እስላማዊ ሊግ» ብሎ ራሱን የሚጠራ፣

2ኛ. ከክርስቲያኑ መካከልም የአንድነት ፓርቲው መስራች የአመራር አካልና አባል የሆኑትን ታዋቂ ሰዎች በማስኮብለል ከተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር መዋሀድን በመቃወም ነፃነት የሚልና ራሱን «ሊብራል ፕሮግረሲቭ» ብሎ የሚጠራ ድርጅት በኤርትራ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ሁለት አንጃ ድርጅቶችን ሁለገብ በሆነ ድጋፍና ግፊት ፈጠረ።

ከእነዚህ ጥቂት ዘግየት ብሎ የተቋቋመው «የምዕዋ እስላሞች ሊግ» የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነት ከሚፃረሩ የምዕራቡ ቆላ ነዋሪዎች «እስላም ሊግ» ራሱን ያገለለ ሲሆን አራተኛው፣ በጊዜው በኤርትራ ከነበሩ የኢጣሊያ ዜጎች፣ ከኢጣሊያዊያንና ከኢትዮጵያዊያን የተወለዱ ክልሶችና በኢጣሊያ መንግሥት የቅኝ አገዛዝ ዘመናት በውትድርና ሲያገለግሉ ቆይተው ጡረታ ላይ የነበሩ ሰዎችን አሰባስበው እንደ ደቡብ ሱማሌ የኢጣሊያ መንግሥት በሞግዚትንት ያስተዳ ድረን የሚል ቡድን በኢጣሊያ ግፊትና የገንዘብ እርዳታ የፖለቲካ ህልውና ሊሰጡት የሞከሩት የኢትዮጵያን አን ድነት የሚቃወመውን ጎራ ያበራከቱላቸው መስሏቸው ነው።

በእንዲህ ያለ ሁኔታ አንዱን ህዝብ በተለያየ የፖለቲካ ዓላማ በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ማደራጀት ብቻ ሳይሆን የኤርትራ ክልል በብሪታኒያ ቅኝ አስተዳደር ስር የማይቆይ ከሆነ በሃይማኖት፣ በጎሳና በአካባቢ ስሜት ቆለኛውንና የእስልምና እምነት ተከታይ የሆነውን ከሱዳን ጋር እንዲቀላቀል፣ ደገኛውንና በአመዛኙ ክርስቲያን የሆነውን ከትግራይ ክፍለ ሃገር ጋር በመቀላቀል ትግራይ ትግሪኝ የተሰኘና ከኢትዮጵያ የተነጠለ ነፃ መንግሥት ለመፍጠር የተለያዩ የፖለቲካ ስልት በማውጣት የኤርትራ ህዝብ ከተቀረው ከወገኑ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ያለአንዳች ገደብና ቅድመ ሁኔታ ለመዋሀድ የነበረው ምኞትና ፍላጎት ተገድፎ ወይም ተገፍቶ መፍትሄው

በፌደሬሽን መተሳሰር እንዲሆን የተባበሩት መንግሥታት 5ኛ ጠቅላላ ጉባዔ ይወስን ዘንድ ምክንያት መፍጠር ቻሉ።

በኤርትራ የኢምፔሪያሊስት ብሪታኒያ ወታደራዊ የቅኝ ግዛት መስተዳድር የመሩ መኮንኖች በጥቂቱ ከዚህ በላይ የገለፅኳቸውን ፀረ-ኢትዮጵያ መሰሪ ተግባሮችን ያከናወኑ የነበሩት ከብሪታኒያ ማዕከላዊ መንግሥት ከለንደን ትዕዛዝና መመሪያ እየተሰጣቸው አልነበረም።

ከአገራቸው ከወታደሩ መኖሪያ የጦር ሰፈሮች ወጥተው በቅኝ ግዛት አገሮች ቤተመንግሥትና ታላላቅ ቪላዎች ውስጥ እንደልባቸው መንደላቀቅ፣ በአገራቸው አንድ ኪሎ ግራም ስጋ ለመግዛት ከሚከፍሉት ባነሰ ገንዘብ የበግና የፍየል ጠቦት መብላት፣ በአፍሪካ ዱሮች ውስጥ የሚፈነጩትን ዝሆኖች፣ ጎሾች፣ ቀጭኔዎችና አጋዘኖች ወዘተ እያደኑ መጫወትና ዓመቱን በሙሉ ማለትም 365 ቀኖች ፀሀይ እየሞቁ ውቅያኖሶችን መዋኘትን የመሰሉ ደስታዎች በአውሮፓ አህጉር ስለማያገኙ በቅኝ ገዥነት ለመኖር ካላቸው ፍላጎት የተነሳ በእነሱ ጫማ ስር በወደቀው በታዳጊው ዓለም ህዝብ ላይ በራሳቸው አነሳሽነት የሚፈጥሯቸው ችግሮች ናቸው።

ለማጠቃለል፣ የአካባቢያችን ተስፋፊዎች፣ የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎችና ኢምፔሪያሊዝም በተለያዩ ጊዜያቶችና በፈረቃ እየተመላለሱ በህዝባችን አንድነት፣ በአገራችን የእድገት ሂደት ጣልቃ በመግባት የፈፀሟቸው ወታደራዊና ባህላዊ ወረራዎች መሰሪ የፖለቲካ ሴራዎች፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ ለሚገኝበት ኋላቀርነት ብቻ ሳይሆን ለሰላም እጦታችን ላለፉት ሰላሳ ዓመታት በሰሜኑ ክልል ለገጠመን የእርስ በእርስ ጦርነትና ብሎም ለኤርትራ መገንጠል ዋና ምክንያቶች ናቸው።

ክፍል አስራ አምስት

ምዕራፍ አስራ ሰባት

የኤርትራ ክልል ህዝብ ፌደሬሽኑን ለማፍረስ የወሰነው ፌደሬሽኑ ከመቋቋሙ በፊት ነው።

ሃምሳ ዓመታት በፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት አስር ዓመታት በኢምፔሪያሊስት ብሪታኒያ መንግሥት ቅኝነት፣ በጠቅላላው ስልሳ ዓመታት ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያና ከወገኑ ከኢትዮጵያ ህዝብ ተነጥሎ ሲሰቃይ የነበረውን የኤርትራ ክፍለ ሃገር ህዝብ ጋር መልሶ ለማዋሀድ በተባበሩት መንግሥታት ማህበር መድረክ የተደረገው የፖለቲካ ትግል እልህ አስጨራሽና እጅግ ውስብስብ ስለነበረ የመንግሥታቱ ማህበር 5ኛ ጠቅላላ ስብሰባ ኤርትራና ኢትዮጵያ በፌዴራላዊ መፍትሄ መልሰው እንዲተሳሰሩ መወሰኑ ታላቅ የፖለቲካ ድልነው በማለት የኢትዮጵያ መንግሥት በታላቅ ደስታ የተቀበለው ሲሆን በኤርትራ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አመራር አካላትና መላው የማህበሩ አባላት በእጅጉ ነው ያዘኑበት።

የማህበሩ አመራር አካላት የመንግሥታቱን ማህበር 5ኛ ጠቅላላ ስብሰባ ውሳኔ እንደሰሙ የማህበሩን ማዕከላዊ አመራር አካላት ስብሰባ ጠርተው ውይይት በማድረግ ውሳኔውን እውነት የሌለበትና ፍርደ ገምድል ነው በማለት በኤርትራ ውስጥ የሚኖረው ብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ ህዝብ የታገለው ለኢትዮጵያዊነቱ፣ ለሰንደቅ ዓላማውና ለአንድነቱ እንጂ ለፌደሬሽን ስላልሆነ ውሳኔውን አንቀበልም።

የኤርትራ ብዙሃኑ ህዝብ የማይደመጥና ፍትህዊ ውሳኔ የማይሰጠው ከሆነ ለአንድነታችን ካስፈለገ የትጥቅ ትግል ለማካሄድ ዝግጁ ነን የሚል ውሳኔ አሳልፈው ይህንኑ ውሳኔ በቅድሚያ አዲስ አበባ ላለው የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት የሚገልፅ በንቡረዕድ መላከ ሠላም ዲሜጥሮስ ገ/ማርያም የሚመራ ልዑካን ላኩ።

የልዑካኑ ቡድን በቀድሞው ቤተመንግሥት ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጋር ተገናኝቶ ለአያሌ ዘመናት የኤርትራ ህዝብ ለአንድነቱ ያደረገውን ትግል በዝርዝር ካስረዳ በኂላ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር ልዑካንን በመሩት በንቡረዕድ መላከ ሠላም ዲሜጥሮስ አማካኝነት ከዚህ እንደሚከተለው አቀረበ።

«ግርማዊ ሆይ! የኤርትራ ህዝብዎ የታገለው አንዳች ገደብና ቅድመ ሁኔታ ለሌለበት አንድነቱ፣ ለሰንደቅ ዓላማውና ለንጉሠ ነገሥቱ ነው።

የኤርትራ ህዝብ ወደ ግርማዊነትዎ የላከን ከዚህ ዓላማው ዝንፍ እንደማይል ግለፁልኝ ብሎ ነው» ካሉ በኋላ ቆራጡ ቄስ እልህ በተሞላው ስሜትና ድፍረት ከዚህ የሚከተለውን ጥያቄ ለንጉሡ አቀረቡ።

«የአንድነት ኃይል የሆነው ኢትዮጵያዊያን በኤርትራ ብዙሃን ነን። በትግሉም አሸናፊ ነን። ይሄ አልታመነ እንደ ሆነ እንደገና ለማሳየት እንችላለን።

ግርማዊ ሆይ! ዛሬ ኤርትራ በእጅዎ ናት። ህዝቡ ታዛዥምና ፍፁም ታማኝም ነው። ይህንን ፍርደ ገምድል ውሳኔ እንዴት ይቀበላሉ? ለዙፋንዎ ቅንአት የለዎትም እንዴ?» የሚል ነበር።

ከራሳቸው ከንብረዕድ ዲሜጥሮስ ብቻ ሳይሆን በቢትወደድ አስፍሀና በሌሎችም በአብዛኞዎቹ የኤርትራ አርበኞች እንደተነገረኝ ንጉሡ የተወረወረባቸው ጥያቄ ኃይለ ቃል ብቻ ሳይሆን ድፍረትም የተላበሰ በመሆኑ ሳይቆጡ ራሳቸውን ተቆጣጥረው በዝምታ ለተወሰነ ጊዜያት ከቆዩ በኋላ በኤርትራ ህዝብ ስም ለቀረበላቸው ጥያቄ ከዚህ የሚከተለውን ተናገሩ።

«የመንግሥታቱ ማህበር ይህንን ውሳኔ እንዲሰጥ በፖለቲካው መድረክ የተደረገውን ትግልና የእኛን አቋም በውል ባትረዳም የተናገርከው በሙሉ እውነት ከመሆኑ በላይ በእውነተኛ የሃገር ፍቅር ስሜት ነው።

በኤርትራ ያለውን ህዝባችንን ፍላጎት፣ ምኞትና ስሜቱን የምናውቅለት መሆናችንን እናንተም ትስቱታላችሁ ብለን አንገምትም።

ሞያ በልብ ነው ይባላል። የኤርትራ ህዝባችን ለአንድነቱ ካደረገው ትግልና ከከፈለው መሥዕዋትነት ጋር የማይመጣንና ፍላጎቱን ያሟላ ባይሆንም ወደንና ፈልገን ሳይሆን አማራጭ በማጣታችን ተገድደን የተቀበልነው የመንግሥታቱ ማህበር ውሳኔ በእናንተ አመራርና በኤርትራ ህዝባችን ዕሉ ትግል የተገኘ የመጀመሪያ ድል መሆኑን አምናችሁ በመቀበል ህዝቡን ማሳመን ያስፈልጋል።

ከዚህ የሚቀጥለው ሁለተኛው ድል እንግሊዞችን ከኤርትራ በአስቸኳይና በሰላም ማስወጣት ይሆናል። እንግሊዞች የሚወጡልን ይህንን የመንግሥታቱን ማህበር ውሳኔ በፀጋ ስንቀበል ብቻ ነው። እንግሊዞች ከወጡ በኋላ ህዝባችን የሚፈልገው ይሆናል» የሚል ነበር።

ልዑካኑ የንጉሡን ምክር ለበስ ትዕዛዝ ተቀብለው ወደ ኤርትራ በመመለስ ለላካቸው የአንድነት ማህበር አመራር አቀረቡ።

የማህበሩ አመራር አካላትም የንጉሡን ውሳኔ በአክብሮት ተቀብለው የመንግሥታቱን ማህበር ውሳኔ ወደ ተግባር ተተረጉሞ፣ ፌደሬሽኑ ተቋቁሞ እንግሊዞች ከኤርትራ የሚወጡበትን ጊዜ በጉጉት ሲጠብቁ ቆዩ።

በመንግሥታቱ ማህበር 5ኛ ጠቅላላ ስብሰባ ውሳኔ መሰረት ኤርትራና ኢትዮጵያ በፌደሬሽን የሚተሳሰሩበትን ልዩ ልዩ ደንቦችና ፌደሬሽኑ የሚተዳደርበትን ህገ መንግሥት አዘጋጅ ኮሚሽን በተባበሩት መንግሥታት ጉባዔ ተሰይሞ ወደ ኤርትራ በመምጣት ህገ መንግሥት የማርቀቁንሥራ ጀምሮ ወደ ማገባደዱ በተቃረበበት ጊዜ በኮሚሽኑ አባላትና በኢትዮጵያ መንግሥት ተወካዮች መካከል ውዝግብ የፈጠሩና ብዙ ያጨቃጨቁ መሰረታዊ የህግ ጉዳዩች በርካታ ስለነበሩ ሁሉንም ከመዘርዘር ተቆጥቤ አንዱን ብቻ ላቀርብ እወዳለሁ።

ህገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽኑ የፌደራሉን መስተዳድር ህልውና መግለጫ ወይም ምልክት የሆነ ሰንደቅ ዓላማ መኖር አለበት ብሎ ያቀረበው ሃሳብ በአንድነት ማህበር መሪዎች ተሰምቶ፣ እኛ ሳንሞት ቆመን በኤርትራ ምድር ከእንግዲህ ወዲያ ከኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ሌላ አይቆምም፣ አይውለበለብም በማለት ከፍ ያለ አመፅ አስነስተው ዳግም የንጉሡ ነገሥቱን ጣልቃ ገብነትና በእሳቸው አሳሳቢነት ገላጋይ ሽማግሌዎችን በጠየቀ ጥረት ፌደሬሽኑን መቀበል እንደ አስፈለገ ሁሉ እንግሊዞች እስኪወጡ ድረስ የፌደራሉንም አርማ መቀበል ግድ መሆኑን ለአንድነት ማህበር አመራር አካላት ዳግም በማስገንዘብ አመፁን ማብረድ ተቻለ።

በኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር የሚመራው የኤርትራ ህዝብ በሙሉ ፌደሬሽኑንን የተቀበለው እንግሊዞችን በሰላም ከአገሩ ለማስወጣት ብቻ ስለነበረ የማህበሩ አመራር ፌድሬሽኑን ለማፍረስ የወሰነው ፌደሬሽኑ ከመቋቋሙ በፊት ነው።

ፌደሬሽኑ አስር ዓመት ለመቆየት የቻለው የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ባለሥልጣኖች በተለይም በፀሐፊ ትዕዛዝ ወ/ጊዮርጊስ፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በአቶ አክሊሉ ሀብተ ወልድና አፍቃሪ ፌደሬሽን በሆኑት የአንድነት ተቃዋሚዎች ጥረት ነው።

ምዕራፍ አስራ ስምንት

ከሠላሳ ዓመታት በላይ ለተካሄደው የእርስ በእርስ ጦርነት መንስኤውና ብሎም እድገቱ

እንግሊዞች ኤርትራን እንደ ቅኝ ገዥ ወታደራዊ አስተዳደር መስርተው ለአምስት ዓመታት ያህል ከቆዩ በኋላና የኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች የነበሩ አገሮች ጉዳይ ከአራቱ ኃያላን መንግሥታት እጅ ወጥቶ ወደ የተባበሩት መንግሥታት ማህበር በተመራ ጊዜ በኤርትራ ብቸኛ የነበረው አንድና አንጋፋ የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር ተቃዋሚ የሆኑ አራት አንጃ የፖለቲካ ድርጅቶች በአጭር ጊዜና በተከታታይ አቋቋሙ።

የእነኝህ የእያንዳንዱ የፖለቲካ ድርጅቶች ምኞት፣ ፍላጎትና ጥያቄ በጣም የተለያየና አንዱ የሌላው አንጃ ወይም ተፃራሪ ነበር። የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር ጥያቄ፣ ያለአንዳች ግዴታና ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ ከኢትዮጵያጋር ውህደት የሚል ነው።

በኤርትራ ምዕራባዊ ቆላማ ክልል ነዋሪ የሆኑትን የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ የተለያዩ ማህበረሰቦችና ብሄረሰቦችን እንወክላለን የሚለው ዋናው አንጃና ራሱን «የሙስሊም ሊግ» ብሎ የሚጠራው ድርጅት ለሚቀጥሉት አስር ዓመታት በእንግሊዝ መንግሥት የሞግዚት አስተዳደር ስር ከቆየን በኋላ የወደፊቱን እድላችንን እንወስናለን ሲል «ሊብራል ፕሮግረሲቭ» የተባለው ድርጅት ነፃነትን ጠየቀ። ኢጣሊያ ተመልሳ መጥታ እንደ ደቡብ ሱማሌ እኛንም በሞግዚትነት ታስተዳድረን ያለም ድርጅት ነበር።

እነዚህን የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች እያንዳንዳቸውን በገፅ ተገናኝቶ ጥያቄያቸውን ለማዳመጥና እንወክለዋለን የሚሉት ህዝብ የሚኖርበትን መልክአ ምድራዊ ክልል፣ የህዝቡን መጠን፣ ባህሉንና የሚተዳደርበትን የኢኮኖሚ ምንጭ ፍላጎቱን አጥንቶ የደረሰበትን ግኝት ለተባበሩት መንግሥታት ማህበር እንዲያቀርብ በመንግሥታቱ ማህበር ትዕዛዝ ወደ ኤርትራ የተላከው ከአምስት የመንግሥታቱ ማህበር አባል አገሮች ማለትም ከበርማ፣ ከደቡብ አፍሪካ፣ ከኖርዌይ፣ ከጓቲማላና ከፓኪስታን በተወጣጡ ግለሰቦች ከተቃመረው መርማሪ ኮሚሽን አባላት መካከል ሦስቱ ማለትም የበርማ፣ የደቡብ አፍሪካና የኖርዌይ ተወካዮች በህብረት ያቀረቡትና በተባበሩት መንግሥታት ማህበር 5ኛ ጠቅላላ ስብሰባ የፀደቀው የፌዴሬሽን መፍትሔ ከኤርትራ ህዝብ ብዙሃኑን እወክላለሁ የሚለው የአንድነት ፓርቲ የአመራር አካላት አባላትና ጠቅላላው ደገኛና ህዝበ ክርስቲያን ያዘነበትና የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በጣም ቅር የተሰኘበት ቢሆንም ውሳኔውን ፍርደ ገምድል ነው ብሎ ለመኮነን ግን በኔ አስተያየት በጣም የሚከብድ ነው።

በፖለቲካ ዲሞክራሲ መርህ የብዙሃን ድምፅ መደመጥና መከበር አለበት የሚባል ቢሆንም ይህንን ማለት ግን በተለይም በመንግሥት አስተዳደርና በህብረተሰቦች ማህበራዊ ህይወት ጉዳይ የአናሳዎቹ ወይም የህዳጣኑ ድምፅ፣ ፍላጎት፣ ስሜትና መብት ይዳፈናል ማለት አይደለም። በሌላ አነጋገር ፖለቲካዊ ዲሞክራሲ አንዱን አንስቶ ሌላውን ጥሎ ሳይሆን ሁሉን አሰባሳቢ መሆን አለበት ማለት ነው።

በተለይም የኤርትራን ሙስሊሞች ስጋትና ፍርሀት መርማሪው ኮሚሽን እንደ አላየና እንደ አልሰማ ሆኖ ማለፍ ስለማይችል በዚያን ጊዜ በኤርትራ ስለነበሩ የፓርቲዎች አቋምና ጥያቄ ብቻ ሳይሆን አጠቃላዩን የህብረተሰብ ጥንቅር የአካባቢና የጎሳ ስሜትና መንፈሳዊ እምነት ወዘተ ረገድ ያለው ስብጥር ሲታይ ከፌዴሬሽን መፍትሄ ሌላ የተሻለ አማራጭ መፍትሄ ነበር ብሎ ለማሰብ የሚያዳግት ነው።

በጊዜው የፌደሬሽን ትርጉምና ከፖለቲካ መፍትሄነቱ አንፃር የሚያስገኛቸውን ፋይዳዎች ከመረብ ወዲያና ወዲህ ያለው ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ቀርቶ ምሁራን በሚባሉትም ዘንድ የጠራ ግንዛቤ መኖሩ የሚያጠያይቅ ነው።

በዓለማችን ፌደሬሽን በመባል የሚጠሩ ግን በአወቃቀር፣ በቅንጅትና በጥቅማቸው የተለያዩ የፌደሬሽን ዓይነቶች አሉ።

የተለያዩ የፌደሬሽን ዓይነት ወይም ለጊዜው የፈረሰውን የኤርትራን ፌደሬሽን የቅርፅና የይዘት ዝርዝር መተንተን ሳያስፈልግ አንድ አጠርና ጠቅለል ያለ ሃሳብ መስጠት ቢያስፈልግ የኤርትራና የኢትዮጵያ ህዝቦች ከስልሳ ዓመታት መነጣጠል በኋላ መልሰው የተዋሀዱበት ፌደራላዊ ቅንጅት፣ በሁለት ሉአላዊና እቻ አገሮች ወይም መንግሥታት መካከል የተደረገ ውህደት ሳይሆን በኢትዮጵያ ዘውዳዊ መንግሥት ስር ለኤርትራ ክልል ህዝብ የተሰጠ የራስ ገዝ ክልላዊ አስተዳደር ወይም (Rgional Autonomy) ነው።

የኤርትራ ህዝብ ከስልሳ ዓመታት የቅኝ ግዛት ቀንበር ነፃ ወጥቶ ከወገኑ ከተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር መልሶ የመዋሀዱ ዜና በአገር አቀፍ ሲናኝ መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ በእጅጉ አስደስቷል።

በተለይ በኤርትራ ለአንድ ወር ያህል የታየውን የደስታና የፈንጠዚያ ሁኔታ ይህንን ታሪክ ለመፃፍ የመረጃ ምንጭ የሆኑኝ የትግሉ ተዋናይ የነበሩ አዛውንት አርበኞች በድህረ አብዮት የገለፁልኝ አንድ ታላቅ ማህበራዊ ወይም ህዝባዊ ሠርግና ምላሽ ነበር በማለት ነው።

በተባበሩት መንግሥታት ማህበር 5ኛ ጠቅላላ ስብሰባ ለኤርትራ የተሰጠውን ውሳኔ ፍርደገምድል ብለው ያወገዙት የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር የአመራር አካላትና መላው አባላት አንድነትን ተቃዋሚ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች አመራር

አካላትና አባላት በህብረት የፌደሬሽኑን ምስረታ ደግፈው የልደቱን በዓል በሚያስደንቅ ሁኔታ በደስታ አክብረዋል።

የአንድነት ተፃራሪ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች የአመራር አካላት፣ የክልሉ ታዋቂ ታላላቅ ሰዎችና የአገር ሽማግሌዎች፣ የክርስትናና የእስልምና መንፈሳዊ አባቶች እና በኢትዮጵያ ጠላቶች አደራጅነትና ግፊት የኤርትራ ክልል ህዝብ መከፋፈል ችግርና ብሎም ትግል ውስጥ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ፌደሬሽኑ መመስረት ድረስ ከነቤተሰባቸው ቀንደኛና አክራሪ ፀረ-አንድነት የነበሩት ራስ ተሰማ አስመሮም ሳይቀሩ ለአፄ ኃይለ ሥላሴ የድጋፍና የደስታ መግለጫ መልዕክት ልከዋል።

ከሐማሴን አውራጃ የሚወለዱትና የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር ዋና ፀሃፊ የነበሩት የ42 ዓመት ጎልማሳ አቶ ተድላ ባይሩ የፌደሬሽኑ መስተዳድር መሪ ወይም (Chief Executive) ሆነው ቁጥራቸው 68 ከነበረው የምክር ቤቱ አባላት 42 ድምፅ አግኝተው በመመረጣቸው፣ የምዕራብ ቆላ ተወላጅ የሆኑት ብዙ ተከታይ ያላ ቸውና የታወቁት የ40 ዓመት እድሜ ጎልማሳና በትግሉ ጊዜ ቀንደኛ ተቃዋሚ የነበሩት ሼህ ዓሊ መሀመድ ሙሳ ራዳይ የኤርትራ ህዝብ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት እንዲሁ በክርስቲያኑም መማክርት ከፍተኛ ድምፅ አግኝተው ከመመረጣቸው ሌላ አንድነቶችና ተቃዋሚዎች የምክር ቤቱ መቀመጫ እኩል በመካፈላቸው በተቃዋሚዎች በኩል መሰረታዊ የሆነ የአቋምና የሥነ-ልቦና ለውጥ ፈጥሯል።

ነፃነትና የባዕዳን መንግሥት የሞግዚት አስተዳደር የጠየቁ ፀረ - አንድነቶች በሙሉ የፌደሬሽኑ ፅኑ ደጋፊ ወይም አፍቃሪ ፌደሬሽን ሆኑ ነው የተባልነው።

ፌደሬሽኑ በትግሉ ዘመን ተፃራሪ የነበሩትንና የተከፋፈሉትን ኤርትራዊያን መልሶ አስተባብሯል አሰባስቧል። የአንድነት ተቃዋሚ የነበሩት ሁሉ ማለት ይቻላል ከኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አባላት ጋር በሰላም፣ በመከባበርና በመተሳሰብ ተቻችለን ለመኖር እንችላለን የሚል እምነት አድሮባቸዋል።

የፌደሬሽኑ ልደት በዓል የፈጠረው የህዝቡ ልዩና ታሪካዊ ደስታ ከአንድ ወር ያላነሰ ጊዜ ወስዶ አከተመና ህዝቡ ወደየዕለት የግል ተግባሩ ሲሄድ የፌደሬሽኑ ባለሥልጣኖችና ባለሚሎችም ወደየተግባራቸው ተመለሱና ስራ መስራት ተጀመረ።

የአንድነት ተቃዋሚ የነበሩት ሁሉ ማለት ይቻላል ከኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አባላትጋር በሰላም፣ በመከባበርና በመተሳሰብ ተቻችለን ለመኖር እንችላለን የሚል እምነት አድሮባቸዋል።

የፌደሬሽኑ ልደት በዓል የፈጠረው የህዝቡ ልዩና ታሪካዊ ደስታ ከአንድ ወር ያላነሰ ጊዜ ወስዶ አከተመና ህዝቡ ወደ ዕለት ተግባሩ ሲሄድ የፌደሬሽኑ ባለሥልጣኖችና ባለሚሎችም ወደየተግባራቸው ተመለሱና ስራ መስራት ተጀመረ።

የፌደሬሽኑ ምክር ቤት የአመራር አካላት ቅድሚያውን ትኩረት የሰጧቸው ተግባሮች መማክርቱ ህዝቡ የጣለባቸ ውን አደራ መወጣት ይቻላቸው ዘንድ ምክር ቤቱን የሚያንቀሳቅሰውን ውስጣዊ መዋቅር በበቂ የስራ መመሪያና የሰው ኃይል፣ በቁሳቁስና በፋይናስ ማደራጀት፣ መማክርቱን ከአዲሱ ስራቸው በተለይም ከህገ መንግሥቱና ከእሱም ከሚመነጩት ልዩ ልዩ ህጎችና የስራ መመሪያዎች ወዘተ ጋር ማስተዋወቅ ነበር።

በስራ አስፈፃሚው ወይም በመስተዳድሩ በኩል የመስተዳድሩን ልዩ ልዩ የስራ ዘርፎች የሚመሩ የመምሪያ ሃላፊዎችን መምረጥ፣ በየዘርፉ የሚያስፈልጉ ባለሞያዎችን ሚሟላትና ብሎም ከህገ መንግሥቱና ከምክር ቤቱ የሚመነጩትን ህጎች ወደ ተግባር ለመተርጎም በሚያስችል ሁኔታ ካቢኔውንና ክልላዊ አስተዳደሮችን ማለትም አውራጃና ወረዳዎችን በተዋረድ ማደራጀትን በመሳሰሉ በርካታ ስራዎች ላይ ማትኮር ነበር።

ብዙሃኑ የኤርትራ ህዝብ የጠየቀው በነፃነት ከተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ያለ አንዳች ግዴታና ቅድመ ሁኔታ መልሶ መዋሀድን ወይም ኢትዮጵያዊነትን እንጂ የፌደሬሽን አስተዳደር ስላልሆነ ለጊዜው ፌደሬሽኑ እንዲቋቋም የደገፈው እንግሊዞችን በሰላም ከአገር ለማስወጣት ብቻ ስለሆነ የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር የአመራር አካላት ፌደሬሽኑን ለማፍረስ የወሰኑት ከመቋቋሙ በፊት መሆኑ በአንባቢ ዘንድ ይታወሳል።

ስለሆነም በአንድነት የአመራር አካላት በኩል የሚውጠነጠነው ፌደሬሽኑ ሳይቆይና ሥር ሳይሰድ በአስቸኳይ ማፍረስ ስለነበር በምክር ቤቱ ውስጥ ላሉት የፓርቲው አባላትና ለመስተዳድሩ የአመራር አካላት የፌደሬሽኑን መዋቅር ማጠናከርና ማጠባበቅ ትታችሁ ለማፍረስ በሚያስችለን ሁኔታ ማላላቱንና የማወላለቁን ስራ በአስቸኳይ ጀምሩ የሚል መመሪያ ሰጡ። የሰጡት መመሪያም በተግባር እየተተረጎመ መሆኑን ለማወቅ በመከታተል በየጊዜው ያላቋረጠ ግፊት ማድረጋቸውን ቀጠሉ።

ከአንድ ሰው በላይ ያወቀው ነገር ለብዙ ጊዜ ምስጢር ሆኖ ሊቆይ አይችልምና በየጊዜው የሚሰጡት መመሪያና ለተግባራዊነቱም የሚያደርጉት ግፊት በተቃዋሚዎች ዘንድ ከመታወቁ ባሻገር በእነሱም አማካኝነት በአሥመራ ከተማ ተቀማጭ ለነበሩ የኃያላኑ መንግሥታት ቆንሲል ጀነራሎች ጆሮ ስለደረሰ የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ቀደም ብለን እንደገመትነውና እንደፈራነውም ፌደሬሽኑን ሊያፈርስ ወስኗል የሚል አሉባልታ ማናፈስ ይጀምራሉ።

ከተቃዋሚዎች ያገኙትን መረጃ እውነትነት ለማረጋገጥ የምንሰማው ነገር ምን ያህል እውነት ነው? የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እንደራሴ ቢትወደድ አንዳርጋቸው መሳይና ምክትላቸው ፊታአውራሪ አስፋሀ ወ/ሚካኤል ፌደሬሽኑን እንድታፈርሱ ተፅእኖ እያደረጉባችሁ ነው? ወይስ በነፃነት ስራችሁን መስራት ችላችኋል ወዘተ

የሚሉ ጥያቄዎችን እያንዳንዳቸው እየተፈራረቁ ለፓርላማው ፕሬዝዳንት ለሼህ ዓሊ ራዳይና ለመስተዳደሩ መሪ ለአቶ ተድላ ባይሩ በመደጋገም በመቅረብ ማስቸገር ከየመንግሥታቸው ተልከው ኤርትራ የተገኙበት ተልዕኳቸው ነውና ቋሚ ሥራቸው አድርገው ይያያዙታል።

አዲስ አበባ ያሉትም ዋናዎቹ የየመንግሥታቱ አምባሳደሮች አሥመራ ያሉት የሚያቀብሏቸውንና በአካባቢው የቃረሚቸውን መረጃዎች መሰረት አድርገውና የየራሳቸውንም ፈጠራ ጨምረው በተለይም የብሪታኒያ፣ የፈረንሳይና የሰሜን አሜሪካ መንግሥታት ተወካዮች አስመራ ካሉት ጋር በተመሳሰለ ሁኔታ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለአቶ አክሊሉ ሀብተ ወልድ እንዲሁ ተደጋጋሚ ጥያቄ ስለሚያቀርቡና አፄ ኃይለሥላሴም መንግሥታቸው የኤርትራን ፌደሬሽን ሊያፈርስ ነው ተብሎ የቀረበባቸውን ክስ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው ሲነገራቸው በቤተ መንግሥቱ ውስጥና በአካባቢው የተወሰነ ውዥንብር ይፈጠራል።

በኤርትራ የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አመራር በታላቅ ምስጢርነት የተያዘው ፌደሬሽን የማፍረስ ጉዳይ በአዲስ አበባ የአደባባይ ምስጢር ሆኖ በጎዳና መወራት ይጀመራል።

ለውዥንብሩም ዓይነተኛ ምክንያት ንጉሡ ራሳቸው ናቸው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ከፌደሬሽኑ ህልውና ጋር የተያያዘውን ጉዳይ አፄ ኃይለሥላሴ ለማንም ሳያጋሩ ብቻቸውን ይዘው አማካሪያቸው ከሆኑት ከኤርትራ እንደራሴያቸውና ከምክትል እንደራሴያቸው ጋር ብቻ ስለሚመክሩና ለቀሩት የመንግሥታቸው ባለሥልጣኖች ሁሉ ምስጢር ስለነበር ነው።

የውጭ ጉዳይ ምንስትሩ አቶ አክሊሉ ሀብተ ወልድ የኤርትራን ጉዳይ በተመለከተ ብዙ የደከሙና ብሎም አገራቸውን ለድል ያበቁ የፖለቲካው ትግል ኮከብ ተዋናይ ጀግና ቢሆኑም ከፌደሬሽኑ መቋቋም በኋላ ህግን በሚመለከት ጉዳይ ከማማከር በስተቀር ፌደሬሽኑን ለማፍረስ ስለሚደረገው ጥረት የሚያውቁት ነገር አልነበረም።

የአፄ ኃይለሥላሴ ቀኝ እጅ፣ ዋና አማካሪና የመንግሥታቸውም መሪ የሆኑት ፀሐፌ ትዕዛዝ ወ/ጊዮርጊስ በኤርትራ ያለውን የአስተዳደር፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጉዳይ ወዘተ ችግሮች ለማቃለል ከማዕከላዊ መንግሥት የሚሰጠውን ድጎማና ማናቸውንም ድጋፍ የመስጠቱን ተግባር የሚመሩ ቢሆኑም ፌደሬሽኑን በማፍረስ ረገድ የሚስጥር ተካፋይ አልነበሩም።

አፄ ኃይለሥላሴ እነኝህን ሁለት ቁልፍ ቦታ ላይ ያሉ ሰዎች ከምስጢሩ ያገለሏቸው የፌደሬሽኑን መፍረስ አጥብቀው የሚቃወሙ መሆናቸውን ስለሚያውቁ ነው።

በድህረ አብዮት በትግሉ ውስጥ የአመራር አካላት አባላት የነበሩት አንድነቶችና ተቃዋሚ የነበሩትም የሙስሊም ሊግ አባላት ብቻ ሳይሆኑ ከመሀል አገርም እነ ጀነራል አበበ ገመዳ፣ እነ ጀነራል አማን እና ጓድ አማኑኤል አምደ ሚካኤል ወዘተ ብዙዎቹ እንደነገሩን ከፌደሬሽኑ ልደት በኋላ የኤርትራ ህዝብ በአጠቃላይ የፖለቲካ ድርጅቶች የአመራር አካላት በተለይ በድርጅት ብቻ ሳይሆን በግለሰብም ደረጃ መሠረታዊ የአቋምና የሥነ-ልቦና ለውጥ አድርገዋል።

የቀድሞዎቹ የነፃነት፣ የእንግሊዝና የኢጣሊያ መንግሥት ሞግዚትነት ጥያቄ ያቀረቡ የአንድነት ብቻ ሳይሆን ዐረ - ኢትዮጵያ የነበሩ ሁሉ በፌደሬሽኑ መፍትሄነት ከኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር ጋር በተደረሰበት ስምምነት መሰረት ገንጣይና አፈንጋጭ አቋማቸውን ትተው አፍቃሪ ፌደሬሽን ሆነዋል።

የቀድሞ ተቃዋሚዎች አቋማቸውን ለውጠው በአንድ ዓላማ በመሰባሰብ የፌደሬሽን ደጋፊ ሲሆኑ ፌደሬሽኑ በተመሰረተ በአንድ ዓመት ሂደት ውስጥ በኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር የአመራር አካላት መካከል ጥቂት የመደፍረስ ሁኔታ ተከሰተ።

በአንድነቶች መደፍረስ የተነሳ አዲስ የተከሰተውን አሰላለፍ ስንመለከት በኤርትራ የፌደሬሽኑ የተለያዩ የአመራር አካላት መካከል ሦስት ቡድኖች ተፈጥረዋል ማለት ይቻላል፡-

እነሱም የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነት አጥባቂዎች፣ አፍቃሪ ፌደሬሽን ወይም ፌደራሊስቶች እና ከሁለቱም ጎራዎች አፈግፍገው ለዘብተኛና ገለልተኛ አቋም የያዙ የመሀል ሰፋሪዎች ቡድን።

በመሀል አገርም ኤርትራ ውስጥ በተፈጠረው ሁኔታ የተነሳና የፌደሬሽኑን ህልውና በተመለከተ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣኖች መካከልና ከባለሥልጣኖቹም ክልል ውጭ የኤርትራን ጉዳይ በንቃት በሚከታተሉ የኤርትራ ክፍለ ሃገር ተወላጆችና በተቀሩት ኢትዮጵያዊያን መካከል ከኤርትራው አሰላለፍ ጋር የሚመሳሰሉ ቡድኖች ተፈጥረዋል።

አንደኛውና የመጀመሪያው እነ ዐሐፌ ትዕዛዝ ወ/ጊዮርጊስና እነ አቶ አክሊሉ የሚገኙበት ቡድን ሲሆን፣ ይህ ቡድን ከሁሉ በፊት እስከ አሁን ፌደሬሽኑ በኤርትራም ሆነ በመሀል አገር አንዳችም የፈጠረው ችግር የለም። ወደፊትም ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ብቻ ሳይሆን ከመረብ ወዲህ ባሉት የተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች ነዋሪ ህዝብ አንድነት መልካም ምሳሌነት የሌለው ችግር ስለሚፈጥር በሂደት አስጊ ነው እየተባለ የሚነገረውን ትንቢት ለመቀበል እንቸገራለን።

ከዚህ ስጋት ይልቅ ፌደሬሽኑ ተጠናክሮ በዕናትና ብቃት ሊሰራ የሚችልበትን ሁኔታ ብንፈጥር ለአፍሪካ አገሮች መልካም ምሳሌ ከመሆኑ ሌላ ይህንን ተመልክተው ሱማሌዎችም ተመልሰው ከእናት አገራቸው ከኢትዮጵያ ይቀላቀሉ ዘንድ ጠቃሚ መሳሪያ ሊሆን ስለሚችል መፍረስ የለበትም የሚለው የመጀመሪያው ብርቱ አቋማቸው ሲሆን፣ መፍረሱ ከታመነበት ደግሞ መፍረስ ያለበት በራሱ በኤርትራ ህዝብ እንጂ በሌላ በማንም መሆን የለበትም ከማለት ባሻገር ይህም ቢሆን እንዲህ በጥድፊያ ሳይሆን በበቂ ጥናትና ዝግጅት የተባበሩት መንግሥታት ማህበርን ህግ በማይጥስ ሁኔታ መሆን አለበት የሚሉ ስለሆነ ሌላው አፍቃሬ ፌደሬሽን ናቸው ማለት ይቻላል።

እስከ አሁን የተመለከትነውን የአፍቃሬ ፌደሬሽን ቡድን አቋም በብርቱ የሚቃወመዉ ወይም ሁለተኛውና ፍፁም ውህደት የሚያራምደው ቡድን ማለትም ንጉሡን ጨምሮ ከኤርትራው የአገር ፍቅር ማህበር ጋር ፍፁም የወገነውና ኢትዮጵያዊያንን ሁሉ የሚወክለው ከባዱ ቡድን የያዘውን አቋም እጠቅሳለሁ።

1ኛ. የኤርትራ ህዝብ የታገለውና የጠየቀው ኢትዮጵያዊነቱን እንጂ የፌደሬሽን አስተዳደር አይደለም። ይህንን ከታሪካችን የማይገጥም ዲቃላ ነገር ያመጣብን የኤርትራን ክልል ብቻ ከማየት በስተቀር ስለተቀረው ኢትዮጵያ ህዝብ ምንም ያላየና የማያውቅ የተባበሩት መንግሥታት ማህበር መርማሪ ኮሚሽን ነው።

2ኛ. የኤርትራ ክልል ህዝብ ከተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ በምንም አይለይም። የኢትዮጵያ ህዝብ ከኤርትራ ክልል ህዝብ በላቀ ሁኔታ የአያሌ የቋንቋ ቤተሰቦች የሆኑ ማህበረሰቦችና ብሄረሰቦች ጥንቅር በሃውርታዊ ህዝብ ነው።

3ኛ. በመንፈሳዊ እምነት ረገድም የታየ እንደሆነ በኤርትራ ክልል ውስጥ ከሚኖሩት ሙስሊሞች፣ በወሎ፣ በከፋና በሐረርጌ ወዘተ የሚኖሩት ቁጥር በጣም የላቀ ስለሆነ የሃይማኖት ልዩነት ኢትዮጵያዊያንን ለመከፋፈል ምክንያት ሊሆን አይችልም።

ቀድሞም ኢትዮጵያዊነቱን የጠየቀው አሁንም ባዕዳን የጫኑበትን የፌደሬሽን አስተዳደር እንዲፈርስ የጠየቀው ራሱ የኤርትራ ህዝብ ስለሆነ ፍላጎቱ መከበርና ጥያቄው ፍትሐዊ መልስ ማግኘት አለበት የሚል ሌላው የኢትዮጵያ ህዝቦች አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር ነው ማለት ይቻላል።

በዚህ ዓይነት ልዩነት አሥመራ ያሉት የፌደሬሽኑ አመራር አካላትና የአዲስ አበባ ማዕከላዊ መንግሥት ባለሥልጣን መሀከል ካለው መጓተት በተጨማሪ የኃያላኑ መንግሥታት ጣልቃ ገብነት ተጨምሮ ፌደሬሽኑ ሳይፈርስ ዓመታዊ ልደቱን አከበረ።

በፌደሬሽኑ ዓመታዊ ልደት አፄ ኃይለ ሥላሴ ለሁለተኛ ጊዜ ኤርትራን በጎበኙበት ጊዜ እንደራሴያቸውን ራስ ቢትወደድ አንዳርጋቸው መሳይን፣ ምክትል

እንደራሴያቸውን ፊታውራሪ አስፍሐ ወ/ሚካኤልንና የመስተዳድሩን መሪ አቶ ተድላ ባይሩን ደጃዝማች አድርገው ከመሾማቸው በላይ ሌሎችንም ማለትም የፌደሬሽኑን መማክርት የመስተዳደሩን ሹማምንት የየአውራጃና የየወረዳ አስተዳዳሪዎችንና ሌሎችም በብዛት የተለያዩ ሹመትና ሽልማት አርከፍክፈውና በጠቅላላ በገብኝታቸው የተመለከቱትን የክልሉን የስራ ክንዋኔዎች አመስግነው በመመለሳቸው ደጃዝማች ተድላ ባይሩ የንጉሡ ፍላጎት ያልገባቸው ይመስላል የያዙት የፌደራሊስቶች አዝማሚያ የተወደደላቸው መስሏቸው ልባቸው ከመደንደኑ ሌላ ሥልጣኑም ስለጣማቸው ከአገር ፍቅር ማህበር አመራር በመራቅ የሚሰጣቸውን አመራር ለመቀበል ዳተኛ ሆኑ።

ለአገር ፍቅር ማህበር የአመራር አባላትና አካላት የተሰጠው ሹመትና ሽልማት በነራስ አንዳርጋቸው መሳይና በነደጃዝማች አስፍሐ ወ/ሚካኤል ሃሳብ አቅራቢነትና በፈጠሩት የግለሰቦች መመዘኛ መስፈርት ከፌደሬሽኑ በፊት በትግሉ ዘመን የላቀ አስተዋፅኦ ላደረጉ ባለውለታዎች እንደሆነ ይገመታል።

ተቃዋሚ በነበሩት የእስላም ሊግ የአመራር አካላትና አባላት የተሰጠው አቋማቸውን ለውጠው ከአንድነቶች ጋር በመወገን ፌደሬሽን ለማፍረስ ይተባበራሉ ወይም ያገለግላሉ ለሚባሉ ግለሰቦች መሆኑ አያጠያይቅም።

ከአገር ፍቅር አባላት መካከል የሹመቱና የሽልማቱ ተጋሪ ያልሆኑት ከማዘናቸው በላይ እነሱ ሳያገኙ ዐረ-ኢትዮጵያ የነበሩ ራቢጣዎች በመሾማቸውና በመሸለማቸው በእጅጉ የተበሳጩና ያለቀሱ የአንድነት ፓርቲው አባላት ጥቂት አይደሉም ነው የተባለው።

በእስላም ሊግ አባላት በኩል ሹመትና ሽልማት ያገኙት ቢደሰቱም ያላገኙት አፍቃሬ ፌደሬሽን በመሆናችን ወይም በቀድሞው አቋማችን ምክንያት ነው ከሹመቱና ከሽልማቱ በረከት የተገለልነው ከማለት ባሻገር ንጉሠ ነገሥቱ የኤርትራን ፌደሬሽን ሹማምንት ሿሚና ሻሪ የመሆን ሥልጣን የላቸውም። የሚሰሩት ሁሉ ፌደሬሽኑን ለማፍረስ ካላቸው ዓላማ የሚመነጭና የፌደሬሽኑን ህገ መንግሥት የጣሰነው በማለት ለተባበሩትመንግሥታት ጽህፈት ቤት ክስ ያቀረቡ ነበሩ።

አፄ ኃይለ ሥላሴ በኤርትራ ልዩ አማካሪዎቻቸው አሳሳቢነት በፌደሬሽኑ አንደኛ ዓመት ልደት የሰጡት ሹመትና ሽልማት ውጤቱ ሲገመገም ተጠቃሚዎቹ መደሰታቸው ባያጠያይቅም ብዙ አኩራፊ ነው የፈጠረው።

የቀድሞው የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር ዋና ጸሐፊና የፌደሬሽኑ መስተዳድር ዋና መሪ የሆኑት ደጃዝማች ተድላ ባይሩ የአገር ፍቅር ማህበር ለሰጣቸው ታላቅ ሃላፊነትና ለጣለባቸው እምነት የተዘጋጁ ሆነው ባለመገኘታቸውና

አያሌ ቅድመ ሁኔታዎችን ባለማዘጋጀታቸው የፌደሬሽኑ ህልውና ዓመታትን አስቆጠረ።

በሁለቱ ታላላቅ ጎራዎች ማለትም በአንድነት አጥባቂዎችና በፌደሬሽን አፍቃሪዎች መካከል ቆመው የወሳንሳ የተወጠሩት ደጃዝማች ተድላ ባይሩ ንጉሡ ራሳቸው ፌደሬሽኑን አፍርስ ብለው እስካላዘዙኝ ድረስ ከሌላ አቅጣጫ የሚመጣውን አልቀበልም በማለት ከመሐል ሰፋሪዎች ጋር ሆነው የአገር ፍቅር ማህበር ለሚሰጣቸው መመሪያ ጆሮ ዳባ እንዳሉ ቀጠሉ።

ይህም ሆኖ በአሥመራና በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆኑት የአራቱ ኃያላን መንግሥታት ተወካዮች ፌደራሊስቶች በሚያቀብሏቸው መረጃ አፄ ኃይለሥላሴ የኤርትራን ፌደሬሽን ሊያፈርሱ ነው እያሉ የሚያቀርቡት ክስም ያለማቋረጥ ስለቀጠለ ለማስተባበል ተብሎ በኤርትራ የዘውዱ እንደራሴ ራስ አንዳርጋቸው መሳይ በ1953 ዓ.ም የፓርላማውን መደበኛ ስብሰባ ሲከፍቱ የንጉሠ ነገሥቱ መልዕክት ብለው በሰጡት መግለጫ ያለ ኤርትራ ህዝብ ፈቃድና ፍላጎት ፌደሬሽኑን ማንም እንደማይነካ በንጉሡ ስም የሰጡትን ዋስትና ደጃዝማች ተድላ ባይሩ እውነት ነው ብለው በማመን ይመስላል የአገር ፍቅር ማህበር አመራር አካላት የፌደሬሽኑን ህልውና አስመልክተው ባነጋገሯቸው ቁጥር ይህንን የምንነጋገርበት ጊዜ አይደለም። ከፌደሬሽኑ ህገ መንግሥትና ከንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ ውጭ ልሰራ አልችልም እያሉ እቅጩን መናገር ጀመሩ።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በገሀድና በአደባባይ ንግግር ባደረጉ ቁጥር እኔ የማውቀው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኤርትራ ንጉሥ መሆናቸውንና ኤርትራ ኢትዮጵያዊት መሆኗን ብቻ ነው። ከዚህ ሌላ የማውቀው ነገር የለም ማለትን ስለአዘውተሩ የአገር ፍቅር ማህበር አመራር አካላት ተድላ ባይሩ እኛን ከድቶና የጋራ ዓላማችንን ስቶ ትቶን ሄዷል በማለት በአፍቃሬ ፌደሬሽን ወይም በፌደራሊስትነት ፈርጀው ከማህበራቸው በማስወጣት ከሥልጣናቸው ለማንሳት ወስነው ይህንንም የሚያስረዳ ደብዳቤ ፃፉላቸው።

በድህረ አብዮት የኤርትራን ችግር መንስኤ ለማወቅና እንዲሁም መፍትሔው ምንድን ይመስላችኋል በተሰኙ ጉዳዮች ዙሪያ ከብዙ የአገር ፍቅር ማህበር አባላት ጋር በተወያየሁበት ጊዜ ስለደጃዝማች ተድላ ባይሩም ማንነት ለማወቅ ፈልጌ ላቀረብኩላቸው ጥያቄዎች ያሉኝ፣ ተድላ የፌደሬሽኑ መስተዳድር መሪ ካደረግነው በኋላ ሥልጣን ጥሞት ከኛ መነጠሉ እውነት ቢሆንም ለአንድነት ታላቅ ተጋድሎ ካደረጉት ግንባር ቀደም ታጋዮች መካከል አንዱ ነው።

በኋላም ቢሆን እስከ መጨረሻው በኢትዮጵያዊነቱ በኩል የሚያጠያይቅ ሰው አልነበረም። ፌደሬሽኑን የመምራት ሥልጣን ከተሰጠው በኋላ የፖለቲካ ሥልት ድህነት የታየበት ከመሆኑ ሌላ አዋቂ ወይም ብልህ የልብ አማካሪ ስላልነበረው

የኢትዮጵያን ፊውዳላዊ ገዥ መደቦች ፖለቲካ በአጠቃላይ በጣም የሚወዳቸው ብቻ ሳይሆን የሚያመልክባቸውን ንጉሥ ባህሪ በተለይ የተገነዘበ ሰው አልነበረም ነው ያሉኝ።

እውነትም የደጃዝማች ተድላን የዋህነት የሚያስረዳው ፌደሬሽኑን እንዲያፈርሱ የተላኩትን የንጉሡን አማችናየ ዘውዱ እንደራሴ በስራዬ ጣልቃ እየገቡ ስለሚያስቸግሩኝ ይነሱልኝ ብለው ንጉሡን መጠየቃቸው ነው።

የአገር ፍቅር ማህበር አመራር አካላት ተድላ ባይሩን ከፌደሬሽን አፍቃሪዎች ጋር ይፈርጇቸው እንጂ እሳቸው ግን ከማንም ጋር አልነበሩም።

ከፓርላማው መማክርትና ከካቢኔው አባላት መካከል በጣም ጥቂት የሥራ ባልደረቦቻቸውና በተለይም ከምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት ከሼህ አሊ ራዳይ በስተቀር ወዳጅና ደጋፊ አልነበራቸውም። የአገር ፍቅር ማህበር የአመራር አካላት ከማህበሩ አባልነት ያገለሏቸው መሆኑን የሚያስረዳ ደብዳቤ ከፃፉላቸው በኋላ ይሰጧቸው የነበረውን ድጋፍና እርዳታ ማቆም ነፈጓቸው። አልፈውም የኤርትራን ህዝብ ያስደሰቱ መስሏቸው የሚያደርጓቸውን ጥረቶች በማንኳሰስ፣ በማራከስና በህዝቡ በማስጠላት እሳቸው ቀን ሲገነቡ የዋሉትን አንድነቶች ሌሊት በማፍረስ ታላቅ ችግር ላይ ጣሏቸው። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ አፄ ኃይለሥላሴ ለሦስተኛ ጊዜ ጉብኝት ኤርትራ ሄደው ለሳምንታት በቆዩበት ጊዜ በሰሙትና በተመለከቱት ስላልተደሰቱ እንደወትሮው በማመስገን ፈንታ ስለነቀፏቸው ቅስማቸው ተሰበረ።

የሥልጣናቸው ማክተሚያ በተቃረበበትና የፌዴሬሽኑ ህልውና አጠያያቂ ደረጃ ላይ በደረሰበት ጊዜ መፍትሔ ይገኛል በሚል ተስፋ ለንጉሡ ለማስረዳት አዲስ አበባ መጥተው ንጉሡ ፊት ስለነሷቸው ምንም ነገር ሳይፈፀሙ ወይም ሳያስፈፅሙ ወደ አገራቸው ተመለሱ። ከዚያም ተስፋ በቆረጠ ስሜት፣ ብስጭትና እልህ በህግ የማይደገፉ ስህተቶችን በመስራት የሚገደሉበትን መሳሪያ ራሳቸው ለጠላቶቻቸው አቀባይ ሆኑ።

በመጨረሻም ከፓርላማው ጠቅላላ መማክርት ጋር በገቡት የማይታረቅ ቅራኔ መማክርቱ በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ መግደል እንዲሉ ብቸኛ አጋርና ወዳጃቸው ከነበሩት ከፓርላማው ፕሬዝዳንት ጋር ከሥልጣናቸው ሊያስወግዷቸው ሲዶልቱ ሁለቱም ቀድመው ፌደሬሽኑ በተመሰረተበት ሦስተኛ ዓመት መገባደጃ ሐምሌ 29 ቀን 1955 ዓ. ም በራሳቸው ፈቃድ ሥልጣናቸውን ለቀቁ።

ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ

ደጃዝማች አስፍሐ ወ/ሚካኤል ደጃዝማች ተድላ ባይሩን ተክተው

ለኤርትራ ፌደሬሽን መስተዳድር መሪነት መመረጥ

በኤርትራ ክፍለ ሃገር ከአካለ ጉዛይ አውራጃ ስለሚወለዱትና በዚህ ጊዜ የ40 ዓመት ጎልማሳ ስለነበሩት ደጃዝማች አስፍሐ ወ/ሚካኤል ማንነት በአጭሩም ቢሆን በትግላችን ቅፅ አንድ መግለጫ በአንባቢ ዘንድ ይታወሳል።

በፋሽስት ኢጣሊያ የቅኝ ግዛት ዘመን ለኢጣሊያኖች የአመራር አካላት በአስተርጓሚነትና በፖለቲካ አማካሪነት በማገልገል ለጊዜው ለኢጣሊያኖች በምንደኝነት ካደሩ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ታማኝነትና የላቀ ሥልጣን የነበራቸው አስፍሐ ወ/ሚካኤል በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያም በአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በተለያዩ ስራዎችና እንዲሁም ሃላፊነቶች እየተዘዋወሩ በመስራት በርካታ ተሞክሮ ያላቸው ከመሆናቸው ሌላ የኤርትራ ክፍለ ሃገር ተወላጅ በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን ስለ ኤርትራ ባላቸው እውቀትና የፖለቲካ ችሎታቸው የክፍለ ሃገሩን ህዝብ ከወገኑ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር መልሶ ለማዋሀድ በተደረገው የሃገር ውስጥ፣ በውጭ አገርና በተለይም በተባበሩት መንግሥታት ማህበር ሸንጎ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ የአቶ አክሊሉ ሁብተ ወልድና የንጉሠ ነገሥቱ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ብቻ ሳይሆን በኤርትራ የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አመራር አካላት አማካሪ በመሆን ከፍ ያለ አገልግትሎ መስጠታቸው በብዙ ኢትዮጵያዊያን የሚነገርላቸው ቢትወደድ አስፍሐ ወ/ሚካኤል በፀረ-አንድነቶች ዘንድ ይህ ታላቅ የአገር ፍቅርና የአርበኝነት ተግባራቸው ኤርትራን ለኢትዮጵያ እንደሸጡ ከሐዲ ወንጀለኛ አስቆጥሯቸው በድህረ አብዮት በ1967 ዓ.ም በጀነራል አማን አምዶም ትዕዛዝ ከቀድሞው የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር እንዲቀላቀሉ ከተደረገበት እስር ቤት ፈተን በነፃ በለቀቅናቸው ወቅት ነበር ላነጋግራቸውና ላውቃቸው የቻልኩት።

የኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክልል መለዮ ለባሽ ተወካይ በሆኑት የደርግ አባላት አማካኝነት በዝና ብቻ ስለማውቃቸው ስለ ቢትወደድ አስፍሐ ማንነት በጥልቀት የተረዳሁት የትግል አጋራቸውና በእጅጉ ወዳጃቸው በሆኑትና በሌላው ታሳሪ ታላቅ የአንድነት አርበኛ በንቡረ ዕድ መላከ ሠላም ዲሜጥሮስ ገ/ማርያም ነው።

ለንጉሠ ነገሥቱ በተለይ ለቀሩት የመንግሥቱ ባለሥልጣኖች በአጠቃላይ የኤርትራ ጉዳይ ባለሟል (Expert) ሆነው በማማከር በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘንድ መወደድንና ታማኝነትን ያገኙ ሰው በመሆናቸው እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1952 ዓ.ም የኤርትራ ክፍለ ሃገር በፌደሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር መልሶ ሲቀላቀልና ቢትወደድ አንዳርጋቸው መሳይ በኤርትራ የመጀመሪያው የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ ሲሆኑ

ፊታውራሪ አስፋሐ ወ/ሚካኤል በምክትል እንደራሴነት ዋናውን እንደራሴና የኢትዮጵያን አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አመራር አካላት እንዲያማክሩ በንጉሠ ነገሥቱ የተሾሙ ናቸው።

የአንድነት ዓላማ አክራሪ ከሆኑት ኤርትራዊያን አንዱ ከመሆናቸው ባሻገር በተፈጥሮ ብልህነታቸውና በፖለቲካ ሥልታቸው ፌደሬሽኑን የማፍረስ ተልዕኮ የተሰጣቸው ናቸው ለማለት ይቻላል። በኤርትራ የፈፀሙትን የአርበኝነት ተግባር ሲያጫውቱኝ ንጉሡ ይህንን ትዕዛዝ ሰጡኝ ባይሉም ስለ ተልዕኳቸው ሳይሸሽጉ በኩራት አስረድተውኛል።

በኤርትራ የዘውዱ ምክትል እንደራሴ እንጂ በህዝብ የተመረጡ የፌደሬሽኑ ፓርላማ መማክርት ወይም የመስተዳድሩ ካቢኔ አባል ስለአይደሉና የአንድነት ተቃዋሚዎች የሙስሊም ሊግ አባላትና የኤርትራን ጉዳይ እንዲከታተሉ ታላላቆቹን መንግሥታት ወክለው በአስመራ ከተማ የሚገኙት ቆንሲል ጀነራሎች ሁሉ ፌደሬሽኑን የማፍረስ ተልዕኮ ያለው ነው በሚል ጥርጣሬ ስለሚመለከቷቸው እሳቸውም ሆኑ ዋናው እንደራሴ ሥራችንን የምንሰራው በታላቅ ምስጢርና ጥንቃቄ ነው ብለውኛል።

ከሥራዎቻቸውም ዋና ዋናዎቹ የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አመራር አካላትን በአጠቃላይና የመስተዳድሩን መሪ ደጃዝማች ተድላ ባይሩን በተለይ ማማከር፣ ማትጋትና ከማዕከላዊ መንግሥት የሚፈልጉትን ማናቸውንም ድጋፍና እርዳታ መስጠት ነበር ብለዋል።

አንባቢ እንደሚያስታውሰው በኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር ፌደሬሽኑን ለማፍረስ የተወሰነው ከመቋቋሙ በፊት ስለነበር ከተቋቋመ በኋላ የማፍረሱ ተግባር ከአንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንዲከናወን ታቅዶ ነበር። በጊዜ ሂደት ከተግባር መረዳት እንደተቻለው የማፍረሱ ተግባር ከተገመተው በላይ ውስብስብ ሆኖ ከመገኘቱ ሌላ አንድ ዓመት በቂ ጊዜ ሆኖ ባይገኝም ደጃዝማች ተድላ ባይሩ በኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር ዓላማና ውሳኔ መሰረት ፌደሬሽኑን ለማፍረስ ዓላማ ከመስራት ፋንታ የፌደሬሽኑን ህገመንግሥት የሚጠናከርበትን ተግባር በማከናወን ብሎም በተለይ ደጃዝማች ሆነው ከተሾሙ በኋላ ሥልጣን ስለጣማቸው ራሳቸውን ከፖለቲካ ማህበሩ አግልለውና ከመመሪያው አፈንግጠው የምንሰጣቸውን ምክር አልሰማም ብለው አፍቃሬ ፌደሬሽን በመሆን የሥራችን ዋና መሰናክል ሆኑ ነው ያሉት።

ከአስፍሐ ንግግር መረዳት እንደሚቻለው ደጃዝማች ተድላ ባይሩን በዚያ ሁኔታ ከሥልጣናቸው ለማስነሳት በተደረገው ጥረት ከአንድነቶች ጋር ትልቅ አስተዋፅኦ ያደረጉ በመሆናቸው አቤ ኃይለሥላሴ ተድላን እንዲተኩ እንደ አዘጋጇቸው መገመት ይቻላል።

ተድላ ባይሩ በቃኝ አልቻልኩም ብለው የተመረጡበትን ጊዜ ሳይሸፍኑ በሦስተኛው ዓመታቸው ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው ሲለቁ ማን ይተካቸው ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ በጊዜው እንደጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው የአፄ ኃይለሥላሴን መንግሥት ይመሩ የነበሩት ፀሐፊ ትዕዛዝ ወ/ጊዮርጊስና በኤርትራ የዘውዱ እንደራሴ ራስ አንዳርጋቸው መሳይ የተለያዩ ሰዎችን ለምርጫ ሲያቀርቡ አፄ ኃይለሥላሴ "በኔ በኩል የተመረጠው ብቸኛው ወራሽ አስፍሐ ወ/ሚካኤል ነው" አሉ ነው የተባለው።

ደጃዝማች ተድላ ባልሸፈኑት ቀሪ አንድ ዓመት በጊዜያዊነት ለፌደሬሽኑ መስተዳድር መሪነት ከተወዳደሩት ሦስት ሰዎች መሀከል የንጉሠ ነገሥቱ ምክትል እንደራሴነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በፓርላማው መማክርት አስፋሐ ወ/ሚካኤል ከፍተኛ ድምፅ አግኝተው እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ነሐሴ 8 ቀን 1955 ዓ.ም በኤርትራ የፌደሬሽን መስተዳድር ሁለተኛው መሪ ሆነው ተመረጡ።

የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አባላትአንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ፌደሬሽኑ ስር ከመሰደዱ በፊት እናፈርሰዋለን ብለው እንደገመቱት ሳይሳካ ቀርቶ በደጃዝማች ተድላ ባይሩ መሪነት የሦስት ዓመት እድሜ ያገኘውን ፌደሬሽን ደጃዝማች አስፋሐ ወ/ሚካኤል በቀረው አንድ ዓመት ውስጥ አፈርሳለሁ የሚል ዓላማ አንግበው ቢነሱም ከዚህ በኋላ እንደምናየው ወይም ታሪክና ተግባር እንደ አሳዩን ከበሮ በሰው እጅ እንዲሉ ፌደሬሽኑን ለማፍረስ ሰባት ዓመታት አስፈልጓቸዋል።

በአገር ፍቅር ማህበር አባሎች ምኞት መሰረት ደጃዝማች ተድላ ባይሩ በአንድ ዓመት ውስጥ ፌደሬሽኑን ለማፍረስ ያለመቻላቸው ብቻ ሳይሆን ፈቃደኛም አልሆኑም ተብለው ከመኮነናቸው ባሻገር «ደጃዝማች ፌደራሊስት» የሚል ስም የሰጧቸው አስፋሐ ስር ከመሰደዱ በፊት ፌደሬሽኑ መፍረስ አለበት እንዳላሉ ሁሉ የመስተዳድሩን ሥልጣን ሲረከቡ ቀዳሚ ተግባራቸው ያደረጉት ፌደሬሽኑን ለማፍረስ በርካታ ቅድመ ሁኔታዎችን በጥንቃቄና በማያዳግም ሁኔታ ማዘጋጀት ስለሚያስፈልግ ጊዜ ስጡኝ ረጅም ጊዜ ያስፈልገኛል ብለው አንድነቶችን ማግባባትና ማሳመን ነበረባቸው። የንግግር ችሎታና ተናግረው የማሳመን ስጦታ ያላቸው አስፋሐ ከንጉሡ ጀምሮ በመላው የአገር ፍቅር ማህበር አባላት ታምነው በጠየቁት መሰረት "የሚያስፈልግህን ጊዜ በመውሰድ እንዳሻህ አድርግ" ተባሉ።

ፌደሬሽኑን ለማፍረስ በቅድሚያ የሚሰሩ ብዙ ስራዎች አሉ። እነዚህም ስራዎች በቂ ጊዜ ይጠይቃሉ ቢሉም የመስተዳድሩን ሥልጣን በተረከቡ ማግሥት ፌደሬሽኑን ለመጣል መገዝገዙን ጀመሩ።

ከሁሉ በፊት ፌደሬሽኑን ለማፍረስ የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ ያሉት የሁለተኛውን ዙር የፓርላማ መማክርት የምርጫ መሰናዶ ነው።

ሁለተኛው ዙር የፓርላማ መማክርት ምርጫ መሰናዶ ፌደሬሽኑን ለማፍረስ እንደ መጀመሪያ ቅድመ ሁኔታ የተወሰደበት ምክንያት ከምርጫው በፊት ባለው ሰፊ ጊዜ በህዝቡ ውስጥ ሰፊ ቅስቀሳ በማድረግ አንድነቶችንና የአንድነት ደጋፊዎችን በብዛት ለማስመረጥ በማቀድ ነው።

ደጃዝማች አስፋሐ ለሁለተኛው ዙር የምክርቤት አባላት ምርጫ መሰናዶ ብቻ ሳይሆን ለጠቅላላው ስራቸው ክንዋኔ አመቺ የሆኑ ሁለት ቀብ ነበራቸው።

አንደኛው ቀብ፣ ምክትል የዘውዱ እንደራሴነታቸው ሲሆን ሁለተኛው የመስተዳድሩ መሪነታቸው ነው። በእነዚህ አመቺ ሁኔታዎች ሁለተኛው የፓርላማ መማክርት አባላት ምርጫ መሰናዶ በእቅዳቸው መሰረት በስኬታማነት ይሰምርላቸው ዘንድ፣

1ኛ. አብዛኛውን የሙስሊም ሊግ አባላት የሆኑትን የምክር ቤቱን አባላት እንዲሁም የአብዛኛውን ቆለኛ ህዝብ ድጋፍ ለማግኘት የደጃዝማች ተድላ ባይሩ ወዳጅ በመሆናቸው ተድላን ለማስነሳት ብቻ ሲባል ከሥልጣናቸው የተነሱትን የመጀመሪያውን የፓርላማ ፕሬዝዳንት ሼህ አሊ ራዳይን ለንጉሡ በማሳሰብ በኤርትራ የዘውዱ እንደራሴ የአማካሪነት ሥልጣን እንዲሰጣቸው አደረጉ።

2ኛ. ለተወሰነ ጊዜ ሊረዱ ይችላሉ ባይረዱም እንኳን ለስራችን እንቅፋት አይሆኑም በማለት ራሳቸው በሼህ አሊ ራዳይ ምትክ ለፓርላማው ፕሬዝዳንትነት ያስመረጧቸው ሼህ ኢድሪስ መሐመድ አደም እንደተጠበቀው ተባባሪ ሆነው ባለመገኘታቸው ባላቸው ዘዴ መላውን የፓርላማ መማክርት አግባብተውና አሳምነው ከፕሬዝዳንትነት ሥልጣናቸው እንዲነሱ በማድረግ በፓርላማው አባላትና እንዲሁም በቆለኛው ህዝብ ዘንድ ብዙ ተከታይ ያላቸው የሼህ አሊ ራዳይ ወገንና ወዳጅ የሆኑትን ሼህ መሀመድ ፈረጅን ለፕሬዝዳንትነት አስመረጡ።

3ኛ. ሌላውን የደጃዝማች ተድላ ባይሩ ወዳጅና አፍቃሪ ፌደሬሽን የሆኑትን የፓርላማውን ምክትል ፕሬዝዳንት ብላታ ደምሰስ ወ/ሚካኤልን አስነስተው በምትካቸው የአንድነት አርበኞች አውራ የሆኑትንና ለእሳቸውም የትግል አጋርና የልብ ወዳጅ ናቸው የሚባሉትን ንቡረዕድ መላከ ሠላም ዲሜጥሮስ ገብረ ማርያምን አስመረጡ።

ሼህ አሊ ራዳይና ንብረዕድ ዲሜጥሮስ የረጅም ጊዜ ወዳጆች ሲሆኑ ሁለቱም ደግሞ እንደዚሁ የአስፍሐ ወዳጆች፣ በስራ የሚግባቡ፣ አንድ ዓላማና ተግባር ያላቸው ናቸው።

ንቡረዕድ ዲሜጥሮስ የአንድነቶች መሪ ሲሆኑ ሼህ አሊ ራዳይ ደግሞ የፓርላማው መማክርት ከሆኑት የሙስሊም ሊግ አባላት ከግማሽ ቁጥር በላይ የሚደግፏቸውና የሚከተሏቸው ናቸው።

ንቡረዕድ መላከ ሠላም ዲሜጥሮስ የፓርላማው ምክትል ፕሬዝዳንት መሆን ራሱ ብቻ ፌደሬሽኑን ለማፍረስ ግማሽ መንገድ እንደመራመድ የሚቆጠር ነበር።

በትግላችን ቅፅ አንድ በአጭሩም ቢሆን ስለንቡረዕድ መላከ ሠላም ዲሜጥሮስ ገ/ማርያም የተገለፀውን አንባቢ ያስታውሳል ብየ እገምታለሁ።

ንቡረዕድ መላከ ሠላም ዲሜጥሮስ ገ/ማርያም በኤርትራ ለአንድነት በተደረገው ትግል ወደር የሌላቸው ኢትዮጵያዊና አቻ የሌላቸው የአንድነት አርበኞች ቁንጮ ናቸው።

ወዳጆች የሆኑና በስራ የሚግባቡ፣ በዓላማና በተግባር የተዋሀዱ ሰዎች በፌደሬሽኑ አመራር ከፍተኛው ቁልፍ ቦታ ላይ መገኘት በፓርላማው ውስጥ ያሉትን መማክርትና ከፓርላማ ውጭ ያለውን የኤርትራን ህዝብ የሚያስተባብርና የሚያሰባስብ ስለሆነ ደጃዝማች አስፋሐ ወ/ሚካኤል የሁለተኛው የፓርላማ መማክርት ምርጫ መሰናዶ በፈለጉት ሁኔታ ስኬታማ ሆኖላቸዋል ማለት ይቻላል።

4ኛ. በመስተዳድሩ መሪነታቸው አስተዳደራቸው ሁሉንም በእኩልነት የሚያይ ፍትሀዊ አስተዳደር ሆኖ መላውን የኤርትራ ህዝብ ድጋፍ ያስገኘላቸው ዘንድ በደጃዝማች ተድላ ባይሩ አመራር ጊዜ አምስት የነበሩትን የመስተዳድሩን ሰክሬቴሪያት ቁጥር ወደ ስድስት ከፍ በማድረግ ስራውን ለክርስትናና ለእስልምና እምነት ተከታዮች እኩል አካፈሏቸው።

ደጃዝማች አስፋሐ በመጀመሪያው የአንድ ዓመት ጊዜያዊ ሥልጣናቸው ማለትም እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ከግንቦት ወር 1955 ዓ.ም እስከ 1956 መስከረም ድረስ ከዚህ በላይ እንደተገለፀው በቅድሚያና በብርቱ ያተኮሩበት ትልቁ ስራ የሁለተኛውን ዙር የፓርላማ መማክርት ምርጫ ማዘጋጀት ነው።

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1952 ዓ.ም እንግሊዞች ባዘጋጁት የመጀመሪያው የፓርላማ መማክርት ምርጫ ከመላው የኤርትራ አውራጃዎች ሠላሳ አራት (34) ከክርስቲያኖች ሠላሳ አራት (34) ከሙስሊሞች እንዲመረጡ ስለአደረጉ በሁለተኛው ዙር ምርጫም ይሄው የኮታ ድልድል እንዲጠበቅ ታቅዷል።

የሃይማኖት ክፍያው ሳይዛባ ለምርጫው ከሚወዳደሩት ክርስቲያኖችም ሆነ እስላሞች ውስጥ የአንድነት ደጋፊ ዎች የሆኑ በብዛት እንዲመረጡና በፓርላማው ውስጥ አንድነቶችና የአንድነት ደጋፊዎች ቁጥር የበላይነትን ይይዝ ዘንድ የሚቻለው ሁሉ እንዲደረግ ተወስኗል።

እንግሊዞቹ ባዘጋጁት የመጀመሪያው ምርጫ ውድድር የእስላም ሊግ ወገኖች አብዛኛው በሊጉ አመራር ከፍተኛውን ስፍራ የያዙና ቀንደኛ ፀረ-አንድነቶች እነ

ኢብራሂም ሱልጣን፣ እነ ዑመር ቃዲና መሰሎቻቸው በብዛት ምር ጫውን አሸንፈው በአንድነት አንጃነት የፓርላማው መማክርት አባል ነበሩ።

በሁለተኛው ዙርምርጫ በአንድነቶች፣ በአንድነት ደጋፊዎችና ተቃዋሚዎች መካከል ለአንድ ወር ያህል ከፍተኛ የውድድር ትግል ተደረገ።

ከውድድሩ ፍፃሜ በኋላ የምርጫው ውጤት ሲታይ አስፍሐ በአቀዱት መሰረት በፓርላማው ውስጥ አንድነቶችንና የአንድነትን ደጋፊዎች ብዙሃን ያደረገ ሆኖ ተገኘ።

ከመላው ኤርትራ አውራጃዎች ሠላሳ አራት (34) ክርስቲያኖችና ሠላሳ አራት (34) እስላሞች ተመረጡ ከኢጣሊያና ከአረብ አገሮች ጋር የጠበቀ ግንኙነትና እንዲሁም ሁለገብ ድጋፍ ያላቸው የራቢጣው ቀንደኛ መሪዎች አብዛኛዎቹ በምርጫው ወደቁ።

የንቡረዕድ ዲሜጥሮስና የደጃዝማች አስፋሐ ወዳጆች ብቻ ሳይሆኑ የአንድነት ደጋፊ የሆኑት የእነ ሼህ አሊ ራዳይ ወገኖችና ሌሎችም በብዛት ተመረጡ።

በሁለተኛው ዙር ምርጫ በኢትዮጵያ አንድነቶች ብዙሃን የተሞላው ምክር ቤት በፋንታው ደጃዝማች አስፋሐ ወ/ሚካኤልን ለመስተዳድሩ መሪነት ቀደም ብለው በጊዜያዊነት ለአንድ ዓመት የተመረጡትን የፓርላማውን ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት በድጋሚ ያለአንዳች ተቃውሞና ድምፀ ተአቅቦ በሙሉ ድምፅ መረጣቸው።

ደጃዝማች አስፋሐና እድምተኞቻቸው በጊዜያዊነት ሥልጣን ከያዙበት እንደ አውሮፓ አቆጣጠር 1955 ዓ.ም ጀ ምሮ እስከ ሁለተኛው የፓርላማ መማክርት ምርጫ እስከ 1956 ዓ.ም መጀመሪያ ድረስ በአንድ ዓመት ውስጥ የተከናወነው የተግባር ውጤት እንደተጠበቀው ፌደሬሽኑን ለማፍረስ ያስፈልጋሉ የተባሉትን የመጀመሪያዎቹን ቅድመ ሁኔታዎች ያሟላ በመሆኑ በአዲስ አበባና በአሥመራ ከፍ ያለ ደስታን ፈጥሯል።

ደጃዝማች ተድላ ባይሩና የተቀሩትም የእሳቸው እድምተኞች የነበሩት የፌደሬሽኑ ከፍተኛ የአመራር አካላት ከምክር ቤቱና ከመስተዳድሩ ሥልጣናቸው ከተነሱበት ጊዜ ጀምሮ እነደጃዝማች አስፍሐ በጊዜያዊነት ከመሩበት የአንድ ዓመት ጊዜ እስከ ሁለተኛው ዙር የፓርላማ ምርጫ ድረስ የተከናወኑትን ፌደሬሽኑን የመገዝገዝ ተግባሮችና ውጤታቸው ወደ ማፍረስ የሚወስደውን ጎዳና በሚገባ የጠረጉ ናቸው ተብሎ በኤርትራ የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አመራር አካላትና ንጉሡን ጨምሮ በማዕከላዊ መንግሥት ባለሥልጣኖች ሲታመን የሚያስከትለው መዘዝ ግን በማንም ዘንድ ግንዛቤ ያገኘ አይመስልም።

ከፀረ-ኢትዮጵያዊነትና ከፀረ-አንድነት አቋም ተመልሰው በኢትዮጵያ አንድነት ግን አፍቃሬ ፌደሬሽን አቋም የያዙትን የራቢጣውን ሊግ አመራር አካላት ከፌደሬሽኑ ስልጣን ተሳታፊነት ባገለላቸው የአንድነቶች ድርጊት ያኮረፉ መሆናቸውንና ይህም ኩርፊያ ውሎ አድሮ የሚያስከትለውን መዘዝ ወደፊት በሂደት የምንመለከተው ይሆናል በማለት ለአንባቢ ጠቋሜ ወደ ምዕራፍ ሃያ አመራለሁ።

ምዕራፍ ሃያ

የደጃዝማች አስፍሐ ወልደ ሚካኤልና እድምተኞቻቸው የሆኑት ከፍተኛ የምክር ቤቱና የመስተዳድሩ አመራር አካላት ሁለተኛው የሥልጣን ዘመን

ደጃዝማች አስፍሐ ወ/ሚካኤል በጊዜያዊነት ለአንድ ዓመት በፓርላማው መማክርት ተመርጠው የፌደሬሽኑን መስተዳድር የመምራት ሥልጣን በተረከቡ ማግሥት «ፌደሬሽኑን ለማፍረስ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ። እነኝህም ተግባሮች ጊዜንና ጥንቃቄን የሚጠይቁ ስለሆነ ጊዜ ስጡኝ ሲሉ የኢትዮጵያን አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አመራር አካላት አባላትን መጠየቃቸው ይታወሳል።

ለማፍረስ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች ያሏቸውን ተግባሮች ማለትም የሁለተኛውን ዙር የፓርላማ መማክርት ምርጫ መሰናዶ አጠናቀው ምርጫው ተካሂዶ የተጠበቀው ውጤት ተገኝቶ አስፍሐና ግብረ አበሮቻቸው ወደ ሁለተኛው መደበኛ ሥልጣን ማለትም የሚቀጥለውን የአራት ዓመታት ጊዜ ሥልጣን በተረከቡ ማግሥት ደግሞ አሁንም ደረጃ በደረጃ የሚከናወኑ ሥራዎች ስለአሉ ፌደሬሽኑን ማፍረስ በአጭር ጊዜና በጥድፊያ የምንደርስበት ግብ አይደለምና ትዕግሥት ያሻል የሚል ማሳሰቢያ ለአንድነቶች አቀረቡ።

ይህንን ማሳሰቢያ አቅርበው ለተከታታይ ሦስት ዓመታት የታወቁ ወይም ጎልተው የታዩ ፌደሬሽኑን የመገዝገዝ እርምጃ ያልወሰዱ ብቻ ሳይሆን ድምፃቸውም ስለአልተሰማ ከመሀል አገር ወዳጆቻቸው አንዳንዶቹ አስፍሐም እንደ ተድላ ባይሩ የመስተዳድሩን ሥልጣን ከደጃዝማችነት ማዕረግ ጋር በማጣጣም ላይ ያሉ ይመስላል በማለት እንደ አሟቸው ገልፀውልኝ በእሳቸው በኩል ግን ፌደሬሽኑን ለማፍረስ ያስቻሉን እጅግ ጠቃሚ ሥራዎች የተሰሩት ከሁለተኛው ዙር የፓርላማ ምርጫ በኋላ በተገኘው ጊዜ ነው የሚሉ ናቸው።

በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ስለተሰሩት እጅግ ጠቃሚ ስራዎች ሲያብራሩም በሁለተኛው መደበኛ የሥልጣን ዘመን ያተኮር ነው። ህዝቡ በሚኖርባቸው መንደሮች፣ በሚውልባቸው የስራ ቦታዎች፣ በቤተክርስቲያንና መስጊዶች ወዘተ የትምህርትና የውይይት መድረኮችን ከፍተን የህዝቡን ንቃተ ህሊና በማዳበር ማንነቱንና ምንነቱን ያውቅ ዘንድ ታሪኩን በማስተማር ከወገናችን ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ፍፁምመዋሀዱ የሚያስገኘውን ታሪካዊ፣ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፋይዳዎች በማስረዳት ወትሮም የነበረውን የአገር ፍቅርና ብሄራዊ ስሜት ወይም ኢትዮጵያዊነቱን በከፍተኛ ደረጃ የገነባነው በዚህ ጊዜ ነው።

ኢትዮጵያዊነትን ይበልጥ ለማዳበር ለሦስት ዓመታት ያህል ያለ ማቋረጥ በህዝቡ ውስጥ የተሰሩት ስራዎች ሦስት ፍሬያማ ውጤቶችን አስገኝተዋል።

እነሱም-

1ኛ. የኤርትራን ፌደሬሽን አቋም ለማዋቀርና ህገ መንግሥት ለማርቀቅ የተባበሩት መንግሥታት ማህበር የላከውኮ ሚሽን የኤርትራን ህዝብ ሳይጠይቅ እንደውም እየተቃወመ የፌደሬሽኑ ህልውና ገላጭ ወይም ምልክት ነው ብሎ በኤርትራ ያቆመውን ባለሰማያዊ ቀለም ባንዲራ ወርዶ የኢትዮጵያ ህዝብ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ብቻውን ይውለበለብ ዘንድ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ታህሳስ 24 ቀን 1959 ዓ.ም ለፓርላማው መማክርት ያቀረብነው ሃሳብ ያለአንዳች ተቃውሞ በመማክርቱ ሙሉ የድጋፍ ድምፅ እንዲፀድቅ ማድረግ ተቻለ።

2ኛ. በኢትዮጵያ ሁለት መንግሥቶች እንዳሉ በማስመሰል «የኤርትራመንግሥት» እየተባለ እንዲጠራ ሰይሞ የሄደውን ስም ሰርዘን እንደተቀሩት የኢትዮጵያ ክፍለ ሃገሮች ሁሉ የኤርትራ አስተዳደር እንዲባል መራሄ መንግሥት ይባል የነበረውም ግለሰብ አስተዳዳሪ ተብሎ ይጠራ ዘንድ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በግንቦት ወር 1960 ዓ.ም ለፓርላማው መማክርት ያቀረብነው የለውጥ ሐሳብ ያለ አንዳች ተቃዉሞና ተአቅቦ በመማክርቱ ሙሉ የድጋፍ ድምፅ እንዲፀድቅ ማድረግ ተቻለ።

3ኛ. በሦስተኛው ዙር የፓርላማ መማክርት ምርጫ ጊዜ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታይ የሆነው ጠቅላላው የኤርትራ ህዝብ ማለት ይቻላል ከየአውራጃውና ከየወረዳው እስከ መንደር የምክር ቤት ተወካዩቹን በመረጠበት ጊዜ ማነው ኢትዮጵያዊ? ማነው ለአገሩና ለሰንደቅ ዓላማው ታማኝ እያለ በመጠየቅ የኢትዮጵያን አንድነት ደጋፊዎች በነቂስ በመምረጡ ምክንያት አንድም ተቃዋሚና አፍቃሪ ፌደሬሽን ሳይቀላቀል የፓርላማውን መማክርት በሙሉ የአንድነት ደጋፊዎች ማድረግ ተችሏል።

በኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አባላትና በአንድነት ደጋፊዎች የተሞላው የሦስተኛው ዙር የፓርላማ መማክት በአዲሱ አጠራር የኤርትራ አስተዳዳሪ የተባልኩትን እኔን የሁለተኛው ፓርላማ ፕሬዝዳንት የነበሩትን ሼህ መሀመድ ፈረጁንና እንዲሁ በሁለተኛው ዙር ፓርላማ ምክትል ፕሬዝዳንት የነበሩትን ንቡረዕድ መላከ ሠላም ዲሜጥሮስ ገ/ማርያምን በድጋሚ ለሦስተኛ ጊዜ ያለ አንዳች ተቃውሞ በሙሉ የድምፅ ድጋፍ ተመረጥን ብለዋል።

ደጃዝማች አስፍሐ ወ/ሚካኤል ደጃዝማች ተድላ ባይሩን ከአንድነቶች ጋር ሆነው «ደጃዝማች ፌደራሊስት» የሚል ስም ከመስጠት ባሻገር በመጀመሪያው ዙር የፓርላማ ዘመን ፌደሬሽኑን ለማፍረስ ፈቃደኛ አልሆኑም ብለው ከወቀሷቸው ሰዎች አንዱ የሁለት ዙር የፓርላማ የስራ ዘመን በመውሰዳቸው ሳይወቀሱ በረቀቀ ዘዴና ደረጃ በደረጃ ባከናወኑት ፌደሬሽኑን የመገዝገዝ ተግባራቸው ለማፍረስም እንደሚበቁ የተማመኑባቸው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በኤርትራ እንደራሴያቸው የሆኑትን ቢትወደድ አንዳርጋቸውን የራስነት ማዕረግ ሰጥተው ወደ አገር አስተዳደር

ሚኒስትርነት በማዛወር በምትካቸው የቀድሞ አማቻቸውን ሌ/ጀነራል አቢይ አበበን በኤርትራ ሁለተኛው እንደራሴያቸው አድርው በሾሙበት እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1961 ዓ.ም ደጃዝማች አስፍሐ ወ/ሚካኤልንም የቢትወደድ ማዕረግ በመስጠት አስደሰቷቸው።

እንደ ቢትወደድ አስፍሐ አነጋገር ከሦስተኛው ዙር የፓርላማ መማክርት ምርጫ በኂላ ለመጨረሻ ጊዜ ፌደሬሽኑን ለማፍረስ ከተወሰዱት እርምጃዎች ትልቁና ወሳኙ በ1962 ዓ.ም መገባደጃ ላይ በግንቦት ወር ጃንሆይ እንደተለመደው ኤርትራን ለመጎብኘት በመጡ ጊዜ አጋጣሚውን በመጠቀም የተሰራው ስራ ነው።

በዚህ ጉብኝት ጃንሆይ ኤርትራ በሰነበቱበት ጊዜ ለሦስተኛው ዙር የፓርላማ መማክርት፣ በመስተዳድሩ ውስጥ ለሚሰሩ ሹማምንት፣ ለአውራጃና ለወረዳ አስተዳዳሪዎች፣ የመንግሥት ተቀጣሪ ሳይሆኑ በግል ጥረታቸው ለሚተዳደሩ፣ ጡረታ ላይ ላሉና ለአንድነት ለታገሉ እውቅ ሰዎች በኔ አቅራቢነት የጃነሆይ መልካም ፈቃድ ሆኖ ከባላምባራስነት እስከ ደጃዝማችነት ድረስ ያለውን ልዩ ልዩ ማዕረግ ለበርካታ ሰዎች ሹመት ማሰጠት መቻላችን ነው።

ከሹመትም በላይ በተጨማሪ እንዲሁ ለበርካታ ባለውለታዎች እንደ አገልግሎታቸው የተለያዩ ደረጃ ያላቸውን ኒሻኖች፣ የገንዘብና የተለያዩ የቁሳቁስ ስጦታዎች ማሰጠት ስለተቻለ በኤርትራ በአጠቃላይ በአስመራ ከተማ በተለይ የፈጠረው ደስታ ከጠበቅነው በላይ እጅግ ከፍ ያለ ሆነ።

ብረትን ማረቅና ማነፅ የሚቻለው በእሳት በጋለ ጊዜ ነው እንዲሉ እኛም የኢትዮጵያዊነት ስሜት በጋለበት በ1962 ዓ.ም ከንቡረዕድ ከመላከ ሠላም ዲሜጥሮስና ከሌሎችም የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር የአመራር አካላት ጋር ሆነን ፌደሬሽኑን ለማፍረስ የመጨረሻውን እርምጃ ለመውሰድ መላውን የፓርላማ መማክርት አስተባበርን።

የመማክርቱ ሙሉ ስምምነት ከተገኘ በኂላ ፌደሬሽኑን ለአንዴና ለመጨረሻ አስወግደው ከእናት ኢትዮጵያ ጋር ፍፁም ውህደት ለማድረግ ሁሉም መስማማታቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድ ተዘጋጅቶ የመማክርቱ የስም ዝርዝር ሰፍሮበት ለውሳኔያቸው ማስረጃነት ተብሎ መማክርቱ እንዲ ፈርሙበት ከተደረገ በኂላ እንደራሴው ሌ/ጀነራል አቢይ አበበ የተዘጋጀውን ሰነድ ይዘው አዲስ አበባ በመሄድ ውሳኔያችንን ለጃንሆይ አቅርበው በማስረዳት መልካም ፈቃዳቸውን እንዲያመጡልን ጠይቀናቸው ወደ አዲስ አበባ እንዲሄዱ አደረግን።

ለጃንሆይ በላክነው ሰነድ ራስጌ እጠቅሳለሁ «የስም ዝርዝራችን ከዚህ ግርጌ የተመለከተው እኛ የኤርትራ ህዝብ ተወካዮች ለግርማዊነትዎ ልባዊ ፍቅር ያለው ታማኝ የኤርትራ ህዝብዎ ለብዙ ጊዜ የቆየና በተደጋጋሚ ባቀረብልን ጥያቄ፣ ምኞትና

ፍላጎት መሰረት ይህንን ከኢትዮጵያ ህዝብ ተነጥለን እንድንታይ ያደረገ ፌደሬሽን የተባለ ህገ መንግሥት አፍርሰን ሙሉ የአስተዳደር ውህደት ለማድረግ ቁርጠኛ ውሳኔ ስለአደረግን የግርማዊ ንጉሠ ነገሥታችንን መልካም ፈቃድ እንጠይቃለን» የሚል ነው።

እንደራሴው ሌ/ጀነራል አቢይ አበበ በጥያቄያችን መሰረት ከጃንሆይ ጋር ለብቻ ከተነጋገሩ በኋላ የጠየቅነው ተፈቅዶ በዚያው ዕለት ማለትም እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ህዳር 13 ቀን 1962 ዓ.ም አስመራ ተመለሱ።

የንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ከተገኘ በኋላ የኤርትራ ህዝብ ተወካይ የሆኑት የፓርላማው መማክርት ህዳር 15 ቀን 1962 ዓ.ም ተሰብስበው ያለ አንዳች ተቃውሞና ድምፅ ተአቅቦ በተባበረ ሙሉ ድምፅ ፌደሬሽኑን በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ማፍረሳቸውን በብዙሃን ማሰራጫ ሲያበስሩ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ውሳኔውን በታላቅ ደስታ ተቀብሎ ለፌደሬሽኑ ልደት እንደ አደረገው ሁሉ የግብአተ መሬት በዓሉንም ከዳር እስከ ዳር በታላቅ ሥርዓት አከበረ።

የተባበሩት መንግሥታት ማህበር አምስተኛ ጠቅላላ ጉባዔ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ታህሳስ 2 ቀን 1950 ዓ.ም ምሽት ላይ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌደሬሽን እንድትቀላቀል ከወሰነበት ሰዓት ጀምሮ ፌደሬሽኑ እስከ ተቋቋመበት፣ በፌደሬሽኑ ልደት፣ ፌደሬሽኑን ለመገዝገዝና ብሎም ለማፍረስ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አባላት ከኤርትራ ህዝብ ጋር ሆነው ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ህዝቦች ፍፁም ውህደት ሲሉ የወሰዷቸውን ተከታታይ እርምጃዎች ከዚህ በላይ ተመልክተናል።

ለፍፁም ውህደት የተደረገው ጥረት መሪና አስተባባሪ ከሆኑት የአገር ፍቅር ማህበር የአመራር አካላትና አባላት ከሌሎችም ማለትም ታሪኩን ከተከታተሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለውህደቱ ስኬታማነት አስተዋፅኦ ካደረጉ በስራውም ከተባበሩና በገለልተኝነት ታዛቢ ከነበሩ የኤርትራ ክፍለ ሃገር ተወላጆችና ከመሀል አገር ነዋሪዎች ከልዩ ልዩ የታሪክ ማስረጃዎች ብቻ ሳይሆን በትግሉ ጊዜ የአንድነት ተፃራሪና በኋላም ከፌደሬሽኑ መመስረት በኋላ አፍቃሬ ፌደሬሽን ከነበሩት ኤርትራዊያን ጭምር መረዳት እንደተቻለው የኤርትራ ፌደሬሽን የተቋቋመውና በኋላም የፈረሰው በኤርትራ ህዝብ በራሱ ፈቃድና ፍላጎት መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው።

በኋላ ለተፈጠረው ችግር መፍትሄ ፍለጋ በድህረ አብዮት ያነጋገርናቸው የቀድሞ የአንድነት ተቃዋሚዎችና በኋላ የፌደሬሽን አፍቃሪዎች ጭምር ያስረዱን፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አባላት ፌደሬሽኑን ለማፍረስ የተጠቀሙት ስልት ኃይልን ሳይሆን አብዛኛውን የፌደሬሽን አፍቃሪዎች በማግባባትና በማሳመን የአንድነት አቋም እንዲይዙ በማድረግ ነው።

የፌደሬሽኑ ማቋቋሚያ ህገ መንግሥት በሥራ ላይ እንዲውል በብያኔ ድምፅ ያፀደቁት የኤርትራ ህዝብ ተወካዮች አስፈላጊ መስሎ በታያቸው ጊዜ በህዝቡ ጥያቄና በምክር ቤታቸው መማክርት ብያኔ ድምፅ ፌደሬሽኑን ለማፍረስ የወሰዱት እርምጃ ዲሞክራሲያዊ ባህሪውና ህጋዊነቱ አጠያያቂ ባይሆንም እነዚያ እጅግ የተከበሩ ብቻ ሳይሆኑ፣ የአካባቢ ጠባብ ስሜትንና የጎሳን አጥር ሰብረው የወጡ፣ አርቆ አስተዋይና ነፃ ኢትዮጵያዊያን በኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ ታላቅ ስፍራ ያላቸው ታላላቅ አርበኞች እንደዚያ የጠሉትን ፌደሬሽን ለማፍረስ ያከናወኗቸው ተግባሮች በሙሉ እንከን አልባ ነበሩ ማለት አልነበረም።

ያከናወኑት የአርበኝነት ተግባር የኤርትራን ክልል ህዝብና የኢትዮጵያን ህዝብ ፍፁም ውህደት የፈጠሩ ብቻ ሳይሆን ከፌደሬሽኑ መፍረስ በኋላ ለተፈጠረው ችግር መንስኤ መሆኑን መካድ የሚቻል አይደለም።

በትግላችን ቅፅ አንድ በዚህም በቅፅ ሁለት ላይ የመስፋፋት ፍላጎት የተጠናወታቸውና ቅኝ ግዛት የጠማቸው የአካባቢው ታሪካዊ ጠላቶቻችንና የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች ለአምስት መቶ ዓመታት እየተመላለሱ በመፈራረቅ ሲያጠቁንና ስንከላከል መኖራችን ተገልጿል።

የኤርትራ ችግር ትናንት በተፈጠሩና የፖለቲካ ጎርፍ ባመጣቸው፣ የአረቦች የዘይት ዶላር በፈጠራቸው «በጀብሐና በሻዕቢያ» የተወጠነ ሳይሆን ለረጅም ጊዜ የተደረጉብን ወታደራዊና ባህላዊ ወረራ ውጤት ስለመሆኑ ብዙ ተብሏል።

በመጨረሻም ከ18ኛ ምዕተ ዓመት መገባደጃ ጊዜ ጀምሮ ለሃምሳ ዓመታት ኤርትራን ቅኝ ግዛቱ ያደረገውን የፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ከኢትዮጵያ ምድር ለማስወጣት የተባበረን የኢምፔሪያሊስት ብሪታኒያ መንግሥት ሠራዊት ሌላ ቅኝ ገዥ ሆኖ በኤርትራ ሠራዊት ከኤርትራ ለማስወጣትና የኤርትራን ክልል ህዝብ ከወገኑ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር መልሶ ማዋሀድን ዓላማው አድርጎ የተቋቋመውን የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር በመፃረር እንግሊዞች የፈጠሯቸው ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-አንድነት የፖለቲካ ድርጅቶች ጥያቄዎች ሲጠቃለሉ ዓይነተኛ ዓላማቸው ኤርትራን ከኢትዮጵያ ነጥሎ የባዕዳንን መሣሪያ የሆነ ደካማና አሻንጉሊት ንዑስ መንግሥት በኤርትራ መመስረት ነበር።

እነዚህ ከኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር ዓላማና ፍላጎት እጅግ የራቁ አንጃ ገንጣዮችን በሠላም ጎዳና ግማሽ መንገድ በማስኬድ አቀራርቦ የኢትዮጵያን ህዝብ ሠላምና ደህንነት፣ ታሪክና የአንድነት ችግር ለማስወገድ አንድነቱን ቢያንስ በፌደሬሽን ቁርኝት ለማስጠበቅ የተባበሩት መንግሥታት ማህበር አምስተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ከወሰነው የተሻለ መፍትሄ ነበር ብሎ ለማሰብ ያዳግታል።

በታወቁና ስርበሰደዱ፣ ባዕዳን ጣልቃ ገቦች በፈጠሯቸው ታሪካዊ የፖለቲካ ችግሮች ኢትዮጵያና ከኤርትራ ጋር ፌደራላዊ ቁርኝትን መፍትሄ አድርጋ በመቀበል በዓለም የመጀመሪያም የመጨረሻም አገር አልነበረችም።

በአገራቸው የቆዳ ስፋትና በህዝባቸው ብዛት ከኢትዮጵያ በጣም የሚልቁ፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝት፣ በአገር ልማትና ግንባታ እጅግ እርቀውን የሄዱ በርካታ መንግሥታት አደረጃጀታቸው ፌደራላዊ ነው።

የኤርትራን ፌደሬሽን ያቋቋመውን ህገ መንግሥትይዘት ብንመለከት ንጉሡ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና ብዙዎቹ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣኖች፣ መሳፍንቱና መኳንንቱ እንደ አዩትና እንደዘጉበት ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት ጠንቅ ይሆናል ተብሎ የሚፈራ፣ የንጉሡ ነገሥቱን መለኮታዊ ሥልጣን የሚያንኳስስና የሚቀንስ አልነበረም።

የኤርትራ ክፍለ ሃገር ተወላጆች ብቻ ሳይሆኑ ብዙዎቹ የመሀል አገር ነዋሪ ኢትዮጵያዊያንም እንደሚያምኑትና እንደ ሚገምቱት ለኤርትራ ክልል የሠላም ችግር መንስኤ የፌደሬሽኑ መፍረስ ከሆነ በማለት በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግሥት በ1968 ዓ.ም በመፍትሄነት ያቀረበው ክልላዊ የራስ ገዝ አስተዳደር ሥልጣን (Regional Autonomy) ከማዕከላዊ መንግሥት ጋር ያለው ቁርኝት፣ በጋራ ገንዘብ፣ በውጭ ጉዳይና በሃገር መከላከያ ጉዳዮች ብቻ ሆኖ የተቀሩት ማለትም አስተዳደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ወዘተ ጠቅላላ ጉዳዮች የክልሉ በመሆናቸው ከፈረሰው ፌደሬሽን በጣም የላቀ ጠንካራ ሥልጣን ያለው ራስ ገዝ ነበር።

ራሳቸውን ጀብሐና ሻዕቢያ በማለት የሚጠሩት ገንጣዮች ያኮረፉት የፌደሬሽን አፍቃሪዎች ብሶታቸውን የተወጡ መስሏቸው ለበቀል የጀመሩትን የትጥቅ አመፅ አጋጣሚ እንደ መረማመጃ ተጠቀሙበት እንጂ ዓላማቸው የፈረሰውን ፌደሬሽን ለማስመለስ ሳይሆን ኤርትራ የኢትዮጵያ መንግሥት ቅኝ ግዛትናት ብለው በፈጠሩት የሐሰትና የክህደት ታሪክ ላይ ተመስርተው ለመገንጠል የቆሙ ስለሆነ አብዮታዊው መንግሥት ያቀረበላቸውን የላቀ ክልላዊ የራስ ገዝ ሥልጣን መፍትሄ ለመቀበል ፈቃደኞች አልሆኑም።

ለኤርትራ ችግር በመፍትሄነት የተባበሩት መንግሥታት ማህበር 5ኛ ጠቅላላ ጉባዔ የወሰነውና በኋላም የኤርትራ ክፍለ ሃገር ህዝብ በተወካዮቹ አማካኝነት ያፀደቀው የፌደሬሽን አስተዳደር የተመሰረተበትን የህገ መንግሥት ይዘት ከዚህ እንደሚከተለው ብንመለከት፣

1ኛ. ከዚህ በፊት እንደተባለው በሁለት አቻና ሉአላዊ መንግሥታት መካከል የተደረገ ፌደራላዊ ጥምረት ወይንም ትስስር ሳይሆን በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘውዳዊ መንግሥት ሥር የሚተዳደር ክልላዊ የራስ ገዝ አስተዳደር ነው።

የኤርትራን ፌደሬሽን ወይንም ክልላዊ የራስ ገዝ አስተዳደር ከሌሎቹ የአገሪቷ ክልላዊ አስተዳደሮች ወይንም ክፍለ ሃገሮች ልዩ የሚያደርገውና ራስገዝ ያሰኘው ለክልሉ ህዝብ መተዳደሪያና መመሪያ የሆነ ህግ የማውጣት ሥልጣን ያለውና በህዝብ ተመርጠው ህዝቡን የሚወክሉ መማክርትን የያዘ የህዝብ ምክር ቤት ወይንም ፓርላማና ፓርላማው ወይንም ህዝባዊው ሸንጎ የሚያወጣቸውን ህጎች በአስፈፃሚነት ወደ ተግባር እየተረጎመ ህዝቡን የሚያስተዳድር መስተዳድር ወይም የተደራጀ ስራ አስፈፃሚ (Executive) ያለው በመሆኑ ነው።

2ኛ. በዓለም ላይ ካሉት አብዛኛዎቹ ፌደራላዊ የመንግሥት አደረጃጀት ልዩ የሚያደርገው ከፌደሬሽኑ የህዝብ ምክር ቤትና መስተዳድር በላይ ዘውዱን የሚወክል የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ መኖሩ ነው።

3ኛ. የዘውዱ ተወካይ እንደራሴ በፌደሬሽኑ ክልል የሃገር መከላከያን፣ የውጭ ጉዳይን፣ የውጭ ንግድን፣ ጠቅላላ ፋይናንስን፣ የአሰብንና የምፅዋን ወደቦች ጨምሮ የአየርና የባህር መንገዶችንና መጓጓዣዎችን አካቶ ጠቅላላ የመገናኛ ጉዳዩችን የመቆጣጠርና ስራዎቹ በአግባቡ መከናወናቸውን የማረጋገጥ ሥልጣን አለው።

4ኛ. በኤርትራ ክልል ውስጥ ያሉትና ድንበርተኛ ወይም ተጎራባች የሆኑትን የባህር ጠረፎች፣ የደሴቶች፣ ዓሣ ማስገር፣ የመርከቦች ዘገባና የወደብ ጉዳዮች ከውጭ ጉዳይ፣ ከብሄራዊ ደህንነትና ከሃገር መከላከያ ጉዳዮች ጋር የተሳሰሩ በመሆናቸው ማዕከላዊ መንግሥትን የሚመለከቱ የስራ ዘርፎች ናቸው።

5ኛ. የዘውዱ ተወካይ እንደራሴ በፌደሬሽኑ የፓርላማ መማክርት የሚወጡ ህጎች በስራ ላይ ይዉሉ ዘንድ የማፅደቅ ሥልጣን አለው። እንደራሴው ያላፀደቀው ህግ በስራ ላይ ሊውል አይችልም።

6ኛ. የዘውዱ ተወካይ እንደ ራሴ በፌደሬሽኑ ፓርላማ መማክርት ተመክሮባቸው የሚወጡት ህጎች ከማዕከላዊ መንግሥት ፖሊሲና ህጎች ጋር የሚጋጩ መስሎ ከታየው የማገድ ሥልጣን አለው።

7ኛ. በራስ ገዙ ክልል ውስጥ የሚነሱ ክሶችና በራስ ገዙ የፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጣቸው ጉዳዩች ላይ ዜጎች በግል ወይም በወል እንዲሁም ድርጅቶች ይግባኝ ቢጠይቁ የማዕከላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን የማየት ሥልጣን አለው።

8ኛ. ዜግነትን በተመለከተ በራስ ገዝ ክልል ውስጥ የሚኖሩት ዜጎች በሙሉ ኢትዮጵያዊ ዜጎች ናቸው።

የኤርትራን ፌደሬሽን ህገ መንግሥት ያረቀቀው የተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽን የፌደሬሽኑን መስተዳድር በእንግሊዝኛ ቋንቋ (Government of Eritrea) በሚል ስያሜ ነው በህገ መንግሥቱ ውስጥ ያሰፈረው። ይህ ስም ወደ አማርኛችን ሲመለስ የኤርትራ መንግሥት ማለት ስለሆነ የኤርትራ ክልል ህዝብም ይህንን ስያሜ ተከትሎ መስተዳድሩን «መንግሥቲ ተድላ» ደጃዝማች ተድላ ባይሩን ደግሞ «መራሂ መንግሥት» እያለ ነበር የሚጠራቸው። የመንግሥት መሪ እንደማለት ነው።

እዚህ ላይ አንባቢ ሊያጤነው የሚገባ ነገር ኮሚሽኑ ለፌደሬሽኑ በጠቅላላ የሰጠው ስም ከፌደሬሽኑ አደረጃጀትና ሥልጣን ጋር የሚጣጣም ያለመሆኑን ነው።

ህገ መንግሥቱ በሚረቀቅበት ጊዜ በአርቃቂው ኮሚሽን አባላትና በኢትዮጵያ መንግሥት ተወካዮች መካከል ከፍ ያለ ክርክርና የአመለካከት ልዩነት በመፍጠሩ በብዙ ጉዳዮች ላይ ያልተስማማው የኢትዮጵያ መንግሥት የህገ መንግሥቱን አንዳንድ የህግ አንቀፆች ብቻ ሳይሆን በጠቅላላ ህገ መንግሥቱንና ፌደሬሽኑን ጨርሶ ወደ አለመቀበል ውሳኔ በማምራቱ የኮሚሽኑ ተልዕኮም መክሸፍ ደረጃ ላይ መድረሱን የተገነዘቡት የኮሚሽኑ አባላት በአንድ ወገን ስለ ኢትዮጵያ መንግሥት ስጋትና ፍላጎት ተገቢውን ግንዛቤ በመውሰድ ለማግባባትና በሌላ በኩል ደግሞ ተፃራሪ የሆኑት የፖለቲካ ድርጅቶች ማለትም የኢትዮጵያ ህዝቦች አንድነት የአገር ፍቅር ማህበርና አንድነት ተቃዋሚዎችን ለማቀራረብና ቢቻልም ሁሉንም በማስደሰት ተልዕኮአቸውን ስኬታማ ለማድረግ የተጠቀሙት የረቀቀ የዲፕሎማሲ ቋንቋ ነው።

የፌደሬሽኑን መስተዳድር መንግሥት በተሰኘስም መሰየማቸው በኢትዮጵያ ሁለት መንግሥት ሊኖር አይችልም የሚሉትን የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አባላትን የሚያስቆጣ መሆኑን ስለሚያውቁ አንደኛ፣ የመንግሥት መሪ የሚባለውን ግለሰብ «ስራ አስፈፃሚ» (Executive) አሉት እንጂ እንደ መንግሥት መሪ ፕሬዝዳንት ወይም ጠቅላይ ሚኒስትር የተሰኘ ስምና ማዕረግ አልሰጡትም።

ሁለተኛ፣ መንግሥት የሚል ስም በሰጡት ተቋም ማለትም ለመስተዳድሩ እንደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ሁሉ « Cabinet» ቢሉትም ከሁሉ በፊት አስተዳዳሪው በእነሱ አጠራር ከስራ አስፈፃሚው ግለሰብ ሌላ በካቤኔቱ ውስጥ የሚገኙት ሰዎች የጥቂት የስራ ዘርፎች ማለትም የአስተዳደር፣ የፋይናንስ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጉዳዮች ወዘተ መምሪያ ኃላፊዎች ወይም ፀሃፊዎች (Secretorite) የሆኑ አምስት ሹማምንት ብቻ ሲሆኑ በማዕረግ ደረጃ ወይም ፕሮቶኮል ሚኒስትሮች አልነበሩም።

መንግሥትና ካቢኔት ተብለው በህገ መንግሥት ውስጥ የሰፈሩት ለተቃዋሚዎቹ መደለያ የሆኑ ዲፕሎማሲያዊ ቃላቶች ብቻ ሲሆኑ የመስተዳድሩ መሪ ወይም ስራ

አስፈፃሚው ግለሰብ በፓርላማው መማክርት ከተመረጠ በኋላ በቅድሚያ በትክክል መመረጡን ከማረጋገጥ ባሻገር የተመረጠበትን ሥልጣን ለመረከብ የዘውዱ ተወካይ እንደራሴ ፈቃድና ይሁንታ ያስፈልገዋል።

መንግሥት የተሰኘ ስም የተሰጠው የኤርትራ ክልል ራስገዝ መስተዳድር ላዕላይ መዋቅር ውስጥ ማለትም በምክር ቤቱ፣ በመስተዳድሩ፣ በአውራጃና በወረዳ ክልሎችና በልዩ ልዩ መንግሥታዊ በሆኑ የአገልግሎት ተቋሞች ውስጥ ለተሰለፉት የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝና አጠቃላይ የስራ ማስኬጃ ወጭና ፍጆት አልፎ አልፎ ለክልሉ ልማትና ግንባታ የሚያስፈልገውን ገንዘብ የራስ ገዙ ክልል ሊሸፍን ስለማይችል በየዓመቱና በየምክንያቱ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ማዕከላዊ መንግሥት ይደጉም ዘንድ ማመልከትና ለየስራው አግባብ ያላቸውን የማዕከላዊ መንግሥት መስሪያ ቤቶችን ከራስ ገዙ መስተዳድር ጋር ማስተባበር የዘውዱ ተወካይ እንደራሴ ሥራ ነው።

የኤርትራን ፌደሬሽን ያቋቋመውን ህገ መንግሥት ይዘት በመጭመቅ በጣም ጎላ ብለው የሚታዩትን ብቻ ገለፅኩ እንጂ በህገ መንግሥቱ ውስጥ ሳይሰፍሩ በተግባር ብቻ የሚታዩ ጉዳዩች ብዙ ሲሆኑ አሁንም በጣም ባጠረ ሁኔታ ጥቂቶቹ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ. የኢትዮጵያ መንግሥት መከላከያሠራዊት ልዩልዩ የጦር ክፍሎች፣ ፀጥታ አስከባሪዎችና የደህንነት ጥበቃ ኃይሎች መጠናቸውና ዓይነታቸው ሳይወሰን እንደ አስፈላጊነታቸው ያለ አንዳች ገደብ በራስ ገዙ ክልል በማናቸውም ጊዜና ስፍራ መስፈርና መንቀሳቀስ ይችላሉ።

2ኛ. ንጉሠ ነገሥቱ የፌደሬሽኑን የምክር ቤት አባላትና የመስተዳድሩን ሹማምንት በህዝብና እንዲሁም በፓርላማው መማክርት ተመርጠው ስራቸውን ከጀመሩ በኋላ ያላቸውን ማዕረግ ከማሳደግ ኒሻንና ልዩ ልዩ ሽልማት ከመስጠት ያገዳቸው ነገር አልነበረም።

3ኛ. ማዕከላዊ መንግሥት ከምክር ቤቱና ከመስተዳድሩ ውጭ ያሉትን የኤርትራ ክልል ነዋሪዎች ከኤርትራ ከውጪ ወደ ሌሎቹ የአገሪቱ ክልሎች በማዛወር እንደየ ችሎታቸው ልዩ ልዩ ስራ መስጠት፣ በተለያዩ ኃላፊነቶች ላይ ማስቀመጥ፣ እንደ አስፈላጊነቱ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ልዩ ልዩ ሥልጠና መስጠት ወዘተ መሾምና መሻር ይችላል።

4ኛ. በትምህርት አመራር ረገድ ሥርዓተ ትምህርቱን የማውጣትና እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው ማሻሻል፣ የትምህርት ቤቶች ግንባታና ሥርጭት፣ የትምህርት መረጃ ቁሳቁሶች እደላ፣ የኤርትራን ራስ ገዝ ክልል ጨምሮ የአገሪቱ ዜጎችሁሉ በአገር ውስጥ፣ ለውጭ አገር ለከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ወዘተ የማዕከላዊ መንግሥት የስራ ድርሻና ኃላፊነት ነው።

የኤርትራ ፌደሬሽን የተቋቋመበትን ህገ መንግሥት አጠቃላይ ይዘትና በህገ መንግሥቱ ውስጥ ሳይደነገገ በተግባር በራስ ገዙ አስተዳደር ከማዕከላዊ መንግሥት ጋር ያለው የስራ ግንኙነትና የአስተዳደር ቁርኝት ሰፊ ስለሆነ ተደማጭነቱም የዚያኑ ያህል ከፍተኛ ነው።

የፌደሬሽኑን መቋቋም ምክንያት ስንመለከትም፣ በጊዜው ከነበረው የኤርትራ ክልል ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ከፌደሬሽን ሌላ አማራጭ መፍትሄ እንደአልነበረ ግልፅ ነው።

የፌደሬሽኑ ጥቅም ወይንም ፋይዳ ምንድን ነው ተብሎ ቢጠየቅ መልሱን ለማግኘት ከፌደሬሽኑ በፊት የነበሩትን የኤርትራ ሁኔታዎች በጥቂቱም ቢሆን መዳሰስ ያስፈልጋል።

ከሁሉ በፊት መታወስ ያለበት ለአምስት መቶ ዓመታት የአካባቢው ተስፋፊዎች በፈረቃ ላደረሱብን ጥቃትና ወረራ መመላለሻ በር የሆናቸው በባህር ጠረፍነቱ የኤርትራ ክልል መሆኑን ነው።

ከ18ኛው ምዕተ ዓመት መገባደጃ ጀምሮ የፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት ወሮ በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ ክብርና ነፃነታችንን ከመገፈፋችን ባሻገር ለ50 ዓመታት በቅኝ ገዥነት የተቀመጠው በኤርትራ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ በአፍሪካ ምድር ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ታላቅ ተጋድሎና መስዋዕትነት የፋሽስት ኢጣሊያን ወራሪ ሠራዊት ከመረብ ወንዝ ምላሽ ማስወጣት ቢቻልም በኤርትራ ክልል ነዋሪ የሆነው ወገናችን በኢጣሊያና ብሎም በእንግሊዞች የቅኝ አገዛዝ ቀንበር ውስጥ እስከ ነበረ ድረስ የኢትዮጵያዊያን ነፃነት የተሟላ አልነበረም።

የኤርትራ ክልል ነዋሪ ህዝብ ከባዕዳን ቅኝ ተገዥነት ተላቆ በነፃነት ከወገኑ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታና ገደብ በአስቸኳይ መዋሀድን ዓላማው አድርጎ ለመታገልና ህዝብን ለማታገል የተቋቋመውን መሪ ድርጅት የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበርን በመፃረር ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተነጥላ ነፃ አገር መሆን አለባት የሚሉ ገንጣይ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ጠላቶች ድጋፍና ግፊት ተቋቁመው የኤርትራን ህዝብ ከወገኑ ከኢትዮጵያ ህዝብ መነጠ ብቻ ሳይሆን የኤርትራን ህዝብ ራሱን ደገኛና ቆለኛ በሚል የአካባቢ ስሜትና በኃይማኖት ልዩነት ከፋፍለው ታሪኩን ብቻ ሳይሆን ደብዛውንም የሚያጠፋ እጅግ አደገኛ ሁኔታ መፍጠራቸው ይታወሳል።

ፌደሬሽኑ አማራጭ የሌለው መፍትሄ ሆኖ የተገኘበት ምክንያት ተቃዋሚዎቹን ነፃነት ወይም መገንጠል ከተሰኘና ከኢትዮጵያ ህዝቦች አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር

እጅግ የራቀ ተፃራሪ አቋማቸውን አስለቅቆ በማቀራረብ በመሀከላቸው የነበረውን የሰላና የማይታረቅ ቅራኔ ማለዘብ ብቻ ሳይሆን ፍፁም አስለውጦ በኢትዮጵያ ዘውዳዊ መንግሥት ስር በራስ ገዝ አስተዳደር ውህደትን መፍጠሩና ክልሉን ከከፋ አደጋ ማዳኑ ነው።

ከፌደሬሽኑ መመስረት በኂላ በቀድሞዎቹ ተፃራሪ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል የነበረው ቅራኔ ፍፁም ውህደትን በሚያራምዱት በኢትዮጵያ ህዝቦች አንድነት የአገር ፍቅር ማህበርና የፌደሬሽን አስተዳደርን በሚደግፉ መካከል የነበረ መናኛ ልዩነት እንጂ በኂላ ለ30 ዓመታት እንደሆነው በአንድነቶችና በገንጣዮች መካከል የሚካሄድ ፍልሚያ ወይም ጦርነት አልነበረም። ከሰላሳ ዓመታት በላይ ለተካሄደው የእርስ በእርስ ጦርነት ዋና ምክንያቶች ናቸው ባይባሉም ወደ ማይታረቀው ቅራኔ መረማመጃ የሆኑት መንስኤዎች ከዚህ የሚከተሉት መሆናቸው ይታመናል።

1ኛ. በሁለተኛው የፓርላማ መማክርት ምርጫ የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አባላትና የኢትዮጵያን አንድነት የሚደግፈው እስላማዊ ሊግ በህብረት በምክር ቤቱ ውስጥ የነበሩትን የተቃዋሚ ድርጅቶች የአመራር አካላት የነበሩ ቀንደኛ ግለሰቦች በምርጫው እንዲሸነፉ በማድረጋቸው አኮረፉ።

2ኛ. የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አባላትና ደጋፊዎቻቸው በሦስተኛው ዙር የፓርላማ መማክርት ምርጫ ጊዜ አብዛኛውን ቀድሞ ገንጣዮች የነበሩትንና በኂላ ፌደሬሽን አፍቃሪ የሆኑትን ወደ አንድነት አቋም ሊያመጡ ቢችሉም አመራር ላይ የነበሩትን ቀንደኛ ተቃዋሚዎች ግን ሊያካትቱ ወይንም ሊመልሱ አልቻሉም።

የኤርትራን ፌደሬሽን መስራች የሆኑትን የፓርላማ መማክርት የእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር ባስተናገደው ምርጫ የተመረጡት የተቃዋሚ ድርጅቶች አባላት በአጠቃላይና የራቢጣው ድርጅት ቀንደኛ የአመራር አካላት በሙሉ ተመርጠው እንደነበረ ይታወሳል።

እነ ቢትወደድ አስፍሐ ወ/ሚካኤል ጠቅላላው የአንድነት የአመራር አካላትና አባላት ከተቀሩት የአንድነት ደጋፊዎች ጋር ፌደሬሽኑን በማፍረስ የመጨረሻ መሰናዶ ብለው ለህዝቡ ባደረጉት ቅስቀሳ በሦስተኛው ዙር የፓርላማ መማክርት ምርጫ ጊዜ ፌደሬሽን አፍቃሪ የተባሉትን በሙሉ ማለት ይቻላል በምርጫው እንዲሸነፉ ማድረጋቸው የአኩራፊውን ቁጥር ያበራከተ ብቻ ሳይሆን አኩራፊዎች ተሰባስበው ወደ ቀድሞ ገንጣይ አቋማቸው እንዲመለሱ አስተዋፅኦ አድርጓል ማለት ይቻላል።

3ኛ. በ1962 ዓ.ም በግንቦት ወር አፄ ኃይለሥላሴ እንደ ተለመደው ኤርትራን የጎበኙበትን አጋጣሚ ጊዜ በመጠቀም ፌደሬሽኑን ለማፍረስ ይረዳል ተብሎ በአንድነቶች በታቀደው እቅድ መስረትና በቢትወደድ አስፍሐ ወ/ሚካኤል አቅራቢነት ንጉሡ ካርከፈከፉት በርካታ ሹመትና ሽልማት የተገለለ ፌደሬሽን አፍቃሪዎች ብቻ

ሳይሆኑ ከኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አባላትም መካከል የሹሙቱና የሽልማቱ በረከት ያልደረሳቸው በርካታ ሰዎች ስለእኛ አገልግሎትና ኢትዮጵያዊነት መስካሪው አስፍሐ ወ/ሚካኤልን የመሰለ የፋሽስት ኢጣሊያ ቅጥረኛ ባንዳ ነው ወይ? በማለት ክፉኛ ከማዘን ባሻገር ለንጉሡ የነበራቸውን ፍቅርና በመንግሥታቸው ላይ የነበራቸውን እምነት አጡ።

በእነ ቢትወደድ አስፍሐና በጠቅላላው በኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር የአመራር አካላትን ንጉሡን ጨምሮ በአብዛኛው የማዕከላዊ መንግሥት ባለሥልጣና ትዘንድ ፌደሬሽኑን አፍርሶ ፍፁም ውህደትን ለማምጣት የተወሰዱት እርምጃዎች በሙሉ በመላው የኤርትራ ክልል ህዝብ ፈቃድ፣ ፍላጎትና ተሳትፎ ነው የሚል ዕኑእምነት ስለነበራቸው አኩራፊዎች መኖራቸውንና ኩርፊያውም ውሎ አድሮ ሊያስከትል የሚችለውን ጠንቅ ፌደሬሽኑ ከመፍረሱ በፊት ሊረዱትና ሊያስቡበት የቻሉ አይመስልም።

ቢትወደድ አስፍሐ ወ/ሚካኤል ያለ አንዳች ስጋት ሳያመነቱ ፌደሬሽኑን ለማፍረስ ያስቻሏቸውን ሁኔታዎች አስመልክተው እንደገለፁልን፣ «በሁለተኛው ዙር የፓርላማ መማክርት ምርጫ በምክር ቤቱ ውስጥ የነበሩትን የአንደኛውን ዙር ተመራጭ የተቃዋሚዎች ቁጥር ክፉኛ አመነመነው።

በሦስተኛው ዙር የፓርላማ መማክርት ምርጫ ምክር ቤቱን ከተቃዋሚዎች አፅድተን በኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አባላትና በደጋፊዎቻችን ብቻ ሞላ ነው።

ምክር ቤቱን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር በመቻላችንና የምንፈልገውን ለመወሰንና ለማስወሰን በመብቃታችን የኤርትራ መንግሥት እየተባለ ይጠራ የነበረውን መስተዳድር «አስተዳደር» መርሐ መንግሥቲ ወይም የመንግሥት መሪ እየተባለ ይጠራ የነበረውን ግለሰብ «አስተዳዳሪ» በመባል እንዲጠሩ መደረጉ፣ የፌደሬሽኑ ወይንም የኤርትራ መንግሥት ህልውና ምልክት ነው የሚባለውን አርማ አውርደን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ብቻውን እንዲውለበለብ ማድረጋችን፣ በግንቦት ወር 1963 ዓ.ም ጃንሆይ ኤርትራን በጎበኙበት ጊዜ መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ በሦስተኛው ዙር በህዝቡ ለተመረጡ የፓርላማ መማክርት፣ የመስተዳድሩ ሹማምንት ከእነዚህ ተቋማት ውጭ ላሉ ህዝቡ ለሚያከብራቸውና ለሚወዳቸው አያሌ ታዋቂ ለአንድነት የታገሉ ሰዎች ከባላምባራስነት እስከ ደጃዝማችነት በብዛት የሰጡት ሹመት፣ ኒሻንና ልዩ ልዩ ሽልማቶች የህዝቡን መሪዎች ብቻ ሳይሆን ህዝቡን በጣም ስለአስደሰተው ወትሮም የነበረውን የህዝቡን የአገር ፍቅር ስሜትና ኢትዮጵያዊነትን በከፍተኛ ደረጃ አጋለው» በማለት ነው።

ምዕራፍ ሃያ አንድ

ከፌደሬሽኑ መፍረስ በኋላ

ባላቋረጠ ትግልና በሚያስደንቅ ስልት ፌደሬሽኑን በመገዘገዝና ብሎም በማፍረስ የተገኘውን ውጤት ያስገኙት የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አመራር አካላትና አባላት ውህደቱ ዘላቂና ፍፁም ሆኖ ኤርትራ የኢትዮጵያ አስራ አራተኛ ክፍለ ሃገር ሆና ከሌሎቹ ጋር የምትጣጣምበትን ሁኔታ ከዚህ እንደሚከተለው አዘጋጅተው ነበር።

ከፌደሬሽኑ መፍረስ በኋላ ጀነራል አቢይ አበበ ከአንድነቶች ጋር ላከናወኑት ታላቅ ተግባር በንጉሡ የላቀ ሹመት ተሰጥቷቸው አንድ ታላቅ የአመራር ስፍራ ይይዛሉ እንጂ ዳግም የኤርትራ ክፍለ ሃገር አስተዳደር እንደ ራሴ ይሆናሉ የሚል ግምት ስላልነበረ ቢትወደድ አስፍሐ ወ/ሚካኤል የአዲሱ የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ዋና አስተዳዳሪ ሆነው በእሳቸው ስር ክርስቲያኑን ህዝብ የሚወክሉት ንቡረዕድ መላከ ሠላም ዲሜጥሮስ ገ/ማርያምና የእስልምና እምነት ተከታዩን ህዝብ የሚወክሉት ደጃዝማች ሼክ አሊ ራዳይ ምክትል አስተዳዳሪዎች በመሆን ህዝቡን በሚገባ አስተባብረው እንዲመሩ፣ በክፍለ ሃገሩ ልዩ ልዩ የስራ ዘርፎች፣ የአውራጃዎችና የወረዳ አስተዳዳሪዎችም ለውህደቱ ስኬታማነት በፍፁም ኢትዮጵያዊነትና በጥንካሬ የሚሰሩ ሰዎችን በጥንቃቄ ከመረጡ በኋላ እንደራሴው ሌ/ጀነራል አቢይ አበበ ለንጉሡ አቅርበው ያስፈፅሙላቸው ዘንድ ሃሳባቸውን በዝርዝር አቅርበው ነበር።

ሌሎችም ማለትም፣ ውህደቱን ፍፁምና ዘላቂ የሚያደርጉ ዘዴዎችን በጥንቃቄ ካዘጋጁ በኋላ እንደራሴዉ ሌ/ጀነራል አቢይ አበበ ለንጉሡ አቅርበው ያስፀድቁላቸው ዘንድ አቅርበዉላቸው ነበር።

ከዚህም ሌላ በተለይ ቢትወደድ አስፍሐ ወ/ሚካኤል መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ አስደስቻለሁ፣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሰጡኝን ተልዕኮ በሚያጠግብ ሁኔታ ስለፈፀምኩ የአዲሱ የኤርትራ ክፍለ ሃገር አስተዳዳሪነት ብቻ ሳይሆን ራስ ቢትወደድ አድርገው ይሾሙኛል የሚል እምነትና ተስፋ ነበራቸው ነው የተባለው።

ፌደሬሽኑን የመገዝገዝና ብሎም የማፍረሱ ተግባራት የተከናወነው በኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር መሪነትና በአብዛኛው የኤርትራ ክልል ህዝብ ፍላጎትና የተግባርም ተሳትፎ ቢሆንም ከአመራር አካላቱ ቢትወደድ አስፍሐ ወ/ሚካኤልና ንቡረ ዕድ መላከሠላም ዲሜጥሮስ ገ/ማርያም የማፍረሱ ዋና መሀንዲሶች ናቸው ቢባሉም የንጉሰ ነገሥቱ እንደራሴ የሌ/ጀነራል አቢይ አበበ አስተዋፆ በተለይም በመጨረሻው ጊዜ የወሳኝነት ባህሪ ስለነበረው የኢትዮጵያ አንድነት የአገርፍቅር

ማህበር የአመራር አካላት ያቀረቡትን እቅድና አንድነቱን በዘላቂ መልክ የመገንባቱን ሃሳብ ለንጉሡ ነገሥቱ አቅርበው ለማስፈፀም ይተባበራሉ የሚል ሙሉ እምነት ነበረ።

ብዙ ኢትዮጵያዊያን ቢትወደድ አስፍሐ የራስ ቢትወደድነት ማዕረግ ቢሰጣቸው የሚበዛባቸው ካለመሆናቸው ሌላ አፍቃሪና ደጋፊያቸው የሆነውን የኤርትራን ክልል ህዝብ ባላቸው ችሎታና ዘዴ የማስተባበሩና የማስተዳደሩ እድል ተሰጥቷቸው ቢሆን ኖሮ ተቃዋሚዎችን ተቋቁመው ውህደቱን ዘላቂና ፍፁም ያደርጉት ነበር። በማለት የሚሰጡትን አስተያየት እኔም እጋራለሁ።

አኩራፊዎች ወይም ፌደሬሽን አፍቃሪዎች የሚፈጥሯቸውን ማናቸውንም ችግሮች ከህዝቡ ጋር ሆነው መቋቋም ይችሉ ዘንድ እንደተለመደውና እንደውም በተሻለ ሁኔታ ለአመራራቸው ስኬታማነት የማዕከላዊ መንግሥትን ድጋፍ መስጠት ሲገባ ከፌደሬሽኑ መፍረስ በኋላ ጀነራል አቢይ አበበ የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር ተባባሪ ሆነው አልተገኙም።

አፄ ኃይለሥላሴና እንደራሴያቸው ጀነራል አቢይ እነቢትወደድ አስፋሐና በጠቅላላውም አንድነቶች ፌደሬሽኑን የማፍረስ ተልዕኮዋቸውን ፈፅመዋልና ከእንግዲህ ወዲያ የኛ ተግባር መሆን ያለበት ያኮረፉትን ተቃዋሚዎች (ራቢጣዎች) ለማስደሰት በአዲሱ የኤርትራ ክፍለ ሃገር አስተዳደር የበላይ ባለሥልጣንነትን ማቀዳጀት ወይም የአንድነቶች የበላይ ማድረግ ነው ከማለት ባሻገር እነቢትወደድ አስፍሐ፣ እነንቡረዕድ መላከ ሠላም ዲሜጥሮስና መሰሎቻቸው የአገር ፍቅር ማህበር መሪዎች ኤርትራን ከሚመለከቱ ጉዳዮች ብቻ ሳይሆን ከኤርትራም ክልል መራቅ አለባቸው ብለው የወሰኑ ይመስላል።

የኤርትራ ራስ ገዝ አስተዳዳር (ፌደሬሽን) ከፈረሰ ከአንድ ወር በኋላ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ 14ኛ ክፍለ ሃገራቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ ለመጎብኘት በኤርትራ ክፍለ ሃገር ርዕሰ ከተማ በአስመራ ተገኝተው ከማዕከላዊ መንግሥት ባለሥልጣኖቻቸውና ከኤርትራ የአገር ፍቅር ማህበር የአመራር አካላት ከአንዳቸውም ጋር ሳይመክሩ ከኤርትራ ክፍለ ሃገር እንደራሴያቸው ከሌ/ጀነራል አቢይ አበበ ጋር ከዚህ የሚከተሉትን ታላቅ ስህተቶች ሰሩ።

1ኛ. ፌደሬሽኑ ከፈረሰ ከአንድ ወር በኋላ ቢትወደድ አስፋሐ ወ/ሚካኤል፣ ንቡረዕድ መላከ ሠላም ዲሜጥሮስ ገ/ማርያምንና ሌሎችንም በፌደሬሽኑ አስተዳደር ቁልፍ ቦታ የነበራቸውን የአገር ፍቅር ማህበር አመራር አካላት የሆኑ ግለሰቦች በኤርትራ ክልል መቆየት የለባቸውም ተብሎ ወደ አዲስ አበባ እንዲዛወሩ ተደረገ።

2ኛ. ወደ አዲስ አበባ እንዲዛወሩ ከተደረጉትም ውስጥ ቢትወደድ አስፍሐ ወ/ሚካኤል ብቻ በማዕከላዊ መንግሥቱ ውስጥ የፍርድ ሚኒስተር ሆነው ሲሾሙ ዋናው የኤርትራ አርበኞች ቁንጮና መሪ ንቡረዕድ መላከ ሠላም ዲሜጥሮስ ያለ

አንዳች ማዕረግ የማዕከላዊ መንግሥት የህግ መወሰኛ ምክርቤት ተራ አባል ሆነው እንዲቀመጡ ተደረገ።

እንዲህ መደረጉ በኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር መላ አባላት ላይ ታላቅ ድንጋጤና ሀዘን ፈጥሮ ሳለ በኤርትራ ለረጂም ጊዜ በፀረ-አንድነትና በፀረ-ኢትዮጵያነት ከታወቁና ቀደም ባለው ረጂም የቅኝ ተገዥነት ዘመናት የፋሽስት ኢጣሊያኖች፣ ቀጥሎም በመጨረሻው ዘመን የእንግሊዝ መንግሥት ወታደራዊ ገዥዎች መሳሪያ በመሆን የአንድነት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ዐር በመሆን የኢትዮጵያን አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር በፅኑ ሲታገሉ የኖሩት የዋናው ተቃዋሚ የራስ ተሰማ አስመሮም ቤተሰብ የሆኑትን ፊታውራሪ ተስፋ ዮሐንስ በርሄን በሚኒስትር ደኤታ ማዕረግ ከንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ ከሌ/ጀነራል አቢይ አበበ ቀጥሎ የክፍለ ሃገሩ ምክትል አስተዳዳሪ መደረጋቸው ምንም እንኳን ከፌደሬሽኑ መመስረት በኋላ አንድነቶች ባደረጉት የማግባባት ጥረት ቀደም ብለው የደጃዝማች ተድላ ባይሩና በኋላም የቢትወደድ አስፍሐን አስተዳደር የደገፉ ቢሆንም በዋናው የነፃነትና የአንድነት ትግል ጊዜ ቀንደኛ ብቻ ሳይሆኑ እጅግ አደገኛ ፀረ-አንድነትና ፀረ-ኢትዮጵያ የነበሩትን ደጃዝማች ሼክ አሊ ሙሳ ራዳይን እንዲሁ በሚኒስትር ደኤታ ማዕረግ በድጋሚ የጠቅላይ ግዛቱ እንደራሴ አማካሪ አድርጎ በመሾም ክፍለ ሃገሩን ለራቢጣዎች መስጠቱ መላውን የኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አባላት በእጅጉ አሳዘነ።

3ኛ. ለነፃነትና ብሎም ለኢትዮጵያ አንድነት የተደረገውን ትግል በቆራጥነት ከመሩት ግንባር ቀደም የኤርትራ አርበኞች አንዱ ከመሆን ባሻገር አክራሪ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኛ የነበረውና ከፌደሬሽኑ መመስረት በኋላ ከሻለቅነት እጅግ በተፋጠነ እድገት በሦስት ዓመታት ውስጥ ብ/ጀነራል ለመሆን የበቃው የክፍለ ሃገሩ ፖሊስ አዛዥ ተድላ እቁቢት፣ ሲታገላቸው ለነበሩት ራቢጣዎች ጠላቶች መታዘዝን አልፈቅድም በማለት በአስመራ ከተማ ጽህፈት ቤቱ ውስጥ ራሱን በመግደሉ እጅግ ያዘኑት የአገር ፍቅር ማህበር አባላት «ኢትዮጵያ ወይም ሞት ብለን በመታገል ኤርትራን ከእናታችን ከኢትዮጵያ ጋር መልሰን ባዋህድን ማግሥት ለውለታችን ወሮታ መክፈል ያሉት ይመስላል በሰራው ስራ እንድናፍር፣ እንድናዝንና እንድናለቅስ ንጉሠ ነገሥታችን አዘውናል» በማለት ብሶታቸውን እየገለፁ ብዙዎች ከተቃዋሚዎች ጎራ ተቀላቀሉ፣

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና እንደራሴያቸው ሌ/ጀነራል አቢይ አበበ ምናልባት በኢትዮጵያ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አባላትና በፌደሬሽን አፍቃሪዎች መካከል የተፈጠረውን ቅራኔ ለማለዘብ ወይም ፌደሬሽኑን ለማፍረስ ሲባል የተሰራውን ስህተት ለማረም ብለው ይሆናል የአንድነት ተቃዋሚዎች በአንድነቶች ላይ የሥልጣን የበላይነትን እንዲቀዳጁ ማድረጋቸው አንድነቶችን ከማሳዘንና ከማስለቀስ፣ የኤርትራ ክልል ተቆርቋሪና ባለቤት አልባ፣ ወደፊት እንደምንመለከተው የገንጣዮች መፈንጫ ከማድረግ ሌላ ያስገኘው ፋይዳ የለም። የኤርትራ ክልል ህዝብ በዚህ አሳዛኝ ሁኔታ

ላይ በወደቀበት በ1959 ዓ.ም አኩራፊና ፌደሬሽን አፍቃሪዎች ተሰባስበው «የኤርትራ ነፃነት ንቅናቄ» የተባለ ድርጅት አቋቁመው ለተወሰነ ጊዜ በህቡዕ የከተማ ትጥቅ ትግል ለማካሄድ ሞከሩ::

በጥቂት የኤርትራ ምሁራንና የሠራተኛው ማህበር አመራር አካላት ህብረት የተቋቋመው ንቅናቄ የአፄ ኃይለ ሥላሴን አገዛዝና የኢትዮጵያን አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር ከመቃወምና በተለይም የሠራተኛውን ማህበር ብሶት ከማስተጋባት ባሻገር የዓላማ ጥራትና ድርጅታዊ ጥንካሬ ስለአልነበረው በአጭር ጊዜ ውስጥ ሲፈርስ የቀድሞው ገንጣዮችና በኂላ ፌደሬሽን አፍቃሪ የሆኑት ራቢጣዎች ኢድሪስ አዋቴ በሚባል የቤንአምር ብሄረሰብ አባልና የእስልምና እምነት ተከታይ ሽፍታ ማዕከልነት በኂላ የኤርትራ ነፃ አውጭ (E.L.F) በአረብኛ ቋንቋ ጀብሐ በመባል ለታወቀው ገንጣይ የወንበዴ ሠራዊት እርሾ ወይንም መሰረት የሆኑትን ጥቂት የደፈጣ ተዋጊዎች በኤርትራ ምዕራባዊ ቆላ ውስጥ አቋቁመው መጠሪያ ስማቸውን የኤርትራ ነፃ አውጭ ቢሉም ከምንዝር ተዋጊው እስከ አመራሩ በሙሉ የቤንአምር ብሄረሰብ አባላትና የእስልምና እምነት ተከታዮች ብቻ ከመሆናቸው ሌላ ሠላማዊውን ክርስቲያን ህዝብ ከመግደልና ከመዝረፍ ያለፈ ነፃ አውጭ የሚያሰኛቸው የፖለቲካ ተግባር ሲያከናውኑ ያልታዩ በአብዛኛው ዘላን መሀይምና ገጠሬ ስለነበሩ በመንግሥት በኩል የተሰጣቸው ግምትና ትኩረት አልነበረም ለማለት ይቻላል::

የኢትዮጵያን ድክመትና ብሎም ውድቀት የሚመኙት አረቦች በአጠቃላይና ግብፆች በተለይ በኤርትራ ምዕራባዊ ቆላ የበቀሉትን የጥቂት ሽፍቶች ዝና ሲሰሙ አበባ እንደሚቀስሙ ንቦች ተሯሩጠው ወደ ግብፅ በመውሰድ አደራጅተው፣ መሳሪያና ርዕዮተ ዓለም አስታጥቀው በ1960 ዓ.ም ካይሮ ላይ የኤርትራ ነፃ አውጭ ግንባር (E.L.F) መቋቋሙን ለዓለም አሳወቁ::

የጀብሐ መመስረት በኢትዮጵያ በውል የታወቀውና የኢትዮጵያ መንግሥትም ለዚህ ገንጣይ ድርጅት ትኩረት መስጠት የጀመረው ከካይሮ መግለጫ በኂላ ነው::

በባዕዳንም በወገንም በብዙ ሰዎች ዘንድ በኤርትራ ገንጣዮችና በኢትዮጵያ የአንድነት ኃይሎች መካከል ከሰላሣ ዓመታት በላይ በተካሄደው የትጥቅ ትግል ወይም የእርስ እርስ ጦርነት መንስኤው የፌደሬሽኑ መፍረስ ነው ተብሎ የሚታመን ቢሆንም በኔ ጥናትና ግንዛቤ ተጨማሪ ምክንያቶች በመሆን ከፌደሬሽኑ መፍረስ የላቀ አስተዋፆ ያደረጉና የተለያዩ ኃይሎችንና የህብረተሰብ ክፍሎችን ያካተተ በርካታና ውስብስብ ጉዳዩች ያሉበት ስለሆነ እነኝህን በትግላችን ታሪክ መደምደሚያ ቅፅ ሦስት የጦርነቱ ዋና ሰለባ ከሆኑት የጦር ኃይሎቻችንና ከኤርትራ ህዝብ ሌላ በጠቅላላው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በህይወት፣ በአካል፣ በመንፈስና በሀብት ወዘተ ካደረሰው ጉዳት ጋር ለማቅረብ ለአንባቢ ቃል በመግባት ወደ ትጥቅ ትግሉ ታሪክ አመራለሁ::

ምዕራፍ ሃያ ሁለት

ራሱን የኤርትራ ነፃ አውጭ በአረበኛ «ጀብሐ» ብሎ የሚጠራው ገንጣይ ድርጅት መመስረት

ንቡረዕድ መላከ ሠላም ዲሜጥሮስ እንደነገሩን ፌደሬሽኑ ከመፍረሱ ጥቂት ወራት በፊት ጀነራል አቢይና ተከታዮቻቸው የፌደሬሽኑ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች የከረንን ከተማ በጎበኙበት ጊዜ የእጅ ቦምብ በመወርወር የግድያ ሙከራ ያደረጉት ሰዎች ማንነት ባይታወቅም ያኮረፉ የቀድሞው የእስላም ሊግ አመራር አካላት ለብቀላ ብለው የወሰዱት እርምጃ መሆኑን መገንዘብ አልተሳነንም ነው ያሉት።

ግድያውን የሞከረው የሽፍታ ቡድን መሪና ተከታዮቹን ተከታትሎ ለማወቅ በመንግሥት በኩል የተደረገው ጥረት ረዘም ያለ ጊዜ ስለጠየቀና ፈጣን እርምጃ ለመውሰድ ባለመቻሉ ምክንያት ሽፍቶቹ የወንጀል ተግባራቸውን ያለማቋረጥ ቀጠሉ።

ፌደሬሽኑ ከፈረሰ በኋላ አዘውትረው ከሚፈፅሙት የቅሚያ፣ የዘረፋና የግድያ ተግባር መረዳት እንደተቻለው የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር የአመራር አካላትንና አባላትን ብቻ ሳይሆን ጠቅላላውን ህዝበ ክርስቲያን ጠላታቸው በማድረግ የበቀል ዒላማቸው ሊያደርጉት ነው የሞከሩት።

ብዙ ጉዳት ካደረሱ በኋላነው የቆላው ክልል ነዋሪ በሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አባላት በአንድነት ደጋፊዎችና በክልሉ የደህንነት ሠራተኞች ከፍ ያለ የጋራ ጥረትነው የሽፍቶቹን ማንነት ማወቅ የተቻለው።

የሽፍቶቹ ማንነት በመንግሥት ዘንድ ከታወቀ በኋላ በክልሉ ፀጥታ አስከባሪ ኃይሎች ታድነው እንዲያዙ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ፀጥታ አስከባሪዎች መንቀሳቀስ ሲጀምሩ ነው ይጠረጠሩ የነበሩትን የሽፍቶቹን አደራጂዎችም በእርግጠኝነት ለማወቅ የተቻለው።

የቀድሞው ፀረ-አንድነትና ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነው የእስላም ሊግ ቀንደኛ የአመራር አካል አባላት የነበሩና የፌደሬሽኑ መስራች የሆነው ምክር ቤት አባል ሆነው ለሦስት ዓመታት ከሰሩ በኋላ ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት የምክር ቤቱ ፕሬዝዳንትና የመስተዳድሩ መሪ በፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን ለቀው እነፊታውራሪ አስፍሐ ወ/ሚካኤል ሲተኩ በተደረገው ሁለተኛና ሦስተኛ የምክር ቤት መማክርት ምርጫ ውድድር በመውደቃቸው ያኮረፉ ፌደሬሽን አፍቃሪዎች፣ ኢድሪስ አዋቴ የሚባለውን የቤንአምር ብሄረሰብ አባል፣ የእስልምና እምነት ተከታይና የታወቀ ሽፍታ በገንዘብ ደልለው በእሱ አሰባሳቢነትና ብሎም መሪነት ያቋቋሙት ጀብሐ የተባለው ገንጣይ ድርጅት ሠራዊት ጥንስስ የሆነውን የሽፍታ ቡድን ዝርዝር በሚያስተማምን ሁኔታ ማወቅ የተቻለው።

በዚህ ጊዜ ነበር ከሸፍቶቹ መሀከል አንዳቸው ቢያዙ ያጋልጡናል በሚል ፍራቻ በእንግሊዞች ቅስቀሳና ድጋፍ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አንጻ የሆነ የእስላም ሊግ የተባለ የፖለቲካ ድርጅት አደራጅና ከፍተኛ የአመራር አካላት በሙሉ ማለት ይቻላል አገራቸውን ለቀው ወደ ባዕድ አገር የኰበለሉት።

በቡድንና በግለሰብ ተነጣጥለው ቀደም ባለው ረጂም የትግል ዘመን ሁለገብ ፀረ-ኢትዮጵያ ድጋፍ ሲሰጧቸው ወደ ነበሩት አገሮች ወደ ኢጣሊያና ወደ ተለያዩ አረብ አገሮች ሲሄዱ ዋናው የአመራር አካል ማለትም እነኢብራሂም ሁልጣን፣ ኡመር ቃዲ፣ ኢድሪስ መሐመድ ወዘተ ያሉበት ቡድን የሄደው ወደ ዋናዋ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላት ወደ ግብፅ ነበር።

ከዚህ ቀጥሎ ስለ ጀብሐ አመሰራረት ታሪክ የምተርከው በግብፅ ርዕስ ከተማ በካይሮ የኤርትራን ክልል ህዝብ ከወገኑ ከኢትዮጵያ ህዝብ ለመገንጠል የተደገሰልንን ከሰላሣ ዓመታት በላይ የወሰደ የእርስ በርስ ጦርነት እቅድ ወደ ግብፅ ከሄደው ቡድን የጀብሃ አባላት ከድተው ወደኛ በገቡ ጊዜ የነገሩንን መሰረት በማድረግ ነው። ከዚህ ቡድን አባላት ከፊሉ ከሃያ አምስት ዓመት በኋላ በእርቅ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በኢትዮጵያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ ሕ.ድ.ሪ) መንግሥት ውስጥ የኤርትራ ቀላማው ክልልና የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ የተለያዩ ማህበረሰብና ብሄረሰብ አባላት ህብረተሰቦች የራስ ገዝ ክልል ባለቤት በመሆን ለኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮት ደህንነትና ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት እንታገላለን ብለው ቃል የገቡልን ሰዎች ነበሩ። እነሱም የፈረሰውና ራሱን ጀብሐ ብሎ ይጠራ የነበረው ገንጣይ የፖለቲካ ድርጅት አመራር አባላት ነበሩ። የተረኩልንን ታሪክ የሚከተለው ነው።

ወደ ግብፅ የሄደው ዋናው የእስላም ሊግ በመባል ይጠራ የነበረው የፖለቲካ ድርጅት አመራር አካል አባላት ከፌደ ሬሽኑ መመስረት በፊት ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ያደርጉት በነበረው ትግል ለረጅም ጊዜ ከግብፅ መንግሥት ጋር ድርጅቱን አገናኝ በመሆን ሲረዳቸው የነበረውን ከግብፅ መንግሥት የውጭ ጉዳይና ከብሄራዊ ደሕንነት ሚኒስቴሮች ተወጣጥቶ በጋራ ይሰራ የነበረ ቡድን አባላትን ተገናኝተው ከኤርትራ እስላማዊና አረባዊ ህዝብ ከፍ ያለ ምስጢራዊ መልዕክት ይዘን የመጣን ልዑካን ስለሆንን ከከፍተኛ የግብፅ ባለሥልጣናት ጋር አገናኙን ብለው ይጠይቃሉ።

በርከት ያሉ ቀናቶች ከተቆጠሩ በኋላ የግብፅ መንግሥት የውጭ ጉዳይና የብሄራዊ ደህንነት ሚኒስትሮች በጋራ ተቀብለው ያነጋግሯቸውና ኢትዮጵያዊያኑ ያቀረቡት ጥያቄ ከእነሱ አቅም በላይ መሆኑን በመግለፅ ከእነሱ ለላቀ ከፍተኛ አካል ዘንድ ሊያቀርቡላቸው እንደሚሞክሩ ተስፋ በመስጠት ያሰናብቷቸዋል።

አሁንም ሳምንታቶችን ካስቆጠረ ደጅ ጥናት በኋላ ሚኒስትሮቹ ለግብፅ ምክትል ፕሬዝዳንትና ለዓለም እስላሞች ኮንፍረንስ ሰብሳቢ ፕሬዝዳንት ለአንዋር ሳዳት ያቀርቧቸዋል።

ኢትዮጵያዊያኑ የኤርትራ የእስላም ሊግ ድርጅት መሪዎች ወደ ግብፅ የመጡበትን ምክንያት ከዚህ እንደሚከተለው ለግብፁ ምክትል ፕሬዝዳንትና የዓለም እስላሞች ኮንፍራንስ ሰብሳቢ ፕሬዝዳንት ተልዕኮአቸውን ይገልፃሉ።

«የኤርትራ ህዝብ ከቅኝ ገዥዋ ከፋሽስት ኢጣሊያ ገዥ መደብና ከወራሪው ሠራዊት ጋር ለሃምሳ ዓመታት ሲታገል ኖሮ ድልን በተቀዳጀበት ጊዜ ነፃነቱን ከማግኘት ፋንታ በተባበሩት መንግሥታት ማህበር ውሳኔ አረባዊና እስላማዊ የሆነው የኤርትራ ህዝብ በሐበሻ ክርስቲያናዊ መንግሥት የዘውድ አገዛዝ ስር በፌደሬሽን ትስስር እንዲስተዳደር ተወሰነ።

የተባበሩት መንግሥታትን ውሳኔ በፅኑ ተቃውመን ፍትሃዊ ፍርድ በማጣታችን የፌደሬሽኑ አስተዳደር ከክርስቲያኑ ዘውዳዊ መንግሥት መድሎና ቀጥተኛ ጭቆና በመከላከል አንፃራዊ ነፃነት ሊሰጠን ይችል ይሆናል በሚል እምነት ተቀበልን።

የአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘውዳዊ መንግሥት ፌዴሬሽኑን አፍርሶ ኤርትራን የኢትዮጵያ መንግሥት አስራ አራተኛ ክፍለ ሃገራዊ አስተዳደር ለማድረግ ያቀደውን እቅድ በመቃወም ስለታገልነው ህዝቡን በገንዘብ በመደለልና በኃይልም በማስፈራራት ባለፉት ሁለት የፌደሬሽኑ ምክር ቤት መማክርት ምርጫ ደጋፊዎቹን ብቻ አስመርጦ እኛን ተቃዋሚዎቹን በሙሉ ከኤርትራ ፖለቲካ ተሳትፎ ፍፁም ስለአገለለንና ህዝቡንም እንዳሻው መርገጥ ስለጀመረ ጠቅላላውን ሁኔታ በዘለቄታ መልኩ ስንመለከተው ከክርስቲያኑ የአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘውዳዊ መንግሥት ጋር ሠላማዊ የፖለቲካ ትግሉ የትም እንደማያደርሰን በመገንዘባችን ህዝቡን ከዚህ ጨቋኝ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት ወስነን የትጥቅ ትግል ስለጀመርን ታላቋን የግብፅ መንግሥትና በግብፅ አማካኝነትም ከዚህ በፊት እንደተደረገው የመላውን አረብና እስላማዊ መንግሥታት የማያቋርጥ ሁለገብ እርዳታ እንለምናለን » የሚል ነበር።

የግብፅ ምክትል ፕሬዝዳንት ለኢትዮጵያዊያኑ በርካታና የተለያዩ ጥያቄዎችን አቅርቦላቸው የቡድኑ አባላትም ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች በፈረቃ መልስ ከሰጡት በኂላ እሱም በበኩሉ ለኢትዮጵያዊያኑ የሰጣቸው መልስ ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

«የኤርትራ ህዝብ ከኢጣሊያ ቅኝ ተገዥነት ከተላቀቀ በኂላ የራሱ የሆነ ነፃ መንግሥት አቋቁሞ በነፃነት እንዲኖር ላቀረበው ጥያቄ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ፍፁም ፍትህ አልባ የሆነ ውሳኔ በመስጠቱ ግብፅን ጨምሮ መላው የአረብና የእስልምና እምነት ተከታይ መንግሥታት በጊዜው ከኤርትራ ህዝብ ጎን ቆመን መታገላችንን ታውቃላችሁ።

በፌደሬሽን አስተዳደር እንድትተዳደሩ የመንግሥታቱ ማህበር ጠቅላላ ስብሰባ ውሳኔ ከሰጠም በኂላ የአፄኃይለሥላሴ መንግሥት የፌደሬሽኑን አስተዳደር በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚያፈርሰው ፀወቅቱ የተነበይነው አገሮች ጥቂት አልነበርንም ትንቢታችን ትክክል ነበር። ምክንያቱም ይሄው የምትነግሩኝ ኃይለ ሥላሴ ፌደሬሽኑን ሊያፈርስ እየተዘጋጀ ነውና።

በበኩሌ እናንተ የያዛችሁትን አቋም በጠቅላላ የጀመራችሁትን የትጥቅ ትግልና ለትግሉም ስኬታማነት ከአረቡ ዓለም የምትጠይቁትን እርዳታ ሙሉ በሙሉ ደጋፊ ነኝ።

ሆኖም ያቀረባችሁት ጥያቄ በኔ የሚወሰን ስላልሆነ ለሪፓብሊኩ መሪ ለፕሬዝዳንት ጋማል አብደል ናስር አቀርብላችኋለሁ» የሚል አስደሳች ተስፋ ሰጠን።

አንዋር ሳዳት በእጅጉ የተባበረን ብቻ ሳይሆን ምናልባት እዚያው ካይሮ ከተማ በፖለቲካ ጥገኝነት የሚኖረው የቀድሞው ተቃዋሚ የፕሮግሬሲቭ ፓርቲ መሪ የነበረው ወልደአብ ወልደማሪያም ስለ ኢትዮጵያ ይነግራቸው ይሆናል ያለበለዚያም ግብፃዊያኑ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ ሁኔታ በታላቅ ትኩረት ይከታተሉ ይሆናል ማለት ይቻላል የግብፁ ምክትል ፕሬዝዳንት ስለ አገራችን ብዙ የሚያውቅ ሰው ስለነበረ በእኛ በኩል የማስረዳት ችግር አልገጠመንም።

እንደተለመደው ለጥቂት ሳምንታቶች ደጅ ከጠናን በኋላ ዛሬ በማናስታውሰው ቀን በካይሮ ሰዓት አቆጣጠር ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ገደማ ፕሬዝዳንት ናስር አስጠርቶን ጽህፈት ቤቱ ተቀብሎ አነጋገረን።

የሚያስደስት ገፅታ ያለው ግዙፍ ሰው ነው። የለበሰው ወታደራዊ ልብስ ነበር። ፍልቅልቅ ባለ ፈገግታ ከወንበሩ ተነስቶ እያንዳንዳችንን በመጨበጥ ተቀብሎ መቀመጫ ጋበዘን።

ምክትል ፕሬዝዳንቱ ሳዳት ስለ እኛ ተልዕኮ በዝርዝር ያስረዳው ይመስለናል ናስር ብዙ ጥያቄ ሳያቀርብልን ከዚህ የሚከተለውን ንግግር አደረገልን።

«እናንተ አምርራችሁ ለመታገል ከተዘጋጃችሁና በምንሰጣችሁ እርዳታ በሚገባ ለመገልገል ከቻላችሁ ልንረዳችሁ ፈቃደኞች ነን ካለ በኋላ ንግግሩን በመቀጠል እናንተ ኤርትራን ነፃ ለማውጣት ከቻላችሁ ቀይ ባህርን የሚያዋስን ከኢትዮጵያ ሌላ ጣልቃ ገብ አገር ስለማይኖር ቀይ ባህርን የአረቦች ባህር ብለን ለመጥራት ይቻለናል።

ግብፅ ለነፃ አውጭው ሠራዊታችሁ ሥልጠናና የትጥቅ አቅርቦት፣ የገንዘብና የልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ወዘተ ድጋፍ በተቻላት መጠን ታቀርብላችኋለች።

የኔ ምክትል ፕሬዝዳንት ወንድም አንዋር ሳዳት የዓለም እስላም ህዝቦች ኮንፈረንስ ሰብሳቢ ፕሬዝዳንት ስለሆነ የአረብና የእስላም አገሮችን ለድጋፍ እናስተባብርላችኋለን። ወንድም አንዋር ግብፅንና እንዲሁም እኔን በመወከል ከእናንተ ጋር የሚደረገውን ዘላቂ የተራድኦ ውል ይዋዋላል።

በአረቡና በእስላሙ ዓለም ተቀባይነት ኖሮት አጥጋቢ ድጋፍ የሚያስገኝላችሁን ድርጅታዊ የፖለቲካ ፕሮግራም ከእናንተ ጋር ከማዘጋጀት ባሻገር የሚያስፈልጋችሁን ሁለገብ ድጋፍ እንዲያስተናግድና በሁሉም ረገድ እንዲረዳችሁ የእናንተ ባልደረባ አድርጌ ሰጥቻችኋለሁና ከእሱና ከእሱ ረዳቶች ጋር በትብብር ስራችሁን እንድትቀጥሉ ይሁን» በማለት በድጋሚ እያንዳንዳችንን በመጨበጥ ሲያሰናብተን የተሰማን ደስታ ወሰን አልነበረውም ከፍ ያለ ምስጋና አቅርበን ወጣን።

ምዕራፍ ሃያ ሦስት

ጀብሐን ለመመስረት በካይሮ የተቋቋመው ኰሚቴና በቅድም ተከተል ያከናወናቸው ተግባሮች

ፕሬዝዳንት ጋማል አብደል ናስር በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ምክትል ፕሬዝዳንቱ አንዋር ሳዳት የኤርትራ የነፃነት ትግል ጉዳይ ዋናና የበላይ ኃላፊ ሆኖ እሱን በሚወክለው የግብፅ መንግሥት ብሄራዊ ደሕንነት ሚኒስትር ሰብሳቢነት ከደሕንነት፣ ከመከላከያና ከውጭ ጉዳይ ሚንስቴሮች በተወጣጡ ባለሞያዎችና መለስተኛ ባለሥልጣኖች ጋር ኢትዮጵያዊያኑን ቡድን ያካተተ ኮሚቴ ተቋቁሞ ጀብሐን የማቋቋሙን ስራ ጀመረ።

በምክትል ፕሬዝዳንቱ በአንዋር ሳዳት መመሪያ መሰረት የጀብሐ አደራጅ ኮሚቴ በቅድሚያ ያተኮረባቸው ከዚህ የሚከተሉት ጉዳዮች በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቀቁ።

እነሱም፣ 1ኛ የጀብሐ የፖለቲካ ፕሮግራሞ፣ 2ኛ የጀብሐን ድርጅታዊ መዋቅር ማዘጋጀት ነበሩ። ዝግጅቱ ለፕሬዝዳንት ናስር ቀረቦ እንደተደሰተበትና በተግባር ላይ ይውል ዘንድ እንደ አፀደቀው በምክትል ፕሬዝዳንቱ በሳዳት አማካኝነት ለኮሚቴው ተገለፀልን።

ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያዊያኑ ቡድን በኩል የስራ ክፍፍል እንዲደረግ በግብፃዊያኑ ሀሳብ ቀርቦ መስማማት ስለተቻለ አምስት ሰዎች ያሉበት አነስተኛ ቡድን ላልተወሰነ ጊዜ በካይሮ ከተማ ተቀምጦ ከግብፃዊያኑ ጋር ለቀሪዎቹ ተከታታይ ስራዎች የአጭር፣ የመሀከለኛና የረዥም ጊዜ እቅድና ለእቅዱ ተግባራዊነትም የአፈፃፀም መርሀ ግብር አዘጋጅቶ በዚያ እየተመራ የወታደራዊውን፣ የፖለቲካውን፣ የፕሮፖጋንዳውንና ለድርጅቱ የሚያስፈልጉትን ሁለገብ እርዳታዎች የማሰባሰቡን ሥራ እንዲሠራ፣

በካይሮ ከተማ ከሚቀመጠው ከዋናው ቡድን የተቀነሱት ኢትዮጵያዊያን የእስልምና ሊግ አመራር አካላት ወደ ኢጣሊያና ወደ ተለያዩ የአረብ አገሮች የሄዱትን የአመራሩ አካላት አባላት ከያሉበት በመጥራት ራሳቸውን በሰው ኃይል አጠናክረውና የሥራ ክፍፍል አድርገው በሱዳንና በኢትዮጵያ ውስጥ የመስኩን ሥራ እንዲሰሩ ተወሰነ።

ኢትዮጵያዊው የመስክ ቡድን ወደ ሱዳን ከመመለሱ በፊት በምክትል ፕሬዝዳንቱ በአንዋር ሳዳት ለሁለተኛ ጊዜ የሁሉም ማለትም የግብፃዊያንና የኢትዮጵያዊያን የጋራ ስብሰባ ተደርጎ ወደ ሱዳን የሚመለሰው ቡድን ቅድሚያ ሰጥቶ በአስቸኳይ ያከናውናቸው ዘንድ የተሰጡት ሥራዎች፣

1ኛ. ነፃ አውጭውን የጀብሐ ሠራዊት የሚመሩ መኮንኖች በግብፅ፣ በሶሪያ፣ በኢራቅና በአልጀሪያ የጦር አካዳሚዎች ውስጥ ገብተው በአጭር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን የጦር አመራር ሞያ በአጠቃላይ የደፈጣ (የጎሪላ) ውጊያ አመራር በተለይ እንዲማሩ ሁለት መቶ ሰዎች በአስቸኳይ መልምሎ ወደ ግብፅ እንዲልክ፣

2ኛ. መኮንኖቹ ሠልጥነው ከተመረቁ በኋላ በአስቸኳይ ሰፊውን የጀብሐን ሠራዊት ማሰልጠን፣ ማስታጠቅ፣ ማደራጀትና ለውጊያ ማሰማራት በሚያስችል ሁኔታ ለኤርትራ የቀረበ ሥፍራ ከሱዳኖች ጋር በህብረት መርጦ በሱዳን ውስጥ ማዘጋጀት።

3ኛ. በኤርትራ ውስጥ በመዋጋት ላይ የሚገኘውና የጀብሐ ሠራዊት ጥንስስ ነው የሚባለው ጦር ከአጭር ጊዜ የደፈጣ ውጊያ ሥልጠና ተሐድሶ ልምምድ ጋር አዲስ የሚቀርብለትን የነፍስ ወከፍና የቡድን መሣሪያዎች የመጠቀም ትምህርት፣ የጀብሐን የፖለቲካ ፕሮግራም ከማስተዋወቅ ጋር የፖለቲካ ንቃት ትምህርቶችን መስጠት፣

4ኛ. ለጦሩ በጠቅላላ የሚያስፈልጉት ዘመናዊ የነፍስ ወከፍና የቡድን መሣሪያዎች፣ ትጥቆች፣ የአልባሳት፣ የመገናኛና የህክምና መሣሪያዎች ዓይነትና መጠን ከመድሃኒት መዘርዝር ጋር በአስቸኳይ በካይሮ ከተማ ለሚገኘው የጋራ ኮሚቴ ማቅረብ ነበሩ።

እነዚህ ጀብሐን ለመመስረት የታቀዱ እቅዶችና በእቅዱም መሰረት ለአፈፃፀሙ ሂደት የተነደፉ መርሀ ግብሮች ተግባር ላይ ውለው ፍሬ መስጠት በጀመሩበት እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1960 ዓ.ም መገባደጃ ላይ የጀብሐ መመስረት በካይሮ ከተማ በግብፅ መንግሥት ብሔራዊ የራዲዮ ጣቢያ አማካኝነት መላው የአረብኛ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝብ እንዲያውቀው ተደረገ።

ክፍል አስራ ስድስት

ምዕራፍ ሃያ አራት

በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ የተቋቋመውና በአገራችን ሰሜን ምሥራቅና ደቡብ አረቦች ያወጁብንን የእጅ አዙር ጦርነትና ግልፅ ወረራ መከላከል እጣው የሆነው የመከላከያ ሠራዊታችን አጭር ታሪክ።

የግብፅ መሪ ጋማል አብድል ናስር እንደተናገረው ቀይ ባህርን የአረቦች ባህር ለማድረግ በሰሜን ኢትዮጵያ የተደገሰልንን ጦርነት የመከላከል ግንባር ቀደምግዳጅ የነበረው ሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር ከገንጣዮች ጋር ያደረገውን የትጥቅ ትግል ወደ መተረኩ ከማምራቴ በፊት በምሥራቅና በደቡብ የአገራችን ክልሎች የታወጀብንን የውስጥ ቡርቦራና የውጭ ወረራ ለመከላከል በመጀመሪያው ረድፍ ተሰልፈው የተፋለሙትን የአገሪቷን የመከላከያ ሠራዊት አካል የጦር ክፍሎች በቅድሚያ ለአንባቢ ማስተዋወቅ ጠቃሚ ይመስለኛል።

ለኢትዮጵያ ህዝብ ክብር፣ ለዳር ድንበሩ መጠበቅና ለማህበራዊ ደህንነቱ የተሰለፉትን የአገሪቱን የመከላከያ ሠራዊት ለአንባቢ ማስተዋወቅ ያስፈለገበት ምክንያት የአብዮታዊ ትግላችንን ታሪክ ለማያነቡ ሁሉ በቅድሚያ ዘመናዊ የምንለውን የጦር ኃይላችንን አመሰራረት፣ አደረጃጀት፣ ስምሪትና የትግል ታሪክ የተሟላ ግንዛቤ ከማስጨበጥ ባሻገር በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ የተደራጀው ሠራዊት በድህረ አብዮት ዳግም በቅርፅም ሆነ በይዘት በዓይነትም ሆነ በመጠን የቱን ያህል እንደተሻሻለና እንዳደገ ለማስገንዘብ ጭምር ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ በጠቅላላው ማለት ይቻላል የትግል ታሪክ እንደመሆኑ መጠን የሃገር መከላከያ ሠራዊት ጉዳይ ለህዝቡና በአገሪቱ የፖለቲካ ሥልጣን ማማ ላይ ለተፈራረቁ መሪዎቻችን ሁሉ ከማንም በላይ የላቀ አንገብጋቢ ጉዳይ በመሆን እስከዛሬው እስከ እኛ ትውልድ ድረስ ቆይቷል።

ኢትዮጵያችን እንደ አንድ ሉዓላዊ አገር ከተመሰረተችበት ጊዜ ጀምሮ በአውሮፓ የኢንዱስትሪ አብዮት እስከፈነዳበት ጊዜ ድረስ ኃይል የተሰማቸውና እብሪት ወጥሮአቸው ሊወሩን የመጡ ባዕዳን ወራሪዎችን ለመመከትና አንዳንዴም አስፈላጊ ሆኖ እኛም ባህር ተሻግረንና የሰው ድንበር ጥሰን በተሰናዘርንበት ጊዜ ሁሉ የተፋለምነው እንደ ጠላቶቻችን ሁሉ ባመረትነው የራሳችን ጥንታዊ ወይም ባህላዊ የክንድ መሣሪያችን ስለነበር የጠየቀን መስዋዕትነት የከፋ እንደሆነ እንጂ በትግሉ ያፈርንበትና የተሸነፍንበት ጊዜ አልነበረም።

የአገራችንን ዙሪያ ድንበር፣ መግቢያና መውጫ የባህር በራችንን ጠላቶቻችን ተቆናጠው ሊከቡንና ሊያፍኑን የበቁት በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ በተገኘው የሳይንስና የቴክኖሎጂ ግኝት የትየለሌ ቀድመውንና ጥለውን ስለሄዱ ወይንም ስለአደጉ የሰለጠኑና የተደራጁ ዘመናዊ የጦር ኃይሎቻቸውን ዘመናዊ ትጥቅ ለማስታጠቅ በመቻላቸው ነው።

በዚህ ሁኔታ ዘመናዊ የጦር ኃይል አደራጅተው የአፍሪካንና የእስያን አህጉራት ለመቀራመት ከተነሱት ከአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች አንዱ ብቻ ሳይሆን ቀንደኛ ግንባር ቀደም የነበረው የቱርክ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት በ15ኛው ምዕተ ዓመት የባህር ድንበራችንን ጥሶ በመግባት ሊፈታተነን ችሏል።

ከቱርኮች ጋር ሲፋለሙ ከኖሩት ከእነአፄ ዘርያዕቆብ፣ አፄ ሚናስ፣ አፄ ሠርፀ ድንግል ወዘተ በኋላ ማለትም በመጨረሻ እንዲሁ ከቱርኮች ጋር የመፋጠጥና አልፎ አልፎም የመፋለም እጣ የገጠማቸው አፄ ቴዎድሮስ ቱርኮችን ካሉበት ወይንም ከተቆጣጠሯቸው የጠረፍ ክልሎችና የባህር በሮቻችን አልፈው እንዳይመጡ በንቃት እየተከላከሉ ከእሳቸው በፊት ሥርዓተ አልበኛ መሳፍንቶች ከመሩት የእርስ በርስ የሲቪል ጦርነትና መከፋፈል አገሪቱን በማውጣት፣ የየመሳፍንቱ ወታደሮች በገበሬው ላይ የሚፈፅሙትን ዘረፋና ቅሚያ በማቆም ብለውም ቱርኮችን ከኢትዮጵያ ምድር ረግጠው በማስወጣት የህዝቡን አንድነትና ነፃነት በፅኑ መሰረት ላይ ሊያቆም የሚችል ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት ያለ ጠንካራ ብሄራዊና መደበኛ የመከላከያ ሠራዊት ሊታሰብ እንደማይችል ከማንም በፊት ቀድመው የተገነዘቡ በመሆናቸው ለኢትዮጵያ አንድነትና ብሎም ግንባታ ከአቀዷቸው አብይና ቀዳሚ ተግባሮች ሁሉ ቀዳሚ ያደረጉት ዘመናዊ የአገር መከላከያ ሠራዊትን ግንባታ ነበር።

በጦር መሣሪያ ረገድም ከእሳቸው በፊት ከነበሩት የአመራር አባቶቻቸውና ከእሳቸው በኋላም ኢትዮጵያን ከመሩ ነገሥታቶች ሁሉ ልዩና ብቸኛ የሚያደርጋቸው የመከላከያ ሠራዊታቸውን ዘመናዊ መሣሪያ ለማስታጠቅ የነበራቸው እቅድ ከአውሮፓ መሣሪያ በመሸመት ሳይሆን በአገራቸው ውስጥ በማምረት ኢትዮጵያን የራሷ ወታደራዊ ቴክኖሎጂ ወይንም የመከላከያ ኢንዱስትሪ ባለቤት እንድትሆን ለማድረግ ነበር።

በሥርዓተ አልበኛ መሳፍንቶች የተመራው የእርስ በርስ የሲቪል ጦርነትና የአገሪቱ መከፋፈል በቴዎድሮስ አመራርና ክንድ በማክተሙና የአንድነት መሠረት ድንጋይ ተጥሎ የአንድነት ታሪክ እንደገና በመቀጠሉ ከቴዎድሮስ በኋላ ለመጡት ነገሥታት ዋናውንና እጅግ አደገኛውን የአገሪቱን ውስጣዊ ችግር በአብዛኛው ያቃለለ በመሆኑ በጣም የተሻለ ሁኔታ የፈጠረ ቢሆንም ከቴዎድሮስ በኋላ ያለው ጊዜ የኢምፔሪያሊዝም ጊዜ ወይንም ዘመነ ኢምፔሪያሊዝም በመሆኑ የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች በገሀድ በርሊን ከተማ ላይ ተሰብስበው ህብረት በመፍጠር የአፍሪካን አህጉር በሙሉ ሲቀራመቱ፣ ብሪታኒያ፣ ፈረንሳይና ኢጣሊያ ቱርኮችን ተክተው

ኢትዮጵያን ከበባ ቀለበታቸው ውስጥ በማስገባታቸው አንድነታችን ብቻ ሳይሆን ህልውናችንም እጅግ አሳሳቢ በሆነ አደጋ ላይ ወደቀ።

የብሪታኒያ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ኢትዮጵያን የሚያዋስኑትን ጎረቤት አገሮች ሱዳንን፣ ኬኒያንና ሰሜን ሱማሌን፣ ኢጣሊያ ኤርትራንና ደቡብ ሱማሌን ስትይዝ ፈረንሳይ ጅቡቲን ተቆጣጠረች።

ቴዎድሮስን የተኩት አፄ ዮሐንስ ከበባ ብቻ ሳይሆን የብዙ ሺህ ኢትዮጵያዊያንን ደምና ህይወት የጠየቀ ተደጋጋሚ ወረራ በኤርትራ ገጥሟቸው በመታገል ላይ እያሉ ነው በመተማ የጦር ሜዳ ሞት የቀደማቸው።

ምኒልክ ከዮሐንስ የተረከቧት ኢትዮጵያ ዙሪያዋን በሙሉ የተከበበች ብቻ ሳይሆን ከመረብ ወንዝ ወዲያ ያለው ወገናችን የኢትዮጵያ ህዝብ በፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት የቅኝ ግዛት መዳፍ ውስጥ ወድቋል።

እነዚህ በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ሥልጣን ላይ የወጡና የተከበቡ ነገሥታት የገጠማቸውን እጅግ አደገኛ ሁኔታ ተቋቁመው የኢትዮጵያን ነፃነት ለማቆየት ይቻላቸው ዘንድ የአቅምና የጊዜ እጥረት በመኖሩ እንጂ ከከበቧቸው የጠላት ሠራዊቶች ጋር የሚመጣጠን ጠንካራ ዘመናዊ የመከላከያ ሠራዊት ለማቋቋም መመኘታቸው የሚያጠያይቅ አይደለም።

ምኒልክ የፋሽስት ኢጣሊያን ወራሪ ሠራዊት አድዋ ላይ ሊገቱት የቻሉት ከፈረንሳይና ከሩሲያ የገዙት መሣሪያ በዓይነትም ሆነ በመጠን የኢጣሊያ ወራሪ ሠራዊት ከታጠቀው የተሻለ በመሆኑ ነው።

ከፈረንሳይ የተገዙት የተራራ መድፎች የተኩስ እርቀታቸውና የጥይቶቻቸው ምት ውጤት ከኢጣሊያ መድፎች የተሻሉ ከመሆናቸው በላይ ኢጣሊያኖች በአድዋ ውጊያ ታንክና የጦር አውሮፕላኖች ቀርቶ ሠራዊታቸውንና ሠራዊቱ የሚያስፈልገውን ስንቅና ቁሳቁስ የሚያጓጓዝ የየብስ ተሽከርካሪም ስለአልነበራቸው እንደ እኛው አጋሰስ ወይም የጋማ ከብት እየጎተቱ ነበር የመጡት። በሰው ኃይል አሰላለፍም አንድ ለሃያ ነበርን።

ለአንድ የኢጣሊያ ዘመናዊ ወይንም ሥልጡን ወታደር ሃያ የታጠቁ የኢትዮጵያ ገበሬዎች በማሰለፋችን ሲሆን የተከፈለውም መስዋዕትነት እንደ ሠራዊታችን ቁጥር እጅግ የበዛ ነበር።

በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በቋሚነት የንጉሠ ነገሥቱን ደህንነት ለመጠበቅና ቤተ መንግሥቱን የሚያስከብር የክብር ዘበኛ ጦር በራሳቸው ቀጥተኛ እዝና ቁጥጥር ለማደራጀትና ብሔራዊ መደበኛ የአገር መከላከያ ሠራዊት ለማቋቋም የታደሉ መሪ አፄ ኃይለሥላሴ ብቻ ናቸው። ራስ ተፈሪ ከነገሡ በኋላ ከቤልጅየም

መንግሥት ጋር በመዋዋል በጥቂት የቤልጅየም የጦር መኮንኖች እርዳታ የቤልጅየም ሥሪት በሆነ መሣሪያ የክብር ዘበኞቻቸውን አደራጁ።

የፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት በአድዋ የጦር ሜዳ የኢትዮጵያ ጀግኖች በተከላካይነት ያደረሱበትን ውድቀት ለመበቀል ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ቀንድን የሮማዊያን ቅኝ ግዛት ማድረግ አለብኝ በማለት ለረጅም ጊዜ ሲያልም በነበረው ዓላማው መሰረት ኢትዮጵያን ለመውረር በደቡብ ሱማሌና በኤርትራ ዘመናዊ ትጥቅ የታጠቀ የጦር ኃይል አካብቶ ለወረራ መሰናዳቱ ስለታወቀ የፋሽስቶችን ጥቃት የሚመክት ዘመናዊ የመከላከያ ሠራዊት ማደራጀት ወሳኝነት ነበረው።

የሚቋቋመውን መደበኛ የመከላከያ ሠራዊት የሚያሰለጥኑና የሚመሩ መሪዎችን ማለትም የጦር መኮንኖችን በቅድሚያ ማሰልጠን ደግሞ አማራጭ የሌለው ሌላው ወሳኝ እርምጃ መሆኑ ታውቆና ተመክሮበት ከተወሰነ በኋላ አከራካሪ የሆነው ነገር በማሰልጠንና በማደራጀት ረገድ የሚረዳን አገር ወይንም መንግሥት ማን ይሁን? የሚለው ጥያቄ ነበር።

ይህ ጉዳይ አከራካሪ የሆነበት ምክንያት በሠራዊት አሰለጣጠንና አደረጃጀት በበለፀገ ልምዳቸው የታወቁ አያሌ የአውሮፓ መንግሥታት መኖራቸው ቢታወቅም ከጠላታችን ከፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት ጋር የቀረበ ወይንም የጠበቀ ግንኙነት ሳይኖረውና በእኛ ላይ ሳይመሳጠር ለእኛ የሚወግን፣ ቅን አስተያየትና ልባዊ ወዳጅነት ያለው አገር ወይንም መንግሥት ማን ሊሆን እንደሚችል ማወቅና ማመኑ እጅግ አስቸጋሪ ነገር በመሆኑ ነበር።

በእድገት ብዙ የቀደሙና በጦር ኃይላቸው መጠንና ጥራት ገናና የሆኑት አብዛኛው የአውሮፓ ታላላቅ መንግሥታት አፍሪካን በቅኝ ግዛትነት የተቀራመቱና ለወደፊትም ቅኝ ግዛታቸውን ይበልጥ የማስፋፋት ምኞታቸውን የማይገቱ የቅኝ ግዛት ጥመኞችን ሠራዊት አደራጁልኝ ብሎ መጠየቅ ነብርን በጎቼን ጠብቅልኝ ብሎ እንደመጠየቅ ስለሆነ እንደነዚህ ያሉት መንግሥታት ከሚፈፅሙት እኩይ ተግባር የራቀ ወዳጅ አገር ለማግኘት ጉዳዩ በጥንቃቄ መጠናት ነበረበት።

በዚህ መሰረት በተደረገው ጥናት የኢትዮጵያን መስፈርት ያሟላ የስዊድን መንግሥት ከመሆኑ ባሻገር የተጠየቀውን ድጋፍ ለመስጠት ፈቃደኛና ተባባሪ ሆኖ በመገኘቱ በአገራችን ታሪክ የመጀመሪያውንና ታሪካዊውን የጦር መኰንኖች ማሠልጠኛ የጦር አካዳሚ የሚያቋቁሙና እጩ መኰንኖችን የሚያሠለጥኑ መኰንኖችን እንዲልክ ተጠየቀ።

የጦር መኰንኖቹ የሚሰለጥኑበት የጦር አካዳሚ የት ይቋቋም ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ እንዲሁ በተለያዩ አማራጭ ስፍራዎች ላይ ውይይት ከተደረገ በኋላ ከአዲስ አበባ ከተማ አርባ አራት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሸዋ ክፍለ ሃገር በመናገሻ አውራጃ

ውስጥ የምትገኝ ሆለታ በመባል የምትታወቅ ወረዳ በመልክአ ምድሯ አቀማመጥ፣ በአየር ንብረቷ ተስማሚነትና በአካባቢው የተፈጥሮ ውበት የተመሰጡት ዳግማዊ ምኒልክ አልፎ አልፎ ለመዝናናት የእረፍት ጊዜያቸውን በፀጥታ የሚያሳልፉበት አንድ እጅግ የተዋበ ቤተመንግሥት አሰርተው በቤተ መንግሥቱ አሰራር በመደሰታቸው ቤተመንግሥቱንና አካባቢውን «ገነት» የተሰኘ ስም ሰጡት፡፡

ምኒልክ ከአካባቢው ተፈጥሮ ባላነሰ ቤተመንግሥቱንም በመውደዳቸውና ለአጫጭር ቀናቶችም ቢሆን እዚያ ማረፉን በማዘውተራቸው ለቤተ መንግሥቱ ሠራተኞች፣ በማጀብ ለሚከተሏቸው መኳንንትና መሳፍንቶች ማረፊያ የሚሆኑ የተለያዩና የተዋቡ ቤቶች፣ ቤተ መጻሕፍትና ቤተክርስቲያን፣ የተለያዩ የመሥሪያና የጽሕፈት ቤቶች የስንቅ፣ የጦር መሣሪያና የተለያዩ ቁሳቁሶችን ማስቀመጫ ግምጃ ቤቶች፣ የጋማ ከብቶችና የእርድ ከብቶች ማደሪያና የገፈራቸውን ቤት፣ ከንጉሡ ጀምሮ ለመሳፍንቱ፣ ለመኳንንቱ እንዲሁም ለካህናቱና ለሠራዊቱ የምግብና የመጠጥ ማደራጃ የሚሆን ስሙን አስናቀ ብለው የሰየሙት አንድ ውብና ግዙፍ የግብር አዳራሽ አሰርተው ነበረ፡፡

ከአካባቢው የተፈጥሮ ውበት፣ ከመልክአ ምድሩ አቀማመጥ አመቺነት፣ ለርዕሰ ከተማው ለአዲስ አበባ ካለው ቅርበት ባሻገር ከቤተ መንግሥቱ ጋር ሌሎቹ ቤቶችና ድርጅቶች ለጦር አካዳሚው ግልጋሎት በጣም የተመቹ ሆነው በመገኘታቸው«ሆለታ ገነት» የተባለችው ወረዳ የአገሪቱ የጦር አካዳሚ እንዲቋቋምባት ተወሰነ፡፡

የስዊድን ወታደራዊ መምህራን የጦር መኰንኖች እስኪመጡ ድረስ በአካዳሚው ቅጥር ግቢ በተጨማሪ የሚያስፈልጉ የመኖሪያ፣ የመሥሪያና ለእጩ መኰንኖች ትምህርት መስጫ ቤቶች እንዲሰሩና አስፈላጊው የአገልግሎት መስጫ ተቋማት እንዲደራጁ ከተደረገ በኋላ ሕዳር 2 ቀን 1927 ዓ.ም የተለያዩ ወታደራዊ ሞያ ያላቸው አምስት መኰንኖች ከስዊድን አዲስ አበባ ገቡ፡፡

መምህራትና ለአካዳሚው ልዩ ልዩ ሥራዎች የሚያስፈልጉ ኢትዮጵያዊያን ተጠቃለው ወደ አካዳሚው ከገቡ በኋላ በአዲስ አበባ ከተማ ከነበሩ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተመለመሉ የ1ኛ ዓመት ተወዳዳሪ ወጣቶች ወደ አካዳሚ ው ከገቡ በኋላ በቅደም ተከተል የ2ኛና የ3ኛ ዓመት ተወዳዳሪዎችም ከተቱና የሥልጠናው ተግባር ተጀመረ፡፡

የመማሪያ ቋንቋ ፈረንሳይኛ ሲሆን እያንዳንዱ ውድድር ወይንም «ኮርስ» እንዲሸፍን የታቀደው የትምህርት ጊዜ ሦስት ዓመታት ነበር፡፡

የፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት በሰሜን፣ በምሥራቅና እንዲሁም በደቡብ የአገራችንን ድንበር እየጣሰ ወረራ በመጀመሩ ወጣቶች በአስቸኳይ ትምህርታቸውን እንዲያጠናቀቁ ግድ ሆነ፡፡ ወዲያውም ከገበሬው ሠራዊት የፋሽስቶችን ጥቃት ለመከላከል እንዲደራጅ የተፈለገውን መደበኛ ጦር በአጣዳፊ አሰልጥነውና አደራጅተው እንዲመሩ ሲባል የሦስት ዓመቱ የሥልጠና ጊዜ ታጥፎ

በአንድ ዓመት ሥልጠና ብቻ እንዲያበቃ በመወሰኑ ወጣቶቹ እንደ ኮርስ ቅደም ተከተላቸው የመጀመሪያዎቹ 1ኛ ዓመቶች በሙሉ የመቶ አልቅና፣ የ2ኛና የ3ኛ ዓመት ተመራቂዎች በምክትል የመቶ አልቅና ማዕረግ በመመረቃቸው በአንድ ጊዜ 148 ወጣት መኰንኖችን ማፍራት ተቻለ።

መኰንኖቹ ከተመረቁ በኋላ እንደየችሎታቸውና እንደየፈተና አወጣጣቸው እየተመዘኑ ለውጊያ በአስቸኳይ እንዲያሰለጥኑና እንዲያዘጋጁት በተመለመለው ሰፊ ጦር ውስጥ በተለያየ ደረጃ የአመራር ስፍራ ተደልድለው «ብርጌድ ኃይለሥላሴ» የተሰኘ ስም የተሰጠውን የመጀመሪያውን የኢትዮጵያ መደበኛ ጦር በመምራት ለውጊያ ተሰማሩ። የገነት የጦር አካዳሚም ለመጀመሪያዎቹ እጩ መኮንኖች የአንድ ዓመት ሥልጠና ከሰጠ በኋላ አገሪቱ በፋሽስቶች በመወረሯ ምክንያት በ1928 ዓ.ም ሥራውን ለማቆም በመገደዱ ስዊድናዊያኑ የአካዳሚው ወታደራዊ መምህራን ወደ አገራቸው ለመመለስ ተገደዱ።

የፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ለኢትዮጵያ ህዝብና ለተዋጊዎቹ ፍፁም ባዕድና እንግዳ የሆኑ ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችን ታጥቆ የመጣ ከመሆኑ በላይ በዓለም መንግሥታት ህግ በተከለከለ የጋዝ መርዝ በመጠቀሙ፣ የተለያዩ አርበኞች የነፍስ ወከፍ መሣሪያዎችን ታጥቆ የተሰለፈው የኢትዮጵያ ገበሬ ሠራዊት ለመከላከል ያደረገው ተጋድሎ ስኬታማ ባለመሆኑ አገራችን ተወረረች።

በብሪታኒያ መንግሥት እርዳታ በ1932 ዓ.ም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወራሪውን የፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት ሠራዊት መልሰው ለማጥቃት ከተሰደዱበት ከእንግሊዝ ወደ ሱዳን በመምጣት በስደት ላይ ከነበሩ ወጣት ኢትዮጵያዊያን መካከል የጦር መኰንን ለመሆን የሚያስችል የቀለም ትምህርት ያላቸውን ጥቂቱን ለእጩ መኰንንነት የተቀሩትን ብዙኃኑን በተራ ተዋጊ ወታደርነት የሚያሰለጥንና የሚያደራጅ የጦር ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት በሱዳን ርዕሰ ከተማ በካርቱም አቅራቢያ ሶባ በመባል በሚጠራ ስፍራ ተቋቁሞ በብሪታኒያ መንግሥት የጦር መኮንኖች የአጭር ጊዜ ሥልጠና ተሰጥቶት አፄ ኃይለ ሥላሴን ከሱዳን አጅቦ ወደ ኢትዮጵያ እንዲያመጣ የተደራጀና «የጌዲዮን ብርጌድ» በመባል የሚጠራ አንድ እግረኛ ብርጌድ በታሪክ ከጠላት ወረራ በፊት ተቋቁሞ ከነበረው «የብርጌድ ኃይለሥላሴ» ጦር የቀጠለ ሁለተኛ መደበኛ ጦር ነው።

የብሪታኒያ መንግሥት የመከላከያ ሠራዊት አካል የሆኑ ሁለት ግብረ ኃይሎች አንደኛው ከሱማሌ ምድር ተነስቶ በምሥራቅ ኢትዮጵያ የመሸገውን የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ሠራዊት እየደመሰሰ ወደ መሃል ኢትዮጵያ ሲመጣ ሁለተኛው ግብረ ኃይል ከሱዳን ምድር ተነስቶ በኤርትራ የመሸገውን የፋሽስት ኢጣሊያ ጦር እንዲሁ እየደመሰሰ ኤርትራን በተቆጣጠረበት ጊዜ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን በማጀብ ከሱዳን ተነስቶ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት በጐንደርና በጎጃም ክፍለ ሃገራት ሲታገሉ ከነበሩት የኢትዮጵያ ፀረ-ፋሽስት አርበኞችጋር በመቀላቀል ከአሜድላ ጀምሮ ፋሽስቶችን እየወጋ አዲስ አበባ የገባው ኢትዮጵያዊው የጌዲዮን ብርጌድ ነው።

ምዕራፍ ሃያ አምስት

በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ የተቋቋመው ዘመናዊ የምድር ጦር የአመሰራረት ሂደትና ለወታደራዊ ግዳጅ ስምሪት

የፋሽስት ኢጣሊያን መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ከኢትዮጵያ ምድር ወግቶ ለማስወጣት ይደረግ በነበረው ትግል የኢትየጵያ ፀረ-ፋሽስት አርበኞች ተባባሪ በመሆን በእርዳታ ወደ አገራችን የመጣው የብሪታኒያ መንግሥት ጦር የመጣበትን ተልዕኮ ፈፅሞ ከኢትዮጵያ ከመውጣቱ በፊት ማለትም የኢትዮጵያ ህዝብ በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ሠራዊት ላይ በጦር ሜዳ ድል በተቀዳጀበት ማግሥት ከብሪታኒያ መንግሥት በተላከ ወታደራዊ ልዑካን «British Military Misoion to Ethiopia » በመባል ሲጠራ በነበረው ወታደራዊ ቡድን አባላት የእንግሊዝ መኮንኖች በመሪነትና በመምህርነት በ1934 ዓ.ም መባቻ ጀምሮ የገነት የጦር አካዳሚ እንደገና ሥራውን በመቀጠል አዲሱን የምድር ጦር ሠራዊት የሚመሩ መኰንኖችን የማፍራት ተግባሩን ጀመረ::

በብሪታኒያ መንግሥት ወታደራዊ ልዑካን በ «B.M.M» የፋሽስት ወረራ ሰለባ ከመሆን በተረፉና በጤንነት በሚገኙ የገነት አካዳሚ ምሩቃንና በሰባ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ጊዜያዊ የጦር ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት በተመረቁ መኮንኖች የጋራ አመራር በአብዛኛው ከኢትዮጵያ ፀረ-ፋሽስት አርበኛ ሠራዊትና ፋሽስት ካሠለጠናቸው ምንደኛ ሠራዊት «ባንዶች» መካከል ልጅነት፣ ጤንነትና ወታደራዊ ተመክሮ ያላቸው ግለሰቦች እየተመለመሉ የተሐድሶ ሥልጠና እየተደረገላቸው በመደራጀት ላይ የነበረውን የኢትዮጵያ የጦር ኃይል በተሻለ መጠንና ይዘት፣ በተሻለ ትጥቅና ወታደራዊ ቁሳቁስ አቅርቦት መልሶ ለማደራጀት በአስራ ዘጠኝ መቶ አርባኛው ዓመተ ምህረት አጋማሽ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ከሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ጋር በአደረገው የመከላከያ ተራድኦ ውል መሠረት የአገሪቱ የምድር ጦር በአራት እግረኛ ክፍለ ጦሮችና ለክፍለ ጦሮቹ የውጊያና የቴክኒክ አገልግሎት ድጋፍ በሚሰጡ ልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍሎች በጠቅላላው በ40,000 በአርባ ሺህ የሰው ኃይል የተዋቀረ ነበር::

የምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያ በእዙ ሥር ያሉትን ሦስት እግረኛ ክፍለ ጦሮች ለአገሪቱ ደህንነት ጥበቃና ድንበር ማስከበር ከዚህ ግርጌ በተመለከተው ሁኔታ በአገሪቱ አራት ማዕዘናትና እንዲሁም በመሃል አሰማራቸው::

1ኛው እግረኛ ክፍለ ጦር ልዩ ልዩ የውጊያና የቴክኒክ አገልግሎት ሰጪዎቹን በአጠገቡ ያቀፈ፣ ጠቅላይ ሰፈሩንና የእዝ ማዕከሉን በአገሪቱ ርዕስ ከተማ በአዲስ አበባ አድርጎ በእዙ ሥር ካሉት አራት እግረኛ ብርጌዶች ውስጥ አንደኛውን ብርጌድ

በምዕራብ ኢትዮጵያ በከፋ ክፍለ ሃገር አስማርቶ የብርጌዱን መምሪያ በክፍለ ሃገሩ ርዕሰ ከተማ በጂማ አደረገ::

ሁለተኛውን ብርጌድ ለአዲስ አበባ ከተማና ለአካባቢው ጥበቃ አስማርቶ የብርጌዱንም መምሪያና ጠቅላይ ሰፈር በዚያው በአዲስ አበባ ከተማ መህል አደረገ::

ለሶስተኛውን ብርጌድ መመሪያና በእዙ ስር ካሉት እግረኛ ሻለቆች ጋር የሸዋ ክፍለ ሃገርንና የአገሪቱን ጠቅላላ ማዕከላዊ ክልል ለመጠበቅ በሚያስችል ሁኔታ በሸዋ ክፍለ ሃገር በደብረብርሐን ከተማ አሰፈራቸው::

አራተኛውን እግረኛ ብርጌድ ለደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጥበቃ ብቻ ሳይሆን ሱማሌን ተከፋፍለው ቅኝ ግዛታቸው በማድረግ ከተጎራበቱን ባዕዳን የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች የኢጣሊያንን መንግሥት ጭምር በንቃት ለመቆጣጠር በሚያስችል ሁኔታ የብርጌዱን መምሪያ፣ ጠቅላይ ሰፈሩንና በብርጌዱ እዝ ስር ካሉ እግረኛ ሻለቆች አንዱን በሲዳሞ ክፍለ ሃገር በቦረና አውራጃ ርዕሰ ከተማ ነጌሌ ላይ አድርጎ ከተቀሩት ሁለት እግረኛ ሻለቆች አንዱን ባሬ በሚባለው፣ ሌላውን ዶሎ በሚባለው ሁለት የጠረፍ አውራጃዎች ላይ አሰፈራቸው::

ለሶስተኛው እግረኛ ክፍለ ጦር ልዩ ልዩ የውጊያ ድጋፍ ሰጪዎችና የቴክኒክ አገልግሎት ሰጪ ክፍሎችን በአጠገቡ በማቀፉ ጠቅላይ ሰፈሩንና የእዝ ማዕከሉን ሐረር ከተማ ላይ አድርጎ በእዙ ሥር ካሉት እግረኛ ብርጌዶች ዘጠነኛውንና አስረኛውን፣ ሁለቱን የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች የብሪታኒያንና የኢጣሊያንን መንግሥታት በንቃት እየተቆጣጠሩ ጠቅላላውን የጠረፍ ጥበቃ ስራ እንዲያከናውኑ በኦጋዴን ክልል የተለያዩ አውራጃዎች ሲያስማራ የ11ኛውን ብርጌድ ጠቅላ ይሰፈሩን ሐረር ከተማ ላይ በማድረግ በክፍለ ሃገሩ ደጋማ አውራጃዎችና እንዲሁም ከጅቡቲ ጋር ለሚያዋስነን ቆላማ አውራጃ ጠረፍ ጥበቃ በሚያመች ሁኔታ በብርጌዱ እዝ ስር ከሚገኙት እግረኛ ሻለቆች፣ 31ኛውን በሐረር ከተማ፣ 12ኛውን በአዳልና ኢሳ አውራጃ ርዕሰ ከተማ ድሬዳዋ ላይ 7ኛውን በአሰበ ተፈሪ አውራጃ ከተማ ላይ አስፍሮ የተሰማራበትን ወታደራዊ ግዳጅ ይወጣ ነበር::

የሐረርጌ ክፍለ ሃገር የአየር ንብረት በነፋሻ ደጋማ አውራጃዎችና ሙቀታቸው ከበድ ባሉ ቆላማ አውራጃዎች የተከፈለ ከመሆኑ ሌላ ቆላማው የኦጋዴን ክልል በእድገት ኂላ ቀርነቱ ምክንያት ምንም ዓይነት የልማት ስራ የማይካሄድበት፣ የከተማ አገልግሎት ማለትም እንደ ሆስፒታልና ትምህርት ቤቶችን የመሳሰሉብቻ ሳይሆን ንፁህና ቀዝቃዛ ውሃም የሌለበት በመሆኑ ጦሩ ቤተሰቡን በደጋው ክልል ትቶ በመሄድ ቤተሰብ አልባ ኑሮ የሚኖር ደረቅ ጦር በመሆኑ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን በነፋሻዎቹ ደጋማ አውራጃዎች እየተናፈሰ ከቤተሰቡ ጋር የመኖር እድል እንዲኖረው ሲባል ከደጋማዎቹ ወደ ቆላማዎቹና እንዲሁም ከቆላማዎቹ አውራጃዎች ወደ ደጋማዎቹ አውራጃዎች በፈረቃ ይዘዋወር ስለነበርና በሌሎችም ምክንያቶች

የየብርጌዶቹ ጠቅላይ ሠፈሮች በመሆን በተለያዩ ጊዜያቶች የቀብሪ ደሃር፣ የዋርዴር፣ የደገሐቡር፣ የጂጂጋና የሐረር ከተሞች እንዲሁ በፈረቃ አገልግለዋል የየሻለቆቹ ጠቅላይ ሠፈሮችም እንደዚሁ።

አንባቢ ለማስተዋል እንደሚችለው አገሪቱ አራት እግረኛ ክፍለ ጦሮች ነበራት ካልኩ በኋላ በሦስት እግረኛ ክፍለ ጦሮች ላይ ብቻ ያተኮርኩበት ምክንያት በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ እንደ ሌሎቹ እግረኛ ክፍለ ጦሮች መለያ ቁጥር ያልተሰጠው የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ ክፍለ ጦር በንጉሡ እንጂ በምድር ጦር መምሪያ የሚታዘዝ ባለመሆኑና የግዳጅ ስምሪቱም ከሌሎቹ ሦስት እግረኛ ክፍለ ጦሮች የተለየ በመሆኑ ነው።

የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ ክፍለ ጦር መምሪያ፣ በእዙ ስር ያሉትን እግረኛ ብርጌዶች ከነሻለቆቻቸው፣ የውጊያና የቴክኒክ አገልግሎት ድጋፍ ሰጪ ልዩ ልዩ ክፍሎቹን አንድ ላይ አሰባስቦ በአገሪቱ ርዕሰ ከተማ በአዲስ አበባ በቤተመንግሥቱ አቅራቢያ ሰፍሮ የሚኖር ነው።

በ1953 ዓ.ም በወርሐ ታህሳስ በእነጀነራል መንግሥቱ ንዋይ የተደረገው የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ከከሸፈ በኋላ የመፈንቅለ መንግሥት አመፅ ተዋናይ የነበረው የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘብ ክፍለ ጦር ባልደረባ ከነበሩት መኮንኖች፣ ባለ ሌላ ማዕረግተኞችና ተርታ ወታደሮች መካከል ከፊሉ ወደ ተለያዩ ሌሎች በምድር ጦር መምሪያ እዝ ስር ባሉ እግረኛ ክፍለ ጦሮች ውስጥ በማዛወር እንዲበታተኑ በማድረግ ከሌሎች እግረኛ ክፍለ ጦሮች ተነጥለው በመጡ የጦር ክፍሎች እንዲበወዝ ከተደረገ በኋላ፣ አንደኛ እግረኛ ክፍለ ጦር የተባለ መጠሪያ ሲሰጠው ቀድሞ አንደኛ እግረኛ ክፍለ ጦር በመባል የሚታወቀው ክፍለ ጦር አራተኛ ተብሎ እንዲጠራ ተደረገ።

በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ ስለተቋቋመው የኢትዮጵያ ዘመናዊ የምድር ጦር በአጠቃላይና በእዙ ሥር ስለአቀፋቸው እግረኛ ክፍለ ጦሮች በተለይ አጠርና ጠቅለል ባለ ሁኔታ ይህንን ያህል ካልኩ በኋላ ወደተነሳሁበት ዋና ርዕሴ ወደ ኤርትራ ችግር በመመለስ ከኤርትራ ገንጣዮች ጋር ሲፋለም ወደኖረው ወደ ሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር አጭር ታሪክ አመራለሁ።

ምዕራፍ ሃያ ስድስት

በሰሜን ኢትዮጵያ ለአገሩ አንድነትና ለኢትዮጵያ ህዝብ ማህበራዊ ደህንነት ከገንጣዮች ጋር ሲፋለም ስለኖረው ሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር አጭር ታሪክ

በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ በምድር ጦር መምሪያ እዝ ሥር የተዋቀሩት እግረኛ ክፍለ ጦሮች ከ1953 ዓ.ም የመፈንቅ ለመንግሥት ሙከራ በኋላ የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ ክፍለ ጦርም ተካቶ አገሪቱ አራት እግረኛ ክፍለ ጦሮች ነበሯት በ.ባልም ክፍለ ጦሮቹ በተሰጣቸው ወታደራዊ ግዳጅ ለጥበቃ በተሰማሩበት ክልል ዓይነትና አቀማመጥ በአካባቢው የፖለቲካ ባህሪ ልዩነት ምክንያት ክፍለ ጦሮቹም ለአገራቸው ይሰጡ የነበረው ብሔራዊ አገልግሎት፣ አኗኗራ ቸው፣ ገጠመኞቻቸውና ይከፍሉ የነበረው መስዋዕት የአንዱ ከሌላው የተለየ ነበር።

የመከላከያ ሠራዊታችን አባላት ብቻ ሳይሆኑ ህዝባችንም ጭምር እንደሚያውቀው በምሥራቃዊው የአገራችን ክልል ለሚኖረው ህዝብ ደህንነትና ለአገሩ ዳር ድንበር ጥበቃ ከተሠማራበት ጊዜ ጀምሮ በተለይም ከሱማሌ ጋር የሚያዋስነንን ጠረፍ የኦጋዴን ክልል ከእንግሊዞች ከተረከበበት ከ1941 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ተስፋፊው የጀነራል ዚያድ ባሬ መንግሥት ወረራ ማለትም እስከ 1969 ዓ.ም መገባደጃ ድረስ የሱማሌ መንግሥት ወደ አገራችን እያሰረገ ከሚያስገባቸው ሽብርተኞችና በሂደት ከመደበኛው ወራሪ ሠራዊት ጋር በመፋለም በዘመናዊ የመከላከያ ሠራዊታችን ታሪክ ወደር የሌለው መስዋዕትነትን ሲከፍል ከኖረው ከ3ኛው አንበሳ ክፍለ ጦር ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ ሁለተኛው ዋሊያ ክፍለ ጦር ይጠቀሳል። ከኤርትራ ፌደሬሽን መፍረስ በኋላ በተፈጠረው የኤርትራን ክፍለ ሃገር ከኢትዮጵያ የመገንጠል የትጥቅ አመፅ ከገንጣዮች ጋር በማፋለም መሪር መስዋዕትን የከፈለው በሰሜን ኢትዮጵያ የአገሩን ዳር ድንበር፣ የክልሉን ህዝብ ሰላም፣ ማህበራዊ ደሕንነትና የኢትዮጵያን አንድነት ለማስከበር የተሰማራው ይህ ሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር ነው።

ሁለተኛው እግረኛ ክፍለ ጦር ዋሊያ የተባለ ቅፅል ስም የተሰጠው በአገራችን ሰሜናዊ ክልል በተለይም በትግራይ፣ በኤርትራና በጐንደር ክፍለ ሃገራት መካከል ራስ ዳሽን በመባል የሚታወቀውን ታላቁን ተራራ በሚያካብቡት የአካባቢው ተራሮች ላይ የሚኖረውንና በዓይነቱ ወይንም በዘሩ በዓለም ብቸኛ በመሆን በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኝ ትልልቅ ቀንዱ ወደ ኋላ የተቆለመመ የፍየል ዝርያ ሆኖ በሚኖርባቸው ተራሮች ከፍተኛነትና ቀዝቃዛነት እንደ በግ ፀጉር በመልበሱ ለተመለከተው ሁሉ በጣም የሚያስደስት ውብ እንስሳ የሚኖርበትን የአገራችንን ሰሜናዊ ክልል የመጠበቅና የማስከበር ኃላፊነት የተሰጠው ክፍለ ጦር በመሆኑ ነው።

በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ ከ1945 ዓ.ም ማለትም የኤርትራ ክልል ህዝብ ከወገኑ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር እንደገና ከተቀላቀለበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ የአመራር አካሉን ወይንም የማዘዣ ቦታውን ኤርትራ ክፍለ ሃገር ርዕሰ ከተማ አሥመራ ላይ አድርጎ ለመላው የአገራችን ሰሜናዊ ክፍለ ሃገራት ማለትም ለትግራይ፣ ለወሎና ለጐንደር ጥበቃ የተሰማራው አንድ እግረኛ ክፍለ ጦር ብቻ ሲሆን እሱም ከዚህ በላይ እንደተገለፀው ሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር ነው::

ሁለተኛው እግረኛ ክፍለ ጦር በኂላ ሁለተኛ ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ለሰሜኑ ክፍለ ሃገራት አማካይና መገናኛ በሆነ በወሎ ክፍለ ሃገር ርዕሰ ከተማ ከደሴ ወጣ ብሎ በሚገኝና ጢጣ ተብሎ በሚጠራ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ሠራዊት ሥሪት በሆነ የጦር ሰፈር በ1934 ዓ.ም ተቋቋመ::

የክፍለ ጦሩ መስራችና የመጀመሪያው አዛዥ ብ/ጀነራል መርዕድ መንገሻ ይባላሉ:: እኝህ መኰንን በ1953 ዓ.ም በአገሪቱ የነበሩትን የመከላከያ ሠራዊት ከፍተኛ መኰንኖች በማስተባበር መርተው በእነ ጀነራል መንግሥቱ ንዋይ የተሞከረውን መፈንቅለ መንግሥት በማክሸፋቸው በሌ/ጀነራልነት ማዕረግ የአገሪቱ የመከላከያ ሚኒስትር ለመሆን የበቁ ናቸው::

ሁለተኛው እግረኛ ክፍለ ጦር የእዝ መምሪያውንና ጠቅላይ ሰፈሩን ደሴ ከተማ ላይ አድርጎ በእዙ ሥር ከነበሩት እግረኛ ብርጌዶች ስድስተኛውን በትግራይ ክልል፣ ስምንተኛውን በጐንደር ክልል ፀጥታ ለማስከበርና ለጠረፍ ጥበቃ አሰማርቶ ለአስራ አንድ ዓመታት ማለትም የኤርትራ ክልል ነዋሪ ህዝብ ከወገኑ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በፌደሬሽን መልሶ እስከ ተዋሀደበት እስከ 1945 ዓ.ም ድረስ በኢምፔሪያሊስት ብሪታኒያ መንግሥት ወታደራዊ ቅኝ አገዛዝ ሥር የነበረውን የኤርትራ ክፍለ ሃገርና እንዲሁም በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ አጎራባቻችን የሆነውን ሌላውን የኢምፔሪያሊስት ብሪታኒያ መንግሥት ወታደራዊ ቅኝ ግዛት የሆነውን የሱዳንን ሁኔታ በንቃት ይከታተል ነበር::

በ1945 ዓ.ም ኤርትራ ከእናት አገሯ ከኢትዮጵያ ጋር በፌደሬሽን ተመልሳ ስትዋሀድ የሁለተኛው እግረኛ ክፍለ ጦር የጥበቃ ቀጠና ከቀድሞ ይዞቱ ስለሰፋና ማለትም ከወሎ፣ ከትግራይና ከጐንደር ክፍለ ሃገራት በተጨማሪ ኤርትራ ስለተጨመረ ከሶስተኛውና ከአንደኛው እግረኛ ክፍለ ጦሮች በተወጣጡ እግረኛ ሻለቆች የተዋቀረና 12ኛ የተባለ መለያ የተሰጠው እግረኛ ብርጌድ ስለተጨመረለት አዲስ የተቋቋመው 12ኛ ብርጌድን ለኤርትራ ክልል ህዝብ ደህንነትና ለጠረፉ ጥበቃ ወደ ኤርትራ አሰማራው::

12ኛ እግረኛ ብርጌድ በኢትዮጵያ የምድር ጦር አካል ከሆኑ የጦር ክፍሎች አዲሱን የኤርትራ ክልል ምድር በመርገጥ የመጀመሪያው ሆኖ የኤርትራን ክፍለ ሃገር ጥበቃ ተረከበ::

የ12ኛ እግረኛ ብርጌድ መስራችና የመጀመሪያው አዛዥ ኮለኔል አበበ ገመዳ ይባላሉ:: አበበ ገመዳ በ12ኛው እግረኛ ብርጌድ አዛዥነታቸው እዚያው ኤርትራ ለረጂም ጊዜ ቆይተው በጊዜ ሂደት የሁለተኛው ዋሲያ እግረኛ ክፍለ ጦር፣ ከዚያም የሰስተኛው አንበሳ ክፍለ ጦርና በመጨረሻም እስከ አብዮታችን ፍንዳታ ድረስ የአፄ ኃይለሥላሴ የክብር ዘብ ክፍለ ጦር አዛዥና የንጉሠ ነገሥቱ ልዩ ኤታማዦር ሹም ነበሩ::

ኮሎኔል አበበ ገመዳ የ12ኛ እግረኛ ብርጌድን መምሪያና ጠቅላይ ሰፈር በኤርትራ ክፍለ ሃገር ርዕሰ ከተማ በአሥመራ በማድረግ በብርጌዱ ዕዝ ሥር ካሉት እግረኛ ሻለቆች ውስጥ የ33ኛ ሻለቃን ጠቅላይ ሠፈር እዚያው አሥመራ ላይ በማድረግ በሻለቃው መምሪያ ዕዝ ሥር ካሉት እግረኛ ሻምበሎች በክፍለ ሃገሩ ምዕራባዊ ቆላ አውራጃዎች ማለትም አንዱን የሻምበል ጦር ለተሰነይ ሌላውን ለቆርዳት አውራጃ ጥበቃ አሰማሯቸው::

የ34ኛ እግረኛ ሻለቃ መምሪያንና ጠቅላይ ሠፈር በክፍለ ሃገሩ ደጋማ ክልል ማይሐበር ላይ በማድረግ የሻለቃውን ከባድ መሣሪያ ሻምበል ጦርና ሁለቱን እግረኛ ሻምበሎች እዚያው ማይሐበር በሻለቃው ጠቅላይ ሠፈር ሠፍረው ለሐማሴን አውራጃ ጥበቃ መድቦ የቀረውን አንዱን እግረኛ ሻምበል ጦር ለምፅዋ አውራጃ፣ ለከተማውና እንዲሁም ለወደቡ ጥበቃ አሰማራ::

የ35ኛውን እግረኛ ሻለቃ መምሪያና ጠቅላይ ሠፈር እዚያው አሥመራ ከተማ በማድረግ ሻለቃው የክፍለ ሃገሩን ርዕሰ ከተማ አሥመራንና የተቀሩትን ደጋማ አውራጃዎች ማለትም የሰራዬን፣ የአካለ ጉዛይንና የከረንን ጥበቃ እንዲረከብ ተደረገ::

12ኛ እግረኛ ብርጌድ በግንባር ቀደም የጦር ክፍልነት የኤርትራን ክፍለ ሃገር ጥበቃ ተረክቦ እራሱን ከአካባቢው ጋር ማለማመድና ማናቸውንም ነገር በቁጥጥሩ ሥር ማድረጉ እንደተረጋገጠ ሁለተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር መምሪያውን፣ ጠቅላይ ሠፈሩን፣ የውጊያ ድጋፍና ልዩ ልዩ የቴክኒክ አገልግሎት ሰጪ ክፍሎቹን ከወሎ ክፍለ ሃገር ርዕሰ ከተማ ከደሴ አንቃንቆ ኤርትራ ክፍለ ሃገር ርዕሰ ከተማ አሥመራ ላይ አደረገ::

ከ12ኛ እግረኛ ብርጌድ ሌላ በሁለተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ዕዝ ሥር ያሉት ስድስተኛና ስምንተኛ ብርጌዶች ከነሻለቆቻቸው በነበሩበት ማለት ስድስተኛ ብርጌድ ጠቅላይ ሠፈሩን ኩያ ላይ በማድረግ ሻለቆቹን ለተቀረው ትግራይና ወሎ ክፍለ ሃገር ስምንተኛ ብርጌድ ጠቅላይ ሠፈሩን አዘዞ ላይ አድርጎ ለጐንደር ክፍለ ሃገር ጥበቃ እንደተሰማሩ በያሉበት እንዲቆዩ ተደረገ::

የኤርትራ ክልል ነዋሪ ህዝብ ከወገኑ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር መልሶ በፌደሬሽን ከተዋሀደ በኋላ እስከ ፌደሬሽኑ መፍረስ ድረስ በትግላችን ቅፅ አንድ የመከላከያ

ሠራዊታችንን የሰው ኃይል አስመልክቼ ባደረግሁት ገለፃ ለማሳወቅ እንደ ሞከርኩት በጦር ኃይሎቻችን ልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች ውስጥ ያለው የሰው ኃይል በየምክንያቱ ማለትም በሞት፣ በጡረታና በክዳት ወዘተ ሲጓደል በሌሎች በተለይም በለሙት አገሮች እንደሚደረገው በጦር ኃይላችን ተቋም ውስጥ ያሉ ልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች በሠላምም ሆነ በጦርነት ጊዜ በየምክንያቱ የሰው ኃይላቸው ሲጓደል ወዲያው የሚተካ ማዕከላዊ የጦር ማሰልጠኛ ማከማቻና ማደያ ማዕከል ወይንም «Man power Depot» ስለሌለን ሁለተኛ ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦርም እንደሌሎቹ እግረኛ ክፍለ ጦሮች ሁሉ በእዙ ስር ያሉትን እግረኛ ብርጌዶች አካቶ በአቋም ዘጠኝ ሺህ ያህል የሰው ኃይል እንዲኖረው ይወሰን እንጂ የውጊያ ድጋፍና የቴክኒክ አገልግሎት ሰጪ ልዩ ልዩ ክፍሎችን ጨምሮ እስከ አብዮታችን ፍንዳታ ድረስ የሰው ኃይሉ ተሟላ ቢባል ከሰባት ሺህ የበለጠበት ጊዜ አልነበረም።

የኤርትራ ክፍለ ሃገር ህዝብ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በፌደሬሽን መልሶ ከተቀላቀለ በኋላ እስከ ፌደሬሽኑ መፍረስ ከአስር ዓመታት በላይ የሠራዊቱን ተሳትፎ የሚጠይቅ ምንም ዓይነት የፀጥታ ችግር ስላልነበር እስከ 1955 ዓ .ም ድረስ ለኤርትራ ክልል ጥበቃ የተሰማራው ከክፍለ ጦሩ የውጊያና የቴክኒክ አገልግሎት ድጋፍ ሰጪ ክፍሎች ጋር አንድ እግረኛ ብርጌድ ብቻ ሲሆን ከዚህም ጦር ላይ እየተቀነሰ አንድ እግረኛ ሻለቃ ጦር ለኮንጎ የተባበሩት መንግሥታት ማህበር ፀጥታ ለማስከበር ሥራ ተልዕኮ ነበር።

ተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት የደፈጣ ተዋጊ ጦሮቹን ሠላማዊ ሰዎች በማስመሰል የአካባቢው ከብት አርቢ ህዝብ የሚለብሰውን ዓይነት ጨርቅ እያለበሰ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት አሥርጎ በማስገባት የሚያከናውነውን ሽብር ከፍ ከማድረጉ በላይ በሁለቱ አገሮች ድንበር ላይ ባሉ በርካታ የጠረፍ ከተማችና መተላለፊያ ኬላዎች ላይ ለፀብ አጫሪነት ያሰማራቸው መደበኛ የጦር ክፍሎች ውጊያ በከፈቱብን በ1956 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ ከሚገኘው ከአንደኛው የክብር ዘበኛ ክፍለ ጦር ክፍሎች አንድ እግረኛ ብርጌድ ጦር በተደራቢነት ወደ ለሶስተኛው አንበሳው እግረኛ ክፍለ ጦር በተላከበት ጊዜ በሁለተኛ ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር እዝ ሥር ካሉት እግረኛ ሻለቆችም 33ኛው ከአሥመራ ወደ ሐረርጌ ተልኮ ለሶስተኛው አንበሳ እግረኛ ክፍለ ጦር ተደርቦ ስለነበር በዚያ የጊዜ ክልል ውስጥ በኤርትራ ምድር የቀሩትና በ12ኛው እግረኛ ብርጌድ መምሪያ የሚታዘዙት እግረኛ ሻለቆች፣ 34ኛውና 35ኛው ማለትም ሁለት ሻለቆች ብቻ የሆኑበት ጊዜ ነበር። ከሰሜን አሜሪካ መንግሥት ጋር በተደረገው የመከላከያ ተራድኦ ውል መሰረት በዚያን ጊዜ የአንድ የኢትዮጵያ እግረኛ ሻለቃ ጦር ጠቅላላ የሰው ኃይል 631 (ስድስት መቶ ሰላሣ አንድ) ሰው ነው።

የ34ኛና የ35ኛ ሻለቆች የሰው ኃይል እንደተሟላ ቆጥረን የሁለቱን ሻለቆች ጠቅላላ የሰው ኃይል ከብርጌዱ ጠቅላይ ሠፈርና የብርጌዱ አጋዥ መሣሪያ ከሆነው ከ4.2 ኢንች አዳፍኔ ሻምበል ጦር ጋር ብናሰላው በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ በኤርትራ

ክልል ጠረፉን ለማስከበርና የህዝቡን ደህንነት ለመጠበቅ የተሰማራው የ12ኛ እግረኛ ብርጌድ የሰው ኃይል 1562 አንድ ሺህ አምስት መቶ ስልሳ ሁለት ነበር።

በኤርትራ ክልል ለጥበቃ ከተሰማሩት እግረኛ ሻለቆች አንዱ የሆነው 33ኛው ሻለቃ መቀነስ ያስከተለው ችግር አልነበረም። ምክንያቱም በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ የሠራዊቱን ተሳትፎ የሚጠይቅ ምንም ዓይነት የፀጥታ ወይንም የሠላም መታወክ ስጋት ካለመኖሩ ሌላ ችግር ቢከሰትም አስፈላጊ ከሆነ ለአሥመራ ከተማ በአንድ መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት አዲግራት ላይ ሠፍሮ የሚገኘውን የመድፈኛ ሻለቃ ጦር ጭምር በትግራይና በጐንደር ክፍለ ሃገራት ውስጥ የሚገኙትን ሁለት እግረኛ ብርጌዶች ከሃያ አራት ሰዓት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ወደ ኤርትራ ለመላክ ስለሚቻል ነው።

ክፍል አሥራ ሰባት

ምዕራፍ ሃያ ሰባት

ለኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክልል ድንበርና ለህዝቡ ማህበራዊ ደህንነት ጥበቃ የተሰማራው ሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር ከገንጣዮች ጋር ያደረገው ፍልሚያ

ራሱን «የኤርትራ ነፃ አውጭ» በአረብኛ «ጀብሐ» ብሎ የሚጠራው ገንጣይ ድርጅት እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1960 ዓ.ም በግብፅ ርዕሰ ከተማ በካይሮ ራዲዮ መቋቋሙን ገለፀ:: አከታትሎም በግብፅ፣ በሱዳን፣ በሶሪያ፣ በአልጀሪያና በቻይና በሰለጠኑለት የጎሪላ መሪ መኰንኖች የድርጅቱን ተዋጊ ሠራዊት በብዛት ሱዳን ውስጥ አሰልጥኖ ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት የኤርትራን ህዝብ የማሸበር ተግባሩን ጀመረ:: የሌ/ጀነራል አቢይ አበበ በኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር የአመራር አካላትና በጠቅላላውም በማህበሩ አባላት በመጠላታቸው ልዑል አሥራተ ካሳ የኤርትራ ክፍለ ሃገር አስተዳዳሪ ሆነው ተተኩ:: ይህ ሁሉ ሲሆን የጀብሐ ሠራዊት መሠረት ወይንም ጥንስስ ነው የምንለው በሐሚድ እድሪስ አዋቴ የተመራው ሽብር ፈጣሪ ሽፍታ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የሰራው ሁሉ ፋይዳ ቢስ ነበር:: ከቶውንም ከረን ከተማ ላይ የእጅ ቦምቦችን በመወርወር በእነ ሌ/ጀነራል አቢይ አበበ ላይ አደጋ ለማድረስ ከመሞከር፣ በምዕራባዊ ቆላማ አውራጃዎች ነዋሪ የሆኑ ክርስቲያኖችን፣ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አባላትንና አንድነት ደጋፊዎችን ከመዝረፍ፣ አልፎ አልፎ መከላከያ የሌላቸው ሠላማዊ ሰዎች ላይ ያለ ምክንያት ርህራሄ አልባ ግድያ ከመፈፀም በስተቀር የመንግሥቱን ሠራዊት የተዳፈረበት ጊዜ አልነበረም::

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1962 እና 63 ዓ.ም በጨቅላ የጎሬላ የደፈጣ ውጊያ ሥልት የመንግሥቱን ጦር ለመተናኮል ቢሞክርም በፈንጂ ወጥመድ ከመጠቀምና አነስተኛ ቁጥር ባላቸው የሽፍታ ጓዶች አደጋ ጥሎ ከመሸሽ ያለፈ ነገር ሲሰራ አልታየም::

በመንቀሳቀስ ላይ ባሉ አነስተኛ የመንግሥቱ ጦሮች ላይ አነስተኛ አደጋዎችን ማድረስ በጀመረም ጊዜ ጦሩ እግር በእግር በመከታተል አሳዶ ስለሚደመስሳቸው ትንኮሳቸው በእነሱው ላይ የከፋ ጉዳት ያደርስባቸው ነበር እንጂ የጠቀማቸው ነገር አልነበረም::

በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ ማለትም በ1961-62 እና 63 ዓ.ም በምዕራባዊው ቆላማ አውራጃዎች ውስጥ ፀጥታ የሚያስከብሩና ሽብርተኞቹን እያደኑ የሚመቱ ጥቂት ተነጣይ እግረኛ ሻምበሎችና ፈጥኖ ደራሽ ፖሊሶች ብቻ ነበሩ::

በተለያዩ የአረብ አገሮችና በህዝባዊ ቻይና ድጋፍ ሥልጠና ያገኙ የጀብሐ መኰንኖች ከግብረ አበሮቻቸው ጋር በሱዳን ምድር ያሰለጠነውን ብዛት ያለው ዘመናዊ ጎሪላ ቀደም ብሎ በኤርትራ ውስጥ ሲዋጋ ከቆየው ሽፍታ ጋር በማስባጠር አደራጅተው ጠቅላላ ጉባዔ በመባል የሚጠራ የጀብሐ የመጨረሻ ከፍተኛ የወታደራዊ አመራር ማዕከል በሱዳን ውስጥ አቋቋሙ።

ይህ ከፍተኛ የአመራር አካል ኃላፊነቱ ለወታደራዊው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካውንምና በጠቅላላው ሁለንተናዊ ኃላፊነት ያለው የድርጅቱ የአመራር ማዕከልና የሠራዊቱ ጠቅላይ መምሪያ ነው።

በዚህ ጠቅላይ መምሪያ እዝ ስር ሠራዊቱን ለውጊያ በመስክ የሚመሩ አምስት የቀጣና ወታደራዊ እዞችን አቋቁመው በአራቱ የቀጠና እዞች የሚመራውን ጦር በቆላማው ምድርና የእስልምና እምነት ተከታይ በሆነው ህብረተሰብ መኖሪያ ክልል ሲያሰማሩ፣ አምስተኛውን የቀጠና ወታደራዊ እዝ ክርስቲያኑ ህብረተሰብ በሚኖርበትና ለቆላማው ክልል ወሰንተኛ በሆነው በሰሜናዊው ደጋማ ክልል አሰማርተው በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ባልታሰበና ባልተጠበቀ ሁኔታ ከመንግሥቱ ጦርና ከፖሊሱ ኃይል ጋር ፊት ለፊት ውጊያ እየገጠሙ በመጋተር ክልሉን የውጊያ አውድማ አደረጉት።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የኤርትራ ክፍለ ሃገር ምዕራባዊ ቆላማ ክልል እንደ ወትሮው በሁለት እግረኛ ሻምበል ጦርና በክልሉ ፈጥኖ ደራሽ ፖሊሶች ፀጥታውን ማስከበር የሚቻል ባለመሆኑ የሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር መምሪያ በጐንደርና በትግራይ ክፍለ ሃገራት የሰፈሩትን እግረኛ ብርጌዶች ጦሮች አብዛኛውን ወደ ኤርትራ ክፍለ ሃገር በማዛወርና በተለይም የቆላማ አውራጃዎችን ፀጥታ የማስከበር ተግባሩን በሰው ኃይል በማጠናከር ጀብሀ በሰላማዊ ህዝብና በመንግሥቱ ጦር ላይ የሚያካሂደውን ጥቃት ለመከላከል ሞከረ።

አዲሱ የኢትዮጵያ ትውልድ በአጠቃላይ፣ ለውጥ ፈላጊው ምሁርና ተማሪው ህብረተሰብ በተለይ ከመንግሥትና ከአገራቸው ባህል ጋር በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ መጋጨት እንደጀመሩና ከመናኛ ቅራኔዎች ተነስተው ወደ ፀረ-መንግሥት አመፅ እንዲያመሩ መንስኤ ወይንም ምክንያት የሆኑ ታሪካዊ ክስተቶች የ1953 ዓ.ም የታህሳሱ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች አንድነት ማህበር መቋቋም፣ ተማሪው የኢትዮጵያ አርሶ አደሮችን የአያሌ ምዕተ ዓመታት የመሬት ለአራሹ ጥያቄ ይዞ አደባባይ መውጣትና በዚሁ ጊዜ ውስጥ በኤርትራ ራሱን «የኤርትራ ነፃ አውጭ» በአረብኛ «ጀብሐ» ብሎ የሚጠራ አገር ገንጣይ ድርጅት መፈጠር እንደሆኑ ይታወቃል።

በ1953 ዓ.ም በነጀነራል መንግሥቱ ንዋይና ግርማሜ ነዋይ፣ በኰሎኔል ወርቅነህ ገበየሁና በግብረ አበሮቻቸው የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ ክፍለ ጦር መኰንኖች የአፄ ኃይለሥላሴን ዘውዳዊ መንግሥት አገዛዝ ለመጣል የሞከሩትና በሚያሳዝን

ሁኔታ የከሸፈውን ፀረ ዘውድ ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት በመደገፍ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ተማሪዎችና መምህራን በሠልፍ አደባባይ በመውጣት አሀዱ ብለው ከመንግሥት መጋጨት ጀመሩ።

ግጭቱ ወደ መደበኛ ትግል ተሸጋግሮና ትግሉም በጊዜ ሂደት እድገት አሳይቶ ተማሪው መንግሥትን አስገድዶ በተማሪዎች ማህበር በመሰባሰብ ተደራጅቶ በአገሪቱ የፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ በመግባት መሬት ለአራሹ፣ ሥልጣን ለህዝቡ ወዘተ በማለት መሰረታዊ የፖለቲካ ጥያቄዎችን ይዞ ዳግም አደባባይ በመውጣት ከመንግሥቱ የፀጥታ አስከባሪ ኃይሎችጋር ከመፋጠጥ አልፎ ወደ አካላዊ ግጭትና ትግል ተሸጋገረ።

ከ1953 ዓ.ም ወርሐ ታህሳስ በኋላ የተማሪዎች ንቅናቄ በአጠቃላይ ወይንም በጅምላ ማለት ይቻላል ፀረ መንሥት አቋም ያዘ።

ከ1953 ዓ.ም ወርሐ ታህሳስ በኋላ የኢትዮጵያ አዲስ ትውልድ ከገዥው መደብ ጋር የማይታረቅ ቅራኔ ውስጥ መግባት ብቻ ሳይሆን ከአገሩ ወይንም ከራሱ ባህል ጋር መጣላትም ጀመረ።

የወጣቱ ወላጅ ህብረተሰብ ወይንም ቤተሰብ በነበረው እጅግ ዝቅተኛ የፖለቲካ ማህበራዊ የንቃት ደረጃ በወጣቱ ህሊና ላይ ባደረሰው ተፅእኖና በወጣቱም የእድሜ ለጋነት ምክንያት የጨቋኙ ፊውዳል ሥርዓት ማህበር አራማጅ ገዥ መደብ መሪ የሆኑትን ንጉሥ መተኪያ የሌላቸው፣ በእግዚአብሄር የተመረጡና የተሰየሙ ከማለት ባሻገር ፀሐዩ ንጉሥ እየተባለ በወላጆቹ፣ በመምህራኖቹና በመንፈሳዊ አባቶች እየተነገረው ስለአደገ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ረጅም ዕድሜ እየለመነ ሲዘምርና ወላጅ አባቱን ትቶ በንጉሡ ስም ሲምል የኖረው ወጣት ከ1953 ዓ.ም ወርሐ ታህሳስ በኋላ ግፍና ጭቆና ይቁም፣ የዘውድ አገዛዝ ያብቃ በማለት በንጉሡና በመንግሥታቸው ላይ ንቀትና ጥላቻ አደረበት።

ይህ ተማሪውን በፀረ- ዘውድ ወይንም በፀረ - መንግሥት አቋም ያሰባሰበ አዲስ አመለካከት ግብታዊ እንጂ ከዚያ ባሻገር የአፄው መንግሥት ምን ይሁን ? በምን ዓይነት መንግሥት ይተካ? ኢትዮጵያ ምንዓ ይነት መንግሥት ያስፈልጋታል? በሚል በጠራና ዘላቂ በሆነ የፖለቲካ ዓላማና ፅንሰ ሃሳብ ላይ የተመሰረተ አመለካከት አልነበረም።

በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ የኤርትራን ፌደሬሽን መፍረስ በመቃወም የቀድሞው በኢትዮጵያ አንድነት ተቃዋሚነት በኤርትራ ምዕራባዊ ቆላማ ክልል ነዋሪ የሆኑትን የእስልምና እምነት ተከታይ የተለያዩ ማህበረሰቦችንና ብሔረሰቦችን አባላት ከሞላ ጎደል በማሰባሰብ አደራጅቶ ራሱን እስላማዊ ሊግ ብሎ ይጠራ የነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበርን አንጃ ያቋቋመውና ራሱን «የኤርትራ ነፃ

አውጭ» በአረብኛ «ጀብሐ» ብሎ የሚጠራው አገር ገንጣይ ድርጅት ሲቋቋም፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ማህበር አባላት የሆኑ ጥቂት የኤርትራ ክፍለ ሃገር ተወላጆች የተማሪው ማህበር ንቅናቄ ከሚያራምደው ጅምላ ፀረ-መንግሥት አቋም በላይ አልፈው በቋንቋ ቤተሰብነትና በአካባቢ ጠባብ ብሔርተኛነት ስሜት ተመርተው «ጀብሐ» የተባለው ገንጣይ ድርጅት እንዴት እንደተቋቋመ፣ በነማን ድጋፍና ግፊት እንደተቋቋመና ለምን ዓይነት ዓላማ እንደተቋቋመ ሳይገነዘቡ የኤርትራ ነፃ አውጭ በተሰኘ ስም ራሱን በመጥራቱ ብቻ በጭፍን የጀብሐ ደጋፊ ሆኑ።

በሂደት ከጀብሐ ደጋፊነትና ከፀረ- መንግሥት አቋማቸውም አልፈው፣ የጨቋኙ የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የአመራር አካላትና ጠቅላላው ገዥ መደብ የአማራው ብሔር አባል ነው በማለት ፀረ አማራ አቋም ይዘው በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዩኒቨርስቲው ውስጥ በጎሳ የፖለቲካ ዓላማ ላይ የተመሠረተ የጠባብ ብሔርተኝነት ቅስቀሳ ጀመሩ።

በጎሰኛ ወይንም በጠባብ ብሄርተኛ የፖለቲካ ቅስቀሳው የተሳቡ ጥቂት የትግራይ ክፍለ ሃገር ተወላጆችና ጥቂት የኦሮሞ ብሔረሰብ አባላት የሆኑ ተማሪዎችም ስለአጀቧቸው የተማሪው አንድነት ማህበር ንቅናቄ በጎሳ ፖለቲካ ተከፋፈለ።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በጥቂት የኤርትራ ክፍለ ሃገር ተወላጅ በሆኑ ተማሪዎች የተጀመረ የቋንቋ ቤተሰብነትና የአካባቢ ጠባብ ብሔርተኛ ስሜት በጊዜ ሂደት ከፍተኛ ዕድገትና ስፋት አሳይቶ ወይንም ጎልብቶ የብሔረሰቦች ጉዳይ በተማሪው ማህበር ንቅናቄ የፖለቲካ አጀንዳዎች ዋናውንና ግንባር ቀደሙን ስፍራ በመያዝ ከዩኒቨርስቲው ቅጥር ግቢ ወጥቶ ወደ ተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች ተዛመተ።

ጀብሐ ከተቋቋመ ጥቂት ዓመታት በኋላ «የኤርትራ ክልል ሕዝብ በታሪክ የኢትዮጵያ ሕዝብ አካል ሆኖ አያውቅም፣ የኤርትራ ሕዝብ የኢትዮጵያ ክርስቲያናዊ መንግሥት ቅኝ ግዛት ስለሆነ የጀብሐ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው» ብሎ ባወጣው የፖለቲካ ፕሮግራም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የተፈጠረው የጀብሐ ደጋፊ ጠባብ ብሔርተኛ የተማሪ ቡድን እንደ እውነት ተቀብሎ በዩኒቨርስቲው ውስጥ ከማዳነቅና ከማራባት ባሻገር የቡድኑ አባላት «እኛ በአዲስ አበባ የተገኘነው የኤርትራ ክልል ተማሪዎች የኢትዮጵያ መንግሥት የትምህርት ዕድል (ስኮላርሺፕ) ስለሰጠን እንጂ የኢትዮጵያ ዜጋ ሆነን አይደለም» እያሉ በዩኒቨርስቲው ቅጥር ግቢ ብቻ ሳይሆን በአዲስ አበባ መሸታ ቤቶች ሁሉ እየዞሩ በገሀድ መናገር ጀመሩ።

የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ይህንን የመሰለውን ክህደትና አገር የማፍረስ ተግባር ብቻ ሳይሆን ጠቅላላውን ፀረ አንድነትና ፀረ-መንግሥት የሆነውን የተማሪውን ማህበር ንቅናቄ ለማቆም በከፍተኛ የትምህርት ተቋም ተማሪዎች ላይና በማህበራቸው

የአመራር አካላት ላይ ከባድ የኃይል እርምጃ መውሰድ በጀመረበት ጊዜ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ አገርን የመገንጠል ዓላማ የሚያራምደው ጠባብ ብሔርተኛ ቡድን አባላት አብዛኛው ማለት ይቻላል በአንድ በኩል ከመንግሥቱ የፀጥታ አስከባሪዎች ብትር ለመሸሽ፣ በሌላ በኩል ከመንግሥቱ ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር በመቀላቀል መንግሥትን ለመበቀል ይመስላል የትምህርት ገበታቸውን ጥለው እየኰበለሉ በመሄድ የጀብሐን አፈጣጠርና የሚያራምደውን ዓላማና ተግባር በውል ሳይረዱ በአካባቢ ጭፍን ስሜት ተነሳስተው በተማሪ ወጣት የሰው ኃይል አጠናከሩት።

በዚህ ጊዜ የተማሪው ማህበር አባላት ሁሉ ባይሆኑም በከፊል ከነበሩበት ማህበራዊ የፖለቲካ ንቃት ደረጃ ምክንያት ኤርትራዊያኑ ተማሪዎች ከጀብሐ መቀላቀል የብሔረሰቦችን ንቅናቄ ከማጠናከር ባሻገር የአፄ ኃይለሥላሴን መንግሥት መበቀል የሚያስችል አብዮታዊ ተግባር አድርገው በመመልከት በአንባቢ ዘንድ ይታወስ እንደሆነ ከ1955 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አብዮታችን ዋዜማ ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ በአራት ኪሎና በስድስት ኪሎ ቀበሌ አካባቢ ዘወትር ከቀትር በኂላ ወደ ማታ የምንሰማው የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች መፈክርና መዝሙር፣ ፋኖ ተሰማራ እንደነ ሆቺሚኒ እንደቼጉቬራ የተሰኝ ነበር።

በዚህ የንቃት ደረጃ፣ አስተሳሰብና ቅስቀሳ በአገር ውስጥ ያለው ብቻ ሳይሆን በውጭ በአውሮፓ፣ በሰሜን አሜሪካ ወዘተ የነበሩት የተማሪው ማህበር አባላት ሁሉም ባይሆኑ ጥቂት የትግራይና የኦሮሞ ወዘተ ብሔረሰቦች አባላት የኤርትራዊያኑን ድርጊት እንደ በጎ ነገር በመመልከትና የእነሱን አርአያ በመከተል ከትምህርት ገበታቸው እየኮበለሉ ወደ የተወለዱበት ክልሎች ገጠር ወይንም ዱር በመሄድ ከኢትዮጵያ ጠላቶች መሣሪያ እየተቀበሉ አገራቸውን መውጋት ጀመሩ።

ይህንን ርዕስ ለማጠቃለል፣ በድህረ ፋሽስትና በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ፣ በኤርትራ አሚድ ኢድሪስ አዋቴ፣ በኦጋዴን የደገሐቡር አውራጃ ባላባት የነበረው ደጃዝማች መቅተል ጻሒር፣ በባሌ ዋቆ ጉቱ የሚባሉት ግለሰቦች ከመሯቸው ፀረ-አንድነትና ፀረ-መንግሥት የትጥቅ ትግሎች በኂላ ጀብሐ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በተለይም በአብዮታችን መቃረቢያና ዋዜማ በአገሪቱ የተለያዩ ክልሎች እንደ እንጉዳይ የፈሉትን በትጥቅ የታጀቡ በየብሔረሰቦች ወይንም በአገሪቱ የተለያዩ የቋንቋ ቤተሰቦች ስም የተካሄዱትን አመፆች የአደራጁትና የመሩት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ንቅናቄ የአመራር አካላትና አባላት የነበሩ ወጣቶች ናቸው።

ከዚህ በኂላ በሚከተለው ታሪክ አንባቢ ለመረዳት እንደሚችለው ራሱን «የኤርትራ ህዝብ ነፃ አውጭ» በአረብኛ «ሻዕቢያ» ብሎ የሚጠራውን ሌላውን ገንጣይ ድርጅት ያቋቋሙና ዛሬ ኤርትራን ገንጥለው መሪ የሆኑት አብዛኛዎቹ ግለሰቦች ከዚህ በላይ እንደገለፅኩት የቀድሞው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ንቅናቄ አባል የነበሩ ናቸው።

የቀድሞው ፀረ-አንድነት የኤርትራ እስላሞች ሊግ የአመራር አካላት የነበሩት የጀብሐ መሥራቾች ለትጥቅ አመፁ ዓይነተኛ ምክንያት ያደረጉት የፌደሬሽኑን መፍረስ በመቃወም ሲሆን እነሱን የተከሉት አዲሶቹ መሪዎች የሐሰት ታሪክ በመፍጠር «የኤርትራ ህዝብ የእስልምና እምነት ተከታይ ብቻ ሳይሆን በዘሩም አረባዊ ህዝብ ሆኖ ሳለ በክርስቲያናዊው የሐበሻ መንግሥት ቅኝነት የተያዘ ስለሆነ የጀብሐ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው» የሚል የፖለቲካ ፕሮግራም ለመላው አረብና እስላም አገሮች አሰራጭቶ ሊያሰባስብ በቻለው በርካታ የትጥቅ፣ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ የትጥቅ ትግሉን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከቆላማው ክልል ወደ ደጋማው ክልል ማለትም የክርስትና እምነት ተከታይ ወደ ሆነው ህብረተሰብ ክፍል ማሸጋገር ቻለ።

የጀብሐ ሠራዊት በአጭር ጊዜ ውስጥ የመንግሥቱን ሠራዊት በውጊያ ለመጋተር የበቃ በመሆኑና የእስልምና እምነት ተከታይ በሆነው ህዝብ ውስጥ ከመላው አረብና እስላም አገሮች ስለሚያገኘው የፖለቲካ፣ የቁሳቁስና የሞራል ድጋፍ አስመልክቶ ካደረገው ቅስቀሳ ጋር የሠራዊቱን ብዛትና የትጥቁን ጥራት በገሀድ ለማሳየት በመቻሉ በምዕራባዊው ኤርትራ ቆላማ ምድር የሚኖሩ የተለያዩ ማህበረሰቦችና ብሔረሰቦች አባላት ሁሉም ባይሆኑ ቢያንስ ከፊሉ የፖለቲካ ፕሮግራሙን ተቀብለው የደገፉትና የተከተሉት ሲሆን ሁሉም የእስልምና እምነት ተከታዮች ብቻ ነበሩ።

የግብፅ መንግሥት የቀድሞ በኤርትራ እራሱን እስላማዊ ሊግ ብሎ ይጠራ የነበረውን የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገሬ ፍቅር ማህበር ተቃዋሚ አንጃ ቀንደኛ የአመራር አካላትን በአገሪቱ ርዕሰ ከተማ በካይሮ ተቀብሎ በማስተናገድ «ጀብሐ» የተባለውን ገንጣይ ድርጅት ያቋቋመበትን የፖለቲካ ፕሮግራም ከመንደፍ ጀምሮ የገንጣዮን ድርጅት ተዋጊ ሠራዊት በኢትዮጵያ ግዛት ለጥፋት ከማሰማራት ባሻገር የድርጅቱ ዓላማ ግቡን ይመታ ዘንድ ጀብሐን ከመላው የአረቦች መንግሥታትና በጊዜው አፄ ኃይለሥላሴ የሚመሯትን ኢትዮጵያ ተፃራሪ ከነበሩት እንደ ሶቪየት ህብረትና እንደ ህዝባዊት ቻይና ወዘተ ከመሰሉ መንግሥታት ጋር ያስተዋወቀው በኮሎኔል ጋማል አብደላ ናስር ይመራ የነበረው የግብፅ መንግሥት ነው።

ኰሎኔል ጋማል አብደላ ናስር በዚህ ጊዜ ውስጥ ራሱን የመላው አረብ አገሮች መሪ አድርጎ በመቁጠር መላውን የአረብና የእስላም አገሮች በፀረ- እስራኤል ግንባር ለማስተባበር በአገሩ በግብፅ ርዕሰ ከተማ በካይሮ በቅድሚያ የአረብ ሊግን፣ ብሎም የእስላሞች ኮንፍረንስን በቅድም ተከተል ማቋቋሙ ይታወሳል።

ከዚህም አልፎ በወቅቱ በእነሱ አስተሳሰብ የአረብ ተራማጅ አገሮች የሚላቸውን ኢራቅን፣ ሶሪያን፣ አልጀሪያን፣ ሱዳንንና ፍልስጤሞችን እንደጥንቱ በእሱ የበላይ መሪነትና በግብፅ ማዕከልነት የተማከለ አንድ ግዙፍ የአረቦች ህብረ መንግሥት ለማቋቋም የአረብ አንድነትን ቅስቀሳ አድርጎ ከሶሪያ ጋር የተጀመረው ውህደት ሳይሳካ ቀርቶ በአጭሩ እንደተቀጨም ይታወሳል።

በኮሎኔል ጋማል አብደላ ናስር መሪነትና በግብፅ ማዕከልነት የአረቦችን ህብረ መንግሥት ለመፍጠር የተደረገው ሙከራ ያለመሳካቱን በመረዳት ብቻ ሳይሆን ቢሳካም ኖሮ ዘለቄታ ኖሮት የአረቦችን ፍላጎት የሚያሟላ አልነበረም ከሚሉ አረባዊያን መካከል በሌላ መልክና ይዘት በፀረ-አይሁድ ግንባርነት ሌሎች ሁለት ተቋማት ተፈጠሩ።

እነዚህም- 1ኛ. በአክራሪ እስላማዊ እምነት ወይንም እስላማዊ ርዕዮት እስልምናን የማስፋፋት ዓላማ ያነገበ የእስላማዊ ወንድማማቾች ድርጅት፣

2ኛ. በእስልምና እምነት ወይንም ሃይማኖት ላይ ሳያተኩር በፀረ-አይሁድ ግንባር አመራር አረባዊነትንና የአረቦች ግዛትን ማስፋፋት ዓላማው ያደረገ «ባአዝ» በተባለ ስም የሚጠራ የአረብ ብሔርተኛ የፖለቲካ ድርጅት ተቋቋመ።

የእነዚህ ሁለት አረባዊ ድርጅቶች ተመሳሳይነት በፀረ-አይሁድነታቸው ብቻ ሲሆን በተቀረው ጠቅላላ ግብርና ዓላማቸው በጣም የተለያዩ ፍፁም የማይስማሙ ወይም የማይጣጣሙ ብቻ ሳይሆን አንዱ ሌላውን እንደጠላቱ በመመልከት የተዋጉና የሚዋጉ ተቋሞች ናቸው።

የእስልምና ወንድማማቾች ድርጅት በአረብነት ወይንም በዘር ልዩነት ሳይሆን በእስላማዊ እምነት ወይንም ሃይማኖት አክራሪነት ላይ የሚያተኩር የዘርና የጆግራፊ ድንበር የማይመለከት ድርጅት ነው።

በኢራቅ፣ በሶሪያ፣ በፍልስጤም የፖለቲካ አመራሩን የያዙትና «ባአዝ» (Ba'ath) በመባል የሚጠሩት የፖለቲካ ፓርቲዎች በሚያራምዱት ርዕዮተ ዓለም አንድነት ላይ የተመሰረቱ በየአገራቸው የፖለቲካ ሥልጣን ላይ ያልወጡና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኙና በአብዛኛው የአረብ አገሮች ውስጥ ያሉ «ባአዞች» ህብረት አረባዊ ብሔርተኝነትንና የአረቦችን ግዛት የማስፋፋት ዓላማ የሚያራምድ ድርጅት ነው።

ባአዞች ራሳቸውን በአረቡ ዓለም ብቸኛ ተራማጅ አድርገው ከማሰብ አልፈው በእነሱ አመለካከት የበአዝ ፍልስፍና ወይንም ርዕዩ ተዓለም አረባዊ ሶሺሊዝም ነው ሲሉ፣ የእስላም ወንድማማቾችን፣ ከጊዜው ወደ ኋላ የቀሩ አድሃሪና አረባዊውን ህዝብ ብቻ ሳይሆን የዓለምን እስላማዊ ህዝቦች የሚከፋፍሉ ከፋፋዮች ናቸው በማለት አምርረው ይጠሏቸዋል።

ኮሎኔል ገማል አብደል ናስር በሚመራው የግብፅ መንግሥት አስተባባሪነት ከመላው የአረብ መንግሥታት ጋር መተዋወቅ የቻሉት የጀብሐ አመራር አካላት መላው የኤርትራ ሕዝብ በእምነቱ እስላም ከመሆኑ ባሻገር በዘሩም አረብ ስለሆነ ይህንን ህዝብ ከክርስቲያናዊው የሐበሻ ዘውዳዊ መንግሥት ቅኝነት ነፃ ለማውጣት የሚታገለው ድርጅታችን የአረብ ሊግ አባልነት መብት ሊሰጠው ይገባል ብለው

ያቀረቡት ጥያቄ በሊጉ አባል አገሮች ሁለት ሦስተኛ የድጋፍ ድምፅ ሳያገኝ ቀርቶ ጥያቄያቸው ውድቅ በሆነ ጊዜ ነበር የጀብሐ መሪዎች ድርጅታቸውን የባአዝ ፓርቲ አባል ያደረጉት።

በባአዝ ፓርቲ ዓላማ መሠረት የኤርትራ ህዝብ በሙሉ በእምነቱ እስላም ነው ከማለት ባሻገር በዘሩም አረብ ነው። የትግላችን ዓላማ ይህንን እስላማዊና አረባዊ ህዝብ ከሐበሻ ዘውዳዊና ክርስቲያናዊ መንግሥት ቅኝነት ነፃ አውጥተን በባአዝ ፓርቲ ከሚመራው አረባዊ ህዝብና ክልል ጋር መቀላቀል ነው በሚለው አቋማቸው መሰረት የባአዝ ፓርቲ የአረቦች ግዛት ብሎ በሠራው ልዩ የፖለቲካ ካርታ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ የአረቡ ዓለም አካል እንድትሆን የገቡትን ውለታ ለመላው የድርጅቱ አባላት ለመላው ተዋጊ ሠራዊትና ለመላው የኤርትራ ቆላማ ክልል ነዋሪ ህዝብ ስለ አሳወቁ በተለያዩ የአረብ አገሮች ካሉት የባአዝ ፓርቲዎች በአጠቃላይ ከኢራቅና ከሶሪያ መንግሥት በተለይ ቋሚ የትጥቅ፣ የገንዘብና የቀለብ ተመፅዋች ሆኑ።

ምዕራፍ ሃያ ስምንት

«የኤርትራ ህዝብ ነፃ አውጭ» በአረብኛ «ሻዕቢያ» ብሎ ራሱን የሚጠራው ሌላው ገንጣይና የጀብሐ አንጃ ድርጅት መፈጠር

አንባቢ እንደሚያስታውሰው እነ ተማሪ ኢሳይያስ አፈወርቂ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮብልለው ወደ ኤርትራ በረሐ በመሄድ ጀብሐን የተቀላቀሉት የጀብሐን ዓላማና ማንነት አውቀው ሳይሆን በኤርትራዊነትና በአካባቢ ስሜት ብቻ የጭፍናቸውን እንደነበር ተገልጿል።

ጀብሐን ከተቀላቀሉ በኂላ ያዩትና የተረዱት -

1ኛ. ጀብሐ ከኤርትራ ቆላማ ክልሎች ነዋሪ ከሆኑ የተለያዩ ማህበረሰቦችና ብሔረሰቦች መካከል በተመለመሉ ግለሰቦች የተሞላና በደጋማው ክልሎች ከሚኖሩ ማህበረሰቦችና ብሔረሰቦች አንድም ሰው ያልቀላቀለና የኤርትራን ህዝብ ፈፅሞ የማይወክል ድርጅት ከመሆኑ በላይ እነሱ ድርጅቱን እስከ ተቀላቀሉ ድርስ፣ የድርጅቱ አመራር አካላትና አባላት በሙሉ የእስልምና እምነት ተከታይ መሆናቸውን ነው።

2ኛ. ድርጅቱ እንደ ፓለቲካ ድርጅትና እንደ ነፃ አውጭ ድርጅት በዲሞክራሲያዊ መርህ የማይመራ፣ በድርጅቱ አባላት መካከል እኩልነትና የአባላት ግለሰቦች መብት የማይታወቅበትና ምንም ዓይነት ዲሞክራሲያዊ አሰራር የሌለበት መሆኑን፣

3ኛ. ድርጅቱ የኤርትራ ነፃ አውጭ የተባለ ስም ለብሶ የአመራር አካላቱ ብቻ ሳይሆኑ አብዛኛው ተራ አባላት ኤርትራዊነታቸውንና ብሎም አፍሪካዊነታቸውን ክደው አረባዊ ህዝብ ነን የሚሉ መሆናቸው፣

4ኛ. ግንባሩ ከአረብ አገሮች ጋር ያለው ዝምድናና ትስስር ከፍተኛ ከመሆኑ ባሻገር የአረብ ብሔርተኛነትንና የአረቦች ግዛትን በማስፋፋት ዓላማና ርዕዮት የሚመራው «የባአዝ ፓርቲ» አባል መሆኑ፣

5ኛ. የድርጅቱ አመራር አካላት ጀብሐን ከአቋቋሙበት ጊዜ ጀምሮ ደገኛውና ክርስቲያኑ የኤርትራ ህዝብ እኛን ከድቶና ለክርስቲያኑ ገዥ መደብ ወግኖ ፌደሬሽኑን በማፍረስ ኤርትራን ለአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ሸጧል በሚል ቅስቀሳ ህዝቡን ስለመረዙትና ተዋጊው ሠራዊት በአደረበት ጥላቻ በክርስቲያኑ ህዝብ ላይ የሚወስደው እጅግ አሳዛኝ የሆነ የግፍ እርምጃ ፈፅሞ ያልጠበቁት አስደንጋጭ ድርጊት ነው የገጠማቸው።

በእነዚህ ከብዙ በጥቂቱ ከአንድ እስከ አምስት ተራ ቁጥር በተገለፁት የጀብሐ አመራር አካላት አመለካከት በድርጅቱ አቋምና በተዋጊው ሠራዊት ድርጊት

የተደናገጡና ባልጠበቁት ከፍተኛ ችግር ውስጥ የወደቁት ክርስቲያኖቹ ብቻ ሳይሆኑ እስላሞቹም ነበሩ።

በኤርትራዊነታቸው የሚያምኑ፣ ዓላማችን የኤርትራን ህዝብ ከኢትዮጵያ መንግሥት ቅኝነት ነፃ ማውጣት ከሆነ ከሃይማኖት ልዩነት፣ ከጎሰኛነትና ከአካባቢ ጠባብና ኋላቀር ስሜት ራሳችንን ማፅዳት አለብን የሚሉ የእስልምና እምነት ተከታዮች ቁጥር የሚናቅ ካለመሆኑ ባሻገር በፍርሃትና በመታፈናቸው ስሜታቸውን ለመግለፅ ይሳናቸው እንጂ ከህዝቡም መካከል «እኛ ኤርትራዊያን እንጂ አረባዊያን አይደለንም» የሚሉት ቁጥር በድርጅቱ የአመራር ተፅእኖ አረቦች ነን ከሚሉት በእጅጉ የላቀ ነበር።

የድርጅቱ የአመራር አካላት ከሆኑትና ተሰሚነት ካላቸው ግለሰቦች ውስጥ ስለ ኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ እውቀት ካለው ከብሪታኒያ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ወታደራዊ ቅኝ አገዛዝ ጋር ያደርግ በነበረው ትግል የኢትዮጵያ አንድነት ደጋፊ ከነበረው ከምስራቃዊው ቆላማ ክልል በተለይም ከምፅዋ አውራጃ የተወለደውና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር የነበረው የጀብሐ ፀሃፊ መምህር ኡስማን ሳላህ ሳቤን የመሰሉ ታዋቂ ግለሰቦችና ተከታዮቻቸው እንደ ክርስቲያኖቹ የጀብሐን ማንነት ሳይረዱ ድርጅቱን የተቀላቀሉ ሁሉ በጀብሐ መሪዎች እጅግ የተሳሳተ ብልሹና አደገኛ አመራር በጣም የሚያዝኑ ስለነበሩ ጀብሐ ከመነሻው የተከፋፈለ ነበር ማለት ይቻላል።

የጀብሐ ድርጅታዊ ሁኔታ ይህንን ቢመስልም በክፍለ ሃገሩ ፀጥታ አስከባሪ ፖሊሶችና በጦሩ ላይ አልፎ አልፎ በተቀዳጃቸው ወታደራዊ ድሎች መሪዎቹ ሰክረውና ተብተው ስለነበር በውስጣቸው ያለውን ቅራኔ በሚገባ ያጤኑት አይመስልም።

በዚህ ጊዜ ነበር አፄ ኃይለሥላሴ ጀነራል አቢይ አበበን አንስተው በምትካቸው ልዑል ራስ አሥራተ ካሳን በኤርትራ ሦስተኛ እንደራሴያቸውና የክፍለ ሃገሩ አስተዳዳሪ አድርገው የሾሟቸው።

በኤርትራ ክፍለ ሃገር ርዕሰ ከተማ በአስመራ ውስጥ አቶ እርቂ ዳኘው ይባል በነበረ ግለሰብ ይመራ የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥት ብሔራዊ የአገር ደህንነት ተቋም የኤርትራ ቅርንጫፍ የአመራር አካላት ዘግበው ባቀዩን በጣም ጠቃሚ የመረጃ ሰነድ አማካኝነት እንደተረዳነው ልዑል ራስ አሥራተ ካሳ የኤርትራ ችግር ስር መስደዱንና በአገር ላይ ከፍተኛ አደጋ የሚያስከትል መሆኑን በመረዳታቸው የክፍለ ሃገሩን አስተዳደር እንደተረከቡ የሥራቸው መጀመሪያ አድርገው ካተኮሩባቸው ጉዳዮችና ካከናወኗቸው ተግባሮች ቅድሚያ የሰጧቸው ዋና ዋናዎቹ ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ በማለት የመረጃው ሰነድ ከዚህ እንደሚከተለው ይዘረዝሯቸዋል።

አቶ እርቂ ዳኘው፣ የንጉሠ ነገሥቱን የክብር ዘበኛ መኮንኖች ባፈራው የጦር አካዳሚ የመጀመሪያው ውድድር ተካፋይና በአወጣጥ አንደኛ የነበሩት፣ በችሎታቸው በአስተዋይነታቸውና በብሩህ ጭንቅላታቸው አፄ ኃይለሥላሴ የወደዷቸው ከመሆናቸው በላይ ታላቅ እምነት ጥለውባቸው ለራሳቸው ህይወት ብቻ ሳይሆን ለሃገር ደህንነት ጭምር ከፍተኛ ኃላፊነትን የሰጧቸው የኰሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ የወንድም ልጅና እንደ አጎታቸው በደህንነት ጥበቃው ሞያ የተካኑና የሰከኑ ሰው እንደነበሩ ይነገርላቸዋል።

ልዑል አሥራተ ካሳ የኤርትራ ክፍለ ሃገር አስተዳዳሪነትን በተረከቡበት ጊዜ ራሱን ጀብሐ ብሎ የሚጠራው ገንጣይ ድርጅት የታወቁ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበርን የአመራር አካላትና አባላት፣ ከሲቪሉም ከመለዮ ለባሹም ወገን አንዳንድ ከፍተኛ የመንግሥቱን ባለሥልጣኖች በቀን ብርሃን አሥመራ ከተማ እየገባ ለመግደል በመቻሉ እጅግ ተብቶ ስለነበር ከዚህ ድርጊቱ ለመግታት ብቻ ሳይሆን በሚሰማው ሁኔታ በጦር ኃይል በብርቱ ለመገሰፅ በአንደኛ ደረጃ የወሰዱት እርምጃ የክፍለ ሃገሩ ህዝብ ተረጋግቶ አስተማማኝ ሠላም እስኪሰፍን ድረስ የአስቸኳይ ጊዜ አስተዳደር አዋጅ ማወጅና ጦሩን ብቻ ሳይሆን የክፍለ ሃገሩን የፖሊስ ኃይል ባጠቃላይ ሁኔታ የመንግሥቱን ሠራዊት በሰው ኃይል መገንባትና የውጊያ ብቃታቸውን ማዳበር ነበር።

ከሃገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ ከሃገር አስተዳደር ሚኒስቴርና ከፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ መምሪያ ከፍተኛ የአመራር አካላት ጋር በመመካከር በሁለተኛ ደረጃ የወሰዱት አስመስጋኝ እርምጃ ከኤርትራ ክፍለ ሃገር የተመለመሉ ክርስቲያን ወጣቶችን በእስራኤላዊያን የጦር መኮንኖች ፀረ-ጎሪላ በሆነ የኮማንዶ ውጊያ እንዲሰለጥኑ በማድረግ ሰባት ሻለቃ የፖሊስ ፈጥኖ ደራሽ ኮማንዶ ጦር ዘመናዊ ትጥቅ አስታጥቀው በኤርትራ አውራጃዎች ሁሉ በማሰማራት ከሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት ጋር በህብረት የጀብሐን ጦር እያሳደዱ እንዲመቱ ማድረግ ነበር።

በተጠቃሹ የመረጃ ዘገባ ሠነድ ላይ የእነ አቶ እርቂ ዳኘው ግምገማ ጀብሐን ለመገሰፅ የተወሰደው እርምጃ አመርቂ ውጤት ያስገኘ መሆኑን ያስረዳና ገለፃውን በመቀጠል ልዑል ራስ አሥራት ካሳ በንጉሡ ተሹመው ኤርትራ እንደመጡ ያስተዋሉት የጀብሐ እንቅስቃሴ ከገመቱትና ከጠበቁት በላይ አድጎ ስለአገኙት ኃይልን ወይንም ወታደራዊ ክንድ ማሳየት አስፈላጊ ሆኖ ቢታያቸውም የኤርትራ ችግር መፍትሄ ፖለቲካዊ እንጂ ወታደራዊ አይደለም ብለው ስለሚያምኑ ያለ ውጊያ ሠላማዊ መፍትሄ አስገኛለሁ የሚል ጠንካራ እምነት ስለነበራቸው ሠላማዊ መፍትሄ ለማግኘት ያለመታከት የሚቻላቸውን ሁሉ ማድረግ ነበር።

«ሁላችንም የአንዲት ኢትዮጵያ ልጆች ሆነን ሳለ ለባዕዳን ጥቅም በባዕዳን ግፊትና ድጋፍ እርስ በርስ እየተዋጋን ደም መፋሰሱንና የጋራ አገራችንን ማፍረስን አቁመን

ለጋራ ደህንነታችን በጋራ በመወያየት መክረን የማናስወግዳቸው ችግሮች ሊኖሩ አይችሉምና ተገናኝተን እንወያይ» በሚል አቀራረብ በተለያዩ ጊዜያቶች በተደጋጋሚ ለጀብሐ መሪዎች የሠላም ጥሪ አደረጉ።

የጀብሐ መሪዎች በተደጋጋሚ ለተደረገላቸው የሠላም ጥሪ ጆሮ ዳባ ልበስ ማለት ብቻ ሳይሆን የሽብርና የጥፋት ተግባራቸውን በላቀ ሁኔታ የሚያደርጉት ጥረት ተስፋ አስቆራጭ ሆነ።

ስለሆነም፣ በጀብሐ ውስጥ ያሉትን ቅራኔዎችና አያሌ ድክመቶች በመጠቀም ድርጅቱን ከፋፍሎ ኃይሉን ማዳከም አማራጭ የሌለው መፍትሄ ሆነ።

«የኤርትራ ክፍለ ሃገር ህዝብ መላውን የእስልምና እምነት ተከታይና አረባዊ ህዝብ ነው» ከማለት በላይ ህዝበ ክርስቲያኑን ማጥቃት ከጀመሩት ከጀብሐ መሪዎች ጋር የከረረ ቅራኔ ውስጥ የገቡና ከክርስቲያኑም ከእስላሙም ወገን የሆኑ ሁለት አንጃ ቡድኖች መፈጠራቸውን በመረዳታችን ይህንን የመረጃ ግኝት ለልዑል አሥራተ ካሳ አቀረብንላቸው ይላል ተጠቃሹ የመረጃ ሰነድ። ልዑልነታቸው ያቀረብንላቸውን የመረጃ ግኝት ለጉዳዩ አግባብ ያላቸውና ጠንካራ ኢትዮጵያዊ ብሔርተኞች ናቸው ከሚባሉ ጥቂት የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር የአመራር አካላት ጋር ከተመካከሩበት በኋላ በቀረበላቸው ሀሳብ መሠረት በጀብሐ ውስጥ ያሉትን ቅራኔዎችና አያሌ ድርጅታዊ ድክመቶቹን በመጠቀም በተፈጠሩ ቅራኔዎች መስመር ከፋፍሎ ድርጅታዊ ኃይሉን ለማዳከም የሚያስችል እቅድና የአፈፃፀም ሥልት ተነደፈ።

በእቅዱም መሠረት የኤርትራ ህዝብ መላውን የእስልምና እምነት ተከታይና አረባዊ ህዝብ ነው ከማለትና በኢትዮጵያ የአረብ ብሔርተኝነትና የአረቦች ግዛትን ለማስፋፋት ሲባል በኤርትራ ክርስቲያናዊ ህዝብ ላይ የጀብሐ ሠራዊት የሚያካሄደውን ጥቃት ለመከላከል በአቶ ኡስማን ሳላህ ሳቤና በአቶ ኢሳያስ አፈወርቅ የሚመሩት አንጃ ቡድኖች ከጀብሐ አፈንግጠው የራሳቸውን ድርጅት ያቋቁሙ ዘንድ ከፍተኛ ቅስቀሳና ግፊት ተደረገ።

በኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር የአመራር አካላትና አባላት በተደረገላቸው ቅስቀሳ የተነሳሱቱና የጀብሐን አመራር አምርረው የጠሉት ቡድኖች በድፍረትና በግልፅነት ለመጀመሪያ ጊዜ፤

«ድርጅታችን የኤርትራን ህዝብ ከኢትዮጵያ መንግሥት ቅኝነት ነፃ ለማውጣት የቆመ ከሆነ፣ በድርጅቱ አባላት መካከል መፈራራት፣ አንዱ ሌላውን በመጠራጠርና በጥላቻ ላይ የተመሠረተ ቅራኔ መፍጠር ሳይሆን በአንድነት በመተማመንና በመተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ኤርትራዊ ብሔርተኝነትን በመፍጠር የኤርትራን ህዝብ በአንድነት ለአንድ ብሔራዊ የፖለቲካ ዓላማ ማንቀሳቀስ መቻል አለብን።

ከጎረቤቶቻችን አረብ መንግሥታት የምናገኘው ድጋፍ ለትግላችን ግብ መምታት ወሳኝነት ስለአለው ያለአግባብ እንዳይበላሽ ከፍ ባለ ጥበብና ጥንቃቄ ጠብቀን በመያዝ ድርጅታችንን የአረብ ብሔርተኛነትና የአረቦችን ግዛት ማስፋፊያ መሣሪያ ሳናደርገው፣ በዓለም ላይ በየአህጉሩና በየሃገሩ ቅኝግዛትን ከሚታገሉ የአርነት ግንባሮችና ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር በማቀራረብ ዓለም አቀፋዊ እውቅናና ድጋፍ በማግኘትና በሠራዊታችን ውስጥ ተራማጅ አስተሳሰብና አመለካከት እንዲሰረፅ ማድረግ አለብን» የሚል ሃሳብ በወል አቀረቡ።

የጀብሐ መሪዎች ለአሥር ዓመታት ያህል ለመላው አረብ መንግሥታት «የኤርትራ ህዝብ አረባዊ ህዝብ ነው። ጀብሐ የሚታገልለት ዓላማ ኤርትራን ከሐበሻ ቅኝነት ነፃ አውጥቶ ከአረቡ ዓለም ጋር ለመቀላቀል ነው ብለው የገቡትን ቃል በመለወጥ ሌላ አቋም መያዙ ጨርሶ የማያዋጣቸው ከመሆኑ በላይ የአረቡ ዓለም የሚሰጣቸው ድጋፍ ቢቆም የጀብሐ ህልውና እንደሚያበቃ የሚያምኑት የጀብሐ መሪዎች ከአረቦች እንድንርቅ የሚያደርገንን ሃሳብ አመንጪዎች፣ ጀብሐን ለማፍረስ የመጡ የሐበሻው መንግሥት ቅጥረኛ ልዑካን ናቸው» በማለትና የተለመደውን በጎሳና በሃይማኖት ልዩነት ላይ የተመሰረተ ጥላቻ በሠራዊቱ ውስጥ በመዝራት ወደ ተንኰልና ወደ የኃይል እርምጃ ስለአመሩ አቶ ኢሳይያስና ተከታዮቹ ክርስቲያን ተዋጊዎች ከጀብሐ አፈንግጠው ተሰወሩ።

እነዚህ ጀብሐን ለማፍረስ ከመንግሥት የተላኩ ቅጥረኞች ሳያመልጡ መመታት አለባቸው በማለት የጀብሐ መሪዎች ጦር ልከው እግር በእግር በመከታተል የሚያሳድዷቸው በመሆኑ የኰብላዩ ቡድን አባላት በኤርትራ ምስራቃዊ ክልል በረሃ ውስጥ ሆነው ከጀብሐ አፈንግጠው የራሳቸውን ድርጅት እንዲያቋቁሙ ከመከሯቸው ከኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አመራር አካላትና ከመንግሥቱ የመረጃ ወኪሎች ጋር ግንኙነት ፈጥረው ያሉበትን አደገኛ ሁኔታ አስረዱ።

ሁኔታው ለልዑል ራስ አስራተ ካሳ ከተነገረና ከአንድነቶች ጋር ከተመከረ በኋላ በቅድሚያ ቡድኑ በጀብሐ ጦር ጥቃት በማይደርስበት ሥፍራ እንዲጠለልና የሚያስፈልጉት አስቸኳይ እርዳታዎች ከተደረጉለት በኋላ አቶ ኡስማን ሳላህ ሳቤ ከሚመራው ሌላው አፈንጋጭ ቡድን ጋር ተቀላቅሎ በመደራጀት ጀብሐን እንዲቋቋምና ብሎም እንዲያዳክም ከማነሳሳት ጀምሮ የመሣሪያና የገንዘብ ድጋፍ በመስጠት ሻዕቢያን ለመገንባት በልዑል ራስ አስራተ ካሳ አመራር መንግሥት ታላቅ ጥረት አድርጓል።

ጀብሐ በአስመራ ከተማ ውስጥ ቃኘው በመባል በሚታወቀው የጦር ሰፈር ነዋሪ የነበሩትን የሰሜን አሜሪካ መንግሥት የጦር ኃይል አባላትን አዘውትሮ የሚተናኰል ፀረ ምዕራብ አክራሪ እስላማዊ ድርጅት መሆኑን በመገንዘብና የልዑል ራስ አስራተ

ካሳን ጥረት በማጠናከር አሜሪካዊያንም ለሻዕቢያ የማይናቅ የትጥቅና የገንዘብ ድጋፍ ሰጥተዋል።

የአቶ ኡስማን ሳላህ ሳቤና የአቶ ኢሳይያስ አፈወርቂ ተከታይ የሆኑት ሁለት ቡድኖች ህብረት ፈጥረው በአቶ ኡስማን መሪነት «ሻዕቢያ» የተባለውን ድርጅት በመመሥረት ጀብሐ በማይቆጣጠረው የክፍለ ሃገሩ ምሥራቃዊ ቆላ ማና ደቡባዊ ደጋማ ክልሎች በተወሰኑና ስትራቴጂካዊ አቀማመጥ ባላቸው ሥፍራዎች ላይ ጦራቸውን አስፍረው ከጀብሐ ጋር ምንም ዓይነት ግጭት ሳይፈጥሩ ድምፃቸውን በማጥፋት ከሁለቱ ክልሎች በአጠቃላይ ከደጋው ክልል በተለይ የሰው ኃይል በገፍ እየመለመሉ ከኢትዮጵያ መንግሥትና ከሰሜን አሜሪካ መንግሥት የውጭ የስለላ ድርጅት «C.I.A» በሚሰጣቸው ገንዘብና ትጥቅ ራሳቸውን በተሻለ ሁኔታ ለማደራጀትና ለማጎልበት የአንድ ዓመት ያህል ጊዜ ጠይቋቸዋል።

የጀብሐ ፀሃፊ የነበረውና ከጀብሐ አፈንግጦ ከአቶ ኢሳይያስ ጋር ህብረት በመፍጠር ሻዕቢያን የመሠረተው አቶ ኡስማን ሳላህ ሳቤ ከሚያውቃቸው አረባዊ የገንዘብ ምንጮች ባስገኘው ድጋፍ ለሻቢያ በአጭር ጊዜ መደራጀትና መጎላበት ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ማድረጉ ይነገርለታል።

ጀብሐም ቢሆን ለመጀመሪያው ዓመት ከመንግሥቱ ጦር ጋር ከመዋጋት በስተቀር ሻቢያን የመተናኰልና የማጥቃት ፍላጎት አላሳየም።

ሻዕቢያም ከጀብሐ ጋር የሚያቋቁመኝ አቅም ወይንም ኃይል አለኝ ብሎ በራሱ ለመተማመን እስከቻለበት ጊዜ ድረስ ቅድሚያውን የሰጠው ጀብሐን በጦር ሜዳ ለመውጋት ሳይሆን ለኤርትራ ክፍለ ሃገር ህዝብ፣ ለተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብና እንዲሁም ለውጪው ዓለም ሕልውናውን ማሳወቅና በጀብሐ ላይ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ማካሄድን ነበር።

የጀብሐን የሐሰት ታሪክ ፈጣሪነት፣ የጎሳና የሃይማኖት ጠባብነትና ፀረ-ክርስቲያንነት በማጋለጥ «በኤርትራ ቆላማው ክልል ነዋሪ የሆነው ህዝብ አረባዊ ህዝብ ነው በማለት ኤርትራን ለአረቦች ለመሸጥ የተቋቋመ ድርጅት ነው ሲለው፤

ጀብሐም በበኩሉ «ሻዕቢያ የኤርትራ ህዝብ ነፃ አውጭ ድርጅት ሳይሆን ጀብሐ የሚያካሂደውን የነፃነት ትግል እንዲያኮላሽ በኢትዮጵያ መንግሥት የተቀጠረ አምባገነን ድርጅት ነው» ወዘተ በማለት ሁለቱም ድርጅቶች በፕሮፖጋንዳው ውጊያ ላይ ብቻ ለተወሰነ ጊዜ አትኩረው ነበር።

ሻዕቢያ በተቋቋመበት በመጀመሪያው አፍላ ጊዜ ከፕሮፖጋንዳው ጦርነትና አልፎ አልፎ በአነስተኛ ኃይል ወይንም የሰው ቁጥር በአንዳንድ ያልተጠበቁ አጋጣሚዎች

ከጀብሐ ጦር ጋር ሲገናኝ ከሚያደርጋቸው ግጭቶች በስተቀር በጥናትና በዕቅድ የተመራ ጠጣር ወይንም ከባድ ውጊያ የተዋጋበት ጊዜ አልነበረም።

ሁለቱ ተፃራሪ ድርጅቶች በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ የሻዕቢያ መሪ አቶ ኡስማን ሳለህ ሳቤ ለእኛ ግልፅ ባልሆነ የጤና መታወክ ምክንያት ሲሞት ሌላው የእስልምና እምነት ተከታይ የሆነው አቶ ረመዳን መሐመድ ኑር የተባለ ግለሰብ ተተክቶ የሻዕቢያ ሁለተኛ መሪ ሆነ።

በአቶ ረመዳን መሐመድ ኑር የአመራር ድክመት ይሁን ወይንም በእስላምነቱ ምክንያት በድርጅቱ ውስጥ ያሉት ብዙሃን ተዋጊዎች የክርስትና እምነት ተከታይ በመሆናቸው አመራሩን በክርስቲያን ግለሰብ ለማስያዝ እንደሆነ ዳግም ለኛ ግልፅ ባልሆነ ምክንያት በሻዕቢያ ውስጥ የሥልጣን ትግል ተከስቶ በተፈጠረው የከረረ ቅራኔ ከክርስቲያኑም ከእስላሙም ወገን በረከት ያሉ ሰዎች ህይወት የግጭቱ ሰለባ ሆነ።

ከዚህ ውስጣዊ ግጭት በኋላ በመሃከላቸው እርቅ ወረደ፣ ሠላምና መረጋጋት የሰፈነ በመሰለበት ጊዜ፣ አቶ ኢሳይያስ አፈወርቂ አሁንም በርካታ የድርጅቱን አባላት ህይወት በጠየቀ መፈንቅለ መንግሥት ዓይነት ድርጊት አቶ ረመዳን መሐመድ ኑርን ከሥልጣን በማስወገድ ሦስተኛው የሻዕቢያ መሪ ሆነ ነው የሚለው የእነ አቶ እርቁ ዳኘው የመረጃ ግኝት ሰነድ።

«ለብዙ ታቦቶች ተስላ የፀነሰቺው ሽል ገደላት ይባላል» ይህንን ያሉት አቡነ ፊሊጶስ ናቸው። በ1967 ዓ.ም መገባደጃ ላይ በነሐሴ ወር የምነግርዎ ከፍ ያለ የአገር ጉዳይ ስለአለኝ እባክዎ ያነጋግሩኝ ብለው ጠየቁኝና የደርጉ ጽሕፈት ቤት በነበረው በታላቁ የምኒልክ ቤተመንግሥት ተቀበልኳቸው። ከዚያ በፊት በስምም ሆነ በመልክ አላውቃቸውም። በጣም የሸመገሉ የዕድሜ ባለፀጋ ቢሆኑም በመንፈስ ብቻ ሳይሆን በአካልም ጠንካራና ቀልጣፋ፣ በጣም ንቁ ሰው ናቸው። ወደኔ ያመጣቸውን ጉዳይ ከመግለጣቸው በፊት ራሳቸውን አስተዋወቁኝ።

በኤርትራ ክፍለ ሃገር በሐማሴን አውራጃ መወለዳቸውን፣ ወላጆቻቸው በኦርቶዶክስ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ኰትኩተው ስለአሳደጓቸው እስከ ጵጵስና እውቀትና ማዕረግ መድረሳቸውን፣ ለአካለ መጠን ከደረሱበት ጊዜ ጀምሮ የኤርትራን ክልል ህዝብ ከፋሽስት ኢጣሊያ ቅኝነት ነፃ ለማውጣት የታገሉ መሆናቸውን፣ እንግሊዞች እንደ ነፃ አውጭ የትግል አጋር መስለው ከመጡ በኋላ ኢጣሊያኖችን ተክተው ሌላ ቅኝ ገዥ በመሆናቸው እነሱንም ከአገራችን ለማስወጣትና የኤርትራን ክፍለ ሃገር ህዝብ መልሰን ከወገኑ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ለመቀላቀል ለሚደረገው የአርነትና የአንድነት ትግል አመራር የሚሰጠንን የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበርን ከአቋቋሙት ጥቂት ኤርትራዊያን አንዱ መሆናቸውን፣ የኤርትራ ክልል ህዝብ ከተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በፌደሬሽን ከተቀላቀለ በኋላ ኢየሩሳሌም ባለው የኢትዮጵያ ገዳም ጳጳስ ሆነው እንዲሰሩ በአፄ ኃይለ ሥላሴ በመታዘዛቸው

ለአያሌ ዓመታት ያገለገሉ መሆናቸውን፣ ከዚያም በኂላ በኤርትራ የተከሰቱትንና የተፈራረቁትን ደስታዎችና እንዲሁም ችግሮች ተካፋይ መሆናቸውንና «ሻዕቢያ» የሚባለው ገንጣይ ድርጅት ስለተቋቋመበት ሁኔታ እስከ አቶ ኢሳይያስ አፈወርቂ ሥልጣን አያያዝ ድረስ በሰፊው አስረዱኝ።

በመጨረሻም የምነግርዎ ከፍ ያለ ጉዳይ አለኝ ያሉትን አንስተው በኤርትራ የአንድነታችንና የሠላማችን ጠንቅ በመሆን የሚታገለንን ድርጅት «ጀብሐን» የፈጠሩና ያዘመቱብን ግብፆች ሲሆኑ ይአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ ብለን መንግሥታችንን በማማከር ለጀብሐ ፀር «ሻዕቢያን» የፈጠርነው እኛ ነን። ሻዕቢያ በሚባለው ድርጅት ውስጥ ከአመራሩ እስከ ምንዝሩ በጠቅላላ የደገኛው ክርስቲያን ህብረተሰብ ልጆች ናቸው።

ዛሬ የሻዕቢያ መሪ የሆነው ኢሳይያስ አፈወርቂ ኤርትራ ይወለድ እንጂ አባቱም እናቱም የትግራይ ተወላጆች ሲሆኑ እሱን ያሳደጉትና ያስተማሩት ደግሞ የወሎ ክፍለ ሃገር እንደራሴ የነበሩትና የታወቁት ኢትዮጵያዊ አጎቱ ደጃዝማች ሰለሞን አብራሐ በደሴ ከተማ ነው።

«ለብዙ ታቦቶች ተስላ የፀነሰችው ሺል ጨንግሮ ገደላት» እንደሚባለው አረቦች ካዘመቱብን ከጀብሐ ይልቅ ለአንድነታችን አስጊ ሆኖ የተገኘው እኛ የፈጠርነው ሻዕቢያ ነው መባሉ በእጅጉ አስገርሞኛል፣ አሳዝኖኛልም።

እነዚህ ልጆች ብዙ ርቀው ሳይሄዱ ከሚያውቋቸው ጥቂት ወንድሞቼ ጋር ሆኜ ወደ ወላጆቻቸው፣ ወደ ሠላምና ወደ አገራቸው ለመመለስ ሙከራ አደርግ ዘንድ የክቡርነትዎን መልካም ፈቃድና እንዲሁም እርዳታ እለምናለሁ አሉኝ።

"ይህንን ማድረግ ይቻላል ብለው ይገምታሉ?" ብላቸው «ሰው ሠራሽ የሆኑ ችግሮች መፍትሄ የሚያገኙትም በሰው ነው ብዬ ስለማምን ነው የእርሶን ፈቃድ የጠየቅሁት ይፍቀዱልኝና ልሞክር» ስለ አሉኝ በሃሳባቸው ተስማምቼ ለተልእኮአቸው መሳካት ያስፈልጋሉ የተባሉትን ሁኔታዎች ሁሉ አመቻችቼና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ የሚገባውን ትዕዛዝና መመሪያ ሰጥቼ ይረዱኛል ብለው ከመረጧቸው ጥቂት ሰዎች ጋር ወደ ኤርትራ ተላኩ።

ከተላኩ በኂላ በጠቅላላ የሚያከናውኗቸውን ተግባሮችና በደህንነታቸውም በኩል የየቀኑን ውሎአቸውን ከመከታተል ሌላ ስለ አቡነ ፊሊጶስ ማንነት የበለጠ ለማወቅ የኤርትራ አርበኛ አዛውንቶችን ጠይቁ እንደተረዳሁት በኤርትራ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የሃገር ፍቅር ማህበር የተመሰረተው አሥመራ ከተማ በሚገኘውና ደብረ ቤዛን በመባል በሚጠራው ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ወይንም ደጀ ሠላም ውስጥ አቡነ ማርቆስ በሚባሉት የገዳሙ የበላይ መሪ ሰብሳቢነት ሲሆን አቡነ ፊሊጶስ ከመስራቾቹ ካህናት አንዱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ችያለሁ።

የኤርትራን ክፍለ ሃገር አውራጃዎች ሁሉ በመጎብኘት ህዝቡን በወል፣ የታወቁ የአገር ሽማግሌዎችንና መንፈሳዊ አባቶችን በግል አነጋገሩ። እሳቸው እንደነገሩኝ የኤርትራ ህዝብ በሙሉ ሠላም ፈላጊና የእሳቸው የሠላም ተልዕኮ ደጋፊ ነው። በክፍለ ሃገሩ ራዲዮና ጋዜጦች ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ስለ አንድነትና ሠላም ተቀባይነትና ተደማጭነት ባለው ይዘትና ወዝ ሰበኩ።

ከአንደበታቸው ከሚፈሰው አባታዊና መንፈሳዊ ቁምነገሮች ላይ ያለ እረፍት ለወራቶች በኤርትራ ደጋና ቆላማ ክልሎች በመዘዋወር ያሳዩት የአካልና የመንፈስ ጥንካሬ ብዙዎቻችንን አስገርሞናል።

በመጨረሻም በኤርትራ ደቡባዊ ምሥራቅ ክልል ውስጥ በምትገኝ አንዲት መንደር ሻዕቢያ የሚባለውን ድርጅት መሪ አቶ ኢሳያስ አፈወርቂን ለማግኘት በመቻላቸው እንደነገሩኝ ደስታቸው ወሰን አልነበረውም።

ከአቶ ኢሳይያስ ጋር ተገናኝተው ደረሰብኝ፣ አወረደብኝ ያሏቸውን ስድቦች ዛሬ ለማስታወስ የማይቻለኝ ከመሆኑ ሌላ ስድቡን መልሶ መድገም አስፈላጊም ስለማይመስለኝ ትቼ፤ እሳቸው ከነገሩኝ አንዱን ብቻ ለአንባቢ እገልፃለሁ «የአማራው ዳዳስ አቡነ ጴጥሮስ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ምድርም ለፋሽስት ኢጣሊያ እንዳይገዙ ገዝቶና አውግዞ ሲሞት አንተ እጅህን ስጥ ልትለኝ መጣህ» በማለት የሐዘን ማቅ ነው ያለበሳቸው።

ከአቶ ኢሳይያስ ስድብ በኋላ ኤርትራ ሳይቆዩ ወዲያው ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው እንደማስታውሰው በጓድ ብርሃኑ ባየህ በኩል ይመስለኛል ሊቀመንበር መንግሥቱ ጊዜ ካላቸው የደከምኩበት ጉዳይ ባለመሳካቱ ባዶዬን ብመለስም በህዝቡ በኩል ያየሁትንና የሰማሁትን ብነግራቸው ጠቃሚ ይመስለኛል ስላሉ ተቀብዬ አነጋገርኳቸው።

“ይሔ............... አንተ ብሎ ....ሰደበኝ በማለት እያለቀሱ ካስረዱኝ በኋላ፣ በተሰጠኝ ዕድል በድጋሚ አመሰግናለሁ የኢትዮጵያ አምላክ ከእርሶ ጋር ሆኖ ብርታቱን ይስጥዎት” ብለውኝ አሰናበትኳቸው።

አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ሻዕቢያ የተባለው ገንጣይ ድርጅት መሪ ከሆነ ከአስራ አንድ ዓመት በኋላ በቀይ ኮኮብ ዘመቻ ጊዜ በሮም ከተማ ለነበረው የኢትዮጵያ መንግሥት ኤምባሲ እጁን በመስጠት ወደ አገሩ ወደ ኢትዮጵያ የተመለሰው፣ ከሻዕቢያ መስራቶች አንዱና የአቶ ኢሳይያስ የቅርብ ጓደኛና የሻዕቢያ ደህንነት ወይንም የመረጃው መምሪያ ሃላፊ ባለሥልጣን የነበረው አቶ ተክላይ ገብረማርያም ሻዕቢያ ከጅብሐ እንዴት እንደተነጠለና የተነጠለበትን ምክንያቶች፣ ስለ አቶ ኡስማን ሳላህ ሳቤና ስለ አቶ ረመዳን መሐመድ ኑር ማንነትና ግለሰባዊ ባህሪያት፣ ስለአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ማንነትና እንዴት የሻያዕቢያ መሪ ለመሆን እንደቻለ፣ ሻዕቢያ ከደገኛው ህዝበ

ክርስቲያን፣ ከኢትዮጵያ መንሥትና ከሰሜን አሜሪካ መንግሥት የውጭ አገር የስለላ ድርጅት (C.I.A) አማካኝነት ያገኝ ስለነበረው የትጥቅ፣ የገንዘብና የተለያዩ ቁሳቁሶች ድጋፍ በራሱ ፈቃድ የሰጠው ሰፊ የጽሑፍ ምስክርነት በአቶ እርቂ ዳኘው ይመራ በነበረው የኢትዮጵያ የአገር ደህንነት የኤርትራ ቅርንጫፍ አመራር አካላት ካቀዩን የመረጃ ዘገባና አቡነ ፊሊጶስ ከሰጡን መረጃዎች ጋር ፍፁም ተመሳሳይ ነው።

በጎሳና በሃይማኖት ጠባብነት ከሁሉም በላይ በኤርትራዊነትና በአረባዊነት ጥያቄ የጀብሐ መከፋፈልና የሻቢያ መፈጠር ሁለቱም ድርጅቶች አንዱ ሌላውን በመወንጀል የሚያካሂዱት የፕሮፖጋንዳ ውጊያ ይዘት በኤርትራ የተፈጠረውን ችግር ለመከታተልና ለማወቅ ንቃቱና ብቃቱ ያላቸውን ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ታላቅ ውዥንብር ውስጥ ከቶ ነበር ማለት ይቻላል።

ብዙዎች ባገኙት የመረጃ ዓይነት ወይንም በመሰላቸው ግምት፤ ሻዕቢያ በኤርትራ ክልል የሚኖረውን ህዝበ ክርስቲያን ከጀብሐ ጥቃት ለመከላከል ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የሚታገል ወዶ ዘማች አርበኛና የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር ወታደራዊ ክንፍ ነው ያሉ፤

ታሪካዊ ጠላቶቻችን ያወጁብንን የእጅ አዙር ጦርነት በአገሩና ወገኑ በሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚያካሂደውን የአረቦች ምንደኛ ድርጅት ጀብሐን ከፋፍሎ ለማዳከምና ብሎም ለማውደም በመንግሥት የተደራጀ ኃይል ነው ያሉ፤

ምሁራንና የወጣቱ ህብረተሰብ ክፍሎች በተለይ ሻዕቢያ የኢትዩጵያ ተማሪዎች አንድነት ማህበር አብዮታዊ ንቅናቄ አባልና አካል የሆኑ ኤርትራዊ ምሁራን የሚመሩት፣ የኢትዮጵያን ፊውዳላዊ ሥርዓተ ማህበር ለመለወጥ የሚታገል አብዮታዊ ድርጅት ነው በማለት የየራሳቸውን ምኞትና አስተያየት የሰጡ ግለሰቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች ብዙ ናቸው።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባል የነበሩ የኤርትራ ክፍለ ሃገር ተወላጅ የሆኑ ወጣት መኮንኖች ብቻ ሳይሆኑ ከከፍተኛ መኮንኖችም መካከል እነ ጀነራል አማን የመሰሉ ሰዎች በቅድመ አብዮት ሲነግሩን የነበረው «ሻዕቢያ» ለኢትዮጵያ ህዝብ ማህበራዊ ለውጥ የሚታገል አብዮታዊ ፋኖ መሆኑን ስለነበር በትግላችን ቅፅ አንድ እንደገለፅኩት በአብዮታችን መቃረቢያና ዋዜማ ሻዕቢያን ሌላው የአብዮት ፋና ወጊ ኃይል አድርገን የተመለከትን ነበርን።

የኢትዮጵያን ህዝብ አብዮት ቋያ የለኮሰው በደቡብ ኢትዮጵያ የአገራችን ድንበር ላይ ይገኝ የነበረው የአራተኛው እግረኛ ብርጌድ ጦር ሲሆን፣ አብዮቱን ያቀጣጠለው ደግሞ በኤርትራ ክፍለ ሃገር ይገኝ የነበረው ሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር ስለነበር የመንግሥቱ ሠራዊትና ሻዕቢያ በኤርትራ የአፄ ኃይለሥላሴን መንግሥት ለመጣል አመፃዊ ግንባር ፈጥረዋል ብለው ያሰቡም ሰዎች ቁጥር ጥቂት አልነበረም።

በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ሻዕቢያን በተመለከተ የብዙ ኢትዮጵያዊያን ግምት ፍፁም የተሳሳተ ነበር። በኋላ በጊዜ ሂደት መረዳት እንደተቻለው የጀብሐና የሻዕቢያ የእውነቱ መሠረታዊ ልዩነት የመደብ፣ የርዕዮተ ዓለም፣ የሃይማኖት፣ የአረብነትና የኤርትራዊነት ወዘተ ሳይሆን የሥልጣን ትግል ነበር።

ከብዙ ዓመታት በኋላ በአብዮቱ ሂደት ከሁለቱም ገንጣይ ድርጅቶች እያፈነገጡ ወደ አገራቸውና ወደ አብዮቱ ከተመለሱ ግለሰቦችና በተለይም ድርጅታዊ በሆነ አቋም ከስህተታቸው ታርመው የአገራቸውን አንድነትና አብዮቱን ደግፈው ከተመለሱት ቡድኖች በግልና በወል እንዳስረዱንና በተጨማሪም ሻዕቢያ አንዴ ባወጣው የአቋም መግለጫ "የኤርትራ ምድር ከአንድ የፖለቲካ ድርጅት በላይ ማስተናገድ አይችልም። ይህ የሆነ እንደሆነ የእርስ በርስ ጦርነት እንጂ ወደ ኤርትራ ነፃነት መሸጋገር አይቻልም" ሲል ለሥልጣን የሚደረገውን ትግል ይፋ አድርጎታል።

ክፍል አሥራ ስምንት

ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ ማህበራዊ አብዮት መፈንዳት፣ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በአገሪቱ ምሥራቅና ደቡባዊ ክልል ጠረፎች ከተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጋር ለውጊያ መፋጠጥ፣ መላዋ ኢትዮጵያ በአብዮታዊ ማዕበል መናወጥ፣ የኤርትራ ገንጣዮች መናጠጥና ረዥሙ የእርስ በርስ ጦርነት የመጧጧፍ ጅምር።

በኤርትራ የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴና የክፍለ ሃገሩ አስተዳዳሪ ልዑል ራስ አሥራተ ካሳ በወሰዱት ጀብሐን በወታደራዊ ኃይል የመገሠፅ እቅድ መሠረት በኤርትራ የሰለጠኑ ሰባት የፖሊስ ኮማንዶ ሻለቆችና በመጠኑም ቢሆን በጎደለው የሰው ኃይል እንዲጠናከር በተደረገው 2ኛው ዋለያ እግረኛ ክፍለ ጦር የህብረት ውጊያ የተመታው ጀብሐ ራሱን መልሶ ለማቋቋምና ከቁስሉ ለማገገም ቢያንስ አንድ ወይንም ሁለት ዓመታት ያስፈልገዋል ተብሎ ተገምቶ ነበር።

በዚህም ምክንያት ከእሱ ተነጥሎ ራሱን ያደራጀውን ሻዕቢያን አሳዶ በእንጭጩ ለማጥፋት ያደረገው ሙከራ ስኬታማ አልነበረም።

በጀብሐ መከፋፈል ወይንም ራሱን ሻዕቢያ ብሎ የሚጠራው ድርጅት ከጀብሐ አፈንግጦ በአንጃነት መደራጀት በአስከተለው የሁለቱም ገንጣይ ድርጅቶች ድክመት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮት መፈንዳት ለእነሱ አገርን የመገንጠል ዓላማ ተግባራዊነት አመቺ ሁኔታን የሚፈጥርላቸው ስለመሰላቸው ይመስላል ውጊያ ቢከፍቱ የመንግሥቱን ወታደር የትኩረት አቅጣጫ በመለወጥ አብዮቱን ያደናቅፋል ብለው በማሰብ ወይንም በሠራዊታችን ላይ ድንገተኛና መጠነ ሰፊ ጥቃት ለመሰንዘር የሚያስችላቸውን ዝግጅት ሲያደርጉ በመሆኑ ብቻ ለእኛ ግልፅ ባልሆነ ምክንያት ከየካቲት 1966 ዓመተ ምህረት ጀምሮ እስከ ጥቅምት 1967 ዓመተ ምህረት ድረስ እርስ በእርሳቸውም ሆነ ከሠራዊታችን ጋር ምንም ዓይነት ግጭት አልፈጠሩም ነበር።

የተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት የጦር ኃይሎች በሁለቱ አገሮቻችን የጋራ ድንበሮች ላይ እየተከማቹ ቢሆንም ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ በዚህ ጊዜ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሊቀመንበር በመሆኑ ውጊያ እንደማይከፍት በማወቃችንና በሰሜን ኢትዮጵያ ገንጣዮችም ከፍ ብዬ በገለፅኩት የጊዜ ክልል ውስጥ የእኛን ትኩረት የሚጠይቅ ችግር ባለመፍጠራቸው ባገኘነው አንፃራዊ የሠላም ጊዜ በእቅድ እየተመራን ያለአንዳች የደም ጠብታና ያለአንዳች የጥይት ድምፅ በተፅግሥትና

በጥበባዊ የትግል ሥልት ዘውዱን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ አውርደን ለመጣል ቻልን።

እንባቢ እንደሚያስታውሰው የጀብሐ ሠራዊት ጥንስስ ያልኳቸው ኢድሪስ አዋቴ በሚባለው ግለሰብ የተመሩ ሽፍቶች በኤርትራ የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ በነበሩት በሌ/ጀነራል አቢይ አበበና ተከታዮቻቸው በነበሩ የክልሉ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ላይ የእጅ ቦምብ ከወረወሩበት ጊዜ ጀምሮ ለአሥር ዓመታት ማለትም፤ ልዑል ራስ አሥራተ ካሳ እንደራሴ እስከሆኑበትና ከዚያም በኋላ እስከ አብዮቱ መቃረቢያና ዋዜማ ድረስ በተሽከርካሪ መንገዶች ላይ ፀረ ተሽከርካሪ ፈንጂዎችን በማጥመድ በሰውና በንብረት ላይ አደጋ ከማድረስና ድልድዩችን ከማፍረስ፣ የክልሉን ነዋሪ ሠላማዊ ህዝብ እንቅስቃሴዎች ከማወክና ከመዝረፍ በተለይም ህዝበ ክርስቲያኑን ከማጥቃት፣ ሠራዊቱና ፀጥታ አስከባሪ ፖሊሶች በተሽከርካሪ ሲንቀሳቀሱ በደፈጣ ውጊያ አደጋ አድርሰው ከመሰወር ያለፈ ቆመው ፊት ለፊት ከወታደሩ ጋር በመጋተር ጠንካራ ውጊያ የተዋጉበት ጊዜ ብዙ አልነበረም።

በርካታ የሰው ኃይልና እንዲሁም ብዙ ሰዓት የጠየቀ ጠንካራ ውጊያ አደረጉ የሚባልበት ጊዜ ቢኖር ወታደሩ እነሱን አሳዶ ለመምታት በሚፈልጋቸው ጊዜ በሚፈጠሩ ግንኙነቶችና ግጭቶች እንጂ ገንጣዮች የማጥቃቱን ቀደምትነት ወስደው ጦሩን፣ ፖሊሱን፣ የጦር ሠፈሮችንና የህዝብ መናኸሪያ ከተሞችን የወረሩበትና ያጠቁበት ጊዜ አልነበረም።

ከአብዮቱ ዋዜማ ከ1966 ዓ.ም መጀመሪያ ጀምሮ እስከ የአፄ ኃይለሥላሴ ፊውዳላዊ የዘውድ መንግሥት መገርሰስ ድረስ በነበረው ከአንድ ዓመት በላይ በኢትዮጵያ የተፈጠረውን ሕዝባዊ ነውጥ ሲያስተውሉና ሲከታተሉ የነበሩት ጎረቤቶቻችን የሱማሌና የሱዳን መንግሥታት ብቻ ሳይሆኑ አብዛኛው አረባዊ መንግሥታት ለኢትዮጵያ ገንጣዮች ከዚህ የተሻለ ጊዜ ስለማይኖር በተፈጠረላቸው አመቺ ሁኔታ ተጠቅመው ኤርትራን ይገነጥሉ ዘንድ በአጣዳፊ የትጥቅና ልዩ ልዩ የቁሳቁስ ድጋፍ በገፍ አቅርበው ባደረጉት ግፊትና ማበረታታት ገንጣዮቹ ወትሮ ከምናውቀው ጨቅላ የደፈጣ ውጊያ ሥልት ወጥተው በአጭር ጊዜ ውስጥ በአደረጉት ከፍተኛ የእድገት እመርታ በሰው ኃይላቸው ብዛት፣ በትጥቃቸው መጠንና ጥራት ከመንግሥቱ ወታደር ጋር መጋተር ብቻ ሳይሆን የማጥቃቱን ቀደምትነትም ወሰዱ።

በዚህ ጊዜ ነበር ጀነራል አማን የሰሜኑን ክልል ጦር ይጎበኛሉ በሚል ሽፋን ከገንጣዮቹ ጋር እርቀ ሠላም የሚያስገኝ የፖለቲካ መፍትሄ ያፈላልጉ ዘንድ ወደ ኤርትራ የላክናቸው።

ጀነራል አማን መንግሥትን ከገንጣዮቹ አመራር ጋር በማገናኘት ለሠላማዊ መፍትሄ ውይይት ይረዳሉ በማለት ከክልሉ ነዋሪዎች መሀከል የመረጧቸው ሰዎች በሙሉ ራሳቸው ገንጣዮች ስለሆኑ በሥልጣን ሽሚያ እርስ በርሳቸው በመዋጋት ላይ

ያሉትን ገንጣይ ድርጅቶች አስታርቀውና አስተባብረው መንግሥታችንን እንዲያስወጉ ካልታቀደ በስተቀር ለኢትዮጵያ አንድነትና ሠላም ይሠራሉ ተብሎ አይታሰብም በማለት የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አመራር አካላትና አባላት በሙሉ የጀነራል አማንን ምርጫ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ለጀነራል አማን የተሰጠውን ተልዕኮ በብርቱ ተቃዉመው ነበር።

የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማሕበር አባላት በእጅጉ የምናከብራቸው፣ የምናደንቃቸውና የምናምናቸው ቢሆንም፤ ጀነራል አማንንም በኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ፍንዳታ ማግሥት ከጡረታ ላይ ጠርተን የአገር መሪነትን ያህል ታላቅ ክብርና ሥልጣን የሰጠናቸው ሰው ናቸው። አንባቢ እንደሚያስታውሰው በአብዮቱ ዋዜማ ጀነራል አማን "የኤርትራ ችግር ለአብዮቱ እንቅፋትና እክል ይሆናል ብላችሁ ሳታስቡ ለኔ ልትተዉት ትችላላችሁ" በማለት ለኔና ለሻለቃ ተፈራ ተክለ አብ ቃል ስለገቡልን እንመናቸውና ማንነታቸውን ከተግባራቸው እንረዳ በማለት በሠላሙ ግኝት ይረዱናል ብለው የመረጧቸው ሰዎች ለሠላሙ ውይይት መጀመር የማይታለፍ ቅድመ ሁኔታ አድርገው ያቀረቡትን የአንድ ወገን የተኩስ አቁም ጥያቄ ተቀበልነው። መቀበል ብቻ ሳይሆን መላው የሰሜኑ ጦራችንና የክልሉ ሠላም አስከባሪ የፖሊስ ሠራዊት ከየጦር ሠፈሩ እንዳይወጣ የሚገድበውን የጀነራል አማን ትዕዛዝም ተስማምተን ተቀበልነው።

በአጭር የጊዜ ሂደት ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አባላት ጥርጣሬና ትንቢት በጣም ትክክል መሆኑን በተጨባጭ ያየነው፣ በኤርትራ ገንጣዮችና በአንድነት ኃይሎች መሀከል የትጥቅ ትግል ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ሁለቱ ገንጣይ ድርጅቶች (ጀብሐና ሻዕቢያ) እርስ በርስ መዋጋታቸውን ትተው የውጊያ ቀጠና ተከፋፍለው በአንድ ጊዜና በሕብረት በሕዳር መጀመሪያ 1967 ዓመተ ምህረት የአሥመራን ከተማ ወረው ለመቆጣጠር ያደረጉት ያልተሳካ ሙከራ ሲያደርጉ ነው።

ወረራው በመንግሥትና በመንግሥቱ ሠራዊት በኩል ፈፅሞ ያልተገመተና ያልተጠበቀ ድንገተኛና አደገኛ ሙከራ ነበር። በዚህም በብዙ መቶ የሚቆጠሩ የሠራዊታችንን አባላት የሕይወት መስዋዕት ከፈሉበት።

ይህንን የመሰለ ክህደትና አደጋ በአገር ላይ ደርሶ ሳለ የሠላም ልዑካን የተባሉትን ሰዎችም ሆነ ጀነራል አማንን እንዴት ታስወርሩናላችሁ ብለን በኃላፊነት ሳንጠይቃቸው የገንጣዮቹን ወረራ ለመመከትና ብሎም በመልሶ ማጥቃት ለመቅጣት ይቻል ዘንድ ከመሐል አገር ተጨማሪ ጦር ወደ ኤርትራ በአጣዳፊ በአየር መጓጓዣ እንዲላክ የተደረገው ጥረት እንዳይሳካ ያውኩን ጀመር። አልፈው ተርፈውም የደርጉን ውሳኔ በመቃወም ጀነራል አማን ጉባኤውን ረግጠው ስለመውጣታቸውና ይህም በአገራችን ላይ ያስከተለው አሳዛኝ ሁኔታ በኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ

ቅፅ አንድ በዝርዝር ስለተገለፀና በአንባቢያን ብቻ ሳይሆን በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚታወቅ ስለሆነ እዚህ በድጋሚ መግለፅ አስፈላጊ አይሆንም።

የኤርትራ ገንጣይ ድርጅቶች በሕብረት የአሥመራን ከተማ ለመውረር በሞከሩበት ጊዜ፣ የኤርትራን ሕዝብ ደህንነትና የክልሉን ሠላም ለማስከበር ከገንጣዮች ጋር ይፋለም የነበረው ሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር በዕዙ ሥር ሦስት እግረኛ ብርጌዶችና ሰባት የክፍለ ሃገሩ ፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ኮማንዶ ሻለቆች ስለነበሩት፤

1ኛ - የስምንተኛውን እግረኛ ብርጌድ መምሪያ አቆርዳት ከተማ ላይ አድርጎ ሦስት እግረኛ ሻለቆችና ሁለት የፖሊስ ፈጥኖ ደራሽ ኮማንዶ ሻለቆችን በምዕራባዊው ቆላማ ክልል ማለትም፤ በባርካና በጋሽና ሰቲት አውራጃዎች በማሰማራት፤

2ኛ- የ12ኛውን እግረኛ ብርጌድ መምሪያውን ከረን ከተማ ላይ በማድረግ ሦስት እግረኛ ሻለቆቹን ከሁለት የፖሊስ ፈጥኖ ደራሽ ኮማንዶ ሻለቆች ጋር በከረንንና በሳሕል አውራጃ አሰማርቶ ገንጣዮች የተፈጠሩባቸውንና ምሽጎቻቸውን ብቻ ሳይሆን የፍልሚያው አውድማ ያደረጓቸውን አውራጃዎች እየተከላከለ፤

3ኛ- ደጋማዎቹን አውራጃዎች፣ ማለትም የሠራዬን፣ የአካለ ጉዛይን፣ የሐማሴንን፣ የምፅዋንም አውራጃ ከነወደቡ ስድስተኛው እግረኛ ብርጌድ መመሪያውን ደንጎሎ ከተማ ላይ አድርጎ በሁለት እግረኛ ሻለቆችና በሁለት ፈጥኖ ደራሽ የፖሊስ ኮማንዶ ሻለቆችን ይዞ አራት አውራጃዎችን ከምፅዋ ወደብና ከባህሩ ጠረፍ ጋር የአሥመራንም ከተማ ሠላምና ፀጥታ እንዲያስከብሩ ነበር የተሠማሩት።

አራት አውራጃዎችን አሥመራን ከሚያክል ከተማ ጋር ከገንጣዩች ጥቃት እንዲከላከሉ የተሠማሩት ሁለት እግረኛ ሻለቆችና ሁለት የፖሊስ ሻለቆች ከተሰጣቸው የጥበቃ ግዳጅ ጋር የማይመጣጠኑ መሆናቸውን ስለአወቁ ነው ለሠላም ተብሎ በመንግሥት ብቻ የታወጀውን የአንድ ወገን የተኩስ አቁም አዋጅና በክልሉ ያሉት የጦር ክፍሎችና የፖሊስ ኃይሎች ከየሠፈራቸው እንዳይንቀሳቀሱ ታዘው መታሰራቸው የፈጠረላቸውን ጥሩ አጋጣሚ ተጠቅመው የጦሩን ሠፈር እያሳበሩ አልፈው ያለ ችግር በመንዝ ነው መላው የወንበዴ መንጋ አሥመራን የወረራት።

ጀነራል አማን የደርጉን ጉባዔ ረግጠው ከወጡ በኋላ በተገኘው አንፃራዊ ሠላምና መረጋጋት ተወይይተን ባሳለፍነው ውሳኔ መሠረት ከአንደኛና ከአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦሮች የተወጣጡ ሁለት እግረኛ ብርጌዶችን በመደመር ሁለት እግረኛ ሻለቆችን በተፋጠነ ሁኔታ በዚያው ዕለት በአየር አንጉዘን አሥመራ ከተማ ስለ አደረስንላቸው የአሥመራ ከተማና የአካባቢው የጦር ክፍሎች ከመሐል አገር በተላከላቸው ተጨማሪ ጦር ተጠናክረው በአየር ኃይላችን እየተረዱ ባደረጉት መልሶ ማጥቃት ገንጣዮቹን አዳሽቀው ነው ወደ መጡበት የመለሷቸው።

ምዕራፍ ሰላሣ

ደርግና ብ/ጀነራል ጌታቸው ናደው

በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ዋዜማ በተለይም የአብዮቱ ፋና ወጊ የምንለው አራተኛ እግረኛ ብርጌድ ጦር አምፆ የምድር ጦር ሠራዊት አዛዥ የነበሩትን ጀነራል ድረሴ ዱባለን ከጥቂት ረዳቶቻቸው ከፍተኛ መኰንኖች ጋር ለጉብኝት ነገሌ ቦረና ሄደው ከአሰራቸው በኋላ የተቀሩትም የአገሪቱ የተለያዩ የጦር ክፍሎች የአራተኛውን ብርጌድ ፈለግ በመከተል አዛገሮቻቸው የሆኑ ከፍተኛ መኰንኖችን ማሰራቸው ይታወሳል።

ከአብዮቱ ዋዜማ ጀምሮ እስከ አብዮቱ አጥቢያ ማለትም አብዮታዊው ደርግ እስከ ተቋቋመበት ጊዜ ድረስ አገሪቱ አመራር አልባ እንደነበረች ሁሉ የአገሪቱ መከላከያ ሠራዊትም በየጦሩ ክፍሎች ያሉትን አዛዥ መኰንኖች በተለይም ጀነራል መኰንኖችን በቁጥጥሩ ሥር ከማዋሉ ሌላ ከፊሎቹን ከሥራቸው በማባረሩና የተቀሩትንም በጡረታ ከሠራዊቱ በማግለሉ ከመከላከያ ሚኒስቴር ጀምሮ አብዛኛው የጦር ክፍሎች አዛዥ ወይንም አመራር አልባ ሆነው ነበር።

ልጅ እንዳልካቸው መኰንን በንጉሡ ትዕዛዝ አቶ አክሊሉ ሀብተ ወልድን ተክተው ጠቅላይ ሚኒስትር ከሆኑ በኋላ ባወጡት የፖለቲካ ፕሮግራም ያለ አግባብ የበለፀጉት፣ በሥልጣናቸው የባለጉትና ሕዝቡን የበደሉ ባለሥልጣኖችን ወንጀል የሚመረምር መርማሪ ኰሚሽን ተቋቁሞ በሚያደርገው ምርመራ ወንጀለኝነታቸው የተረጋገጠ ባለሥልጣኖች ለፍርድ ይቀርባሉ ብለው ከአስታወቁ በኋላ ሠራዊቱ አብዛኛውን አውራ የአገሪቱን መሳፍንት፣ መኳንንትና ጉልተኞችን ከየቤታቸው እየለቀመ በቁጥጥር ሥር በአዋላቸው ጊዜ በመከላከያ ሠራዊቱም ውስጥ ከገዢው መደብ አካላትና አባላት ጋር በደም፣ በጋብቻና በጥቅም የተሳሰሩ ናቸው፣ አንዳንዶቹ የመሬት ከበርቴም ናቸው፣ በሙስና የተበከሉ ናቸው ወዘተ የተባሉትን መኰንኖች በማሰርና በጡረታ በማግለል የአገሪቱን መከላከያ ተቋም በሙሉ አፀዳው።

በአንባቢ ዘንድ እንደሚታወሰው አገሪቱ በውጭ ተስፋፊዎች በተከበበችበትና የአገር ተወላጅ በሆኑ ገንጣዮች እየተቦረቦረች ባለችበት ጊዜ የረጅም ጊዜ ሥራ ልምድና ወታደራዊ ተመክሮ ያላቸውን ከፍተኛ የጦር መኰንኖች በሙሉ ማጣት ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ለሠራዊቱ በማስረዳት ከፍተኛ ወታደራዊ እውቀት ያላቸውን በአገር ወዳድነታቸው፣ በመልካም ምግባራቸውና ከሙስና የፀዱ በመሆናቸው የምናውቃቸውን በጣም ጥቂት ጀነራል መኰንኖችን ለማትረፍ ታግለን ካቆየናቸው መሐከል አንዱ ብ/ጀነራል ጌታቸው ናደው ነበሩ።

በኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ አንድ እንደገለፅኩት ከቀደምቶቹና ከነባሮቹ የአገሪቱ ጀነራል መኰንኖች መሀከል ጀነራል አማንን ጠርተን የጦር ኃይሎች

ኤታማዦር ሹም እንዲሆኑ ማድረግ የቻልነው እንዲሁ ፀረ-ጀነራል ከሆነው ሠራዊት ጋር ታግለን ነው።

በጣም የሚያስገርመው ነገር ጀነራል አማን የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታ ማጆር ሹም ከሆኑ በኋላ የመከላከያም ሚኒስትርነቱንና የምድር ጦር ሠራዊት አዛዥነቱንም ጠቅልዪ ካልያዝኩ በማለት ከማስቸገራቸው በላይ ከኔ ሌላ ጀነራል መኖር የለበትም፣ አንድም ሌላ ጀነራል ማየት አልፈልግም በማለት ሌላ ፀረ - ጀነራል መሆናቸው ነው።

ይህንን የመሰለው ሥልጣንን የማሰባሰብ ፍላጎት በኛ በኩል ለሥልጣን መስገብገብ ብቻ ሳይሆን ምናልባት ከእኛ የሰወሩትና ከእኛ ዓላማ የተለየ ሌላ የፖለቲካ ዓላማ ሊኖራቸው ይችላል በማለት እሳቸውን ሳናማክር ያሉንን በእጅ ጣት የሚቆጠሩ ጀነራል መኰንኖች በሚመጥኑበት የሥራ መስኮች ባሰማራንበት ጊዜ ጀነራል ግዛው በላይነህን የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም፣ ጀነራል ጌታቸው ናደውን የምድር ጦር ሠራዊት አዛዥ አድርገን በመሾማችን ከጀነራል አማን ጋር ግጭት ለመጀመሩ ምክንያት ሆኗል። ይህን ከገለፅኩ በኋላ ወደ አርእስቴ «ጀነራል ጌታቸው ናደውና ደርግ» ወደ ተባለው ታሪክ ከማምራቴ በፊት ስለ ግለሰቡ ማንነት በጥቂቱ ለማስረዳት እወዳለሁ።

ከዚህ በኋላ የምገልፅው ብ/ጀነራል ጌታቸው ናደው በአብዮታችን አፍላ ወቅት የፈጠሩት ፀረ-አብዮት ቀውስ በዚህ ጊዜ አገሪቱ ከነበራት አንድ ሻለቃ አየር ወለድ ጦር ጋር የተያያዘ በመሆኑ ለግንዛቤ ይበጅ ዘንድ የአየር ወለድ ሻለቃችንን ታሪክ በአጭሩ ከአንባቢ ጋር ማስተዋወቅ ያስፈልጋል።

ጀነራል ጌታቸው በፈጠሩት ቀውስ የተነሳ የአየር ወለድ ሻለቃችንን ለአንባቢ ማስተዋወቅ ካስፈለገ ደግሞ፣ በዓለም ወይንም በብዙ አገሮች አየር ወለድ በመባል የሚታወቀው ጦር በታሪክ መቼና ለምን ዓይነት ወታደራዊ ተግባርና ዓላማ እንደተፈጠረና የሚሰጠውን ወታደራዊ አገልግሎት በጥቂቱ ወታደር ላልሆኑ አንባቢዎች ማሳወቅ እወዳለሁ።

አየር ወለድ ጦር በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግሥት በጀርመን አገር በጀርመኖች የመከላከያ ሠራዊት ውስጥ የተፈጠረ፣ በአገራችን በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም አዲስ ዓይነት ዘመናዊ ጦር ነው።

አዲስና ዘመናዊ የሚያሰኘው፣ የተፈጠረበት ጊዜ ቅርብ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ ካሉት እግረኛ ጦሮች ወታደራዊ ሥልጠና የላቀ ተጨማሪ ኰማንዶ በመባል በታወቀው ልዩ ወታደራዊ ሞያ ሥልጠና ያለውና ከአየር ወደ ምድር በጃንጥላ በድንገት በመውረድ ጠላቱን ለመውጋት የተዘጋጀና የተደራጀ አጥቂ ጦር በመሆኑ ነው።

ኰማንዶ የተባለውን በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተሰየመ ስም ለጊዜው ተስማሚ የአማርኛ ትርጉም ስለአላገኘሁለት ብቻ ሳይሆን መላው ዓለም ማለት ይቻላል በዚሁ ስም የሚጠቀም በመሆኑ እኔም ይህንኑ ስም ተጠቅሜያለሁ።

ከተግባር አኳያ ኰማንዶ ማለት፤ በከፍተኛ የአካል ማጠንከሪያ ትምህርትና ባላሰለሰ ልምምድ አካሉ የጠነከረና የተገነባ፣ ማናቸውንም አስቸጋሪ የሆኑ የመሬት ገፅታዎችና የተፈጥሮ መሰናክሎችን የማለፍ፣ ፈጥኖ የመራመድ፣ አስፈላጊ ሲሆን የመሮጥ፣ በመሣሪያ ብቻ ሳይሆን ያለ መሣሪያም በእጁ የመዋጋት ብቃትና ችሎታ ያለው ጦር ማለት ነው።

አየር ወለድን ጦር አዲስና ዘመናዊ የሚያሰኘው ሌላውና ምናልባትም ዋናው ምክንያት በእግርና በየብስ ተሽከርካሪ በመጓዝ የሚባክነውን ረጅም ጊዜ በማሳጠር ከአይሮፕላን በማናቸውም ወቅት ማለትም በሌሊትም ሆነ በቀን በአንድ ወታደራዊ ግብ ወይንም በጠላት ይዞታ በሆነ ወረዳ ላይ ወርዶ የሚያጠቃ ጦር መሆኑ ነው።

የዚህን አዲስና ዘመናዊ ጦር ጠቀሜታ ለማስገንዘብ አንድ የአየር ወለድ ጦር ታሪክና አስደናቂ የውጊያ ገድል ለአንባቢ ማቅረብ እወዳለሁ።

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲጀመር ጀርመኖች ኦስትሪያንና ፖላንድን ከወረሩ በኋላ ሦስተኛዋ ዒላማቸው ፈረንሳይ እንደነበረች በመታወቁ ፈረንሳዮች የመከላከል ዝግጅት ማድረግ የጀመሩት ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት በዋዜማው ነበር።

ጀርመኖች በመጠነ ሰፊ ሜካናይዝድ በምድር የሚያደርጉትን ማጥቃት ተከላክሎ ለመመለስ ያስችለናል ብለው ያመኑበትን የማጂኖ ምሽግ በመባል የሚታወቅ ምሽግ በፈረንሳይና በጀርመኖች የጋራ ድንበር ላይ እጅግ ረጅምና ታላቅ በብረት ገንብተው በምሽጋቸው ውስጥ መሣሪያቸውን ደግነው የጀርመንን ወራሪ ሠራዊት ይጠባበቁ ነበር።

ረዥም ጊዜ፣ አያሌ የሰው ጉልበትና ከፍ ያለ ገንዘብ ወጥቶበት በብረትና በሲሚንቶ የተገነባው ምሽግ ከእርዝማኔውና ከይዞቱ ታላቅነት ባሻገር በውስጡ የቀለብ ማከማቻ፣ የሞቀ ምግብ ማዘጋጃና በቧንቧ የሚፈስ ንፁህ ውሃ ማደያ፣ መላውን ሠራዊት የሚያገናኝ የመገናኛ ድርና የሕክምና አገልግሎትን ወዘተ የመሳሰሉ አገልግሎቶች ያሉት በዚያን ጊዜ ብቻ ሳይሆን እስከ ዛሬም በዓለም ወታደራዊ ታሪክ የትም ያልተሰራ ምሽግ ነበር።

ጀርመኖች የማጂኖን ምሽግ ጥሰው በማለፍ ፈረንሳይን ለመውረር ፍፁም እንደማይቻላቸው ስለተገነዘቡ የዘየዱት ታሪካዊ ዘዴ ከዚያ በፊት በዓለም የማይታወቀውንና ያልታየውን አየርወለድ ሠራዊታቸውን በጃንጥላ ከማጂኖ ምሽግ በስተጀርባ ፈረንሳይ ርዕሰ ከተማ ፓሪስ ላይ ማውረድ ነበር።

በዚህ ባልታወቀና ባልተጠበቀ ሁኔታ በድንገተኛ ጥቃት አገሩ የተወረረችበት የፈረንሳይ የጦር ኃይል አንዲት ጥይት ሳይተኩስ ፈርሶ ተበታተነ።

በራሪ ነብር በመባል የሚጠራው የኢትዮጵያ አየር ወለድ ጦር በ1952 ዓመተ ምህረት በሸዋ ክፍለ ሃገር በደብረ ዘይት ከተማ በአየር ኃይላችን ሠራዊት መኖሪያ ሠፈር አቅራቢያ ተመሰረተ።

በደብረ ዘይት ከተማ ከአየር ኃይል ሠራዊት ጋር የተጎራበተበት ምክንያት ለውጊያ ግዳጅ የሚንጓዘው በአየር መጓጓዣ ስለሆነና ከአየር ኃይል ጋር እጅና ጓንት በመሆን በምስጢርና በፍጥነት ቀልጣፋ ንቅናቄ ለማድረግ እንዲያስችለው ነው። የአየር ወለድ ሻለቃችን መሥራችና የመጀመሪያው አዛዥ፣ ሻለቃ መኰንን ሙላት ይባላሉ።

በአገር ፍቅርና ብሄራዊ ስሜታቸው፣ ለሚለብሱት ወታደራዊ መለዮ ባላቸው ፍቅር፣ በወታደራዊ ሞያ ብቃታቸውና ሞራላቸው የታወቁ ምሥጉን የጦር መኰንን ነበሩ።

የአየር ወለድ ሻለቃ መሥራች የሆኑትን ምርጥ ወጣት መኰንኖች፣ የበታች ሹማምንቶችንና እንዲሁም በተርታ ውትድርና የአየር ወለድ ጦር አባል የሚያደርገውን መሥፈርት ያሟሉ ወጣቶችን ከየጦር ክፍሉና ከየትምህርት ት/ቤቱ ከመመልመል ጀምሮ ተገቢውን ሥልጠና በመስጠት በጥብቅ ወታደራዊ ሥነ ምግባርና ሥነሥርዓት ገንብተው፣ የሻለቃውን ጦር መለያ የክንድ ምልክት የተቆጣ ነብር ምስል በማድረግ የሻለቃውን ጦር "በራሪ ነብሮች" የሚል ስም የሰጡ አዛዥ፣ በሥራቸው ባህሪ ምክንያት ከደብረዘይት ከተማ ወደ አዲስ አበባ አዘውትረው እየነዱ ሲመላለሱ ነው በመኪና አደጋ ያረፉት።

ሻለቃ መኰንን ሙላትን ተክተው ሁለተኛው የአየር ወለድ ሻለቃ አዛዥ የሆኑት መኰንን በወታደራዊ ችሎታቸውና በጠቅላላ ባህሪያቸው ከሞላ ጎደል ሻለቃ መኰንን ሙላትን የሚመስሉት ሻለቃ ጌታቸው ናደው ይባላሉ።

ሁለቱም መኮንኖች በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ በገነት ጦር ትምህርት ቤት የ19ኛው ጊዜ ውድድር እጩ መኰንን ሆኜ ከተቀሩት የኰርስ ጓደኞቼ ጋር ያስተማሩን መምህሮቻችን ስለነበሩ ደህና አድርጌ አውቃቸዋለሁ።

ሻለቃ ጌታቸው ናደው የአየር ወለድ ሻለቃን ከአስር ዓመታት በላይ በአዛዥነት ከመምራት ሌላ በኤርትራ ልዑል ራስ አሥራተ ካሣ የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴና የክፍለ ሃገሩ አስተዳዳሪ በነበሩበትና ገንጣዮቹ እጅግ ናጠው አሥመራ ከተማ እየገቡ በቀን ብርሃን የሁለተኛው ዋለ.ያ እግረኛ ክፍለ ጦር አዛዥና ኢታማዦሩ ሳይቀሯቸው ከፍተኛ መኰንኖችንና የሲቪል ባለሥልጣኖችን መግደል በጀመሩበት ጊዜ አየር

ወለዱን ሻለቃ በውጊያ መርተው በአስገኙት ውጤት መልካም ስም ከማትረፍ ባሻገር የማዕረግ ዕድገትም አግኝተውበታል።

እንደ ኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር በአስራ ዘጠኝ መቶስ ልሳኛው ዓ.ም መጀመሪያ ገደማ በሶቪየት ህብረት መንግሥት የመከላከያ ተራድኦ የሚረዳው ጎረቤታችን የሱማሌ መንግሥት በመገንባት ላይ ባለው እጅግ ዘመናዊ የጦር ኃይል ውስጥ አራት የታንክ ብርጌዶችንና አራት ሜካናይዝድ ክፍለ ጦሮችን ማደራጀቱ በመታወቁ መንግሥታችን ባደረበት ሥጋት ተመሳሳይ ጦር ለማቋቋም በነበረው እቅድ መሰረት በአገራችን ወታደራዊ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የመጀመሪያውን ሜካናይዝድ ብርጌድ በአንበሳው ሶስተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ዕዝ ሥር ጅጂጋ ከተማ ላይ ሲያቋቁም ብርጌዱን ለማቋቋምና ብሎም ለመምራት ሞያውና ብቃቱ ያላቸው መኮንኖች ከተለያዩ የጦር ክፍሎች እየተመረጡ ሲሰባሰቡ፣ ኰሎኔል ጌታቸው ናደው ከአየር ወለድ ሻለቃ አዛዥነታቸው ተነስተው የአዲሱ ሜካናይዝድ ብርጌድ አዛዥ ሆኑ።

ሞያውና ብቃቱ አላቸው ተብሎ ከተሰባሰቡት መኰንኖች እኔም አንዱ ከመሆኔ ሌላ ከብርጌዱ መምሪያ መኰንኖችም አንዱ በመሆኔ በገነት ጦር ትምህርት ቤት ሻምበል ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ በኰሎኔልነት ማዕረግ የሜካናይዝዱ ብርጌድ አዛዥ በሆኑ ጊዜ በሻምበልነት ማዕረግ የቅርብ ረዳታቸው በመሆን አውቃቸዋለሁ።

አለባበስ የሚያውቁ፣ ቀንንና ኩሩ፣ በጣም አጭር የማይባል አማካኝ ቁመት፣ ከላይ እስከ ታች የተደላደለና የተገነባ ሰውነት፣ ገብስማ ፀጉርና ግርማ ሞገስ ያላቸው መኰንን ናቸው።

ለማህበራዊ ለውጥ የሚታገሉ አብዮተኛ ባይሆኑም ፊውዳላዊዉን መንግሥት የሚደግፉና በሥርዓቱም ተጠቃሚ የሆኑ አድሃሪ አልነበሩም።

ከጊዜው አንፃርና የማዕረግ አቻቸው ከሆኑ መኰንኖች ጋር ሲመዘኑ ጥሩ ጠቅላላ ዕውቀትና የፖለቲካ ንቃት ያላቸው ነበሩ።

አንደበተ ፍቱህና የመናገር ችሎታ ያላቸው፣ ሳያመነቱና ሳይፈሩ የሚወስኑ፣ ፈጣን፣ ደፋር፣ አንድ ጥሩ የጦር መኰንን ሊኖረው የሚገባው የማጥቃት ባህሬ ያላቸውና በአጠቃላይ ጥሩ ወታደርና ጥሩ አዛዥ ወይንም ጥሩ የመስክ ወይንም የጦር ሜዳ መሪ ናቸው።

ያቋቋምነውና እንደ ልጃችን የምንወደው ሜካናይዝ ብርጌድ አገሪቱ የምትጠብቅበትን ተግባር አሟልቶ የያዘ ስመጥርና አጥቂ ጦር ይሆን ዘንድ በማደራጀቱና በመገንባቱ ረገድ የኔን ሞያና አስተዋፅኦ በሚመለከት ሌት ተቀን እንደምሰራና ከልቤ የምጥር ብቻ ሳይሆን የቅርብ ረዳታቸውና አማካሪያቸውም ስለነበርኩ በመሀከላችን መግባባትና መተሳሰብ ተፈጠረ።

ጠቅላላ ባህሪያቸውንና ወታደራዊ አመራራቸውን ስወድ፣ የማልወድላቸው ነገር ቢኖር ጀብደኝነታቸውንና ጉረኝነታቸውን ብቻ ነበር።

አየር ወለዱን ሻለቃ ከገንጣዮች ጋር እያዋጉ በኤርትራ በቆዩበት ጊዜ ከአንዱ አውራጃ ወደ ሌላው አዘውትረው በመዘዋወር መልክአ ምድሩን፣ የሕዝቡን ባህሪና ባሕል አጥንተዋል።

ስለ ኤርትራ ሁኔታ ያስተዋሉትንና የታዘቡትን እንደነገሩኝ፣ መንግሥት ለኤርትራ ችግር ተገቢውን ትኩረት አልሰጠም፣ ከገንጣዮቹ ጋር የሚታገለው ጦር በትክክል እየተመራ አይደለም። በፖለቲካውም ረገድ ያለው ሁኔታ ከወታደራዊው ሁኔታ ቢብስ እንጂ አይሻልም። የኤርትራ ችግር ከእኛ ቁጥጥር ውጭ ሆኖ የአረቦች መጫዎቻ ኳስ ሆኗል የሚሉ ነበሩ።

የአዲሱ ሜካናይዝድ ብርጌድ መሥራችና የመጀመሪያው አዛዥ ሆነው ሳለ ከአስር ዓመት በላይ ለመሩት ለአየር ወለዱ ሻለቃ ያላቸው ፍቅር አልተለወጠም።

የአየር ወለዱን ጦር ቀይ መለዮ ካለማውለቃቸው ሌላ ጂጂጋ ተቀምጠው ደብረዘይት ያለውን የአየር ወለድ ሻለቃ ጦር ሁኔታ በጥብቅ ከመከታተል ባሻገር በእጅ አዙር ይመሩት ነበር ማለት ያስደፍራል።

የሻለቃው አዛዥ በነበሩ ጊዜ የመምሪያ መኮንኖቻቸው ከነበሩት ጋር በተለይ፣ ከጠቅላላው የሻለቃው መኮንኖች ጋር ብቻ ሳይሆን ከበታች ሹማምንቱ ጭምር በአጠቃላይ የጠበቀ ግንኙነት ነበራቸው።

ሜካናይዝድ ብርጌዱ በተቋቋመ በሁለተኛው ዓመት በአብዮታችን መቃረቢያ እኔ በሻለቅነት ወደ ቀድሞው ክፍሌ ወደ ሐረር ስመለስ እሳቸውም በብ/ጀነራልነት ማዕረግ ለብዙ ጊዜ አገልግሎት የሰጡበት የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጦር ትምህርት ቤት አዛዥ ሆኑ።

በገነት የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የጦር ትምህርት ቤት አዛዥ ከሆኑም በኋላ የአየር ወለድን መለዮ ካለማውለቃቸው ሌላ ከአየር ወለድ መኮንኖችና የበታች ሹማምንቶች ጋር ያላቸውን ግንኙነት አላቋረጡም።

በአብዮቱ ፍንዳታ አጥቢያ እነ ሻለቃ አጥናፉ አባተ በአዲስ አበባ አካባቢና በውስጧ ላሉ ልዩ ልዩ ተቋሞች ጥበቃ በአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ሥር ያሉ እግረኛ ጦሮችን ሲያንቀሳቅሱ ኃይል በማጠሩ የአየር ወለድንም ሻለቃ ጦር ከደብረ ዘይት ጠርተው ነበር።

በአብዮቱ ማግሥት ሁሉም ነገር በጦሩ ቁጥጥር ስር ከዋለና አንጻራዊ መረጋጋት ከተፈጠረ በኋላ ለጥበቃ የወጣው ጦር በከፊል ወደ ጦር ሠፈሩ ሲመለስ፣ ከአየር

ወለድ ሻለቃ አንድ ሻምበል ጦር ብቻ ከአራተኛ ክፍለ ጦር አባላት ጋር በክፍለ ጦሩ ግቢ ውስጥ ለደርጉ ጥበቃ እንዲውል ተደርጎ ነበር።

ወደ ኋላ በጊዜ ሂደት እንደተረዳነው፣ ጀነራል ጌታቸው ለደርጉ ጥበቃ ከተመደቡት የአየር ወለድ ጦሮች ጋር በፈጠሩት የመገናኛ ድር የአራተኛ ክፍለ ጦርን ግቢና የደርጉን የዕለት ተዕለት ሁኔታ ይከታተሉ ነበር።

በሐምሌ ወር ይመስለኛል አሁን ስሙን የማላስታውሰው ለደርጉ ጥበቃ የተመደበው የአየር ወለድ ሻምበል ጦር አዛዥ የነበረው መኰንን እኔ ዘንድ ቀርቦ፤ «ጀነራል ጌታቸው ናደው አዲስ አበባ መኰንኖች ክበብ አስጠርተውኝ የምነግርህ ብርቱ ጉዳይ አለኝና እባክህ አነጋግረኝ ብለህ ለሻለቃ መንግሥቱ ንገርልኝ በማለት ልከውኛል» ስለአለኝ የሚፈልጉኝ አስቸኳይና ብርቱ ጉዳይ ስለመሰለኝ አሁን ክበብ ያሉ ከሆነ ጥራቸውና አነጋግራቸዋለሁ አልኩና ደርጉ ጽሕፈት ቤት መጥተው ተገናኘን።

የደርጉ ሊቀመንበር ሆኜ በመመረጤ የተሰማቸውን ደስታና በአብዮታዊ አመራሬ እሳቸው ብቻ ሳይሆኑ ሕዝቡና መላው ሠራዊት እንደተደነቁ ከገለፁልኝ በኋላ በገነት ጦር ትምህርት ቤት የዕዝና የመመሪያ መኰንን ትምህርት በመማር ላይ ያሉትን ተማሪ መኰንኖች ይገፍ ለጥናት ወደ ጎጃምና ጐንደር ክፍለ ሃገራት ስለምሄድ እግረ መንገዴን ስለ አብዮቱና በተለይም ስለ ኢትዮጵያ ትቅደም ዓላማ ህዝቡን እንዳስረዳ በአንተ በኩል ለህዝቡ እንድናገር የምትፈልገውን ነገር ዘርዘር አድርገህ እንድታስረዳኝ ነው ላገኝህ የፈለኩት አሉኝ።

እንደዚያ ያለ ነገር በማሰባቸው አመስግኜ አሁን የደርጉን ስብሰባ እየመራሁ ስለሆነ አይመቸኝምና በጠየቁኝ ጉዳይና በሌላም ሰፋ ባለ ሁኔታ እንድንወያይ እሁድ ጠዋት በአራት ሰዓት ገደማ እንገናኝ በማለት አሰናበትኳቸው።

በቀጠሮአችን መሰረት እሁድ ጠዋት በደርጉ ጽሕፈት ቤቴ ተገናኝተን ዘና ባለ ሁኔታ ለሦስት ሰዓት ያህል ከመወያየታችን በላይ ለሚያደርጓቸው ንግግሮች የተለያዩ አርዕስቶችና ማስታወሻ የሚሆናቸውን ዝርዝር በጽሁፍ አዘጋጅቼ ስለነበር ይዘው ሄዱ።

እኔን ሳይጠይቁኝ ወይንም ሳይነግሩኝ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ሄደው ደርግ ለጎጃምና ለጐንደር ህዝብ የአብዮቱን ዓላማ እንዳስረዳ ተልዕኮ የሰጠኝ ስለሆነ አንድ ጋዜጠኛ ቡድን ያስፈልገኛል በማለት አስፈቅደው ጀነራል ጌታቸው ናደው ለዚህ አውራጃ ለዚህ ወረዳ ለዚህ ከተማ ወዘተ ሕዝብ ስለ ኢትዮጵያ ትቅደም ዓላማ ገለፃ አደረጉ እየተባለ የሚሠራጨውን ዜና የሰሙና የተመለከቱ የደርግ አባላት "የመጀመሪያው የለውጥ ሐዋሪያ ጀነራል" የሚል ስም ሰጧቸው።

በዚያው ሰሞን በነሐሴ ወር ይመስለኛል ከጀነራል አማንና ፀረ-ጀነራል ከሆነው ሠራዊታችን ጋር ታግለን አተረፍናቸው ያልኳቸውን ጀነራል መኮንኖች እንደ ችሎታቸውና ዝንባሌያቸው እንደ ማዕረግ ቅደም ተከተላቸው በተለያየ ኃላፊነት ላይ ስናስቀምጥ ጀነራል ጌታቸው ናደው በደርግ ጠቅላላ ስብሰባ ከፍተኛ ድምፅ አግኝተው የምድር ጦር ሠራዊት አዛዥ ሆኑ።

የምድር ጦር ሠራዊት አዛዥ መሆናቸው ከአየር ወለድ ሻለቃ ጦር ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ያጠናከረላቸው ብቻ ሳይሆን የደርጉም ደህንነት ጥበቃ የኔ ኃላፊነት ነው በማለት የደርጉን ጥበቃ ብርጌድ ውስጣዊ ሁኔታ በዝርዝር ለማወቅና ጣልቃ ለመግባት ስለሚያደርጉት ሙከራና ይህንንም ሲያደርጉ ከኛ ከጥበቃ ብርጌዱ አዛገሮች ጋር መገናኘትና መነጋገር ሲገባቸው በብርጌዱ ጥበቃ ላይ ካለው የአየር ወለድ ሻምበል መኮንኖች አማካኝነት ማድረጋቸውን አልወደድነውም በማለት የብርጌዱ አዛዥ የነበሩት ኰሎኔል መርዕድ ንጉሴና የዘመቻው መኮንን ሌ/ኰሎኔል ዳንኤል አስፋው አመልክተውኝ ለደርጉ ደህንነት በማሰብ የሚያደርጉት ነው ብዬ ባስብም የአየር ወለዱ መኮንኖች ተግባር ሥነ ስርዓት የጎደለው ስለሆነ የሻምበሉን ጦር በሙሉ ወደ እናት ክፍሉ መመለስ ነበረብን።

በዚህ ሁኔታ እያለን ጀነራል አማን በፈጠሩት ቀውስ ምክንያት ከደርግ አመራር ሲወርዱ እንደሚታወቀው በሰሜን የኤርትራ ክፍለ ሃገር የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አስተዳዳሪና የጦሩ የበላይ አዛዥ የነበሩት ብ/ጀነራል ተፈሪ ባንቲን የደርጉ ሊቀ መንበር ስናደርግ ብ/ጀነራል ጌታቸውን ከምድር ጦር ሠራዊት አዛዥነት አንስተን በጀነራል ተፈሪ ፈንታ ተካናቸው።

ምዕራፍ ሠላሳ አንድ

በብ/ጀነራል ጌታቸው ናደው የተመራው የአየር ወለድ ሻለቃ ጦር ፀረ-አብዮት አመፅ

በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ አብዮታዊው መንግሥት ከገጠሙት አያሌና ውስብስብ ችግሮች ዋናውና እጅግ አንገብጋቢው በኤርትራ ለመገንጠል የሚደረገው የትጥቅ ትግል ከመሆኑ ባሻገር፣ አረቦች በአገራችን የፈነዳውን ሕዝባዊ አብዮት መልካም አጋጣሚ አድርገው በመመልከት ለገንጣዮች የሚሰጡትን ሁለንተናዊ ድጋፍ በዓይነትም ሆነ በመጠን እጅግ ከፍ በማድረጋቸው ወንበዴዎቹ በትጥቃቸው ዓይነትና ጥራት በተዋጊ የሰው ኃይላቸው ዓይነትና ብዛት ከፍ ያለ ዕድገት ደረጃላይ የደረሱና የክፍለ ሃገሩን ርዕሰ ከተማ አሥመራን ለመቆጣጠር እስከ መሞከር የተገ በዙበት ወይንም የናጠጡበት ጊዜ ነበር።

ብ/ጀነራል ጌታቸው ናደውን ከምድር ጦር ሠራዊት አዛዥነት አንስተን የኤርትራ ክፍለ ሃገር የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አስተዳዳሪና የሰሜኑ ጦር የበላይ አዛዥነታቸው ለአገራቸው በኤርትራ የሚሰጡት አገልግሎት ስለሚልቅ ነው።

ኤርትራ በፌደሬሽን ከእናቷ ከኢትዮጵያ ጋር ከተዋሐደችበትና ከፌደሬሽኑም መፍረስ በኋላ ለክልሉ ታሪክና የፖለቲካ ባሕሬ በሚሰጠው ክብደትና ትኩረት ምክንያት አስተዳዳሪ እየሆኑ በንጉሡ ነገሥቱ የተሾሙት፣ የንጉሡ አማች ራስ አንዳርጋቸው፣ ሌላው የንጉሡ አማች ሌ/ጀነራል አቢይ አበበና በመጨረሻም ማለትም እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ ልዑል ራስ አሥራተ ካሣ እንደነበሩ በአንባቢ ዘንድ ይታወሳል።

የምድር ጦር ሠራዊት አዛዥ የማዕረግ ደረጃና ፕሮቶኮል የአንድን ክፍለ ሃገር ሕዝብ ከሚያስተዳድር ባለሥልጣን የሚበልጥ አይደለም።

ጀነራል ጌታቸው በኤርትራ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አስተዳዳሪ ብቻ ሳይሆኑ ከፍ ብየ የገለፅኳቸው የክፍለ ሃገሩ አስተዳዳሪ የነበሩ ያልነበራቸውን ሥልጣን ተሰጥቷቸው የሰሜኑ ጠቅላላ መለዮ ለባሽ ማለትም፣ የሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር፣ የአየር ኃይሉ፣ የባህር ኃይሉና የፖሊስ ሠራዊትም የበላይ አዛዥ ናቸው።

በየትም ክፍለ ሃገራት በሌለ ቤተ መንግሥት ውስጥ እየኖሩ በቤተ መንግሥት ቁሳቁስና በቤተ መንግሥቱ ሠራተኞች የሚገለገሉ ከመሆናቸው በላይ ደምወዛቸውም ከምድር ጦር አዛዥ መኰንን ደመወዝ የላቀ ነው።

ከሁሉ በላይ ይህንን ታላቅ ኃላፊነት ሰጥተን ወደ ኤርትራ ስንልካቸው አገሪቱ ለኤርትራ የምትሰጠውን ቅድሚያና ትኩረት አስረድተን፣ በእሳቸው ላይ ያለንን ዕምነት ከመግለፅ በላይ የጠበቀ አብዮታዊ አደራ ሰጥተን ነበር።

እጅግ የሚያሳዝነው ይህንን ማድረጋችን ብቻ ሳይሆን ቀድሞውንም እሳቸውን የምድር ጦር ሠራዊት አዛዥ ማድረጋችን ትልቅ ስህተት ነበር።

ከአስራትና ብሎም ከሞት አድነን ይህንን ያህል እምነት ጥለንባቸውና ይህን ያህል ኃላፊነትና ክብር የሰጠናቸው ሰው እኛ ላስቀመጥናቸው ስፍራና ለሰጠናቸው ግምትና እምነት ጨርሶ የማይመጥኑ ብቻ ሳይሆን የአእምሮ ጤንነትም የነበራቸው እንደሆኑ በሂደት አንባቢ የታሪካቸውን ፍፃሜ ሲያነብ ይረዳዋል። ይህንን እንድል ያስገደዱኝን ምክንያቶች ከዚህ እንደሚከተለው ለማስረዳት እሞክራለሁ።

በመጀመሪያ ደረጃ እሳቸው ለራሳቸው በነበራቸው ግምት፣ ምኞትና ግብዝነት ብቻ ሳይሆን ከኔ ጋር በነበራቸው ቀረቤታና የቆዬ ወዳጅነት ምክንያት ይመስለኛል በጀነራል አማን ምትክ የደርጉ ሊቀመንበር ለመሆን ራሳቸውን አጭተዋል።

እሳቸው የተመኙት ነገር ሳይሆን ቀርቶ ብ/ጀነራል ተፈሪ በንቲ የደርጉ ሊቀመንበር እንዲሆኑ በመመረጣቸው ከፍ ያለ ቅሬታ አድሮባቸዋል።

ጀነራል ተፈሪ በንቲና ጀነራል ጌታቸው ናደው በጣም የተለያዩ ሰዎች ናቸው። የተፈሪን ማንነት ወደፊት በተገቢው ጊዜና ቦታ እገልፃለሁ።

የደርጉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በጀነራል አማን ምትክ የደርጉ ሊቀመንበር ለመሆን ይመጥናሉ ያላቸውን በጣም ጥቂት ከፍተኛ መኰንኖች ለደርጉ ጠቅላላ ስብሰባ ለውሳኔ ባቀረበበት ጊዜ «እርሶ በደርጉ አባላት ድጋፍ አግኝተው የተቃወመዎት እርሶ ይደግፈኛል ያሉት ሊቀመንበር መንግሥቱ ነው» ተብሎ ደርጉ ውስጥ በነበሩ ወኪሎቻቸው የአየር ወለድ ሻለቃ ባልደረቦች ስለተነገራቸው በእኔ ላይ ያደረባቸውን ጥላቻ ሳይከልሉ ሲያወግዙኝ በብዙ ሰዎች ዘንድ ተደምጠዋል።

በሁለተኛ ደረጃ፣ የደርጉ ሊቀመንበር ባለመሆናቸው በማዘን ላይ እያሉ ከምድር ጦር ሠራዊት አዛዥነት የተነሱት በተፈላጊነትና በሹመት ሳይሆን እንደሽረት ስለተመለከቱት ፀረ-መንግሥቱ ብቻ ሳይሆን ፀረ-አብዮት መንፈስ ተሠረፀባቸው።

ይህንን ያህል መለወጣቸውን ብቻ ሳይሆን ወደ እብደቱም ማዘንበላቸውን መረዳት የቻልነው ብዙ ዘግይተን በለየለት የጥፋት ጎዳና ላይ መራመድ በጀመሩበት ጊዜ ነው።

በአፄ ኃይለሥላሴ አገዛዝ ዘመን የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎች በአጠቃላይ የፖሊስ ሠራዊቱን ጨምሮ የምድር ጦር ሠራዊቱ በተለይ በደመወዝ አከፋፈል በቀለብ

አቅርቦትና በአልባሳት እደላ መድሎ ወይንም በከፋፍለህ ግዛ የአስተዳደር መርህ ላይ የተመሰረተ ነበር።

የደመወዝ አከፋፈሉና የቀለብ አቀራረቡ በእነ ጀነራል መንግሥቱ ንዋይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ጊዜ ለሠራዊቱ ገብተው በነበረው ቃል መሰረት በጥቂቱ፣ በታላቁ አብዮታችን አጥቢያ ልጅ እንዳልካቸው መኮንን አቶ አክሊሉ ሀብተ ወልድን ተክተው ጠቅላይ ሚኒስትር በሆኑበት ማግሥት የሠራዊቱን ድጋፍ ለማግኘት ሲሉ መጠነኛ መሻሻል የተደረገ ሲሆን፣ በአልባሳት አቅርቦት በኩል የተሻሻለ ነገር ስላልነበረ በአብዮቱ ፍንዳታ ማግሥት ካተኮርንባቸው የአስተዳደር ጉዳዮች አንዱ የመከላከያ ሠራዊቱ በአለባበስ ልዩነት እንዳይከፋፈል ማድረግ ነበር። ይህ ብቻ ሳይሆን የሚታደለው ልብስ ይዘትና ጥራት እንዴትና በምን ዓይነት መሻሻል ይደረግ? በሚል አጀንዳ ላይ በምንነጋገርበት ጊዜ ከብዙ የደርግ አባላት በምድር ጦሩ ሠራዊት ውስጥ ያሉት የጦር ክፍሎች የሚለዩት በሚያደርጉት መለዮ ሳይሆን መለዮው ላይና ክንድ ላይ በሚደረጉ የክፍል መለያ ምልክቶች ቢሆን ይሻላል። በወደቀው ሥርዓት ጊዜ በጦር ኃይሎችና በጦር ክፍሎች መሀከል የነበረውን መከፋፈል፣ መናናቅና ጥላቻ አስወግዶ አብዮታዊውን የጦር ኃይል በዓላማና በተግባር ብቻ ሳይሆን በአለባበስም አንድ ያደርገናል ሲሉ ሃሳብ አቀረቡ። ይህንንም ጠቅላላው ስብሰባ በሙሉ ስለተስማማበት ሃሳቡን ለሰፊው ሠራዊትም አቅርበን በአድናቆት ጭምር መላው የጦር ኃይሎች በመደሰት መስማማታቸውን ገለፁልን።

በአገሪቱ የጦር ኃይሎች ድጋፍና ፍላጎት መሰረት ሠራዊታችንን እንደበለፀጉት አገሮች ሠራዊት በአለባበሱ ማዘመን ብቻ ሳይሆን የውጊያ ልብስ፣ የአዘቦት ወይም የስራ ልብስና እንግሊዞች (ኤ.ዩኒፎርም) በሚሉትና በአማርኛችን የክት ልብስ በሚባለው ልዩነትና መድሎ ሳይኖር ተርታዎቹን አብዮታዊ ወታደሮች ከመኮንኖቹ ጋር በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ባለባበስ አመሳሰልናቸው።

በዚህ ውሳኔ መሠረት የንጉሡ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ ክፍለ ጦር ያደርገው የነበረው ካስክ ባርኔጣ፣ የታንከኛው ጦር ያደርገው የነበረው ጥቁር መለዮና የአየር ወለዱ ሻለቃ ጦር የሚያደርገው ቀይ መለዮ እንዲቀሩና መላው የምድር ጦር ሠራዊት አዲሶቹን መለዮዎች እንዲለብስ በህግ ሲደነገግ፤ ቀዩ የአየር ወለድ ጦር መለዮ መቅረት የለበትም ሲሉ የከረረ ተቃውሞ ያቀረቡ ብ/ጀነራል ጌታቸው ናደው ብቻ ሆኑ።

መቃወም ብቻ ሳይሆን መላው ሠራዊት ሕጉን አክብሮ አዲስ የታደለውን አንድ ዓይነት መለዮ ሲለብስ እሳቸው አዲስ አበባ ሲመጡ ብቻ አዲሱን መለዮ እየለበሱ ኤርትራ ክፍለ ሃገር ባሉ ጊዜ የአየር ወለዱን መለዮ መልበስ ቀጠሉ።

ጀነራል ጌታቸው ወደ ኤርትራ ከመላካቸው በፊት የሰሜኑን ጦር ለማጠናከር በርከት ያለ ኃይል ማለትም ሁለት እግረኛ ብርጌዶችና መደመር አንድ እግረኛ ሻለቃ ይህንኑ

ያህል መጠን ያለው አባት ጦር፣ ብሄራዊ ጦርና የሰባት ዓመት ምልስ ወታደሮች የተሀድሶ ሥልጠና በመስጠትና የአመራር አካላት ፈጥረንላቸው በማደራጀት ልከን ስለነበር ጀነራል ጌታቸው ሥራቸውን እንደጀመሩ በዚህ ኃይል ተጠቅመው በገንጣዮች ላይ ያላቋረጠ የጥቃት ዘመቻ ያደርጉ ዘንድ ትዕዛዝ በሰጠናቸው ጊዜ፣ እሳቸው ከሚያካሂዱት ወታደራዊ ዘመቻ ጋር በተጓዳኝ የሚከናወን የፖለቲካ፣ የፕሮፖጋንዳ ተግባርና የሠላም መፍትሄ ፍለጋ ዕቅድ አዘጋጀን፡፡

የዕቅዱ አንደኛው ክፍል፣ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ሁለቱም ገንጣዮች ማለትም «ጀብሐ» እና «ሻዕቢያ» የፖለቲካ ፕሮግራማቸው አካልና የፕሮፖጋንዳ ሥልት አድርገው፤

1ኛ. ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌላትና ራሷን ችላ የኖረች ነፃ ሃገር ነበረች፣

2ኛ. ኤርትራን ወራ በቅኝ ገዥነት የኖረችው ኢጣሊያ ስትወጣ ጎረቤታችን ኢትዮጵያ ተተክታ ዳግም በመውረር ቅኝ ስለ አደረገችን የኛ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው፡፡

3ኛ. ዘይት አምራች ከሆኑ አረብ አገሮች ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ፣ የኤርትራ ሕዝብ በሙሉ የእስልምና እምነት ተከታይ ብቻ ሳይሆን በዘሩም አረባዊ ሕዝብነው ወዘተ በማለት ሲያሳስቱና የክፍለ ሃገሩን ወጣት ትውልድ የጥፋት ዓላማቸው አስፈፃሚ ለማድረግ የክህደትና የፈጠራ ታሪክ ሲያስተምሩ በመንግሥት በኩል ይህንን በማስተባበልና የማጋለጥ እርምጃ ባለመወሰዱ ከወታደራዊው እርምጃ ጋር አዳብለን የማጋለጥ ዘመቻ ለማድረግ አቀድን፡፡

ሁለተኛው ክፍል፦

ወታደራዊውና የፕሮፖጋንዳው ዘመቻ እየተካሄደ፤ ለችግሩ ሠላማዊና ፖለቲካዊ መፍትሄ ሊያስገኝ ይችል ይሆናል ብለን ያዘጋጀነው ራስ ገዝ የውስጥ አስተዳደር ላይ የተመሠረተ የሠላም ውይይት ከገንጣዮቹ ጋር ለማድረግ የዕቅድ ዝግጅት አድርገን እነኝህም ዕቅዶች በተግባር የሚተረጎሙበትን መቼና እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆኑ ያደረግነውን መሰናዶ ለማስረዳት ጀነራል ጌታቸውን የቅርብ ረዳቶቻቸውና በሥራውም ተካፋይ ለመሆን አግባብ ካላቸው ሰዎች ጋር አዲስ አበባ ጠርተን በደርጉ ጽሕፈት ቤት ባሳወቅናቸው ጊዜ በእሳቸው በኩል የሚጠበቅባቸውን ወታደራዊውን ጉዳይ አስመልክተው ጥያቄ አቀረቡ፡፡

ያቀረቡትም ጥያቄ «አሁን በአሥመራ ከተማ ውስጥና በዙሪያው ያከማቸናቸው አባት ጦሮች፣ ብሄራዊ ጦርና የሰባት ዓመት ምልስ ጦሮች የሚሰጡት አገልግሎት፣ ቋሚ የመከላከያ ወረዳ ይዘው የገንጣዮችን ጥቃት የመከላከል እንጂ በዕቅዱ ላይ የተገለፀውን ዓይነት የማጥቃት ተግባር በማከናወን አባት ጦሮች በእርጅና ምክንያት

የአካል ድክመት ያለባቸው ሲሆኑ የተቀሩት ብሄራዊ ጦሩና የሰባት ዓመት ምልሶች የውጊያ ልምድ የላቸውም።

ባሉኝ መደበኛ ተዋጊ እግረኛ ጦሮች የማጥቃቱን ተግባር ሳከናውን በተጠባባቂነትና በመቺ ኃይልነት የምይዘው ኃይል ስለሚያስፈልገኝ አሁን በተለያዩ ሥፍራዎች ተበታትኖ ያለውን የአየር ወለድ ሻለቃ ሰብስባችሁ ስጡኝ» የሚል ነበር።

በጥያቄያቸው መሠረት አየር ወለዱ ሻለቃ ጦር ለሁለተኛ ጊዜ የኛ ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር መቺ ኃይል ሆኖ እንዲሠራ ፈቀድንላቸው።

ጥያቄያቸውን ሲያቀርቡ እኛ ለማጥቃት ስንነቃነቅ ገንጣዮቹ የአስመራን ከተማ ዙሪያ መከላከያ በድንገት ቢጥሱ ብለው የገለፁልን ሥጋት በአንድ አየር ወለድ ሻለቃ ጦር ብቻ ይቃለላል ብዬ ለማሰብ ስለተቸገርኩ ከመከላከያው ኰሚቴ ሊቀመንበር ከጓድ ሻለቃ ተስፋዬ ገብረኪዳን ጋር ተማክሬ የደርጉን ደህንነት ይጠብቅ የነበረውን አንድና ብቸኛ የታንክ ሻምበል በተጨማሪና በአስቸኳይ እንዲላክላቸው አደረግን።

ይህንን ያደረግነው የደርጉን ብቻ ሳይሆን የአገሪቱን ርዕሰ ከተማ የአዲስ አበባንም ጥበቃ በሁለተኛ ደረጃ በማየት ለአስመራ ከተማ ደህንነት ቅድሚያ በመስጠት ነው።

ከአየር ወለዱ ሻለቃ ጋር በአጣዳፊ ወደ ኤርትራ የላክነው የታንክ ሻምበል አዛዥ ሻምበል ጥላሁን ማንያዘዋል ይባላል።

አብዮታዊ ሰደድ የምንለው ፓርቲያችን መሥራች አባል ነው። በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በአሰብ ወደብ በኩል በባሕር መጓጓዣ አስመራ ከደረሰ በኋላ «ሳልዘጋጅ በድንገት በመታዘዜና በአጣዳፊ በመነቃነቁ ለጥበቃ ብርጌዱ ማስረከብ የሚገባኝን አንድ ከፍተኛ ነገር ሳላስረክብ መጥቻለሁና በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ አስረክቤ እመለስ ዘንድ ለክፍለ ጦሩ አዛዥ ለኰሎኔል ኃይሉ ገብረሚካኤል የአየር መጓጓዣ እንዲያዙልኝ ይነገርልኝ» የሚል ጥያቄ በስልክ በቀጥታ ለኔ አቀረበልኝ።

ሻምበል ጥላሁንን ወደ ኤርትራ ስልከው ለጀነራል ጌታቸው ያለኝን በጎና ወዳጃዊ አመለካከት እሳቸው በነገሩኝ መሠረት ስለ ኤርትራ ያለኝን ሥጋት እሱም በታንከኛነቱ ብቻ ሳይሆን በአብዮታዊ ሰደድ ካድሬነቱ ለአብዮቱ ዘብ እንዲቆምና በአስመራ ከተማ ከሚገኘው የፓርቲያችን አመራር አካላት ጋር ግንኙነት በማድረግ የሚሰራውን የፖለቲካም ተልዕኰ ሰጥቼው ነው የላኩት።

አላስረከብኩም ስለሚለው ነገር የደርጉ ጥበቃ ብርጌድ አዛዥ ቢጠየቅ በእሱ በኩል የሚያውቀው ነገር እንደሌለ ስለገለፀ ሻምበል ጥላሁን በአስቸኳይ በአየር መጓጓዣ ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት የፈለገበትና ባልተለመደ ሁኔታ በቀጥታ ለኔ ስልክ ለመደወል የተገደደበት አንድ ትልቅ ጉዳይ ቢኖረው ነው። ምናልባትም እኔ ከሰጠሁት የሥራ

መመሪያና ተልዕኮ ጋር የተያያዘ ችግር ቢገጥመው ይሆናል በማለት የክፍለ ጦሩ አዛዥ በአየር መጓጓዣ እንዲልኩት ትዕዛዝ ተሰጠለትና መጣ::

አዲስ አበባ እንደደረሰ ወዲያው ወደ ደርግ ጽሕፈት ቤት መጥቶ ከብ/ጀነራል ጌታቸው ናደው ለሊቀመንበር መንግሥቱ የተላከ መልዕክት ይዤ ስለመጣሁ አቅርቡኝ ይልና እኔ ዘንድ ቀርቦ ከዚህ የሚከተለውን ነገረኝ::

«ጀነራል ጌታቸው እርስዎ እንደሚያስቡትና ለኔም እንደነገሩኝ የእርሶም ወዳጅ የአብዮቱም ወገን ወይንም ደጋፊ አይመስሉኝም:: እንደውም አደገኛ ሰው ይመስሉኛል::

በሰጡኝ ትዕዛዝ መሠረት አስመራ ከተማ እንደገባሁ በዚያው ዕለት ከቀትር በኋላ ጽሕፈት ቤታቸው በመሄድ ከአየር ወለዱ ሻለቃ ጋር የክፍለ ጦሩ መቼ ኃይል ሆኘ እንድሠራ ከደርግ ተልኪያለሁ በማለት እንድነግራቸው የነገሩኝን የቃል መልዕክት ስነግራቸው እንኳን ደህና መጣህ ሳይሉኝ በጣም ከት ብለው በመሳቅ፤ መንግሥቱ ከራሱ ጥበቃ ላይ አንስቶ አንተን ከነታንኮችህ እንዴት ሊልክ ቻለ? ለምንስ ፈለገ? ብለው ጠየቁኝ::

ሁኔታቸው እጅግ ስለአስገረመኝና ስላስደነገጠኝም የምለው ጠፍቶኝ ዝም ብዬ ሳስተውላቸው ንግግራቸውን በመቀጠል፤ እንደ አየር ወለዱ ጦራችን እናንተንም ታንከኞችን መታወቂያችሁ፣ የክፍላችሁ መኩሪያና መለያ የሆነውን ጥቁር መለዮአችሁን መንግሥቱ ስለገፈፋችሁ በጣም አዝኛለሁ በማለት ብዙ ተናገሩ::

በእርሶ ላይ ያደረባቸው ጥላቻና ድፍረታቸው ያመፁና ለአንድ ትልቅ ጥፋት የተዘጋጁ መሆናቸውን ያስረዳል:: የአየር ወለዱን ሻለቃ ጦር ጠይቀው የወሰዱት ገንጣዮችን ለመውጋት ሳይሆን በመለዮ ቅስቀሳ አድርገው ላቀዱት ጥፋት ከአየር ወለዱ ሻለቃም በላይ የሚያስፈልጋቸውን አንድ የታንክ ሻምበል ጦር ስለላኩላቸው እጅግ ከመደሰታቸው ባሻገር የእርሶን የአገር ፍቅር ስሜት በየዋህነት እንደተደረገ ስሕተት በመገመት ይመስለኛል::

በሰጡኝ ትዕዛዝ መሠረት ከክልሉ የአብዮታዊ ሰደድ አመራር አካላትና ከወታደራዊ ደህንነት ኃደች ጋር በአደረግሁት ግንኙነት እንደተረዳሁት ስለመለዮ አለባበስ የወጣውን ህግ ጥሰው ቀዩን የአየር ወለድ ጦር መለዮ መልበስ ያልተው መሆናቸውን ሲሆን ይህንን እኔም ተመልክቻለሁ::

ስለ እርሶም ሆነ ስለደርግ በጎ ነገር አይናገሩም:: የአየር ወለድ ሻለቃው አባል የበታች ሹማምንቶች በህቡዕ በጦሩ ውስጥ ፀረ-ደርግ ቅስቀሳ ጀምረዋል::

እኚህ ሰው ካሳዩኝ እብሪትና ድፍረት አንድ የተማመኑበትና ያለቀለት ነገር ያዘጋጁ መስሎ ስለታየኝ ይህንን ላሳውቅዎት ነው የመጣሁት» አለኝ::

የመኰንኑን ንግግር በጥሞና ከአዳመጥሁ በኋላ፤ ተጨማሪ ግንዛቤ ለማግኘት "ስለ ሰሜኑ መለዮ ለባሽ ህብረት፤ ለአብዮቱ ስላለው ወገናዊ ስሜትና በጀነራል ጌታቸው ላይ ስላለው አስተያየት የተረዳኸው ነገር አለ?" ብዬ ላቀረብኩለት ጥያቄ «የክልሉ የፓርቲያችንና የወታደራዊ ደህንነት ጓዶች ጠንካሮች በአብዮታዊ ትብብር የሚሰሩና የሚያስተማምኑ ሆነው ነው ያገኘኋቸው።

በአጠቃላይ ጦሩ ለወሬና ለአድማ ጊዜ የለውም ከፊሉ በየቀኑ የአስመራን ከተማ አካባቢ የመከላከያ ምሽግ ውጭ ሲቃኝና ሲያስስ ከፊሉ ቤቱ ምሽግ ነው።

ጠቅላላው የክልሉ መለዮ ለባሽ አብዮታዊነቱና ሕብረቱ ጥሩ ነው በጠቅላላው የአብዮቱ ደጋፊ ነው ማለት ይቻላል። በተለይም በጓድነትዎ ላይ ትልቅ እምነትና ፍቅር አለው።

ጀነራል ጌታቸው ወደ ኤርትራ የሄዱት በቅርቡ ከመሆኑ በላይ ኤርትራን የመሰለ ክፍለ ሃገር የማስተዳደርና ጦሩን በበላይነት የመምራት ግዙፍ ኃላፊነቶች ስለአሏቸው ህዝቡንም ሆነ ጦሩን ቀርበው ያውቁታል ለማለት ያስቸግራል። ወታደራዊ ካድሬዎቹና ወታደራዊ ደህንነቶች ናቸው ከጦሩ ጋር በምሽግ ውስጥ የሚኖሩት» አለኝ።

በአጭር ጊዜ ውስጥ በኤርትራ ያለውን ሁኔታ በዝርዝር ከመከታተሉና ከመገንዘቡ በላይ የተፈጠረውን አደገኛ አዝማሚያ በማስተዋል ፈጥኖ አዲስ አበባ በመምጣት ስላሳወቀኝ አመስግኜ በተጨማሪ የሰጠሁት ትዕዛዝ፤

"የአሰብን ወደብና አካባቢውን እንዲጠብቅ የላክነው አንድ የክብር ዘበኛ ክፍለ ጦር አካል የሆነ እግረኛ ሻለቃ አዛዥ የነበረው ሌ/ኰሎኔል ብርሃኑ ኃይሌ በአሰብ ከተማ የደርግን መንግሥት ገልብጫለሁ በማለት በወታደራዊ ራዲዮ ለጥቂት ቀናት የኢትዮጵያን አየር በውዥንብር እንደ አጠነው ሁሉ፣ ሌላው እብድ ብ/ጀነራል ጌታቸው በአንድ ሻለቃ አየር ወለድ ጦር የኢትዮጵያን ሕዝብ ማህበራዊ አብዮት ቀልብሰው የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ መመኘት የጤንነት ስላልሆነ የኤርትራን የራዲዮ ጣቢያ ተጠቅመው ለመከላከያ ሠራዊታችን ብቻ ሳይሆን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ብሎም በውጪው ዓለምም የወሬ ቀውስና ውዥንብር ሊፈጥሩ ስለሚችሉ ከዛሬ ጀምሮ የኤርትራን የራዲዮ ጣቢያ ጥበቃ ለአንተ ሰጥቼሃለሁ።

በዚህ ረገድ ችግር እንዳይገጥምህ ለክፍለ ጦሩ አዛዥ ለኰሎኔል ኃይሉ ይህንኑ አሳውቅልሃለሁ ካለ እኔ ትዕዛዝ የራዲዮ ጣቢያውን ጥለህ የትም እንዳትንቀሳቀስ። ታንክ፣ ፀረ-እግረኛና ጥሩ የማጥቂያ መሣሪያ ቢሆንም እውር ስለሆነ በተለይም በሌሊት ከጠላት ራሱን ለመከላከል ስለማይችል የሚረዳህ በኤርትራ ውጊያ ከፍ ያለ ዝና ያተረፈውንና ስመ ጥሩውን 31ኛ እግረኛ ሻለቃ አዝልሃለሁ። የዚህ ሻለቃ አዛዥ

ሻለቃ ክፈተው መርኔ ስለሚባል አስመራ እንደደረስክ ተገናኘውና በጋራ የሕብረት ውጊያ ዕቅድ አውጡ" የሚል ነበር።

ሻምበል ጥላሁን ማንያዘዋልን ወደ ኤርትራ ካሰናበትኩ በኋላ የጦር ኃይሎች ወታደራዊ ደህንነት ኃላፊውን መኰንንና የአገር ደህንነቱን ሚኒስትር ጠርቼ በኤርትራ ጀነራል ጌታቸው ናደው የሚያካሂዱትን ሴራ እንዴት እንዳልደረሱበትና እንዳልነገሩኝ ብጠይቃቸው፤ «ከሁሉ በፊት ጀነራል ጌታቸውን ተከትሎ የሰሜን ጦር በደርግ ላይ ያምፃል ብለን ካለማመናችን ሌላ በችኰላ ጥሬ ነገር ይዘን በመቅረብ እንዳናሳስትዎ ብለን ጊዜ ለመግዛት ተወያይተንበት ያደረግነው እንጂ የቀረበልዎት መረጃ ትክክል ነው» ሲሉ እነሱም ስለአረጋገጡ ጠላትን መናቅ አይገባምና ሁኔታውን እየተከታተላችሁ አሳውቁኝ ብዬ ትዕዛዝ በመስጠት ጉዳዩን ለእነሱ ተውኩት።

ምዕራፍ ሰላሣ ሁለት

ብ/ጀነራል ጌታቸው ናደው በኤርትራ እንዲያከናውኑ በደርግ የተሰጣቸውን ተልዕኮ በመርሳት በፀረ-አብዮት ተግባራቸው ላይ ብቻ ስለማተኮራቸው

በኤርትራ ክፍለ ሃገር የሚካሄደውን የትጥቅ አመፅና የፖለቲካ ችግር ለማቃለልና ቢቻልም ጨርሶ ለማስወገድ ያቀድነው ዕቅድ አካል የሆነውን ወታደራዊ ጉዳይ በሙሉ ለጀነራል ጌታቸው በመስጠት ወይንም በሙተው በደርግ በኩል የተቀሩትን ሁለቱን ማለትም፤ የገንጣዮችን በክህደትና በሐሰት ላይ የተመሠረተ የፈጠራ ታሪክ የሚያጋልጥና ለክፍለ ሃገሩ አዲስ ትውልድ እውነተኛ ታሪኩን የሚያስተምር የታሪክና የፖለቲካ ትንተና እያዘጋጀ በኤርትራ ክፍለ ሃገር ብዙሃን ማሰራጫዎች እንዲሰራጭ በሳምንት ሁለት ጊዜ ወደ ኤርትራ የሚላክ ሥነ ጽሁፍ የሚያዘጋጅ ከደርግ አባላት፣ ከሕዝብ ማደራጃ ጽሕፈት ቤትና ከሌሎችም ባለሞያዎች የተወጣጣ ቡድን አቋቋምን፡፡

ታሪክን ማስተማሩንና የገንጣዮችን ፈጠራ የማጋለጡን ተግባር ከኤርትራ ክፍለ ሃገር የራዲዮ ፕሮግራምና ጋዜጦች ዝግጅት ጋር አስተባብሮ እየመራ በቅንጅት የሚሰራ በደርጉ የማስታወቂያ የቅስቀሳና የፕሮፖጋንዳ ኰሚቴ ሊቀመንበር በሻለቃ አሥራት ደስታ የሚመራ አንድ ንዑስ ቡድንና በራስ ገዝ አስተዳደር (Regional Autonomy) መፍትሄነት ሠላምን ለመፍጠር ከገንጣዮች ጋር የሚደረገውን ግንኙነትና የፖለቲካውን ሥራ በአጠቃላይ ኤርትራ ክፍለ ሃገር ካሉት የአንድነት ደጋፊ የፖለቲካ ሰዎችና ለሥራው አግባብ ካላቸውና ጠቃሚ ከሆኑ የክፍለ ሃገሩ ባለ ሥልጣኖች ጋር ሆኖ ደርግን በመወከል የሚሰራ አንድ ሌላ ንዑስ ቡድን በሻለቃ ሲሣይ ኃብቴ የሚመራና የሕዝብ ማደራጃ ጽሕፈት ቤት አመራር ኰሚቴ ሰብሳቢ ከሆነው ከኀድ ኃይሌ ፊዳ ጋር በመላክ ዕቅዱን ወደ ተግባር የመተርጎም ጥረት ቀጠለ፡፡

በኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ አንድ ላይ እንደገለፅኩት ሻለቃ ሲሣይና ሻለቃ አሥራት ደርግን ወደ ቀኝ ለማስኬድ የሚታገለን ቀኝ ክንፍ ቡድን ቀንደኛ መሪዎች ናቸው፡፡

በሠላማዊ መፍትሄ ፍለጋና ገንጣዮችን ለማጋለጥ ሥራ ወደ ኤርትራ የላክናቸው በደርግ ውስጥ ባላቸው የሥራ ሃላፊነት ነው፡፡

ሻለቃ አሥራት በገነት ጦር ትምህርት ቤት ከጀነራል ጌታቸው ጋር ለዓመታት አብሮ የሠራና ደርግን በሚመለከት ጉዳይ ወሬ አቅራቢ የመረጃ ወኪላቸው ነው፡፡

ማን ማንን ጠምዝዞ ወይንም አሳምኖ አቋም ለማስያዝ እንደቻለ ለኛ ግልፅ ባይሆንም በሁለት ሳምንት በኤርትራ ቆይታቸው ሁለቱ የደርግ ሻለቆች ከጀነራሉ ጋር አብዮቱን የመቀልበስ የጋራ አቋም ለመያዝ ችለዋል።

ጀነራል ጌታቸው ከሁለቱ ሻለቆች ጋር ብቻ ሳይሆን የመቶ አለቃ ስለሺ በየነና የመቶ አለቃ በዕውቀቱ ካሳ ጋርና እንዲሁም የአየር ወለድ ሻለቃ ባልደረባና የዕድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ መመሪያ ሃላፊ ካደረግነው ከሻለቃ ኪሮስ ዓለማየሁ ጋር በነበራቸው የጠነከረ ግንኙነትና የዓላማ አንድነት በደርግ ላይ እንደ ሸረሪት የስለላ መረባቸውን አድርተው ነበር ማለት ይቻላል።

ይህንን ማወቅ የቻልነው ብዙ ዘግይተን የደርግ አባልና የአየር ወለድ ሻለቃ ባልደረባ በሆኑ የአብዮቱ ታማኝ አርበኞች በ፶ አለቃ በቀለ ደገና በ፶ አለቃ ፍቅሬ ዘርጋባቸው ሲሆን ከእነዚህ ጋር ዋናው ረዳታችን የደርጉ ጥበቃ ብርጌዱ የዘመቻ መኮንን ሌ/ኮሎኔል ዳንኤል አስፋው ነበር።

ዳንኤል የአብዮታዊ ሰደድ መሥራች አባል ነው። ጀነራሉ ዳንኤልን በአየር ወለድ ሻለቃ ባልደረብነቱ በማጥመድ የጥፋት ተባባሪያቸው ሊያደርጉት ሞክረው ስለተቃወማቸው ከኔ ቀጥሎ የጥፋት ዒላማቸው አድርገውት እንደነበር ታውቋል።

ጀነራሉ በአስመራ ከተማ በአየር ወለድ ሻለቃ አባላት መሣሪያነት የስሜኑን መለዮ ለባሽ በደርግ ላይ ለማሳመፅ የሚያደርጉትን ቅስቀሳ እንደ ቀጠሉ ነበር።

ሻለቃ ሲሣይና ሻለቃ አሥራት ከሁለት ሳምንት ቆይታ በኂላ የተላክንበት ተልዕኮ በመልካም ሁኔታ የተያያዘ በመሆኑና ባለቤትም ያገኘ በመሆኑ ለጊዜው የኛ እዚህ መቀመጥ አላስፈለገምና እንድንመለስ ይፈቀድልን ብለው ስለ አመለከቱ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱ አደረግን።

ጀነራል ጌታቸው በዕቅዱ መሠረት እንዲያከናውኑ ስለተሰጣቸው የሥራ ድርሻ የጀመሩትና ያመለከቱንም ነገር አልነበረም። የጀመሩት አመፅ አንድ አመርቂ መፍትሄ ከማግኘቱ በፊት የሠራዊቱን እንቅስቃሴ በተጨማሪ የጀመሩትን ሴራ ማስፋፊያ ሊያደርጉት ይችላሉ ብለን በመገመት በእኛም በኩል የጠየቅናቸው ነገር አልነበረም።

ሻለቃ ሲሣይና ሻለቃ አሥራት ወደ አዲስ አበባ በተመለሱ ማግሥት ደብረ ዘይት በአየር ወለድ ሻለቃ መኖሪያ ሠፈር የሻለቃውን ንብረት ለመጠበቅና የጦሩን ቤተሰብ ለማስተዳደር ወዘተ በተሰኘ ከለላ እኔ በደብረዘይት መንገድ ላይ ሳልፍና ሳገድም አድፍጦ በመጠበቅ እንዲገድል ጀነራል ጌታቸው ግዳጅ የሰጡትን ነፍሰ ገዳይ ቡድን እንዲሸፍኑ ሲባል ከሻለቃው ጦር ተነጥለው እንዲቀሩ የተደረጉ የሻለቃው ጠቅላይ ሠፈር ሻምበል አባሎች ከሻለቃው ግምጃ ቤት መሣሪያቸውን አውጥተው አምፀናል በማለት በአየር ወለድ ሻለቃና በአየር ኃይል ሠራዊት መኖሪያ ሠፈር መሐከል

በግምት አምስት ኪ/ሜትር ያህል ርቃ ከሁለቱ የጦር ሠፈሮች ምሥራቅ በምትገኝ አንዲት ትንሽ ኮረብታ ላይ መሽገው ውጊያ የሚፈልግ ይምጣና ይሞክረን ብለው ተቀመጡ።

እዚያው ደብረ ዘይት ከአየር ወለድ ሻለቃ መኖሪያ ሠፈር በግምት አስር ኪ/ሜትር ያህል እርቆ በሚገኝና ለምለም በመባል የሚጠራ የጦር ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ውስጥ በኰሎኔል አለማየሁ ደስታ በኋላ ብ/ጀነራል የሚታዘዝና የኰማንዶ ሥልጠናውን አገባዶ ለምረቃ የተቃረበ ነበልባል በመባል የሚጠራ እግረኛ ክፍለ ጦር ነበረን።

አመፁ እንደተሰማ ኰሎኔል አለማየሁ ደስታ ራሳቸው በአንድ ሻለቃ ነበልባል ጦር ያችን ኮረብታ አስከብበው አየር ወለዶቹ አንዲት ጥይት ሳይተኩሱ በቁጥጥር ሥር ስለ አዋሏቸው የደብረ ዘይቱ የአየር ወለዶች አመፅ በዚሁ አበቃለት።

ጀነራል ጌታቸው ደብረ ዘይት ያለ አንድ ያልተሟላ ሻምበል ጦር መንግሥት ላይ አምፆ የሚያስገኘው ፋይዳ አለ ብለው ሳይሆን ሠራዊቱን ለአመፅ ለመቀስቀስ ምክንያት በመሆን ይረዳኛል በሚል ግምት እንደ አደረጉት ይታመናል።

በአስመራ ከሚገኘው የአየር ወለድ ሻለቃ ጦር ውስጥ ከእሳቸው ጋር ልዩ ግንኙነት ያላቸውንና የአመፁ ቀንደኛ መሪ ያደረጓቸውን ጥቂት የበታች ሹማምንቶች ጽሕፈት ቤታቸው ጠርተው «ደርግ ደብረዘይት የቀሩትን ወንድሞቻችሁንና ቤተሰባችሁን በነበልባል ጦር አስከብቦ አስፈጃቸው» ብለው ሲነግሯቸው በአየር ወለድ ሻለቃ ሠፈር ውስጥ ከፍ ያለ ሽብር ተፈጠረ።

የአየር ወለዱ ሻለቃ ጦር ከፊሉ ማለት ይቻላል በቡድን በቡድን ሆኖ በአስመራ ከተማና በዙሪያው ባሉ የሁለተኛው ዋሊያ ክፍለ ጦር ሠራዊት የጦር ሠፈሮች እየተዘዋወሩ «ሁለተኛ ሬቮሉሽን ጀምረናልና ተባበሩን» እያሉ በድምፅ ማጉያ ቀኑን በሙሉ ሲለፍፉ ውለው በምሽቱ የአየር ወለድ አባላት የበታች ሹሞች በአመዛኙ ያሉበት ኰሚቴ በማቋቋም በአየር ወለዱ ሻለቃ ሠፈር ውስጥ ሰዶልቱ አድረው በበነጋታው ወደ ጀነራል ጌታቸው ጽሕፈት ቤት በመሄድ «ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማሪያምን መላው የሰሜን መለዮ ለባሽ ለጥያቄ ስለሚፈልጋቸው በአስቸኳይ መጥተው ያነጋግሩት ዘንድ እንድንጠይቅ ወክሎናል» በማለት ያመለክታሉ።

የሴራው ጠንሳሽና በጠቅላላውም የአመፁ መሪ እሳቸው ጀነራል ጌታቸው ሲሆኑ ዓላማቸውም እኔን አስመራ አስጠርተው ለማሰር ወይንም ለማስገደል ነው።

ይህንን የመሰለውን መላ ለመጠቀም በመሞከር እሳቸው የመጀመሪያው ሰው አይደሉም። በ1967 ዓ.ም ከዙፋኑ መገርሰስ ማግሥት ጀነራል አማን በደቡብ ኢትዮጵያ የሚኖረውን ጦር እንበኛለሁ ብለው ነገሌ ቦረና በመሄድ የአራተኛው እግረኛ

ብርጌድ አዛዥ ከነበሩት ከሌ/ኰሎኔል ጌታቸው ባልቻ ጋር በመመሳጠር ሻለቃ መንግሥቱንና ሻለቃ አጥናፉን መላው የአራተኛ እግረኛ ብርጌድ ጦር ለብርቱ የሃገር ጉዳይ ሊያነጋግራቸው ይፈልጋል በማለት ጦሩ ሳይጠይቅ በጦሩ ስም አስጠርተው ስንሄድ በማሰር ወይንም በመግደል ደርግን ለመበተን ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀርቷል።

የአየር ወለድ ሻለቃ የበታች ሹማምንቶችን ይህንን በሉ ይህንን አድርጉ እያሉ በማዘዝ አመፁን የሚመሩ መሆናቸውን ለመሰወር ይመስላል «እኔ የክፍለ ጦሩ የበላይ አስተዳዳሪ እንጂ አዛዥ ስለ አይደለሁ የጦሩን ጥያቄ ወደ በላይ አካል እንዲያቀርብላችሁ የክፍለ ጦሩን አዛዥ ኰሎኔል ኃይሉ ገብረሚካኤልን ጠይቁ» ብለው የበታች ሹማምንቱን ወደ ኰሎኔል ኃይሉ ከመምራት ባሻገር፣ ኰሎኔል ኃይሉ የሠራዊቱን ጥያቄ ለሻለቃ መንግሥቱ እንዲያቀርቡ ያዟቸዋል።

ኰሎኔል ኃይሉ እንደታዘዙት ለኔ ከመንገር ፊንታ በስልክ ለሻለቃ አጥናፉ አባተ ሲነግሩት እኔ መንግሥቱ አይደለሁም መንገር ያለብህ ለመንግሥቱ ነው በማለት ስልኩን ይዘጋባቸውና ኃይሉ ይህንን አለኝ ብሎ ለኔ ይነግረኛል።

ኰሎኔል ኃይሉ ደውለው ይነግሩኛል ብዬ ስጠብቅ ሁለት ቀናቶች አለፉ። የበታች ሹማምንቱ ኰሚቴ እንዴት መልስ አላገኘንም በማለት ከመደንፋት ሌላ ሴራውን በጦሩ ውስጥ ለማዳረስ ጥረታቸውን ቀጥለዋል።

ከሁለት ቀን በኋላ ራሴ ለኰሎኔል ኃይሉ ደውዬ በሻለቃ አጥናፉ በኩል የላኩት መልዕክት ደርሶኛል። ይህንን የመሰለውን ጉዳይ ማመልከት ያለብዎት ለኛ ሳይሆን ለጀነራል ጌታቸው ነው የሚል ትዕዛዝ ሰጠኋቸው።

ከዚህ በኋላ ሁለቱ ሰዎች ማለትም ጀነራል ጌታቸውና ኰሎኔል ኃይሉ ሲነጋገሩ ሌሎች ቀናቶች ስለተቆጠሩ ለጀነራል ጌታቸው ደውዬ ምንም ነገር እንዳልሰማ ሰው የተለመደውን የሠላምታ ንግግር ተለዋውጠን ኤርትራ ሰላም ነው ወይ? ምን አዲስ ነገር አለ? ብዬ ስጠይቃቸው «አልሰማህም ብዬ አልጠራጠርም። መላው የሰሜን መለዮ ለባሽ፣ ፖሊሱ፣ የባሕርኃይሉ፣ የአየር ኃይሉና መላው የሁለተኛ ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር በጠቅላላ ሻለቃ መንግሥቱን የምናነጋግራቸው የኤርትራ ጉዳይ ስለአለ መጥተው ያነጋግሩን በማለት ላይ ናቸው» አሉኝ።

ታዲያ ምን አደረጋችሁ ብዬ ስጠይቃቸው «ጦሩ ያቋቋመው ኰሚቴ ጥያቄውን ያቀረበው ለኰሎኔል ኃይሉ ስለ ነበርና የጥያቄያቸውንም ዝርዝር የሚያውቀው እሱ ስለሆነ ለጓድነትህ እንዲያመለክት ነግሬው የነገረህ መሆኑን ስላሳወቀኝ የአንተን ውሳኔ እየተጠባበቅን ነው» አሉኝ።

ከኔ ምንም የሚጠበቅ ነገር የለም። ጀነራል የጨዋታና የቀልድ ዘመን ሳይሆን ሥር ነቀል በሆነ ሕዝባዊ አብዮት ውስጥ ያለን ሰዎች ስለሆንን እንደሚያውቁት አብዮታዊ መፈክራችን ሁሉም በያለበት ለአብዮቱ ዘብ ይቁም ነውና በእነዚህ ማንንም በማይወክሉ ጋጠ ወጥ የአየር ወለድ የበታች ሹማምንቶች ኰሚቴ ላይ አስፈላጊውን የሥነ ሥርዓት እርምጃ ወስዳችሁ ውጤቱን አሳውቁን ብያቸው ስልኩን ዘጋሁ።

በዚያው ዕለት ለሊቀመንበር ጀነራል ተፈሪ ደውለው ምን እንደአሏቸው አላውቅም ጀነራል ተፈሪ ቢሮዬ መጥተው «ይህ ጉዳይ ባለቤት አልባ ሆኖ ከቁጥጥር ውጭ እንዳይሆን በጣም እሰጋለሁና በአስቸኳይ አንድ ነገር ይደረግ» አሉኝ።

ምን ይደረግ ይላሉ? ብዬ ስጠይቃቸው አንተ የማይቻልህ ከሆነ እኔ ለመሄድ ፈቃደኛ ነኝ ስለ አሉኝ የእርሶ መሄድ አስፈላጊ መስሎ ከታየዎት ይሄዱ በማለት በሃሳባቸው ተስማማሁ።

ከአነጋገራቸውና ከጠቅላላ ሁኔታቸው መረዳት እንደሚቻለው የአመፁ ተካፋይ መሆን ቀርቶ ጀነራል ጌታቸው ስለሚያደርጉት ነገር እሳቸው የሚያውቁት ነገር የለም።

ጀነራል ተፈሪ በማዕረግ እድገት የሚገድሟቸው ወይም ብዙ የሚቀድሟቸው ቢሆንም ሁለቱ ጀነራሎች የረዥም ጊዜ ጓደኞች ስለሆኑ ያመፀው ጦሩ ሳይሆን ጀነራል ጌታቸው ናቸው ብየ ልነግራቸው አልፈለግሁም።

ጀነራል ጌታቸው ናደው መላውን የሰሜኑን መለዮ ለባሽ የሚወክል ነው ብለው በሚነግሩን የበታች ሹማምንት ኮሚቴ ውስጥ ከጀነራል ጌታቸው ሰዎች በጣም የላቀ ማህበራዊ ንቃት ያላቸውና ለአብዮቱ ዘብ የቆሙ የፓርቲያችንና የሠራዊቱ ደህንነት ጥበቃ አባል የሆኑ ጓዶቻችን ነበሩበት።

ጀነራል ተፈሪ በንተ አስመራ በመሄድ ጀነራል ጌታቸው ናደው የሁለተኛው ዋሊያ ክፍለ ጦር አዛዥና ሌሎችም ከፍተኛ መኰንኖች በተገኙበት በአስመራ ቤተመንግሥት የበታች ሹማምንቱን ኰሚቴ ጠርተው ለማነጋገር ሲሞክሩ ከኰሚቴው መሀከል አንዱ ቀንደኛ የጀነራል ጌታቸው መሣሪያ የሆነ የበታች ሹም ከተቀመጠበት ተነስቶ በጎላ ድምፅ «ክቡር ጀነራል የምንወክለው የሰሜን ኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ የጠራው የደርጉን መሪ እንጂ እርስዎን ስለ አይደለ ጊዜዎን በከንቱ ባያባክኑ መልካም ነው ብዬ ሃሳብ አቀርባለሁ» ብሎ ሲቀመጥ የተቀሩትም የኰሚቴው አባላት አዎ በማለት መደገፋቸውን ገለፁ።

ጀነራል ተፈሪ የደርጉ ሊቀመንበር እኔ ነኝ ብለው ሲገልፁ ሌላው የበታች ሹም ተነስቶ « ክቡር ጀነራል የደርጉ መሪ ሻለቃ መንግሥቱ እንጂ እርሶ ያለመሆንዎ የአደባባይ ምስጢር ነውና ከኔ በፊት የተናገረው ጓድ እንዳለው እኔም በከንቱ ወርቃማ

ጊዜዎን አያባክኑ የሚል ሃሳብ አቀርባለሁ» ሲል ሌሎቹም እንደዚሁ እየተነሱ ብዙ ሕገ ወጥ የብልግና ንግግር ተናገሯቸው።

ሁኔታው ሊ.ቀ መንበር ተፈሪን የሚያሳፍርና የሚያዋርድ ቢሆንም በታወቀ ትዕግሥታቸው የበታች ሹማምንቱን ሃሳብ ለማስለወጥ ብዙ ሙከራ ካደረጉ በኋላ ለዛሬ እዚህ ላይ እናቁምና እናንተም ወደ የሠፈራችሁ ሄዳችሁ እንደገና መክራችሁ የሚያስማማን መፍትሔ ይዛችሁ እንደምትመለሱና ዳግም እዚሁ እንደምንገናኝ ተስፋ አደርጋለሁ በማለት ከአሰናበቷቸው በኋላ ስልክ ደውለው የደረሰባቸውን ውርደት ካስረዱኝ በኋላ ሰዎቹ እኔ የምለውን ሊያዳምጡና ሊቀበሉ ቀርቶ ከኔ ጋር ለመነጋገርም ፍላጎት የላቸውምና ምን ባደርግ ይበጃል ትላለህ? ብለው ጠየቁኝ።

ስለ ደረሰባቸው ነገር በጣም ማዘኔን ከገለፅኩላቸው በኋላ ከሻለቃ መንግሥቱ ኃላፊነትና የሥራው ባህሪ ሌላ ቡተለይ በአሁኑ ጊዜ አሥመራ ለመምጣት ስለማይችል የኰሚቴው አባላት በሙሉ አዲስ አበባ ብትሄዱ ተቀብሎ ሊያስተ ናግዳችሁና ሊያነጋግራችሁ ደስተኛ ነው ብለው ይንገሯቸውና ይህንን የማይቀበሉ ከሆነ እኔ በስልክ አነጋግራቸዋለሁ የሚል ሃሳብ አቅርቤ ተስማማን።

ከኰሚቴው ጋር ለሁለተኛ ጊዜ ተገናኝተው ሃሳባቸውን ለውጠው እንደሆነ ሲጠይቋቸው ጡሩ የሰጠን ተልዕኮ ስለሆነ በኛ ሥልጣን የምንለውጠው ነገር ሊኖር አይችልም የሚል መልስ ሰጡ።

«ሻለቃ መንግሥቱ ሊመጣ ያልቻለው ፋታ በማጣት በሌላ ትልቅ ሥራ በመጠመዱ ነው። ኰሚቴው በሙሉ አዲስ አበባ ሄዶ ሊያነጋግረው ፈቃደኛ ቢሆን ለማነጋገር በጣም ደስተኛ ነው» ሲሏቸው ሻለቃ መንግሥቱ እንዲያነጋግሩት የሚፈልገው ጠቅላላውን የክልሉን መለዮ ለባሽ እንጂ እኛን ስላልሆነ እዚህ መምጣታቸው በግድ አስፈላጊ ነው በሚለው አቋማቸው ፀኑ።

ጀነራል ተፈሪ «የኰሚቴው አቋም ይህ ከሆነ ከመሃከላችሁ አንድ ሰው ምረጡና ሻለቃ መንግሥቱን በስልክ ያነጋግረው» ብለው ያቀረቡት ሃሳብ ተቀባይነትን ስለአገኘ ኰሚቴው የመረጠውን የበታች ሹም ከዚህ በሚከተለው ሁኔታ አነጋገርኩት።

"ደርግ ያለበትን ውጥረትና ጊዜ የማይሰጥ የሥራ ሸክም ሊ.ቀመንበር ጀነራል ተፈሪ አስረድተዋችኋል ብዬ አምናለሁ። ከአብዮቱ ፍንዳታ ማግሥት በተለይም የአሮጌው ሥርዓት ቁንጮ የሆነው ዘውድ ከተገረሰሰበት ጊዜ ጀምሮ በኦጋዴን ያሉት የአንበሳው ክፍለ ጦር አካል የሆኑ የጦር ክፍሎችና በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኘው የአራተኛ እግረኛ ብርጌድ ጦር በመደጋገም እንድጎበኛቸውና የሚኖሩበትን ሁኔታ ተመልክቼ በጥቂቱም ቢሆን ችግሮቻቸውን እንዳቃልልላቸው ጠይቀውኝ ልጎበኛቸው ባለመቻሌ ተስማምተን ያገኘነው መፍትሔ፤ ጡሩ ከመሀከሉ አወጣጥቶ ከሚልካቸው ወኪሎቹ ጋር ተገናኝተን መወያየት ነው።

እንደሚታወቀው ንፁህና ቀዝቃዛ ውሃ በማይገኝበት፣ የሕክምና አገልግሎት በሌለበት ጠፍ በረሐ ከቤተሰቡ ተለይቶ አገሩን የሚያገለግል ጦር ጥያቄ መቀበል ያልቻለኩ ሰው ኤርትራ የሚኖረው ሠራዊት አሥመራ ካልመጣ ይላል ብዬ አላስብምና ለጓዶችህ ይህንኑ አስረድተህ አዲስ አበባ ስትመጡ የማናስወግደው ችግር ይኖራል ብዬ አልገምትም።

እኔ እንዳልኩህ በዚሁ መንፈስ አስረዳና መልሱን እዚያው ለሊቀመንበር አሳውቃቸው" ስለው በዚሁ ሁኔታ አስረዳለሁ ብሎኝ የስልክ ንግግራችንን አቆምን።

ጀነራል ተፈሪ እንደነገሩኝ የበታች ሹሙ ከኔ ጋር በስልክ ከተነጋገረ በኂላ ሻለቃ መንግሥቱ ለኰሚቴው እንዳስረዳ የነገሩኝን ለመግለፅ ከሰዓት በኂላ ያለውን ጊዜ ይስጡንና ነገ ጠዋት እንድንመለስ ይፍቀዱልን ብሎ ይጠይቅና ይፈቀድላቸዋል።

በበነጋታው የኰሚቴው አባላት በሙሉ ተመልሰው በመምጣት ሻለቃ መንግሥቱ በሰጡት ትዕዛዝ መሠረት ኰሚቴው አዲስ አበባ ለመሄድ መስማማቱን ይገልፁና ጀነራል ተፈሪ ራሳቸው ከመምጣታቸው በፊት አሥመራ እንዳሉ ኰሚቴውን ወደ አዲስ አበባ በአየር መጓጓዣ ላኩልን።

የደርግ አባልና የኔ የቅርብ ረዳት የሆነው ሻምበል መንግሥቱ ገመቹ ከአውሮፕላን ማረፊያ በመቀበል በጥሩ ሆቴል አሳረፋቸው።

አዲስ አበባ በገቡበት ቀን በምሽቱ ሻምበል መንግሥቱ ለኰሚቴው አባላት የበታች ሹማምንቶች ጥሩ የእራት ግብዣ አድርጎላቸው ከእራት በኂላ እየጠጡ በሚዝናኑበት ጊዜ ሻለቃ መንግሥቱን ኤርትራ የሚያስጠራ ምን ጉዳይ እንደነበራቸው ሲጠይቃቸው፣ የአየር ወለድ ሻለቃ ባልደረቦች ማን እንዲህ ብሎ ነገራችሁ ብለው አይጠይቁን እንጂ በደብረዘይት ቀሪ የአየር ወለድ ሻለቃ ጠቅላይ ሠፈር አባላትንና መላውን የጦሩን ቤተሰብ ደርግ በነበልባል ጦር አስፈጃቸው ተብሎ ስለተነገረን በተሰማን ጥቃትና መሪር ብሶት ምክንያት ነው ሲሉ የተቀሩት ማለትም የሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር አባል የሆኑት፣ ደቀ መሐሪ ላለው ጦር ከአሥመራ የሚላከውን ወርሐዊ ቀለብ አጅቦ ሲጓዝ በነበረው የአንድ ሻምበል ጦር ላይ ሻዕቢያ በመንገዱ ግራና ቀኝ ደፈጣ አድርጎ ተሽከርካሪዎቹን በሙሉ በፀረ-ታንክ መሣሪያ ከነወታደሩ ስለ አጋያቸው በተሰማን ብስጭት ነው። በማለት እጅግ የሚያሰቅቀውን የወንድሞቻችንን የነደደና የከሰለ አፅም ፍቶግራፍ ለማሳየት ይዘን መጥተናል በማለት የነገሩትን በበነጋታው ሻምበል መንግሥቱ ነገረኝ።

በጠየቁት ጥያቄ መሠረት ያመጡትን አሳዛኝ ፍቶ ግራፎች ለደርጉ ስብሰባ ከማሳየታቸው በፊት ደርግ በነበልባል ጦር አስፈጃቸው ተብሎ ስለተነገራቸው መሠሪና የሐሰት ወሬ የሆነውን እንዲረዱ ከሻምበል መንግሥቱ ገመቹ ጋር ሁሉንም ወደ ደብረ ዘይት ላክናቸው።

በነበልባል ጦርም ሆነ በአየር ወለድ ጦር አንድ ጥይት እንዳልተተኰሰ፣ የሞተ ቀርቶ ከወታደሩም ሆነ ከጦሩ ቤተሰብ መሃከል አንድም ሰው እንዳልቆሰለ በመረዳት በማዘንና በመገረም ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው በሆቴላቸው አደሩና በአራተኛው ቀን ያመጡትን ፎቶ ግራፍ ለደርጉ አባላት እንዲያሳዩና ለደርጉ የሚገልፁት ነገር ካለም እንዲገልፁ አደረግን።

በአሥመራ ከተማ በየጦር ሠፈሩ እየተዘዋወሩ ሁለተኛ ዙር ሬቮሉሽን ለማካሄድ ተነስተናል በማለት የደርግን መንግሥት ለመገልበጥ የተነሱት ሰዎች ከደብረዘይት መልስ በኋላ በደርጉ አዳራሽ ያደረጉት ነገር ቢኖር ያመጡትን በእርግጥም እጅግ አሳዛኝ የነደደ የወንድሞቻችንን አፅም ፎቶ ግራፎች ማሳየትና ስለተቀረው ስህተታቸው ደርጉን ከፍ ያለ ይቅርታ መጠየቅ ነበር።

በእኛም በኩል ያንን የመሰለ ፀረ-አብዮት አመፅ ለዚያውም ኤርትራ ውስጥ እጅግ በምናከብረውና ከምናምነው ታጋይ ሠራዊት ሕሊና እንዳልመነጨ የምናውቅ መሆናችንን አስረድተን በተፈጠረው አጋጣሚ ደርግ ጽሕፈት ቤት ከተገኙ ዘንድ ስለ ሥር ነቀሉ ሕዝባዊ አብዮት ዓላማና ስለደርጉ ተልዕኰ ስለ አገሪቱ ጠቅላላ ፖለቲካዊ ኢኰኖሚያዊ፣ ወታደራዊ ሁኔታና በተለይም በምሥራቅ ኢትዮጵያ ጎረቤታችን የሱማሌ መንግሥት በሚያደርገው የወረራ መሰናዶ ያለብንን ሥጋት ከማስረዳት ሌላ በሰሜንም ያለብንን ችግር ቢቻል ፈፅሞ ለማስወገድ ባይቻል ለማቃለል የጀመርነውን የፕሮፖጋንዳ ሥራ፣ ወታደራዊ የውጊያ እቅድና የሠላም መፍትሄ ፍለጋ ጥረታችንን አስረድተን እነሱም በበኩላቸው ወደ ኤርትራ ሲመለሱ ለሠራዊቱ ይህንኑ እንዲያስረዱና አብዮታዊ ትብብራቸውን እንዲቀጥሉ በማሳሰብ ውይይታችንን አበቃን።

ከዚያም የኰሚቴው አባላት በሙሉ እኔ ዘንድ ቀርበው ለአንድ ሰዓት ያህል ከአነጋገርኳቸው በኋላ ጀነራል ተፈሪን በአሥመራ ቤተመንግሥት በነበረው ውይይት ላይ በጣም ያሳዘኗቸው ስለሆነ ቢሮአቸው ሄደው ይቅርታ እንዲጠይቁ ከተደረገ በኋላ፣ ለራሳቸውም ሆነ ለልጆቻቸው ወይንም ለቤተሰቦቻቸው አንዳንድ ነገር የሚገዙበትና እነሱም በአዲስ አበባ እስከቆዩ ድረስ ችግር ሳይገባቸው በመጠኑ የሚዝናኑበት ጥቂት ገንዘብና የአንድ ሳምንት ፈቃድ ሰጥተን አሰናበትናቸው። የብ/ጀነራል ጌታቸው ናደው ፀረ-አብዮት ሴራም በዚሁ አበቃ።

የደርግን ሥራ አስፈፃሚ ኰሚቴ ስብሰባ ጠርቼ ሊቀመንበሩ ስብሰባውን እየመሩ በጀነራል ጌታቸው ናደው ስለተመራው ፀረ-አብዮት አመፅ ሙከራ የሚያትትና ብሎም አመፁ መክሸፉን የሚያበስረውን አጀንዳ አቅርቤ ምን ይደረግ? የሚል ጥያቄ ባቀረብኩበት ጊዜ ነበር በምስጢር ተይዞ የነበረውን ጉዳይ ሊቀመንበሩን ጨምሮ የደርጉ ሥራ አስፈፃሚ ኰሚቴ አባላት ለመጀመሪያ ጊዜ የሰሙት።

በደርጉ አባላት ዘንድ ጀነራል ጌታቸው ይህንን የመሰለ ክህደትና ፀረ-አብዮት ድርጊት ይፈፅማሉ ተብሎ የማይታሰብ ከመሆኑ ሌላ ድርጊቱም አንድ ጤናማ አእምሮ ያለው ሰው የሚፈፅመው ተግባር ስለ አይደለ በጣም ነው ያስገረማቸው።

በቀረበው አጀንዳ ላይ ከተወያየን በኋላ ምን ይደረግ? ለተሰኘው ጥያቄ መልስ ፍለጋ ስናመራ ጀነራል ተፈሪ እኛ በችኮላ እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት በትዕግሥት ጥቂት ጊዜ እንሰጠውና የእሱን እምነትና ክህደት ወይንም ከዚህ በኋላ የሚለውንና የሚያደርገውን ብንጠብቅ ጠቃሚ ይመስለኛል የሚል ሃሳብ ስለ አቀረቡ በእሳቸው ሃሳብ ሁላችንም ተስማማን።

ከኤርትራ ገንጣዮች ጋር የጋራ ችግራችንን በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል የውይይት መድረክ የሚፈጥሩ ቅድመ ሁኔታዎችን የማዘጋጀት ተልዕኮ የተሰጣቸው ልዑካን ስለ አከናወኑት ተግባርና ስለ ደረሱበት ሁኔታ እየተከታተሉ ያሳውቁናል ብለን የምንጠብቃቸው ሰው ምንም ነገር ሳያሳውቁንና በተለይም የእሳቸው ዋና የሥራ ድርሻ የሆነውን ወታደራዊ ጉዳይ በተመለከተ ምንም ነገር ሳያደርጉ፣ ፈቃድ ሳይጠይቁና ወይንም ሳያሳውቁ አዲስ አበባ መጥተው የራሳቸው በሆነው መኖሪያ ቤታቸው መቀመጣቸውን ለማወቅ የቻልነው በአገር ደህንነት ሰዎቻችን አማካኝነት ነው።

ጀነራል ተፈሪ ፈቃድ ሰጥተዋቸው ነው ብዬ በማመን የመጡበት ምክንያት ለዕረፍት ነው ወይስ በቤተሰብ በኩል የገጠማቸው ችግር አለ? ለምን ያህል ጊዜ ነው ፈቃድ የሰጧቸው ብዬ ስጠይቃቸው ፈቃድ ሊሰጡ ቀርቶ አዲስ አበባ ስለመምጣታቸው ከኔ ነው የሰሙት።

የሀገር ደህንነቱን ሚኒስትር ጓድ ኮሎኔል ተስፋዬ ወልደሥላሴን ጠርቼ ስለ ጀነራል ጌታቸው አዲስ አበባ የመምጣት ምክንያትና ከመጡም በኋላ ምን እያደረጉ እንደሆነ ብቻ ሳይሆን ስለጤንነታቸው ጭምር የሚያውቀው ነገር እንዳለ ጠየቅሁት።

በእሱ ግምት ጀነራሉ አዲስ አበባ የመጡት የበላይ አካልን አስፈቅደው ለዕረፍትና ቤተሰባቸውን ለመጎብኘት ነው ብሎ ያስብ እንደነበረና እቤታቸው ተቀምጠው በተለይ በምሽት ለነ ሻለቃ ሲሣይና ለነ ሻለቃ ኪሮስ አለማየሁ ወዘተ እየደወሉ ምን አዲስ ነገር አለ ብለው ከመጠየቅ ሌላ ከደርግም ውጭ ለብዙ ሲቪል ግለሰቦችና መለዮ ለባሾች እየወደሉ መነጋገራቸው መደመጡንና በደህንነቱ የመረጃ ግኝት፣ ጀነራል ጌታቸው አመፁን የሞከሩት ብቻቸውን እንዳልሆነና የባዕዳንም እጅ እንዳለበት ገልፆ የጀመሩት አመፅ ከሽፏል ተብሎ የተሳሳተ ግምት እንዳይወሰድ አሳሰበኝ።

ኮሎኔል ተስፋዬ የሰጠኝን መረጃና እንዲሁም ማሳሰቢያ ለጀነራል ተፈሪ ከገለፅኩላቸው በኋላ ምን ማድረግ እንደሚገባ የእሳቸውን ሃሳብ ብጠይቃቸው አሁንም

ትዕግሥታችንን ሳንጨርስ አንተም እኔም እቤቱ ስልክ ደውለን እናነጋግረው በስልክ የማይገኝ ከሆነ ደግሞ ቤቱ ሰው እንላክና ያለበትን ሁኔታ እንረዳ አሉኝ።

በዚህ ተስማምተን ሁለታችንም ለአንድ ቀን በመደጋገም ስልክ ስንደውል ራሳቸው ጀነራል ጌታቸው ይሁኑ ወይም ሌላ ሰው እንደሆነ አይታወቅም ስልኩን እያነሳ እኛን በማዳመጥ መልስ ሳይሰጥ እየዘጋ ስለአስቸገረ የደርጉ ጥበቃ ብርጌድ የዘመቻ መኰንን የሆነውን ሌ/ኰሎኔል ዳንኤልን ላክነው።

ዳንኤል በኢ.ህ.አ.ፓ የሞት ፍርድ ከተፈረደባቸው አብዮታውያን አንዱ በመሆኑ በማናቸውም የሥራ ጉዳይ የሚንቀሳቀሰው በታጠቁ ወታደሮች ታጅቦ ስለነበረ ወደ ጀነራል ጌታቸው ቤት የሄደውም ከሁለት የታጠቁ ወታደሮች ጋር ነበር።

በተሽከርካሪ ቤታቸው ደርሶ የአጥር ግቢው በር እንዲከፈትለት መጥሪያ ደጋግሞ ቢደውል የሚመጣ ሰው ስለ ታጣ አንዱ ወታደር አጥሩን ዘሎ በመግባት በሩን ከውስጥ ከከፈተላቸው በኋላ ገብተው ወደ ቤት ሲያመሩ ጀነራል ጌታቸው የቤታቸውን ፊት ለፊት መስኮት በመክፈት በመስኮቱ ደፍ ላይ መትረየስ ጠምደው ተኩስ በመክፈታቸው ኰሎኔል ዳንኤልና ሁለቱ ወታደሮች መሬት ይዘው ራሳቸውን ለመከላከል በሰጡት የተኩስ መልስ ጀነራሉ ተመተው ወደቁ።

ኰሎኔል ዳንኤል ቤቱ ውስጥ ገብቶ የተደናገጠውን ቤተሰብ ካጥናናና የጀነራል ጌታቸውን መሞት ከተረዳ በኋላ ወደ ደርግ ጽሕፈት ቤት በመመለስ ስለገጠመው ሁኔታና ስለ ጀነራል ጌታቸው ማረፍ ለደርጉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ባስረዳው መሠረት በምሽቱ የዜና ማሠራጫ ጊዜ ጀነራል ጌታቸው ናደው ከፀረ-አብዮት ተግባራቸው ጋር ማረፋቸው ለሕዝቡ ተገለጠ።

በበነጋታው የወንጀሉ ተባባሪና በደርጉ ውስጥ የመረጃ ወኪላቸው የነበሩት የመቶ አለቃ ስለሺ በየነና የመቶ አለቃ በዕዉቀቱ ካሣ ወደ ጎጃም ክፍለ ሃገር ኰብልለው በመሄድ በቢቸና አውራጃ ውስጥ ሽፍታ አደራጅተን ደርግን ልንወጋ ነው የመጣነው እያሉ ሲያወሩ የሰማ የገበሬ ማህበር ይዞ ሁለቱንም ገደላቸው።

የወንጀሉ ተባበሪ መሆን ብቻ ሳይሆን የአመፁ ቀንደኛ መሪዎች የነበሩት ሻለቃ ሲሣይ ኃብቴና ሻለቃ ኪሮስ አለማየሁ በቁጥጥር ሥር ሲወሉ አሥመራ ከተማ የሚገኘው አየር ወለድ ጦር ተሸበረ።

የደርግን መንግሥት ለመገልበጥ ሲካሄድ የነበረው ፀረ-አብዮት ሴራ መክሸፍና የጀነራል ጌታቸው ናደው በድንገት መሞት፤ የሴራው ተባባሪ ከሆኑት የደርግ አባሎች መሃከል የሁለቱ መኰንኖች መኮብለል፣ የሁለቱ መታሰርና ሌሎቹ በመፈለግ ላይ መሆናቸውን በመስማትና እነሱ የሴራው ጠንሳሽና ቀንደኛ ተባባሪ መሆናቸው

ከማንም በላቀ ተጠያቂ እንደሚያደርጋቸው ስለሚያውቁ አብዛኛው የሻለቃው ጦር ማለት በተለይም አብዛኛው መኰንኖች ክፉኛ ተደናገጡ።

የጀነራል ጌታቸው ምኞት ቀንደኛ አስፈፃሚዎችና የሴራው ጠንሳሽ የሆኑት በአስመራ ከተማ ባሉት የጦር ሠፈሮች ውስጥ እየሮጡ፣ ሁለተኛውን ሬቮሉሽን ዳግም ጀምረናል፤ የደርግ መንግሥት ለማውረድ ወስነን ተነስተናልና ተባበሩን ሲሉ የሚሰማቸውና የሚያስተውላቸው የከተማው ነዋሪ ሠራዊት ሳይወክላቸው በስሙ ፀረ-አብዮት ተግባር ማከናወናቸውንና የሟቹ የጀነራል ጌታቸው ናደው መሣሪያ መሆናቸውን የተገነዘበው ሠራዊት በትዕዝብት እንደ እብድ ውሻ ነበር የተመለከታቸው። የሚከተላቸው ጦር ባይኖርም የሚያደርጉትን ወታደራዊ ሥነ-ሥርዓትና ግብረ ገብነት የጎደለው ብልግና ለሕዝብ ማሳየታቸው ሠራዊቱን የሚያሳፍር ስለነበር የሁለተኛ ዋሲያ እግረኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ኰሎኔል ኃይሉ ገብረሚካኤል፣ አየር ወለዱ ሻለቃ ጦር በሙሉ ጓዙን አንስቶ ወደ መንደፈራ እንዲሄድና የ30ኛውን እግረኛ ሻለቃ ጥበቃ እንዲረከብ ትዕዛዝ ሰጡ።

ይህንን እርምጃ ለጊዜው ራሳቸው ወሰዱ እንጂ ለኛ አላሳወቁንም። ክልሉ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚተዳደር የጦር ሜዳ ስለሆነ የሠራዊቱ አባሎች በግልም ሆነ በወል የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ መጋፋትና ያለመፈፀም በህግ የሚደርስባቸው ቅጣት ህይወትን እስከመክፈል የሚያደርስ መሆኑን የሚያውቁት የአየር ወለድ ሻለቃ አዛዥና መላው ጦር ትዕዛዙን ተቀብሎ ጉዞውን ወደ መንደፈራ ቀጠለ። መንደፈራ የስራዬ አውራጃ ከተማ ሲሆን ከአስመራ ከተማ በኔ ግምት ከስልሳ እስከ ሰማኒያ ኪሎ ሜትር ይርቃል።

የሻለቃ አዛዡ ሌ/ኰሎኔል አለማየሁ አስፋው በተሽከርካሪ የሚጓዘውን የሻለቃውን ጦር ጉዞ ጀፕ ተሽከርካሪ ላይ ሆኖ እየመራ ከመንደፈራ ከተማ ቅጥርና ከ31ኛ እግረኛ ሻለቃ መኖሪያ ሠፈር ውጭ አልፎ የመረብን ወንዝ በመሻገር በአድዋ በኩል ወደ መሀል አገር በሚወስደው አስፋልት መንገድ ቀኝ ጠርዝ ላይ ቆሞ የሻለቃው ጦር በሙሉ ከተሽከርካሪዎቻቸው ላይ ወርደው በአንድ ሥፍራ እንዲሰበሰቡ አደረገ። የቆሙበት ሥፍራ ከኤርትራ ክልል ውጭ ከመሆኑ ሌላ በኤርትራ ደቡብና በትግራይ ሰሜን ክልል የመሸገው የሻዕቢያ ይዞታ ነው።

ደርግ በተቋቋመ ማግሥት ጀነራል አማንን በቅድሚያ የደርጉ ሊቀመንበር ከዚያም የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹምና የመከላከያ ሚኒስትር ከማድረግ በላይ ደርግን ወክለው እንደ አገሪቱ ርዕሰ ብሄር እንዲሰሩ በማድረግ፣

ብ/ጀነራል ተፈሪ በንቲን የደርጉ ሊቀመንበር ማድረግና ብ/ጀነራል ጌታቸው ናደውን በቅድሚያ፣ የምድር ጦር አዛዥ በኋላም የኤርትራ ክፍለ ሃገር አስተዳዳሪና የመላው የሰሜን መለዮ ለባሽ ሠራዊት አዛዥ በማድረግ ረገድ የተሰራው ታላቅ ስህተት የማንም ሳይሆን የእኔ ነበር።

በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የአየር ወለድ ሻለቃ ጦር አዛዥ ከነበሩት ከሻለቃ መኮንን ሙላት በኋላ ጀነራል ጌታቸው ናደውን የተረከቡት ኰሎኔል አለም ዘውድ በአብዮቱ አጥቢያ ከሠራዊቱ በደረሰባቸው ተቃውሞ አዛዥነታቸውን ትተው ወደ ጎጃም ክፍለ ሃገር በኰበለሉ ጊዜ ለአየር ወለድ ሻለቃ አዛዥነት ይገባሉ ተብለው በእጩነት በደርግ የመከላከያ ኰሚቴ የቀረቡልኝ ሦስት መኰንኖች ነበሩ።

እነሱም፦ 1. ኰሎኔል ዘውዴ ገብረየስ

2. ሌ/ኰሎኔል አበራ አበበ

3. ሻለቃ ክፈተው መርኔ ሲሆኑ ሌ/ኰሎኔል አለማየሁ አስፋው በእጩነት እንኳ የተመረጠ አልነበረም።

ኰሎኔል ዘውዴ ገብረየስና ሌ/ኰሎኔል አበራ አበበ ከሻለቃ አዛዥነት በላቁ ከፍተኛ የጦር ክፍሎች እንዲያዙ የታጩ ሰዎች ስለነበሩ ከምርጫው ሠርዘን የቀረን ሻለቃ ክፈተው መርኔ ለአየር ወለድ ሻለቃ ጦር አዛዥነት በጣም ተገቢ መኰንን ሆኖ ቢገኝም በኤርትራ ከገንጣዮች ጋር በሚደረገው ፍልሚያ በተደጋጋሚ ለብዙ ጊዜ ብዙ የጦር ሜዳ ጀብዱ ያስመዘገበና በሰሜኑ ጦር ውስጥ ታላቅ ስም ያተረፈው የ31ኛ እግረኛ ሻለቃ አዛዥ ስለነበርና በዚያን ጊዜ እሱን የመሰለ መኰንን በኤርትራ እጅግ የሚያስፈልገን ከመሆኑ በላይ የሚያዘው ክፍል ብቻ ሳይሆን መላው የሰሜኑ ጦር በጣም የሚወደውን ጀግና መኰንን ከእዚ ማንሳቱ ስለከበደኝ በእሱ ፋንታ ሌ/ኰሎኔል አለማየሁ አስፋው እንዲሆን ለኰሚቴው ሃሳብ አቀረብኩ።

የደርግ የመከላከያ ኰሚቴ አብዛኛው አባላት ብዙ ምክንያቶችን በመደርደር አለማየሁን የአየር ወለድ ሻለቃ ጦር አዛዥ የሚያደርገው ወታደራዊ ግልጋሎትና ብቃት የሌለው፣ በመከላከያ ሚኒስቴር ሕንፃ ውስጥ ከአንዱ መምሪያ ወደ ሌላው በመዘዋወር የጀነራል መኰንኖች ተላላኪ በመሆን ያደገ እንጂ ምንም ዓይነት የጦር አመራርና የውጊያ ልምድ የሌለው ነው። ለአብዮቱ መታመኑንም እንጠራጠራለን። በማለት ሲቃወሙ በያዘው ማዕረግ ተላላኪ መሆን የእሱ ጥፋት ሳይሆን ተላላኪ ያደረጉት ጀነራሎች ጥፋት ስለሆነ የእነሱን ስህተት እኛ መድገም የለብንም።

በእድሜው ወጣት ነው። ከብሪታኒያ መንግሥት የምድር ጦር ሠራዊት የመኰንኖች ማሰልጠኛ አካዳሚ ከሳንድኸረስት የተመረቀና የተማረ ልጅ ስለሆነ እድል እንስጠውና እንሞክረው ብዬ የአየር ወለድ ሻለቃ አዛዥ በማድረግ ሌላ ስህተት ሠርቻለሁ። የአየር ወለዱን ሻለቃ ጦር ከተሽከርካሪ አስወርዶ አንድ ቦታ ላይ በመሰብሰብ ንግግር ሊያደርግ ሲዘጋጅ ከመናገሩ በፊት የመንደፈራ ከተማንና የ31ኛ ሻለቃን ሠፈር አልፈው ትግራይ ጠረፍ ድረስ የመጡበት ምክንያት የክዳት አዘማሚያ መሆኑን የተረዱ፣ በሴራው ውስጥ ያልነበሩና በሴራውም የማያምኑ መኰንኖች መንደፈራን አልፈን እዚህ ድረስ የመጣንበት ምክንያት ምንድን ነው? ብለው

ሲጠይቁት «እንደሰማችሁት ጀነራል ጌታቸውና ሌሎችም የመፈንቅለ መንግሥት ተባባሪዎች በአዲስ አበባ ተመትተዋል፡፡ የተቀሩትም እየታደኑ ስለሆነ የእኛም ደሕንነት በቀናት የሚቆጠር ጉዳይ ብቻ ነው፡፡ ከእንግዲህ ወዲያ ለኛ ለአየር ወለዶች ደርግ በሚመራው መከላከያ ሠራዊት ውስጥ ቦታ የለም፡፡ ከደርግ ጋር የሚያኖረን ሁኔታ አብቅቷልና ያለን እድል ከኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ከ(ኢ.ህ.አ.ፓ) ሠራዊት ጋር ተቀላቅለን ደርግን መታገል ብቻ ነው» አለ ነው የተባለው፡፡

የሌ/ኰሎኔል አለማየሁ አስፋውን ንግግር ያዳመጡት ጥቂት መኰንንኖችና አብዛኛው የሻለቃው ጦር «በርስዎ ሃሳብ አንስማማም እርሶና ግብረ አበሮችዎ ስታውጠነጥኑ ለነበራችሁት ፀረ-አብዮት ሴራ ተካፋይ አልነበርንም፣ የአንድ ግለሰብ መሣሪያና ሎሌ አልነበርንም፣ አይደለንም፡፡ እኛ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አካል ብቻ ሳንሆን የኢትዮጵያ በራሪ ነብሮች ስለሆንን (የኢ.ህ.አ.ፓ) ጆሌ በመሆን አገራችንንና አብዮታችንን አንወጋም» የሚል መልስ ሲሰጡት «እኔን የምትከተሉ በስተቀኝ እኔን የምትቃወሙ በስተግራ ተሠለፉ» የሚል ትእዛዝ ሲሰጥ ጦሩ እንደየምርጫው ተከፋፍሎ ሲሠለፍ ተከታዮቹን ይዞ በመሄድ ከሻዕቢያ ጋር ተቀላቀለ ነው የተባለው፡፡

ክህደቱን በመቃወም እኛ የኢትዮጵያ አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊት አካልና የኢትዮጵያ በራሪ ነብሮች ነን ያሉት በሻምበል ተስፋዬ ኃብተማሪያም በኋላ ብ/ጀነራልና የሕብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ብሄራዊ ጀግና አመራር ወደ መንደፈራ ከተማ ከተመለሱ በኋላ ሻምበል ተስፋዬ የሆነውን ነገር በቀጥታ ለክፍለ ጦሩ አዛዥ ለኰሎኔል ኃይሉ ገብረሚካኤል በስልክ ሲያመለክት ኰለኔል ኃይሉም በቀጥታ ለኔ በመደወል «ሌ/ኰሎኔል አለማየሁ አስፋው የአየር ወለዱን ሻለቃ ጦር በከፊል ይዞ ወደ ሻዕቢያ ገብቷል» በማለት ስለገለፁልኝ የደርጉ ሥራ አስፈፃሚ ኰሚቴ አባል በሻምበል ብርሃኑ ባየህ የሚመራ የደርግ ልዑካን ወደ መንደፈራ ላኩ፡፡

ጓድ ሻምበል ብርሃኑ ከመኰንኖቹም ከጦሩም አብዛኛዎቹን ስለሚያውቃቸው አረጋግቶና በእነሱ ላይ ምንም ዓይነት እርምጃ እንደማይወስድ ከመግለፅ ባሻገር አለማየሁ ሊያፈርስ የሞከረው ሻለቃ በቅርብ ጊዜ ውስጥ በብርጌድ ደረጃና ብሎም በክፍለ ጦር ደረጃ እንደሚደራጅ ከአስረዳ በኋላ ከክፍለ ጦሩ አመራር አካላት ጋር በመመካከር በቅድመ አብዮት የአየር ወለዱ ሻለቃ ባልደረባ የነበረ ሻለቃ ሽባባው ዘለቀ የሚባል ጀግና መኰንንን የሻለቃው አዛዥ በማድረግ ተመለሰ፡፡

ክፍል አስራ ዘጠኝ

ምዕራፍ ሰላሣ ሦስት

ገንጣዮች የውጊያ ሥልታቸውን በመለወጥ ደረጃ በደረጃ በሠራዊታችን ላይ ተከታታይ ጥቃት መሰንዘርና ብሎም የክፍለ ሃገሩን ርዕሰ ከተማ አሥመራን መክበብ።

ራሳቸውን «ጀብሐና ሻዕቢያ» ብለው የሚጠሩት አገር ገንጣዮች፤ ጀነራል አማን በአመቻቹላቸው ሁኔታዎች ተጠቅመው ጥቅምት 17 ቀን 1967 ዓ.ም አሥመራን ለመያዝ ሙከራ አድርገው አብዮታዊ ሠራዊታችን በመልሶ ማጥቃት ውጊያ አይቀጡ ቅጣት ቀጥቶ ከመለሳቸው በኋላ እንደገና በቀላሉ እንዳያንሰራሩ የታቀደውን ተከታታይነት ያለው የዘመቻ እቅድ ብ/ጀነራል ጌታቸው ናደው ተግባራዊ ካለማድረግ ሌላ መንግሥት የመገልበጥ ሴራ ሲያዉጠነጥኑና ሠራዊቱን ሲበጠብጡ በሰጧቸው ሰፊ ጊዜ ተጠቅመውና እንደገና ተደራጅተው ወትሮ ከሚያደርጉት ተንኩሶ ከመሸሽ ፋንታ ቆመው የመንግሥቱን ወታደር በውጊያ ከመጋተር አልፈው አንዳንድ ጠቃሚ ሥፍራዎችን፣ የልማት ድርጅቶችን፣ መንገድና ድልድዮችን ወዘተ በአነስተኛ የሰው ኃይል በየቦታው ይጠብቁ የነበሩ ፖሊሶችንና የጦሩን አባሎች እየከበቡ ተራ በተራ መደምሰስ አዘውተሩ።

ጀብሐ በሕዳር ወር 1968 ዓ.ም በኤርትራ ምዕራባዊ ቆላማ ክልል በጋሽና ሰቲት አውራጃ ከተማ በተሰነይ የሚገኘውን የወገንን 24ኛ እግረኛ ሻለቃ ጦር በድንገት ከቦ ከነጦር ሠፈሩ ደመሰሰ።

በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ በዘመናዊው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ታሪክ በ1937 ዓ.ም በሐረርጌ ክፍለ ሃገር በአዳልና ኢሳ አውራጃ የኢሳ ማህበረሰብ አማፂያን በ12ኛው እግረኛ ሻለቃ ጦራችን ላይ ከአደረሱት አደጋ ወዲህ ይህንን የመሰለ አደጋ አገራችን ሲያጋጥማት ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር።

የተሰነይ ከተማ ከሰላ ከሚባለው የሱዳን መንግሥት የጠረፍ ከተማ ትይዩ በቅርበት የሚገኝ የኢትዮጵያ የጠረፍ ከተማ ሲሆን ከአስመራ ከተማ ርቀቱ በኔ ግምት ከሁለት መቶ ኪሎ ሜትር በላይ ይሆናል።

የጋሽና ሰቲት አውራጃ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ በአመዛኙ ሜዳማ በመሆኑ የሰቲት ከተማ የተገነባችው አውላላ ሜዳ ላይ ስለሆነ ለገንጣዮች ጥቃት የተጋለጠና በጣም ያመቸ በመሆኑ ጦሩ ራሱን ለመከላከል ፍፁም አስቸጋሪ ነበር።

የ24ኛ እግረኛ ሻለቃ መምሪያ ከበላይ አካል ማለትም ከብርጌዱና ከክፍለ ጦሩ መምሪያዎች ጋር አስፈላጊውን የወታደራዊ ራዲዮ ግንኙነት እንኳን ለማድረግ

ባልቻለበት ሁኔታና ከሻለቃው ጦር እጅግ የላቀ የሰው ኃይል ይዞ በመጣ ጠላት በድንገትና በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው ተደምስሶ ውጊያው ያበቃው ተሰነይ ከአስመራ በጣም በመራቁና ውጊያውም በአጭር ጊዜ ውስጥ በማክተሙ ምክንያት ረዳት ጦር ለመላክ የሚያችል ሁኔታ አልነበረም።

የአየር ኃይላችን አባላት የ24ኛ እግረኛ ሻለቃን የጦር ሠፈርና አካባቢውን ቃኝተው ስለ ውጊያው ሁኔታ እንዲያስታውቁን በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት አስፈላጊውን ቅኝት አድርገው ያስረዱን «በጦር ሠፈሩ ውስጥ ምንም ዓይነት የሚንቀሳቀስ ነገር ወይንም ሰው ልናይ አልቻልንም። ማየት የቻልነው ጢስና የሚቃጠሉ ቤቶችን ብቻ ነው። በህይወት ያሉ የጦር አባሎች ይገኛሉ ብሎ ተስፋ ማድረግ የሚቻል አይመስለንም» በማለት ነበር።

በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ የደርጉ አመራር አካላት በየሰዓቱ የተለያዩ አሳዛኝና አስደንጋጭ መርዶዎችን መስማት የየቀኑ ዉሎአችን ባህሬ ቢሆንም የ24ኛ እግረኛ ሻለቃ ጦር በገንጣዮች መደምሰስ እጅግ አስደንጋጭ መርዶ ነበር።

አብዮቱ ለኢትዮጵያ ፍቱን መድሃኒት ነው። አብዮቱ ለኤርትራ ችግር አማራጭ የሌለው ብቸኛ መፍትሔ ነው። ችግሩ ያለውጊያ በሠላም ይፈታል ወዘተ በሚለው እምነታችን ዓይነ ህሊናችን ተጋርዶ ስለነበር ከተሰነይ በኋላም ሊከተሉ ወይንም ሊደርሱ የሚችሉትን የባሱ ወይንም የከፋ አደጋዎች ለመመልከት ስለተሳነን እንጂ የአብዮቱ ረመጥ በዚያ ዓይነት ሊለመጥጠን ገና አሐዱ ብሎ መጀመሩ ነበር።

ጀብሐ ከተሰነይ ቀጥሎ የአቆርዳትን ከተማ ከተቆጣጠረ በኋላ የባሬንቱን ከተማ መውረር ሲጀምርነው አብዮታዊ ሠራዊታችንና ሕዝቡ በሚያስደንቅ ህብረት መክተው ያቆሙት።

ምዕራፍ ሰላሣ አራት

ናቅፋ ላይ የ15ኛ እግረኛ ሻለቃ ጦር በሻዕቢያ መከበብ

ቃሮራ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ካርታ ለሚመለከት አንባቢ በኤርትራ ሰሜን ከሱዳን ጋር በሚያዋስነን ሹል የመሬት ቅርፅ ላይ የምትገኝ በጣም ትንሽ የጠረፍ ከተማ ነች። በዚህች ከተማ ትይዩ በሱዳን ውስጥ የሱዳን ቃሮራ የምትባል ሌላ ትንሽ የጠረፍ ከተማ ትገኛለች።

እነዚህ የኢትዮጵያ ቃሮራና የሱዳን ቃሮራ በመባል የሚጠሩ ተጎራባች ትንንሽ የጠረፍ ከተሞች በሁለቱ ጎረቤታማ አገሮች መካከል በአብዛኛው ህገወጥ ገበያ መለዋወጫና የሁለቱም አገሮች ሠላዮች መመላለሻ ወይንም መውጫና መግቢያ በመሆን ሲያገለግሉ ኖረው አረቦች ጀብሐን አደራጅተው ካዘመቱብን በኋላ የገንጣዮች መውጫና መግቢያ በሮች ብቻ ሳይሆኑ የመሣሪያ፣ የሥንቅ፣ የመድኃኒትና የተለያዩ ቁሳቁሶችን በስውር ማቅረቢያ በሮች በመሆናቸው የሁለቱንም አገሮች ትኩረት የሚስቡ ሆኑ።

የሱዳን መንግሥት በአገራችን የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብቶ ገንጣዮችን ከመርዳት ባሻገር በቃሮራ ከተማ አቅራቢያ ጦር በማሥፈሩ የኢትዮጵያም መንግሥት በአፀፋው ለጠረፉ ጥበቃ የ15ኛውን እግረኛ ሻለቃ ጦር ናቅፋ ላይ አሠፈረ።

የ15ኛ እግረኛ ሻለቃ መምሪያ ደግሞ በበኩሉ ከሻለቃው የተነጠለ አንድ እግረኛ ሻምበል ጦር ኢትዮጵያ ቃሮራ ላይ አሥፍሮ የቃሮራን በርና አካባቢውን መቆጣጠር ጀመረ።

አጠቃላይ የቁጥጥር ይዞታውን በኤርትራ ምሥራቃዊ ቆላማ ክልሎች በቀይ ባሕር ዳርቻ ከቃሮራ እስከ ምፅዋ አውራጃና በመጠኑም ወደ ኤርትራ ደቡባዊ ደጋማ ክልል ጠጋ አድርጎ ጦሩን በማስፈር ከጀብሐና ከመንግሥቱ ጦር ጋር የተፋጠጠው «ሻዕቢያ» በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በግንቦት ወር 1968 ዓ.ም ዛሬ በማላስታውሰው ዕለተ ቀን ቃሮራ የሠፈረውን የ15ኛ እግረኛ ሻለቃ ተነጣይ እግረኛ ሻምበል ጦር በድንገትና በሌሊት ከቦ በማደር ጎሕ ሲቀድ በመጠነ ሰፊ ጦር ውጊያ ከፍቶ በጥቂት ሰዓት ውስጥ ጦሩን ደምስሶ ከተማዋንና የጦሩን ሠፈር መቆጣጠር ቻለ። ቃሮራ በኔ ግምት ከናቅፋ ርቀቱ ከ50 ኪ/ሜትር ቢያንስ እንጂ አይበልጥም።

የ15ኛ እግረኛ ሻለቃ መምሪያ ረዳት ጦር ልኮ ከበባውን በመስበር ተነጣይ ሻምበሉን እንዳያስጥል ሻዕቢያ በቃሮራና በናቅፋ መሀከል ባለና ለውጊያ አመቺ በሆነ ወታደራዊ መሬት ላይ መጠነ ሰፊ ጦር አስደፍጦ መንገዱን መዝጋቱን የሚያመለክት መረጃ ለሻለቃው መምሪያ የደረሰ ከመሆኑ ሌላ በሻለቃው ጠቅላይ ሠፈር ከቀሩት ሁለት እግረኛ ሻምበሎች አንዱ ለእርዳታ ቢላክ አጥጋቢ ውጤት ማስገኘቱ አጠራጣሪ

ከመሆኑ ሌላ የናቅፋ ከተማና የጦሩ ጠቅላይ ሠፈር ለሌላ ጥቃት ስለሚጋለጡ ረዳት ጦር ለመላክ ሳይቻል ቀረ።

ናቅፋ የሳህል አውራጃ ከተማ ያለበት ወረዳ ሲሆን የሳህል አውራጃ ከምዕራባዊዎቹ ቆላማ አውራጃዎች አንፃራዊ ነፋሻነት የሚሰማው ሆኖ አፋቤት ከሚባለው የሳህል አውራጃ ወረዳ ሸለቋአማ ምድር ጀምሮ ወደ ላይ ወደ ሰሜን እስከ ሱዳን ድረስ በሚዘልቁ የተራሮች ድርብርብ ሰንሰለት የታጠረ ነው ከማለት ይልቅ በተፈጥሮ ድርብርብ ተራሮች የተገነባ ነው ማለት ነው የአካባቢውን የተፈጥሮ ገፅታ በትክክል የሚገልፀው።

የ15ኛ እግረኛ ሻለቃ ጦር ያለበት የሳህል አውራጃ ከተማ ናቅፋ ከኋላው ከፊትም ከግራም ከቀኝም በተራሮች ሠንሰለቶች በታጠረ ከፍተኛ መሬት ላይ የሚገኝ ቢሆንም ከተማው የተሰራው በአካባቢው ካለ ከፍተኛ ጠረጴዛ መሳይ ሜዳ ላይ ስለሆነ ዙሪያውን ያሉት ከፍተኛ መሬቶች ይገዙታል።

የሳህል አውራጃን ከግራው የሚያጎራብተው የባርካ አውራጃ ከቀኝ የሚያጎራብተው ቀይ ባህር ሲሆን ከኋላው ማለትም በሰሜን በኩል የሚያጎራብተው የሱዳን መንግሥት ግዛት ነው። ናቅፋ ከክፍለ ሃገሩ ርዕሰ ከተማ ከአሥመራ የሚርቀው በኔ ግምት ከ250 እስከ 300 ኪ/ሜትር ይሆናል።

የ15ኛ እግረኛ ሻለቃ አዛዥ ሻለቃ ማሞ ተምትሜ በቅድሚያ ቃሮራ የሚገኘው ተነጣይ እግረኛ ሻምበል ጦር መደምሰሱን፣ ቀጥሎም ናቅፋ ያለው የሻለቃው ጦር በሻዕቢያ ጦር በመከበቡ ውጊያ ላይ መሆኑን በመግለፅ ሻዕቢያ ያለውን ኃይል አሰባስቦ የከበበን ስለሆነ ረዳት ጦር በአስችኳይ እንዲላክልን ብሎ ብርጌዱን ሲጠይቅ በግልባጭ ለሁለተኛ ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር መምሪያ፣ ለምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያ፣ ለጦር ኃይሎች ጠቅላይ መመሪያና ለጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግም አሳወቀ።

የመልእክቱ ቅጂ እንደደረሰን በደርግ በኩል ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የአገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት አመራር አካላት የሚሉትንና የሚወስዱትን እርምጃ እንጠብቅ ሳንል ጣልቃ ገብተን ሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር 15ኛ እግረኛ ሻለቃ የጠየቀው ረዳት ጦር ከየትም ተፈልጎ በአስቸኳይ እንዲላክለት የሰጠነው ትዕዛዝ ቅጂ ለ15ኛ ሻለቃና እንዲሁም ለተጠቀሱት የመከላከያ ሠራዊታችን የበላይ አመራር አካላት ሁሉ እንዲደርስ አደረግን። ከየትም ተፈልጎ ያልንበት ምክንያት መላው ሠራዊታችን በመላው የአገሪቱ ማዕዘናትና በመሀልም በተስፋፊዎችና በውስጥ ፀረ አብዮት ኃይላት በውጊያ የተጠመደ በመሆኑ በመሃል አገር ለዚህ ጉዳይ የሚውል ተጠባባቂ ጦር ስለአልነበረን ነው።

የ15ኛ እግረኛ ሻለቃ አዛዥ ለሁለተኛ ጊዜ በተመሳሳይ ሁኔታ ባስተላለፈው መልዕክት «በከባድ ውጊያ ላይ የምንገኝ ከመሆናችን በላይ ሻዕቢያ ከበባውን ለማጥበብ

ከመሞከር ባሻገር ተጨማሪ ኃይል አምጥቶ የህልውናችን ዋስትና የሆነውን የአውሮፕላን ማረፊያውን ሜዳ ለመቆጣጠር የሚያደርገውን ጥረት ለመግታት ስንከላከል የምንዋጋበት ወረዳ በመስፋቱ ጦራችን ስለተበታተነና አሰላለፋችን በመሳሳቱ ሁኔታው እጅግ አሳሳቢ ሆኗል» የሚል ነበር።

በዚህ ጊዜ የሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር መምሪያ «በአየርም በየብስም ረዳት ጦር ለመላክ እያዘጋጀን ስለሆነ የአውሮፕላን ማረፊያው በእናንተ ቁጥጥር ውስጥ መቆየት ወሳኝነት አለውና በተቻለ ብርታት እየተከላከላችሁ ቆዩ» የሚል ትዕዛዝ ሲሰጥ ለሁላችንም በቅጂ አሳወቀ።

ሁለተኛ ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ለ15ኛ እግረኛ ሻለቃ የሰጠውን ትዕዛዝ ምክንያት በማድረግ በደርግ በኩል፣ ከሌላም የውጭ የመረጃ ምንጫችን እንደተረዳነው የ15ኛ ሻለቃ ሁኔታ በጣም አሳሳቢ ስለሆነ ረዳት ጦር በአጣዳፊ መላክ ያስፈልጋል። በየብስ የምትልኩት ረዳት ጦር ናቅፋ ለመድረስ ረጂም መንገድ መጓዝ ያለበት ከመሆኑ በላይ በየመንገዱ ላይ የሻዕቢያ አዘግይ ጦር ሊገጥመውና ይበልጥ ሊያዘገየው ስለሚችል በየብስ የመላኩ ጉዳይ እንደ ተጠበቀ ሆኖ በአየር ለምትልኩት ጦር ቅድሚያውን መስጠት ወሳኝነት አለውና በአስቸኳይ ይፈፀም።

ሻዕቢያ የአውሮፕላን ሜዳውን እንዳይቆጣጠር ያሉን ተዋጊ አውሮፕላኖች በሙሉ ፋታ ሳይሰጡ እንዲደበደቡ ከማዘዛችን ሌላ ያሉንን ወታደራዊ መጓጓዣ አውሮፕላኖችና ሄሊኮፕተሮች ልክንላችኂል ብለን ለሁለተኛ ዋሊያ ክፍለ ጦር አዛዥ ብቻ ስናሳውቅ ለጉዳዩ ምስጢርነት ስንል ለሌሎች ለማናቸውም አላሳወቅንም።

ለዚህ ጉዳይ አፈፃፀም በመሃል አገር ማለትም በአዲስ አበባ የነበረንን አንድ ነበልባል በመባል የሚታወቅ ኮማንዶ ሻለቃ ጦር ስንልክላቸው በእነሱም በኩል የናቅፋን መልክአ ምድር ደህና አድርጎ የሚያውቅና በተዋጊነቱም የተመሰገነ አንድ የፖሊስ ኮማንዶ ሻለቃ ጨምረው በቅድሚያ በሄሊኮፕተር ምልልስ ማጓጓዝ ተጀመረ።

በአንድ አገር ውስጥ እርስ በርስ በሚደረግ ውጊያ ትልቁ ችግር የጦርን ገበና ወይንም ምስጢር ለመጠበቅ ያለመቻል ነው።

በኤርትራ የጀብሐና የሻዕቢያ ረዳቶች ብቻ ሳይሆኑ የሰለጠኑ የመረጃ ወኪሎቻቸውም በሕዝቡ፣ በፖሊሱ ሠራዊትና በጦሩ ውስጥ በብዛት የተሰገሰጉ በመሆናቸው ናቅፋ ላይ ጦር በአየር መጓጓገ ለማውረድ የታቀደውን እቅድ ቀድመውና ፈጥነው ለገንጣዮች ያሳወቁ ይመስላል ሻዕቢያ የናቅፋን አውሮፕላን ማረፊያ መቃረቢያና አካባቢ በአየር መቃወሚያ መሣሪያ አጥሮ ሄሊኮፕተሮቹ ማረፍ ቀርቶ እንዳይቀርቡም በማድረጉ የናቅፋን አየር ማረፊያ ተጠቅመን ጦር ለማቅረብ ስለአልተቻለ ሌላ ዘዴ መፈለግ ነበረብን።

ከናቅፋ ከ10 እስከ 15 ኪ/ሜትር ምሥራቅ በምትገኝና ሄሊኮፕተር ሊማሳረፍ በምትመች ናኖ በተባለች ገላጣ ቦታ ላይ በናቅፋ አየር ማረፊያ ላይ ለማረፍ ተዘጋጅተው የነበሩትን ሁለት ኰማንዶ ሻለቆች በሄሊኮፕተር ለማውረድ ተወስኖ በመጀመሪያ ነበልባል ሻለቃውን ማውረዱ ሲጀመር አሁንም ሻዕቢያ በቅድሚያ መረጃ የደረሰው ይመስላል በተጠቀሰቺው ሜዳማ ሥፍራ አካባቢ በነበረ ሰዋራ ሸለቆ ውስጥ በርካታ ገንጣይ ጦር አስደፍጦ የኛን ጦር ማረፍ ሲጠባበቅ ነበረና በመጀመሪያዎቹ አራት ሄሊኮፕተሮች ተጓጉዞ ያረፈውን የነበልባል ኰማንዶ ጦር የሻዕቢያ ጦር ወዲያው ከበባ አድርጎ ለመማረክ ያደረገውን ሙከራ ተቋቁሞ በሚያስደንቅ ጀግንነት ብርቱ ውጊያ አድርጎ ከአባላቱ አብዛኛው በመሰዋታቸውና በመቁሰላቸው የቀረው አነስተኛ ጦር ወደ አፋቤት ለማፈግፈግ በመገደዱ 15ኛ ሻለቃን ከከበባ ለማውጣት የተደረገው ሁለተኛው ጥረት ከሸፈ።

አፋቤት ከናቅፋ ወዲህ የሚገኝ የሳህል ሌላው የወረዳ ከተማ ሲሆን 16ኛው እግረኛ ሻለቃ የሚገኝበት ሥፍራ ነው።

ከዚህ በኋላ በምድር በየብስ መጓጓዣ ለመሄድ ተዘጋጅቶ የነበረው ረዳት ጦር በተጨማሪ በአየር መጓጓዣ ለመጓጓዝ ተዘጋጅተው የነበሩትን ሁለት ኰማንዶ ሻለቆች በመጨመር በከባድ መሣሪያዎችና በብረት ለበስ ተዋጊ ተሽከርካሪዎች የተጠናከረ ግብረ ኃይል የኤርትራ ክፍለ ሃገር የፖሊስ ሠራዊት አዛዥ በነበሩት በኰሎኔል ለሜሳ በዳሶ አዛዥነት በመንገዱ ላይ የሚያገኘውን የሻዕቢያንም ሆነ የጀብሐን ጦር እየጠረገ እንዲሄድ ተወሰነ።

የኤርትራ ፖሊስ አዛዥ ኰሎኔል ለሜሳ በዳሶ የግብረ ኃይሉ አዛዥ እንዲሆኑ የተደረገበት ምክንያት በግብረ ኃይሉ ውስጥ ከተካተተው ጦር አብዛኛው የኤርትራ ፖሊስ ኰማንዶዎች ከመሆናቸው ሌላ ቀደም ባለው ጊዜ ፈጥኖ ደራሽ በመባል የሚጠሩትን የፖሊስ ተዋጊዎች በኋላም የፖሊስ ኰማንዶዎችን ከእስራኤል መኰንኖችጋር በማሰልጠን ለብዙ ጊዜ የሰሩና በብዙ የጦር ሜዳ ያዋጉ ጥብቅ ወታደራዊ ሥነ ሥርዓት አስከባሪ፣ ቆራጥና ጀግና መኰንን በመሆናቸው ነው።

በዚህ አጋጣሚ ለአንባቢ መግለጥ ያለብኝ በኒልሰን ማንዴላ የተመሩት የደቡብ አፍሪካን ነፃ አውጭ የደፈጣ ተዋጊዎች በአዲስ አበባ ለማሠልጠንና ለማደራጀት በተደረገው ጥረት ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ካደረጉት የፖሊስ መኰንኖች አንዱ መሆናቸውንም ነው።

በግብረ ኃይሉ ውስጥ የተካተቱትን የተለያዩ የጦር ክፍሎች ከየቦታው ለማሰባሰብና ለማደራጀት፣ ጦሩ እርስ በርሱ እንዲተዋወቅ፣ ይህንን ረገርምና ውስብስብ ውጊያ እንዲመሩ ከየጦር ክፍሉ የተመረጡ መኰንኖችን ለመደልደልና የውጊያ ብቃታቸውን ለማሻሻል ሲባል በከረን ከተማ አካባቢ ግብረ ኃይሉ የህብረት ውጊያ ልምምድ ለማድረግ የጠየቀው ጊዜ ቀናትን ሳይሆን ሳምንታትን ሆነ።

በናቅፋ ከገንጣዮች ጋር የሚዋጋው የ15ኛ እግረኛ ሻለቃ ጦር እየተዳከመ በመሄዱ መጠን የጠላትም ግፊትና ተፅእኖ እያየለ ከመሄዱ ጋር በጦሩ እጅ የነበረው ወርሃዊ ቀለብ፣ መድኃኒትና ከሁሉም በላይ የጥይት መጠን እየተመናመነ መሄድ ታላቅ ጭንቀት ውስጥ ከተተን። ከከረን ወደ ናቅፋ የሚወስደው መንገድ በገንጣዮች ቁጥጥር ሥር ያለ ከመሆኑ በላይ የመንገዱ ዓይነትና የአካባቢው ተፈጥሮ ለተሽከሪካሪ ጉዞ በጣም አስቸጋሪ ነው።

የከረን አውራጃ ምድር በጠቅላላውና የከረን ከተማ ከኤርትራ ደጋማ ክልሎች ከሐማሴን፣ ከሰራዬና ከአካለ ጉዛይ አውራጃዎች ጋር የተያያዙት የኮረብታ ሰንሠለቶች ከአሥመራ ከተማ አካባቢ ተነስተው በከረን ወደ ምዕራባዊና ምሥራቃዊ ቆላማ አውራጃዎች የሚወስደውን አንድና ብቸኛ የተሽከሪካሪዎች መተላለፊያ መንገድ ግራና ቀኝ እያካበቡ በመሄድ መሳህሊት በመባል በሚጠራው በር ላይ ግማሽ ክብ ሠርተው በመግጠም ይቆማሉ።

ከመሳህሊት በር በኋላ ያለው ምድር ከከፍተኛው የደጋው መሬት ወደ ዝቅተኛው ቆላማ መሬት በከፍተኛ ደረጃና በአንዴ አዘቅዝቆ ወይንም አሽቆልቁሎ በመውረድ ወደ ጋሽስቲት፣ ወደ ባርካና ሳህል አውራጃዎች አጋማሽ ድረስ ሜዳማ ይሆንና ከዚያ በኋላ ማለትም ከአቆርዳትና ከአፋቤት ከተማ በኋላ አቀበቱ እንደገና እስከ ሱዳን ይቀጥላል።

ከከረን ከተማ እስከ መሳህሊት በር ድረስ ያለው መንገድ ግራና ቀኝ ከፍ ብዬ በጠቀስኳቸው ኮረብታዎች የታጠረ ሆኖ ጎድጓዳና ሽለቆ መሰል ዝቅተኛ መሬት በመሆኑ የከረን ከተማ የተቀመጠበት ኮረብታ ከአካለ ጉዛይ አውራጃ ጋር የተያያዙት ኮረብታዎችና የእነዚህም መጨረሻ የሆነው የመሳህሊት በር መንገዱን ይገዙታል።

ወደ ናቅፋ እንዲሄድ የተዘጋጀው ግብረ ኃይል ጠቅላላ ወታደራዊ ቁሳቁሱንና ሥንቁን በተሽከርካሪዎች ጭኖ በመጓዝ የመሳህሊትን በር አልፎ ወደ ቀኝ በመዞር ወይንም በመታጠፍነው ወደ ናቅፋ የሚወስደውን መንገድ የሚያያዘው።

ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት ከገንጣዮች ጋር በሚደረገው የትጥቅ ትግል የአብዮታዊ መከላከያ ሠራዊታችን ዋና ችግር የራሱን ወታደራዊ ገበና ወይንም ምስጢር ለመጠበቅ ያለመቻሉ ነው እንደ ማለቴ ሁሉ አሁንም በየብስ ወደ ናቅፋ ለመጓጓዝ የተዘጋጀውን ግብረ ኃይልና የተዘጋጀበትንም ምክንያት ወዴት እንደሚሄድ ሻቢያ በመረጃ ወኪሎቹ አማካኝነት ቀደም ብሎ የተረዳ ይመስላል ኃይሉን ከያለበት አሰባስቦ የመሳህሊትን በር በመዝጋት በበሩ ፊት ለፊት፣ ግራና ቀኝና እንዲሁም መንገዱን የሚያካብቡትን ኮረብታዎች ግራና ቀኝ በስፋትና በጥልቀት መሽጎ የወገንን ግብረ ኃይል ጦር ሚገድልበት ሥፍራ ድረስ እስኪገባለት እድፎጦ ይጠብቅ ኖሯል።

የሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር መምሪያ፣ ብርጌዱና እንዲሁም የዘማቹ ግብረ ኃይል ስለሻዕቢያ እንቅስቃሴ የመረጃ ድህነት ስለነበራቸው ሻዕቢያ ኃይሉን በሙሉ የሰበሰበው በናቅፋ 15ኛ ሻለቃን በመክበብ ላይ ብቻ ያተኮረ ነው የሚል ግምት ሳይኖራቸው አይቀርም።

ምክንያቱም ወደ ኤርትራ ምዕራባዊ ቆላም ሆነ ምሥራቃዊ ቆላማ አውራጃዎች ለመሄድ መተላለፊያ የሆነውን የመሳህሊትን በር ቀደም ብለው በጦር ለማስያዝ አልሞከሩም።

ግብረ ኃይሉ ተነቃንቆ በመሳህሊት በር አካባቢ ሻዕቢያ ባዘጋጀው የመግደያ መሬት ሲገባለት ተኩስ በመክፈት ከፍተኛ አደጋ በማድረሱ ከግንባር ቀደሙ ጦር አብዛኛውና በቀላሉ የማይተኩ የጦር መሪዎች ወደቁ።

ጠላት ካዘጋጀው መግደያ መሬት የግብረ ኃይሉን ጦር ለማስወጣት ሲባል መጠነኛ ሥልታዊ ማፈግፈግ ተደርጎ ጦሩን መልሶ በማቋቋምና የሻዕቢያ ምሽጎች ላይ አስፈላጊው የከባድ መሣሪያ ድብደባ ከተደረገ በኋላ ምሽጉን ለመጣስ በመጀመሪያው ዕለት ከተደረገው ሙከራ ሌላ በተለያዩ ቀናቶች ተደጋጋሚ የማጥቃት ጥረቶች ተደረጉ።

የወገን ጦር አዛገኖች የግብረ ኃይሉ ጦር በመቁሰልና በመሰዋት ኃይሉ ሲቀነስባቸው የሚተኩት ተጠባባቂ ወይንም ተተኪ ደጀን ጦር ስለአልነበራቸው ያንኑ ጦር እየመላለሱ በማዋጋት በጠላት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ቢያደርሱም ሻዕቢያ ሙታኑንና ቁስለኞቹን ከውጊያው ግንባር ወዲያው በማግለል አዲስ ጦር ከናቅፋ እያመጣ ይተካል።

ግብረ ኃይሉን እስከ ናቅፋ መርተው 15ኛ ሻለቃን ከሻዕቢያ ከበባ ያስወጣሉ ብለን እምነታችንን የጣልንባቸው የግብረ ኃይሉ መሪዎች በእልህ ከናቅፋ በመለስ አንመለስም እያሉ ለጦሩ አርአያ ለመሆን በውጊያው የመጀመሪያ ረድፍ ተሠልፈው ውጊያውን በጀግንነት ሲያጋፍሩ ብዙዎቹ ጠላቶቻቸውን እየጣሉ ስለወደቁ የጦሩ ኃይል በብዛት ከመቀነሱ ባሻገር የመሪዎችም ከፍተኛ እጥረት ተፈጠረ።

በዚህ ጊዜ ወታደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ በኤርትራ የነበሩብን ችግሮች ገንጣዮች ከአረቡ ዓለም በሚያገኙት ለጋስ የገንዘብና የትጥቅ እርዳታ ምክንያት እጅግ መናጠጥ፣ እኛ በብዙ አቅጣጫ በውጊያ መወጠራችንና ከፍ ያለ የሰው ኃይል እጥረት፣ የጠላት ሠላዮች ከኛ ሠራዊት ጋር መሳውን ተቀላቅለው ሲገኙ እኛ ከነበረብን የመረጃ ድህነት ሌላ፣ በአብዮቱ ፍንዳታ ወቅት ሠራዊታችን የወደቀው አሮጌ የፖለቲካ ሥርዓት ተጠቃሚና የፊውዳሉ ገዥ መደብ መሣሪያ ናቸው የሚላቸውን አዛዦቹን ማሠር በተገደደበት ምክንያት የተፈጠረውን ወታደራዊ የሥነ ሥርዓት መበላሸት በማረምና በማቃናት በነበረበት ለመመለስ ብዙ ጊዜ የወሰደብን በመሆኑ

አገርንና አብዮትን ለማዳን የምናደርገውን የትጥቅ ትግል ለመምራት እጅግ አዳጋች አድርጎት ነበር።

የግብረ ኃይሉ ጦር የመሳህሊትን ምሽግ ለመስበር በተደጋጋሚ ያደረገው ማጥቃት ያለመሳካትና ያስከፈለው ከፍያ ለመስዋዕትነት ያስከተለውን ብሶት በመጠቀም በግብረ ኃይሉ ውስጥ የነበሩ የገንጣዮች ወኪሎች፣ የኢሕአፓ ጀሌዎችና ሥርዓት አልበኞች ባደረጉት አፍራሽ ቅስቀሳ የግብረ ኃይሉ ጦር ደፈረሰ።

«ደክሞናል፣ ኃይላችን ተመናምኗል ሌላ አዲስ ጦር አምጡ አንዋጋም» እስከ ማለት ስለደረሰ በየብስ ረዳት ጦር ልክን በናቅፋ ሻዕቢያ የከበበውን የ15ኛ ሻለቃ ጀግና ጦር ከከበባው ለማውጣት በታቀደው መሠረት የተደረገው ከፍተኛ ጥረት ዳግም ከሸፈ።

ከበባውን ሠብሮ የሚያወጣን የወገን ግብረ ኃይል ከዛሬ ነገ ይደርስልናል ብለው በታላቅ ተስፋ እየተዋጉ ይጠባበቁ የነበሩትን የ15ኛ እግረኛ ሻለቃ ሠራዊትና ለመሪዎቹ እናንተን ከከበባው ለማውጣት ያዘጋጀነው ግብረ ኃይል ሻዕቢያ የመሳህሊትን በር በመዘጋቱ ለመክፈት ታላቅ ተጋድሎ እየተደረገ ስለሆነ በእናንተም በኩል በብርታት ተከላከሉ ከማለት ሌላ የግብረ ኃይሉ ጥረት ከሽፏል የሚል ተስፋ አስቆራጭ መርዶ ለመናገር ባለመፈለጉ በርቱና ተከላከሉ በማለት እያበረታታን በሌላ መንገድ ሌላ መፍትሄ የሚያስገኝ የተሻለ ጦር ስናፈላልግና ስናሰባስብ ሳምንታት ተቆጠሩ።

ጊዜው እየተራዘመ በሄደ መጠን በውጊያው የሚሰዉትና በከባድ ቁስል ምክንያት ከውጊያ ውጭ የሚሆኑት አባላት ቁጥር በየቀኑ እየጨመረ ሲሄድ በተቃራኒው ሻዕቢያ ኃይሉን እያጠናከረ ከበባውን እያጠበበ ከመሄዱ በላይ የ15 ሻለቃ ጦር ወርሃዊ ቀለብና የጥይት መጠን እየተመናመነ መሄድ ችግሩን ይበልጥ ውስብስብና ይበልጥ አደገኛ እያደረገው በመሄዱ እጅግ ከፍ ያለ ሥጋትና ብሶት የተሰማው የ15ኛ ሻለቃ አዛዥ ሻለቃ ማሞ ተምትሜ ለጊዜው በምሥጢር የተያዘውን የሻዕቢያ ከበባ ይፋ በማድረግ ለመላው የአገሪቱ የመከላከያ ኃይሎች ማለትም ከሻለቃ ደረጃ እስከ ክፍለ ጦር ደረጃ ላሉት የምድር ጦር ክፍሎች፣ ለአየር ኃይሉ ሠራዊት፣ ለባህር ኃይሉ ሠራዊት ወዘተ በወታደራዊ ራዲዮ በየቀኑ ስለከበባውና በየቀኑም ጠላት ስለሚያደርሰው ጉዳት ማሳወቅ ወይንም ማሰማት ቋሚና የየዕለት ተግባሩ አደረገው።

«የአገር ያለህ፣ የወገን ያለህ፣ የመንግሥት ያለህ ድረሱልን» በማለት በየቀኑ ከሚያስተላልፏቸው ኢትዮጵያዊ የሆነን ዜጋ ልብ ከሚያደሙ ምልዕክቶች አንዱን ብቻ ለአንባቢ ለማሳወቅ እፈልጋለሁ።

«በናቅፋ በገንጣዮች ተከበን ከወገን እርዳታ ሊደርስልን አልቻለም። በአገራችን፣ በጠረፋችን በአረብ ምንደኞች ተከበን በጥይት ስንደበደብ ሳምንታት ተቆጠሩ።

ለአገራቸው አንድነት ሲፋለሙ ጥለው የወደቁ ጀግኖች ወንድሞቻችንን አስከሬን አፈር ማልበስ አስቸጋሪ ነገር ሆኖ ከሙታን ጋር ምሽግ ውስጥ ውለን እናድራለን።

ሐኪም የለን፣ መድኃኒት የለን፣ ለአገራቸው አንድነት ሲፋለሙ የቆሰሉ ወንድሞቻችን ሳይሞቱ በህይወት እያሉ ምሽግ ውስጥ እየበሰበሱ ናቸው» የሚል ነበር።

የ15ኛ ሻለቃን ጦር ከሻዕቢያ ከበባ ለማውጣት ከተደረጉት ያልተሳኩ ጥረቶች በኋላ በመጨረሻ የቀረን ምርጫ አንድ ብቻ ነበር።

እሱም በዚያን ጊዜ አገሪቱ የነበራትን አንድ የአየር ወለድ ሻለቃ ጦር ናቅፋ አውሮፕላን ማረፊያ ሜዳ ላይ በጃንጥላ ማውረድ ብቻ ነበር።

አሁንም እጅግ የሚያሳዝነው ነገር አገሪቱ አንድ ሻለቃ ብቻ አየር ወለድ ጦር ቢኖራት እሱም በተለያዩ ምክንያቶችና በተለያዩ ውጊያዎች ኃይሉ ከመቀናነሱ ሌላ ብ/ጀነራል ጌታቸው ናደውና ሌ/ኮሎኔል አለማየሁ አስፋው በከፊል ለአፈረሱት ለናቅፋ ዝላይ አንድ የተሟላ ሻምበል ጦር እንኳ ለማግኘት ያለመቻላችን ነው።

እንደተቀሩት የአገሪቱ ተዋጊ እግረኛ ሻለቆች ሁሉ የአየር ወለድ እግረኛ ሻምበል የሰው ኃይል አንድ መቶ ሰላሣ አንድ ሲሆን ከጠቅላላው የአየር ወለዱ ሻለቃ ጦር፣ በጤናማነታቸው፣ በሁለንተናዊ ለውጊያ ብቃትና ዝግጅታቸው ናቅፋ ላይ ለመዝለል የቻሉትና የተገኙት፣ በሻምበል ተስፋዬ ሀብተ ማርያም በኋላ ብ/ጀነራልና የህብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጀግና የተመሩ ፈቃደኞች ወይንም ወደ ዘማቾች ዘጠና ዘጠኝ ሰዎች ብቻ ነበሩ።

ናቅፋ ላይ 15ኛ እግረኛ ሻለቃን የከበበውን የሻዕቢያ ጦር ብዛት ከኛ አየር ወለድ ሻምበል የሰው ኃይል መጠን ጋር ስናመዛዝነው ናቅፋ ላይ እንዲዘሉ የምንሰጠው ትዕዛዝ ለሁሉም የሞት ፍርድ የመስጠት ያህል ተሰምቶን ነበር።

ያንን የመሰለ እጅግ አስቸጋሪ ውሳኔ ለመወሰን የቻልነው ራሳቸው አየር ወለድ ወታደሮቻችን በወሰኑት ቆራጥ ውሳኔ ላይ በተመሠረተ ፈቃደኝነታቸው ጥቅምት 21 ቀን 1969 ዓ.ም በ0700 ሰዓት ማለትም ከጧቱ አንድ ሰዓት እንዲዘሉ ተደረገ።

በዚህ ጊዜ አየር ወለድ ጦራችን ናቅፋ ላይ መዝለል በጠላት ዘንድ እንዳይታወቅ የተደረገው የምስጢር ጥበቃ ጥረትና ጥንቃቄ ስኬታማ ስለነበረ አየር ወለዳችን በሻዕቢያ ላይ ድንገተኝነትን አገኙ።

በራሪ ነብር የተባለ ስም የተሰጣቸው ወደ ዘማች ጀግኖች ነብርነታቸውን በግብርም በማሳየት ናቅፋ አየር ማረፊያ ሜዳ ላይ ዘለው እጅግ አነስተኛ በሆነ መስዋእትነት

ከፍ ያለ ድልን በመቀዳጀት ከአንድ ሰዓት በላይ ባልወሰደ ውጊያ ከናቅፋ አየር ማረፊያና ከአካባቢው የሻዕቢያን ጦር ወግተው ለማባረር ቻሉ።

በዚህ ጊዜ የ15ኛ እግረኛ ሻለቃ ጦር የአየር ወለዱን ጦር ዝላይ ስኬታማ ለማድረግ ከምሽጋቸው በመውጣት የአደረጉት ተጋድሎ፣ የከፈሉት መስዋዕትነትና የጀግናው አየር ኃይላችን ሚና ለድሉ መገኘት ወሳኝነት ነበራቸው።

ደርግ የአየር ወለድ ሻለቃ ጦር ናቅፋ አየር ማረፊያ ሜዳ ላይ እንዲዘል ትዕዛዝ ሲሰጥ አየር ወለዱ ጦር ከ15ኛ ሻለቃ ጦር ጋር በመቀላቀል ምሽግ ውስጥ ገብቶ የመከላከል ውጊያ እንዲያደርግ ወይንም የመከላከሉን ውጊያ እንዲሳተፍ ሳይሆን የአየር ማረፊያውንና አካባቢውን ከሻቢያ ጦርና ከአየር መቃወሚያ መሣሪያዎች ቁጥጥር ውጭ ካደረገ በኋላ የሻዕቢያን ከበባ መስበር ብቻ ሳይሆን የሻዕቢያን ጦር ከናቅፋ የሚያስወጣ በርካታ ረዳት ጦር ሲላክ አየር ወለዱ ሻምበል በዚያው የአየር መጓጓዣ ወደ አሥመራ እንዲመለስ ነበር።

ይህንንና ሌሎችንም ተግባሮች እንደ አስፈላጊነታቸው በቅደም ተከተል የማስፈፀም ኃላፊነት ያለበት የሁለተኛ ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር መምሪያ በመጀመሪያው ዕለት ማለትም ጥቅምት 21 ቀን፤

1ኛ ለብዙ ሳምንታት በመሰቃየት ላይ ለነበሩት ቁስለኞች ቅድሚያውን በመስጠት ለሕክምና ወደ አሥመራ ማግለል፤

2ኛ ጦሩ በረሃብ ይሰቃይ ስለነበረ በአጣዳፊ ትኩስና ደረቅ የውጊያ ቀለብ እንዲቀርብለት፤

3ኛ በ15ኛ ሻለቃ ጦር እጅ የነበረው ጥይት አልቆ ስለነበረ ጠላት የመልሶ ማጥቃት ከመሠንዘሩ በፊት በአጣዳፊ ለ15ኛ ሻለቃ ጦር ብቻ ሳይሆን ከበባውን ይሰብር ዘንድ ለሚላከው በርካታ ጦር ጭምር ቢያንስ ሁለት መደበኛ ጭነት ጥይት በቅድሚያ እንዲቀርብና ከዚህ በኋላ የተዘጋጀው ረዳት ጦር በዚያው ዕለት በአውሮፕላኖችና በሄሊኮፕተሮች ቅንጅት እንዲጓጓዝ ነበር የታቀደው።

በዚህ ቅደም ተከተል መሠረት ቅድሚያ የተሰጣቸው ሥራዎች እየተከናወኑ ሳለ ከቀይ ባህር የተነሳው ርጥበት ያዘለና ጨለማ በሚመስል ከባድ ጉም የናቅፋን ከተማ ብቻ ሳይሆን የሳህልን አውራጃ ሸፈነው።

የአካባቢውን የተፈጥሮ ባህሪ ለመለወጥ ስለማይቻል እንጂ በዚህ ወቅት ገንጣዮች በጉምና አዋራ እየተከለሉ በጠቅላላው ኤርትራ በሠራዊታችን ላይ ጠቅላላ ዐውደ ጥቃት ከጥቅምት ወር አጋማሽ ጀምሮ እስከ ታህሣሥ ለወራቶች የሚሠነዝሩ መሆናቸው ከልማድ የታወቀ ነው።

በዚህ እጅግ አስቸጋሪ ወቅት በተለይ በምሥራቃዊው ቆላማ ክልል ከጉሙ ጋር አብሮ በሚመጣ የኤርትራ ህዝብ ከምሲ እያለ የሚጠራው አቧራ የሚያስነሳ በጣም ኃይለኛ አውሎ ነፋስ ብርሃንን በመሸፈንና ጨለማውን ጉም በበለጠ በማጠናከር የሰውን የማየት ኃይል በእጅጉ የሚቀንስ በመሆኑ ምክንያት በአምስት ሜትር ርቀት ውስጥ ሰው ለሰው ለመተያየት አይቻልም።

አየር ወለዱ ጦር በዘለለበት ሰዓት ማለትም ጥቅምት 21 ቀን 1969 ዓ.ም ከጧት ጀምሮ አብዛኛው የ15ኛ እግረኛ ሻለቃ ጦር ከምሽጉ በመውጣት በሁለትና በሦስት ኪ/ሜትር ርቀት የጠላት መከለያ፣ መጠጊያና ማጥቂያ የሆኑ ከፍተኛና ቁልፍ ወታደራዊ መሬቶችን በመቆጣጠር አየር ወለዱ ጦር በጃንጥላ ሲወርድ ከምድር ሻዕቢያ ሊያደርስ የሚችለውን ጥቃት ለመከላከል ሲባል ጦሩ በስፋት ከምሽጉ በመራቅ ተበታትኖ ስለሚገኝ በድንገት የተለወጠው የአየርን ብረት ሁኔታ ለሻዕቢያ መልሶ ማጥቃት ሁኔታውን ያመቻቸለት በመሆኑ ወትሮ ከነበረው በላይ በርካታ ተጨማሪ ጦርና ከባድ መሣሪያዎችን ከያለበት ናቅፋ ላይ አሰባስቦ ሊያጠቃ ስለ መዘጋጀቱ አስተማማኝ መረጃ ስለ አገኘን የከፋ ወሳኝ አደጋ ላይ ከመውደቃችን በፊት መላውን የሻለቃውን ጦር ከአሰማራንበት መልሰን ምሽግ ለማስገባት ስለተገደድን፣ በድንገት በተፈጠረው የአየር ንብረት መለወጥ ምክንያት የተዘጋጀውን ረዳት ጦር ማጓጓዝ ቀርቶ ተዋጊ አውሮፕላኖቻችንም ሊረዱን ስለማይችሉ አየር ወለዱ ሻምበል አሁን ከኛ ብዙ ርቆ በሚገኝበት በአይሮፕላን ማረፊያና በአካባቢው ብቻውን ቢቀር ወይንም ቢቆይ በሻዕቢያ ስለሚመታ ከ15ኛ ሻለቃ ጦር ጋር ምሽግ ገብቶ የመከላከሉን ውጊያ እንዲያጠናክርና የአየር ንብረቱን ሁኔታ መለወጥና ያለመለወጥ ሻዕቢያ የሚወስደውን ዕያሄ ተግባር መጠበቁ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን አማራጭ የሌለው ግዴታ ነው በማለት የ15ኛ ሻለቃ አዛዥ ሻለቃ ማሞ ተምትሜ ለሁለተኛ ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ያቀረበው ሃሳብ ከረን በሚገኘው የሶስተኛ እግረኛ ብርጌድ አዛዥም ስለተደገፈ የአየር ወለዱ ሻምበል ጦር የአውሮፕላን ማረፊያውንና አካባቢውን ለቆ ምሽግ ገብቶ ከ15ኛ እግረኛ ሻለቃ ጋር በመቀላቀል የመከላከሉን ውጊያ እንዲያጠናክር ተደረገ።

ሻዕቢያ በፊት ተመልካቾቹ የወገንን ጦር ሁኔታና እንቅስቃሴ ይከታተል ወይንም ይቆጣጠር ኖሮ አየር ወለዱ ሻምበል ጦር ወደ ምሽግ በገባበት ቀን ምሽት ጨለማን ከለላ አድርጎ ጠቅላላ ጦሩን አንቀሳቅሶ የአውሮፕላን ማረፊያ ሜዳውንና ጠቅላላ የቀድሞ የመሬት ይዞታውን መልሶ ከመቆጣጠር ባሻገር ጨለማው ጉምና ከምሲ አቧራ የሚያስነሳ አውሎ ንፋስ በፈጠሩለት ሁኔታ ተጠቅሞ ከጠብመንጃ ተኩስ የውጤት ርቀት ባነሰ ወደ ወገን ጦር ቀርቦ ከወገን ጦር ተኩስና ከአየር ኃይላችን ድብደባ የሚከልለውንና የሚመከትበትን ጠንካራና ጥልቅ ምሽግ ሲሰራ የወገን ጦር ማየትና መቃወም አልቻለም።

ሻዕቢያ ቀድሞ ከነበረው መጠኑ በላቀ ጦር ከበባውን እጅግ ከማጥበቡና ተፅእኖውን በማጠናከር በምሽግ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የወገንን ጦር አባላት በመተረኛ ተኳሾቹ

በቀላሉ መግደል የሚችልበት ሁኔታ ቢፈጥረም የአየር ንብረቱ ሁኔታ እስኪለውጥ ድርስ ለጥቂት ሳምንታት በወገን ጦርና በሻዕቢያ ጦር መካከል የዓይን ግንኙነትና የተኩስ ልውውጥ አልነበረም።

የቁስለኞች ለሕክምና ወደ ሆስፒታል መላክ፣ የሥንቅና የጥይት አቅርቦቱ የወገንን ጦር የተዋጊነት መንፈስና ሞራል ስለአጠናከረው ለተወሰኑ ሳምንታት «አድኑን፣ ከከበባው አውጡን ወዘተ» በማለት በወታደራዊ ራዲዮ 15ኛ እግረኛ ሻለቃ ያስተላልፍ የነበረው መልዕክት የቆመ ቢሆንም በደርግና በተቀሩትም የበላይ አመራር አካላት ዘንድ ያለው ሥጋት፣ ጭንቀትና ውጥረቱ ይበልጥ ጨመረ እንጂ አልተቀነሰም። ከበባውን ለአንዴና ለመጨረሻ በመስበር ሻዕቢያን ከናቅፋ ለማባረር ያዘጋጀነውን በርካታ ጦር ከማቅረባችን በፊት ተፈጥሮ ጣልቃ ገብቶ በማሰናከሉ መፍትሔ አልባ የሆነው ከበባ ቀናትና ሳምንታትን ብቻ ሳይሆን ወራቶችን አስቆጠረ።

አልፎ አልፎ ለቀናቶችና አንዳንዴም ለሳምንታት ከምሲውና ጉሙ ለቀው የፀሐይ ብርሃን በሚተካበት ጊዜ ተጠቃሚው ሻዕቢያ ነው።

ሻዕቢያ የከበባውን ቀለበት እጅግ አጥብቦ ከአየር ኃይላችን ድብደባ ከተከለለበትና ከተመከተበት ምሽጉ በየቀኑ የወገንን ምሽግ ከሁለት እስከ ሦስት ሰዓቶች ድረስ በከባድ መሣሪያ ከደበደበ በኋላ እየደጋገመ በርካታ ማጥቃቶችን ያለማቋረጥ በመሠንዘሩ በወገን ጦር ላይ የሚያደርሰውጉዳት አየር ወለድ ሻምበል ጦር በጃንጥላ ከመውረዱ በፊት ከደረሰው የቁስለኞችና የሙታን ቁጥር በጣም ልቋል። ከጦሩ ሌላ የጦሩ መሪዎች አብዛኛዎቹ ሲሰዉ ከቆሰሉት መካከል አንዱ የሻለቃው አዛዥ ሻለቃ ማሞ ተምትሜ ነበር።

በወገን ጦር አካልና ህይወት ላይ የሚደርሰው ጉዳት በየቀኑ እንደቀጠለ ሆኖ እጅግ አሳሳቢ የሆነው የሥንቅና የጥይቶች መጠን ዳግም እየተመናመነ መሄድ ነው። ይህንን ችግር ለመቋቋም ደግሞ ያለን አንድና ብቸኛ መፍትሄ ለጦሩ የሚያስፈልጉትን ጥይቶችና ስንቃ ስንቆች ወዘተ በጃንጥላ መወርወር ብቻ ነው።

ከፍ ብዬ እንደገለፅኩት የወገንና የጠላት ምሽጎች እጅግ የተቀራረቡ በመሆናቸው ጉሙና አቧራ የሚያስነሳው ከምሲ ነፋስ ለተወሰነ ጊዜ መጠኑ ቢቀንስም አሁንም ከቀይ ባህር የሚነሳው ንፋስ ኃይለኛ በመሆኑ ለወገን ጦር ከሰማይ በጃንጥላ የሚጣለው ቀለብና ጥይት በነፋስ እየተገፋ አብዛኛው በሻቢያ ይዞታ ውስጥ ስለሚወድቅ ለአገሪቱ ጠላት ቀለብና ጥይት አቅራቢ ሆንን።

በወገን ጦር ይዞታ ውስጥ የወደቀውን የወገን ጦር ከምሽጉ እየወጣ ለመሰብሰብና ለማንሳት ጥረት በሚያደርግበት ጊዜ በጠላት መትረየሽ ተኳሾች እየተመታ የሚወድቀው ቁጥር እየበዛ በመሄዱ የሚከፈለው መስዋዕትነት በጣም መሪርና የማይቻልም ሆነ።

ሻዕቢያ ምሽጉን ከወገን ምሽግ ጋር በጣም አጠጋግቶ በመገንባቱ ምክንያትና በአየር ንብረቱ ተፅእኖ አየር ኃይላችን ጠላትን ከወገን ለይቶ ለመምታት ከመቸገሩ ሌላ ከሻዕቢያ ምሽግ ጥንካሬ የተነሳ በሻዕቢያ ጦር ላይ የሚደርሰው ጉዳት አጥጋቢ አልሆነም።

በእንዲህ ያለ ሁኔታ የሚካሄደው ውጊያ ስድስት ወራት ያህል ጊዜ ስለወሰደና በኛ በኩል ምንም ዓይነት መፍትሄ ለማግኘት ባለመቻሉና ጠላት ባላቋረጠ ሁኔታ የወገንን ጦር ለመደምሰስ በሚሠነዝረው ጥቃት በወገን በኩል የመከላከሉን ውጊያ በንቃትና ወደር በሌለው ጀግንነት ከሚዋጋው ጦራችን የሙታኑና የቁስለኛው ብዛት ስለአየለ ሁኔታው ተስፋ አስቆራጭ እየሆነ ቢሄድም ሻዕቢያን እያካፈልን ሥንቅና ጥይት በጃንጥላ መጣሉና አየር ኃይላችን ጠላትንና የጠላትን ይዞታ በየቀኑ መደብደቡን አላቋረጠም።

ምዕራፍ ሰላሣ አምስት

በናቅፋ የ15ኛ እግረኛ ሻለቃ ጦር ከገንጣዮች ጋር ያደረገው የመከላከል ውጊያ ፍፃሜ

ከፍተኛ መስዋትነት ተከፍሎባቸው ከጠላት የተነጠቁትን ወታደራዊ ጠቀሜታ ያላቸው ቁልፍ መሬቶችንና በተለይም ብቸኛ ድርጅታዊ ድጋፍና ሲያስፈልግ የሰው ኃይል ማቅረቢያ የሆነውን የአውሮፕላን ማረፊያ ሜዳ በድንገተኛ የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ወይንም አስገዳጅነት ለቀው የ15ኛ እግረኛ ሻለቃና አየር ወለዱ ጦር ምሽጋቸው ውስጥ መግባት፣ ለወገን ጦር ታላቅ ውድቀት ብቻ ሳይሆን በናቅፋ የሚደረገው የአብዮታዊ ጦራችን የመከላከል ትግል ፍፃሜ ጅምር ሲሆን ለሻዕቢያ ድንገተኛ የአየር ንብረት ለውጥ በፈጠረለት አጋጣሚ ያለ ውጊያ የተቀዳጀው ታላቅ ድል ነበር።

ናቅፋ ላይ ከስድስት ወር ውጊያ በኂላ በወገንና በጠላት መካከል የነበረው የሰው ኃይል ሚዛን ሲገመገም አንድ ለሰባት ነበር።

ይህም ሆኖ ሻዕቢያ ያለማቋረጥ አዘወትሮ የሚሠነዝረውን ጥቃት በመመከት በወገን ጦር ላይ ከሚደርሰው እጅግ የላቀ እጥፍ ድርብ ጉዳት እያደረሰ ጠላትን በመመለስ የጠላትን ምኞት ቢያመክነውም በወገን ላይ የሚደርሰው ጉዳት ከቀን ወደ ቀን በመብዛቱ ሁኔታው ከወገን ጦር አቅምና ቁጥጥር ውጭ እየሆነ ሄደ።

መጋቢት 13 ቀን 1969 ዓ.ም ጥዋት ከ15ኛ እግረኛ ሻለቃ መምሪያ ከናቅፋ ለሁለተኛ ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ሲፅፍ የሶስተኛ እግረኛ ብርጌድ መምሪያና ለደርግ የደረሰውን የወታደራዊ ራዲዮ መልዕክት ለአንባቢ እገልፃለሁ።

«አንድና ብቸኛ አለኝታችን የሆነው አየር ኃይላችን በአየር ንብረት ለውጡ ምክንያት የሚሰጠንን እርዳታ ካቆመ ቀናቶች በመቆጠራቸው ሻዕቢያ በመፈንጠዝና በእኛ ላይ በመፈንጨት ላይ ይገኛል።

ከወገን ጦር በቁጥር የሚበልጠው በመሰዋትና በመቁሰል ከውጊያ ውጭ በመሆኑ ለማያቋርጠው የጠላት ከባድ መሣሪያዎች ከፍ ያለ የተኩስ ኃይል ከፍ ያለ ተፅዕኖ ራሳችንን ለመከላከል የማንችልበት ሁኔታ ላይ ከመድረሳችን ሌላ ጨለማው ጉምና ከምሲው እይታችንን ሙሉ በሙሉ ስለጋረደው ጠላት በቀላሉ እየተጠጋ የምሽጋችንን ዙሪያ በማጥቃት ላይ ይገኛል» የሚል ነበር።

ይህ መልዕክት ለሁላችንም የደረሰው ከጧቱ በ0700 ሰዓት ሲሆን ከቀትር በኂላ ወደ ማታ «የመከላከያ ወረዳችንን ምዕራባዊ ቀጠና በጥሩ ሁኔታ ይዘውልን የነበሩት የኤርትራ ክፍለ ሃገር ኰማንዶ ፖሊሶች በሙሉ ከድተውን ከጠላት ጋር በመቀላቀል

ብቻ ሳይሆን ወታደራዊ ገበናችንን በማጋለጥና ጠላትን እየመሩ በማምጣት አብረው እየወጉን ነው» የሚል ነበር።

ከጧቱ በ0700 ሰዓት የተጀመረው የጠላት ማጥቃት እስከ 1500 ሰዓት ድረስ ቀጥሎ ብዙ የወገን ጦር አባላት ወደቁብን።

የኤርትራ ፖሊስ ኰማንዶዎች ከፍተው በሰጡት ክፍተት ተጠቅሞ ጠላት የምሽጋችንን ምሥራቃዊ ቀጠና በመስበር ኃይሉን በገፍ አሠልፎ በጥልቀት በማጥቃቱና ከሰዎቻችን አብዛኛዎቹ በመሰዋታቸው የተረፉት ጥቂቶች ወደ ሻለቃው ጠቅላይ ሠፈር አፈግፍገው ሲመጡ «ሻዕቢያ የህይወታችን እስትንፋስ የሆነውን ውሃችንን ያዘው» በማለት ለሁለተኛ ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ሲያስታዉቁ ለደርግም በደረሰው መልዕክት የናቅፋ ውጊያ ፍፃሜ መሆኑን ስለተገነዘብን ጠላት በጉምና በከምሲው እየተከለለ እንደመጠቀሙ ሁሉ እናንተም ከጉሙና ከከምሲው በተጨማሪ በምሽቱ ጨለማ ከለላ ተጠቅማችሁ በአመቻችሁ መንገድ የጠላትን ከበባ ሰብራችሁ በመውጣት ለናቅፋ ቅርብ ወደ ሆነው ወደ አፋቤት ለማፈግፈግ ሞክሩ የሚል ትዕዛዝ እንዲሰጣቸው ለሁለተኛ ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር መምሪያን በተለየ ሁኔታ ትዕዛዝ ሰጠን።

በኋላ እንደ አሳወቁን የመገናኛ ወታደራዊ ራዲዮናቸውን ጠላት እንዳይጠቀምበት ሲሉ ከጥቅም ውጭ አድርገውት ስለነበረ የማፈግፈግ ትዕዛዙን ከሰጠንበት ደቂቃ ጀምሮ ከ15ኛ እግረኛ ሻለቃ ጋር ግንኙነት ስላልነበረን በሻምበል ተስፋዬ ኃብተ ማሪያም የተመራው ጦር አፋቤት 16ኛው እግረኛ ሻለቃ ጦር ጠቅላይ ሠፈር ከገባ በኋላ ነው የሆነውን ሁሉ ማወቅ የተቻለው።

የሻዕቢያን የመጨረሻውን ከበባ በመስበር ከመጨረሻው ጥቃት ራሱን በማዳን ከናቅፋ ወደ አፋቤት ስለ አፈገፈገው ጦር ከመሪው ከሻምበል ተስፋዬ ኃብተማሪያም ሪፖርት እንደተረዳነው፣

1ኛ አብዛኛው ቁስለኞች በቀራቸው የመጨረሻ ኃይልና ትንፋሽ የመጨረሻውን የመከላከል ውጊያ ሲሳተፉ አብዛኛዎቹ በተደጋጋሚ የቆሰሉ ከመሆናቸውና ደማቸው ፈሶ በማለቁ ማፈግፈግ ስለተሳናቸው እየተዋጉ እምሽጋቸው ውስጥ ሲቀሩ፣ የሻለቃው አዛዥ ሻለቃ ማሞ ተምትሜ ከበባው በወገን ጦር ተሰብሮ ሰባሪው ጦር ማፈግፈግ ሲጀምር በጦሩ ድጋፍና እርዳታ ወደ አፋቤት የተወሰነ እርቀት ከተጓዘ በኋላ እኔን ተስፋ የሌለኝንና ያለቀልኝን ሰው ተሸክማችሁ ስትጓገዙ በሚባክነው ጊዜ ምክንያት ናቅፋን ከለቀቅን በኋላ አስፈላጊ ያልሆነ ከንቱ መስዋዕት መክፈል ስለሌለባችሁ እኔን እዚሁ ተውኝና መንገዳችሁን በፍጥነት ቀጥሉ።

ይሄ የኔ የአዛዣችሁ የመጨረሻ ትዕዛዝ ነው በማለት በመንገዱ ዳርቻ በነበረች አንዲት ቁጥቋጦ ውስጥ ገብቶ የታጠቀውን የሽጉጥ ጥይት በመጠጣት ራሱን ገደለ።

2ኛ የሻዕቢያን ከበባ ሠብሮ ከመጣው ጦር አብዛኛውና በሻምበል ተስፋዬ የተመራው ጦር ወደ አፋቤት የሚወስደውን መንገድ ሲጠቀም በጣም ጥቂት የ15ኛ ሻለቃና የአየር ወለዱ ጦር አባላት የከረንን መንገድ ይዘው ተጓዙ::

3ኛ የአፋቤትን መንገድ የተያያዙት አብዛኛዎቹ የጦሩ አባሎች በመንገዳቸው ላይ የተለያዩ የሻዕቢያ ደፈጣ እየገጠማቸው በቀልጣፋ ጀግንነት ጠላትን እየደመሰሱ በማለፍ ብዙ ከተጓዙ በኋላ በጉዞው ርዝማኔና በተለይም በውሃ ጥም እጅግ ተዳክመው ጦሩ በሙሉ ማለት ይቻላል አፋቤት ከተማ በጣም ከተቃረበ በኋላ መራመድ ተስኖት ሲወድቅ፣ በሻምበል ተስፋዬ ትዕዛዝ ጥቂት ብርቱ ወታደሮች አፋቤት 16ኛ እግረኛ ሻለቃ ጦር ሠፈር በመድረስ ስለአመለከቱና እርዳታ ስለጠየቁ ከውሃና ከምግብ ሌላ መጓጓዣ ተልኮላቸው የተላከላቸውን ውሃ ከጠጡና ምግቡን ከተመገቡ በኋላ ትንሽ አርፈው አፋቤት መግባት ቻሉ::

የ15ኛ እግረኛ ሻለቃ ባልደረባ የሆኑ 72 ሰዎችና የአየር ወለዱ ሻምበል ጦር አባል የሆኑ 23 ሰዎች በጠቅላላው 95 ሰዎች በጤና እንደደረሱ ሪፖርቱ አስገንዝቦናል::

የከረንን አቅጣጫ ይዘው የተጓዙት 20 የ15ኛ እግረኛ ሻለቃና የአየር ወለዱ ሻምበል ጦር አባሎች ከአመራር እጦትና በውጊያ ጊዜ ጠላት በሚቆጣጠረው ክልል ውስጥ የማምለጥና የመሰወር ጉዞ የሚያደርግ ጦር ሊመራበት የሚገባውን የጉዞ ሥነስርዓት ላለመቀበል በተፈፀሙ ስህተቶች ምክንያት ራሳቸውን ለጠላት ቃፊሮችና ለአካባቢው የጠላት ታጣቂዎች በማጋለጣቸው ሁሉም በጥይት ተደብድበው ሲወድቁ በወገን ሬሳ መሀከል በሙተኛት የሞተ መስሎ የተረፈና ቀን በጫካ ውስጥ በመደበቅ ሌሊት እየተጓዘ ከረን መግባት በቻለ ወታደር አማካኝነት ለመረዳት ተቻለ::

አብዮታዊ ጦራችን በኤርትራ ከገንጣዮች ጋር ለኢትዮጵያ አንድነት ባደረጋቸው ተጋድሎዎች በአንድ እግረኛ ሻለቃ ደረጃና አቅም የ15ኛ እግረኛ ሻለቃ ጦር ሻዕቢያን ከፍ ያለ መስዋዕትነት በማስከፈል የመጀመሪያውና ብቸኛው ወደር የሌለው ጀግና ጦር ነው::

አየር ወለድ ጦራችን ከአንድ ሻምበል ባነሰ አነስተኛ የሰው ኃይል ለወገኑ፣ ለአገሩና ለአብዮቱ ለመሰዋት በነበረው ፈቃደኝነት ናቅፋ አውሮፕላን ማረፊያ ሜዳ ላይ በድንገት በጃንጥላ ወርዶ በሻዕቢያ ላይ የተቀዳጀው ድል አየር ወለዳችንን ብቻ ሳይሆን መላውን አብዮታዊ ሠራዊታችንን ያኮራና በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ለዘላለም ሲታወስ የሚኖር ታላቅ ወታደራዊ ገድል ነው::

ከደርግ በተሰጠው መመሪያ መሠረት የጠላትን ከበባ ሠብረው በመውጣት አፋቤት የገቡት የ15ኛ እግረኛ ሻለቃና የአየር ወለድ ሻምበል አባሎች ወዲያው ከአፋቤት ወደ ከረን በሄሊኮፕተር ከከረን ወደ አስመራ በአውሮፕላን ተጓጉዘው በኤርትራ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የክፍለ ሃገሩ የበላይ አስተዳዳሪና በጦሩ የበላይ አዛዥ፣ በክፍለ ሃገሩ

ከፍተኛ ባለሥልጣኖች፣ በሁለተኛ ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር አዛዥና በክፍለ ጦሩ የበላይ መኰንኖች በአውሮፕላን ማረፊያ የጀግና አቀባበል ከተደረገላቸው በኋላ ጀግኖቹ በሙሉ ሆስፒታል ገብተው በማረፍ ሙሉ የጤና ምርመራና እንደ አስፈላጊነቱ መጠነኛ የሕክምና አገልግሎት ተሰጣቸው።

ከሆስፒታል ሲወጡ ለጀግናው ለ15ኛ እግረኛ ሻለቃ አዛዥ ለሻለቃ ማሞ ተምትሜ የኰሎኔልነት ለሻምበል ተስፋዬ ኃብተማሪያም የሻለቅነት ማዕረግ ሲሰጥ ለተቀሩትም ጀግና መኰንኖች፣ የበታች ሹማምንቶችና ተርታ ወታደሮች ሁሉ እንደ ጦር ሜዳ ሞያና ተግባራቸው የማዕረግ እድገት ተሰጣቸው።

ናቅፋ ላይ በተደረገው የመጨረሻው የመከላከል ውጊያ በተደጋጋሚ በመቁሰላቸውና ደማቸው ፈሶ በማለቁ ከወንድሞቻቸው ጋር ለማፈግፈግ ያልቻሉት ጀግኖች በሙሉ በህይወት በጠላቶቻቸው እጅ ላለመውደቅ ራሳቸውን እንደገደሉ ይታመናል።

በድህረ አብዮት በአገሪቱ አራት ማዕዘናትና በመሐል ከተስፋ ለዘውድ ፀረ-ህዝብ ፊዉዳሎች፣ ከአምስተኛ ረድፎች፣ ከአገር ገንጣዮችና ከውጭ ወራሪዎች ጋር ለተፋለሙና ለሚፋለሙ ጀግኖቻችን የሚሰጡ ኒሻኖችንና ሜዳዮችን እስከናዘጋጅና ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊታችን በሰሜን በገንጣዮች ላይ የመጀመሪያውን ድል እስኪቀዳጅ ድረስ ቆይተው ከተቀሩት ብዙሃን የኢትዮጵያ ጀግኖች ጋር የናቅፋው ጀግኖችም የተለያዩ ደረጃ ያላቸውን ታላላቅ የጦር ሜዳ ጀብዱ ሜዳይና ኒሻን ሲያገኙ ሌ/ኰሎኔል ተስፋዬ ኃብተማሪያም (በኋላ ብ/ጀነራል) በናቅፋ ብቻ ሳይሆን በምሥራቅ ግንባርም እንዲሁ የላቀ ጀብዱ ስለፈፀመ የህብረተሰባዊት ኢትዮጵያን የላቀ የአብዮታዊ ጀግና ሜዳይ አግኝቷል።

ክፍል ሃያ

ምዕራፍ ሠላሣ ስድስት

ከተሰነይና ከናቅፋ ውድቀት በኋላ ሁለቱም ገንጣይ ድርጅቶች በተለያየ ጊዜና በፈረቃ ባሬንቱን ለመቆጣጠር ያደረጉት ያልተሳካ ጥረት፤ የአቆርዳትና የከረን መያዝ::

በኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ አንድ እንደተገለፀው የተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት በሕዳር ወር 1970 ዓ.ም የሐረርጌን ክፍለ ሃገር ርዕሰ ከተማ ሐረርን ለመያዝ የመጨረሻውን ጥቃት በሠነዘረበት ጊዜ የኤርትራ ገንጣዮችም «ጀብሐና ሻዕቢያ» የተፈጠረላቸውን አጋጣሚ በመጠቀም ከሱማሌ ወራሪ ሠራዊት ጋር አብረው የኤርትራን ክፍለ ሃገር ርዕሰ ከተማ አሥመራን ለመቆጣጠር ለሁለተኛ ጊዜ ከቆላው ወደ ደጋው ክልል ያደረጉት መንደርደር ይታወሳል::

በኤርትራ ምድር በኢትዮጵያ አንድነት ኃይሎችና በከሐዲ አገር ገንጣዮች መካከል በቅድመ አብዮት ለ15 ዓመታት ሲካሄድ የነበረው የእርስ በርስ ጦርነት በድሕረ አብዮት ኢትዮጵያም በተባባሰ ሁኔታ ከመቀጠሉ ሌላ በተጨማሪ በመላው ኢትዮጵያም በተከሰተው በትጥቅ የታጀበ የጠባብ ብሄረሰቦች ፀረ-አንድነትና ፀረ አብዮት አመፅ፣ በጠቅላላው የመደብ ትግል፣ በተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወረራ ፍልሚያዎቹ የሚካሄዱባቸው ግንባሮች መስፋትና የአገሪቱ ጠላቶች መብዛት ምክንያት የምድር ጦር ሠራዊታችን እጅግ ከመወጠሩ ባሻገር የሚከፈለው መስዋዕት ባስከተለው ከፍ ያለ የሰው ኃይል እጥረት እንደገጠመን በብዙ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ የሚታወቅ ይመስለኛል::

በኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊትና በከሐዲ አገር ገንጣዮች መካከል ከማለት ይልቅ በኢትዮጵያ የአንድነት ኃይሎችና በከሐዲ አገር ገንጣዮች መካከል ያልኩበት ምክንያት የኤርትራ ክፍለ ሃገር ሕዝብ ለአንድነቱና ለኢትዮጵያዊነቱ ለሃምሳ ዓመታት ከኢጣሊያ ፋሽስቶች ጋር፣ ለአሥር ዓመታት ከእንግሊዝ ወታደራዊ አገዛዝ ጋር ከመታገል ባሻገር ከአብራኩ ከወጡ ገንጣዮች ጋር ከሰላሣ ዓመታት በላይ ስለተዋደቀ ነው::

በድህረ አብዮት በአገር ገንጣይ ከሐዲዎችና በኢትዮጵያ የአንድነት ኃይሎች መካከል ሲካሄድ የነበረው የትጥቅ ትግል ሂደት ለፍቶና አድኅ መላው የኤርትራ ምድር ማለት ይቻላል የጦር ሜዳ የሆነው በ1967 እና በ1968 ዓ.ም ሲሆን በ1969 እና በ1970 ዓ.ም አብዮታችንና አንድነታችን ብቻ ሳይሆኑ የኢትዮጵያ ህልውና እጅግ የከፋ አደጋ ላይ የወደቀበትና የውስጥና የውጭ ጠላቶቻችን ኢትዮጵያ አለቀላት ብለው ያሟረቱበት ጊዜ ነበር::

በዚህ እጅግ ፈታኝ በሆነ የጊዜ ክልል ውስጥ ሁለቱም ገንጣይ ድርጅቶች «ጀብሐና ሻቢያ» ከአረቡ ዓለም በገፍ በቀረበላቸው መሣሪያና ትጥቅ፣ የተለያዩ ቁሳቁሶችና ስንቃስንቅ ወዘተና በተፈጠረላቸው ለእነሱ ያመቸ ጊዜ ተጠቅመው ከደጋውም ከቆላውም ክልሎች ተዋጊ የሰው ኃይል በገፍ በመመልመልና አዲስ የውጊያ ሥልት በመጠቀም ሁለቱም ድርጅቶች ያላቸውን ኃይል እያሰባሰቡ በተራራቁ ሥፍራዎችና በየአውራጃዎቹ ፀጥታ የሚያስከብሩ የመንግሥቱን ተዋጊ እግረኛ ሻለቆችንና የፖሊስ ኃይሎችን ተራ በተራ እየከበቡ መደምሰስ ጀመሩ።

«ጀብሐ» በጋሽና ሰቲት አውራጃ ከተማ በተሰናይ የነበረውን የወገን 24ኛ እግረኛ ሻለቃ፣ «ሻዕቢያ» በሳህል አውራጃ በናቅፋ ከተማ የነበረውን የወገን 15ኛ እግረኛ ሻለቃ ጦሮች አጥቅተው ከተሞቹን ለመቆጣጠር በመቻላቸው ተብተውና ልብ አግኝተው ዳግም ጀብሐ የባሬንቱን ከተማ ለመቆጣጠር ተደጋጋሚ ግን ያልተሳካ ጥረት አደረገ። በኤርትራ ህዝብ መሃከል ከፌደሬሽኑ መፍረስ በኋላ ለአንድነቱና ለኢትዮጵያዊነቱ ከገንጣዮች ጋር በመታገል ወደር የሌለውን የኩናማ ብሄረሰብ ለማጥፋት ሁለቱም ገንጣዮች በፈረቃ ታላቅ ጥረት አድርገዋል።

ባሬንቱ ከሌሎቹ ቆላማ አውራጃዎች ጋር ሲመዛዘን ቅድሚያ የሚሰጠው ስትራቴጂካዊ አቀማመጥ ያለው አውራጃ ባይሆንም ጀግናውን የኩናማ ብሄረሰብ ከጥፋት ለማዳን ስንል ከተለያዩ የጦር ክፍሎች የተውጣጣ በቂ ኃይል በማሰማራታችንና ሕዝቡም የታጠቀ ስለነበረ፣ በባሬንቱ ከተማ ዙሪያ ያሉ ኮረብታዎች፣ ከፍተኛና ጠቀሜታ ባላቸው ወታደራዊ መሬቶች ላይ ጠንካራ ምሽጎችን መሽጎ ከአብዮታዊው ጦር ጋር በህብረትና በፅናት እየተዋጋ አሳፍሮ በመመለስ እስከ መጨረሻው ማለትም በምሥራቅ በወራሪው የሱማሌ መንግሥት የጦር ኃይል ላይ የተሟላድል ከተቀዳጅን በኋላ ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊታችን ገንጣዮችን ከኤርትራ ደጋማና ቆላማ ክልሎች እየመነጠረ ወደ ጠረፉና ወደ ሱዳን እስኪያባርራቸው ድረስ ባሬንቱ አልተደፈረም።

ባሬንቱን መቆጣጠር ባይቻላቸውም ደግሞ ጀብሐ ከተሰናይ በመንደርደር ከሻዕቢያ ጋር ተባብሮ መጋቢት 20 ቀን 1969 ዓ.ም በባረካ አውራጃ ብቻ ሳይሆን ለጠቅላላው የኤርትራ ቆላማ ክልል እንደ ርእሰ ከተማ በሚቆጠረው በአቆርዳት ከተማ የነበረውን የስምንተኛ እግረኛ ብርጌድ መምሪያ፣ የአንደኛ እግረኛ ሻለቃንና የአንድ ፖሊስ ኮማንዶ ሻለቃ ጦሮችን ከበው ከደመሰሱ በኋላ «ሻዕቢያ» ከናቅፋ ተንደርድሮ አፋቤት የነበረውን የወገን 16ኛ እግረኛ ሻለቃ ጦር በጠቅላላው በ1969 ዓ.ም አጋማሽ ጊዜ ብቻ የመንግሥቱን አራት እግረኛ ሻለቆች፣ ሁለት የፖሊስ ኮማንዶ ሻለቆች በፈረቃና በተከታታይ አጥቅተው የኤርትራን ምሥራቃዊና ምዕራባዊ ቆላማ አውራጃ ከተሞችን በሙሉ ለመቆጣጠር ቻሉ።

እነ ኡስማን ሳላሕሳቤ፣ እነ ረመዳን መሐመድ ኑርና እነ ተማሪ ኢሳይያስ አፈወርቅ ከጀብሐ አፈንግጠው ራሱን ሻዕቢያ ብሎ የሚጠራውን የጀብሐ አንጃ ድርጅት ከአቋቋሙበት ጊዜ ጀምሮ ሁለቱ ገንጣይ ድርጅቶች በሥልጣን ሽሚያ ሲዋጉ ኖረው በዚህ ጊዜ ውስጥ ማለትም በ1969- 1970 ዓመታቶች የኢትዮጵያ መንግሥት ጦር በብዙ የውጊያ ግንባሮች በተወጠረበትና ተዋጊ የሰው ኃይል እጥረት በደረሰበት ጊዜ ከሱማሌ መንግሥት ጋር ተባብረው የኢትዮጵያን አብዮታዊ መንግሥት በመጣል ኤርትራን ይገነጥሉ ዘንድ ያስታረቋቸውና ያስተባበሯቸው በሠላም ፍለጋና በእርቅ ሰበብ ጀነራል አማን መርጠው የላኳቸው የጥፋት ልዑካን ናቸው።

የስድስት ሻለቃ ጦሮች በገንጣዮች መደምሰስና ጠቅላላው የኤርትራ ቆላማ ክልሎች ከእጃችን መውጣት እንደ እግር እሳት ቢለበልበንም ለደጋውና ለቆላው ክልሎች እንደ መገናኛ በር የሚቆጠረውና ስትራቴጂካዊ አቀማመጥ ያለው የከረን አውራጃና በተለይም ከተማው በእኛ ቁጥጥር እስካለ ድረስ በመሃል አገር ስልጠና ላይ የነበሩትን ሁለት እግረኛ ክፍለ ጦሮች ወደ ሰሜን በመውሰድ ከረን ላይ ከሚገኘው ግብረ ኃይል ጋር አቀናጅተን በአጭር ጊዜ ውስጥ መልሰን ለማጥቃት ተዘጋጅተን ሳለ ወራሪው የሱማሌ መንግሥት ሠራዊት ባልተጠበቀ ሁኔታ የሐረርን ከተማ መክበብና ብሎም ለመቆጣጠር መቃረብ የኤርትራን ቆላማ ክልል መልሰን ለመያዝ ያቀድነውን ዕቅድና ለአፈፃፀሙም ያደረግነውን ያለቀለት መሰናዶ አከሸፈው።

የእቅዳችንን መክሸፍ የተገነዘቡት ገንጣዮች ማለትም «ጀብሐ» ከአቆርዳት ተንደርድሮ በድጋሚ ባሬንቱ የነበረውን አብዮታዊ ጦራችንን ሲወጋ «ሻዕቢያ» ከአፋቤት ተንደርድሮ መሳህሊት በር ላይ መሽጎ የተቀመጠውን መጠነ ሰፊ ጦር አጠናክሮ ከረን ከተማ ላይ ያለውን ጦራችንን መውጋት ጀመረ።

የኤርትራ ክፍለ ሃገር ደጋማና ቆላማ ክልሎች መለያ ድንበር ወይንም ወሰን በመሆን ዝቅተኛውን ወይም ቆላማ ምድር የሚገዛውና ዙሪያውን በኰረብታ ሰንሰለቶች ተከቦ በከፍተኛ መሬት ላይ የተቀመጠው የከረን ከተማና አካባቢው፣ ከቆላው ምድር የሚመጣን ጠላት አቁሞ ለረዥም ጊዜ ለመከላከልና ብሎም መልሶ ለማጥቃት በጣም አመቺ ነው።

ይህም በአንድ የታሪክ አጋጣሚ ማለትም፣ እንደ ኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር በ1940 ዓ.ም የኢትዮጵያ ህዝብ ለነፃነቱ የሚያደርገው የትጥቅ ትግል አጋር በመሆን የፋሽስት ኢጣሊያን ወራሪ ሠራዊት ከኤርትራ ምድር ለማስወጣት ከሱዳን ምድር የተነሳው የሕንድ፣ የአፍሪካና የብሪታኒያ ዜጎች ቅምር ወይም ቅይጥ የጦር ኃይል ወደ ኤርትራ ደጋማ ክልል በመዝለቅና ብሎም የኤርትራን ክፍለ ሃገር ርዕሰ ከተማ አሥመራን ለመቆጣጠር በወራሪው የፋሽስት ኢጣሊያ ሠራዊት ላይ የሠነዘረው ጥቃት ለአያሌ ወራቶች የተገታበትና በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ወታደሮች ህይወት ሲያስከፍል ይህንኑ ያህል በመቁሰል ከውጊያ ውጭ እንዲሆኑ አድርጓል።

አንባቢ እንደሚያስታውሰው በ1969 ዓ.ም ህረት በጥቅምት ወር ራሱን ሻዕቢያ ብሎ የሚጠራው አገር ገንጣይ ድርጅት የወገን ጦር ባላሰበውና ባላወቀው ጊዜና ሁኔታ ከሱዳን ግዛት በመንደርደር በቅድሚያ ቃሮራ ላይ የነበረውን የ15ኛ እግረኛ ሻለቃ አንድ ተነጣይ እግረኛ ሻምበል በሌሊት በመክበብ አጥቅቶ ከደመሰሰ በኋላ ወደ ናቅፋ በማምራት የናቅፋን ከተማ፣ የ15ኛ እግረኛ ሻለቃን የጦር ሠፈርና ራሱን የሻለቃውን ጦር በከበበ ጊዜ የሁለተኛ ዋለያ እግረኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ወዲያው በአጣዳፊ ከተለያዩ እግረኛ ብርጌዶች የተነጠሉ ወይንም የተወጣጡ ሁለት እግረኛ ሻለቆችን፣ ሁለት ፈጥኖ ደራሽ ኮማንዶ ሻለቆችና አንድ አየር ወለድ ሻለቃ አሰባስቦ በከባድ መሣሪያዎችና በተዋጊ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች በማጠናከር የክፍለ ሃገሩ ፖሊስ ሠራዊት አዛዥ በነበሩት በኮሎኔል ለሜሳ በዳሶ አዛዥነት አንድ መቺ ግብረ ኃይል ከረን ከተማ ላይ ማደራጀቱ ይታወሳል።

ይህ ግብረ ኃይል ሻዕቢያ የመሸገበትን የመሳህሊትን በር ሠብሮ ለማለፍ ቢሳነውም ከጦሩ ብዛትና የከረን ከተማ የተቀመጠበት መልክአ ምድር ለመከላከል ባለው አመቺነት ከገንጣዮች በሚገባ ተከላክሎ የወገን ጦር መልሶ ለማጥቃት እስከሚችልበት ጊዜ ድረስ ያቆያል የሚል ተስፋ ነበረን።

በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ የአገሪቱ ጠላቶችና የአብዮቱ ፀሮች ኢትዮጵያ አለቀላት እያሉ በሚነዙት መሰሪ ፕሮፖጋንዳ ህዝቡ እንደመረበሹ ሁሉ በአብዮታዊ ሠራዊታችንም ውስጥ በጥቂቱም ቢሆን ለጠላት ፕሮፖጋንዳ ጆራቸውን በመስጠታቸው በተለይ በጉዳዩ አስቸኳይነት የተነሳ ከየጦር ክፍሉ ተወጣጥቶ የተሰባሰበው የጦሩና የፖሊስ ቅይጥ ግብረ ኃይል በፀረ-አንድነትና በፀረ አብዮት ኃይላት የተበረዙና በጠላት ፕሮፖጋንዳ የተመረዙ ይመስላል የአየር ወለዱ ሻለቃው ብቻ ሲቀነስ ሶስተኛ እግረኛ ብርጌድ መምሪያ አመራር ሥር በተለያዩ ከባድ መሣሪያዎችና በተዋጊ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች የተጠናከረው ግብረ ኃይል በሙሉ ያለአንዳች ውጊያ እጁን ለሻዕቢያ ሰጠ።

ሻዕቢያ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአያሌ ከባድ መሣሪያዎችና ብረት ለበሶች ጋር ቁጥራቸው እጅግ በርካታ የሆኑ ልዩ ልዩ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎችን ከአንድ ብርጌድ መምሪያ ጋር አራት ሻለቃ ጦሮችን ያለውጊያ በቀላሉ መማረክ ቻለ።

በዚሁ ጊዜ ውስጥ በጐንደር ክፍለ ሃገር ጠረፍ በሁመራ አውራጃ ከተማ ላይ ሆኖ የአካባቢውን ፀጥታና የአገሪቱን ጠረፍ እንዲያስከብር የተሰማራው፣ በአቆርዳት ከተማ በጀብሐና በሻዕቢያ ሕብረት የተደመሰሰው የስምንተኛው እግረኛ ብርጌድ አካል የሆነው አራተኛ እግረኛ ሻለቃ ያለ አንዳች ውጊያና የጠላት ተፅእኖ እጁን ለሱዳን መንግሥት በመስጠት ሱዳን ግዛት ከገባ በኋላ ራሱን የኢትዮጵያ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ህብረት ብሎ ሚጠራው ተስፋ ለዘውድ ከፊዉዳሎች ጥርቅም ድርጅት ጋር ተቀላቀለ።

1ኛው አብዮታዊ ሠራዊታችን በባሌና በሲዳሞ ክፍለ ሃገራት ሰባት መቶ ኪ/ሜትር ጠለቆ ከገባው ወራሪ ሠራዊት ጋር ተናክሶ ባለበትና፣ በሐረርጌ ክፍለ ሃገር ርዕሰ ከተማ በሐረር በ15 እና በ20 ኪ/ሜትር ርቀት ተከቦ የሞት ሽረት ተጋድሎ በሚያደርግበት ጊዜ በሰሜን ኢትዮጵያ በ1969-1970 ዓ.ም ብቻ በኤርትራ ቆላ በውጊያ ጀብሐና ሻዕቢያ ሰባት ሻለቃ ጦር ሲያሳጡን፤ በከረንና በሁመራ ያለውጊያ ለጠላት እጃቸውን ከሰጡት ጋር አስራ ሁለት ተዋጊ ሻለቆችን አጣን።

የኤርትራ ደጋማ አውራጃዎች ጠላትን መመከቻ፣ በርና ለመከላከል ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያለውን የከረንን ከተማ ማጣት ገንጣዮች በደጋማው ኤርትራና በከፊል ምሥራቃዊ ቆላማ ምድር ማለትም በምፅዋ አውራጃ ወዘተ እንደፈለጉ እንዲፈነጩ ሰፊ ዕድል የሰጣቸው ታላቅ ድል ሲሆን ለሰሜኑ ሠራዊታችን ታላቅ ውድቀት ነበር።

ምዕራፍ ሠላሣ ሰባት

የከረን በር ከተጣሰና የከረን ከተማ በገንጣዮች እጅ ከወደቀ በኋላ ለቀጣዩ አንድ ዓመት አብዮታዊ ሠራዊታችን፣ በባሬንቱ ከተማ፣ በደጋማዎቹ አውራጃዎች፣ በምፅዋ ከተማና ወደቡ ያደረገው ፍልሚያ።

በ1968- 1969 ዓ.ም በኤርትራ ቆላማ አውራጃዎች በተደረጉ ፍልሚያዎች የተሰውትና በከረንና በሁመራ ያለው ጊያ ለጠላት እጃቸውን የሰጡት የሰሜኑ ጦራችን ከፊል የሆኑት የጦር ክፍሎች በመቀነሳቸው ከፍ ያለ የኃይል እጥረት ከመድረሱ ሌላ የጦሩ ሞራልና የተዋጊነት መንፈስ የተጎዳ ሲሆን፣ ገንጣዮች በተቀዳጁት ጊዜያዊ ድል ተኩራርተውና ተብተው በመላው ደጋማ አውራጃዎች ማለትም፣ በአካለጉዛይ በሠራዬና በሐማሴን የውጊያ ቀጠናዎችን ተከፋፍለው በቅንጅት ጠቅላላ ወረራ ስለጀመሩ አብዮታዊ ሠራዊታችን በሙሉ ያለ እረፍት በየቀኑ ለሕዝቡ ሠላምና ደህንነት፣ ለእያንዳንዱ አጥቅ የደጋው መሬት ከገንጣዮች ጋር በመፋለም እየጣለ ይወድቅ ነበር።

አንባቢ እንደሚያስታውሰው በኤርትራ ያለው ጦራችን በገንጣዮች ላይ በነበረው ሁለንተናዊ የበላይነት ፍልሚያው ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 1967 ዓ.ም ድረስ የማጥቃቱ ቀደምትነት በሠራዊታችን እጅ ስለነበረ ገንጣዮችን እያሳደደና የገቡበት እየገባ ይመታቸው ነበር።

ከ1967 ዓ.ም መጀመሪያ ጀምሮ የአካባቢው ነባር የኢትዮጵያ ጠላቶች ብቻ ሳይሆኑ ኢምፔሪያሊዝምና አድሀሮት ለገንጣዮች የሚሰጡትን ሁለገብ ድጋፍ በእጥፍ ድርብ በማሳደጋቸው ገንጣዮቹ በማምረቻ ድርጅቶች፣ በልዩ ልዩ የልማት ድርጅቶች፣ የሕዝብ መኖሪያ በሆኑ ከተሞች፣ በመንገድና ድልድዮች፣ በውሃ ማደያዎች ላይ አደጋ እየጣሉ ከማፈራረስና ንብረት ከማውደም አልፈው የስልክና የኤሌትሪክ መሥመሮችን መበጣጠስ በመጀመራቸው ጦራችን እነኝህን የገንጣዮች የጥፋት ኢላማ የሆኑ ድርጅቶች፣ ልማቶችና ንብረቶች በቋሚነትና በሚያስተማምን ሁኔታ ለመከላከል ሲባል ጦራችን ከአጥቂነት ወደ ተከላካይነት መዛወር ቢገደድም ከገንጣዮች ጋር የነበረው የኃይል ሚዛን ለወገን ጦር ያደላ ነበረ።

ከ1969 ዓ.ም ሰኔ የተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ጦር ዓለም አቀፍ ድንበራችንን በሦስት አቅጣጫ ማለትም፣ በሐረርጌ፣ በሲዳሞና በባሌ ጥሶ 700 ሰባት መቶ ኪ/ሜትር ከገባና የከረን ከተማ በገንጣዮች እጅ ከወደቀ በኋላ በአብዮታዊ ሠራዊታችንና በገንጣዮች መካከል ያለው የኃይል ሚዛን ወደ ጠላት ያደላ ሆነ።

አብዮታዊ ሠራዊታችን ቀደም ብዬ ከዚህ በላይ የጠቃቀስኳቸውን ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው የተለያዩ ነጥቦችን ብቻ ሳይሆን የብዙ ሕዝብ መናኸሪያ የሆኑትን

የደጋማው አውራጃ ከተሞችን ከገንጣዮች ወረራ ለመከላከል በሚያደርገው ጥረትና የሚጠበቁ ቦታዎች ከመብዛታቸውና ሠራዊታችን የሚዋጋባቸው የውጊያ ቀጠናዎች ከመስፋታቸው የተነሳ ገንጣዮች በሚያገኟቸው ክፍተቶች ወደየአውራጃው ከተሞች ብቻ ሳይሆን አሥመራ ከተማ ድረስ ሠርገው በመግባት ሠላማዊዎቹን ወይንም ሲቪሎቹን የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ የሠራዊቱን አዛዥ መኰንኖችና በተለይም የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት የአገር ፍቅር ማህበር አመራር አካላትን በነቂስ እያደኑ በቀን ብርሃን መግደል ጀመሩ::

የተለያዩ የመንግሥት፣ የድርጅቶችንና የግለሰቦችን ንብረት ከማውደም ባሻገር የአየር ኃይል ሠራዊታችንን የጦር ሠፈር ከነተዋጊ አውሮፕላኖቹ ጋር ለማጥፋት ያልተሳካ ሙከራ ከማድረግም አልፈው፣ የጦር መሣሪያዎች፣ የተለያዩ ጥይቶችና ፈንጂዎች፣ ትጥቆች፣ አልባሳትና ሥንቆች የተከማቹበትን በአሥመራ ከተማ ውስጥ የነበረ የሰሜኑን ሠራዊት ዋና ግምጃ ቤት የአሥመራ ከተማ የተቀመጠበት ምድር እስኪንቀጠቀጥ ድረስ በፈንጂ አጋዩት::

አለን የምንለው የአገሪቱ የምድር ጦር ሠራዊት በሙሉ ማለት ይቻላል ከወራሪው የሱማሌ መንግሥት የጦር ኃይል ጋር በመተናነቅ ላይ ስለነበር ከሰሜን ገንጣዮች ጋር ለሚታገለው አብዮታዊ ሠራዊታችን የምንልክለት ምንም ዓይነት ጦር አልነበረንም::

በዚህ ጊዜ ነበር ከዚህ በፊት ያልተደረገና ያልተለመደ መላ በመፈለግ ከመሃል ኢትዮጵያ በቅደም ተከተል ከዚህ በታች የተመለከቱትን ረዳት ኃይሎች በዳግም የእናት አገር ጥሪ ወደ ሰሜን መላክ የቻልነው::

በ1ኛ ደረጃ፤ በምድር ጦር ሠራዊታችን ውስጥ የሰባት ዓመት ግልጋሎት ሰጥተው ወደ ሠላማዊ ኑሮ የተሰናበቱትን ወታደሮች ለዳግም ግልጋሎት በጦር አቋም በማደራጀት የተሐድሶ ሥልጠና በመስጠት ሁለት ብርጌድ ጦሮችን ላክን::

በሁለተኛ ደረጃ፣ በቅድመ አብዮት የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የየክልሉን ፀጥታ ለማስከበርና ከውጭ የባዕዳን ወረራ ቢሠነዘርብን በክተት ጥሪ ለመጥራት በሚል ሰበብ መደበኛ ሠራዊቱ በመንግሥት ላይ ቢያምፅ ለመቃወም ወይም ለመከላከል የሚችል አንጻ ኃይል ለመፍጠር ተብሎ ብሄራዊ ጦር በተሰኘ ስም ከገበሬው መሃል በመመልመል በተወሰኑ ክፍለ ሃገራት በተለይም በመሃልና በሰሜን እያሠለጠነ በዚያው በገበሬው ውስጥ በጦር አቋም ማደራጀት ተጀምሮ ስለነበር ከእነዚህ መሃል ሦስት ሻለቃ ጦር በመመልመል፣ በጦር አቋም በማደራጀትና የተሃድሶ ሥልጠና በመስጠት አሰማራን::

በ3ኛደረጃ፣ ለረጂም ዓመታት በምድር ጦር ሠራዊታችን ውስጥ አገልግለው በጡረታ በመሰናበት እረፍት ላይ ከነበሩት አባት ጦሮች መካከል እድሜያቸው በስልሳ ዓመት ክልል ውስጥ ያለና ጤንነት ያላቸውን ከየነበሩበት ክልል በመመልመል

የተሃድሶ ሥልጠና ሳያስፈልጋቸው በሻለቃ ጦር ደረጃ አደራጅተን ስድስት ሻለቃ ጦር ላክን።

እነዚህ በእናት አገር ጥሪና በፈቃዳቸው የመጡ ምልስ ጦሮች በተለይም የሰባት ዓመት ምልሶችና ብሄራዊ ጦሮች ካላቸው ወታደራዊ ልምድ፣ ወታደራዊ መሰናዶና ከውጊያ ብቃት አንፃር ከፍተኛ የደፈጣ ውጊያ ሥልጠና፣ የብዙ ዓመታት የውጊያ ልምድና ከፍተኛ የመንቃንቅ ችሎታ ያለውን ገንጣይ ጎሪላ ተንቃንቀው ለማጥቃት የሚመጥኑ ስላልነበሩና አባት ጦሮችም ቢሆኑ ረጂም ወታደራዊ ልምድና ተመክሮ ያላቸው ይሁኑ እንጂ ከጡረታ እረፍት ተመልሰው ከጎሪላ ጋር እየሮጡ እንዲዋጉ ስለማይጠበቅ መደበኛው ጦር በቋሚነት ከገንጣዮች ጥቃት የሚጠብቃቸውን የመንግ ሥት መሥሪያ ቤቶች፣ የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶች፣ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ የሆኑ ተቋማትን ጥበቃ እንዲረከቡና መደበኛው ጦር በውጊያው ላይ ሲያተኩር እነሱም የመከላከሉን ውጊያ እንዲያጠናክሩና እንዲረዱ ብቻ ተደረገ።

የአባት ጦሮች የረጂም ጊዜ ወታደራዊ ተመክሮና ጥልቅ የሃገር ፍቅር ስሜት፣ ለእናት አገራቸው በእርጅና ዘመናቸው ከጡረታ እረፍት ላይ ተነስተው በጦር ሜዳ የሰጡት አገልግሎት፣ ያሳዩት የነበረው ሥነ ሥርዓት አክባሪነትና ጀግንነት ለመላው አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊታችን ታላቅ አርአያነት ነበረው።

አባት ጦሮች፤ የአሥመራን ከተማ ውስጥ፣ የአዲ ቀይህን ከተማ ውስጥ፣ የምፅዋን ከተማ፣ የወደቡን ዙሪያና በተለይም ከወደቡና ከከተማው ፊንጠር ብሎ የሚገኘውንና ጉጉርሱም በተባለው ሥፍራ ላይ የሚገኘውንና የገንጣዮች የጥፋት ዒላማ የነበረውን የሲሚንቶ ፋብሪካ ደሕንነትና ፀጥታ ብዙ ሊያሻሽሉት ቢችሉም ወደ ገንጣዮቹ ያጋደለውን የኃይል ሚዛን ግን የሚለውጡ አልሆኑም።

አባት ጦሮች በተደረገላቸው የእናት አገር ጥሪ በፈቃዳቸው ለፍልሚያ የተሰለፉት በሰሜን ግንባር ብቻ ሳይሆን በምሥራቅም ነበር።

በምሥራቅ ግንባር የሐረርን ከተማ ከሱማሌ ሠራዊት ወረራ ለማዳን በተደረገው ቀውጢ ውጊያ ውስጥ ከአደረጉት ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ሌላ ከጂቡቲ እስከ አዲስ አበባ ከተማ የተዘረጋው የባቡር ሐዲድ የተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት የጥፋት ዒላማ ስለነበረ ከአዋሽ ድልድይ ጀምሮ እስከ ደወሌ ድረስ 600 ኪ/ሜትር ርዝመት ያለውን የባቡር መጓጓዣ መሥመር ከሱማሌ መንግሥት ወታደሮች ጋር ብቻ ሳይሆን ከአገር ተወላጅ ምንደኞች ጋር ጭምር እየተዋጉ ከጥፋት ተከላክለው ለማቆየት ችለዋል።

ድንበራችንን 700 ኪ/ሜትር ጥሶ የገባውን ቁጥሩ 158.000 አንድ መቶ ሃምሳ ስምንት ሺህ የሚደርስ ሜካናይዝድ ጦር በሰባት ወር ውጊያ ከፊሉን ደምስሰን ከፊሉ

ፈርጥጦ ወደ አገሩ እንዲመለስ ማድረግ ስንችል የሰሜኑ የእርስ በርስ ጦርነት ሳይቆም የአገሪቱ ጠላቶችና የሕዝባዊው አብዮታችን ዐሮች እየተቀባበሉ ከሰላሣ ዓመታት በላይ ስለ አራዘሙት፣ እኔ እስከማውቀው ድረስ ወደ ሰሜን የጦር ግንባር ከዘመቱት የአባት ጦር አባላት መካከል አንድም ግለሰብ ወደቤቱ የተመለሰ የለም።

«ጀብሐ» የኤርትራን ክፍለ ሃገር ደጋማ ሰሜንና ሰሜን ምዕራብ ክልል፣ «ሻዕቢያ» ምሥራቃዊውንና ምሥራቃዊ ደቡቡን ክልል የውጊያ ቀጠና ተከፋፍለው በአደረጉት ተከታታይ የጥቃት ዘመቻ የሠራዊቱንና የአካለ ጉዛይን አውራጃዎች አብዛኛውን ገጠር መቆጣጠር ቻሉ።

ከዚህ ከፍ ብዬ በብዙ አጋጣሚ እንደገለፅኩት በመላ የአገሪቱ አራት ማዕዘናት በውጊያ በመወጠራችንና በሠራዊታችን ላይ በደረሰው ተደጋጋሚ ከፍ ያለ ጉዳት ምክንያት በገጠሙን ከፍ ያለ የሰው ኃይል እጥረት የሕዝቡ መናኸሪያ የሆኑትን ከተሞች ሁሉ ከጥቃት ለማዳን ባለመቻላችን ከአዲቀይሕና ከሐማሴን አውራጃ ከተሞች በስተቀር የተቀሩትን የአውራጃ ከተሞች ማለትም፤ አዲኳላንና መንደፈራን ያዙ። ከዚህ ሌላ ከአሥመራ ከተማ ውጭ ያሉትን ከተሞች፣ ደቀ መሐሪንና ሰንአፌን ወዘተ ተቆጣጥረው በእነዚህ ከተሞች ጥበቃ ላይ የነበረውን የወገን 8ኛ እግረኛ ሻለቃ ጦር ደመሰሱ። ከትግራይ ክፍለ ሃገር ከአድዋ አውራጃና ከአዲግራት አውራጃ ወደ ኤርትራ ክፍለ ሃገር የሚወስደውን ሁለት አውራ የየብስ ተሽከርካሪ ጎዳናዎች በመዝጋት የኤርትራን ክፍለ ሃገር ከተቀረው ኢትዮጵያ ቆረጡት።

ከመሐል ኢትዮጵያ በየብስ መጓጓዣ የኤርትራን ክፍለ ሃገር የሚያገናኙት አውራ መንገዶች በገንጣዮች መዘጋት ማለት ለገንጣዮች የቱን ያህል ታላቅ ድል እንደሆነና በአገሪቱ ላይ በአጠቃላይ፤ በኤርትራ ክፍለ ሃገር ሕዝብና በሠራዊታችን ላይ በተለይ ያስከተለውን ሁለንተናዊ ጉዳትና ችግሮች በኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ አንድ በዝርዝር ያስረዳሁ ስለሆነ እዚህ ላይ ዳግም መመለሱ አስፈላጊ አይሆንም።

የተቀረውን ኢትዮጵያ ከኤርትራ ክፍለ ሃገር ጋር እንዳይገናኝ መንገዶችን በጦር ከዘጉ በኋላ የገንጣዮቹ ቀጣይና ተከታታይ ዕያሄ ተግባር የአሥመራን ከተማ ከምፅዋ ወደብ ጋር የሚያገናኘውን መንገድ መዝጋት ነበር። ይህን ያደረጉት የምፅዋን ከተማ ከነወደቡ በመቆጣጠር ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል የሚያስችላቸውን የመጨረሻ ወረራ ለማድረግ እንደሆነ ከእኛ የተሠወረ አልነበረም።

ስለሆነም፣ በመሐከላዊ ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የተለያዩ ክልሎች ሁለት ዓይነት የጦር ማደራጀት ተግባር የሚከናወን ሲሆን፣

1ኛውና መለስተኛው ዝግጅት የምለው፣ አብዮታዊው የመከላከያ ኃይላችን በምሥራቅና በደቡብ ከሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጋር የሚያደርገውን ትግል

በድል ደምድሞ ፊቱን ወደ ሰሜን እስኪያዞር ድረስ በሰሜን ገንጣዮችን በመገሠፅ ከሩጫቸው የሚያቆማቸው ሲሆን፣ የዝግጅቱ ይዘት ጥሩ ሥልጠናና የውጊያ ብቃት ያለው መጠኑ የተወሰነ መደበኛ ጦር ወደ ሰሜን በመላክ የመከላከሉን ውጊያ ለማጠናከር ነበር።

2ኛው ዝግጅት አያሌ የተለያዩ መደበኛ ጦሮችን ብቻ ሳይሆን ሁለተኛውን ዙር የሕዝባዊ ሠራዊት ሥልጠና ያካተተና የተስፋፊውን የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት መልሶ ለማጥቃት የሚደረግ ዝግጅት ነበር።

እስከዚህ ጊዜ ድረስ ገንጣዮች የአሥመራን ከተማ ከበባ ከቀን ወደ ቀን እያጠበቡ ለመቅረብ፤ አብዮታዊ ሠራዊታችን በበኩሉ የገንጣዮችን እርምጃ ለማቆም በሐማሴን አውራጃ በአሥመራ ከተማ ዙሪያ ያላሰለሰ ፍልሚያ በሚካሄድበት ወቅት፤

በ1ኛ ደረጃ ጥሩ ሥልጠና የተሰጣቸው ብቻ ሳይሆን ጥሩ አብዮታዊ ሞራልና ጥሩ የተዋጊነት ዝና ካተረፉትና ነበልባል በመባል ከሚጠሩት የጦር ክፍሎች አራት እግረኛ ሻለቆች ላክን።

በ2ኛ ደረጃ አዲስ ካሰለጠናቸው እግረኛ ክፍለ ጦሮች ውስጥ፣ በኰሎኔል መርዕድ ንጉሴ የሚመራውንና በዕዙ ሥር አራት እግረኛ ብርጌዶች ያሉትን ሰባተኛውን እግረኛ ክፍለ ጦሮችን በመላክ የአሥመራ ከተማን ዙሪያ መከላከል ብቻ ሳይሆን ባሬንቱን፣ አዲቀይሕንና ምፅዋን የሚከላከሉትን የጦር ክፍሎች ስለአጠናከርናቸው ገንጣዮች አሥመራን የከበባ ቀለበታቸውን ለማጥበብ የሚያደርጉትን ጥረት መግታት ብቻ ሳይሆን መልሶ በመግፋት የቦታ ይዞታችንንም ለማሻሻል ተሞከረ።

በዚህ አጋጣሚ ለአንባቢ መግለፅ ያለብኝ የኢትዮጵያ ተማሪዎች በማህበራቸው የአመራር አካላት ቅስቀሳ የአፄ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ከኤርትራ ገንጣዮች ጋር ሆነን እንዋጋለን ብለው የተሰባሰቡ በጣም ጥቂት የትግራይ ጠባብ ብሄርተኞችን ለማጎላበት ጀብሐና ሻዕቢያ ጥረት የሚያደርጉበት ጊዜ መሆኑን ነው።

በምሥራቅና በደቡብ የጦር ግንባር ድል እስከናገኝ ድረስ በሰሜን የሚደረገውን የመከላከል ውጊያ ለማጠናከር ከመሐል አገር በየጊዜው የተለያየ ዓይነትና መጠን ያላቸውን የጦር ክፍሎች በመላክ የተደረገው የኃይል ግንባታ ሲገመገም ቀድሞ ማለትም ፍልሚያው ከመጀመሩ በፊት የኤርትራ ፌደሬሽን ሲቋቋም የኤርትራን ክፍለ ሃገር ህዝብ ደህንነትና የክልሉን ፀጥታ የማስከበር ሃላፊነት በተረከበው በሁለተኛ ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር ዕዝ ሥር ከሚመራው የጦር ብዛት ሦስት ጊዜ የላቀ ስለሆነ አዲስ አበባ በሚገኘው ብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ ሥር ሆኖ የሰሜኑን ውጊያ የሚመራ የሰሜን ዕዝ የተባለ የዕዝ ማዕከል አቋቋምን።

ይህ ዕዝ በተቋቋመ ማግሥት በታሪካዊው የታጠቅ ጦር ሠፈር በመጀመሪያው ምዕራፍ ከሠለጠኑት ሕዝባዊ ሠራዊታችን መካከል፡-

1ኛ በሌ/ኰሎኔል ተስፋዬ መኩሪያ የሚመራ 1ኛውን ሕዝባዊ ሠራዊት ክፍለ ጦር በአሰብ ወደብ በኩል በባሕር መጓጓዣ ወደ ምፅዋ ላክን።

2ኛ በሌ/ኰሎኔል አበራ አበበ የሚመራ 3ኛውን ሕዝባዊ ሠራዊት ክፍለ ጦር በአየር መጓጓዣ ወደ አሥመራ ላክን።

በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ የሰሜኑን ጦር በመምራት አምስት ከፍተኛ መኰንኖች ተፈራርቀዋል ስድስተኛውና በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ የሰሜኑን ዕዝ አመራር የተረከቡት ኰሎኔል መርዕድ ንጉሴ ነበሩ።

ምዕራፍ ሠላሣ ስምንት

በደቡብ ኤርትራና በምዕዋ አውራጃ በአጠቃላይ በምዕዋ የወደብ ከተማ በተለይ ለረጂም ጊዜና በተደጋጋሚ በአብዮታዊ ጦራችንና በሻዕቢያ መካከል ከተደረጉት መራራ ተጋድሎዎች የመጀመሪያው ክፍል።

በአብዮታዊ ሠራዊታችንና በሻዕቢያ መካከል በምዕዋ ምድር ለረጂም ጊዜና በተደጋጋሚ የተደረጉት ፍልሚያዎች በጠየቁት የጊዜ መጠን ውጊያው የተካሄደበት ከአርባ ድግሪ ሴንቴ ግሬድ በላይ የሆነው የአየሩ ሙቀት፣ ከጠላት የመሬት ይዞታ ጋር ሲነፃፀር ለአብዮታዊ ሠራዊታችን እጅግ አስቸጋሪ የሆነው የመልክአ ምድር አቀማመጥና ወታደሩ የለበሰውን ልብስ ብቻ ሳይሆን ያደረገውን መጫሚያ ሳይቀር እየበላና እየቀረደደ የሚጥለው የጨው ማሳ ምሽግ፣ የውጊያው ጠቅላላ ባህሪና በሁለቱም ተፋላሚዎች በኩል የተከፈለው መስዋዕትነት ከሠላሳ ዓመታት በላይ በተካሄደው የእርስ በርስ ጦርነት በየትኛውም የጦር ሜዳ ያልተደረገና ራሱን የቻለ አንድ ትልቅ መጽሃፍ የሚወጣው፣ እጅግ አሳዛኝ ብቻ ሳይሆን እጅግ ዘግናኝ የውጊያ ታሪክ ነው።

በዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማህበራዊ አብዮት የትግል ታሪክ በጥቂቱ ቆንጥሬ ለአንባቢ ያቀረብኩት የመጽሃፍ ክፍ የሚገልፀው የውጊያውን አጀማመርና የመጀመሪያውን ክፍለ ታሪክ ብቻ ነው።

ወደ ውጊያው ታሪክ ከማምራቴ በፊት ውጊያው የተካሄደበትን መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የምዕዋን ከተማና ቀይ ባሕርን በጥቂቱም ቢሆን ለአንባቢ ማስተዋወቅ አስፈላጊ ይመስለኛል።

ምዕዋ የምንለው የወደብ ከተማ የኤርትራ ክፍለ ሃገር ርዕሰ ከተማ ከሆነው ከአሥመራ የሚርቀው በአንድ መቶ ኪሎ ሜትር ነው።

የሐማሴን አውራጃ ዋና አካል የሆነው የአሥመራ ከተማ የተገነባበት መሬት ከጠቅላላው የአውራጃው ምድር አንፃራዊ ስፋትና ዝርግነት ወይንም ሜዳማነት ያለው ነው።

ከከተማው ክልል ወጣ ብለው ከሚገኙት ትንንሽ ከተሞች ከጊንዳ፣ ከአምባተካላና ከነፋሲት ወዘተ ጀምሮ ያለው የሐማሴን አውራጃ ደቡባዊና የምፅዋ አውራጃ ሰሜናዊ ክልሎች በጠቅላላ ማለት ይቻላል እስከ ዶጋሊ ድረስ እንደ ሠንሰለት የተያያዘና የአሥመራንም የምፅዋንም ከተሞች የሚገዛ ከፍተኛ ኮረብታማ ምድር ነው።

ተያይዘው እስከ ዶጋሌ ድረስ አዘቅዝቀው የሚወርዱት ኮረብቶች ወይንም ከፍተኛ መሬቶች የሚሸፍኑት አብዛኛውን የሐማሴን አውራጃና የምፅዋን አውራጃ

ምዕራባዊውን ክልል ሲሆን ከቀይ ባሕር ጋር የሚዋሰነው ምሥራቃዊው መጠነኛ መሬት ወደ ቀይ ባሕር አዘቅዝቆ የሚወርድ ገደላማ መሬት ነው።

ከአሥመራ ወደ ምፅዋ የሚወስደው አስፋልት የየብስ ተሽከርካሪዎች መንገድ የተሰራው ከምፅዋ አካባቢ ኰረብቶች ሥር በገደላማው መሬት ጠርዝ ላይ ሆኖ ዶጋሊ እስኪደርስ ድረስ ጠመዝማዛ በመሆኑ ገንጣዮች በአነስተኛ የሰው ቁጥር አድፍጠው አደጋ በመጣል በሰውና በመንገዱ ላይ ፀረ ተሽከርካሪ ፈንጂዎችን ለመቅበር ያመቻቸዋል።

በአንድ መቶ ኪ/ሜትር ርቀት ውስጥ በአሥመራና በምፅዋ ከተማ መሐከል ያለውን የመሬት ከፍታ ልዩነት ስንመለከት የአሥመራ ከተማ ያለበት የመሬት ከፍታ ምፅዋ ሲደርስ የቱን ያህል አዘቅዝቆ ወደ ባህር ወለል እንደ ወረደና የፈጠረውን ከፍ ያለ የአየር ንብረት ልዩነት መረዳት ይቻላል።

በአሥመራና በምፅዋ ከተሞች መካከል፣ ከምፅዋ 20 ኪ/ሜትር እርቀ በሚገኝ መለስተኛ ከፍተኛ መሬት ላይ ባለውና ዶጋሊ በመባል በሚጠራው ሥፍራ ላይ የምፅዋን ከተማ ነዋሪ ሕዝብና አብዮታዊ ሠራዊታችንን የሚመግብ ከከርሰ ምድር የሚወጣ ውሃ ማደያ እናገኛለን።

የምፅዋን ከተማ ከተቀሩት የተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች ጋር ስናስተያየው፣ ስፋቱ ወይንም መጠኑ አነስተኛ ሆኖ ውብና ዘመናዊ ከተማ ነው።

ከተማው በውሃ ሁለት ላይ በመከፈሉ በቀይ ባሕር ጠርዝ ላይ ያለው የከተማው አንዱ ክፍል በውሃ የተከበበ ደሴት ሆኖ ከሌላው ሰሜናዊ የከተማው ክፍል ጋር የሚያገናኘውና ተሽከርካሪዎችን እንደልብ የሚያስተላልፍ የየብስ መተላለፊያ በር ወይንም መንገድ አለ።

ከተማው በጠቅላላ፣ ሕዝቡንና ሠራዊቱን የሚያስተናግድ አንድ ግዙፍ ሆስፒታል፣ የተለያየ ደረጃ ያላቸው የትምህርት አገልግሎት መስጫዎች፣ ሆቴሎች፣ የተለያዩ የምግብ ቤቶች፣ የመሸታና የቡና ቤቶች፣ የሲኒማ አዳራሽ፣ የህዝብ መዝናኛ የባህር ዳርቻና የመዋኛ ገንዳዎች ወዘተና በአጠቃላይ አንድ ከተማ ከሞላ ጎደል ሊኖረው የሚገቡ አገልግሎት ሰጪ ተቋሞች ያሉት ከመሆኑ ሌላ የማምረቻ ተቋሞችንም በተመለከተ፣ የከተማውን ነዋሪ ሕዝብና ሠራዊቱን የሚመግብ የዳቦ መጋገሪያ፣ የበረዶ ማምረቻ፣ የጨው ማምረቻና የሲሚንቶ ማምረቻ ወዘተ ፋብሪካዎች ነበሩት።

የአገሪቱ ዋናና ዘመናዊ ወደብ፣ የባሕር አገልግሎት ወይንም (የማሪታይም) መምሪያ ማዕከል፣ ከምፅዋ እስከ አቆርዳት የተዘረጋው የምድር ባቡር መንገዣ

አገልግሎት ማዕከል፣ የአገሪቱ ሰሜናዊ የባሕር ኃይል ሠፈርና የባሕር ኃይል አካዳሚ የሚገኙት በምዕዋ ከተማ ነው።

ከተማው የተገነባው በቀይ ባሕር ጠርዝ ላይ ወደ ባሕሩ በጣም ተጠግቶ ነው። የቀይ ባሕር ጠረፋችን ወይንም የባሕር ድንበራችን ርዝመት ከሰሜን ጫፍ እስከ ደቡባዊ ዳርቻ፣ ከራስ ካሣር እስከ ራስ ዱሜራ ከ1000 ኖቲካል ማይልስ በላይ ርዝመት ያለው ነው።

በእኛና የቀይ ባሕር ተዋሳኝ በሆኑ ጎረቤት አገሮች መሐከል የየሃገራቱ ይዞታ የሆነውና ከምድር 20 ኖቲካል ማይልስ ርቀት ወይንም ስፋት ያለው የባሕር ወለል የማንም ይዞታ ሳይሆን ዓለም አቀፍ የባሕር ክልል ይባላል።

የኢትዮጵያ ይዞታ በሆነው አንድ ሺህ ኖቲካል ማይልስ ርዝመትና ሃያ ኖቲካል ማይልስ ስፋት መካከል አንድ መቶ የሚሆኑ ደሴቶች አሉ።

ለአያሌ ምዕተ ዓመታት ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር ክልል ይዞታዋ ውስጥ አንድ መቶ ደሴቶች አሏት እየተባለ ሲነገር ይኑር እንጂ እኔ እንደተመለከትኳቸው ሰው የሠፈረባቸውና ሰው ማሥፈር የሚችሉት ደሴቶች ሦስት ብቻ ሲሆኑ የተቀሩት ምናልባት በጊዜ ርዝመት ወይንም ሃደት በውሃ ተውጠው ወይንም ውሃ ለብሰው ሊሆን ይችላል ደሴቶች ሳይሆኑ ከባሕሩ ወለል በላይ ትንሽ ብቅ ብለው የሚታዩና በለሊት ለሚጓዙ መርከቦች አቅጣጫ መምሪያ የሚሆኑ መብራቶችን ለማስቀመጥ ያገለግሉ እንደሆን እንጂ ሌላ ጥቅም የማይሰጡ አያሌ የመሬት ጉብታና ቋጥኝ ድንጋዮች ናቸው።

ቀይ ባሕር ዓሣ የበዛበት ባሕር ከመሆኑ ሌላ በመቶ የሚቆጠሩና የተለያዩ የዓሣ ዓይነቶችም ያለው ባሕር ሲሆን ኢትዮጵያን ጨምሮ የአካባቢው አረባዊ አገሮች ከቴክኖሎጂ ኋላቀርነትና የዓሣ ፍጆታቸው ውሱንነት የተነሳ እንዲሁም አረቦቹ የነዳጅ ዘይት ባለ ሀብት በመሆናቸው ከዓሣ ሥጋ ይልቅ የቀንድና የዳልጋ ከብት ሥጋ ስለሚመርጡ በቀይ ባሕር ያልተነካ የዓሣ ሀብት ክምችት አለ።

ከአንዴም ሁለቴ የቀይ ባሕር ክልላችንን በጎበኘሁበት ጊዜ በኛ የባሕር ክልል ውስጥ አያሌ ዶልፊኖችም እንደ አሉ ለመገንዘብ ችያለሁ።

እነዚህ አካላዊ ተፈጥሮአቸውና ባህሪያቸው በጣም የሚያስደስት ቅንና ሰው አፍቃሪ የሆኑ የባሕር እንስሶች ከምዕዋ ወደ አሰብ በወታደራዊ መርከብ ከጓዶቼ ጋር በምንጓዝበት ጊዜ ሳይለዩን ከመርከባችን ግራና ቀኝ እየዋኙና እያጫወቱን አጅበውን እስከ አሰብ ወደብ ድረስ ተጉዘዋል።

ቀይ ባሕር ሞገደኛ ባሕርነው። ከሞገዱ ኃይለኛነት የተነሳ መርከቦች የሚሄዱት እየተናወጡ ስለሆነና የተሳፋሪውን ሰው የሆድ ዕቃ ስለሚንጡ የተበላና የተጠጣ ነገር በሆድ ውስጥ አይቆይም! ያስመልሳል።

በዚህም ምክንያት ቶሎ ቶሎ ስለሚርብ በቀይ ባሕር ላይ የመርከብ ጉዞ በየቀኑ ከሚያስፈልገው መደበኛ ምግብ በተጨማሪ ሁለቴ ወይንም ሦስቴ መመገብ ሊያስፈልግ ይችላል።

የባሕር ኃይላችንን ሠራዊት ችግር ለመረዳት የቻልኩት በዚህ የባሕር ጉዞ ነበር። ሴቶች እህቶቻችን ነፍሰ ጡር ሆነው በቀይ ባሕር ላይ በመርከብ ቢጓዙ የባህር መንገዱ እንደሚያውካቸው አይጠረጠርም።

በቀይ ባሕር ክልል ይዞታችን ውስጥ ያሉት ሰው የሠፈረባቸው ትልልቅ ደሴቶች ዳህላክና ናኩራ በመባል የሚታወቁት ናቸው።

ናኩራ ለሃምሳ ዓመታት በተካሄደው የፋሽስት ኢጣሊያ የቅኝ አገዛዝ ዘመን የኢትዮጵያ ታጋዮች ታሥረው በግዞት የሚሰቃዩበትና የሚሞቱበት የስቃይ ወህኒ ቤት የተሠራበት ደሴት ነው።

ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት የምፅዋ ከተማ ብቻ ሳይሆን ጠቅላላው የምፅዋ አውራጃ በበጋ ወቅት ለዘጠኝ ወራት ያህል ከሠላሳ አምስት ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ በላይ የሆነ ከፍተኛ ሙቀት ሲኖረው በክረምት ለሦስት ወራት ያህል ከባሕሩ ከሚነሳው ኃይለኛ ንፋስ ጋር ተቀላቅሎ የሚመጣው ከዜሮ መቀነስ በታች የሆነ እጅግ የሚቀዘቅዝ አየር ነው።

ሁለት እጅግ የተለያዩ፣ እጅግ ቀዝቃዛና እጅግ ሞቃት የአየር ንብረት ጨው ማሳ ውስጥ መሽጎ ጠላቱን ለሚከላከለው አብዮታዊ ሠራዊታችን ሌላው የስቃይ ምንጮች ነበሩ።

በኢትዮጵያ የተለያዩ ነፋሻ ክልሎች የተወለዱና ያደጉት የሕዝባዊ ሠራዊታችን አባላት ለቀይ ባሕር ክልል የአየር ንብረት ፍፁም ባዕድ ስለነበሩ ወደ ምፅዋ በመርከብ የሚጓጓዘው ክፍለ ጦር አዛዥ የነበረው ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬ መኩሪያ ከሠራዊቱ ጋር አሰብ ወደብ እንደደረሰ በከባድ የፀሐይ ንዳድ ስለተመታና እዚያው አሰብ ህይወቱ በማለፉ ለክፍለ ጦሩ ሌላ አዛዥ መፈለግ ነበረብን።

የክፍለ ጦሩ አባላት ሕዝባዊ ሠራዊቶች በመርከብ ተጭነው በቀይ ባሕር የአየር ንብረት ከአርባ ሰዓት በላይ ተጉዘው የምፅዋ የፀሐይ ንዳድ ሲቀበላቸው፣ ምፅዋ በደረሱ የመጀመሪያው ቀን ብቻ፣ ከክፍለ ጦሩ አባላት መካከል 504 አምስት መቶ አራት በፀሐይ ንዳድና በውሃ ጥም ሞቱብን ካልኩ በኋላ ወደ ውጊያው ታሪክ አመራለሁ።

ሻዕቢያ በደንጎሎና በዶጋሊ መካከል ያሉትን ኰረብታማ መሬቶች በሁለት ክፍለ ሠራዊት ከሁለት ወገን ማለትም፣ አንደኛው ክፍለ ሠራዊት ከአሥመራ ከተማ ወደ ምፅዋ የሚንቀሳቀሰውን ሁለተኛው ክፍለ ሠራዊት ከምፅዋ ከተማ ወደ አሥመራ የሚንቀሳቀሰውን የመንግሥቱን ጦር ለማቆም በሚያስችለው ሁኔታ በሥልታዊ ይዞት አሰልፎ ጥቅምት 2 ቀን 1970 ዓ.ም የአሥመራ ምፅዋን መንገድ ዘጋ::

ሻዕቢያ ይህንን እርምጃ ከመውሰዱ በፊትም ለዓመታት እነኝህን ሁለት አውራጃዎች ማለትም የሐማሴንና የምፅዋን አውራጃዎች የሚካፈሉትን ሰፊና የአሥመራንና የምፅዋን ከተሞች የሚገዛ ተራራማ መሬት በቋሚነት በጦር ለማስያዝ ባለው የሰው ኃይል እጥረት ምክንያት አዳጋች በመሆኑ፤ ከአስመራ ምፅዋ ወይንም ከምፅዋ አሥመራ የሚደረገውን ግንኙነትና የተሽከርካሪዎች ንቅናቄ ደህንነት ለማስጠበቅ በወገን ጦር በኩል ያለው አንድና ብቸኛ አማራጭ ወይንም ማድረግ የሚቻለው የቅፍለት ወይም የኰንቮይ ዘዴን ነው::

ከሁለቱም ከተሞች የሚንቀሳቀሱት ተሽከርካሪዎች የሠራዊቱ፣ የመንግሥትም ሆኑ የግለሰቦች በየሳምንቱ አንዴ የጉዞ ፕሮግራም በማውጣት በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ መንቀሳቀስ ያለባቸውን ወይንም መንቀሳቀስ የሚፈልጉትን ሁሉ ያሰባሰበ ቅፍለት በጦር በማጀብ ነበር መንገዱን መጠቀም የሚቻለው::

በአንባቢ ዘንድ እንደሚታወቀው የኤርትራን ክፍለ ሃገር ከመሃሉ ኢትዮጵያ የሚያገናኙት የየብስ ተሽከርካሪ መንገዶች በገንጣዮች የተዘጉ ከመሆናቸው ሌላ የባሬንቱ፣ የአዲ ቀይሕና የክፍለ ሃገሩ ርዕስ ከተማ አሥመራ በገንጣዮች ተከበዋል::

በእነኝህ ከተሞች ውስጥ የተከበበው ህዝብ ከክፍለ ሃገሩ ገጠር ወይንም ከገበሬው ጋር የነበረው ሁለንተናዊ ግንኙነት የተቋረጠና በመሐከላቸው የነበረው የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚና የንግድ እንቅስቃሴ ጨርሶ የቆመ በመሆኑ ገንጣዮች በከበቧቸው ከተሞች ውስጥ ነዋሪ የሆነው ሕዝብ በሙሉ ማለት ይቻላል በምግብ አቅርቦት በኩል የመንግሥት ተረጂ ከሆነ ቆይቷል::

ሠራዊቱ የሚያስፈልጉት ትጥቆች፣ አልባሳት፣ የጦር መሣሪያዎች፣ ሥንቆች፣ ነዳጅና ቅባት ወዘተ ለክፍለ ሃገሩ አምራች ድርጅቶች የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎች በሙሉ ከመሀል አገር ወደ ኤርትራ የሚመጡትና በኤርትራ አምራች ድርጅቶች የተመረቱት የኢንዱስትሪ ውጤቶችና ማናቸውም ሸቀጦች የሚወጡት በምፅዋ ወደብ ነው::

ሕዝቡ የሚመገባቸው እህሎች፣ ጥራጥሬዎች፣ ማጣፈጫዎች፣ ቡናና ስኳር ወዘተ በጠቅላላ ከመሐል አገር ወደ ኤርትራ የሚገቡት በምፅዋ ወደብ ነው:: ከወደቡ አገልግሎትና ከባሕር መጓጓዣ ሌላ በተለዋጭነት የሚታይ ወይንም የሚታሰብ ነገር ቢኖር የአየር መጓጓዣ ነው::

በአየር መጓጓዣ ማጓጓዝ የሚቻለው ሰዎችንና አንዳንድ በአጣዳፊ ሁኔታ የሚፈለጉ ቁሳቁሶችን ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንጂ ጠቅላላውን የሕዝቡንና የሠራዊቱን ፍላጎትና ፍጆታ ለረጅም ጊዜ በአየር መጓጓዣ ለማቅረብ የአገሪቱ አቅም አይችልም።

የምፅዋ አሥመራ መንገድ ተዘግቶና የወደቡ አገልግሎት ቆሞ የኤርትራን ክፍለ ሃገር ሕዝብ ለመመገብና ሠራዊቱን ለማዋጋት አለመቻል ማለት የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር የገንጣዮች ዓላማና ፍላጎት ተግባራዊ ወደሚሆንበት ጊዜ እየሄድን መሆናችን ለማንም ግልፅ ነበር። ስለሆነም፣ የኤርትራን ክፍለ ሃገር የአስቸኳይ ጊዜ አስተዳደር የአመራር አካላት የሰሜኑን ሠራዊት ዕዝ የአመራርአካላት ያካተተ የአገር መከላከያ፣ የአገር ደሕንነትና የአገር ፀጥታ ጉዳይ ምክር ቤትን አስቸኳይ ስብሰባ አድርገን የአሥመራ ምፅዋን መንገድ በአስቸኳይ መክፈት በሚቻልበት መፍትሄ ላይ መምከር ነበረብን።

በብሄራዊው የአገር መከላከያ፣ የደሕንነትና የፀጥታ ምክር ቤት ስብሰባ የአሥመራ ምፅዋን መንገድ በአስቸኳይ ለመክፈትና በዚህም አጋጣሚ ህዝቡንና ሠራዊቱን የገጠሙት የምግብና የቁሳቁስ አቅርቦት ችግሮች በአስቸኳይ መፍትሄ በሚያገኙባቸው ሁኔታዎች ላይ ውሳኔ ሰጠ።

የተሰጡት ውሳኔዎች አካል የሆነውን ወታደራዊ ዕያሄ ተግባር በተመለከተ ሁለቱ ገንጣይ ድርጅቶች ሥራና የውጊያ ቀጠና ተከፋፍለው ጀብሐ በኤርትራ ደጋማ ክልሎች መሃከል ያሉትን አዲ ቀይህንና አሥመራን ከቦ የከበባውን ቀለበት ከቀን ወደ ቀን ለማጥበብ በሚጥርበት ጊዜ፣ ሻዕቢያ ያለውን ኃይል በሙሉ አሰባስቦ የአሥመራ ምፅዋን መንገድ በመዝጋትና ብሎም የምፅዋን ወደብ ለመውረር ስለአቀዱ፣ የባሬንቱን፣ የአዲቀይህንና የአሥመራን ከተሞች ዙሪያ ከሚከላከሉት የወገን የጦር ክፍሎች መካከል ቢያንስ ከፊሉን ከመከላከያ ምሽግ በማውጣት አሰባስቦና የምፅዋን ከተማና ወደቡን በመከላከል ላይ ያለው ጦር የኋላ ጥበቃ ከሚያደርጉት የአባት ጦር ሻለቆች በስተቀር በሙሉ ከምሽጉ ወጥቶ-

1ኛ ከምፅዋ ተነስቶ በምፅዋ አሥመራ መንገድ ላይ ያለውን የሻዕቢያ ጦር እየወጋ ወደ አሥመራ የሚሄድ አጥቂ ግብረ ኃይል፤

2ኛ ከአሥመራ ተነስቶ በአሥመራ ምፅዋ መንገድ ላይ ያለውን ጠላት እየወጋ ወደ ምፅዋ የሚሄድ ሁለት አጥቂ ግብረ ኃይሎች ተቋቁመው መንገዱን እንዲከፍቱ፤

3ኛ በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ ከሶቪየት ህብረት የምንጠብቃቸው መሣሪያዎች ባለመድረሳቸው በሰሜን ከሚዋጋው መደበኛ ጦራችን ብዛት ያለው ሕዝባዊ ሠራዊታችን የታጠቀው ቀላል መሣሪያዎችን ብቻ በመሆኑ በከባድ መሣሪያዎች ዓይነትም ሆነ መጠን ከገንጣዮች በማይሻል ሁኔታ ላይ ስለነበረን የታቀደውን ውጊያ ተግባራዊ ለማድረግ የዲሞክራቲክ የመንን አመራር ጓዶች ጠይቀን ያገኘናቸውን አንድ

የ122 ሚ/ሜትር ተጎታች መድፍ፣ አንድ የ122 ሚ/ሜትር ቢ.ኤም ሮኬት ወንጫፊ መድፍና አንድ የሶቭየት ህብረት ሥራት የሆነ ቲ.55 የታንክ ሻለቃ የተኩስ ድጋፍ ለአጥቂ ግብረ ኃይሎቹ ይሰጡ ዘንድ እንደ አስፈላጊነታቸው እንዲደለደሉና ውጊያው በአስቸኳይ እንዲቀጥል የብሄራዊና አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ ለሰሜኑ ሠራዊት እዝ ትዕዛዝና መመሪያዎችን ሰጠ።

የሰሜን ዕዝ በተሰጠው ትዕዛዝና መመሪያ መሠረት የራሱን ዝርዝር የሥራ ድርሻ ሠርቶና ሁለቱን አጥቂ ግብረ ኃይሎች አደራጅቶ ከሁለት አቅጣጫ ማለትም፣ ደንጎሎና ዶጋሌን የመነሻ መሥመር በማድረግ መንገድ የዘጉትን ገንጣዮች የማጥቃቱ ውጊያ ተጀመረ።

በኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ አንድና በዚህም በቅፅ ሁለት ላይ በብዙ አጋጣሚዎች ደጋግሜ በኤርትራ ምድር ለኢትዮጵያ አንድነት ከገንጣዮች ጋር በተደረገው የትጥቅ ትግል የወጋን ሰው ሳይሆን መሬቱ ነው እንደማለቴ ሁሉ በዚህ የአሥመራ ምፅዋን መንገድ ለመክፈት በተደረገው ትግል ሁለቱን አጥቂ ግብረ ኃይሎቻችንን የወጋቸው ሻዕቢያ ሳይሆን መሬት ነው።

በአሥመራና በምፅዋ ከተሞች መሃከል አንድ መቶ ኪ/ሜትር ርዝመት ያለውን ከፍ ያለ የአየር ንብረት ልዩነት፣ ሁለቱንም ከተሞች ገዥ የሆኑትን የተራራ ሠንሰለቶችና የመንገዱን ጠመዝማዛነት በጥቂቱም ቢሆን ለአንባቢ አስረድቻለሁ።

ወደ ውጊያው ታሪክ ከማምራቴ በፊት ለአንባቢ ማስረዳት ወይንም ማስታወስ ያለብኝ፣ በታጠቅ የጦር ሠፈር የሦስት ወር ወታደራዊ ሥልጠናውን አጠናቆ ወደ ኤርትራ የተላከው ምንም ዓይነት የውጊያ ልምድ የሌለው ሕዝባዊ ሠራዊታችን ለፍልሚያ የተሠለፈው ከአሥራ አምስት ዓመታት በላይ የውጊያ ልምድ ካለውና የአገሩ የኤርትራ ተወላጅ በመሆኑ የሚዋጋባቸውን የመሬቶች ዓይነት፣ የመሬቶች ብልትና ወታደራዊ ጠቀሜታቸውን በሚገባ ከሚያውቅ በተወለደበትና በአደገበት የአየር ንብረት ክልል ውስጥ ከሚዋጋ ጎሪላ ጋር መሆኑን ነው።

ሕዝባዊ ሠራዊታችን ይህንን ውጊያ የመዋጋት እጣ የገጠመው የኤርትራን ምድር ገና ከመርገጡ በመሆኑ ለኤርትራ የአየር ንብረት በጠቅላላ፣ ለምፅዋ አካባቢ በተለይ ፍፁም ባዕድና እንግዳ በነበረበት ወቅት ነው።

ሻዕቢያ በአሥመራና በምፅዋ ከተሞች መሃከል ያሉትን ሰው አልባ ተራሮች የተቆጣጠረው ያለ ውጊያ ከመሆኑ ባሻገር በተራሮች ላይ ራሱን ለውጊያ ለማዘጋጀት በቂ ወይንም ረጂም ጊዜ አግኝቶ ስለነበረ ከወገን ግብረ ኃይሎች ተኩስ ብቻ ሳይሆን ከወገን አየር ኃይል ድብደባ የሚመክቱት ተለዋዋጭ ምሽጎችን በቅደም ተከተል ወደ ኋላ በጥልቀት ለመገንባት ከመቻሉ በላይ በሁለቱ ማለትም በደንጎሎ ግንባርና በዶጋሌ ግንባር መሃከል አማካኝ ሥፍራ ላይ መጠነ ሰፊ ደጀን ጦር ወይንም ተተኪ

ሁሉቱንም ግንባሮች ለመርዳት፣ ለማጠናከርና ሲያስፈልግም ለመልሶ ማጥቃት አዘጋጅቶ ወይንም አካብቶ ነበር።

ሁሉቱም ግብረ ኃይል ጦሮች፣ የአሥመራ ምፅዋ መንገድ መዘጋትና የምፅዋ ወደብ አገልግሎት መቆም ለኢትዮጵያ ህዝብ ምን ማለት እንደሆነ በሚገባ የተገነዘቡ፣ ከመደብና ከፖለቲካ ንቃት ጋር ከፍ ያለ የሃገር ፍቅር ስሜት ያላቸው ስለነበሩ በእልህና በአብዮታዊ ወኔ «የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት ወደፊት» በማለት እየጣሉና እየወደቁ ጠላት ምሽግ ውስጥ በመግባት እየተናነቁ አንዱን ምሽግ ሲጥሱ ሌላ ምሽግ እየገጠማቸው ተራራ እየቧጠጡ በመውጣት ሌላውን ምሽግ በታላቅ መሰዋዕትነት ሲጥሱ ውለው ፋታ የሚያገኙት ጨለማው የወገንንም የጠላትንም ዓይን ሲጋርድ ብቻ ነው።

በዚህ ዓይነት ተጋድሎ ለቀናቶች በተደረገው ፍልሚያ ከሁሉቱም ግብረ ኃይሎች በቁጥር የሚበልጠው ሰው በመሰዋትና በመቁሰል ከውጊያ ውጭ ከመሆኑ በላይ ጠላት የወገን ጦር የተራራ አቀበቶችን እየቧጠጠ በመውጣት መድከሙን በመመልከት ሁሉቱንም ግብረ ኃይሎች በተጠባባቂ ኃይሉ በፈረቃ መልሶ በማጥቃት የተያዙበትንም ሽንቅ እያስለቀቀ የወገንን ጦር ውጊያው ሲጀመር ወደነበረበት ሥፍራ መለሰው።

የሰሜን ዕዝ ከአሥመራ ከተማ ዙሪያ መከላከልና ከሌሎችም ሥፍራዎች አንስቶ ተጨማሪ ጦር በማቅረብ በተለይ የአሥመራን ግብረ ኃይል በማጠናከር በተደጋጋሚ ከፍ ያለ የማጥቃት ጥረት ቢያደርግም ቀደም ብዬ ለአንባቢ እንደ ገለፅኩት አብዮታዊ ሠራዊታችን የሚዋጋው ከሰው ጋር ሳይሆን ከመሬት ጋር ስለሆነ በሁሉቱም ግብረ ኃይሎች ከፍ ያለ መስዋዕት የተከፈለበት ፍልሚያ ሳይሳካ ቀረ።

ምዕራፍ ሠላሣ ዘጠኝ

የምፅዋ ከተማ ነዋሪ የሆነውን ሕዝብና ሠራዊታችንን የሚመግበው የዶጋሌ የከርሰ ምድር ውሃ ማደያ መያዝና የምፅዋ ወደብ መከበብ።

ጠላት ከምፅዋ ግብረ ኃይል ይልቅ በአሥመራው ግብረ ኃይል የተወሰደበትን የተደጋገመ ብርቱ የማጥቃት እርምጃ መግታትና ብሎም ፍፁም ማስቆም መቻሉን ከተገነዘበ በኋላ ከአሥመራ ግንባር ከፊሉን ኃይል ቀንሶ በመውሰድ በሁለቱ ግብረ ኃይሎች መካከል በተጠባባቂነት ከአስቀመጠው ጦር ጋር አቃምሮ ወደ ምፅዋ ግንባር በማዞር ታህሳሥ 10 ቀን 1970 ዓ.ም በወገን የምፅዋ ግብረ ኃይል ላይ በሠነዘረውና ተከታታይነት በነበረው ያላቋረጠ ጥቃት የወገንን የመከላከያ ምሽግ ብቻ ሳይሆን የዶጋሌን የከርሰ ምድር ውሃ ማደያ አስለቅቆ መያዝ ቻለ።

ጠላት ለምፅዋ ሕዝብ ህይወት የሆነውን የዶጋሌን የከርሰ ምድር ውሃ መቆጣጠር ብቻ አላረካውም። የውጊያ ስልትና ሥነ ሥርዓት በጎደለው ሁኔታ በመዝረክረክ ወደ ምፅዋ ከተማ በማፈግፈግ ላይ የነበረውን የወገን ግብረ ኃይል ጦር እግር በእግር እየተከታተለ በማጥቃት ዳጋ በመባል የሚጠራውንና ከወደቡ በስተሰሜን ያለውን የከተማውን ከፊል አካል ከውሃው ወይንም ከደሴቱ በመለስ ለመቆጣጠር ቻለ።

በአሥመራ ግብረ ኃይል በኩል ሲካሄድ የነበረው የማጥቃት ውጊያ ሳይሳካ ቀርቶ መቆሙን ከሰማንበት ጊዜ ጀምሮ የምፅዋ ግብረ ኃይል ሁኔታ በእጅጉ ስለአሳሰበን የኔ የቅርብ ረዳትና በብሄራዊ አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ የዘመቻ መኰንን የነበረው ሌ/ኰሎኔል ገብረክርስቶስ ቡሊ በሆትላይን ልዩ ስልክ የምፅዋን ግንባር ውጊያ በየደቂቃው ይከታተል ነበር።

የወገን ግብረኃይል በጠላት ጥቃት እየተገፋ በዶጋሌ የከርሰ ምድር ውሃ ማደያ አካባቢ ውጊያው መካሄድ ከጀመረ በኋላ ከምፅዋ ግብረ ኃይል አዛዥ ጋር የነበረን ግንኙነት ተቋረጠ።

ለጥቂት ሰዓቶች የግብረ ኃይሉን አዛዥ ብቻ ሳይሆን ከኋላ በምፅዋ ከተማ ውስጥ ባለው የምፅዋ ግንባር ዕዝ ማዕከል ውስጥ ከሚሰሩ ከማናቸውም መኰንኖች ጋር ለመገናኘት ያደረግነው ጥረት ሳይሳካ ቀረ።

የባሕር ኃይል ሠራዊት አዛዥ የነበረውን ከኰሞዶር ተስፋዬ ብርሃኑን በስልክ ፈልጌ በመገናኘት ስለውጊያው ሁኔታ የሚያውቀው ነገር እንዳለ ያስረዳኝ ዘንድ ጠይቀው የሰጠኝ መልስ፤

"እኔ አሁን የምገኘው በባሕር ላይ በማዘዣ መርከቤ ውስጥ በመሆኑ ስለውጊያው ዝርዝር ነገር ላስረዳዎ ባልችልም የዶጋሊ የከርሰ ምድር ውሃ ማደያ በጠላት ከተያዘ

በኋላ ተዋጊው ጦር በሙሉ ዳጋ የሚባለውን የከተማውን ክፊል ለሜናዊ ክልል ለቆ ወደ ደሴቱ እንደመጣና ክፊሉም ወደ እኛ የጦር ሠፈር እንደገባ ለማወቅ ችያለሁ" አለኝ።

ኮሞዶር ተስፋዬ ብርሃኑ ስለሚያውቀው ከዚህ በላይ ገለፃ ስለማልጠብቅ ለሰሜን ዕዝ አዛዥ ለኮሎኔል መርዕድ ንጉሴ ደውየ ስለምፅዋ ሁኔታ እንዲያስረዱኝ ሳልጠይቅ "በብሄራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያና በምፅዋ ግብረ ኃይል ዕዝ መካከል ያለው ግንኙነት ከተቋረጠ ሰዓታቶች ተቆጥረዋል። በእኔ መረጃ የምፅዋ ከተማ ክፊሉ በገንጣዮች የተያዘ ከመሆኑ ሌላ የምፅዋ ግንባር ዕዝና ቁጥጥር በጠቅላላ የፈረሰ ስለሚመስለኝ በእርስዎ ዕዝ ውስጥ ካሉት ረዳቶችዎ ክፊሉንና የፖለቲካ ካድሬዎችን ይዘው በመሄድ አመራሩን እንዲወስዱና ስለ ሁኔታው በአስቸኳይ እንዲያስታውቁኝ ይሁን" በማለት ትዕዛዝ ሰጠኋቸው።

አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ምፅዋ ሄደው በባሕር ኃይል ጠቅላይ ሠፈር ውስጥ የማዘገር ጣቢያቸውን አቋቁመው የጦሩን ጠቅላላ ሁኔታ ከቃኙና ሁሉንም ነገር ከተመለከቱ በኋላ ደወሉልኝ።

የሆትላይኑን መስመር ስልክ ሌ/ኮሎኔል ገብረክርስቶስ ሰጥቶኝ ሳገኛቸው «ጓድ ሊቀመንበር መርዕድ ነኝ። ምፅዋ ደርሻለሁ። የምገኘው በባሕር ኃይል የጦር ሠፈር ውስጥ ነው። ሁኔታው በጠቅላላ የተበላሸ ነው። እንደተነገረዎት የምፅዋ ግብረ ኃይል ግንባር ቀደም ጦር ክፊሉ ደሴቱ ውስጥ የገባ ሲሆን እዚህ እኔ ያለሁበት የባሕር ኃይሉ ሠፈር ድረስም የመጡ አያለሁ።

የተቀረው በግንባር ያለው ጦር በተለይም ሚሊሻው ክፊሉ እጁን ለጠላት እየሰጠ ሲሆን ክፊሉ የውሃ ጥሙንና የፀሐዩን ንዳድ መቋቋም ስለተሳነው መሣሪያውን እየጣለ በየሥፍራው በብዛት ወድቆ ይታያል። ከወደቁት ውስጥ ክፊሉ ህይወታቸውን ያጡ መሆናቸውን ተመልክቻለሁ።

የምነግርዎት በደሴቱ ውስጥ መግባት ስለቻሉ ያየኋቸውን ነው። ከደሴቱ ውጭ ጠቅላላ ግብረ ኃይሉ ከዶጋሊ ማፈግፈግ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በየመንገዱና ዳጋ የሚባለው ከተማ እስኪደርስና ከደረሰም በኋላ በየቦታው የወደቁ ወገኖቻችን በጣም ብዙ ናቸው ነው የሚባለው።

በአጠቃላይ ውጊያው ላይ በጠላት ጥይት እየተመቱ ከወደቁት የሠራዊታችን አባላት በድካም፣ በፀሐይ ንዳድና በውሃ ጥም ምክንያት የተሰውት ቁጥር ይልቃል። የወጋን ሰው ሳይሆን ተፈጥሮ ነው። ደሴቱ ውስጥ ያለው ቁስለኛ ብቻ በጣም ብዙ ነው። ከውሃ ጥሙና ከፀሐይ ንዳድ በተጨማሪ ደማቸው የፈሰሰው ቁስለኞች የመዳን ተስፋ የላቸውም» አሉኝ።

ኰሎኔል መርዕድ የነገሩኝ ነገር እጅግ የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን ለጆሮም የሚቀፍና የሚዘገንን ነው። ሆኖም ምንም ይሁን ምን ታሪክ የጣለብን ግዴታ ስለሆነ መከፈል ያለበት መስዋዕትነት ተከፍሎ ምፅዋን ማዳን እንዳለብን እኔ ለእርስዎ ልነግርዎት የሚገባ ነገር አይደለም።

አሁን ምን እያደረጋችሁ ነው ምንስ ማድረግ ይቻላል? ብዩ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ የሰጡኝ መልስ «እኛ እዚህ የሚቻለውን ሁሉ እናደርጋለን በእርስዎ በኩል እንዲታዘዝልን አጥብቄ የምጠይቀው 1ኛ ከየትም ተፈልጎና ከምሥራቅ ግንባርም ቢሆን ተቀንሶ ደህና ተዋጊ ጦር በአጣዳፊ እንዲላክልን፣ 2ኛ ታላቁ ችግር ውሃ ነው። ውሃ የሠራዊቱ ህይወት ነው ሠራዊቱ ከማለቁ በፊት በአጣዳፊ ውሃ ከአሰብ በመርከብ እንዲላክልን፣ 3ኛ ምግብ ነው፤ ለሚሊሺያው የተላከው የአገር ባህል ሥንቅ በሙሉ በሙቀት ስለተበላሸና መደበኛውም ጦር ቢሆን ያለውሃ፣ ያለ ማገዶና ያለኤሌትሪ ክኃይል አብስሎ ሊመገብ ስለማይችል ነፍስ አድን የሚሆነው ምግብ ዳቦ ስለሆነ ለአጭር ጊዜ ለመላው ሠራዊት ዳቦ በሄሊኮፕተር በአጣዳፊ እንዲላክልን አሳስባለሁ።

ለጊዜው የማቀርበው ጥያቄ እነኝህን ሲሆን የተቀሩትንና ምናልባትም አሁን ያልታዩኝን ችግሮች በሚቀጥለው ጊዜ አመለክታለሁ» አሉ። "የጠየቋቸው ነገሮች ሁሉ በሚቀጥሉት ሰዓቶች ውስጥ ይደርስዎታል" ብያቸው ለጊዜው ተለያየን።

በገባሁት ቃል መሠረት ምግብና ውሃ በዚያው ዕለት ረዳት ጦር በበነጋታው የደረሳቸው ከመሆኑ ሌላ እሳቸው ያልጠየቁትን ከአዲስ አበባ ሆስፒታሎች የተውጣጣና በፕሮፌሰር አሥራት የሚመራ በአብዛኛው የቀዶ ጥገና ሕክምና ባለሞያ ሐኪሞች ቡድን በዚያው ቀን ተላከላቸው።

በፕሮፌሰር አሥራት አስተባባሪነት የተመራው የሐኪሞች ቡድን ሻዕቢያ የሚወረውረው የአዳፍኔ ጥይት በምፅዋ ሆስፒታል እየወረደባቸው ያለ እረፍት ሌት ተቀን በመሥራት የመዳን ተስፋ ያልነበረውን በሺህ የሚቆጠር ቁስለኛ ህይወት አዳኑ።

ፕሮፌሰር አሥራት ያለ ዕረፍት በመሥራታቸው የተነሳ የልብ ህመም ታመው አደገኛ ሁኔታ ላይ በመድረሳቸው ለሕክምና በአጣዳፊ ወደ እንግሊዝ አገር ልከን ነው ያዳናቸው።

ከዚህ ሌላ ለአንባቢ መግለፅ ያለብኝ ነገር ወዳጆቻችን የደቡብ የመን አመራር ጓዶቻችን ስለ ምፅዋ ሁኔታ አሳውቂያቸው ስለነበረ ከማንም ቀድመው በዚያው ቀን በስድስት ሰዓት ውስጥ ከኤደን በመርከብ የሚጠጣ ንፁህ ውሃ በመላክ የሠራዊታችንን ብቻ ሳይሆን የምፅዋን ከተማ ነዋሪ ሕዝብ ህይወት ከሞት

አተረፉልን። ይህም እርዳታቸው ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊታችን ምፅዋን መልሶ እስከተቆጣጠረበት ጊዜ ድረስ ከአንድ ዓመት በላይ የቀጠለ መሆኑን ነው።

ታሕሣሥ 10 ቀን 1970 ዓ.ም የምፅዋ ግብረ ኃይል ጦር የጠላትን ተከታታይ ብርቱ ጥቃት መመከት ተስኖት ከዶጋሊ በማፈግፈግ የምፅዋን ከተማ ከፊል አካል ዳጋን አልፎ ከተማውን ሁለት ላይ የሚከፍለውን ውሃና የጨው ማሳ አልፎ ወደ የባሕር ኃይል የጦር ሠፈር ገባ።

የሻዕቢያም ጦር እንደ ወገን ጦር በመድከሙ ወይንም በወደቡ አካባቢ ባለ የመንግሥቱ ጦር ጠንካራ ተቃውሞ ሊደርስብኝ ወይንም መልሶ ማጥቃት ሊሠነዘርብኝ ስለሚችል በቅድሚያ የመከላከያ ሥፍራ መያዝና ራሴን ማጠናከር አለብኝ ብሎ በማሰብ ይሁን ወይም ለኛ ግልፅ ባልሆነ ምክንያት የከተማውን ከፊል ሰሜናዊ ክልል ከተቆጣጠረ በኋላ የባቡር ሐዲድ እያፈረሰ የብረት ምሽግ ግንባታ በመጀመሩ የወገንም ጦር ለሊቱን በደሴቱ ውስጥ ባለው የጨው ማሳ ላይ የመከላከያ ምሽጉን ለመሥራት ቻለ።

ከዚህ በኋላ ጦሩ ጠንክሮ እስከ መጨረሻው የጠላትን ጥቃት ከመመከት ሌላ ማፈግፈግ ቢሞክር፣ ኤርትራን ለገንጣዮች በማስረከብ ባሕር ውስጥ በመግባት የዓሣዎች ምግብ እንደሚሆን መሪዎቹ ጦሩን በማስጠንቀቅ አረጋግተው ምሽጉን እንዲያጠናክር አደረጉት።

ከታሕሣሥ 10 ቀን 1970 ዓ.ም ጀምሮ አስራ አንድን አስራ ሁለትንና አስራ ሦስትን ማለትም ለሦስት ቀናት በወገን ጦር በኩል የነበረው ታላቅ ትኩረት በጨው ማሳ ከሻዕቢያ ከባድ መሣሪያና እንዲሁም ከእግረኛ ጦር ጥቃት መከላከል የሚያስችል ጠንካራ ምሽግ መገንባትና የጦሩን የተዋጊነት መንፈስ ማነሳሳት ነበር።

በዚህ ጊዜ ውስጥ ጦሩ በጠቅላላ ሕዝባዊ ሠራዊቱ በተለይ ከውጊያው ጋር ብቻ ሳይሆን ከምፅዋ የአየር ንብረትና ከሌላውም ችግር ጋር እየተለማመደ ሄደ።

እዚህ ላይ ለአንባቢ መግለፅ ያለብኝ ሌላው ነገር በምፅዋ ወደብ የሚገኘው ጠቅላላው የባሕር ኃይል ሠራዊታችን ለተዋጊው ግብረ ኃይል ጦር ምግብና ውሃ ከማቅረብ፣ የሕክምና እርዳታ ከመስጠት እንደ እግረኛ ጦር ለመዋጋት ከመሰለፍ ባሻገር ከባሕር መርከቦች ላይ በተጠመዱ ከባድ መሣሪያዎች የተኩስ ድጋፍ ይሰጥና የሻዕቢያን ምሽግ ይደበድብ የነበረ መሆኑን ነው።

ሻዕቢያ እንደተጠበቀው ያለውን ጦር በሙሉ ከየቦታው በማሰባሰብ ከፍ ያለ ኃይል ከአካበተ በኋላ የምፅዋን ከተማና ወደቡን ለመቆጣጠር ለታሕሳሥ 14 ቀን 1970 ዓ.ም አጥቢያ ለሊት ከምሽቱ ዘጠኝ ሰዓት ጀምሮ' የወገንን የመከላከያ ወረዳ ለሁለት

ሰዓት በከባድ መሣሪያ ተኩስ ከደበደበ በኋላ ጎህ ሲቀድ በአሥራ አንድ ሰዓት ጥልቀትና ስፋት ያለው ከባድ ጥቃት ሠነዘረ።

ፍልሚያው ለሌላ ሁለት ሰዓት ፀሐይ ሙቀቷን እስክትጀምር ድረስ ቆይቶ የወገን ጦር ጀግንነት በተሞላው ብርቱ የመከላከል ውጊያ በመዋጋት ጠላትን በመረፍረፍ ብዙ አስከፍሎ መለሰው።

ጠላት አጥቂ ጦሩን ያሰለፈው በሦስት ረድፍ ጥልቀት ስለነበረ የመጀመሪያው ረድፍ በወገን ጦር ተኩስ ሲረፈረፍ ሁለተኛውን በመተካት ሁለተኛው ሲረግፍ ሦስተኛውን በመተካት በእልህ በመዋጋት በወገን ጦር ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ቢያደርስም አጥቂው የጠላት ጦር በላቀ ሁኔታ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰበት ስለተመለሰ ማጥቃቱን ሊቀጥል አልቻለም በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ ሻዕቢያና ጀብሐ በህብረት ብቻ ሳይሆን በአንድ ዕዝ ማዕከል የሚመሩ ይመስላል። ሻዕቢያ በምፅዋ ከተማ ላይ የመጀመሪያውን ከባድ ጥቃት በወገን ጦር ላይ በሠነዘረበት ጊዜ ጀብሐም በደጋው ክልል ውስጥ ባሉ የውጊያ ቀጠናዎች ማለትም በአሥመራ፣ በአዲቀይሕና እንዲሁም በባሬንቱ ተመሣሣይ ጥቃት ቢሠነዝሩም ውጤታቸው ከምፅዋው ጋር ተመሣሣይ ነበር። የወገን ጦር አልተበገረም።

በምፅዋ ግንባር ሻዕቢያ በሠነዘረው ከባድና ተከታታይ ጥቃት በሦስት ረድፍ ያሠለፈውን ጦር አብዛኛውን ማስቀረት በመቻላቸው የወገን የጦር ክፍሎች ሞራልና የውጊያ ስሜት በጣም ሊሻሻል ቻለ።

ከጠላት የመጀመሪያው ከባድ የማጥቃት ውጊያ ሙከራ በኋላ የተኩስ መለዋወጥ ቆሞ አንፃራዊ እረፍት ወይንም የሠላም ጊዜ በተገኘ ቁጥር የወገን ጦር መሪዎችና የፖለቲካ ካድሬዎች ምሽግ ማጠናከር ብቻ ሳይሆን የጦሩን ሞራልና የመዋጋት ብቃት በበለጠ መገንባት አስቻላቸው።

ይህም ሆኖ ሻዕቢያ ተስፋ ባለመቁረጥ ያለውን ኃይል እስኪያሟጥጥ ድረስ ማለት ይቻላል በታሕሣሥ 19ና በ28 1970 ዓ.ም ሌሎች ሁለት ማጥቃቶችን ከሞከረና አብዮታዊ ጦራችን ክፉኛ መትቶ ከመለሰው በኋላ በእግረኛ ጦር የሚደረግ የጨበጣ ውጊያ ለአንዴና ለመጨረሻ በማቆም በከባድ መሣሪያ ብቻ የመደብደብ ተግባሩን ከአንድ ዓመት በላይ ቋሚ ሥራው አደረገው።

በኤርትራ የኢትዮጵያ ህዝብ ከፋሽስት ኢጣሊያና በኋላም ከኢምፔሪያሊስት ብሪታኒያ ጦር ጋር ለአንድነቱና ለነፃነቱ ያደርግ በነበረው ትግል የምፅዋ አውራጃ ህዝብ ለአንድነት የቆመና ፀረ-አንድነቶችን የታገለ በመሆኑ ገንጣዮች ጥላቻ ስለነበራቸው በዚህ አጋጣሚ ለመበቀል ይመስላል አዘውትረው በአዳፍኔ ተኩስ የሚደበድቡት ከተማውንና ሠላማዊውን ህዝብ ስለነበረ ከተማውን በሙሉ አፍርሰውታል ህዝቡንም ፈጅተውታል።

በ1970 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ከሶቪየት ህብረት መንግሥት የገዛናቸው መሣሪያዎች ስለቀረቡልን የሻዕቢያን ምሽግና ከባድ መሣሪያዎቹን በአፀፋው በመደብደብ በሠላማዊው ሕዝብ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ለማቃለልና ብሎም ለማቆም ተችሏል።

2ኛው አብዮታዊ ነፃ አውጭ ሠራዊታችን ወደ ሰሜን ዘምቶ የኤርትራን ህዝብ ከገንጣዮች ነፃ እስከሚያወጣ ድረስ ከተቀረው የኤርትራ ክልል ህዝብ በእጅጉ የተሰቃየው የምፅዋ ከተማ ነዋሪ ህዝብ ነው።

ጠቅላላው የምፅዋ ከተማ ነዋሪ ህዝብ በዚያ እጅግ ሞቃትማ አገር ለምግብ ማብሰያና ለመጠጥ ብቻ በሚሆን የውሃ ራሽን ከመኖር ሌላ በምግብ አቅርቦትና በጤና አገልግሎት ወዘተ ልክ እንደ ሠራዊቱ የመንግሥት ተረጂ ነበር።

የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነት ከገንጣዮች የትጥቅ ሴራ የኢትዮጵያን ህዝብ የአገር ድንበር ማህበራዊ ደህንነትና አብዮት ከባዕዳን ወረራ ለማዳን ፍልሚያ ያቀድነው የውጊያ ስትራቴጂያችን በሰሜን መከላከል በምሥራቅ ማጥቃት ብለን ከተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጋር ስንዋጋ የአገራችንን ሰሜናዊ ክልል በተለይም የኤርትራን ክፍለ ሃገር ምድር በሙሉ ማለት ይቻላል ገንጣዮች ወረው በሰሜኑ አብዮታዊ ሠራዊታችን የተከበቡትን የባሬንቱን፣ የአዲቀይህንና የአሥመራን ከተሞች ሲከላከል የምፅዋን ከተማ ከሻዕቢያ ጋር ተካፍሎ ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ቆየን።

የተስፋፊውን የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ወረራ ለሰባት ወራት ያህል ተከላክለን በመልሶ ማጥቃት ከኢትዮጵያ ምድር ያስወጣነው በ1970 ዓ.ም በሕዳር ወር መገባደጃ ላይ ነው።

አንደኛው አብዮታዊ የኢትዮጵያ ሠራዊት ያገኘውን አንፀባራቂ ድል በማስፋፋት ወደ ሱማሌ ግዛት ጠልቆ በመግባት የሱማሌን መንግሥትና ወራሪ ሠራዊቱን ይበቀላል የሚል ጥርጣሬና ሥጋት ያደረባቸው የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት፣ የምዕራቡ ዓለምና አረቦች ብቻ ሳይሆኑ ወዳጃችን የሶቪየት ሕብረት መንግሥትም ነበር።

የሶቪቶች ጥርጣሬና ሥጋት ምክንያት አልባ አልነበረም። በመሐከላችን ያሉ እንደመሆናቸው መጠን የኢትዮጵያን ህዝብ የመበቀል ፍላጎት የተገነዘቡ ከመሆናቸው ሌላ አንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት አባላት ለመልሶ ማጥቃቱ በሚዘጋጁበት ጊዜ «የኢትዮጵያ አንበሳ ወደ ሐርጌሳ» የሚልና ሌላም ተመሳሳይ መፈክሮችን ሲሉ የሚሰሙ በመሆናቸው ነበር።

የኢትዮጵያ ህዝብና የአብዮታዊ ሠራዊታችን ፍላጎት ይህንን ይመስል እንጂ የአብዮታዊው መንግሥት አመራር አካላት ፍላጎትና በሱማሌዎች ላይ ከተገኘው ድል ማግሥት ቀጣዩ አስቸኳይ እቅድ፣ ዓለም አቀፉን የቀይ መስቀል ተቋም በመቀስቀስ በእኛና በሱማሌ መንግሥት መሀከል የምርኮኞች ልውውጥ እንዲጀመር በማድረግ በሱማሌዎች አገር በጨለማ ወህኒ ቤት የሚሰቃዩትና በባርነት ግዞት ላይ ያሉትን ወገኖቻችን በአስቸኳይ ወደ አገራቸው መመለስና በኤርትራ በጀብሐና በሻዕቢያ ጦር ተፅዕኖ ሥር ያሉትንና የተከበቡትን ወገኖቻችንን በአስቸኳይ ነፃ ማውጣት ነበር።

ድል አድራጊውና ኃያሉ አብዮታዊ ሠራዊታችን ፊቱን ወደ ሰሜን ያዞራል በምስራቅ የተገኘው ድል በሰሜንም ይደገማል።

ክፍል ሃያ አንድ

ምዕራፍ አርባ

የሁለተኛው ነፃ አውጪ አብዮታዊ ሠራዊታችን መቋቋም።

በኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ አንድ ላይ በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደገለፅኩት የሶማሌን መንግሥት ወራሪ ሠራዊት በመልሶ ማጥቃት ውጊያ ከአገራችን ምድር ረግጠን ለማስወጣት ቀደም ብለን ካደረግነው የተጣደፈ ህዝባዊ ሠራዊት መሰናዶ የተሻለ ሥልጠና ብቻ ሳይሆን እጅግ የተሻለ የጦር መሣሪያ የታጠቁ በርካታ እግረኛ ክፍለ ጦሮችን፣ ሜካናይዝድ፣ ታንከኛና መድፈኛ ወዘተ ብርጌዶችን ያደራጀነው ለምሥራቁና ለደቡቡ የጦር ግንባር ብቻ ሳይሆን በኤርትራ ክፍለ ሃገር በገንጣዮች ተፅእኖ ሥር የወደቀውንና የተከበበውን ህዝብ ነፃ ለማውጣት ለሚደረገው የማጥቃት ውጊያ ጭምር ነበር።

በኤርትራ ለሚደረገው ገንጣዮችን የማጥቃት ውጊያ የተደረገው መሰናዶ የተሻለ ጥራትና የውጊያ ብቃት ያለው ሠራዊት ማዘጋጀት ብቻ አልነበረም።

በጊዜ እጥረትና በልምድ ማጣት ምክንያት ከሱማሌዎች ጋር በምሥራቅና በደቡብ ግንባሮች በተደረጉት ውጊያዎች ያልተደረጉ ከዚህ የሚከተሉትን ልዩ ልዩ መሰናዶዎች ማድረግ ተችሏል።

1ኛ ለሠራዊቱ የሚሰጠውን የህክምና አገልግሎት የመድሃኒትና የህክምና መሣሪያዎች አቅርቦትን ለማሻሻል ተችሏል።

2ኛ በምሥራቅና በደቡብ የጦር ግንባር ከተደረገው በተሻለ ኢትዮጵያዊ ሀኪሞችን የሚያጠናክሩ አያሌ የወዳጅ ሶሻሊስት አገሮች ሀኪሞችን እርዳታ ማግኘት ተችሏል።

3ኛ የመላውን ተዋጊ አብዮታዊ ሠራዊታችንን የጦር ሜዳ ቀለብ በአጠቃላይ በዓይነትም ሆነ በመጠን ለማሻሻል ከተደረገው ጥረት በተጨማሪ በሕዝባዊ ሠራዊቱና በመደበኛ ሠራዊቱ መካከል የነበረውን የቀለብና የደመወዝ አቅርቦት ተመሳሳይ በማድረግ የነበረውን ልዩነት ለማስተካከል ተችሏል።

4ኛ ከሱማሌዎች ጋር በተደረገው ትግል የሠራዊታችን መሪዎች በአጠቃላይ ከላይ እስከ ታችና መላው ምንዝር ወታደር ከፍ ያለ የውጊያ ልምድ አግኝተዋል።

5ኛ ለሠራዊታችን መሰጠት ያለበትን የሕክምና አገልግሎት በሁለንተናዊ መልኩ ከማሻሻል ባሻገር በፍልሚያው በፅኑ የቆሰሉና የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን የአብዮታዊ ሠራዊታችንን አባላት ዘለግ ላለ ጊዜ የሚያገግሙበት የጀግኖች አምባ በመባል የሚታወቅ ዘመናዊ የሕክምናና የማገገሚያ ተቋም በመገንባትና በማደራጀት ለቆሰሉ

ጀግኖቻችን አስፈላጊውን እንክብካቤ ከማድረግ በላይ በዚያው በአምባው ውስጥ ሰው ሠራሽ አካል የሚያመርት ተቋም በማደራጀት የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ጀግኖች ሰው ሠራሽ አካል ለማደል ተችሏል፡፡

6ኛ ያገቡ፣ ትዳርና ቤተሰብ የመሠረቱ የአብዮታዊ ሠራዊታችን አባላት ለአገራቸው አንድነትና ለአብዮቱ ደህንነት ሲፋለሙ የወደቁ ጀግኖቻችን ልጆች አሳዳጊ አልባ ሆነው የትም ሳይጣሉ ወይንም ሳይወድቁ በእንክብካቤ የሚያያድጉበትና የሚማሩበት ዘመናዊ የህፃናት አምባ ለማቋቋም ተችሏል፡፡

7ኛ አንደኛው አብዮታዊ ሠራዊታችን በምሥራቅና በደቡብ የጦር ግንባር ከሱማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጋር በሚታገልበት ጊዜ ስለ ጦርነቱ ሁኔታ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ የሚያውቀው ነገር አልነበረም፡፡

በአገራችን ሰሜናዊ ክልል ገንጣዮችን ለመመንጠር የሚደረገውን የማጥቃት ውጊያ ሂደትና ውጤት ህዝቡ ያውቅ ዘንድ የጦር ሜዳ ዜና አቅራቢ የጋዜጠኞች ቡድን በየውጊያ ቀጠናዎች ከማሰማራት ባሻገር የጦርነቱን ታሪክም ለመመዝገብ አስፈላጊው መሰናዶ ተደርጓል፡፡

አገርና አብዮትን ለማዳን ከተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጋር ባደረግነው ፍልሚያ የማያዳግም ድል ከተቀዳጀን በኋላ ፊታችንን ወደ ሰሜን ያዞርነው በግንቦት ወር 1970 ዓ.ም ነው፡፡ በሰሜን ኢትዮጵያ በአገር ገንጣዮች ላይ የሚደረገውን የጥቃት ዘመቻ መምራት ያለበትን ብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ ከአገሪቱ ርዕሰ ከተማ ከአዲስ አበባ ወደ ትግራይ ክፍለ ሃገር ርዕሰ ከተማ መቀሌ ማዛወር ነበረብን፡፡ ብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ በትግራይ ራሱን ከአቋቋመ በኋላ በአመራሩ ሥር እዚያው ትግራይ ክፍለ ሃገር ውስጥ ሁለተኛውን ነፃ አውጪ አብዮታዊ ሠራዊት ማቋቋም ነበረበት፡፡

የሰሜን ኢትዮጵያን የአየር ንብረት፣ የመልክአ ምድር አቀማመጥ፤ ገንጣዮች ለዓመታት የተቆጣጠሩትን ክልል ስፋት፣ የገንጣዮችን የውጊያ ዘይቤ፣ የአረቡ መንግሥታት ገንጣዮችን ከማደራጀት ባሻገር ለውጊያው የሚያስፈልጋቸውን መሣሪያዎች፣ ትጥቆች ቀለብና ልዩ ልዩ ቁሳቁስ የሚያቀርበውና በሕክምና ረገድም በአገሩ የሚያስተናግደው ጎረቤታችን የሱዳን መንግሥት ሁኔታ በብዙ ረገድ ከሱማሌ መንግሥት፣ ከሱማሌ የመልክአ ምድር አቀማመጥና የሱማሌን መንግሥት ከሚያዋስነው የሕንድ ውቅያኖስ ጋር ፍፁም የተለየ ስለሆነ እነዚህና ታሳቢ ጉዳዮች ያካተተና ያገናዘበ፣ ከምሥራቁና ከደቡብ የውጊያ አሰላለፋችንና የውጊያ ሥልታችን የተለየ የውጊያ ስልት ማቀድና ዘመቻውን የሚያራምደውን የሠራዊት አደረጃጀትና የውጊያ አሰላለፍ በሚገባ በማጥናት የተዘጋጀ ዘመቻ መሆን ነበረበት፡፡

በእነዚህ በጠቀስኳቸው መርሆዎችና ወታደራዊ ፅንሰ ሃሳቦችላይ ተመሥርተን ከዚህ የሚከተሉትን ፅያሄ ተግባሮች በቅድም ተከተል አዘጋጀን። ከአዲስ አበባ ወደ መቀሌ የተንቃነቀው ብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ የወል አመራር አባላት፤

1. ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም ሰብሳቢ
2. ኮሎኔል ተስፋዬ ገብረኪዳን የደርጉ መከላከያ ኮሚቴ ሊቀመንበር ምክትል ሰብሳቢ
3. ሻምበል ለገሠ አስፋው የጦር ኃይሎች የፖለቲካ አስተዳደር ኮሚሳር አባል
4. ሌ/ኮሎኔል ክብረት ጎንጤ የጦር ኃይሎች የፖለቲካ አስተዳደር ምክትል ኮሚሳር አባል
5. ኮሎኔል ኃይለጊዮርጊስ ኃብተማሪያም የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም አባል
6. ሌ/ኮሎኔል ገብረክርስቶስ ቡሊ የዘመቻ መኰንን
7. ሌ/ኮሎኔል ስዩም መኰንን የመረጃ መኰንን
8. ሌ/ኮሎኔል ነጋሽ ዱባለ የሎጀስቲክ አስተባባሪ መኰንን አባል።

ሌ/ኮሎኔል ነጋሽ ዱባለን የሎጀስቲክ አስተባባሪ ያልኩበት ምክንያት ብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ የተቋቋመበት ጊዜያዊ ዓላማ ውጊያውን ለመምራት እንጂ አጠቃላዩን የመከላከያ ሠራዊታችንን የሎጀስቲክና የአስተዳደር ሥራ ለመምራት ስላይደለና የሎጀስቲክ ሥራ የሚመራው በምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያ ስለሆነ ነው።

ምዕራፍ አርባ አንድ

የሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት አደረጃጀትና የውጊያ አሠላለፍ

ሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት የምንለው ተቋም፣ አንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት በደቡብና በምሥራቅ የአገራችን ክልሎች ከተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጋር አገርንና አብዮትን ለማዳን በሚታገልበት ጊዜ በሰሜን የአገራችን ክልሎች በተለይ በኤርትራ ክፍለ ሃገር የገንጣዮችን ጥቃት ሲከላከል የነበረውን ጦር፣ ለሰሜኑ የመልሶ ማጥቃት ውጊያ በትግራይ፣ በጐንደር፣ በአሰብ፣ በሲዳሞና በሸዋ ውስጥ በነበሩን ልዩ ልዩ የጦር ማሠልጠኛ ተቋማት ውስጥ አሠልጥነን ለውጊያ ያዘጋጀናቸውን በርካታ እግረኛ ክፍለ ጦሮች፣ መድፈኛ፣ ሜካናይዝድና ታንከኛ ወዘተ ብርጌዶች ጋር ከምሥራቅ ያመጣናቸውን ሦስት እግረኛ ክፍለ ጦሮች ያካተተ ሠራዊት ነው።

ከምሥራቅ ያመጣናቸው ክፍለ ጦሮች የትም ሳይቆሙ ወደ የውጊያ ተልእኮአቸው ሲያመሩ የተቀሩት የተለያዩ የጦር ክፍሎች ከውጊያ በፊት የተካበቱት በትግራይ ክፍለ ሃገር አብዛኛው በመቀሌ፣ የተቀሩት በኩያ በአክሱምና በሽሬ ከተሞች ነበር።

ሁለተኛው ነፃ አውጪ አብዮታዊ ሠራዊት የማጥቃት ውጊያውን ጀምሮ የኤርትራን ደጋማ አውራጃዎችና ምፅዋን ከገንጣዮች እስኪያፀዳ ድረስ የሚያስፈልጉት ጥይቶች፣ ሥንቆች፣ ነዳጅና ቅባቶች ወዘተ አጠቃላይ ሎጅስቲክ ለዳግም እደላ የተካበቱት በትግራይና በጐንደር ክፍለ ሃገራት ነበር።

የሠራዊቱ አደረጃጀትና የውጊያ አሰላለፍ በመጠነ ሰፊ ሠራዊት ጣላትን በመክበብ በአፈና ውጊያ በመደምሰስ ስልት ላይ የተመሠረተ አደረጃጀትና አሰላለፍ ነው። በዚህ የውጊያ ስልት በብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ አመራር አካላት የተመረጠው የሠራዊት አደረጃጀት የግብረ ኃይሎች አደረጃጀት ነው።

በኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ አንድ ላይ የገለፅኩ ቢሆንም በድጋሚ አንባቢን ለማስታወስ ግብረ ኃይል ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከዚህ እንደሚከተለው አስረዳለሁ።

ግብረ ኃይል የምንለው መጠኑ እንደ አስፈላጊነቱ የሚወሰንና ልዩ የሥራ ተልዕኮ የተሰጠው ቡድን፣ ድርጅት ወይም ተቋም የምስጢር ስም ሲሆን በወታደራዊ ተቋም ውስጥ ብቻ ሳይሆን በሠላማዊ ሥራ ወይም አገልግሎት ሊውል ይችላል።

ከዚህ በላይ ከፍ ብዬ በገለፅኳቸው የተለያዩ ምክንያቶች በሠራዊታችን ውስጥ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የግብረ ኃይሎችን ወታደራዊ አደረጃጀት ለመጠቀም የወሰነው ለሰሜኑ ዘመቻ በሁለተኛው ነፃ አውጪ አብዮታዊ ሠራዊታችን ውስጥ ነው።

ግብረ ኃይል የምንለው የጦር አደረጃጀት የጠላትን መጠንና ዓይነት፣ የሚዋጋበትን የመልካ ምድር ዓይነትና ባህሬ በማመዛዘን ጠላትን ወግተን ለመደምሰስ ያስችላል ተብሎ በወታደራዊ አመለካከት ሲታመንበት ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን፤

በአንድ መጠነ ሰፊ ሠራዊት ውስጥ ለመጠነ ሰፊ ውጊያ የሚደራጁ ግብረ ኃይሎች የሰው ኃይል፣ የሚታጠቁት የመሣሪያዎች ዓይነትና መጠን እያንዳንዱ ግብረ ኃይል እንዲያከናውን ከተሰጠው ግብር ጋር የተመጣጠነ መሆን ስለአለበት በርካታ ግብረ ኃይሎች በተቋቋሙበት ሠራዊት ውስጥ አንዱ ከሌላው የተለየ ሲሆን ሲችል የአንድ ግብረ ኃይል መጠን ከአንድ ክፍለ ጦር በላይ እስከ ሦስት ክፍለ ጦር ብዛት ያለው ሊሆን ይችላል።

በብሔራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ ዕዝ ሥር የተቋቋሙት የሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት ግብረ ኃይሎች ዝርዝር ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

1ኛ. 501 ግብረ ኃይል በኰሎኔል ረጋሳ ጂማ የሚታዘዝ

2ኛ. 502 ግብረ ኃይል በኰሎኔል አሥራት ብሩ የሚታዘዝ

3ኛ. 503 ግብረ ኃይል በኰሎኔል ካሳ ገብረማሪያም የሚታዘዝ

4ኛ. 504 ግብረ ኃይል በዘመቻ መምሪያው ዕዝ ተጠባባቂ (ደጀን)

5ኛ. 505 ግብረ ኃይል የምፅዋን ከተማና ወደብ ከገንጣዮች ሲከላከል የቆየውና በሌ/ኰሎኔል አበራ አበበ የሚ ታዘዝ

6ኛ. 506 ግብረ ኃይል የአሥመራን ከተማና አካባቢውን ለዓመታት ከገንጣዮች ጥቃት ሲከላከል የቆየው ጦር በጠቅላላና በኰሎኔል መርዕድ ንጉሴ የሚታዘዝ።

ግብረ ኃይሎቹ ከተቋቋሙ በኋላ ተከታዩ ተግባር የዘመቻውን ምክር ቤት ማቋቋም ሲሆን የዘመቻው ምክር ቤት አባላት ቁጥር አስራ ሰባት ሆኖ ቅምሩ ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

1. የብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ አመራር አካላት
2. ስድስቱ የግብረኃይሎች አዛዦች
3. ሦስቱ የጦር ኃይሎች አዛዦች ሲሆኑ የምክር ቤቱ ጸሐፊ ሌ/ኰሎኔል ገብረክርስቶስ ቡሊ ነበር።

ወታደር ላልሆኑ አንባቢዎች ግንዛቤ የኃይል አዛዦች የምንላቸው፣ የምድር ጦሩን፣ የአየር ኃይሉን እና የባሕር ኃይሉን አዛዦች ነው።

ሰኔ 20 1970 ዓ.ም መቀሌ በሚገኘው የብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ ጽህፈት ቤት በሆነው የአፄ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት ውስጥ የመጀመሪያው የዘመቻው ምክር ቤት ስብሰባ ተደረገ።

ምክር ቤቱ ተወያይቶ ወይንም መክሮ ውሳኔ እንዲሰጣቸው በዘመቻው መምሪያ የቀረቡ አጀንዳዎች፦

1ኛ. በግብረ ኃይሎች አደረጃጀት፣ የሰው ኃይልና የመሣሪያዎች ምጣኔ ላይ፣

2ኛ. ግብረ ኃይሎቹ እንዲያከናውኑ በተነደፈው የውጊያ እቅድና፣

3ኛ. በሎጀስቲክ መሰናዶና አቅርቦት እቅድ ላይ ተወያይቶ እንዲወሰን ነበር።

የግብረ ኃይሎችን አደረጃጀትና የውጊያግባቸውን በተመለከተ፣ በስብሰባው ሰሞን በተገኘ አዲስ መረጃ የሁለተኛውን ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊትን ጥቃት ለመከላከል ሲል ጀብሐ ብሎ ራሱን የሚጠራው ገንጣይ ድርጅት በኤርትራ ደጋማ አውራጃዎች በትግራይ ጠረፍ ዳርቻ በአደረገው የአሰላለፍ ለውጥና በውጊያ ቀጠናው ስፋት መሠረት በኮሎኔል ካሣ ገብረማሪያም የሚመራው 503 ግብረ ኃይል አመራሩ እንደአለ ሆኖ በንዑስ ግብረ ኃይሎች ቢከፋፈል ውጊያውን ውጤታማ ያደርገዋል የሚል ሃሳብ ከማቅረብ በተረፈ የኃይል አደረጃጀቱንና የውጊያውን እቅድ በማድነቅ ምክር ቤቱ በሙሉ ድምፅ አፀደቀው።

በሎጀስቲክ በኩል የዳግም እደላዎችን አቅርቦት በተመለከተ ለግንዛቤ ያህል አንዳንድ አዛዦች በተለይም ከአሥመራ ከትግራይና ከጐንደር ርቀው የሚዘምቱት ኮሎኔል አሥራትና ኮሎኔል ረጋሳ ከአቀረቧቸው ጥያቄዎች በስተቀር ብዙ ሳያነጋግረን ነው የይሁንታ ውሳኔ የተሰጠው።

ይህ የመጀመሪያው የሰሜን ዘመቻ ምክር ቤት ስብሰባ የወሰደው የሁለት ቀናት ጊዜ ተጠናቆ ስብሰባው ሲያበቃ፣ የሁለተኛውን ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት አደረጃጀት አስመልክተው የምክር ቤቱ አባላት በሙሉ ከፍተኛ ደስታና ኩራት የተሰማቸው መሆናቸውን እያንዳንዳቸው በስሜት ራሳቸውን የገለፁ ሲሆን በሦስት ምዕራፍ ውጊያ እንዲጠናቀቅ የታቀደው የውጊያ እቅድ የኤርትራን ችግር ለአንዴና ለመጨረሻ እንደሚያስወግድ የምክር ቤቱ አባላት በሙሉ ያመኑበት ነበር።

ከስብሰባው ፍፃሜ በኋላ በማግሥቱ ሐምሌ 23 ቀን በሄሊኮፕተር በመንገዝ የየግብረ ኃይሎቹ ሠራዊቶች ሠፍረው በሚገኙባቸው ሥፍራዎች በመቀሌ ከተማ ዙሪያና አካባቢ፣ በኩያ፣ በአደዋ፣ በአክሱምና በሽሬ የምክር ቤቱ አባላት በሙሉ

የሠራዊቱን ጠቅላላ የውጊያ መሰናዶ፣ የሠራዊቱን ትጥቅና አለባበስ፣ ከየመሣሪያዎቹ ጥራትና ብዛት ጋር ወጣቱን ሠራዊት እየተዘዋወርን ለሁለት ቀናት ያህል ጎበኘን።

ሠራዊቱ ሙሉ ትጥቁን ታጥቆ በመሰለፍ ያሳየን አኩሪ የሠራዊት ገፅታና ልቀቁን እንዲሄድ የሚለው የውጊያ ሞራሉ በእጅጉ ተደስተን ወደ መቀሌ ከተመለስን በኋላ የየግብረ ኃይል አዛዦች ወደ የጦር ክፍላቸው ተመለሱ።

ምዕራፍ አርባ ሁለት

የሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት የኤርትራን ክፍለ ሃገር ከገንጣዮች ቁጥጥርና ተፅእኖ ነፃ የማውጣት ዘመቻ

ምዕራፍ አንድ ዘመቻ - በኰሎኔል ረጋሣ ጂማ የሚመራው 501 ግብረ ኃይል በአንደኛው ምዕራፍ ዘመቻ ከጐንደር ተነስቶ በትክል ድንጋይ፣ በሑመራ አድርጎ የተከዜን ወንዝ ተሻግሮ ኤርትራ ክፍለ ሃገር በመግባት በመንገዱ ላይ የሚያገኛቸውን ገንጣዮች እየመታ በመሄድ የጋሽና ሰቲት አውራጃ ርዕሰ ከተማ የሆነውን ተሰነይን ከተቆጣጠረ በኂላ በአውራጃው ውስጥ ያሉትን ገንጣዮች መንጥሮ በማፅዳት ለሚቀጥለው ምዕራፍ ሁለት ዘመቻ መዘጋጀት።

501 ግብረ ኃይል ከአጋዴን እስከ ጐንደር፣ ከጐንደር ከተማ እስከ ሑመራና ብሎም የተከዜን ወንዝ ተሻግሮ ኤርትራ በመግባት ከሑመራ እስከ ተሰነይ ድረስ አብዛኛውን መንገድ በእግሩ የተጓዘ ግብረ ኃይል ነው።

ይህ ግብረ ኃይል የአንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት አካል በነበረበት ጊዜ በምሥራቁ ዋና የጦር ግንባር በቆሬ የተስፋፊውን የሱማሌ መንግሥት ዋና ወራሪ ጦር ጥቃት ለመከላከል በተደረገው ታላቅና መስዋዕትነት የተሞላው ትግል ከፍ ያለ አስተዋፅኦ በማድረግ ለድል ካበቁን የጦር ክፍሎች ግንባር ቀደም በመሆን ድል የቀመሰና ጥሩ የውጊያ ልምድ ያለው ጦር ነው።

501 ግብረ ኃይል፣ የሚታመንና የሚያኰራ ጦር በመሆኑ ነው የገንጣዮች መግቢያና መውጫ ዋና በር የሆኑትን የጠረፍ አውራጃዎች የመቆጣጠርና የማፅዳት ግዳጅ የተሰጠው። ይህ ግብረ ኃይል ገንጣዮችን ከማደራጀት ጀምሮ ሁለንተናዊ ድጋፍ እየሰጠ ከሚያደማን የሱዳን መንግሥት ጋር በሚዋሰነው የአገራችን ክፍል የሚንቀሳቀስ ነው።

በኰሎኔል አሥራት ብሩ የሚመራው 502 ግብረ ኃይል በአንደኛው ምዕራፍ ውጊያ ከትግራይ ሽሬ ተነስቶ በባድሜና በሽንበቆ አድርጎ ባሬንቱ በመግባት ለዓመታት በገንጣዮች ተከቦ በጀግንነት ሲቀጣቀጥ የቆየውን ስምንተኛውን እግረኛ ብ ርጌድ ጦር ከከበባ በማውጣትና የኩናማን ጀግና ሕዝብ ከገንጣዮች ተፅእኖ ነፃ በማድረግ ለሁለተኛው ምዕራፍ የውጊያ ግዳጅ እንዲዘጋጅ።

የሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት ዘመቻ የተጀመረው በክረምቱ መግቢያ ወራት በመሆኑና 502 ግብረ ኃይል በበርካታ ታንኮች የታጀበ ስለነበር በጭቃና በውሃ ሙላት እንቅፋትነት የግብረ ኃይሉ ጉዞ የታወከ ስለነበረ ባሬንቱን ለመቆጣጠር የቻለው ከተሰጠው ጊዜ ጥቂት ዘግይቶ ነበር።

በኰሎኔል ካሣ ገብረማሪያም የሚመራው 503 ግብረ ኃይል በአንደኛው ምዕራፍ ውጊያ በኤርትራ ደጋማ አውራጃዎች ማለትም የአካለ ጉዛይንና የሠራዬን አውራጃዎች ለዓመታት በመቆጣጠር መሽገው የተቀመጡትን ገንጣዮች አጥቅቶ የመደምሰስ የውጊያ ግዳጆች የተሰጠው በጣም ግዙፍ መጠነ ሰፊ ሠራዊት በመሆኑና ከገንጣዮች የውጊያ ሥፍራ አያያዝ ጋር በተገናዘበ ሁኔታ የሚወስደው የማጥቃት እርምጃ ስኬታማ ይሆን ዘንድ ግብረ ኃይሉ በአንድ ዋና እዝ እየተመራ በአሰላለፍ ረገድ በሦስት ንዑስ ግብረ ኃይሎች ተከፍሎ ከዚህ የሚከተሉትን ግዳጆች እንዲወጣ ተወሰነ።

1ኛ 503 ንዑስ ግብረ ኃይል (ሀ) በዛላአንበሳ፣ በአዲቀይህና በሰገነይቲ የሚገኙትን ገንጣዮች እየመታ በመሄድ ደቀ መሐሪን እንዲቆጣጠር

2ኛ 503 ንዑስ ግብረ ኃይል (ለ) ከገሩሠናይ በመነሳት በፆረናና በማይ ዕዳጋ በኩል በመንገዱ ላይ ያገኛቸውን ገንጣዮች እየመታ በመሄድ ደቀመሐሪ ገብቶ ከንዑስ ግብረ ኃይል (ሀ) ጋር መገናኘትና ትዕዛዝ መጠበቅ። የእነዚህ የሁለቱ ንዑስ ግብረ ኃይሎች አዛዥ ሌ/ኰሎኔል ታሪኩ ላይኔ ነበር።

3ኛ 503 ንዑስ ግብረ ኃይል (መ) ከራማ በመነሳት በአዲኳላና በመንደፈራ የመሸጉትን ገንጣዮች ደምስሶ ንቅናቄውን በመቀጠል ድባርዋን መቆጣጠር። የዚህ ንዑስ ግብረ ኃይል አዛዥ ሌ/ኰሎኔል ሠይፉ ወልዴ ነበር።

እነዚህን ሦስት ንዑስ ግብረ ኃይሎች አካቶ የያዘውና በኰሎኔል ካሣ ገብረማሪያም የተመራው 503 ግብረ ኃይል በአንደኛው ምዕራፍ ውጊያ የተዋጋው፣ የኤርትራን ክፍለ ሃገር ደጋማ አውራጃዎች ለዓመታት በመቆጣጠር መሽጎ ከቆየው፣ የገንጣዮች ሁሉ አንጋፋ ከሆነውና ራሱን «ጀብሐ» ብሎ ከሚጠራው ገንጣይ ድርጅት ጋር ነው።

ጀብሐ የተፈጠረበትና ማህበራዊ መሠረቶቼ ናቸው የሚላቸው የኤርትራ ምዕራባዊ ቆላማ ክልሎች አንዱና በር የሆነው በ501 ግብረ ኃይል ቁጥጥር ሥር የዋለ መሆኑን የተገነዘበ በመሆኑ እንደተለመደው ለመሸሽና ወደ ሱዳን ለመግባት እድል እንደሌለው በማወቁ ተስፋ የመቁረጥ ይመስላል ለሳምንታት አልበገር ብሎ የአልሞት ባይ ተጋዳይነት ፅኑት ግል በማድረጉ በወገን ጦር ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ከአደረሰ በኋላ ነው የተደመሰሰው።

ጀብሐ በጠቅላላ ከነበረው ተዋጊ ኃይል ሰማኒያ በመቶ በላይ በሁለቱ ደጋማ አውራጃዎች ስብስቦ በመዋጋቱና ሙሉ በሙሉ በመደምሰሱ በግብረ ኃይሎች ውጊያ በመጀመሪያው ምዕራፍ ተዋጊው ሠራዊት ከትግል ውጪ በመሆኑ ነው የፖለቲካ ድርጅቱ ህልውና የከሰመውና የበላይነቱን ሥፍራ ሻዕቢያ የወሰደው።

በሌ/ኰሎኔል አበራ አበበ የሚመራው 505 ግብረ ኃይል ከአንድ ዓመት በላይ የምፅዋን ከተማ ከሻዕቢያ ጋር ተካፍሎ ወደቡ በጠላት እጅ እንዳይወድቅ ጨው ማሳ ውስጥ መሽጎ ከፍተኛ መስዋዕትነትን በጠየቀ ተጋድሎ ተከላክሎ የቆየ ጀግና ሠራዊት ነው።

በአንደኛው የውጊያ ምዕራፍ ለ505 ግብረ ኃይል የተሰጠው ግዳጅ ከፊሉን የምፅዋ ከተማ ዙሪያ በማጠር የተገነባውን የጠላት ምሽግ ሠብሮ በመውጣት ባላቋረጠ ውጊያና እንቅስቃሴ ጠላትን እያሳደደ በማጥቃት የአሥመራ ምፅዋን መንገድ መክፈት ነው።

መቀሌ ከተማ ላይ ብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ አመራር አካላት የሰሜኑን ዘመቻ ስናቅድ፣ ከገንጣዮቹ ብዛትና ጥንካሬ፣ ከታጠቋቸው የመሣሪያ ዓይነቶች በላይ ለምሽጋቸው ጥንካሬ ልዩ ግምት የሰጠናቸው የምፅዋንና የአሥመራን ከተማ ከበው ለመሸጉ ገንጣዮች ነበር።

እነዚህ ሁለት የወንበዴ ኃይሎች ከምፅዋ እስከ አቆርዳት ከተማ የተዘረጋውን የባቡር ሐዲድ እያፈረሱ በስፋትና በጥልቀት በሰሩት የብረት ምሽጎቻቸው በጣም የሚመኩ ናቸው።

ሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት ከመቋቋሙ በፊት የሰሜኑ ሠራዊታችን ወንበዴዎቹ የተመኩባቸውን የብረት ምሽጎች ለመጣስና ለማፈራረስ በተደጋጋሚ ያደረገው ጥረት ያለመሳካት ብቻ ሳይሆን ያጠቃ በነበረው ሠራዊታችን ላይ ከፍ ያለ ጉዳት መድረሱ ስለማይረሳ በምዕራፍ አንድ ዘመቻ የአሥመራ ምፅዋን መንገድ ለመክፈት በሚወስደው የማጥቃት እርምጃ ቢቻል በወገን ጦር ላይ ጉዳት እንዳይደርስ፣ ባይቻል ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት በተቻለ መጠን ለመቀነስ ከዚህ በታች የተመለከቱትን፣ የሰው ኃይልንና የተኩስ ኃይል የማጠናከር፣ በጠላት ላይ ድንገተኝነትን የማግኘት፣ ጠላትን የማርበድበድና የማታለል መሰናዶዎች ተደርገዋል። እነሱም፤

1ኛ ሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት ከመቋቋሙ በፊት ይደረግ በነበረው የመከላከል ውጊያ የምፅዋን ግብረ ኃይል ያለማቋረጥ ስንገነባ ከመቆየታችን ሌላ በተጨማሪ 505 ግብረ ኃይል በአንደኛው ምዕራፍ በሻዕቢያ ላይ የሚወስደው የማጥቃት እርምጃ ስኬታማ ይሆን ዘንድ ከምሥራቅ ኢትዮጵያ በመጣ አንድ እግረኛ ክፍለ ጦር ከማጠናከር ባሻገር በመሃል አገር የተደራጀ አንድ ሜካናይዝድ ብርጌድ ጨመርንለት።

የተደረበለት ሜካናይዝድ ብርጌድ በጠላት ላይ ድንገተኝነትን እንዲያገኝ ከምፅዋ ወደብ በስተምሥራቅ በምድረ ነክ ጀልባዎች ባህሩ ዳርቻ አውርደን ለጠላት በማይታይበት ሁኔታ ሰውረን ለውጊያ አሰለፍነው።

2ኛ በምሽጉ ውስጥ ያለውን የጠላት አሰላለፍና የተኩስ ኃይል ለማወቅ በመቶ የሚቆጠሩ አሮጌ የከባድ ካሚዮኖች ጎማዎችን ለግብረ ኃይሉ በመርከብ በማጓጓዝ አቅርበን የወገን ጦር ማጥቃቱን ከመሠንዘሩ በፊት በአጥቢያው ሌሊት ብልህ ወታደሮች ተመርጠው ጎማዎቹን በረድፍ ወደ ጠላት ምሽግ እያሽከረከሩ ነድተው በመላክ በሚፈጥሩት ድምፅና ያልተለመደ እንቅስቃሴ ጠላት የኢትዮጵያ ጦር የጨበጣ ጥቃት ጀመረ ብሎ በመከላከል በከፈተው ጠቅላላ ተኩስ የጠላት መሣሪያዎች የት እንዳሉ፣ የጠላት የተኩስ ኃይልና ብርቱ ጎኑ የቱ አቅጣጫ እንደሆነ የግብረ ኃይሉ አዛገች በሚገባ ለማወቅ ቻሉ።

3ኛ በዶጋሌና በምፅዋ ከተማ መሀከል ባለው ሃያ ኪ/ሜትር ርቀትና እንዲሁም ክልሉ ባለው ሜዳማነት ለከተማው ቅርበት ባለው ከከተማው በስተምሥራቅ 505 ግብረ ኃይል የጨበጣ ውጊያ ከመሠንዘሩ አስር ደቂቃ በፊት የአየር ኃይላችን በአንቶኖቭና በዳኮታ የመጓጓገ አውሮፕላኖች ላይ የተጫኑ ወደ አምስት መቶ የሚሆኑ የሰው ምሥልና ቅርፅ ያላቸውን፣ በሚገባ የታጠቁና የለበሱ በድን ወይንም ደም አልባ አየር ወለድ ጦሮችን በጃንጥላ ማውረድ ነበር።

ሻዕቢያ በብረት ምሽጉ ውስጥ የእኛን ማጥቃት እንደለመደው ያለ ጉዳት ተከላክሎ ለመመለስ ያዘጋጃቸውን ሦስት ብርጌዶች ያሰለፈ ሲሆን ለሦስቱ ብርጌዶች ደጀን የሆነ አንድ ሌላ ብርጌድ በዶጋሌ ነበረው።

በ1970 ዓ.ም ነሐሴ 21 ቀን ጎህ ሲቀድና ብርሃን በጥቂቱ ፊቷን ስትገልፅ ከሰማይ እየተምዘገዘጉ በጃንጥላ የሚወርዱትን የኢትዮጵያ ደም አልባ አየር ወለድ ጦሮች የተመለከተው የሻዕቢያ ጦር ተከበብን በማለት ከፊል ኃይሉን ከምሽግ አስወጥቶ የላካቸው ብርጌዶች የኛን አየር ወለድ ጦር ሰማይ ላይ እንዳለ ለማጥቃት ሲሮጡ፣ ከበስተ ምሥራቅ በባህሩ ዳርቻ ራሱን ሰውሮ የቆየው ሜካናይዝድ ብርጌዳችን በረድፍ ተሠልፎ እየሮጠ በመድረስ በዚያ አሸዋማና ገላጣ ሜዳ ላይ ከምሽጉ የወጣውን የሻዕቢያ ጦር እንደአልነበረ አደረገው።

ይህንን የተመለከተው በምሽጉ ውስጥ የነበረው ጦር ከምሽጉ እየወጣ እግሬ አውጪኝ ብሎ ወደ ዶጋሌ መሮጥ ቢጀምርም ሰው ከታንኮችና ከብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ሮጦ ለማምለጥ ስለማይችል ታንኮቹና ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎቹ በመትረየሳቸው እየተኮሱ ከመጣል ሌላ በሰንሠለታቸውና በጎማቸው እየደፈጠጡ ከተጫወቱበት የተረፈውን የግብረ ኃይሉ እግረኛ ጦሮች እየቃረሙ ፈጁት።

በምፅዋ ግንባር በአንደኛው ምዕራፍ ውጊያ ብዙ መስዋዕትነትን ይከፍላል ተብሎ የነበረው የ505 ግብረ ኃይል ሠራዊት ምሽጉን ጥሎ ሲፈረጥጥ ታንኮችና ብረት ለበሶች እያሳደዱ ከፈጁት በአጋጣሚ የተረፈውን ከመልቀምና የወደቀውን ቁስለኛ ከመቃረም በስተቀር የገጠማቸው ሥራ አልነበረም።

ይህም ሆኖ በዚያ ቀውጢ በሆነ ትርምስ ውስጥ ሲሸሹ የነበሩ የሻዕቢያ ወታደሮች የኛ ወታደሮች እየሮጡ ሲቀርቧቸው ፊታቸውን እየመለሱ በመተኮስ የወደቁት ቁስለኞች ሳይቀሩ ከወደቁበት ሥፍራ ቀና እያሉ በመተኮስ ብዙ ሰው ጎዱብን።

የሻዕቢያን ግንባር ቀደም ሦስት ብርጌዶች ታንኮቻችንና ብረት ለበሶቻችን ከእግረኛው ጦር ጋር በምፅዋ ሜዳ ላይ እያሳደዱ ሲያደባዩት አየር ኃይላችን በሚግ ተዋጊ አይሮፕላኖችና በተዋጊ ሄሊኮፕተሮች ከምፅዋ ከተማ በሃያ ኪ/ ሜትር ርቀት ላይ ዶጋሌ የነበረውን የሻዕቢያን ብርጌድ ከአሥመራ በፈረቃ በረራ እየተመላለሱ ሰማኒያ በመቶ የሚሆነውን ስለፈጁት በኛ ግምት ተረፈ የምንለው ያለ ማጋነን ከአስራ አምስት እስከ ሃያ በመቶ ብቻ ቢሆን ነው።

505 ግብረ ኃይል በአንደኛው ምዕራፍ ዘመቻ በምፅዋ ግንባር ምን ጊዜም ያልታየና ያልተገኘ አኩሪ ድል በመቀዳጀት ሻዕቢያን በሚገባ ተበቅሎ ያለ አንዳች ችግር የአሥመራ ምፅዋን መንገድ በመክፈት ግዳጁን ተወጥቷል።

ደም አልባው የአየር ወለድ ጦር ምስል የተዘጋጀው አዲስ አበባ በቤተመንግሥቱ የተሽከርካሪዎች መጠገኛ ሆርሻ ውስጥ ይሰሩ በነበሩ የቴክኒክ ባለሞያዎችና አናጺዎች ሲሆን ሥራውን የመራው ሌ/ኮሎኔል ዳንኤል አስፋው ነበር ዳንኤል አየር ወለድ ጦራችንን ከመሰረቱትና ለረዥም ጊዜ ከመሩት መኰንኖቻችን አንዱ ነበር።

በኰሎኔል መርዕድ ንጉሴ የሚመራው 506 ግብረ ኃይል በቅድመ አብዮት ለጠቅላላው የአገራችን ሰሜናዊ ክፍለ ሃገራት የፀጥታ ጥበቃ ሃላፊነት የነበረውን ሁለተኛውን ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር መሠረት አድርገን የገንጣዮችን የትጥቅ ሴራ ለመቋቋም በየጊዜው ከመሃል አገር የተለያዩ አያሌ የጦር ክፍሎች እየተላኩ የገነቡትና ወደ መጨረሻውም ጊዜ በተለይ የተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት የጦር ኃይል ከወረረን በኋላ የሰሜኑ ችግር እየሰፋና እየከፋ በመጣበት ጊዜ ከአንደኛ እግረኛ ክፍለ ጦር የተነጠለ አንድ እግረኛ ብርጌድ፣ የሰባት ዓመት ምልስ ጦሮችን፣ ብሄራዊ ጦሮችን፣ አባት ጦሮችን፣ አንድ ነበልባል ክፍለጦር፣ አሥራ ሰባተኛውን እግረኛ ክፍለ ጦርና ሁለት ሕዝባዊ ሠራዊት ክፍለ ጦሮችን እየላክን የገነባነው ግዙፍ ግብረ ኃይል ነው።

በምዕራፍ አንድ ውጊያ ለ506 ግብረ ኃይል የተሰጠው የውጊያ ግዳጅ ሁለቱ ገንጣይ ድርጅቶች ማለትም፣ ጀብሐና ሻዕቢያ በፈጠሩት ህብረት የአሥመራን ከተማ ዙሪያ መከላከያ ምሽግ ጥሰው በመግባት ከተማውን እንዳይወሩና የ2ኛውን ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት ምዕራፍ አንድ የዘመቻ እቅድ እንዳያቃውሱ ወትሮም እንደሚያደርገው የመከላከያ ምሽጉን ይበልጥ እያጠናከረ ዕነ የመከላከል ውጊያ ከማድረግ ባሻገር ያለውን መጠነ ሰፊ ሠራዊት ለአራቱ የከተማው ዙሪያ የውጊያ ቀጣናዎች ከፋፍሎ በማሰለፍ የነቃ መከላከል እያደረገ ጠላትን ፋታ ከመንሳት ባሻገር ገንጣዮቹ በጠቅላላ ወይንም በከፊል ኃይላቸውን ከምሽግ አውጥተው 503 ግብረ

ኃይል በኤርትራ ደጋማ አውራጃዎች የሚያራምደውን የማጥቃት ውጊያ እንዳያውኩ ወይንም እንዳያደናቅፉ ባላሰለሰ የመድፍ ድብደባ አንገታቸውን በማስደፋት ሰፍቶ መያዝና ለሰሜኑ ውጊያ አሥመራ ዋናው ሎጅስቲክ ማከማቻችን እንደመሆኑ መጠን አጥቂዎቹ ግብረ ኃይሎች ኤርትራ ከገቡ በኋላ የሚጠይቁትን ዳግም እደላ ማደል ነው፡፡

የነቃ መከላከል ማለት፣ ምሽግ ውስጥ አድፍጦ በመቀመጥ ጠላት ሲያጠቃ መከላከል ብቻ ሳይሆን ከምሽግ እየወጡ በጠላት ላይ የተወሰነ የጥቃት እርምጃ መውሰድ ወይንም ሁልጊዜ በውጊያ መጋፋት ማለት ነው፡፡

ምዕራፍ አርባ ሦስት

ምዕራፍ ሁለት ዘመቻ

ሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት በሰሜን ኢትዮጵያ እንዲያከናውን የታቀደው ዘመቻ፣ በሦስት ምዕራፍ በተከፋፈለ ክፍለ ጊዜ የኤርትራን ክፍለ ሃገር ከገንጣዮች ተፅእኖና ቁጥጥር ነፃ ለማውጣት ሲሆን የዘመቻው አፈፃፀም ቅደም ተከተል ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

1ኛ በምዕራፍ አንድ ዘመቻ ከኤርትራ ምዕራባዊ ቆላማ ክልል፣ የጋሽና ሰቲትን አውራጃ፣ ከደጋማው ክልል፣ የሠራዬንና የአካለጉዛይን አውራጃዎች፣ ከኤርትራ ምሥራቃዊ ቆላማ ክልል የምፅዋን አውራጃ፣ በአጠቃላይ አራት አውራጃዎችን ነፃ ማውጣት፤

2ኛ በምዕራፍ ሁለት ዘመቻ የሐማሴንንና የከረንን አውራጃዎች ነፃ ማውጣት

3ኛ በምዕራፍ ሦስት ዘመቻ የባርካንና የሣህልን አውራጃዎች ነፃ በማውጣት ለአንዴና ለመጨረሻ ኤርትራን ከገንጣዮች ፍፁም ማፅዳት ነበር።

በዚህ የዘመቻ እቅድ መሠረት ከሐምሌ እስከ መስከረም 1971 ዓ.ም ድረስ አራቱ ማለትም፤ 501- 502 -503 እና 505 ግብረ ኃይሎች ግዳጅ በተሰጣቸው የጊዜ ክልል ውስጥ በምዕራፍ አንድ ዘመቻ በአኩሪ ሁኔታ አከናውነዋል።

ለአንደኛው ምዕራፍ ዘመቻ መላው የ2ኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት አካል የሆኑ የጦር ክፍሎች በሙሉ ከትግራይና ከጐንደር ክፍለ ሃገራት ወጥተው ኤርትራ በመግባታቸውና ሁለተኛውንና ሦስተኛውን ምዕራፍ ዘመቻዎች በቅርበት መምራት ስለነበረበት ብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ የማዘገር ማዕከሉን በጥቅምት ወር መጀመሪያ ወደ አሥመራ ከተማ አዛወረ።

በምዕራፍ ሁለት ዘመቻ የሐማሴንና የከረንን አውራጃዎች ነፃ የማውጣት ግዳጅ የተሰጠው በምዕራፍ አንድ ዘመቻ ከአራቱ ግብረ ኃይሎች ጋር የማጥቃቱን ዘመቻ ሳይካፈል የአሥመራን ከተማና አካባቢውን ከገንጣዮች ጥቃት ሲከላከል የቆየውና በኰሎኔል መርዕድ ንጉሴ ለሚመራው 506 ግብረ ኃይል ነበር።

የአሥመራን ከተማ ከአንዴም ሁለት ጊዜ ሻዕቢያ ከግብረ አበሩ ማለትም ራሱን «ጀብሐ» ብሎ ከሚጠራው ሌላው ገንጣይ ጋር በህብረት ለመውረር ያደረጉት ሙከራ በአብዮታዊ ሠራዊታችን እንዲከሽፍ ከተደረገ በኋላ ከምፅዋ ከተማ እስከ አቆርዳት ከተማ የተዘረጋውን የባቡር ሃዲድ እያፈረሰ በአሥመራ ከተማ ዙሪያ በገነባው የብረት ምሽግ ውስጥ ሆኖ ጠንካራ መከላከል እንደሚያደርግና ከምሽጉ ወጥቶ እንዲሸሽ ቢገደድም ከአሥመራ ከተማ እስከ ከረን ከተማና ከዚያም ባሻገር እስከ መሳህሊት በር

ድረስ ያሉትን ለአብዮታዊ ሠራዊታችን እንቅስቃሴ እጅግ አስቸጋሪ የሚሆኑትን የመሬት ገፅታዎች በመጠቀም የሠራዊታችንን ንቅናቄ መግታት ብቻ ሳይሆን ብዙ አደጋዎችን ለማድረስ እንደሚሞክር ገምተናል።

ስለሆነም፤ ጠላት ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳቶች በተቻለ መጠን ለመቀነስ የሚያስችሉ መላዎችን ማለትም ለሠራዊታችን፣ ተነቃናቂነትን፣ ድንገተኝነትን፣ ፍጥነትንና ከሁሉም በላይ ከፍ ያለ የተኩስ የበላይነትን ለማግኘት የሚ ያስችሉትን የተለያዩ ከባድ መድፎችን፣ ተዋጊ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎችንና ታንኮችን ወዘተ የመሳሰሉ የማጥቂያ መሣሪያዎችን አዘጋጅተናል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ይደረግ እንደነበረው በአየር ወይንም በየብስ መጓጓዣዎች ከመሃል አገር ወደ ኤርትራ ማጓጓዝ አስፈላጊ ያልሆነና ከፍ ያለ የገንዘብ ወጪ ከማውጣት ፋንታ በቀለለ ወጪና በገፍ በባሕር አጓጉዘን ለማደል 505 ግብረ ኃይል የአሥመራ ምዕዋን መንገድ እስኪከፍት ከመጠባበቅ ሌላ በአንደኛው ምዕራፍ ዘመቻ የተዋጉት ግብረ ኃይሎች ነፃ ያወጧቸውን አውራጃዎች በሙሉና በሚገባ እስኪቆጣጠሩ ድረስ ሁለተኛው ምዕራፍ ዘመቻ እስከ ሕዳር ወር 1971 ዓ.ም ድረስ እንዲዘገይ ተደረገ።

በሁለተኛው ምዕራፍ ዘመቻ ከፍተኛ ትኩረትና ቅድሚያ የተሰጠው የመጀመሪያው ዕያሄ ተግባር በሐማሴን አውራጃ በአሥመራ ከተማ ዙሪያ ለዓመታት መሽጎ የተቀመጠውን «ሻዕቢያን» በመደምሰስ የአሥመራ ከረንን መንገድ መክፈት ነበር።

ይህ ግዳጅ የተሰጠውና በኰሎኔል መርዕድ ንጉሴ የሚመራው 506 ግብረ ኃይል በሁለተኛው ምዕራፍ ዘመቻ የመጀመሪያው ዕያሄ ተግባሩ ስኬታማ ይሆን ዘንድ አጥቂና ደጀን በመሆን እየተፈራረቁ በተናጠልና በወል የውጊያው ባህሪ በጠየቀ ሁኔታ፣ በህብረትና በመረዳዳት ይዋጉ ዘንድ 506 ግብረ ኃይል በሁለት ንዑስ ግብረ ኃይሎች ተከፍሎ በመዋቀር እንዲደራጅ ተደረገ።

አንደኛው 506 ንዑስ ግብረ ኃይል (ሀ)፣ ሁለተኛው 506 ንዑስ ግብረ ኃይል (ለ) ተብለው ከተሰየሙ በኋላ፣ የንዑስ ግብረ ኃይል (ሀ) አዛዥ ሌ/ኰሎኔል ሁሴን አሕመድ፣ የንዑስ ግብረ ኃይል (ለ) አዛዥ ሌ/ኰሎኔል ተስፋዬ ኃ ብተማርያም ከሆኑ በኂላ ሁለተኛው ምዕራፍ ዘመቻ የሚጀመርበት ጊዜ ሕዳር 12 ቀን 1971 ዓ.ም እንዲሆን ተወሰነ።

በዚሁ ጊዜ ውስጥ ማለትም በሕዳር ወር በኰሎኔል ካሣ ገብረማርያም የሚመራው 503 ግብረ ኃይል፣ በሌ/ኰሎኔል ታሪኩ ላይኔ የሚመራው 503 ንዑስ ግብረ ኃይል (ለ) ብቻ ተቀንሶበት የተቀሩትን ሁለቱን ማለትም 503 ንዑስ ግብረ ኃይል (ሀ) እና 503 ንዑስ ግብረ ኃይል (መ) ላይ በበረሐ ውጊያ ልምድ ያላቸውና

የ505 ግብረ ኃይል አካል ሆነው በምዕዋ ለሻዕቢያ ምሽግ ሰበራ ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ከአደረጉት እግረኛ ክፍለ ጦሮች 10ኛና 15ኛ እግረኛ ክፍለ ጦሮች ታክለውበት 507 ልዩ ግብረ ኃይል በመባል የተሰየመ ግብረ ኃይል በሦስተኛው ምዕራፍ ዘመቻ ወሳኝ ሚና እንዲጫወት በአካለጉዛይ አውራጃ ውስጥ በምስጢር እንዲቋቋም ተደረገ፡፡

በምስጢር ተቋቋመ ስል ሠራዊቱ እንዳይታይ ደበቅነው ወይንም ሠወርነው ማለት ሳይሆን የዚህ ግብረ ኃይል የውጊያ ተልዕኮ የኤርትራን ችግር በወታደራዊ መፍትሄነት ለአንዴና ለመጨረሻ ለመፍታት በሚከናወነው ምዕራፍ ሦስት ዘመቻ ቀዳሚውን ፅያሄ ተግባር ፈፃሚ የሆነ ወሳኝ ተልዕኮ ያለው በመሆኑ ከብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ የአመራር አካላት አምስት ጓዶችና ከአዛዥ ከኰሎኔል ካሣ ገብረማሪያም በስተቀር የግብረ ኃይሉ መለያ ስም የተቋቋመበት ዓላማና የሚሰጠው የውጊያ ተልዕኮ በጠላት ቀርቶ በወገን ጦር አዛዦችም እንዳይታወቅ በመደረጉ ነው፡፡

506 ግብረ ኃይል በሁለት ንዑስ ግብረ ኃይሎች ተዋቅሮ የሻዕቢያን ምሽግ ለመስበር በሚዘጋጅበትና ብሄራዊና አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ ከትግራይ ወደ ኤርትራ በተዛወረበት ጊዜ በሕዳር ወር መጀመሪያ በድንገት በፅኑ ታምሜ ለሕክምና ወደ ውጭ አገር በመሄዬ ምዕራፍ ሁለት ዘመቻ በሚካሄድበት ጊዜ በአመራር ላይ ስላልነበርኩ ከዚህ በኋላ ስለዘመቻው የምተርከው በብሄራዊና አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ አመራር ጓዶች ከሕክምና ስመለስ ስለ ዘመቻው የተነገረኝን ነው፡፡

በሁለተኛው ምዕራፍ ዘመቻ እቅድና ለ506 ግብረ ኃይል በተሰጠው የውጊያ ትእዛዝ መሠረት ሕዳር 12 ቀን 1971 ዓ. ም ለሚጀመረው ውጊያ ቀዳሚው ምሽግ ሰባሪ በሌ/ኰሎኔል ሁሴን አህመድ የሚመራው 506 ንዑስ ግብረ ኃይል (ሀ) እንዲሆን ተወሰነ፡፡

506 ንዑስ ግብረ ኃይል (ሀ) ሕዳር 12 ቀን 1971 ዓ.ም ከሌሊቱ አሥር ሰዓት ጀምሮ በመንቀሳቀስ ወደ ግቡ በሚቃረብበትና የጨበጣ ውጊያ በሚጀምርበት ጊዜ ጠላትም በበኩሉ ራሱን ለመከላከል በሚያደርገው ጥረት በወገን ጦር ላይ ጉዳት ከማድረሱ በፊት ለመደምሰስ፣ አየር ኃይላችን ጎህ ከቀደደበትና ብርሃን ዓይኗን ከገለጠችበት ጊዜ ጀምሮ ከአንድ ሰዓት ባላነሰ ጊዜ ያለማቋረጥ የጠላትን ምሽግ፣ በቦምብ፣ በሮኬትና እንደ አስፈላጊነቱ በመትረየስ ደበደበ፡፡ ቀጥሎም በ506 (ሀ) ግብረ ኃይል ውስጥ ከአንድ እግረኛ ሻምበል ጀምሮ ወደ ላይ በተለያየ ደረጃ ማለትም በሻለቆችና በብርጌዶች ተቋም ውስጥ ያሉት የተለያዩ ከባድ መሣሪያዎች የሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት የተለያዩ ከባድ መድፎች ከአንድ ሰዓት ላላነሰ ጊዜ የጠላትን ምሽግ ከደበደቡ በኋላ በታንኮቻችን ቀደምትነት 506 (ሀ) ንዑስ ግብረ ኃይል የጨበጣ ውጊያውን ጀምሮ በቅደም ተከተል የተገነቡትን የሻዕቢያ የብረት ምሽጎች በመሰባበር ለመጀመሪያው ቀን ውጊያ የተሰጡትን ግቦች በሙሉ በ1100 ማለትም ከጧቱ ወይንም ከቀትር በፊት በአምስት ሰዓት በቁጥጥሩ ሥር ማድረጉን አበሰረ፡፡

የ506 ግብረ ኃይል ግዳጅ የአሥመራን ዙሪያ የሻዕቢያ ምሽግ በመጣስና በመሰባበር ጠላትን በተቻለ መደምሰስና ከምሽጉ አስወጥቶ ከአባረረ በኋላ ቀጣይ ግዳጁ የአሥመራ ከረንን መንገድ መክፈት ነው ብንልም ከምሽጉ እየወጣ ወደ ከረን አቅጣጫ በመዝረክረክ ተበታትኖ የሚሮጠው ጠላት የአሥመራ ከረንን የተሽከርካሪ አውራ መንገድ ተከትሎ ሳይሆን ከመንገዱ ግራናቀኝ ባሉት ወጣ ገባ፣ ገደላገደልና ኰረብታማ መሬቶች ላይ ስለነበረ አጥቂዎቹ የወገን ግብረ ኃይሎች ማለትም፤ 506 (ሀ) እና 506 (ለ) ንዑስ ግብረ ኃይሎች ሥራና የውጊያ ቀጠና ተከፋፍለው ጠላትን እግር በግር እየተከታተሉ የሚያደርጉትን የማሳደድ ውጊያ በጣም አስቸጋሪና አዝጋሚ አድርጎት ነበር።

የብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ አመራር አካላት ቀደም ብለን እቅዱን ስንሰራ እንደገመትነው በመንገዱ ግራና ቀኝ ያሉትን ገኛ ወታደራዊ መሬቶችና ኰረብታዎችን በመጠቀም ሻዕቢያ አዘግይ ጦር እያስቀመጠ በመሸሹ ሁለቱም ንዑስ ግብረ ኃይሎች በተከታታይ ቀናት ማለትም ከ12/3/1971 እስከ 13/3/1971 በመንገዶቻቸው ላይ የማይናቁ ውጊያዎች የገጠሟቸው ሲሆን በተለይ 506 (ለ) ንዑስ ግብረ ኃይል በ13/3/1971 ቀኑን በሙሉ የወሰደ ውጊያ ለመዋጋት ተገድዶ ነበር።

ሻዕቢያ ፋታ ከተሰጠውና ጊዜ ከአገኘ የተበታተነ ጦሩን በማሰባሰብና በማደራጀት፣ የፈረሰውን እዝና ቁጥጥር መልሶ በማቋቋም፣ የአሥመራ ከረንን መንገድ ለመክፈት የወገን ጦር የሚያካሄደውን የውጊያ ሂደት አስቸጋሪና ምናልባትም ቀናቶችን ብቻ ሳይሆን ሳምንታትን እንዲጠይቀን በማድረግ የሁለተኛውን ምዕራፍ የውጊያ እቅድ ከማቃወስ ባሻገር የተበታተነ ጦሩን አሰባስቦ ወደ ሳህል አውራጃ በመሄድ በናቅፋ የተፈጥሮ ምሽጉ እንዳይገባ ለማድረግ አጥቂዎቹ የወገን ንዑስ ግብረ ኃይሎች ያለ እረፍት በሌሊትና በቀን እግር በእግር እየተከታተሉ እንዲያጠቁ ይፈለግ ነበር።

በ14/3/1972 ቀዳሚውና በሌ/ኰሎኔል ሁሴን አህመድ የሚመራው ንዑስ ግብረ ኃይል (ሀ) ከአሥመራ ዙሪያ ምሽግ በኋላ ሁለተኛ ግቡ ተደርጎ የተሰጠውን የአዲተክለዛንን ከተማ ከተቆጣጠረ በኋላ ጊዜ ሳያባክን ግስጋሴውን ወደ ከረን እንዲቀጥል ከበላይ አካል የተሰጠውን ትዕዛዝ ተግባራዊ በማድረግ ላይ እንዳለ፤ አንድ ያልተጠበቀ ድንገተኛና ከባድ አደጋ አጋጠመው።

የብሄራዊና አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ አመራር ሰጪ ጓዶች ብቻ ሳይሆኑ ቦታው ላይ ሲዋጉ የነበሩ በርካታ የፍልሚያው ተሳታፊዎች የነገሩኝ ታሪክ ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

506 ንዑስ ግብረ ኃይል (ሀ) በተለያዩ ከባድ መሣሪያዎችና ታንኮች የታጀበ ከመሆኑ በላይ ለውጊያው የሚያስፈልጉትን ጥይቶች፣ ሥንቅ፣ ነዳጅና ቅባቶች ወዘተ የጫኑ በርካታ የየብስ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች ነበሩት።

ከበላይ አካል የተሰጠው ትዕዛዝ የከረንን ከተማ በአስቸኳይ ከጠላት አስለቅቆ ይቆጣጠር ዘንድ ከአዲተክለዛን ተንቃንቆ ኤላበረድ ገብቶ እንዲያድር ነው።

በታዘዘው መሠረት ከአዲተክላዛን ቀኑ ከመሸ በኋላ ተነስቶ ወደ ከረን የሚወስደውን አስፋልት መንገድ ይዞ በመጓዝ ከአሥመራ ከተማ 70 ኪ/ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘውና ኤላበረድ ተብላ በምትጠራው ትንሽ የገጠር መንደር ቀኑ ከጨለመ በኋላ የጭነት ተሽከርካሪዎችና የታንኮች መብራት እያበራና የሻዕቢያ ጦር በገሐድ እየተመለከተው ይገባል።

አንባቢ እንደሚያስታውሰው በኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅዕ አንድ የጀነራል አማንን ወደ ኤርትራ ተልዕኮና የፈጠሩትን ቀውስ ሳስረዳ በዚች ኤላበረድ ተብላ በምትጠራ የገበሬዎች መንደር አጠገብ ባሉ ገሻር መሬቶች ላይ ገንጣዮች በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ አድፍጠው የሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር አባሎችና የክፍ ለሃገሩ ፈጥኖ ደራሽ ኮማንዶ ፖሊሶች ወደ ከረን ከተማ በተሽከርካሪ ሲጓዙ በከፈቱት ተኩስና በተፈጠረው ግጭት በገንጣዮቹ ላይ የደረሰ ጉዳት ነበር። ይህንን ምክንያት አድርገው ጀነራል አማን ከረን ከተማ ላይ ለህዝቡ ባደረጉት ንግግር ከሰሜኑ ከአብዮታዊ ሠራዊታችን ጋር ከፍ ያለ ቅራኔ ውስጥ እንዲገቡ ምክንያት የሆነችው ይህቺው ኤላበረድ፣ ወደ ከረን የሚወስደው አስፋልት መንገድ የሚያቋርጣት፣ በኮረብታዎች የተከበበች፣ ውሃ ገብ ሸለቆና ጎድጓዳ፣ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የወተት ምርት የሚያመርቱ ገበሬዎች መንደር ነች።

506 (ሀ) ንዑስ ግብረ ኃይል በቀን ብርሃን ብቻ ሳይሆን በምሽትም የአሥመራን ከተማ ዙሪያ የሻዕቢያ ምሽግ አጥቅቶ ከአስለቀቀበት ጊዜ ጀምሮ ለሁለት ተከታታይ ቀኖች እየተዋጋ እስከ አዲተክላዛንና ከዚያም ያለ እረፍት እስከ ኤላበረድ በእግሩ በመጓዙ የድካም ስሜት የነበረው ጦር ነበር ነው የተባለው።

ጦሩ ኤላበረድ ከደረሰ በኋላ በአካባቢው ያለውን ማናቸውንም ነገር በርቀት የመመልከት ችሎታው በጨለማው ምክንያት በጣም ውስን ነበር ከማለት ይልቅ ምንም ነገር ለማየት አይችልም ነበር ማለት ነው የሚሻለው።

የኤላበረድ ከተማና አካባቢው በዚያን ሰዓት ወይም ምሽት ምንም ነገር የማይሰማበት ረጭ ያለና ፍፁም ፀጥታ የሰፈነበት ነበር።

506 (ሀ) ንዑስ ግብረ ኃይል ባለፉት ሁለት ቀናት ማለትም ከ11/3/1971 እስከ 14/3/1971 ድረስ የሻዕቢያ ጦር እግሬ አውጭኝ በማለት ሲሮጥ ስለነበረ ሩጫውን አቁሞ ኤላበረድ ላይ አድፍጦ በመጠበቅ አደጋ ያደርስብናል የሚል ሥጋትና ግምት በግብረ ኃይሉ አዛገች ዘንድ ያልነበረ ነው የሚመስለው።

ይሄ ብቻ አይደለም ግብረ ኃይሉ ኤላበረድ እንደደረሰ ከመሥፈሩ በፊት ወገንን ከድንተገኛ የጠላት ጥቃት የሚጠብቁና ፈጥነው የሚያነቁ ወይም የሚያስጠነቅቁ የውጭ ዘቦች ከማውጣት ባሻገር የግብረ ኃይሉ መረጃ መኰንን ወዲያው ከአካባቢው ነዋሪ ህዝብ ጋር በመገናኘት የአካባቢ መረጃ መሰብሰብ ይገባው ነበር። ይህንን ማድረግ ተዘንግቶ ይሁን ወይም ጠላት ጊዜ ሳይሰጥ ቀርቶ ይህንን ከማድረጋቸው በፊት ቀድሞ አደጋውን ጥሎ እንደሆነ የታወቀ ነገር የለም።

በዚህ ሁኔታ የተመራው 506 (ሀ) ንዑስ ግብረ ኃይል መሣሪያዎቹን አስቀምጦና ትጥቁን አላልቶ ከማረፍና ከመዝናናት ባሻገር ተርቦም ስለነበር ከፊሉ ጦር የሚጠጣውን ውሃና ምግቡን የሚያበስልበትን ማገዶ ለመፈለግ ሲሰማራ ከአሥመራ ከተማ ዙሪያ ምሽግ ወጥቶ የሸሸ ወይንም ቀድሞውንም እዚያው ኤላበረድ የነበረ ወይም የወገን ጦርን ግሥጋሴ ለመግታት ሻዕቢያ ከሳሕል አውራጃ ያመጣው ጦር እንደሆነ አልታወቀም 506 (ሀ) ግብረ ኃይል በሠፈረበትና ከጠብመንጃ የውጤት ርቀት በራቀ ሥፍራ አድፍጦ የወገንን ጦር ሁኔታ ሲያስተውልና ሲያጠና ያመሻል።

የኛ ጦር ለጥቃት ፍፁም በተመቻቸለት ሁኔታ ነው ያለው ብሎ በአመነበት ጊዜ በወገን ጦር ላይ ተኩስ ይከፍታል። የከባድ መሣሪያ ጥይቶችን፣ ነዳጅና ቅባቶችን፣ ሥንቅና የተለያዩ ቁሳቁሶችን ጭነው በቆሙ ተሽከርካሪዎች ላይ በከባድ መሣሪያዎች፣ በታንኮችና በመላው የግብረ ኃይሉ ጦር ላይ ለአኩል ሰዓት ያህል ጊዜ በመተኮስ የወገን ጦር የሠፈረበትን ሠፈር በማጋየትና በማቀጣጠል ድንገተኛ አሸባሪ ሁኔታን ከፈጠረ በኋላ የነፍስ ወከፍ አውቶማቲክ ጠብመንጃዎች፣ የመትረየሶች፣ የፀረ ታንክ መሣሪያ ጥይቶችን በወገን ጦር ላይ የሻዕቢያ ጦር እያርከፈከፈና የእጅ ቦምብ እየወረወረ በጨበጣ ውጊያ ከወገን ጦር ጋር ሲቀላቀል የተፈጠረውን ሽብርና ትርምስ ለመግለፅ ያስቸግራል።

የሁሉቱም ወገን ተፋላሚ ጦር ወገንና ጠላትን መለየት ባለመቻሉ እያንዳንዱ ሰው የቀረበውን ሁሉ ሊገለኝ የመጣ ጠላት ነው በማለት ሳይገድለው በመግደል አሰቃቂ መፋጀት ስለነበረ ለማጥቃት የመጣው የሻዕቢያ ጦርም ከወገን ጦር ባላነሰ የመጨፋጨፉ ውጊያ ሰለባ ነው የሆነው። የ506 ንዑስ ግብረ ኃይል (ሀ) እዝና ቁጥጥር በመፍረሱ ከበላይ አካል ጋር የነበረው የወታደራዊ ራዲዮ ግንኙነት ተቋርጧል።

የ506 (ሀ)ንዑስ ግብረ ኃይል አዛዥ ሌ/ኰሎኔል ሁሴን አሕመድ በ14/3/71 ምሽት ኤላበረድ መድረሱን ለበላይ አካል ካሳወቀ በኋላ ከአንድ ሰዓት ባልበለጠ የጊዜ ልዩነት ከባድ ውጊያ ስለገጠመዉ ነው ግንኙነት የተቋረጠው።

ሁሴን ከባድ ውጊያ ገጥሞኛል ብሎ ካመለከተ በኋላ የራዲዮ ግንኙነት የተቋረጠው በእርግጥም ከባድ አደጋ ገጥሞት እዝና ቁጥጥሩ ቢፈርስ ይሆናልና በሌ/ኰሎኔል ተስፋዬ ኃብተማሪያም የሚመራው 506 (ለ) ንዑስ ግብረ ኃይል

በነጋታው ለእርዳታ በተቻለ ፍጥነት ከአዲተክላዛን ተንቀሳቅሶ ኤላበረድ እንዲደርስ ይታዘዛል።

ሌ/ኰሎኔል ሁሴን ሻዕቢያ ባደረሰበት ያልተጠበቀ ድንገተኛ ጥቃት ተሸብሮና ተመሳቅሎ ወደ መበታተን የደረሰውን የግብረ ኃይሉን ጦር በማሰባሰብና መልሶ በማቋቋም፣ እዝና ቁጥጥሩን መልሶ በመመስረት ጠላት አደጋ ካደረሰበት ጎድጓዳ ሥፍራ ጦሩን አውጥቶ ከኤላበረድ መንደር በስተደቡብ የሚገኘውን ገዥ ወታደራዊ መሬት ተቆናጦ አዳር ያደርጋል።

አጥቂው የሻዕቢያ ጦር ራሱ በከፈተው ውጊያ ክፉኛ የተጎዳና የተዳከመ ስለነበረ የወገን ጦር ሲያፈገፍግ ተከታትሎ ለማጥቃት አልሞከረም።

በ15/3/1971 ንጋቱ ላይ ውጊያ የተጀመረው በ506 (ሀ) ንዑስ ግብረ ኃይል ቀደምትነት በአካባቢው ያሉትን ጠቃሚ ወታደራዊ መሬቶች ቀድሞ ለመቆጣጠር በተደረገ ሽሚያ ነው።

በሌ/ኰሎኔል ተስፋዬ ኃብተማሪያም መሪነት በእርዳታ ከአዲተክላዛን ወደ ኤላበረድ የተንቃነቀው 506 (ለ) ንዑስ ግብረ ኃይል ኤላበረድ የደረሰው በቀኑ አጋማሽ ላይ ወደ ስድስት ሰዓት ገደማ 506 (ሀ) ንዑስ ግብረ ኃይል ከሻዕቢያ ጋር በውጊያ እንደተያያዘ ነው።

በዚህ ጊዜ የ506 ግብረ ኃይል ዋና አዛዥ ኰሎኔል መርዕድ ንጉሴ ሁለቱን ንዑስ ግብረ ኃይሎች አስተባብረው ለመምራት ከአዲተክላዛን ማዘዣ ጣቢያቸው ተነቃንቀው ኤላበረድ ከጦሩ ጋር ተገናኝተዋል።

በዚያው ዕለት ማለትም፣ በ15/3/1971 ከቀትር በኋላ ሁለቱ ንዑስ ግብረ ኃይሎች ግራና ቀኝ በህብረት ሻዕቢያ የተቆጣጠራቸውን ጠቃሚ ወታደራዊ መሬቶች ለማስለቀቅ የሠነዘሩትን ማጥቃት ሻዕቢያ ከመመከት ባሻገር ባደረገው መልሶ ማጥቃት የወገንን ጦር በኃይል ገፍትሮ ወደ ኋላ ስለመለሰውና ጊዜውም በመምሸቱ ወገንም ጠላትም በያሉበት ውጊያውን አቁመው አዳር አደረጉ።

በነጋታው ማለትም፣ በ16/3/1971 ጧት ረፋዱ ላይ ዳግም በሁለቱ ንዑስ ግብረ ኃይሎች ህብረት፣ ከአየር ኃይላችን፣ ከመድፎቻችንና ከታንከኞቻችንጋር በተደረገ ቅንጅት የወገን ጦር ማጥቃት ሠንዝሮ ሻዕቢያ በደረሰበት ከባድ ጉዳት ምክንያት ኤላበረድን ለቆ ወደ ከረን አቅጣጫ በመሸሹ የወገን ጦር እያሳደደ ወደ ከረን ለመሄድ ዳድቶት ነበረ። ነገር ግን 506 ግብረ ኃይል ጠላትን መከተሉን ትቶ እዚያው ኤላበረድ ላይ መልሶ በመቋቋም እረፍት በማድረግ ለሚቀጥለው ግዳጅ ተዘጋጅቶ ትዕዛዝ እንዲጠብቅ በበላይ አካል ተወሰነ።

ይህ ትዕዛዝ በበላይ አካል የተሰጠው ከዚህ ቀጥሎ በምገልጣቸው ምክንያቶች ነው። 506 (ሀ) እና 506 (ለ)ንዑስ ግብረ ኃይሎች ከሕዳር 12 እስከ 15 ለተከታታይ አራት ቀናት ያለ እረፍት አድካሚ ጉዞ ከማድረጋቸው በላይ ኢላበረድ ላይ በ506 (ሀ) ንዑስ ግብረ ኃይል፣ ከፍተኛ የሰው ኃይሉ የተጎዳበት፣ የተቀነሰበትና ረጂ ከባድ መሣሪያዎቹ የወደሙበት ያልተጠበቀ ድንገተኛ አደጋ የደረሰበት ሲሆን፣ መንትያው 506 (ለ) ንዑስ ግብረ ኃይልም ሕዳር 15 እና 16 በተደረገው ውጊያ የደረሰበት ጉዳት ቀላል አልነበረም።

አንባቢ እንደሚያስታውሰው በሁለተኛው ምዕራፍ የዘመቻ እቅድ የ506 ግብረ ኃይል ግዳጅ በአሥመራ ከተማ ዙሪያ ሻዕቢያ ለዓመታት የተቀመጠበትን ምሽግ ከመስበር ጀምሮ በተከታታይ ቀናቶች የአሥመራ ከረንን መንገድ በመክፈት የከረንን አውራጃ ነፃ ማውጣት ነው።

የከረን አውራጃ በአጠቃላይ የከረን ከተማ በተለይ በዙሪያቸው ያለው የመልክአ ምድር ተፈጥሮ ለመከላከል ውጊያ አመቺ ከመሆኑ በላይ በተጨማሪ ለሰፊው የኤርትራ ምዕራባዊ ቆላማ ክልል ወደ ደጋው ክልል ብቸኛ መግቢያና መውጫ በር በመሆኑ ሻዕቢያ የከረንን ከተማ ባለመልቀቅ የመጨረሻውን ተጋድሎ ለማድረግ ያለውን የመጨረሻ ኃይል አሰባስቦ መቀመጡ ስለታወቀ 506 ግብረ ኃይል በአጭር ጊዜ ውስጥ ከረንን ነፃ ያወጣ ዘንድ ለሦስተኛ ጊዜ ከሻዕቢያ ጋር ማጋፈጥ አግባብ ወይንም ተገቢ የሆነ አመራር ካለመሆኑ በላይ አስደሳች ውጤት ይገኛል ተብሎ ስለማይጠበቅ የእቅድ ለውጥ ለማድረግ አስፈለገ።

506 ግብረ ኃይል ለአደረጋቸው ተደጋጋሚ ውጊያዎች ተደጋጋሚ ጉዳቶችና ቀውሶች ባይደርሱበትና በሁለተኛው ምዕራፍ የዘመቻ እቅድ መሠረት ብቻውን ከረንን ነፃ ለማውጣት ቢችል ኖሮ የምዕራፍ ሁለት ዘመቻ በከረን ነፃ መውጣት ስለሚጠናቀቅ፣ በሦስተኛው ምዕራፍ ዘመቻ እቅድ መሠረት፣ በኮሎኔል ረጋሣ ጅማ የሚመራው 501 ግብረ ኃይል ከተሰነይ በኮሎኔል አሥራት ብሩ የሚመራው 502 ግብረ ኃይል ከባሬንቱ ተንቀሳቅሰው በህብረት ውጊያ የባርካን አውራጃ በአጠቃላይ፣ የአቆርዳትን ከተማ በተለይ ነፃ ካወጡ በኋላ በአንድ እዝ ተማክለው 508 ግብረ ኃይል በተሰኘ ስም ለመጨረሻው ወሳኝ ውጊያ ወደ ሳሕል አውራጃ መዝመት ነበረባቸው።

ይህን በማድረግ ፋንታ በተለዋጩ የውጊያ እቅድ መሠረት 508 ግብረ ኃይል ወደ ሣህል አውራጃ ከመዝመቱ በፊት በቅድሚያ ከአቆርዳት ፊቱን ወደ ከረን በማዞር በከበባ የውጊያ ስልት ሻዕቢያን አጥቅቶ በመደምሰስ በኤርትራ የሚደረገውን የእርስ በርስ ጦርነት በ1971 ዓ.ም በሕዳር ወር ከረን ላይ ለመጨረስ ሲሆን፤

508 ግብረ ኃይል የከረንን ከተማ ከሻዕቢያ አስለቅቆ ከተቆጣጠረ በኋላ በመጀመሪያው የምዕራፍ ሦስት ዘመቻ እቅድ መሠረት ወደ መጨረሻ የውጊያ ግቡ ወደ ሣሕል አውራጃ መሄድ ስለነበረበትና የከረን ከተማ ደህንነት አስተማማኝ ይሆን

ዘንድ በሌ/ኰሎኔል ሁሴን አሕመድ የሚመራው 506 (ሀ) ንዑስ ግብረ ኃይል የኤርትራ ቆላማና ደጋማ ክልሎች መገናኛና ለከረን ከተማ በር የሆነውን የመሳህሊትን በር ለአብዮታዊ ሠራዊታችንም ሆነ ለኤርትራ ክልል ህዝብ ክፍት አድርጎ በቋሚነት ያስከብር ዘንድ ከኤላበረድ ተነቃንቆ የከረንን ከተማ በማለፍ የመሣህሊትን በር እንዲቆጣጠር ከበላይ አካል ትዕዛዝ ተሰጠው።

መሣህሊት በመባል የሚጠራው የኤርትራ ቆላማና ደጋማ ክልሎች መገናኛ በር ከከረን ከተማ የሚርቀው 30 ኪሎ ሜትር ሲሆን ጠቅላላውን፣ የመሣህሊትን አካባቢ ተፈጥሮና የመሬት ገፅታ የ15ኛን እግረኛ ሻለቃ በናቅፋ መከበብ አስመልክቼ ለአንባቢ በዝርዝር ያስረዳሁ ስለሆነ እዚህ ላይ መድገም አስፈላጊ አይመስለኝም።

ሻዕቢያ ከዚህ በፊት እንደአደረገው የከረንን ከተማ ለቆ ወደ ሣህል አውራጃ ሲሸሽ የሚከተለውን የአብዮታዊ ሠራዊታችንን ንቅናቄ ለማዘግየትና ቢቻለውም ለመግታት ከዚህ ውጊያ በፊት ቀደም ብሎ ባዘጋጀውና ቀደም ሲል በጥስ ብርጌድን ለመመከት በተጠቀመበት ምሽግ ውስጥ ከፊል ኃይሉን በመቀነስ በአዘግይነት ትቶ ሄዶ ኖሮ 506 (ሀ) ንዑስ ግብረ ኃይል ሻዕቢያን አስለቅቆ የመሣህሊትን በር ለወገን መተላለፊያ ክፍት ለማድረግ ያደረገው ጥረት ባለመሣካቱ 508 ግብረ ኃይል ከከረን ከተማ ተነቃንቆ መሣህሊት በር ላይ የመሸገውን የሻዕቢያ ጦር እንዲደመስስ ተደረገ።

508 ግብረ ኃይል መሣህሊት ላይ መልሶ መቋቋም አድርጎ በምዕራፍ ሦስት ዘመቻ ዕቅድ መሠረት ወደ ሣህል አውራጃ በመንቀሳቀስ አፋቤትን እንዲቆጣጠር ሲታዘዝ ከመሣህሊት አፈግፍጎ የተመለሰው 506 (ሀ) ንዑስ ግብረ ኃይል በሌ/ኰሎኔል አሥራት ብሩ በሚታዘዘው 508 ግብረ ኃይል እዝ ስር በማካከል ወደ አፋቤት እንዲሄድ ተወሰነ።

508 ግብረ ኃይል ያለ ችግር የአፋቤትን ከተማ ከተቆጣጠረ በኋላ ለጥቂት ቀናት እረፍት አድርጎ ከአፋቤት ተንቀሳቅሶ የሣህል አውራጃ ከተማ ወደ አለበትና ሻዕቢያ የተፈጠረበትና የተፈጥሮ ምሽጉ ወደ ሆኑት የናቅፋ ተራሮች ጥግ ደረሰ። ይህን ካልኩ በኋላ ሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊታችን በአንደኛውና በሁለተኛው ዘመቻ ምዕራፎችና እንዲሁም በሦስተኛው ምዕራፍ ዘመቻ ከፊል እቅድ መሠረት ማከናወን የነበረበትን የኤርትራን ክፍለ ሃገር ከገንጣዮች ነፃ ለማውጣት ያከናወነውን የመጀመሪያ የትጥቅ ትግል ክፍለ ታሪክ እዚህ ላይ አቁሜ የሚቀጥለውን የትጥቅ ትግል ሁለተኛውን ክፍለ ታሪክ በኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ ሦስት እንደማቀርብ ለአንባቢ ቃል በመግባት ወደ ሌሎች ጉዳዮች ማለትም፤ የትጥቅ ትግሉ ተዛማጅ ታሪኮች አመራለሁ።

ሻዕቢያ እስከ መጨረሻው ሰውና ጥይት ከረን ላይ ለመዋጋት ያቀደውን እቅድ ለውጦ ወይንም የወገንን ጦር የከበባ የውጊያ እቅድ መሰናዶ ተገንዝቦ ከመከበቡ በፊት እንደተለመደው ወደ ሳህል አውራጃ በመፈርጠጥ በናቅፋ ወረዳ ውስጥ ባሉ ተራራማ

የተፈጥሮ ምሽጎቹ ውስጥ ከመግባቱ በፊት፣ አንባቢ እንደሚያስታውሰው በአካለጉዛይ አውራጃ በምስጢር በመደራጀት በኮሎኔል ካሳ ገብረማሪያም የሚመራው ሰባተኛው ግብረ ኃይል ከከረንና ከአፋቤት ቀኝ በሳህል አውራጃና በቀይ ባህር ዳርቻ ድምፁን አጥፍቶና በተቻለ ራሱን ከጠላት ሰውሮ በመጓዝ ሻዕቢያ ከከረን ፈርጥጦ በናቅፋ ምሽጉ ከመግባቱ በፊት ቀድሞ የናቅፋን ምሽጎችን በመቆጣጠር ሻዕቢያ መግደያ መሬት ላይ ከፊትና ከኋላው በወገን ጦር የከበባ ውጊያ ሥልት ለአንዴና ለመጨረሻ ለመደምሰስ የታቀደ የውጊያ እቅድ ነበር።

508 ግብረ ኃይል ከሚያደርገው እንቅስቃሴ የውጊያውን ዓላማ ቀድሞ ወይንም የ507 ግብረ ኃይልን እንቅስቃሴ በአካባቢው በቋሚነት አሰማርቶ ከሚጠቀምባቸው የውጊያ መረጃ ወኪሎቹ መረጃ ደርሶት እንደሆን አይታወቅም በከረንና በአካባቢው እስከ መሳህሊት ያደርግ የነበረውን ውጊያ አቁሞና መላ ሠራዊቱን ሰብስቦ በፍጥነት በመንቀሳቀስ ወደ ተፈጥሮ ምሽጉ ወደ ናቅፋ ሲመለስ የወገን 507 ግብረ ኃይል ናቅፋን ቀድሞ ሳይቆጣጠር ይቀራል። በዚህ ጊዜ ማለቅ የነበረበት የኤርትራ ጦርነት ለሌላ አስር ዓመታት እስከመገንጠሉ ድረስ ይቀጥላል። ይህ እጅግ አሳዛኝና እጅግ አስቆጪ ታሪክ በዘመቻው መምሪያ ጓዶች እንደተነገረኝ ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

507 ግብረ ኃይል ወደ ናቅፋ የተጓዘበት የቀይ ባህር ዳርቻ የአየር ንብረት በጣም ሞቃትማ ከመሆኑ ሌላ መሬቱም አሸዋማ ስለሆነ ሠራዊቱ ፈጥኖ እንዳይንቀሳቀስ የሚገታ በመሆኑ ጉዞው በጣም አድካሚ ነበር።

የ507 ግብረ ኃይል ጦር አመራር ሻዕቢያ በከረን ውጊያ ለአንዴና ለመጨረሻ ይመታል። ይህ ባይሆን ደግሞ ከበባውን ሰብሮ በመውጣት ወደ ናቅፋ ለመምጣት ቀናቶች ያስፈልጉታል ብሎ በማሰብ የመዝናናት ሁኔታ ያለ ከመምሰሉ ሌላ በናቅፋ ተራሮች ምሥራቃዊ ጎን ከተራራዎቹ ግርጌ ጦሩ ከደረሰ በኋላ ጥቂት እረፍት አድርጎ ቀይ ባህርን በመዋኘት ድካሙን እንዲወጣ ታስቦ ጦሩ ትጥቅና መሣሪያውን አስቀምጦ በሚዝናናበት ጊዜ መላው የሻዕቢያ ጦር ደርሶ ያንን ሁሉ ሠራዊት ከነመሪዎቹ እንዳልነበሩ በማድረግ ያለቀለትን ድል ተነጠቅን።

507 ግብረ ኃይል ከሞላ ጎደል ሁለት ክፍለ ጦር ሲሆን የግብረ ኃይሉ አዛዥ ኮሎኔል ካሳ ገብረማሪያም፣ የአንደኛው ክፍለ ጦር አዛዥ ሌ/ኮሎኔል አይተነው በላይ ሲሆን የሁለተኛው ክፍለ ጦር አዛዥ ሌ/ኮሎኔል ሰይፉ ወልዴ ነበሩ። ጦሩም ሆነ መሪዎቹ ለወሬ ነጋሪ እንኳን አልተረፉም።

ለብዙ ጊዜ በብዙ አጋጣሚ ህብረተሰባዊነትን ወይንም ሶሻሊዝምን ለአገራችን የእድገት አቅጣጫችንና ርዕዩተ ዓለማዊ መመሪያችን አድርገን ከመረጥንበት ጊዜ ጀምሮ ሠላምንና ሶሻሊዝምን ወይንም ሶሻሊዝምንና ሠላምን አንዱን ከሌላው ለይተን የተመለከትንበት ጊዜ እንደሌለ መግለጤ በአንባቢ ዘንድ የሚታወስ ይመስለኛል።

ኢትዮጵያ አገራችን ታሪኳን በሙሉ ለሠላም የታደለች አገር ባለመሆኗ ህዝቡ በአጠቃላይ እኛ መለዮ ለባሽ ወይንም የአገር መከላከያ ሠራዊት የሆን ልጆቿ በተለይ ሠላምን የተጠማን ነበርን።

በአካባቢያችን የሚኖሩት ጎረቤቶቻችን በአጠቃላይና በተለይም የዓባይ ወንዝ ተጠቃሚዎች፣ የእስልምና እምነትንና አረባዊነትን አስፋፊዎች ያወጁብንን ጦርነት የግድ ለመከላከል ተገደድን እንጂ ጦርነቱን እኛ አልጀመርነውም።

ከወደቀው አሮጌ ሥርዓት ተረከብነው እንጂ ጦርነቱን አብዮታችን አላመጣውም አብዮታችን ጦርነቱን ለማቆምና በአፍሪካ ቀንድ ሠላምን ለማስፈን የመጣ ፀረ ጦርነት አብዮት ነው።

ኢትዮጵያ አገራችን ታሪኳን በሙሉ ማለት ይቻላል ለሠላም ያልታደለች በመሆኗ ህዝቧ በአጠቃላይ የመከላከያ ሠራዊቷ በተለይ ለረጂም ዘመን ሠላምን የተጠማን ስለሆንን የኢትዮጵያ ህዝብ ማህበራዊ አብዮት አንዱና ግንባር ቀደም ተልዕኮ በኢትዮጵያ ሠላምን ማስፈን ነበር።

የአብዮታችን ዓላማ አገራችንን ኢትዮጵያን ከዓለም ኋላ ቀር ሠልፈኞች ጭራነት ተራ መንጥቆ ማውጣት፣ ድንቁ ርናን፣ መሃይምነትን፣ ድህነትን፣ እርዛትን፣ ርሀብንና በሽታዎችን መዋጋት ነበር።

ሰው በሰው የማይበዘበዝበት፣ ጭቆናና መድሎ የሌለበት፣ ሠላም፣ ፍትህ፣ ማህበራዊ ብልፅግና የሰፈነባት ኢትዮጵያን መገንባትና ተፈጥሮን መቆጣጠር ነበር። ተፈጥሮን መቆጣጠር ስል፣ የአገራችን አድህሮት እንደተረገሙት ሳይሆን ያለፉት መሳፍንት፣ መኳንንትና የመሬት ከበርቴዎች በስግብግብነት፣ ደሀው ገበሬ ባለማወቅ ደኖቿን በመመንጠር የተፈጥሮ ፀጋዋን ገፈው ያራቆቷትን አገራችንን መልሰን አረንጓዴ እናለብሳታለን ማለታችን ነበር።

የአገራችንን ለም አፈር እየጠራረገ ወደ ባዕድ አገር የሚወስዱትን ወንዞና ጅረቶቻችን ተጠቅመን የመስኖ እርሻ በማስፋፋት ተፈጥሮ የሚያመጣቸውን ቀውሶችና ድርቅን እንቋቋማለን ማለታችን ነው።

የአገራችን ገበሬ በእንካሴ፣ በዶማና በሞፈር መቆፈሩን ትቶ በዘመናዊ የግብርና መሣሪያዎች ተገልጋይ እንዲሆን እናደርገዋለን ማለታችን ነው።

የሰብል ፀር የሆኑ አእዋፍና ተባዮችን የሚከላከልበትና ምርታማ ይሆን ዘንድ የአፈር ማዳበሪያ ንጥረ ነገሮችን እናመርታለን ማለታችን ነው።

የኢትዮጵያ ገበሬዎች ተፈጥሮ ያደላቸውን ለም አፈርና ውሃ በአግባቡ ተጠቅመው ምርታማ ይሆኑ ዘንድ ዘመናዊ የግብርና ጥበብ አስተምረን ዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጂ እናቀርብላቸዋለን ማለታችን ነው።

የአገራችንን ገጠሬ ከኩበት ማገዶ ተገልጋይነትና ከጨለማ የጭቃ ጎጆ አውጥተን በዘመናዊ ቤት እየኖረ በኤሌክትሪክ ብርሃን ተገልጋይ እንዲሆን እናደርገዋለን ማለታችን ነው።

አብዛኛው የሃገራችን ሰው ከምንጭ፣ ከኩሬና ከወንዝ እንስሶችን እየተጋራ መጠጣቱን፣ እናቶቻችንና እህቶቻችን ዘላለም እንሥራ መሸከማቸውን አቁመን ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ቤተሰብ ንፅህና የታከመ ውሃ በየቤቱ በቧንቧ እንዲቀርብለት እናደርጋለን ማለታችን ነው።

አንባቢን ላለማሰልቸት እንጂ ብዙ ማለት ይቻላል። ወደ ተነሳሁበት አርእስት ልመለስና በተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ላይ የማያዳግምና አንፀባራቂ የጦር ሜዳ ድል በተቀዳጀንበት ጊዜ ፊቱን አዙሮ ወደ አገሩ በመፈርጠጥ ላይ የነበረውን የሱማሌ መንግሥት ሠራዊት እስከ ሞቃዲሾ ከተማ ድረስ ተከታትለን መበቀል ሲቻል ድንበራችን ላይ ቆመን በድላችን ማግሥት ከሱማሌ መንግሥት ጋር የእርቀ ሠላም ድርድር የተጀመረው በኛ ቀደምትነትና አሳሳቢነት መሆኑ በአንባቢ ዘንድ የሚታወስ ይመስለኛል።

በአገራችን አራቱ ማዕዘናትና በመሀልም ፀረ ሠላምና ፀረ አብዮት ኃይላት ባወጁብን ጦርነት የተወጠርንበትን አጋጣሚ ተጠቅመው፣ ገንጣዮች የኤርትራን ክፍለ ሃገር አብዛኛውን አውራጃዎች ወረው ለመቆጣጠር በመቻላቸው የመገንጠል ዓላማቸውንም በኃይል እንፈፅማለን በማለት ተብተው ስለነበረ ለኛ የሠላም ጥሪ የሰጡን መልስ ጥይት ቢሆንም ሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊታችን በተቀዳጀው ድል ሳንኩራራ «ሻዕቢያ» ሸሽቶ ወደ ተፈጠረበትና የተፈጥሮ ምሽግ ወደ ሆነው የሣህል አውራጃ በመሄድ በናቅፋ ተራሮች ላይ በተንጠለጠለበት ጊዜ ያቀረብንላቸው ጥያቄ እጃችሁን ስጡ ሳይሆን ከተራራው ወርዳችሁ በሠላም ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠን ሁላችንንም በሚበጅ የሠላም መፍትሄ ላይ እንወያይ የሚል ነው።

ሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊታችን ያደረሰባቸው በጣም ከባድ በትር ስለነበር ከቀድሞው እምቢተኝነትና የእብሪት አቋማቸው ሽብርክ በማለት የሰጡን መልስ፣ የኤርትራ ክፍለ ሃገር ህዝብ ነፃነቱን ወይንም ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር አንድነቱን ይመረጥ ዘንድ የብያኔ ድምፅ እንዲሰጥ እድል ይሰጠው የሚል ጥያቄ ቢያቀርቡም ጥያቄያቸው፣ ቁስላቸው እስኪሽርና አገግመው መልሰው ለመቋቋም፣ ለመደራጀትና ጊዜ ለመግዛት እንጂ ሀቀኛ ጥያቄ እንዳልነበር በሂደት ቀጣዩ ጊዜና ታሪክ በገሐድ አስረድተውናል።

በሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊታችን በሦስት ምዕራፎች የተካሄዱት የኤርትራን ክፍለ ሃገር ህዝብ ከገንጣዮች ነፃ የማውጣት ዘመቻዎች ለማኒያ ከመቶው ተከናውነው በናቅፋ ተራሮች ጥግ በቆምን ማግሥት ጀምሮ ከሻዕቢያ መሪዎች ጋር ለሠላም ግኝት እየተደራደርን በምሥራቅና በደቡብ ኢትዮጵያ የጦር ግንባሮች በተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ላይ በሰሜን ኢትዮጵያ የጦር ግንባር ራሳቸውን ጀብሐና ሻዕቢያ ብለው በሚጠሩት አገር ገንጣዮች ላይ ወታደራዊ ድሎችን ላቀዳጁን፣ ለአንደኛውና ለሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊቶቻችን አባላት ብቻ ሳይሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እናት አገርንና አብዮቱን ለማዳን የተደረገው ትግል ተካፋይ ለሆኑት የመላው የመከላከያ ሠራዊታችን አባላት ለሆኑ፣ ለኃይል አዛገሮች፣ ለሠራዊት አዛገሮች፣ ለግብረ ኃይል አዛገሮችና ለኮር አዛገሮች ወዘተና በእነዚህ ተቋማት ውስጥ ከፍተኛ በሆኑ ቁልፍ ቦታዎች ላይ ለሚሰሩ የመምሪያ መኮንኖችና በመከላከያ ሠራዊታችን መዋቅራዊ ተዋረድ ወይም ጠገግ መሠረት በእያንዳንዱ የጦር ክፍል ውስጥ በጓድ ደረጃ ካሉ ተርታ ወታደሮች ጀምሮ እስከ ጀነራል መኮንኖች ድረስ በአደረጉት አስተዋፅኦ መሠረት እንደ ሞያቸውና እንደ ውሎአቸው እጅግ በርካታ የሆነ የማዕረግ እድገት ሰጠን።

ከተርታ ወታደሮች ጀምሮ እስከ ኰሎኔል መኮንኖች ድረስ የማዕረግ እድገት ያገኙት የመከላከያ ሠራዊታችን አባላትን ሁሉ በስምም በአሐዝም ለመግለፅ ስለሚያዳግት ትቼ በጠቅላላ የተሿሚ ጀነራሎችን ብቻ ብገልፅ በቅድሚያና በአንደኛ ደረጃ የተሾሙት ቁጥር ከሃያ በላይ ነበር። ከእነዚህ ተሿሚ ጀነራል መኰንኖች ውስጥ፤

1ኛ ሌ/ኰሎኔል ተስፋዬ ገብረኪዳን የደርግ የመከላከያ ኮሚቴ ሊቀመንበርና በብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ የኔ ረዳት በሌ/ጀነራልነት ማዕረግ የአገር መከላከያ ሚኒስትር፣

2ኛ ኰሎኔል ኃይለ ጊዮርጊስ ኃብተ ማርያም ቀድሞም በነበሩበት የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹምነት የሜ/ጀነራልነት ማዕረግ፣

3ኛ ኰሎኔል ከፈለኝ ይብዛ ቀድሞም በነበሩበት በምድር ጦር ሠራዊት አዛዥነት የብ/ጀነራልነት ማዕረግ፣

4ኛ ኰሎኔል ፋንታ በላይ ቀድሞም በነበረበት የአየር ኃይል ሠራዊት አዛዥነት የብ/ጀነራልነት ማዕረግ፣

5ኛ ካፕቴን ተስፋዬ ብርሃኑ ቀድሞም በነበረበት የባሕር ኃይል ሠራዊት አዛዥነት የኰሞዶር ማዕረግ ተሰጥቷቸዋል።

ይህ ከላይ እስከ ታች የመከላከያ ሠራዊታችንን ጠቅላላ የአመራር አካላትና ምንዝሩን ወታደር ያካተተ በርካታ የማዕረግ እድገት የተሰጠው ለአገር አንድነትና ለአብዮቱ ደህንነት ሠራዊታችን በአደረገው የፍልሚያ ውጤት ላይ ተመስርተን ሠራዊታችንን ከማስደሰት ሌላ ከአብዮቱ ዋዜማ ጀምሮ እስከ አብዮቱ ማግሥት በየምክንያቱ ከሠራዊቱ የተገለሉትን፣ በፍልሚያው ሂደት የተሰውቱንና የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን መሪዎች የመተካትና የጦር ኃይላችንን መልሶ የማቋቋም ዓላማ ነበረው።

1966 ዓ.ም የካቲት ወር ጀምሮ በአብዮቱ ዋዜማ፣ አጥቢያና ማግሥት ህዝብ በድለዋል፣ ያለ አግባብ በልፅገዋል ወዘተ ተብለው የተከሰሱ የቀዳማዊ ኃይ ለሥላሴ መንግሥት ባለሥልጣኖች ለፍርድ ይቀርቡ ዘንድ በጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኰንን ትዕዛዝ በወታደር እየታደኑ በሚታሰሩበት ጊዜ የአገሪቱ መከላከያ ሠራዊትም በተመሳሳይ

በአገራችን ደቡባዊና ምስራቅ ክልሎች በተስፋፊው የሱማሌ መንግስት ወራሪ ሰራዊትና በሰሜን ገንጣዮች ላይ በአስመዘገብናቸው የጦር ሜዳ ድሎች ግኝት ቆራጥና ወሳኝ አመራር ለሰጡና በነፍስ ወከፍ ጀብዱ ለፈፀሙ አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊታችን አባለት እንደየ ተግባራቸው የተለያዩ ደረጃ ያላቸውን የጦር ሜዳ ጀግኖች ሜዳሊያ ሸልመናል።

ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድነትና ለአብዮቱ ደህንነት ሲፋለሙ ለወደቁ አብዮታዊ ጀግኖቻችን የሚገባቸውን ሜዳሊያ እንደሁኔታው ለአባቶቻቸውና ለልጆቻቸው ሸልመናል።



ይህች የሦስት ዓመት ዕድሜ ያላት ህፃን የጀግና አባቷን ሜዳሊያ ከተቀበለች በኋላ በእናቷ ፈቃድ ህፃናት አምባ ገብታለች።

ሁኔታ ሠራዊቱን በድለዋል፣ በሙስና ተበክለዋል፣ ያለአግባብ በልፅገዋል ያላቸውን የጦር ኃይሉን ከፍተኛ መኮንኖች በተለይም ጀነራል መኮንኖችን ከሲቪሉ ባለሥልጣኖች ጋር እየቀላቀለ በማሰር፣ በጡረታ በማሰናበትና ከሥራቸው በማባረር ከመከላከያ ሚኒስቴር ጀምሮ ጠቅላላውን የጦር ኃይሎችን ላዕላይ መዋቅር አመራር አልባ አድርጎት እንደነበር ይታወሳል።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለን ገንጣዮች በሰሜኑ ጦራችን ላይ የሚያካሂዱትን ጥቃት እያስፋፉ በሄዱበት ጊዜ የተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት በአገራችን ምሥራቅና ደቡብ ክልል የሚገኘውን የአገሪቱን አንድ አምስተኛ መሬት አለኝታዬ ነው በማለት ድንበራችንን ጥሶ 700 ኪሎ ሜትር ጠልቆ በመግባት በወረረን ጊዜ ከፍ ያለ የሠራዊት አመራር ችግር ከመፍጠሩ ሌላ በሠራዊታችን ውስጥ በማድፈጥ ራሳቸውን የከለሉ አንዳንድ አብዮቱ የመጣባቸው የልጅ እንዳልካቸው ምልምል መኮንኖችና የኮንጎን ዘመቻ አበል ተከልክለናል የሚሉ በርካታ የጦሩና የፖሊስ ሠራዊት አባሎች አብዮታዊ ሠራዊታችንን በመከፋፈል ፀረ አብዮት ድርጊቶችን ከመፈፀም ባሻገር ሠራዊቱን በአብዮታዊው መንግሥት ላይ ሊያነሳሱትና እርስ በርሱም ሊያዋጉት በሚሞክሩበት ጊዜ ራሱን የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ «ኢ.ሕ.አ.ፓ» ብሎ የሚጠራው የስም ካባ ለብሶ አብዮቱን የሚወጋ ፀረ አብዮት ድርጅት በገሐድ ማንነቱን ገልፆ በአገሪቱ ገጠርና ከተሞች ነጭ ሽብሩን ማካሄድ ጀመረ።

ኢሐአፓን፣ የሰሜን ገንጣዮችን፣ ተስፋ ለዘውድ ፊውዳሎችንና ጠባብ ብሄርተኞች የአብዮታዊ ሠራዊታችንን አንድነትና ደህንነት ሸርሽረው የአብዮታችንን ድሎች እንዳይነጥቁንና በወራሪው የሱማሌ ሠራዊት ፊት ለሽንፈት እንዳይዳርጉን ለመከላከል የውጊያ አመራሩን በብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ ማዕከል ማማከል አስፈላጊ በመሆኑ በምሥራቅና በደቡብ የጦር ግንባሮች ከተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ጋርና ኤርትራን ከገንጣዮች ነፃ ለማውጣት ውጊያ ያሰለፍናቸውን አንደኛውንና የሁለተኛውን አብዮታዊ ሠራዊቶች በቀጥተኛ እዝ ሥር አድርገን መምራታችን ይታወቃል።

የኤርትራን ክፍለ ሃገር ህዝብ ከገንጣዮች ነፃ ለማውጣት በሰባት ግብረ ኃይሎች፣ በሦስት ምዕራፍ ዘመቻ የተመራው ውጊያ በሳሕል አውራጃ በናቅፋ ተራሮች ጥግ ከደረሰ በኋላ ለጠቅላላው እናት አገርንና አብዮትን ለማዳን መላው አብዮታዊ የጦር ኃይሎቻችን ያስመዘገቡትን አኩሪ የጦር ሜዳ ድሎች ወሮታ አስፈላጊውን የማዕረግ እድገት መስጠታችንን ከዚህ ቀደም ብዬ ለአንባቢ ገልጫለሁ።

በፀረ ኢትዮጵያ ግንባር የተሰባሰቡ ኃይሎች ጦርነት ባወጁብን በ1969 ዓ.ም አብዮታችን አሮጌዎቹን የፖለቲካ ሥርዓት አካላት በማፈራረስ ላይ ነበር እንጂ አዲሶቹን አልገነባም። ህዝቡን የማንቃትና በየዘርፉ የማደራጀቱን ሥራ ጀመርን እንጂ

በአግባቡ አልተጠናቀቀም። አብዮቱን መምራት የነበረበት አብዮታዊ የፖለቲካ ፓርቲ ወይንም ድርጅት ብሎ ነገር አልነበረም።

ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት ሱማሌዎች ወረራውን ሲጀምሩ የአገራችን ከፍተኛ የመከላከያ አመራር ተቋማት ላዕላይ መዋቅሮች በከፍተኛ መሪ መኮንኖች እጥረት ምክንያት ባዶ ስለነበሩ የአገሪቱ መስተዳድር ማለትም የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተቋቋመበትን አገር አቀፍ የመንግሥት ተግባር ማከናወኑን ትቶ ወደ አንድ የመከላከያ ሚኒስቴርነት ተለውጦ ወይንም የመከላከያ ሚኒስቴር ማዕድ ቤት ሆኖ ነበር ለማለት ይቻላል። አብዛኛው የአስተዳደርና ሎጀስቲክ ጠቀስ ሥራዎች የሚሠሩት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ነበር።

ለጦርነቱ የጥይትና ፈንጂዎች፣ የጦር መሣሪያዎች ግዥና አቅርቦት በጠቅላላ፣ ሥንቃስንቅ፣ ነዳጅና ቅባት፣ የመድኃኒት አቅርቦትና የሕክምና አገልግሎት፣ ትጥቅና አልባሳት፣ ጠቅላላየ የብስ፣ የአየርና የባሕር መጓጓዣዎች ጉዳይ ከምድር ጦር ሠራዊት መምሪያ ጋር የሚያከናውነው እኔ የምሰበስበው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ነበር።

በሌላ አነጋገር ከ1968 እስከ 1972 ዓ.ም ድረስ በአብዮቱ አፍላ ዘመን የመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት የአብዮታዊ መንግሥት ሥራና ጠቅላላ ትኩረት በጦርነቱ ላይ ብቻ ነበር።

በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የፖለቲካ ፕሮግራማችን ላይ የሠፈሩት የአብዮቱ ዓላማዎችና መርሃ ግብሮች በጠቅላላ ማለትም፣ የፖለቲካ፣ የርዕዮተ ዓለምና የድርጅት ሥራዎች በከፊል፣ የአገር ልማትና የግንባታ ሥራዎች በጠቅላላ አንዳቸውም አልተጀመሩም ማለት ይቻላል።

ለህዝብ የተሰጡት ተስፋዎችና የተገቡት ቃሎች አብዛኛዎቹ ተግባራዊ ስለአልሆኑ የመንግሥት ተቋማት በአጠቃላይ፣ እኔ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ የሆንኩት ግለሰብና ጠቅላላው የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት የአገር መከላከያ ሚኒስትርን ከላይ እስከ ታች መልሰን በማቋቋም ራሱን ማስቻል ነበረብን።

ሶስቱን የኃይሎች አመራር አካሎች፣ የምሥራቁንና የሰሜኑን የሠራዊት አመራር አካሎችና ከኤርትራ ክፍለ ሃገር በመለስ የሰሜኑን፣ የሰሜን ምዕራቡን፣ የሰሜን ምሥራቁን፣ የደቡቡንና የምዕራቡን ክልል ኮሮች በየክልላቸው መከናወን ላለበት ወታደራዊ ተግባርና በተለይም መከናወን ያለባቸውን ቀሪ ዘመቻዎች መምራት በሚያስችላቸው ሁኔታ በተሟላ የአመራር አካላት አደራጅተን እንዲሰሩ አስፈላጊውን ትዕዛዝና መመሪያ በመስጠት ከአምስት ዓመት በኂላ ፊታችንን ወደ አዲሱ የፖለቲካ ሥርዓትና ወደ አገር ልማትና ግንባታው በማዞር የብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ ማዕከሉን ከአሥመራ ወደ አዲስ አበባ መለስን ይህንን ያደረግነው በ1972

ዓ.ም መገባደጃ በሐምሌ ወር ውስጥ ሲሆን ከተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጋር ያደረግነውን ፍልሚያ በሚያኮራና በማያዳግም ሁኔታ ስለ አጠናቀቅንና በሰሜን ኢትዮጵያ የኤርትራን ክፍለ ሃገር ከገንጣዮች ነፃ የማውጣቱ ዘመቻም በእኛና በሱዳን መንግሥት ግዛት ጠረፍ ላይ በሚገኘው በሳሕል አውራጃ የናቅፋ ወረዳ በስተቀር የሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊታችን የዘመቻ እቅዶች በሙሉ ተግባራዊ በመሆናቸው አብዮታዊ የጦር ኃይላችን በትግሉ የተቀዳጀውን ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ የሚያበስር በአገሪቱ ርዕሰ ከተማ በአዲስ አበባ አብዮት አደባባይ መስከረም 2 ቀን 1973 ዓ.ም በአፍሪካ ምድር ታይቶ የማይታወቅ ወታደራዊ ሠልፍ ተደረገ።

የኢትዮጵያ ህዝብ የድል ብሥራት የሆነው ታላቅ ወታደራዊ ሠልፍ ላይ የትግል አጋሮቻችን የሆኑ አያሌ ሕብረተሰባዊ አገሮችና እንዲሁም ሌሎች የወዳጅ አገሮች ልዑካን፣ አያሌ የተለያዩ አገሮች ጋዜጠኞች ወይንም ዜና አጠናቃሪዎች ስለተጋበዙ ተገኝተዋል።

የአገራችን የሲቪልና ወታደራዊ ባለሥልጣኖች፣ የኢትዮጵያ ህዝባዊ ድርጅቶች አመራር አካሎች፣ የድሉ ባለቤትና የትግሉ ተዋናይ የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ የአብዮት አደባባያችንን እጅግ አጣበውት ነበር።

የ1969 ዓ.ም አብዮታችንን ከቅልበሳ አገራችንን ከወረራ ለማዳን የዘመተው ህዝባዊ ሠራዊታችን ሰኔ 19 ቀን በአብዮት አደባባያችን ያሳየው ዓለምን ያስደነቀ ወታደራዊ ሠልፍ፣ የእግረኛ ሠራዊት በነፍስ ወከፍ ትጥቅ ሲሆን፣ የድልብ ሥራ ትሠልፉ የሠራዊትና የዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች ማለትም መትረየስ የጠመዱ ባለ ጐማ ተሽከርካሪዎች፣ የተለያዩ መሣሪያዎችን የጠመዱ የተለያዩ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች፣ የተለያዩ መድፎች፣ ሮኬት ወንጫፊ መሣሪያዎች፣ ታንኮች፣ ሚሳይል ወንጫፊ አየር መቃወሚያ መሣሪያዎች፣ ተዋጊ ሄሊኮፕተሮችና የተዋጊ ሚግ የጦር አውሮፕላኖች ወዘተ ሠልፍ ነበር።

እንዲህ ያለ ወታደራዊ ሠልፍ በአፍሪካ ምድር የታየው ከኛ በኋላ እንዲሁ ግብፆች ፕሬዝዳንት አንዋር ሳዳት በመራው ሁለተኛው ውጊያ በእሥራኤሎች ላይ የተቀዳጁትን ወታደራዊ ድል ለማብሰርና በታላቋ ሶቪየት ህብረት መንግሥት እርዳታ የገነቡትን የጦር ኃይል ያሳዩበትና በአጋጣሚው ግብፃዊ የእስልምና ወንድማማቾች ወይንም የእስልምና እምነት አክራሪዎች ፕሬዝዳንት አንዋር ሳዳትን የገደሉበት ወታደራዊ ሠልፍ ብቻ ነው።

የአብዮታዊ የጦር ኃይላችንን የጦር ሜዳ ድሎች አብሳሪ በሆነው ታላቅ ሠልፍ ላይ የበዓሉ የክብር እንግዳችን የነበሩት፣ ከተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጋር ስንዋጋ ሠራዊታቸውን ከአብዮታዊ ሠራዊታችን ጎን ያሠለፉት የኩባው አብዮታዊ መሪ ውድ ወዳጃችን ጓድ ፊደል ካስትሮ ሩዝ ነበሩ።

የተጋበዙት የዓለም ጋዜጠኞች ለሚወክሉት የየአገራቸው ህዝብ በቴሌቪዥን በስፋት አሰራጭተውት ስለነበረ ሠልፉን የተመለከቱት ወዳጅ አገሮች ሠልፉን በማድነቅ እንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክት ልከውልናል።

ሠልፉን የተመለከቱ ሁሉ፣ ጠላትም ወዳጅም ከእንግዲህ ኢትዮጵያ አትደፈርም፣ አብዮቷም የማይቀለበስ አይበገሬ አገር ነች ብለው ነበር።

የእኛም ያንን የመሰለ ወታደራዊ ሠልፍ የማሳየት ዓላማ ድሎቻችንን ለማብሠር ብቻ ሳይሆን የአዲሲቱን የአብዮታዊት ኢትዮጵያን የመከላከያ ኃይል ለማሳየት ስለነበር ጥረታችን የተፈለገውን ውጤት አስገኝቶ ነበር።

ይህ ታላቅ ወታደራዊ ሠልፍ የታየበት እለት የኢትዮጵያ ህዝብ በአብዮቱ፣ በአብዮታዊው መንግሥቱና በአብዮታዊው የመከላከያ ኃይሉ በመኩራትና በመመካት እጅግ የተደሰተበት ቀን ነበር።



አብዮታዊው መከላከያ ሠራዊታችን በትግሉ ያስገኛቸው የጦር ሜዳ ድሎች ለማብሰር ከታየው ወታደራዊ ሰልፍ ዘመናዊዎቹን የጦር መሳሪያዎች የሚያሳየው ክፍል በከፊል።



ከተሰለፉት ዘመናዊ የአየር መቃወሚያ በከፊል፡፡

ክፍል ሃያ ሁለት

ምዕራፍ አርባ አራት

አብዮታዊ የጦር ኃይሎችና የሲቪል መከላከያ ድርጅት ከአገር መከላከያ ኢንዱስትሪዎች ጋር ለማቋቋም የታቀደ እቅድ።

አገራችን ኢትዮጵያ ዳግም በቅኝ ግዛት ጥመኞችና በተስፋፊ ወራሪዎች እንዳትደፈር፣ የአካባቢው ታሪካዊ ጠላቶቻችን ኤርትራን ከኢትዮጵያ በመገንጠል አረባዊነትንና የእስልምና እምነትን በማስፋፋት ኢትዮጵያዊያንን ከፋፍሎ በማዳከም ለዘላለም ያልተቀናቃኝ የለም አፈርና የንፁህ ውሃ ተጠቃሚ ለመሆን ብለው በኤርትራ ያወጁብን ጦርነት ለኢትዮጵያ ህዝብ አብዮት ቅልበሳም ዓይነተኛ መሣሪያ ይሆን ዘንድ ከሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ጋር የፈጠሩት ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ አብዮት የቅንጅት ጦርነት በብቃትና በፅናት ተከላክለን በድል ለመወጣት የሚያስችለን ዘመናዊና አብዮታዊ የጦር ኃይሎችና የሲቪል መከላከያ ድርጅት ከአገር መከላከያ ኢንዱስትሪዎች ጋር ለማቋቋም ታቀደ።

ታሪካችንን በሙሉ ማለት ይቻላል ሠላም ለማጣታችንና ለኋላ ቀርነታችን ዋና ምክንያቶች በየጊዜው በፈረቃ በጠላቶቻችን የተደረጉብን ወረራዎችና ጣልቃ ገብነቶች ናቸው። እነዚህ ጥቃቶችና ጣልቃ ገብነቶች ዛሬም ቆመዋል ወይንም አብቅተዋል ለማለት አይቻልም።

ይህንን ለማመን ወይንም ለመገንዘብ ብዙ ሳንመራመር በቅርቡ የተደረገው የተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወረራና ጎረቤቶቻችን መላው የአረብ መንግሥታት ማለት ይቻላል ኤርትራ የሚባለውን ክፍለ ሃገራችንን ለማስገንጠል ከሰላሣ ዓመታት በላይ ያካሄዱብን የህብረት ጦርነት በቂ ማስረጃዎች ናቸው።

የኢትዮጵያ ህዝብ መዘንጋት የሌለበት የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች ተመልሰው ባይመጡ እንኳ የለም አፈራችንና የጣፋጭ ውሃችን ተጠቃሚዎች የሆኑት የአፍሪካ ቀንድና የአባይ ግርጌ አገሮች ምንጊዜም የማይተኙልን መሆናቸውን ነው።

እንደ ከዚህ በፊቱ ምንም ዓይነት የውጊያ ዝግጅት ሳናደርግ ተቀምጠን ጥቃት በተሠነዘረብን ጊዜ ብቻ ሥርገኛ መጣ እንዲሉ ሳይሆን ናፖሊዮን ቦናፖርት፣ ሠላምን ብትፈልግ ለጦርነት ተዘጋጅ እንደ አለው ኢትዮጵያዊያን ሠላምና ደህንነታችንን ከፈለግን ምንግዜም ለጦርነት መዘጋጀት አለብን።

የምሥራቁንና የደቡቡን የአገራችንን ክፍሎች የተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት በወረረበት ጊዜ ለኢትዮጵያ ህዝብ የደረሰብንን ጥቃት ከማስረዳትና አገርና አብዮታችንን ለማዳን የእናት አገር ጥሪ ከማድረግ ጀምሮ የታጠቅን የጦር ማሠልጠኛ

ሠፈር ለማስገንባት፣ ዘማቹን ሠራዊት በታጠቅ የጦር ሠፈር ለማስገባት፣ ዘማቹ ሠራዊት ከከተተ በኋላ የሠራዊቱን ደህንነትና ምቾት፣ የሥልጠናውን ሂደት በየቀኑ ከመከታተል ጀምሮ ለጦር መሣሪያ ግዥ ዓለምን በመዞርና ህዝባዊ ሠራዊቱን ለውጊያ ካሠማራንም በኋላ ውጊያውን በመምራት ለአሥር ወራት ያህል የሚኒስትሮች ምክር ቤትን አመራርና ጠቅላላውን የመንግሥት ሥራ ለተቀዳሚ ሚኒስትራችን ለጓድ ኃይሉ ይመኑ በመስጠት የኔ ሥራ የመከላከያው ጉዳይ ብቻ ሆኖ ነበር ለማለት ይቻላል።

በወራሪው የሱማሌ መንግሥት የጦር ኃይል ላይ የማያዳግምድል ተቀዳጅተን ከአገራችን ባስወጣን ማግሥት ነው ጠቅላላ ትኩረታችንን ወደ ሰሜን ግንባር ያዞርነው።

የብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያችንን ማዕከል ከአዲስ አበባ ወደ ትግራይ ክፍለ ሃገር ርዕሰ ከተማ መቀሌ አዛውረን፣ ሁለተኛውን ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት በግብር ኃይሎች ስናደራጅ፣ ገንጣዮችን መንጥረን ኤርትራን ነፃ ለማውጣት የሚያስችለንን በአራት ምዕራፎች የተከፈለ የዘመቻ እቅድ አቅደን ሠራዊቱን ከትግራይና ከጐንደር ክፍለ ሃገራት ወደ ኤርትራ ምድር ከአስገባንበት ከሐምሌ 1970 ዓ.ም ጀምሮ የሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት የማጥቃት ዘመቻ ሳህል አውራጃ ናቅፋ ተራሮች ጥግ እስከ ደረሰበት ሕዳር 1971 ዓ.ም ድረስ አምስት ወራቶች ስለወሰደብን ከአንድ ዓመት በላይ ከተሰጠኝ አገር የመምራት ተግባሬ ተለይቼ ነበር ማለት ይቻላል።

እንደሚታወቀው የመንግሥታችንን ባለሥልጣኖች ከፍተኛ ትኩረትና የቀን ተቀን ጥረት የሚጠይቁ ሥራዎች የአገር መከላከያው ጉዳይ ብቻ አልነበሩም።

በወሎና በትግራይ የተከሰተውና በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ወገኖቻችንን የፈጀው ረሀብ መፍትሄ ሳያገኝ ድርቁ ወደ ሌሎች ክልሎች እየተዛመተ ነበር።

ረሃብተኛውና የመንግሥት ተረጂ ወይንም ተመጋቢው በድርቅ የተጐዳው ህዝብ ብቻ ሳይሆን የደቡብ፣ የምሥራቁ፣ የሰሜኑና የሰሜን ምዕራቡ ወዘተ ጦርነት ኑሮውን ያናጋውና ከመኖሪያ ክልሉ የተፈናቀለው ህዝብ ቁጥር ብዙ ነበር።

በዚህ ሁኔታ እያለን ነው በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ አውጥተን ወደ ግማሽ ሚሊዮን የሚሆን የመከላከያ ሠራዊት ከማስተዳደር ባሻገር በባዕዳን ወራሪዎችና በአገር ገንጣዮች የታወጀብንን ጦርት የተከላከልነው።

በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የጦር ሜዳ ቁስለኞችን አሳክመን ከማዳን ሌላ በፅኑ የተጐዱትን ወይንም አካላተ ጐዶሎ የሆኑትን ላልተወሰነ ጊዜ እየተንከባከብን፣

በጦርነቱና በተፈጥሮ አደጋዎች ወላጆቻቸውን ያጡ የአገሪቱን ህፃናት ከያሉበት ሰብስበን ማሳደግ ሌላው ግዴታችን ነበር።

እነኝህ ከዚህ በላይ በጥቂቱ የጠቃቀስኳቸው ችግሮች በጦርነቱና ተፈጥሮ ባስከተለው ቀውስ የተፈጠሩት ብቻ ሲሆኑ፣ በአንድ አገር የአንድ መንግሥት ተግባርና ኃላፊነት የሆኑ የህዝብ አስተዳደር፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ዓይነት፣ መጠንና የሚጠይቁትን ትኩረት አንባቢ ለመገመት የሚሳነው አይመስለኝም።

እነኝህ የአገሪቱ መስተዳደር ወይንም የሚኒስትሮች ምክርቤት መክሮባቸው የጋራ ውሳኔ ሲገኝ ወደ ተግባር የምንተረጉማቸው ሥራዎች በጦርነት ውስጥ ሆነን ስለሆነ ሁሉም የኔን አመራርና ተሳትፎ የሚጠይቁ ናቸው።

በሰሜኑ የግብረ ኃይሎች ዘመቻ ሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት መላውን የኤርትራ ምድር ከገንጣዮች ነፃ አውጥቶ ዘመቻው ናቅፋ ከደረሰ በኋላ ከገንጣዮች ጋር ያደረግነውን የሠላም ድርድርና የወታደራዊውን ዘመቻው ጤት ለማስረዳትና ከዘመቻው ጋር ተዛማጅ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት የአገር መከላከያ፣ የብሄራዊ ደህንነትና የፀጥታ ምክር ቤት አባላትን አዲስ አበባ በብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ ማዕከል በሰበሰብኩበት ጊዜ፣ የጤና ጥበቃ፣ የማስታወቂያና የኮንስትራክሽን ሚኒስትሮች፣ የእርዳታ ማስተባበሪያና የውሃ ልማት ኮሚሽኖች ወዘተ በሰሜን ኢትዮጵያ ከሠራዊቱ ጋር ተሠልፈው ስለሚገኙ ዋናውና ጠቅላላው የአገሪቱ አመራርና የዕለት ከዕለት ተግባር ፈፅሞ ወደመቆሙ እያመራ ነበር።

ጓድ ሊቀ መንበር አሁን ለምክር ቤቱ በሰጡት መግለጫ መሠረት እንደተረዳነው በሰሜን የሚካሄደው ወታደራዊ ዘመቻ ከስምንቱ የኤርትራ አውራጃዎች ሰባቱን ነፃ አውጥቶ ሠራዊቱ የሚገኘው በሣህል አውራጃ ብቻ በናቅፋ ተራሮች ጥግ ስለሆነ ቀሪውን ሥራ የሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት ዕዝና ከዚያም ቢያልፍ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ መምሪያና የአገር መከላከያ ሚኒስቴር መልሰው በመረከብ በመሠረቱ የእነሱ የሆነውን ሥራ በመውሰድ ውጊያውን እንዲመሩ ሆኖ ሊቀመንበራችንና ሚኒስትሮቹ ወደ መደበኛ ሥራቸው እንዲመለሱልን እንጠይቃለን በማለት እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ የሚኒስትሮች ምክር ቤትን በመምራት ላይ የነበረው ጓድ ኃይሉ ይመኑና ሌሎቹም ሚኒስትሮች በህብረት አመለከቱ።

ከአገር መከላከያ ሚኒስትሩ ከጓድ ሌ/ጀነራል ተስፋዬ ገብረ ኪዳን ጀምሮ ሁሉም የኃይል አዛገሮችና በተለይም የኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት አዛዥ የነበሩት ጀነራል መርዕድ ንጉሴ «ያልተጠናቀቀውን ቀሪ ውጊያ ለመምራትና ለማጠናቀቅ ችሎታው አለን።

የዕዙ አዛዥነት ሥልጣን የተሰጠን ሠራዊቱን እንድንመራ ተብሎ ይመስለኛል፡፡ ሊ.ቀ መንበር መንግሥቱ ብሄራዊና አብዮታዊውን የዘመቻ መምሪያ ማዕከል አንቀሳቀሰው፣ በቅድሚያ ትግራይ በኋላም አሥመራ በመውሰድ ዛሬ ለተቀዳጀነው አኩሪ ወታደራዊ ድል ስላበቁን ከፍ ያለ አድናቆቴንና ከፍ ያለ አክብሮቴን እየገለፅኩ ሊ.ቀ መንበራችን ወደ አገራዊ ወይንም ብሄራዊ ወሳኝ አመራራቸው ይመለሱልን ሲሉ ክቡራን ሚኒስትሮች ያቀረቡትን ጥያቄ በበኩሌ እደግፋለሁ» ካሉ በኋላ የተቀሩት የሠራዊትና የኃይል አዛዦች የሰጡትን ድጋፍ የመከላከያ ሚኒስትሩ አጠቃሎ የድጋፍ መግለጫ ከሰጠ በኋላ የብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ ማዕከል ከአሥመራ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለስ ተወሰነ፡፡

የአገር መከላከያ፣ የብሄራዊ ደህንነትና የፀጥታ ምክር ቤቱ በወሰነው መሠረት፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ያልተጠናቀቀውን ቀሪ ውጊያ እንዲመሩ፣ ለመከላከያ ሚኒስቴር፣ ለጦር ኃይሎች ጠቅላይ መምሪያና በተለይም ግንባር ቀደም ኃላፊነት ላለበት ለሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊታችን ዕዝ በማስረከብና የእዙን የአመራር አካላት በሙሉ የሥራ ብቃት ባላቸው መኮንኖች ከአሟላን በኋላ የብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ ማዕከል አመራር ጓዶች በሙሉ ወደ አዲስ አበባ ተመለስን፡፡

ወደ አዲስ አበባ ከተመለስን በኋላ እኔ በተለይ ወደ ሚጠብቀኝ ውዝፍ የመንግሥት ሥራ፣ ወደ አዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት አካል፣ ወደ አገር ልማትና ግንባታው ተግባር ከመሄዴና የብሄራዊና አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ ማዕከል ከመፍረሱ በፊት ከብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ አመራር ማዕከል ጓዶች ጋር ለሥራው አግባብ ያላቸውን ጥቂት ሚኒስትሮች ጨምሬ በምሥራቅና በደቡብ ከሱማሌዎች ጋር፣ በሰሜን ከገንጣዮች ጋር ያደረግናቸውን አውደ ውጊያዎች በዓይነ ህሊናችን ወደ ኋላ መለስ ብለን በመመልከት ሰፋ ያሉ ግምገማዎችን አደረግን፡፡

ከግምገማው ያገኘናቸውን ትምህርቶች፣ የተገነዘብናቸውን የዕቅድና የአፈፃፀም ድክመቶች፣ የተፈፀሙ ብክነቶችና በህይወት የተከፈለውን ከባድ መስዋዕትነት በዝርዝር ገላልጠን ተመለከትን፡፡

እነዚህ በጊዜ እጥረትና በሰለጠነ የሰው ኃይል እጦት፣ በጠላ ትአስገዳጅነትና በልምድ እጦት ምክንያት የደረሱና በመድረስም ላይ ያሉ ጉዳቶች በጊዜው ሳይታረሙና መፍትሄ ሳይፈለግላቸው ለረዥም ጊዜ ቀጥለው፣ ባልተጠናቀቀው የትጥቅ ትግልና በአገሪቱ ላይ ድክመትን፣ በአብዮቱ ላይ ውድቀትን ከማስከተላቸው በፊት የሚታረሙበትን የአገሪቱ ብሄራዊ መከላከያ በአስተማማኝ ሁኔታ ደረጃ በደረጃ የሚገነባበትን እርምጃ ለመውሰድ ተስማማን፡፡

ምዕራፍ አርባ አምስት

በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት መቃረቢያና ዋዜማ የተካሄዱት ሁለቱ የጦር ኃይሎች ንቅናቄዎች ግንባር ቀደም ተዋናይና ብለውም መሪ በመሆን የአገሪቱ መለዮ ለባሾች ሳይመርጧቸው እርስ በርሳቸው ተመራርጠው የተሰባሰቡት የአገሪቱ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች

አብዛኛዎቹ የገጠር መሬት፣ የከተማ ቦታና ቤት ከበርቴዎች፣ ከፊውዳሉ ገዥ መደብ ጋር በጋብቻ፣ በመደብ፣ በፖለቲካ ሥልጣንና በንዋይ ጥቅማ ጥቅሞች ወዘተ የተሳሰሩ ነበሩ። በተለይም ትልልቆቹ ማለትም ጀነራሎቹ የንጉሡ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማደጐዎች፣ የጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸውና የመከላከያ ሚኒስትሩ የሌ/ጀነራል አቢይ አበበ ምልምሎች ነበሩ። በመሆኑም የህዝብ ወገንና የለውጥ አራማጅ በመምሰል ሠራዊቱን አወናብደው አብዮቱን ለማዳፈን መሞከራቸው ይታወሳል።

በወጣት መኰንኖች የተመራው ሦስተኛውና የመጨረሻው የጦር ኃይሎች አብዮታዊ ንቅናቄ ጠንሳሾች ከቀደምቱ ከሁለቱ ንቅናቄዎች ትምህርት በማግኘታቸውና ብዙ በመታዘባቸው ለውጡን መምራት ያለባቸው ከንዋይ ሴሰኝነትና ከሙስና የፀዱ፣ ከሠፊው ህዝብ አብራክ የወጡ፣ የሕዝብ ወገን ከመሆን ባሻገር የለውጥ አቀንቃኝ የሆኑ ተራማጅና ማዕረጋቸው፣ ከሻለቃና ከዚያ በታች የሆኑ ወጣት መኰንኖች እንዲመሩ መደረጉ ይታወቃል።

የወጣት መኰንኖች አብዮታዊ አመራር «ደርግ» ከመቋቋሙ በፊት በሁለተኛው የጦር ኃይሎች ንቅናቄ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኰንን የሥልጣን ተቀናቃኞቻቸው የሆኑትን የቀድሞ የአገሪቱን ባለሥልጣኖች ከተወሰኑ ከፍተኛ ጀነራል መኰንኖች ጋር ከሥልጣናቸው በማውረድ በአሠሯቸው ጊዜ የአገሪቱ ሠራዊትም በየክፍሉ ከጥቂት የሌተናል ኰሎኔልነት ማዕረግ ካላቸው በስተቀር ከዚያ በላይ ማለትም ሙሉ ኰሎኔሎችንና መላውን ጀነራል መኰንኖች ከሠራዊቱ አባልነት እንዲገለሉ አድርጓል።

ወራሪው የፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት ሠራዊት ከአገራችን ከወጣ በኋላ ከ1933 ዓ.ም ጀምሮ በመደራጀት ሂደት ላይ የነበረውን ዘመናዊ መከላከያ ሠራዊት በተሻለ ለማደራጀት የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ከሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ጋር የተዋዋለው የመከላከያ ተራድኦ ውል 40,000 አርባ ሺህ ሠራዊት ለማስታጠቅ ስለነበር ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮት ፍንዳታ ድረስ የአገሪቱ ጠቅላላ የጦር መኰንኖች ቁጥር ለአርባ ሺህ ሠራዊት ብቻ አመራር ለመስጠት ተመጥኖ የተወሰነ ሆኖ መቆየቱ ይታወቃል።

ይህም ሆኖ የአርባ ሺህ ሠራዊት ድርጅታዊ ተቋም በሚጠይቀው የመኰንኖች ቁጥር ሠራዊቱ አንድም ጊዜ ተሟልቶ የማያውቅ ሲሆን በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ በደቡብና በምሥራቅ የአገራችን ክልሎች ተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወደ አገራችን እያሠረገ ከሚያስገባቸው ሽብር ፈጣሪዎችና በእነዚህ ክልሎች ውስጥ ከሚነቃነቁ የሱማሌ መንግሥት ምንደኛ ከነበሩ የአገር ተወላጅ ጠባብ ብሄርተኞችና ከሱማሌ መንግሥት መደበኛ ጦር ጋር፣ በሰሜኑ የአገራችን ክልል ራሳቸውን የኤርትራ ክፍለ ሃገር ህዝብ ነፃ አውጭ ነን ከሚሉት ገንጣዮች ጋር ሲደረግ በነበረው የረዥም ጊዜ ውጊያ መኰንኖቻችን እየቆሰሉ በአካል ጉዳትና በመሰዋት ከሠራዊቱ የሚለዩት ቁጥር ከፍተኛ ነበር።

በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ላይ በነበርንበት ጊዜ ነበር በ1969 ዓ.ም በተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት በመወረራችን ራሳችንን ለመከላከል 300,000 ሦስት መቶ ሺህ ህዝባዊ ሠራዊት በእናት አገር ጥሪ ጠርተን ለውጊያ ባደራጀንበት ጊዜ ይህንን ያህል ብዛት ያለው ሠራዊት የሚመሩ መኰንኖችና የበታች ሹማምንት አገሪቱ ስለአልነበራት በሻለቃ ደረጃና ከዚያ በታች እስከ ጓድ ደረጃ የተቋቋሙትን የጦር ክፍሎች በበታች ሹማምንት እንዲመሩ ማድረጋችን በኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ አንድ ተገልጿል።

በድህረ አብዮት ዘውዱ በተገረሰሰ ማግሥት ለእነሱ የተሻለ ጊዜ የተፈጠረላቸው መስሎ የታያቸው ይመስላል የኤርትራ ገንጣዮች የአሥመራን ከተማ በከበቡ ጊዜ በተለይም በ1969 ዓ.ም የሰሜኑን ጦር ለማጠናከር በላክናቸው ሁለት ክፍለ ጦር ህዝባዊ ሠራዊቶች ገንጣዮችን ከከተማው ጠርዝ ጥቂት ገፍቶ ለማራቅና የወገንን ጦር የመከላከያ ይዞታ ለማስፋፋት ተብሎ ከአሥራ አምስት ዓመታት በላይ የውጊያ ልምድ ካለው፣ በሚያውቀው ምድር፣ በሚያው ቀው የአየር ንብረትና በተወለደበት አገር ከሚዋጋ የሰለጠነ ጉሪላ ጋር ውጊያ በጀመሩበት የመጀመሪያ ጊዜ ለአገሩ ባዕድ፣ ለአየር ንብረቱ ፍፁም እንግዳ ከመሆናቸው ሌላ ከዚያ በፊት ምንም ዓይነት የውጊያ ልምድ ስለአልነበራቸው ብቻ ሳይሆን በመሪዎች ታላቅ እጥረት ምክንያት በእያንዳንዱ የውጊያ ግንባር ወይንም የውጊያ ቀጠና የሚቆስሉትና የሚሰውት ቁጥር እጅግ ብዙ ነበር።

ህዝባዊ ሠራዊታችን ከገንጣዮች ጋር በአደረጋቸው የመጀመሪያቹ የአሥመራ ከተማ ዙሪያ ውጊያዎች ጠላት ለአያሌ ወራቶች በጥልቀትና በስፋት ቆፍሮ በብረት ከገነባቸው ምሽጐች ውስጥ ለማስወጣት በተደረገው ትግል የደረሰብን ጉዳት በወጣቶች የተገነባው ህዝባዊ ሠራዊታችንን ህይወት በከፍተኛ መጠን በየቀኑ ከመቅጨት ባሻገር በእጅጉ የጎዳን ጠላት መሣሪያቻችንን መታጠቁ ነው።

ከአሥመራ ከተማ ዙሪያ ውጊያ በፊት በ1967 እና በ1968 ዓ.ም ከገንጣዮች ጋር በተሰነይ፣ በአቆርዳት፣ በናቅፋ፣ በከረንና በመሳህሊት በተደረጉ ውጊያዎች በቅድመ

አብዮት ሠራዊታችን ይገለገልባቸው ከነበሩ የአሜሪካ ሥሪት ከሆኑ መሣሪያዎቻችን፣ ብረት ለበስ ተዋጊ ተሽከርካሪዎችን፣ የተለያዩ አዳፍኔዎችን፣ የተለያዩ ፀረ ታንክ መሣሪያዎችን ወዘተ ሠራዊታችንን እየገፋፉ ታጥቀዋል፡፡

በ1969 ዓ.ም አብዮታዊ ሠራዊታችን የታጠቃቸውን አዲስና ዘመናዊ የዋርሶ ሥሪት መሣሪያዎቻችንን ለገንጣዮች ማስታጠቅ የተጀመረው በአሥመራ ከተማ ዙሪያና እንዲሁም በምፅዋ ውጊያዎች ነው፡፡

ገንጣዮች የኤትራን ክፍለ ሃገር ምዕራባዊናም ሥራቃዊ ቆላማ ክልሎች እስከ ከረን ከተማ ድረስ ከተቆጣጠሩ በኋላ የኤርትራን ክፍለ ሃገር ከመሃል ኢትዩጵያ የሚያገናኙትን የየብስ ተሽከርካሪ መንገዶች ትግራይ ክፍለ ሃገር ድንበር ላይ ከዘጉ በኋላ የልብልብ አግኝተው የአሥመራን ከተማ ከመፅዋ ከተማና ከወደቡ ጋር የሚያገናኘውን የየብስ ተሽከርካሪዎች መንገድ ከሁለት ወገን ማለትም በአሥመራ ከተማና በምፅዋ ከተማ መሃከል ባሉ ኰረብታዎችና ከፍተኛ መሬቶች ላይ መሽገው በመዝጋት ህዝቡንና አብዮታዊ ሠራዊታችንን ሊያፍኑና ብለውም ኤርትራን ሊገነጥሉ በሞከሩበት ጊዜ አሁንም ለሃገሩም ለውጊያውም እንግዳ በሆነው ህዝባዊ ሠራዊታችን ከመሽጉባቸው ተራሮች ለማስለቀቅና መንገዱን ለመክፈት የተደረገው መራራና እልህ አስጨራሽ ትግል በሦስት ሳምንታት ውጊያ የተሰውት የአብዮታዊ ሠራዊታችን አባላት ቁጥር ከአስር ሺህ በላይ መሆኑን መግለፅ የትግሉን መሪርነትና አብዮታዊውን መንግሥት የገጠሙትን ችግሮች ለአንባቢ ያስገነዝባል ብዬ እገምታለሁ፡፡

በእናት አገር ጥሪ ከመላው የአገሪቱ ማህበረሰቦችና ብሄረሰቦች መሀከል የተመለመለው ህዝባዊ ሠራዊት ችግሮች፤ የረዥም ጊዜ ወታደራዊ ሥልጠና ያለማግኘትና የውጊያ ልምድ እጦት ብቻ ሳይሆን፣ በማያውቀው ምድርና በማያውቀው የአየር ንብረት ለገንጣዮች ወይንም ለጉሪላ ውጊያ እጅግ አመቺ በሆነ አስቸጋሪ መሬት ላይ መዋጋት ነው፡፡

ለወገን ሠራዊት እጅግ አስቸጋሪ በሆነው መልክአ ምድር ላይ ሠራዊቱን ለውጊያ የሚያጋፍሩት ግንባር ቀደም መስመራዊ መኰንኖች የጠላት ሰለባ እየሆኑ በአካል ጉድለት ከትግሉ ሜዳ የሚወጡትና የሚሰዉት ቁጥር ብዙ ነበር፡፡

በአካል ጉዳትና በሞት ከአብዮታዊ ሠራዊቱ የሚለዩትን መኰንኖች መተካት ከነበረባቸው የመኰንኖች ማሠልጠኛ ተቋማት አንዱ የነበረው የሐረሩ የጦር አካዳሚ ክፍለ ሃገሩ ሐረርጌ በተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት በመወረሩ የማሠልጠን ተግባሩን ካቆመ ቆይቷል፡፡

በሸዋ ክፍለ ሃገር የሚገኘው አንጋፋው የገነት የጦር ትምህርት ቤት በየዓመቱ የማሠልጠን ችሎታው 120 እጩ መኮንኖችን ብቻ ስለሆነና የሠራዊቱን ፍላጎት ጨረሶ የማያረካ በመሆኑ የገጠመንን ችግር ለማቃለል የወሰድነው እርምጃ በሐረርጌ

ክፍለ ሃገር በድሬዳዋ አውራጃ በሁርሶ ወረዳ ለሠራዊት ማሰልጠኛ ያቋቋምነውን ሰፊናዘመናዊ የጦር ማሠልጠኛ የእጩ መኰንኖች ማሠልጠኛ በማድረግ ጠለቅ ያለ የቀለም ትምህርት፣ መልካም ምግባር ካላቸውና በውጊያ ልምድ ከበለፀጉ የበታች ሹማምንት መሀከል እየመለመልን የስድስት ወራት አጭር ሥልጠና በመስጠት በሺህ የሚቆጠሩ መስመራዊ መኰንኖችን በተከታታይ በየስድስት ወራት እያፈራን ለሠራዊቱ የምናድላቸው መኰንኖች መጠንም ሠራዊቱን ባለማርካቱ ያለአንዳች ሥልጠና ወይንም መደበኛ ወታደራዊ ትምህርት በጦር ሜዳ ውሎና ልምድ ብቻ የአመራር ልምድ ያካበቱትን የበታች ሹማምንት የመኰንን የማዕረግ እድገት በመስጠት በበታች ወይንም በመሥመራዊ መኰንኖች በኩል የሠራዊቱን የመሪዎች ችግር ለማቃለል ያለማቋረጥ ጥረት ይደረግ ነበር።

በዚህ ዓይነት እድገት ከሚሊሺያው ሠራዊት መሀል እስከ ኰሎኔል ማዕረግ የደረሱ አባላትን አስታውሳለሁ። በእነዚህ ከዚህ በላይ በጠቃቀስኳቸው ያላቋረጡ ጥረቶች አብዮታዊ ሠራዊታችን በተለይም ሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊታችን የነበረበትን ከፍ ያለ የወጣት መኰንኖች እጥረት በሚያመረቃ ሁኔታ ለማቃለል ቢቻልም፣ በሠራዊት፣ በኰር፣ በክፍለ ጦርና በብርጌድ ደረጃ ላሉ የጦር ክፍሎች አመራር የሚሰጡ የከፍተኛ መኰንኖችም እጥረት የዝቅተኛ መኰንኖች እጥረት ከፈጠረው ችግር የሚያንስ አልነበረም።

ከሠራዊት ደረጃ ጀምሮ በተዋረድ እስከ ብርጌድ ደረጃ በተለያዩ የማዕረግ ደረጃ የሚገኙትን ከፍተኛ መኰንኖች፣ ከአንዱ የማዕረግ ደረጃ ወይንም የሥልጣን እርከን ወደ ከፍተኛው የማዕረግ እድገትና ከፍተኛ ኃላፊነት ለማሳደግ ወይንም ለማሸጋገር የተደነገገ ህግ ያለን ከመሆኑ ሌላ እንደ ማዕረጉና የኃላፊነቱ መጠን እያንዳንዱ መኰንን ሊማራቸውና ሊያውቃቸው የሚገቡና ረዘም ያሉ ጊዜዎችን የሚጠይቁ የተለያዩ ከፍተኛ ወታደራዊ ትምህርቶች ወይንም ሙያዎች አሉ።

ትምህርቶቹን መውሰድ ወይንም መማር ብቻ ሳይሆን አንድ መኰንን በማዕረግ ማደግ የሚችለው ትምህርቱን ሲማር ባገኘው ውጤት ወይንም መለኪያ ነው።

ጠላቶቻችን ያወጁብን ጦርነት በፈጠረው ውጥረት፣ በአቅም ማነስና በጊዜ እጦት ምክንያት ለከፍተኛ መኰንኖቻችን ሊሰጡ የሚገቡትን ተከታታይ ትምህርቶችን በኢትዮጵያዊያን ወታደራዊ መምህራን በአገር ውስጥ ለመስጠት ባለመቻሉ የተወሰኑ ከፍተኛ መኰንኖችን በፈረቃ ወደ ውጭ የወዳጅ አገር ሄደው ይማሩ ዘንድ ልከናቸው ጦርነቱ በፈጠረው ችግር የተላኩበትን ትምህርት በከፊል እንኳን ሳይሸፍኑ ወደ አገራቸው በመጥራት ለውጊያ ማሰማራት ተገደድን።

ወደ ውጭ አገር ልኰ የማስተማሩ አማራጭ ሊሳካ ባለመቻሉ የወዳጅ አገር ወታደራዊ መምህራንን ወደ አገራችን በመጥራት ኢትዮጵያዊያኑን መምህራን ተክተው በአገር ውስጥ እንዲያስተምሩ በማቀድ ካሉን ጠቅላላ ከፍተኛ መኰንኖች

መካከል ጥቂቱን ከጦር ሜዳ እየመለስን በፈረቃ ከፍተኛ የመምሪያ መኰንንነትና የአዛዥ መኰንንነት ትምህርት ቤት (እስታፍ ኮሌጅ) ገብተው ለአንድ ዓመት ያህል ማስተማር ተጀምሮ ዳግም ጦርነቱ በፈጠረው ውጥረት ትምህርቱን ከጀመሩት መኰንኖች ከፊሉ ትምህርታቸውን አቋርጠው ወደ ጦር ሜዳ ለመመለስ በመገዳዳችን በዚህም በኩል የመኮንኖቻችንን ችሎታ ከፍ በማድረግ ሠራዊቱን ጥራት ያለው ሠራዊት ለማድረግ የተደረገው ጥረት ጥቂቱን ብቻ ለመጀመሪያው ዓመት ከማስተማር ባሻገር ዳግም ለመቀጠል ባለመቻሉ ባዕዳኑን መምህራን መኰንኖች ወደ አገራቸው መልሰን በመላክ ትምህርት ቤቱን ዘጋን፡፡

በበታች መኰንኖችም ሆነ በከፍተኛ መኰንኖች በኩል የነበሩብን ችግሮች ለውጊያ አመራር የምንፈልጋቸው መኮንኖች ወይንም የተዋጊ ካድሬዎች እጥረትና የጥራት ችግሮች ብቻ ሳይሆኑ ወታደራዊውን የፖለቲካ አስተዳደር ሥራ የሚሰሩ ወታደራዊ የፖለቲካ ካድሬዎች ከፍ ያለ የእጥረት ችግር ከችግሮቻችን ሁሉ የከበደ'ና የባሰው ነበር፡፡

በታላቁ ህዝባዊ አብዮታችን ፍንዳታ ማግሥት በጦር ኃይሎቻችን ውስጥ የነበሩት ከፍተኛ መኰንኖች የምንላቸው የሻለቅነት ማዕረግ ያላቸውን መኰንኖች ሲሆን የሌታናል ኰሎኔልነት ማዕረግ የነበራቸው መኰንኖች፣ በወታደራዊ ትምህርታቸውና የረዥም ጊዜ የሥራና የአመራር ልምድ ያላቸውን ከብዙሃኑ የማዕረግ አቻዎቻቸውና እንዲሁም ከበላዮቻቸው ጋር ስናስተያያቸው፣ አንፃራዊ ወጣትነት ያላቸውንና አብዮቱ የመጣላቸው እንጂ የመጣባቸው አይደሉም ብለን የገመትናቸውን መርጠን ከአብዮታዊው ሠራዊት ጋር ቀላቀልናቸው፡፡

እነኝህ መኰንኖች ናቸው በማዕረግ የበላይነታቸውና በእድሜ አንጋፋነታቸው የኃይሎች፣ የሠራዊትና የኰር አዛዦች በመሆንና ከፍተኛዎቹን ቁልፍ የሆኑትን ከፍተኛ የአዛዥነትና የመምሪያ መኰንንነት ሥፍራ የያዙት፡፡

በአብዮቱ የመጀመሪያዎቹ አፍላ ዓመታቶች በምሥራቁም በሰሜኑም አውደ ውጊያዎች የሻለቅነት ማዕረግ ያላቸው ብዙሃኑ መኰንኖቻችን በክፍለ ጦርና ከዚያ በታች በነበሩ የጦር ተቋሞች ነው በአዛዥነትና በመምሪያ መኰንንነት አመራር ሲሰጡ የነበሩት፡፡

ከሌተናል ኰሎኔሎቹ ጀምሮ ሻለቆቹና ሻምበሎቹ በሙሉ በጦር ሜዳው አመራር፣ በአስተዳደርና በሎጀስቲክ ወዘተ ሥ ራዎች የተያዙ ከመሆናቸው በላይ በእነዚህ የሥራ ዘርፎች ከፍተኛ የመኰንኖች እጥረት ስለነበረ በጠቅላላው መከላከያ ሠራዊት ውስጥ አብዮታዊ የፖለቲካ አስተዳደሩን የሚመሩልን ወይንም የሚሰሩ መኰንኖችን በተቻለ ፍጥነት ለማፍራት በነበረን እንገብጋቢ ፍላጎት ከአብዮቱ ፍንዳታ ማግሥት ጀምሮ ለፖለቲካ ትምህርት፣ በፖለቲካ ንቃታቸውና ተሳትፎአቸው፣ ለአብዮቱ ባላቸው ልባዊ ወገናዊነትና በመደብ ጀርባቸው፣ በቋንቋ ችሎታቸው መስፈርት

ከሦስቱ የጦር ኃይሎቻችንና ከፖሊስ ሠራዊታችን መሃከል እየመለመልን ወደ ተለያዩ ወዳጅ ሶሻሊስት አገሮች መላክ የቻልነው፤ ከጥቂት የሻምበልነት ማዕረግ ካላቸው መኰንኖች ጋር ብዙሃን የመቶ አልቅና የነበራቸውን ወጣት መኰንኖችና የበታች ሹማምንቶችን እንደነበረ በመላው ሠራዊት ዘንድ ይታወቃል።

እነዚህ ወጣት መኰንኖችና የበታች ሹማምንቶች የተላኩበትን የፖለቲካ ትምህርት ሁሉም በአኩሪና በአስመስጋኝ ሁኔታ አጠናቀው ወደ አገራቸው እንደተመለሱ እንደ ማዕረግ ደረጃቸውና እንደ ቅጥር ቅደም ተከተላቸው በሦስቱም የጦር ኃይሎች ማለትም፣ በምድር ጦር፣ በአየር ኃይልና በባሕር ኃይል ሠራዊት ውስጥ ተደልድለው በመሥራት በዚህ የሥራ ዘርፍ የነበረብንን ከፍተኛ ችግር ማቃለል ቢጀምሩም ቁጥራቸው የአብዮታዊ ሠራዊታችንን ፍላጎት ሊያረካ ቀርቶ በዚህ ረገድ መሰራት ያለበትን አብዛኛውን ሥራ መሸፈን ባለመቻላቸው ወደ ወዳጅ ሶሻሊስት አገሮች እየላክን ማስተማሩ እንደቀጠለ ሆኖ በአገር ውስጥ የራሳችንን የፖለቲካ ትምህርት ቤት አቋቁመን ከሲቢሉ ህብረተሰብ የተለያዩ ክፍሎች መሃከል የተመለመሉትን በማስተማር ህዝቡን ማንቃትና ማደራጀት በጀመርንበት ጊዜ ከጦር ኃይሎቻችንም ውስጥ እንዲሁ አብዮታዊ የፖለቲካ አስተዳደር ሠራተኞችን ብቻ ሳይሆን የአብዮታዊ ሠራዊታችንን ደህንነት የሚጠብቁ ካድሬዎችንም እያስተማርን በተለያዩ የጦር ክፍሎች ውስጥ ከላይ እስከታች በመደልደል ችግሩን በከፊል አቃለልን።

በአሮጌው የፊውዳል ሥርዓት ወይንም በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ከተርታው ወታደር ጀምሮ ወደ ላይ እስከ የመጨረሻው ከፍተኛ መኰንን ድረስ እያንዳንዱ የሠራዊቱ አባል የሆነ ግለሰብ በማዕረግ የሚልቀውን ሁሉ «ጌታዬ» ብሎ መጥራት የሠራዊቱ ደንብና የቆየ አድሐሪ ባህል ስለነበር ይህንን በማስተው ከጀነራል መኰንኖች እስከ ተርታ ወታደሮች ድረስ በሠራዊቱ አባላት መሃከል ያለው ግንኙነት በማዕረግ ልዩነት ላይ የተመሰረተ የሥራ ክፍፍል እንጂ የጌታና የሎሌ ግንኙነት ስላልሆነ የአብዮታዊ ሠራዊታችን አባላት በሙሉ ጓድ እየተባባሉ እንዲጠራሩ አብዮታዊው መንግሥት ህግ ባወጣበት ጊዜ በአብዮቱ ማግሥት በተስፋፊው የሶማሌ መንግሥት የወረራ ሥጋት ጦሩን ለመምራት ያስፈልጉናል አብዮቱ የመጣባቸው ሳይሆኑ የመጣላቸው ናቸው ብለን ከአብዮታዊው ሠራዊት ጋር ቀላቅለን ከፍተኛ ሥልጣን መስጠት ብቻ ሳይሆን በመሾምና በመሸለም ያሳደግናቸው ጀነራል መኰንኖች ሁሉም ሳይሆኑ ጥቂቶቹ «ጓድ ጀነራል» ብለው ወታደሮች ሲጠሯቸው «የእናንተ ጓደኛ ያደረገን ጊዜ» በማለት አብዮቱን ሲያማርሩ ይደመጡ ነበር።

አብዮታዊ ሠራዊታችንን በአጠቃላይ፤ የሠራዊቱን መኰንኖች በተለይ ማንቃትና አብዮታዊ የፖለቲካ ትምህርት መስጠት ፍፁም የማይታለፍ አንገብጋቢ ጉዳይ ሆኖ ሳለ ጠላቶቻችን ያወጁብን ጦርነት ፋታ ስለነሳን ወደ ውጭ ወዳጅ ሶሻሊስቶች አገር እየላክን በፊረቃ ለማስተማር የነበረን እቅድ ሳይሳካ ቀረ።

መኰንኖቻችን ማርክሲስት ሌኒኒስት ንድፈ ሀሳቦችንና የተለያዩ አብዮታዊ የፖለቲካ መፅሃፍቶችን እንዲያነቡ ከማበረታታትና ከማትጋት ባሻገር በጦር ኃይሎች በተለያዩ የጦር ክፍሎች ውስጥ በተቋቋሙት የውይይትና የጥናት ክለቦች ውስጥ በቋሚነት እንዲሳተፉ ከአደራ ጭምር መመሪያ ሰጥተናቸው አብዛኛዎቹ ወይንም ብዙሃኑ በሙሉ ማለት ይቻላል በፈቃደኝነትና በደስታ ሲሳተፉ ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸው ከፍተኛ መኰንኖች ከፊሎቹ በማዕረግና በእድሜ የሚያንሷቸው የፖለቲካ ካድሬዎች በሚመሯቸው የውይይትና የጥናት ክለቦች ውስጥ ለመሳተፍ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ።

እነኝህ ጥቂት የወደቀው የአሮጌው ሥርዓት ናፋቂና ቅሪት የሆኑ ከፍተኛ ጀነራል መኰንኖች በሠራዊቱ ውስጥ ያሉ የወታደራዊ የፖለቲካ አስተዳደርና የሠራዊቱ የደህንነት ጥበቃ ሥራዎችን የሚሰሩ ካድሬዎች ጥረት መቃወምና ማጥላላት ሥራቸው በመሆኑ ካድሬዎቹም አዛዦቻቸውን አብዮቱ የመጣባቸው አድሐሪዎች ናቸው በማለት በሠራዊቱ ዘንድ ስለሚያጋልጧቸውና ስለሚያስጠሏቸው በሚፈጠረው ቅራኔ አልፎ አልፎ ግጭቶች ይታዩ ጀመር።

ይህ በእንዲህ እያለ የሶሻሊስት አገሮች የሚጠቀሙበትን የውል ወታደራዊ ዕዝ ወይንም አመራር እኛም መጠቀም ጀመርን።

የወል ወታደራዊ እዝ ወይንም አመራርን መጠቀም የፈለግንበት ምክንያት ሶሻሊስት አገሮች ሲጠቀሙበት በማየታችን ብቻ እኛም አይቅርብን ብለን እንደፋሽን የወሰድነው ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብና የአብዮቱ ባህሪ በአጠቃላይ፣ የሰሜን ኢትዮጵያ ማለትም በኤርትራ ክፍለ ሃገር የሚካሄደው እጅግ ውስብስብ የሆነ የእርስ በርስ የሲቪል ጦርነት በተለይ ስለአስገደደን ነበር።

አብዮታዊው መንግሥት ስለአብዮታዊው መከላከያ ሠራዊት ማህበራዊ የፖለቲካ ንቃትና የማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለም ትምህርት መጀመሩ፣ የፖለቲካ ወታደራዊ ካድሬዎችን በሠራዊቱ ውስጥ ማሠማራቱ፣ የወደፊቱን የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ችግኝ መትከል መጀመሩንና የሠራዊቱን ደህንነት የሚጠብቁ ወታደራዊ የደህንነት ካድሬዎችን በሠራዊቱ ውስጥ ማሰማራቱ አገሩንና አብዮቱን ከወረራ ለማዳን አብዮቱ ከመጣለት ከሠራተኛው መደብና ከገበሬው ህብረተሰብ መሃከል በራሱ ፈቃድ የመጣውን ሰፊ አብዮታዊ ሠራዊት፣ ዲሞክራቲክና አብዮታዊ ዲሞክራት የሆኑትን ብዙሃን የሠራዊቱን መኰንኖች ሲያስደስት አብዮቱን የሚደግፉ መስለውና አስመስለው በጦር ኃይሎቻችን ከፍተኛ የአመራር ቦታዎች ላይ የተቀመጡትን ከፍተኛ መኰንኖች ሁሉንም ሳይሆን ወደፊት ሁኔታዎች በፈቀዱላቸው ጊዜ አብዮቱን የመቀልበስ ዓላማ የነበራቸው ጥቂት የአሜሪካ መንግሥት የቀጠራቸው አድሐሪ ምንደኞች በሠራዊታችን ውስጥ ወታደራዊ የወል አመራር መመሥረቱ ስለአስደነገጣቸው በመቃወም ቅስቀሳ ከማድረግ ባሻገር በሲቪሉ ህብረተሰብም ውስጥ

«መንግሥት በማስተዋወቅ ላይ ያለው አዲስ ወታደራዊ የወል አመራር ከገንጣዮች ጋር ለምናደርገው የትጥቅ ትግል የአመራር ችግር የሚፈጥርነው» በማለት ህዝቡንም ማሳሳት ጀመሩ::

ሶሻሊስት አገሮች በአጠቃላይ፤ ታላቋ ሶቭየት ህብረትና ህዝባዊት ቻይና በተለይ በመከላከያ ሠራዊታቸው ውስጥ የወል አመራርን መጠቀም የጀመሩት እንዳው ያለምክንያት ከካፒታሊስት አገሮች ለመለየት ሳይሆን በአብዮታቸው አፍላ ዘመን በገጠማቸው ችግር ከውጭ ኢምፔሪያሊዝም የሠነዘረባቸውን ወረራ ለመከላከል ሲያደርጉት በነበረው ወታደራዊ የትጥቅ ትግል ብቻ ሳይሆን ትግሉ ወይንም ጦርነቱ የመደብ፣ የፖለቲካ፣ የርዕዮተ ዓለምና ከሃገር ውስጥ ፀረ አብዮት ኃይላት ጋር የሚደረግ የእርስ በርስ ጦርነት በመሆኑ፣ አገራቸውን፣ የየህዝባቸውን አንድነት፣ ማህበራዊ ደህንነታቸውን፣ የአብዮታቸውንና የአብዮታዊ ሠራዊታቸውን ደህንነት በመጠበቅ ከጥፋት ለመከላከልና ለማዳን ሲሉ የተጠቀሙበት ፍቱን መድሃኒት ሆኖ ስላገኙት ነው::

ፍቱን መፍትሄ ለመሆኑ ምስክሩ ያንን ፈታኝ ባለብዙ ፈርጅ ትግል በድል ተወጥተው እነኝህ አገሮች ዛሬ የሚገኙበት ሁኔታና ያሉበት የእድገት ደረጃ ነው::

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ ማህበራዊ አብዮት የገጠሙት አያሌ ውስብስብ ችግሮችና ተብትበው የያዙት ቀውሶች በታላቁ የጥቅምቱ በሩሲያና በቻይና ከታዩት የአብዮት ችግሮችና ቀውሶች ሁሉ በእጅጉ የላቁ ናቸው::

የኢትዮጵያን ማህበረሰቦችና ብሄረሰቦች ዓይነትና ባህሪ ከመዘርዘር ለጊዜው ተቆጥበ በኤርትራ ክፍለ ሃገራችን ብቻ አብዮቱ የገጠሙትን ችግሮች ብንመለከት ጊዜና አጋጣሚውን ጠብቆ ተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት የሰነዘረብን ወረራ፣ የኤርትራ፣ የትግራይና የኦሮሞ ብሄረሰቦች ነፃ አውጭ ነን የሚሉት ፀረ አንድነትና ፀረ አብዮት ገንጣይ ድርጅቶች በመላው ኢትዮጵያ በህብረት ያወጁብን ጦርነቶች የተቀሩት ኢሕአፓን የመሰሉት ፀረ ህዝቦች በአገር ላይ የሚያካሂዱትን ቡርቦራ ብንመለከት የታወጁብን ጦርነቶች ከእነኝህ ጋር የምናካሂደው ወታደራዊ የትጥቅ ትግል ብቻ ሳይሆን የዘር ወይንም የጐሳና የኃይማኖት ጦርነቶች ናቸው::

የመደብ፣ የፖለቲካና የርዕዮተ ዓለም ጦርነቶች ናቸው:: በአረብነትና በኢትዮጵያዊነት በሚያምኑ ተፃራሪ ኃይሎች መሃከል የሚካሄድ ጦርነት ነው እነኝህ ተፃራሪ ኃይሎች በሙሉ በኢትዮጵያዊነት ስም ሽፋንና ከለላ ራሳቸውን ከልለው በረቀቀ ዘዴ በአገሪቱ የተለያዩ አስተዳደራዊ ክልሎች፣ በየህብረተሰቡ ውስጥ፣ በመንግሥታችን የተለያዩ የሥራ ዘርፎችና ፋካዎች፣ በአብዮታዊው የመከላከያ ሠራዊታችን ውስጥ ሳይቀር ተሰግስገው የሚያካሂዱብን ጦርነት ነው

ጦርነቱ በአገር ውስጥ ባሉ ወይንም የአገር ተወላጆች በሆኑ የተለያዩ ተፃራሪ ኃይሎች ብቻ የሚካሄድና የሚመራ ሳይሆን፣ ከቀንደኛው የዓለም ሠላምና ደህንነት ፀር ከሆነው ከሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ጀምሮ መላው የዓለም አድህሮትና በተለይም የአካባቢው ታሪካዊ ጠላቶቻችን ሁሉቱንም እጃቸውን የከተቱበት ጦርነት ነው።

ጠላት የት እንዳለ፣ ማን እንደሆነ፣ እንዴት እንደሚሰራና እንደሚንቀሳቀስ ለማወቅ የማይቻልበት እጅግ ውስብስብ የሆነ ባለ ብዙ ፈርጅ ጦርነት ነው።

ኢምፔሪያሊዝም፣ መላው የዓለም አድህሮትና የአገር ውስጥ የአንድነታችንና የአብዮታችን ፀሮች በሙሉ ለአፍሪካ ህዝብ አርአያ ይሆናል ብለው የሚፈሩትንና የሚጠሉትን የኢትዮጵያ ህዝብ ማህበራዊ አብዮት ማዳፈን ወይም መቀልበስ የሚያስችለን ኤርትራን ለመገንጠል የሚደረገው የሲቪል ጦርነት የተሳካ እንደሆነ ብቻ ነው ብለው አንድና ብቸኛ ተስፋ የጣሉበት ጦርነት ነው።

የእነኝህ ፀረ አብዮት፣ ፀረ ህዝብና ፀረ ሠላምየሆኑ የጥፋት ኃይሎች ምኞት እንዳይሳካ የአብዮታዊ መከላከያ ኃይላችን፣ የፖለቲካ አስተዳዳሪ ካድሬዎቻችን፣ የሠራዊቱን ደህንነት ጥበቃ ካድሬዎቻችንና እንዲሁም በሠራዊቱ ውስጥ ያሉ መላው አብዮታዊያን አብዮታዊ ሠራዊቱ ለምንና ለማን እንደሚዋጋ፣ የአገሩ አንድነትና የአብዮቱ ፀሮች እነማን እንደሆኑ እንዲያውቅ፣ በጠላቶቹ ላይ ብርቱ ጥላቻ ኖሮት አምርሮ በቆራጥነት እንዲታገል፣ ለአብዮታዊ መሪዎቹ ፍፁም ታዛዥ የሆነ፣ በአብዮታዊ ሥነ ሥርዓት የታነፀና የመደብ ንቃቱ እጅግ ከፍ ያለ ሠራዊት እንዲሆን የሚያደርጉትን ጥረት አብዮቱ ሾሞና ሸልሞ ካሳደጋቸው የሠራዊቱ ከፍተኛ ጀነራል መኰንኖች መካከል ለኛ ባልተከሰሰተልን ሁኔታ በህቡዕ በአብዮቱ ፍንዳታ ማግሥት የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት የቀጠራቸው አድሃሪ ምንደኞች በማለት ለአንባቢ የገለፅኳቸው ጀነራል መኰንኖች፣ ራሳቸውን ከአገር፣ ከኢትዮጵያ ህዝብ፣ ከአገር መከላከያ ሠራዊቱና ከሕዝባዊ አብዮቱ በላይ እያደረጉ ለእነሱ የጦር ሜዳ አመራር ስኬታማነት የሚደረግ ጥረት መሆኑን ለመገንዘብ ተስኗቸው ሳይሆን በተቀጠሩበት ዓላማ መሠረት ከገንጣዮች ጋር በመተናነቅ ላይ ያለውን ታጋይ ሠራዊት ለሽንፈትና ብሎም ለለየት ውድቀት ለመዳረግ የሠራዊቱን ደህንነትና አንድነት፣ የመደብ ንቃቱንና ለአብዮቱ ያለውን አስተማ ማኝነትና ወገናዊነት በመፍራት የጦር ኃይሎቻችንን የወል አመራርና ዕዝ መመሥረት በብርቱ መቃወም ጀመሩ።

ከአብዮታችን የእድሜ ለጋነት ባሻገር በነበረብን ከፍ ያለ የመኰንኖች እጥረት ውስብስብ ችግር ውስጥ ያሰለጠናቸው ወጣት የፖለቲካው አስተዳደርና የወታደራዊ ደህንነቱ ጥበቃ ካድሬዎቻችንን የገጠማቸው ከባድ ችግር በእጅጉ ቢያሳዝነንም

ከከፍተኛዎቹ የጦር አዛዦች ጋር አልፎ አልፎ የሚታየው ቅራኔና ግጭት በአብዮታዊያን ያልታሰበና ያልተጠበቀ ችግር አልነበረም፡፡

ከኢትዮጵያ ህዝብ አብዮት በፊት ብዙ ቀድመው በተካሄዱት የሩሲያ፣ የቻይና፣ የኮሪያ፣ የቬየትናምና የኩባ ወዘተ አብዮቶች ከታዩት ቅራኔዎች አንዱ ነው፡፡

ለአብዮቱ ወገኖች በአዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት ማህበራዊ ኃይሎችና በአሮጌው ሥርዓት ቅሪቶች መሀከል የግድ መፈጠር ያለበት ቅራኔ ነው፡፡

አብዮቱ ጠንካራና ሐቀኛ አብዮት ሆኖ ተገቢውን መሥመር ይዞ በንቃት የሚመራና በፍጥነት የሚራመድ ከሆነና ካልፈዘዘ ወይንም ካላንቀላፋ በስተቀር ከፀረ አብዮት ኃይላት ጋር ግጭትና ቅራኔዎች መከሰትና መታየት አይቀሬ የመደብ ትግል ባህሬ ነው፡፡

አብዮቱ የአሮጌውን ሥርዓት ቅሪቶች ሙሉ በሙሉ አስወግዶ የራሱን አብዮታዊ የጦር መኰንኖች እስከሚተካ ወይንም እስከሚፈጠር ድረስ የሚጠበቁና የሚታዩ ግጭቶችና ቅራኔዎች ናቸው፡፡

እነዚህ ቅራኔዎች አብዮታዊ ባህሪያቸውን እንደተላበሱ በአብዮቱ የበላይነት በአብዮታዊያን መመራታቸው ቀርቶ የአሮጌው ሥርዓት ቅሪቶችና የአብዮቱ ፀሮች የበላይነቱንና የአጥቂነቱን ሥፍራ ይዘው አብዮቱ እንዳይቀለበስና ብሎም ኢትዮጵያ በገንጣዮች እንዳትከፋፈል ቀደምብዬ በመፅሃፉ ክፍል ሃያ ሁለት ለአንባቢ የገለፅኳቸውን አዲስና ዘመናዊ የጦር ኃይሎችን፣ የሲቪል መከላከያና የመከላከያ ኢንዱስትሪ የአደረጃጀት እቅዶች ከዚህ ግርጌ በተመለከቱት ቅደም ተከተሎች ወደ ተግባር የመተርጐምን ጥረት ደረጃ በደረጃ ጀመርን፡፡

ምዕራፍ አርባ ስድስት

አብዮታዊ የጦር መኰንኖችን ለመተካት የተዘጋጀ ዕቅድ።

አብዮቱን በማራመድና ከአብዮቱ ፀሮች ጋር በመታገል ላይ ያሉትን የአገሪቱን የጦር ኃይል መኮንኖች ለማጠናከር፣ ለአገሪቱ አንድነት፣ ለአብዮቱ ደህንነትና ጤናማ ሂደት አስተማማኝ ዋስትና ለማግኘት ይቻል ዘንድ አብዮቱ የአሮጌውን ሥርዓተ ማህበር ቅሪቶች ከአብዮታዊው ሠራዊት እያገለለ የራሱን አብዮታዊ የጦር መኰንኖች ለመተካት ታቀደ።

በታላቁ አብዮታችን ፍንዳታ ማግሥት በወረረን በተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ላይ የማያዳግም ድል ከተቀዳጀን በኋላ ድል አድራጊውና ኃያሉ አብዮታዊ ሠራዊታችን ፊቱን ወደ ሰሜን በማዞር ሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊታችን በግብረ ኃይሎች የማጥቃት ዘመቻ መላውን የኤርትራ ክፍለ ሃገር ከገንጣዮች እያፀዳ በመገስገስ፣ በሳሕል አውራጃ በናቅፋ ተራሮች ጥግ እስኪደርስ ድረስ ለሦስቱም የአገሪቱ የጦር ኃይሎቻችን የጦር መኰንኖችን ለማፍራት ስንጠቀምበት የነበረው መኰንኖችን የማሰልጠን ዘይቤ የሦስቱ ኃይሎች ማለትም፣ የምድር ጦር ሠራዊቱ፣ የአየር ኃያላችንና የባሕር ኃይላችን ሠራዊት ከአገሪቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወጣቶችን በመመልመል በየበኩላቸው እጩ መኮንኖችን ለመኰንንነት ማሠልጠን ነበር።

የአየር ኃይላችንና የባሕር ኃይላችን እጩ መኰንኖች መኰንን ለመሆን የሚጠይቃቸው የትምህርት ጊዜ ሦስት ዓመታት ሲሆን የምድር ጦር መኰንኖችን ያፈራ የነበረው በሁለት የማሠልጠኛ ተቋማት ነበር።

አንደኛውና አንጋፋው የገነት የጦር ትምህርት ቤት በፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ምክንያት የማሠልጠን ተግባሩ ለአምስት ዓመታት ያህል ከተቋረጠ በኋላ በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ ዘመናዊውን የምድር ጦር ሠራዊት ማቋቋም ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 1945 ዓ.ም ድረስ ትምህርት ቤቱ ያስመረቃቸው አብዛኛዎቹ እጩ መኰንኖች ይመለመሉ የነበረው ከሠራዊቱ መሃከል፣ በወታደራዊ ደንብና ሥነ ስርዓት የታነፁትን፣ ከጥሩ ወታደራዊ ልምድና ተመክሮ ጋር ቢያንስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ያላቸውን የበታች ሹማምንት ሲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ የምድር ጦር ሠራዊቱን ለማቋቋምና ለመምራት የቻሉ መኰንኖችን ለማፍራት ተችሏል።

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ከሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ጋር የመከላከያ ተራድኦ ውል ከተዋዋለ በኋላ መኰንኖችን ወደ አሜሪካ በመላክ የተለያዩ ዓይነትና ደረጃ ያላቸውን ወታደራዊ ሞያና የጦር አመራር እውቀቶች እንዲቀስሙ በማስፈለጉ መማሪያ የሆነውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ በተሻለ

የተማሩ ወጣቶች ከአገሪቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መመልመል ስለአስፈለገ በሠራዊቱ ውስጥ በማገልገል ላይ የሚገኙ ባለ ሌላ ማዕረግተኞች መኰንን የመሆን እድል እንዳይቀርባቸው ሆኖ ግን መደበኛ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያላቸው መሆን ስለነበረባቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መመዘኛ የሆነ ፈተና እየተሰጣቸው ያለፉት ከአገሪቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና ከሠራዊቱ የተመለመሉ እጩ መኮንኖችን መቀበልና ማሠልጠን ሲጀመር፣ የትምህርት ጊዜውም እርዝመት ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመታት ከፍ ብሏል።

ለምድር ጦር ሠራዊት አመራር የሚፈለጉ ወጣት እጩ መኰንኖች እውቀት መመዘኛ የባዕድ ቋንቋ ማወቅ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው በጦር ኃይሎቻችን ውስጥ ሠራዊቱ የራሱ ሐኪሞች፣ መሃንዲሶች፣ የህግ ባለሞያዎች ወዘተ ስለሚያስፈልጉት በአገር ውስጥና በውጭ አገሮች ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች እንዲማሩ ዩኒቨርስቲ ለመግባት የሚያስችል የትምህርት መሰናዶ ያላቸውን ወጣቶች ከትምህርት ቤቶች እየመለመለ ለጦር መኰንንነት ለሦስት ዓመታት የሚያሠለጥን የሐረሩ የጦር አካዳሚ ተቋቋመ።

በጣም በአዝጋሚ ሁኔታም ቢሆን አገሪቱ እየተሻሻለች እንደመሄዷ መጠን በየጊዜው በተሻሉ ወጣት መኰንኖች እየተገነቡ የነበሩት የጦር ኃይሎቻችን ወታደራዊ አካዳሚዎች ያፈሯቸው መኰንኖች ደረጃ ዓለም አቀፍን የመኰንኖች ደረጃ የሚመጥን ስለነበረ ከአያሌ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪ አፍሪካዊ ወዳጅ አገሮች ከሱዳን፣ ከኬኒያ፣ ከዩጋንዳ፣ ከጋና እና ከናይጄሪያ ወዘተ ወጣቶች ወደ ኢትዮጵያ እየተላኩ በአገራችን የጦር አካዳሚዎች ውስጥ ይሰለጥኑ ነበር።

እስከ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮት ፍንዳታ ድረስ በአገሪቱ የጦር ኃይሎች ውስጥ የነበሩት መኰንኖች መጠን አገሪቱ ለነበራት ለ40,000 ሠራዊት አመራር የተመጠነ ስለመሆኑ በተለያዩ አጋጣሚዎች በኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ አንድና በዚህም በቅፅ ሁለት ለአንባቢ ተገልጿል።

በቅድመ አብዮት ለባዕድ ተቀጥረው አገራቸውን ለአሥራ አምስት ዓመታት ሲወጉ የነበሩ የኤርትራ ክፍለ ሃገር ገንጣዮች የአብዮታችን መፈንዳት ለእነሱ የመገንጠል ዓላማ ስኬታማነት አመቺ ሁኔታ የፈጠረላቸው ስለመሰላቸው የጥፋት ተግባራቸውን በበለጠ ማስፋፋታቸውን፣ ሌሎቹ ኋላ ቀር ጠባብ ብሄርተኞች፣ የተለያዩ የአገር ውስጥ አድህሮትና የአብዮቱ ፀሮች ህዝብ የማሸበር ተግባራቸውን መጀመራቸውን የተመለከተው የተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት የአገራችንን ድንበር 700 ኪ/ሜትር ጥሶ በመግባት ስለ ወረረን ለመከላከልና ብለንም ረግጠን ለማስወጣት በአጣዳፊ ሁኔታ ያደራጀነውን ቁጥሩ ወደ ግማሽ ሚሊዮን የሚጠጋ ሠራዊት የሚመሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣት መኮንኖችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማፍራት የተጠቀምንበት የአሰለጣጠን ዘዴ ወራሪውን የተስፋፊው የሱማሌ

መንግሥት ሠራዊት ተከላክለን በሰባት ወራት ውስጥ ከአገራችን ለማስወጣትና ገንጣዮች ተቆጣጥረውት የነበረውን የኤርትራን ክልል ዘጠና በመቶ ነፃ አውጥተን በአገኘነው አንፃራዊ የተሻለ ጊዜ የአሠለጣጠኑን ዘይቤ ፍፁም በመለወጥና ብዙ በማሻሻል የመኮንኖቻችንን ጥራት በጣም ከፍ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ የሆነ አንገብጋቢ ጉዳይ ከመሆኑ ሌላ ቀደም ብዬ ለአንባቢ እንደገለፅኩት ከነበሩን ከፍተኛ መኰንኖች መካከል የተወሰኑትንና እጅግ ከፍተኛ ሥልጣን ላይ የነበሩትን የኃይል፣ የሠራዊትና የክር አዛዦች የዓለም ሠላምና የዓለም አብዮቶች ፀር የሆነው የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት መልምሎ በአብዮታዊው ሠራዊታችን ውስጥ ያሰማራቸው ምንደኞች በሠራዊታችን ውስጥ አድፍጠው ራሳቸውን ሲያደራጁና በበኩላቸውም መሰል ግብረ አበሮቻቸውን በህቡዕ ሲመለምሉ ቆይተው ከአሮጌው ሥርዓት የተረከብነውን በኤርትራ ክፍለ ሃገር የሚካሄድ የእርስ በርስ ጦርነት መጠቀሚያ አድርገው የሚያዙትን ሠራዊት ለሽንፈት በመዳረግ አገርንና ሠራዊቱን የማፍረስና አብዮቱን የመቀልበስ አዝማሚያ በማየታችን በአዲስ ዘዴ አብዮቱ የራሱን የጦር መኮንኖች በአስቸኳይ በማፍራት በትግል ላይ የሚገኙትን የአብዮታዊ ሠራዊቱ አብዮታዊ መኰንኖች የሚያጠናክሩ መኮንኖች የሚያፈራበትን እቅድ ከዚህ በሚከተለው ሁኔታ አቀድን።

በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ሠራዊት ላይ ድል ከተገኘበት ከ1934 ዓ.ም ጀምሮ ይህንን አዲስ አብዮታዊ የጦር መኰንኖች የሚያፈራ እቅድ እስካሰናዳንበት ጊዜ ድረስ፣ ሦስቱ የጦር ኃይሎች ማለትም፣ የምድር ጦር ሠራዊታችን፣ የአየር ኃይላችንና የባሕር ኃይላችን በተለያየ ቦታና ሁኔታ በየፊናቸው እጩ መኰንኖችን ማሠልጠናቸው ቀርቶ፦

1ኛ ሦስቱም ኃይሎች የሚያስፈልጓቸው ወጣት መኰንኖች ምንጭ ወይንም ማሠልጠኛ አንድ ማዕከል ወይንም የጦር አካዳሚ እንዲሆን፤

2ኛ ሦስቱ የጦር ኃይሎች የሚያስፈልጓቸው ወጣት መኰንኖች መጠን ወይንም ቁጥር በኃይሎች ጥያቄ መሠረት እንዲወሰን፤

3ኛ ለሦስቱም ኃይሎች በየዓመቱ የሚያስፈልጉ እጩ መኰንኖች በጦር አካዳሚው ከአገሪቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ት/ቤቶች የሚመለመሉ ወጣቶች እድሜ ከ16 እስከ 18 ዓመት ብቻ ሆኖ በትምህርት ደረጃቸው 10ኛ ክፍልን ያጠናቀቁ እንዲሆኑ፤

4ኛ በጦር አካዳሚው ውስጥ የሚሰጠው ወታደራዊ ትምህርት ብቻ ሳይሆን በከፍተኛ ደረጃ ጥራት ያለው የ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ትምህርት እንዲሆን-

ሀ ሶሻሊስታዊ ርዕዮተ ዓለም ወይንም ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን በጥልቀት

ለ የዓለም ሠራተኞችንና ኮሚኒስቶችን ንቅናቄ ታሪክ

መ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምና ሳይንሳዊ ኮሚኒዝምን በጥልቀት

ሠ የኢትዮጵያ ህዝብ ከፊውዳሊዝም፣ ከተስፋፊዎችና ከቅኝ ግዛት ኃይሎች ጋር ያደረጋቸውን ትግሎችና ብሎም የታላቁን አብዮት ታሪክና የሩቅ ዓላማውን

ረ ጠቅላላ እጩ መኮንኖቹ የኢትዮጵያ ሠራዊት አብዮታዊ መኰንን ወይንም ሶሻሊስት አርበኛ በመሆን የሚሰጣቸው የትምህርት ጊዜ አምስት ዓመት እንዲሆን

ከአምስት ዓመታቱ ውስጥ የመጨረሻዎቹ ሦስቱ ዓመታት የያዙት ወታደራዊ ትምህርቶችን ሲሆኑ፤ የትምህርቶቹ ዓይነቶች እጅግ ብዙ በመሆናቸው ዝርዝር ውስጥ መግባት ሳያስፈልግ ጠቅለል ባለ ሁኔታ ከዚህ የሚከተሉትን ይመስላሉ።

ወታደራዊ ሥነሥርዓትና ደንቦችን፣ ወታደራዊ ሕጎችን፣ ሠልፍና የሠልፍ ሥርዓቶችን፣ የተለያዩ ዓለም አቀፍ እስ ፖርቶችንና የአካል ማጠንከሪያዎችን፣ አይሮፕላኖችን ማብረርና መርከቦችን ማንቀሳቀስን የመሳሰሉት ውስብስብ ያሉት ቴክኒካዊ ሞያዎች ብቻ ሲቀሩ በጠቅላላው በጦር ኃይሎቻችን ውስጥ ያሉ የጦር መሣሪያዎችን አጠቃቀም የእግረኛ ሠራዊት፣ የጎሪላና የዐረ ጎሪላ ውጊያ ስልቶችን፣ የሜካናይዝድ እግረኛ ሠራዊትና የታንከኛ ሠራዊቶች የውጊያ ሥልቶችን፣ የአየር ኃይልና የባሕር ኃይል ሠራዊቶች የውጊያ ሥልቶችን፣ የሦስቱን ኃይሎች ማለትም የምድር ጦር ሠራዊት፣ የአየር ኃይል ሠራዊትና የባሕር ኃይል ሠራዊቶችን የህብረት ውጊያዎች ስልቶችን፣ ጠቅላላ ወታደራዊ አመራርን (Military Leadership) በስፋትና በጥልቀት ይማራሉ።

በዚህ ዓይነት የትምህርት አሰጣጥ የአገሪቱ የጦር መኰንኖች የሦስቱንም ኃይሎች ሞያዎች መማርና ማወቅ በጦር ሜዳዎች ላይ ለሚያደርጓቸው የህብረት ውጊያዎች ታላቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

ለአምስት ዓመታት ለእጩ መኰንኖቹ የሚሰጧቸው ትምህርቶች ጥራትና ሁለገብነት ያላቸው ወታደራዊ ሞያዎች ከመሆናቸው ባሻገር በመኰንንነት የአገልግሎቶቻቸው ዘመናት ለአገራቸው ለኢትዮጵያ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለህዝባዊው አብዮት ፍፁም ታማኝ እንዲሆኑ ለማድረግ ሲሆን ከአካዳሚው ተመርቀው ከወጡ በኋላ ረዥሙን ወታደራዊ አገልግሎት በሚሰጡባቸው ወደየእናት የጦር ክፍሎቻቸው ሲደለደሉ የሚቀሯቸውን ማለትም የሚካኗቸውን ዝርዝር ሞያዎች ያስተምሯቸዋል።

ለማጠቃለል ከ16 እስከ 18 ዓመት ባለ የእድሜ ደረጃ ከየትምህርት ቤቶች ተመልምለው ለአምስት ዓመታት በወታደራዊ አካዳሚ ውስጥ የሚሰለጥኑት ወጣቶች

መኰንኖች በሚሆኑበት ጊዜ ከ21 እስከ 23 ዓመት እድሜ ያላቸው ወጣቶች ሲሆኑ በጦር አካዳሚ ውስጥ የአምስት ዓመት ቆይታቸው በወታደራዊ ሞያ የተሟላ ብቃት ያላቸው፣ በማህበራዊ ንቃት ብቻ ሳይሆን ጥልቅ አብዮታዊ የፖለቲካ እውቀታቸው ለአንዲት ኢትዮጵያና ለሕዝቧ ለአንድ ሠንደቅ ዓላማና ለአንድ ሕዝባዊ የፖለቲካ ዓላማ የቆሙ ሶሻሊስት አርበኞች በመሆናቸው በአሮጌው ሥርዓተ ማህበር ጊዜ በሦስቱ የጦር ኃይሎቻችን መካከል የነበረው መናናቅና በመለዮ መከፋፈል ቀርቶ የሚፋቀሩ፣ የሚከባበሩ፣ የሚተባበሩ፣ የሚተማመኑና ለህብረተሰብአዊው ሥርዓት በታማኝነትና በዓላማ ፅናት የሚታገሉ ሶሻሊስት አርበኞች እንደሚሆኑ ይታመናል። አንድ ሃቀኛ ህዝባዊ አብዮት እንደዚህ ያሉትን የጦር መኰንኖች ማፍራት ካልቻለ መቅኖ እንደማይኖረው በታሪክ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። በእኛም ሃገር የተፈጠረው ይሄው ነው።

ምዕራፍ አርባ ሰባት

1ኛ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥራት ያለውና ዘመናዊ ትጥቅ የታጠቀ፣ መጠኑ

ከአገሪቱ የሀብት ምጣኔ ጋር የተመጣጠነ ቋሚ ወይንም መደበኛ የምድር ጦር ሠራዊት ስለማደራጀት ።

በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ በመላው የአገራችን ማዕዘናትና በመሃል አገር ሲወጉን የነበሩት አገር ገንጣይና አስገንጣዮች፣ የተለያዩ ፀረ አብዮት ኃይሎችን በአጠቃላይ፣ የተስፋፊውን የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት በተለይ ለመከላከል በእናት አገር ጥሪ ያደራጀነው ህዝባዊ ሠራዊት ዳግም ወታደራዊ አገልግሎት እንዲሰጡ የጠራናቸው፣ አባት ጦሮች፣ የሰባት ዓመት ምልስ ጦሮችና በቅድመ አብዮት ብሄራዊ በመባል የሚጠሩት ጦሮች ከመደበኛው ጦር ጋር ሲጠቃለሉ የጠቅላላው የመከላከያ ሠራዊታችን ቁጥር ወደ ግማሽ ሚሊዮን የደረሰበት ጊዜ ነበር።

ይህንን ያህል ሠራዊት የሚለብሰው የደንብ ልብስና ትጥቅ፣ የሚዋጋባቸው የተለያዩ መሣሪያዎች አገሪቱን ከሚጠይቁት ከፍ ያለ የገንዘብ ወጭ ሌላ መላው ሠራዊት የመንግሥት ቀለብተኛና ደመወዝተኛ ነው።

ኢትዮጵያ ታዳጊ አገር ከመሆኗ ሌላ ሰው ሠራሽና ተፈጥሮ አመጣሽ በሆኑ አያሌ ችግሮች ተወራና ተወጥራ ከባዕዳን እህል እስከ መመፅወት የደረሰች ደሃና ኋላቀር አገር መጠኑ ወደ ግማሽ ሚሊዮን የተጠጋ ሠራዊት ማስተዳደር የተገደድነው ባልጠበቅነውና ባልተዘጋጀንበት ጊዜ በውጭ ተስፋፊዎችና በውስጥ ጠላቶች የታወጀብንን ጦርነት ለመከላከል በመገደዳችን ነው።

ከአገራችን ሠራተኛ መደብና ከገበሬው ህብረተሰብ ላብና ወዝ የሚገኘውን ከእጅ ወደ አፍ የሆነ አነስተኛ ገንዘብ በሙሉ ማለት ይቻላል የምናውለው ለጦርነት ነው።

ጦርነቱ በጦር ሜዳ የሚፋለሙትን የአብዮታዊ ሠራዊታችንን ህይወት የሚቀጥፍ ብቻ ሳይሆን የመላውን ህዝባችንንም ደም እየመጠጠ ስለሆነ በእንዲህ ያለው ሁኔታ ለረጅም ጊዜ የምንቆይ ከሆነ በቡሀ ላይ ቆረቆር እንዲሉ አገሪቱ ይበልጥ እየተዳከመች እንደምትሄድ ግልፅ ነበር።

ስለሆነም፣ የምድር ጦር ሠራዊት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ሥልጠና ያለውና ለውጊያ ብቁ የሆነ ዘመናዊ ጥራት ያለው ትጥቅ የታጠቀ ሆኖ ጠቅላላ ቁጥሩ ከ50,000 እስከ 60,000 ብቻ የሆነና ጤንነቱ፣ ምቾቱና ሞራሉ በሚገባ የተጠበቀ የአገርን ድንበር፣ የአገርን አንድነት፣ የህዝቡን ሠላምና ማህበራዊ ደህንነት ማስከበርና በየሁለት ዓመታት ከህዝቡ መሃከል እየተመለመሉ የብሄራዊ ውትድርና አገልግሎት ለአገራቸው የሚሰጡ ወጣቶች መሠረታዊ የውትድርና ሞያ ሥልጠና መስጠት፣

በእያንዳንዱ ዓመት የክለሳ ወይንም የተሃድሶ ሥልጠና በመስጠት በጦርነት ጊዜ በክተት ጥሪ የሚጠሩትን የብሄራዊ ውትድርና ሥልጠኑንና የአገር መከላከያ ደጀን ሠራዊቶች የሚታጠቋቸውን ትጥቆችና የሚዋጉባቸውን መሣሪያዎች በማገባ አዘጋጅቶና ጠብቆ በማቆየት አገሪቱ በምትፈልጋቸው ጊዜ በክተት ጥሪ ሲሰባሰቡ እንደ አስፈላጊነቱ በጦር አቋም አደራጅቶ ለውጊያ አመራር መስጠት ይሆናል።

2ኛ ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ዘመናዊ መደበኛ ጦር በተጨማሪ ጥራትና ዘመናዊ ትጥቅ ያለው መጠኑ ከ10,000 እስከ 15,000 የሆነ ቋሚ ወይንም መደበኛ የጠረፍ ጥበቃ ጦር ስለማደራጀት እቅድ።

ይህ በአገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲቋቋም የተፈለገው ዘመናዊ የጠረፍ ጥበቃ ጦር በአብዛኛው በሦስተኛው ዓለም ታዳጊ አገሮች ጥቅሙ ቀርቶ ስሙም የሚታወቅ አይደለም። ጦሩ የሚመራበት ወታደራዊ ሥነሥርዓትና የሚሰማራበት ወታደራዊ ተግባር በመጠኑ የአንዱ አገር ከሌላው የተለየ ቢሆንም የጠረፍ ጥበቃ ጦር ተደራጅቶና በየአገሪቱ ጠረፎች ለጥበቃ ተሰማርቶ የሚገኘው በሁለቱ ኃያላን ማለትም በሰሜን አሜሪካና በሶቪየት ህብረት፣ በሰሜንና በደቡብ ኮሪያና በቻይና ብቻ መሆኑ ነው የሚታወቀው።

ከሁለቱ የአረቦችና የእስራኤሎች ጦርነት በኂላ የእስራኤል፣ የሶሪያ፣ የሊባኖስና የጆርዳን መንግሥታት የጠረፍ ጥበቃ ጦር እንደ አቋቋሙ ይነገራል።

እስከ ዛሬ በታየውና ከእነዚህ ከተጠቀሱት አገሮች በተገኘው ልምድ በተለይ የሶቪየት ህብረትና የሰሜን ኮሪያ የጠረፍ ጥበቃ ጦሮች ከማናቸውም አገሮች በጣም የተለዩና ከፍ ያለ ልዩ ሥልጠናና ክብረት የጠነከረ ወታደራዊ ሥነስርዓት የተላበሱ፣ የውጊያ ትጥቃቸውና የመገናኛ መሣሪያዎቻቸው እጅግ ዘመናዊና በአየር፤ በየብስና በባህር መቶ በመቶ ፈጥነው የሚንቀሳቀሱ ከከፍተኛ ወታደራዊ ሞያዎች በተጨማሪ የፖለቲካና የመረጃ አሰባሰብ ሥልጠና ያላቸውና እንደተሰማሩበት አጎራባች ድንበር ተዋሳኝ ወይንም አጎራባች የሆነውን አገር ህዝብ ቋንቋ የሚናገሩ ናቸው።

በተግባርም እረገድ እንደማናቸውም ጦር አስፈላጊ በሆነ ጊዜ መዋጋት ብቻ ሳይሆን ስለጎረቤት አገር መረጃዎችን የመሰብሰብና በራሳቸው አገርና በጎረቤት አገር መካከል የሚደረጉትን የአየር፣ የባህርና የየብስ ተሽከርካሪዎችን፣ የእግር እንቅስቃሴዎችንና ግንኙነቶችን የሚቆጣጠሩ ናቸው።

አገራችን ታዳጊ አገር እንደመሆንዋ በመጀመሪያው የጦሩ መቋቋም ጊዜ የሚያስፈልገውን ሁሉ ማስታጠቅና መቶ በመቶ በአየር፣ በባሕርና በየብስ ማንቃነት የሚያዳግት ቢሆን ደረጃ በደረጃ እየተገነባ የሚያድግ የጠረፍ ጥበቃ ጦር ለባሕርና ለየብስ ጠረፍ ጥበቃ የምናቋቁመው ጦር ቁጥሩ ከ 10,000 እስከ 15,000 ሆኖ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩ ተግባሮቹ ባሻገር ሁለተኛ ተግባሩ ለአገሪቱ መከላከያ ተጠባባቂ

ወይንም ደጀን የሚሆኑትን የብሄራዊ ውትድርና ግልጋሎት ምልምል ወጣቶች መደበኛና እንዲሁም የክለሳ ወይም የተሃድሶ ሥልጠና መስጠት ይሆናል ፡፡

3ኛ የብሄራዊ ውትድርና አገልግሎትን ደንብ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ተግባራዊ በማድረግ በሚያስተማምን ሁኔታ በምንፈልገው መጠን ተጠባባቂ ወይንም ደጀን የመከላከያ ኃይል ስለሚደራጁበትና ለጦርነት ስለመዘጋጀት እቅድ፡፡

እኛ ባለን መረጃ በዓለም ላይ የብሄራዊ ውትድርና ግልጋሎት ደንብን በመጠቀም በሚፈልጉት መጠን አገራቸውን የሚከላከሉበት ደጀን ወይንም ተጠባባቂ የመከላከያ ሠራዊት በማደራጀት ረገድ የሚታወቁ አገሮች ብዙ ናቸው፡፡ ሰሜን አሜሪካንንና ታላቋ ሶቭየት ህብረት ብቻ ሳይሆኑ ከምሥራቅም ከምዕራብም አያሌ አገሮችን መጥራት ይቻላል፡፡

ከሁለት መቶ ሚሊዮን በላይ ህዝብ ባላቸው ጠላቶቿየ አረብ መንግሥታት የተከበበችውና በተደጋጋሚ ህልውናዋን ለማስጠበቅ ታላቅ ተጋድሎ በማድረግ የምትታወቀዋ እስራኤል በሠላሙ ጊዜ የምታስተዳድረው ቋሚ ወይንም መደበኛ ጦር መጠን ከአገሪቱ የፖሊስ ሠራዊት ቁጥር ቢያንስ እንጂ የሚበልጥ አይደለም፡፡

በአሃዝ ለመግለፅ ባይቻልም እጅግ በጣም ትንሽ መሆኑየታወቀ ነው፡፡ የተደጋገመውን የአረቦች ጥቃት ተቋቁማ የመለሰቺበትና የምትመካበት የመከላከያ ኃይሏ በሙሉ በብሄራዊ ውትድርና ደንብ አሰልጥናና አደራጅታ በጦርነት ጊዜ በክተት አዋጅ የምትጠራው ደጀን ሠራዊቷ ነው፡፡

ከፊሉ የነዳጅ ዘይት ባለሀብ ትየሆኑ ከአሥራ አምስት አገሮች በላይ በሆኑ አገሮች ውስጥ የሚገኙና በብዙ ሚሊዮን ከሚቆጠሩ የጦር ኃይሎች ጋር በተመጣጠነ ሁኔታ ቋሚ ወይንም መደበኛ ጦር በቋሚነት ለማስተዳደር ብትሞክር ያለ ጦርነት በኢኮኖሚ ድቀት ብቻ የምትወድቅበት ሁኔታ በተፈጠረ ነበር፡፡

በታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ ማህበራዊ አብዮት ፍንዳታ ማግሥት ወደ ቤጂንግ በሄድኩበት ጊዜ ህዝባዊ ቻይና እንደ ዛሬው በኢኮኖሚ ከመበልፀጓና የመከላከያ ሠራዊቷ ኒውክለር መሣሪያ ከመታጠቁ በፊት በኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ወረራ ቢሰነዘረብን ተከላክለን ጠላቶቻችንን ወደ መጡበት እንመልሳቸዋለን ብለን የምንተማመንው በመሣሪያ ሳይሆን በሰው ኃይላችን ነው ነው ያሉኝ፡፡

በዚያን ጊዜ አምስት ሚሊዮን ቋሚ መደበኛ ሠራዊት ሲኖራቸው በብሄራዊ ውትድርና ግልጋሎት ደንብ የሠለጠነው ደጀን የመከላከያ ሠራዊት ቁጥር ከአስራ አምስት ሚሊዮን በላይ ነበር፡፡ ይህ ቁጥር የታጠቀውን ህዝባዊ ሚሊሺያ ሳይጨምር ነው፡፡ ህዝባዊ ሚሊሺያ ማለት ደግሞ መላው የቻይና ህዝብ ማለት ነው፡፡ ስለሆነም

ህዝባዊት ቻይና ለባዕዳን ወረራ ፊፅሞ የማትመችና ጠላቶቿን እንደ እሳት የምትፈጅ አገር ነች።

በዚህ ጉብኝቴ የህዝባዊ ቻይና አመራር ጓዶች የነገሩኝ ሌላው ነገር፤ ረጂም ጊዜ የሚወስድ ወረራ ቢሰነዘርብን ወይንም አንዳንዴ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች እንደሚታየው የማያቋርጥ የአየር ንብረት ቀውስን የመሳሰሉ የተፈጥሮ አደጋዎች ቢያጋጥሙን ለአሥር ዓመታት ህዝባችንን የምንመግበው ተጠባባቂ የእህል ክምችት አለን በማለት ነው።

እኛ የብሄራዊ ውትድርና አገልግሎትን በአገራችን ተግባራዊ ለማድረግ ያቀድነው በአንደኛ ደረጃ የዚህን ምዕራፍ ርዕስ ስጀምር እንደገለጥኩት በረጅሙ ታሪካችን የባዕዳን ጥቃት ወይንም ወረራ ሲሰነዘርብን ብቻ ተነስተን ወይንም ከእንቅልፋችን ነቅተን ሠርገኛ መጣ እንዲሉ መንደፋደፍ ሳይሆን የጠላቶቻችንን ጥቃት ለመመከት ተዘጋጅተን ለመቀመጥ ነው።

ነፃነታችንን፣ ህልውናችንን፣ ድንበራችንን፣ ብሄራዊ ደህንነታችንንና ብሄራዊ ጥቅማችንን ለማስከበር የሚያስችለን አስተማማኝ የመከላከያ ኃይል ለመገንባት ነው።

በድህረ አብዮት የውስጥና የውጭ ጠላቶችቻን በአንዴና በህብረት ባወጁብን ጦርነት ተገደን ራሳችንን ለመከላከል በእናት አገር ጥሪ ያደራጀነው የአገሪቱ አቅም የማይችለውን ወጪ የሚያስከፍለን መጠነ ሰፊ ሠራዊት ኢኮኖሚያዊ እድገታችንን በመጫንና በማቀርቀዝ በቡሀ ላይ ቆረቆር እንዲሉ ለባሰ ድህነት እንዳይዳርገን መጠኑን ቀንሰን በቋጠባ ሥርዓት የሚመራ የአገር መከላከያ ሠራዊት ለማደራጀት ነው።

ከእነዚህ ከዚህ በላይ ከጠቃቀስኳቸው የብሄራዊ ውትድርና ደንብ ጥቅሞች ወይንም ፋይዳዎች ሌላ በሁለተኛ ደረጃ የብሄራዊ ውትድርና ደንብ ጠቃሚነቱ፣ በሂደት ወይንም በጊዜ እርዝመት መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ እሥራኤሎችና እንደ ቻይና ህዝብ ወዘተ ራሱን የሚከላከል፣ የማይደፈርና አይበገሬ ህዝብ ለማድረግ ማስቻሉ ነው።

በብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ ማዕከል ውስጥ አዲሱን ዓይነት ከወታደራዊና ከሲቪል መከላከያ ጋር የአገር መከላከያ ኢንዲስትሪዎችን የማቋቋም ጥናት ከአደረግንና ብለንም ወደ ተግባር የሚወስደንን ዕቅድ ከሠራን በኋላ፣ የብሄራዊ ውትድርና አገልግሎት ደንብን በኃላፊነት በመምራት ተግባራዊ የሚያደርጉ፣ አንድ የብሄራዊ ውትድርና ደንብና አገልግሎት መምሪያ ኮሚሽንና አንድ የአገር መከላከያ ኢንዱስትሪ ኮሚሽን አቋቋምን።

ከአዲስ ዓይነት ወታደራዊና የሲቪል መከላከያ ጋር የመከላከያ ኢንዱስትሪዎች እቅዶችን ከአጠናቀቅን በኂላ ከምርት ዘመቻው ጋር በተቀነባበረ ሁኔታ አያሌ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን ስንጀምር ቅድሚያውን ለብሄራዊ ውትድርና አገ ልግሎት በመስጠት እያንዳንዳቸው ከ10 እስከ 15ሺህና ካስፈለገ ከዚያም በላይ የሚያስተናግዱ በተለያዩ አራት ክፍለ ሃገራት ማለትም፣ በሸዋ፣ በጎጃም፣ በሲዳሞና በባሌ ዘመናዊ የብሄራዊ ውትድርና አገልግሎት ምልምል ወጣቶችን ለውትድርና ማሠልጠኛ ትምህርት ቤቶችንና እንዲሁም በሺህ የሚቆጠሩ እጩ መኰንኖችን ማሠልጠኛ ዘመናዊ የጦር ትምህርት ቤት በሐረርጌ ክፍለ ሃገር በድሬዳዋ አውራጃ ከድሬዳዋ ከተማ ሃያ ኪ/ሜትር ያህል ወጣ ባለና ሁርሶ በመባል በሚጠራ ሥፍራ በመገንባት ለተወሰነ ጊዜ ለአዲሱ የመከላከያ ሠራዊት ግንባታ የሚመለመሉትን እጩ መኮንኖች ማሰልጠኛ አካዳሚ በማዘግየት ለሙከራ ያህል የመጀመሪያዎቹን 20,000 ሃያ ሺህ ብቻ የብሄራዊ ውትድርና ግልጋሎት ሰጪ ምልምል ወጣቶችን አሠልጥነን በሰሜን ጦር ግንባር ለማሰማራት ቻልን።

የብሄራዊ ውትድርና ግልጋሎት ሰጪ ምልምል ወጣቶችን ሥልጠና በተመለከተ የተገነቡት ማሰልጠኛ ተቋማት በአንዴ እስከ አንድ መቶ ሺህ ወጣቶችን የመቀበልና የማስተናገድ ችሎታ ስለአላቸው በየዓመቱ የሚሰለጥኑት ወጣቶች መጠን እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው ሊያድግ የሚችል ነው።

በየዓመቱ በመላ አገሪቱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚያጠናቅቁትና በአሥራ ስምንት ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወጣቶች ቁጥር ወይም መጠን የሚወሰን ቢሆንም በእቅድ ደረጃ በየሁለት ዓመት ማሠልጠን ይቻላል ተብሎ የተገመተው ከ20,000 እስከ 50,000 ወጣቶችን ነው።

የብሄራዊ ውትድርና ግልጋሎት ደንብ ሁለቱንም ፆታዎች ማለትም ወንዶና ሴቱ ወጣቶችን ያካተተ ቢሆንም ስለ ጦር ሜዳውና ስለ ሥልጠናው በሂደት በቂ ጥናት እስከደረግ ድረስ ለመጀመሪያዎቹ ተከታታይ ዓመታቶች ለመመልመል የታቀደው ወንዶ ፆታዎችን ብቻ ነበር።

በብሄራዊ ውትድርና ግልጋሎት ደንብ መሰረት በስድስት ወራት ወታደራዊ ሥልጠና ሂደት በየሁለት ዓመቱ ፈረቃ በአገሪቱ የምናካብተው የአገር መከላከያ ደጀን ሠራዊት መጠን ከዚህ ግርጌ እንደሚከተለው ይሆናል።

የሥልጠናው ጊዜ፣ የአገልግሎቱ ሂደትና የአገር መከላከያ ደጀን ሠራዊቱ ክምችት ምን እንደሚመስል ከዚህ ግርጌ ለአንባቢ ለማመልከት እሞክራለሁ።

በ1974 ዓ.ም በ20,000 ምልምል ወጣቶች የተጀመረው የብሄራዊ ውትድርና ሥልጠና በሃደት የሠራዊቱ መጠን በምን ሁኔታ እንደሚበራከት ከዚህ ግርጌ እንመልከት።

በ1974 ዓ.ም የብሄራዊ ውትድርና አገልግሎት የጀመሩት የመጀመሪያዎቹ 20,000 ምልምል ወጣቶች ከሁለት ዓመት አገልግሎት በኋላ ወደ ትምህርታቸው ወይንም እንደ የፍላጎታቸው ወደ የግል ሥራቸው ሲመለሱ አንደኛ ብሄራዊ የመከላከያ ተጠባባቂ ወይንም ደጀን ተብለው ይመዘገባሉ።

በ1974 ዓ.ም የብሄራዊ ውትድርና ግልጋሎት የጀመሩት ግልጋሎታቸውን ጨርሰው ሲመለሱ አንደኛ ብሄራዊ የአገር መከላከያ ተጠባባቂ ተብለው የተመዘገቡት ሁለተኛ ተጠባባቂ ይባሉና ሁለተኛዎቹ ምልምሎች አንደኛ ተጠባባቂ ይባላሉ።

በ1978 ዓ.ም የብሄራዊ ውትድርና ግልጋሎት ለሦስተኛ ጊዜ የጀመሩት ግልጋሎታቸውን ጨርሰው ሲመለሱ ከእነሱ በፊት የነበሩት ሁለተኛዎቹ ተጠባባቂዎች ሶስተኛ ተጠባባቂ ተብለው ይመዘገባሉ።

በዚህ ዓይነት ቅደም ተከተል ወይንም ሂደት የእድሜያቸውንም መጠን ብንመለከት በ1974 ዓ.ም የተመለመሉት የመጀመሪያዎቹ ምልምሎች በ1978 ዓ.ም የ22 ዓመት ወጣቶች ሲሆኑ፣ በ1976 ዓ.ም የተመለመሉት ሁለተኛዎቹ ምልምሎች የ20 ዓመት እድሜ ወጣቶች ይሆናሉ ማለት ነው።

የ1ኛ፣ የ2ኛና የ3ኛ ጊዜ ምልምሎች ቁጥር ሲደመር በስድስት ዓመታት ውስጥ አገራችን 60,000 ተጠባባቂ የአገር መከላከያ ደጀን ሠራዊት አደራጀች ወይንም አካበተች ማለት ነው።

በዚህ ዓይነቱ ስሌት የአስር ዓመቱን የሥልጠናና የግልጋሎት ሂደት ብናሰላ አገራችን በየአስር ዓመታቱ 100,000 አንድ መቶ ሺህ የመከላከያ ደጀን ሠራዊት ታካብታለች ማለት ሲሆን ይህ ሂደት በቀጠለ መጠን የደጀን ሠራዊቱ ቁጥር ወደ ሚሊየን ሊደርስ ይችላል።

አገራችን የውጭ ወረራ ስጋት ካለባትና የደጀን ሠራዊቱን መጠን ከፍ ማድረግ ከፈለገች በየሁለት ዓመታቱ የሚመለመሉትን ወጣቶች መጠን ከ20,000 ወደ 50,000 ማሳደግ ይቻላል።

የብሄራዊ ውትድርና ሥልጠናውና ግልጋሎቱ ምንጊዜም የማያቋርጥ ስለሆነ ከአገሪቱ የጦር ኃይል አባልነትና ከሚ ጠብቃቸው የክተት ጥሪ ነፃ የሚሆኑት እድሜያቸው ከ60 ዓመት በላይ የሚሆኑት ብቻ ናቸው።

ምዕራፍ አርባ ስምንት

4ኛ ኢትዮጵያ አገራችንን የራሷ የመከላከያ ኢንዱስትሪ ባለቤት ለማድረግ በተጠና ጥናት ላይ የተመሠረተ የግንባታ ዕቅድ።

የኢትዮጵያን ረጂም የህልውና ታሪክ ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመለከት በተለያዩ ጊዜያቶችና በተደጋጋሚ የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ጥመኞችና የአካባቢያችን ተስፋፊዎች የደፈሩንና ብለውም የወረሩን በሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት በጣም ኋላ ቀር በመሆናችንና ራሳችንን የምንከላከልበት የጦር መሣሪያ ለማምረት ባለመቻላችን ነው።

አውሮፓዊያን በኢኮኖሚ እድገት በአጠቃላይ በመከላከያ ኢንዱስትሪ ግንባታ በተለይ ጥለውን ከመሄዳቸው በፊት እኛም እናመርታቸው የነበሩት የክንድ መሣሪያዎቻችን በነፍጥ፣ በመትረየሶች፣ በመድፎች፣ ፈረሶቻችን በታንኮች ከመተካታቸው በፊት የደፈረን አገር አልነበረም።

የፋሽስት ኢጣሊያመንግሥት ወራሪ ሠራዊት በአስራ ዘጠነኛው ዓመተ ምህረት መባቻ የደረሰበትን ሽንፈት ለመቀበል በ1928 ዓ.ም ወረራ የረታንና አገራችንን የተቆጣጠረው የአገራችን ገበሬ ሠራዊት አይቶትና ሰምቶት የማያውቀውን ከሰማይ በአውሮፕላን የሚወረወር ቦምብና የሚረጭ ፈሳሽ መርዝ ጋዝ በመጠቀም ነው።

አሁን በቅርቡ ማለትም በ1969 ዓ.ም ጎረቤታችን የተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት የአገራችንን ድንበር 700 ኪ/ሜትር ጥሶ ከገባ በኋላ ነው ለመሣሪያ ሽመታ ወደ አውሮፓ የሄድነው።

ህልውናችንንና ክብራችንን አስከብረን በነፃነትና በሠላም መኖር ከፈለግን መከላከያ የሰው ኃይል ማደራጀት ብቻ ሳይሆን ራሳችንን የምንከላከልበት የጦር መሣሪያ ለማምረት መቻል አማራጭ የሌለው የመኖር ግዴታ ነው።

የብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ አመራር ጓዶች አዲስ የመከላከያ ኃይል በኢኮኖሚ ቁጠባ ዘዴ ከማደራጀት እቅድ ቀጥለን በሁለተኛ ደረጃ ያተኮርንበት ጉዳይ የመከላከያ ኢንዱስትሪ ግንባታ እቅደን ነበር።

አንድ አገር በተለይም ኢትዮጵያን የመሰለ ታዳጊ አገር የራሱን የአገር መከላከያ ኢንዱስትሪ ለመገንባት ሲያቅድ በጥንቃቄ መታሰብና መጠናት ያለባቸው አያሌና ውስብስብ የሆኑ በቅድሚያ ታሳቢ ጉዳዮች አሉ። ከእነዚህ ታሳቢ ጉዳዮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ።

1ኛ ለግንባታው የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠንና ከዚህ አንፃር የአገሪቱ አቅም፤

2ኛ በዓይነትና በመጠን በቂ የሆነ የሰለጠነ የሰው ኃይል፤

3ኛ ለኢንዱስትሪው ግንባታ ግብአት የሚሆኑ የተለያዩ የማዕድን ሀብት ውጤቶች፤

4ኛ ብረት ማዕድናትን ለማቅለጥና ኢንዱስትሪዎቹን ለማንቀሳቀስ የሚያስችል የኃይል ምንጭና ሥርጭት፤

5ኛ የራሳችንን የመከላከያ ኢንዱስትሪ በማቋቋም አሀዱ ብለን መሠረታዊ የሆኑ የቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ማድረግ ሳያስፈልገን ግንባታውን በአስቸኳይ ለመጀመር ይቻለን ዘንድ የተለያዩ የመከላከያ ቴክኖሎጂ ምንጮችን ወይንም ገበያዎችን (ላይሰንስ) መፈለግና ማግኘት ጥቂቶቹና ዋና ዋናዎቹ ነበሩ። እነዚህን መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች ካሟላን በኋላ ነው ወደ ኢንዱስትሪዎቹ ግንባታ ያመራነው።

የግንባታው አጀማመርና ሂደት በቴክኖሎጂ እረገድ በጣም ውስብስብ ካልሆኑት የጦር መሣሪያዎች ዓይነት በመጀመር በፍላጎታችንና በገንዘብ አቅማችን ላይ በተመሠረቱ ደረጃዎችና ቅደም ተከተሎች ጥናት ላይ ተመሥርተን ከዚህ የሚከተሉትን የኢንዱስትሪ ግንባታዎች ጀመርን

1ኛ በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ የኢምፔሪያሊስት ብሪታኒያ መንግሥት ጦር ከአገራችን ከወጣ በኋላ የምድር ጦር ሠራዊታችን የታጠቀው የቼኮዝላቫኪያ መንግሥት ሥሪት የሆነ «ቼኮዝ» በመባል የሚታወቅ ነፍጥ ወይንም ጠብመንጃ ስለነበርና የሚጎርሰውም ጥይት በቼኮዝላቫኪያ መንግሥት ትብብር በአገራችን ርዕሰ ከተማ በአዲስ አበባ በሚገኘው የጥይት ፋብሪካ ይመረት ነበር።

ከሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ጋር የመከላከያ ተራድኦ ውል በመዋዋል የአሜሪካን ሥሪት የሆኑ የጦር መሣሪያዎችን ስንቀበል የምድር ጦራችን ይገለገልበት የነበረው የቼኮዝሎቫኪያ መንግሥት ሥሪት የሆነውና ቼኮዝ በመባል የሚጠራው ጠብመንጃ የፖሊስ ሠራዊታችን ሲገለገልበት ቆይቶ በድህረ አብዮት የፖሊስ ሠራዊታችንም መሣሪያ የሶቭዬት ህብረት መንግሥት ሥሪት በሆነው «ኤ.ኬ.ኤም» ዘመናዊ አውቶማቲክ ጠብመንጃ በመለወጡ የቸኮዝን ጠብመንጃ ጥይት የሚያመርተው ፋብሪካ የተወሰነ የቴክኒክ ለውጥ አድርጎ «ማካሮቭ» በመባል የሚታወቀውን የሶቭዬት ህብረት ሥሪት ሽጉጥ የ«ኤ.ኬ.ኤም» አውቶማቲክ ጠብመንጃና የተለያዩ የሶቭዬት ህብረት ሥሪት የሆኑ መትረየስ ጥይቶችን እንዲያመርት በማድረጋችን ለመጀመሪያዎቹ ሦስት ዓመታት በየዓመቱ ስልሳ ሚሊዮን ጥይቶችን በማምረት እንዲጀምርና የጥሬ ምርት አቅርቦትና የማምረቻው ሥፍራ በተሻለ ሁኔታ ሲመቻች በየዓመቱ በቢሊዮን እንዲያመርት አቀድን።

2ኛ በዚሁ በ1974 ዓ.ም በሸዋ ክፍለ ሃገር በመናገሻ አውራጃ በሞጆ ወረዳ ከሰሜን ኮሪያ መንግሥት ጋር በተደረገ ትብብር መላው የመከላከያ ኃይላችንና የፖሊስ ሠራዊታችን የታጠቋቸውን የሶቭዬት ህብረት መንግሥት ሥሪት የሆኑ

አውቶማቲክ ሽጉጦች፣ አውቶማቲክ ጠብመንጃዎችንና የተለያዩ መትረየሶችን የሚያመርት ፋብሪካ ከአቋቋምን በኋላ በህዝባዊ ቻይና መንግሥት ትብብር በዚሁ በሞጆ የቀላል መሣሪያዎች ማምረቻ ፋብሪካ ጎን «ዘ23» በመባል የሚታወቅ ለእግረኛ ሠራዊት ውጊያና ለአውሮፕላን መቃወሚያ የሚያገለግል እጅግ ጠቃሚ የሆነ መሣሪያ የሚያመርት ፋብሪካ የሲቪል ግንባታው ሥራ እየተካሄደ ነበር።

3ኛ በሰሜን ኮሪያ መንግሥት ትብብር በሸዋ ክፍለ ሃገር በአምቦ አውራጃ ከ60 ሚ/ሜትር አዳፍኔ ጀምሮ የ81ሚ/ ሜትር አዳፍኔ፣ የ81 ሚ/ሜትር የማይራገጥ ፀረ ታንክ መሣሪያ፣ የ122 ሚ/ሜትርና የ130 ሚ/ሜትር መድፎች የተለያዩ ጥይቶችን፣ የተለያዩ የአውሮፕላን ቦምቦችና የእጅና የጠብመንጃ ቦምቦችንና የተለያዩ የመስክ ፈንጂዎችን የሚያመርት ፋብሪካ ተቋቁሞ የማምረት ተግባሩን ጀምሮ ነበር።

4ኛ ያለማንም ትብብር ወይንም እርዳታ በኢትዮጵያዊያን የተለያዩ ባለሞያዎች ጥረት ለመከላከያ ሠራዊታችን በጠቅላላ የሚያስፈልጉንን ትጥቆች ማለትም የውጊያ ቀበቶ የመጀመሪያ የህክምና መረጃ (set)፣ የልብስ መያዣ ከረጢት፣ (Duffel Bag) የመኝታ ከረጢት፣ ጀበርናና ማሲኖዳ፣ የውሃ ኮዳ ከነልባሱና ከነኩባያው፣ የብረት ባርኔጣ ከነገበሩ፣ የነፍስ ወከፍና የቡድን የተለያዩ ድንኳኖች በተለያየ መጠን ለአየር ወለድ ጦራችን መገልገያ የዝላይ ጃንጥላ ማምረቻ ፋብሪካ በናዝሬት ከተማ ተቋቁሞ የማምረት ተግባሩን ጀምሮ ነበር።

እነዚህ ከዚህ በላይ ከአንድ እስከ አራት ተራ ቁጥር የገለፅኳቸው የመከላከያ ኢንዱስትሪዎች በመጀመሪያ ደረጃ ያለ ብዙ ችግር በአጭር ጊዜ ውስጥ ያቋቋምናቸው ሲሆኑ ከዚህ ግርጌ ከአምስት እስከ ሰባት ተራ ቁጥር የምገልፃቸው በጣም ውስብስብ የሆነ የቴክኖሎጂ ደረጃ ውስጥ ያሉ ከባድ ኢንዲስትሪዎች በመሆናቸው ከፍ ያለ ገንዘብ የሚጠይቁ ብቻ ሳይሆኑ ግንባታቸውም ረዘም ያለ ጊዜ ስለሚወስድ የግንባታው ሂደት በጥንቃቄና ደረጃ በደረጃ ከዚህ በሚከተለው ቅደም ተከተል ለመገንባት ነበር ያቀድነው።

1ኛ በከባድ ኢንዱስትሪ ደረጃ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ከባድ መሣሪያዎች፣ ወታደራዊ መጓጓዣ የየብስ ተሽከርካሪዎች፣ ታንኮች፣ አውሮፕላኖችና መርከቦች ወዘተ በቀጥታ ለማምረት ከመሞከራችን በፊት በእጃችን ያሉትን የሶቪየት ህብረት መንግሥት ሥሪት የሆኑትን እስከ መጨረሻው በሚገባ ልንጠቀምባቸው እንድንችል ብቻ ሳይሆን ወደፊት በማምረቻ ኢንዱስትሪዎቻችን ውስጥ የሚሰሩት ባለሞያዎቻችን ቀደም ብለው በቴክኖሎጂው በቂ እውቀት ይኖራቸው ዘንድ ከፍ ያለውንና የመጨረሻውን ደረጃ ጥገና ማከናወን እንዲችሉ ማድረግ ነበር።

ማናቸውንም የጥገናና የመለዋወጫ እቃዎች የእደላ ተግባሮች በምዕራቡም ሆነ በምሥራቁ አገሮች ከ1ኛ እስከ 4ኛ ደረጃ ሲኖራቸው በአምስተኛ ደረጃ የሚከናወነው አዲሶቹን በኢንዱስትሪ ደረጃ ማምረት ነው።

በሌላ አነጋገር ማናቸውንም ነገር በኢንዱስትሪ ደረጃ ለማምረት በቅድሚያ የሚመረቱትን ቁሳቁሶች ጥገናና እደላ ከአንድ እስከ አራተኛ ደረጃ በሚገባ ማወቅና ብሎም የማምረት ችሎታን መገንባት ያስፈልጋል ማለት ነው።

2ኛ ከከፍተኛ የጥገናና የእደላ ደረጃ አቅም ግንባታ በኂላ ወደ ማምረት ተግባር ከመሄዳችን በፊት ከጥገናና ከእደላ ችሎታ ጋር የመለዋወጫ ዕቃዎችን ለማምረት የአንድን መሣሪያ መንኰራኩር፣ በተለይም የየብስ ተሽከርካሪዎችን፣ አውሮፕላኖችንና መርከቦችን የመሳሰሉትን ወደማምረት በመሄድ በቅድሚያ ከሞተራቸው በመለስ አብዛኛውን አንቀሳቃሾቻቸውን ወይንም የመለዋወጫ ዕቃቸውን ማምረትና ከሞተር በመለስ ሁለንተናቸውን የመገጣጠምና የማደስ አቅም መገንባት ያስፈልጋል።

በዚህ ዓይነት የመከላከያ ኢንዱስትሪ ግንባታ ሥልት መሠረት የኢትዮጵያ አብዮታዊያን በሚቀጥለው የአሥር ዓመት የጠቅላላ ልማትና ግንባታ ዕቅድ ወደ ጠቅላላ ኢንዱስትሪ አብዮት የሚወስደንን ከባድ የመከላከያ ኢንዱስትሪ ግንባታ የጀመርነው ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎች ነበር

3ኛ በሰሜን ኮሪያ መንግሥት ትብብር በአፋር ራስ ገዝ ክልል በአሰብ ወደብ ምሥራቅ ሃያ ኪ/ሜትር ርቀት ላይ በሚገኝና በዕፅዋት በተሸፈነ ነፋሻና ለምለም ግማሽ ደሴት ላይ በአፄ ካሌብ ስም የተሰየመ ለሠላማዊ ተግባርና ለባሕር ኃይላችን አገልግሎት የሚውሉ መርከቦችን መገጣጠሚያና ከሞተር በመለስ የተለያዩ የመለዋወጫ ዕቃዎችን ማምረቻ ኢንዱስትሪ ተቋቁሞ የመጀመሪያውን አንድ ሺህ ቶን ክብደት የምትጭን መርከብ ለሠላማዊ አገልግሎት ማምረት ተችሎ ነበር።

4ኛ ለሦስቱም የጦር ኃይሎቻችን የሚያስፈልጉንን የተለያዩ ዓይነትና መጠን ያላቸውን ወታደራዊ የመጓጓዣ ተሽከርካሪዎችን፣ ከ60 ሚ/ሜትር ጀምሮ የተለያዩ መጠን ያላቸውን አዳፍኔዎችን፣ የማይራገጡ ዐረ ታንክ መሣሪያዎችን፣ የተለያዩ መድፎችን፣ የተለያዩ ተዋጊ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎችንና ታንኮችን ወዘተ በ4ኛ ደረጃ የመጠገንና የማደስ ችሎታ ግንባታን አስቀድመን ብለንም የእነኝህን ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ወታደራዊ ተሽከሪካሪዎችና የጦር መሣሪያዎች መለዋወጫ ዕቃዎችን በማምረት የሚገጣጥምና ብሎም ወደ መፈብረክ ደረጃ የሚሸጋገር ግዙፍ የመከላከያ ኢንዱስትሪ በደብረ ዘይት ከተማ አካባቢ ሰባት መቶ ሺህ ካሬ ሜትር ስፋት ባለው መሬት ላይ የሲቪል ግንባታው ሰማኒያ በመቶ ተጠናቆ የመጠገኛ፣ የማደሻና የመፈብረኪያ መሣሪያዎቹም ሰማኒያ በመቶ ከሶቪየት ህብረት ተልከውልን ከፊሎቹ ቦታው ሲደርሱ ከፊሎቹ በአሰብ ወደብ ይገኙ ነበር። መረጃዬ ትክክል ከሆነ ወያኔ አዲስ አበባ በገባ ማግሥት መሣሪያዎቹን ወደ መቀሌ ወስዷቸዋል።

5ኛ አውሮፕላኖችን ማምረቻ ኢንዱስትሪ ግንባታ ለመጀመር የሚያስችለን ልምድ ለማግኘት በካናዳ መንግሥት ትብብርና ላይሰንስ ባፈሎ በመባል የሚጠራ አነስተኛ አውሮፕላን ለአገሪቱ የግብርና አገልግሎት እንዲውል በኢትዮጵያ አየር መንገድ

የጥገናና የእደላ ተቋም ውስጥ ባሉ ባለሞያዎች የጀመርነው አይሮፕላንን የመገጣጠም ተግባር ውጤታማ ስለነበር በዚህ ልምድና ጥናት ላይ ተመስርተን፣ የአየር መንገዳችንና የአየር ኃይላችን ተቋማት ባላቸው ልዩ ልዩ የሰለጠኑ ባለሞያዎች ቅንጅት ለሠላማዊና ለወታደራዊ ጉዳይ የሚያስፈልጉንን አውሮፕላኖች ማምረት የሚያስችለን እቅድ ከደፍን በኋላ በአገራችን የአቪዬሽን ቴክኖሎጂን ለማስፋፋትና ደረጃ በደረጃ በሚከናወን የግንባታ ሂደት የራሳችንን አውሮፕላኖች ለሠላማዊና ለጦር አገልግሎት የማምረት አቅም ለመገንባት እንድንችል የሁለቱ ተቋማት ማለትም የኢትዮጵያ አየር መንገድና የኢትዮጵያ አየር ኃይል ባለፈው ሰላሣ ዓመታት ውስጥ ያካበቱትና ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ የአውሮፕላኖች ጥገናና እደላ ችሎታ ባሻገር በቅርቡ አየር መንገዳችን በአሳየን የመገጣጠም ውጤት በመበርታትና ከሕንዶች ተመክሮ በመማራችን ሁለቱም ተቋማት ለጋራ ጥቅም በጋራ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሞተር ማነፅ በመለስ የመለዋወጫ ዕቃዎችን የሚያመርቱበትና አውሮፕላኖችን የሚገጣጥሙበት ኢንዱስትሪ በደብረ ዘይት ከተማ በሚገኘው የአየር ኃይላችን የጦር ሠፈር አቅራቢያ የሲቪል ግንባታው ሥራ ስልሳ በመቶ ያህል ተጠናቆ ነበር።

ምዕራፍ አርባ ዘጠኝ

5ኛ በአገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የሲቪል መከላከያ ተቋም ስለመፍጠር ዕቅድ::

ከአገራችን የረጂም ጊዜ ታሪክ ለመረዳት እንደሚቻለው ከቱርኮችና ከአረብ ተስፋፊዎች፣ ከአውሮፓ የቅኝግዛት ኃይሎች በተደጋጋሚ በተሠነዘሩብን ወታደራዊ ወረራዎች የጥቃቱ ገፈት ቀማሽ አገሩን ከወራሪዎች ጥቃት ለመከላከል በውጊያው የመጀመሪያ ረድፍ የሚሰለፈው የገበሬ ተዋጊሠራዊት ቢሆንም ዋናው ተጎጂና የጥቃቱ ሰለባ የአገሪቱ ሰፊ ህዝብ መሆኑ የታወቀ ነው::

ወራሪው የጠላት ሠራዊት በቀጥታ ከሚሠነዝርበት ወታደራዊ ጥቃት ባሻገር የሚዘረፈው፣ ቤትና ንብረቱ የሚፈርሰው፣ ቤትና ንብረቱን ጥሎ የሚሰደደውና ጠቅላላ ኑሮው የሚናጋው ሰፊው ህዝብ ነው:: በየጊዜው የሚከሰቱ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎችም ሰለባ ሰፊው ህዝብ ነው::

በረዥሙ ታሪካችን ሂደት በአገራችን ታዩ፣ ወይንም ደረሱ የተባሉትን ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ወደ ኋላ ብዙ ሄደን ማስታወስ ሳያስፈልግ በቅርቡ በታላቁ ማህበራዊ አብዮታችን መዳረሻ በተከታታይ የአየርን ብረት ቀውስ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የተጎዳውና በዓለም ህዝብ ፊት ለአሰቃቂ ርሃብና ሞት የተጋለጠው ወይም የተዳረገው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው::

በየጊዜው የተሰነዘሩብንን የባዕዳን ወታደራዊ ጥቃቶች በመመከት ቀደም ብለን እንደ አለመዘጋጀታችን ሁሉ በሌሎቹም ሰው ሠራሽና ተፈጥሮ ያመጣቸውን ቀውሶችና አደጋዎችን ለመከላከልና ለመቋቋም አንዱም ተሰናድተን ወይንም ተዘጋጅተን እንደማናውቅ ማስረጃው ይሄው እስከዛሬ ማለትም ይህንን የአብዮታችንን ታሪክ ቅፅ ሁለት እስክፅፍ ድረስ የአየር ንብረት ቀውስ ባስከተለው ችግር የደረሰብንን የእህል እጥረት ማሟላት ተስኖን ከባዕዳን እህል ተመፅዋች ከሆንን ዓመታትን ብቻ ሳይሆን ዘመናትን በማስቆጠር ላይ መገኘታችን ነው::

በእነኝህ በታሪክ አልፎ አልፎ በሚደርሱ ሰው ሠራሽና ተፈጥሮ በሚያመጣቸው አደጋዎችና አውዳሚ ክስተቶች ተጠቂ እኛ ብቻ ሳንሆን በአብዛኛው የዓለም ኋላ ቀር አገሮች ላይ የደረሱና በመድረስም ላይ መሆናቸው የታወቀ ነው::

የሠለጠኑት በእድገት ብዙ የቀደሙንና በሳይንስና ቴክኖሎጂ የለሙት አገሮች በጦርነትና በተፈጥሮ ወዘተ በሚደርሱ አደጋዎች ህዝባቸው ሳይጎዳ ለማዳን የሚነድፏቸው እቅዶች አደጋዎቹ ከመድረሳቸው በፊት ቀድመው የሚያከናውኗቸው ከአደጋዎቹ መከላከያ ወይንም መዳኛ የሆኑ መሰናዶዎችና አደጋዎቹ ሲደርሱ

ህዝባቸው የአደጋዎቹ ሰለባ ከመሆኑ በፊት ፈጥነው የሚወስዷቸው የአደጋ መከላከል ርምጃዎች ወይንም የሥራ ክንውኖች የሲቪል መከላከል ይባላል።

በታሪክ አጋጣሚ በቅድመ አብዮት የሰሜን አሜሪካንን መንግሥት፣ በድህረ አብዮት የሶቭዬት ህብረትን መንግሥት የሲቪል መከላከያ ተቋማት በመጎብኘት ተቋሞች የተቋቋሙበትን ዓላማና የሚያከናውኗቸውን የተለያዩ ተግባሮች በዝርዝር ለማወቅና ለመማር እድል ገጥሞኛል።

በእነኝህ ሁለት ኃያላን መንግሥታት አገሮች የተመለከትኳቸው የየአገራቸውን የሲቪል መከላከያ ተግባር የሚያጠኑ፣ የሚመራመሩና የሚመሩ ተቋማት በጣም ሰፊና ውስብስብ የሆኑ ተግባሮችን የሚያከናውኑ በመሆናቸው የተለያዩ አያሌ ባለሞያዎችን ያካተተ ከፍ ያለ የሰው ኃይል ያላቸው ናቸው።

የተቋማቸውን አቅምና ደረጃ በዝርዝር ማወቅ ባይቻልም ከሌሎች የምዕራብና የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች እንደ ብሪታኒያ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ህዝባዊ ቻይናና ሰሜን ኮሪያን ወዘተ የመሳሰሉት አገሮች የሲቪል መከላከያ ተቋማት እንደአሏቸው ይታወቃል።

የሲቪል መከላከያ ተቋሞችን አቋቁመው በመገልገል የተለያዩ የአደጋ መከላከል ተግባሮችን በማከናወን ከታወቁ አገሮች በተገኙ ልምዶች የታወቁ የአደጋ መከላከል ተግባሮችን ከዚህ ግርጌ በተመለከቱት ሁኔታዎች፣ አደጋዎቹ ከመድረሳቸው በፊት መደረግ ያለባቸውን ልዩ ልዩ መሰናዶዎችን ወይንም ዝግጅቶችንና አደጋዎቹ ከደረሱ በኋላ በሕዝብ ላይ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት መወሰድ ካለባቸው ርምጃዎች ዋና ዋና የምንላቸውንና ጥቂቶቹን ብቻ ከዚህ እንደሚከተ ተለው ለመግለፅ እሞክራለሁ።

ሀ) በመደበኛና በኒዉክሌር ጦርነቶች በህዝብ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለመከላከል ከሚደረጉ መሰናዶዎችና ከደረሱ በኋላ መወሰድ ካለባቸው ርምጃዎች ዋና ዋናዎቹና ጥቂቶቹ፤

1ኛ የምግብ፣ የመጠጥና ውሃ፣ የጤና አገልግሎቶችን ከመስጠት ጋር ህዝቡን ከአውቶሚክ ቦምብ አደጋዎች የሚያድኑ ከመሬት ወለል በታች ጥልቀት ያላቸውን መጠለያዎች (ባንከሮች) የጠላት ዒላማ ሊሆኑይችላሉ ተብለው በሚታሰቡ ከተሞችና የህዝብ መናኸሪያዎች በብቃት መገንባት፤

2ኛ የኬሚካልና የባዮሎጂካል መሣሪያዎች ከሚያደርሷቸው አደጋዎች ህዝቡ ራሱን ይከላከል ዘንድ የሚታደሉትን የፊት መከላከያ (ማስክ) አልባሳትና መጫሚያዎች ለህዝቡ በብቃት ለማደል በሚያስችል ሁኔታ አምርቶ ማስቀመጥ፤

3ኛ በአውቶሚክ ቦምብ ምቶች፣ በጨረራቸው፣ በኬሚካልና ባዮሎጂካል መርዞች ወዘተ በህዝብ ላይ የሚያስከትሏቸውን የተለያዩ ጠንቆች መፈወሻ መድሃኒቶችና

በተለይ የእነዚህ ጠንቆች መፈወሻ የሆኑ ልዩ የሕክምና አገልግሎት ተቋሞችን ማዘጋጀት፤

4ኛ በኒውክሌር ጦርነት ጊዜ ህዝቡ የሚገለገልባቸውና አገሪቱም ወታደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ወዘተ የሆኑ ተግባሮችን በጦርነቱ ጊዜ እንደልብ ማንቀሳቀስ ያስችሏት ዘንድ ከመሬት ወለል በታች በጥልቀት መገናኛዎችን ማለትም የምድር ባቡሮችንና የየብስ ተሽከርካሪ መንገዶችን ማዘጋጀት፤

5ኛ ጦርነቱ ለረጂም ጊዜ የሚካሄድ መደበኛ ወይም የኒውክለር ወይም የሁለቱም ዓይነት መጠነ ሰፊና አገር ዓቀፍ ከሆነ ህፃናትን፣ ከእንስሶችም ቢያንስ የሥጋና የወተት ከብቶችን፣ በጤና መታወክና በእርጅና ራሳቸውን መርዳት የማይችሉ ደካማ አዛውንቶችን ጦርነቱ ወደ ማይደርስበት ወይም የሚደርሰው ጉዳት ቀለል ወዳለበት ክልል ለማግለል የሚያስችል መሰናዶ ማድረግ፤

6ኛ ጦርነቱ ለረጂም ጊዜ የሚካሄድ መደበኛ ወይንም የኒውክሌር ወይም የሁለቱም ዓይነት መጠነ ሰፊና አገር ዓቀፍ ከሆነ አገራቸውን ከባዕድ ጥቃት ሲከላከሉ አካላተ ጎዶሎ የሆኑ ጀግኖች ከሚታከሙባቸው ሆስፒታሎች ሌላ ከሆስፒታል ወጥተው ለረጅም ጊዜ የሚያገግሙበት ሰው ሠራሽ አካል እንደ ጉዳታቸው ዓይነት የሚያገኙበት፣ ራሳቸውን የማይረዱ ሥራ አልባ በመሆንና ከህብረተሰቡ በመገለል ተስፋ እንዳይቆርጡ በየግል ዝንባሌያቸውና በአቅማቸው መጠን የተለያዩ የዕደ ጥበብና ሌሎችንም ሞያ በማስተማር ጀግኖችን የሚያገለግል ልዩ የጀግኖች አምባ ማደራጀት፤

7ኛ ወላጆቻቸው የጦርነት ሰለባ ሆነው አሳዳጊ ላጡ ህፃናት አስፈላጊውን እንክብካቤ እያደረገ በማስተማር የሚያሳድግ የህፃናት አምባ ማደራጀትን የመሳሰሉት ተግባሮች ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው።

ለ) አልፎ አልፎ በሚከሰቱ ሰው ሠራሽና ተፈጥሮ በሚያመጣቸው የአየር ንብረት ቀውሶችና የተለያዩ አፍራሽና አውዳሚ ክስተቶች በህዝብ ላይ ከፍተኛ አደጋዎችን አድርሰው ህዝቡ ከመጎዳቱ በፊትና አደጋዎቹ ከደረሱም በኋላ ለምሳሌም፤

1ኛ ከባድ ንፋስ ከውቅያኖስ በሚያነሳው ውሃና ጎርፍ፣ ያላቋረጠ ከባድ ዝናብ፣ በረዶ፣ ዋግ፣ አንበጣ፣ የተለያየ ፀረ ሰብል ህዋሳት፣ የትል ሠራዊት፣ ያላቋረጠ ድርቅና ሰደድ እሳት የአገሪቱ አርሶ አደሮች ዓመት የደከሙባቸውን አዝርዕቶች አጥፍተው በአገር ላይ ረሀብ ከመፈጠሩ በፊት የእሳት አደጋ መከላከያዎችን፣ ፀረ ተባይ ንጥረ ነገሮችን ወዘተ የመሳሰሉ መከላከያዎች ከማሰናዳት ባሻገር እነዚህን በመሳሰሉ ፀረ ሰብል አደጋዎች በአገር ላይ የእህል እጥረት ተፈጥሮ ህዝብ እንዳይራብ የሲቪል መከላከያ ተቋም ቢያንስ ለአስር ዓመታት ያህል ህዝቡ የሚመገበው ተጠባባቂ እህል በዘመናዊ ጎተራዎች አካብቶ መገኘት፤

2ኛ ሰውንና እንስሶችን በማጥቃት ከፍተኛ ጉዳትና እልቂት ሊያደርሱ የሚችሉ የሰውና የእንስሳ ጤና ጠንቆችን፣ ተላላፊ በሽታዎችና የተለያዩ ደዌዎች ቢፈጠሩ ለመከላከል የሚያስችሉ መድሃኒቶችን በማስመረት አዘጋጅቶ ማስቀመጥ፤

3ኛ ሰብሎችን ከማውደም ባሻገር ለሰው ህይወት አደጋን የሚያስከትሉ ከፍተኛ ጎርፎችና የውሃ ሙላቶች፣ ሰደድ እሳት፣ እሳተ ጎሞራና የመሬት መንቀጥቀጥ ከታየባቸው ክልሎች ነዋሪውን ህዝብ በአስቸኳይ የሚያገልሉ፤ የአየር፣ የባህርና የየብስ መጓጓዣዎችን አዘጋጅቶ መገኘት፤

4ኛ ህዝቡን ከአደጋ ክልሎች ከማግለል ጋር ለህዝቡ ጊዜያዊ መጠለያ የሚሆኑ ድንኳኖችን፣ ተንቀሳቃሽ ቤቶችን፣ የቀንና የሌሊት አልባሳቶችን፣ ጊዜያዊ ማብሰያና መመገቢያ ዕቃዎችን፣ በውጊያ ጊዜ ለአገር መከላከያ ሠራዊት በሚቀርበው ዓይነት ጊዜያዊና ነፍስ አድን ምግቦችንና የጤና አገልግሎቶችን ማቅረብን የመሳሰሉት ተግባሮች ከብዙዎቹ ጥቂቶች ናቸው።

የሲቪል መከላከያ ተቋማትን ከአቋቋሙ የተለያዩ አገሮች ልምድና በራሳችንም ጥናት ላይ ተመሥርተን በአገራችን የሲቪል መከላከያ አገልግሎት ለማቋቋም ያቀድነው በአገራችን ሰሜናዊ ክልል አገር ገንጣዮች በሚያካሂዱት የትጥቅ ሴራና ገንጣዮቹን ከመርዳት ባሻገር ህዝባዊ አብዮታችንን ለመቀልበስ ዓለም ዓቀፍ ኢምፔሪያሊዝምና የአካባቢው አድህሮት ያወጁብን ጦርነት ባስከተለው ከፍ ያለ ጉዳት ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናትና አገርና አብዮትን ለማዳን ሲፋለሙ የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን ጀግኖቻችንን ለመንከባከብ ያቋቋምናቸውን የህፃናት አምባንና የጀግኖች አምባን በ1966 ዓ.ም በወሎና በትግራይ ክፍለ ሃገራት ድርቅ ባስከተለው ከፍተኛ አደጋ ምክንያት አገራችን የተቋቋመውን የአገር ውስጥና የውጭ አገር እርዳታ አስተባባሪ ኮሚሽን ጋር በማካተት ለሥራው የሚያስፈልጉትን ተጨማሪ የተለያዩ የሥራ ዘርፎችን አቋቁሞ የሚመራ የሲቪል መከላከያ ሚኒስቴር ለማቋቋም ሲሆን ከሌሎቹ ጋር ማለትም ከአገር መከላከያ ኢንዱስትሪና ከብሄራዊ ውትድርና አገልግሎት ጋር ፈጥነን ለማቋቋም ያልፈለግነው ከዚህ በኋላ ልናካሂድ ያቀድነውን ብሄራዊ የምርት ዘመቻ የሚያካሂድ ወይንም የሚያስፈፅም የሠለጠነ የሰው ኃይል ከማሰባሰባችንና ድርጅታዊ አቅም ከመገንባታችን በፊት ቸኩለን የውጭና የአገር ውስጥ እርዳታ የሚያሰባስበው፣ የሚያስተባብረውና የሚያከፋፍለው የእርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን የሚሰጠውን አገልግሎት በመግታት ህዝቡን የባሰ ችግር ላይ እንዳንጥለው በማሰብ ነው።

ክፍል ሃያ ሦስት

ምዕራፍ ሃምሳ

ብሄራዊና አብዮታዊ የምርት ዘመቻ

በአገራችን በኢትዮጵያ በሳይንስና ቴክኖሎጂየ ተደገፈ የግብርና ልማት ለማካሄድ ባለመብቃታችን በገበሬዎቻችን የተፈጥሮ ዕውቀትና ልማድ ብቻ ይከናወኑ ከነበሩት ኋላ ቀር የግብርናውና ከንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ በስተቀር በኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ በኩል ምንም ዓይነት ልማትና ግንባታ እንዳልጀመርን ይታወቃል።

ዘመናዊ እርሻዎች፣ የማዕድናት ፍለጋና ቁፈራዎች፣ የተለያዩ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን ግንባታ፣ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች፣ የተለያዩና ዘመናዊ የሆኑ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ተቋማትን መገንባት የጀመሩት በአምስቱ ዓመታት የወረራ ዘመናቸው ኢጣሊያኖች እንደሆኑ ይታወሳል።

ኢጣሊያኖች ከአገራችን ከወጡ በኋላ ከ1933 ዓ.ም እስከ 1940 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያዊያን የተደረጉ ጥረቶች፣ የኢጣሊያኖች ሥሪትና ቅሪት የሆኑት ኢንዱስትሪዎች የማምረት ተግባራቸውን ሳያቆሙ በሙሉ ኃይላቸው እንዲያመርቱ ለማድረግ እንጂ ተጨማሪ ወይንም አዲሶችን ለመገንባት ግዜውም አቅማችንም አልፈቀደልንም።

ፋሽስቱ የኢጣሊያ መንግሥት ቅኝግዛቱ ሊያደርገን ከአንዴም ሁለት ጊዜ በፈፀመብን ወረራ ያደረሰብንን ታሪክ የማይረሳውን ግፍ የተሞላውን ጥቃትና በደል ለመካስ ያለው ይመስላል ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከጦርነቱ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ኢጣሊያንን በጎበኙበት ጊዜ በተፈጠረው እርቀ ሠላም ምክንያት በሁለቱ አገሮች መሃከል መልካም ግንኙነትና ወዳጅነት በመፈጠሩ ከተዋዋሏቸው የተለያዩ የወዳጅነት፣ የትብብርና የተራድኦ ውለታዎች ሁሉ በኢትዮጵያዊያን በኩል ከፍተኛ ግምት ከተሰጣቸው ውሎች የመጀመሪያው ዱቼ ሙሶለኒ ይኖርበት የነበረውን ታላቅ የኢጣሊያ ቤተመንግሥት በሮም ከተማ የሚገኘው የኢትዮጵያ መንግሥት አምባሳደር መሥሪያና መኖሪያ ቤት እንዲሆን የኢጣሊያ ህዝብ ምክር ቤት መስጠቱ፤

ሁለተኛው፤ በሁለተኛው ወረራቸው ማለትም፣ በ1928 ዓ.ም አገራችንን ወረው ርዕሰ ከተማችንን አዲስ አበባን ከተቆጣጠሩ በኋላ በዘረፋ ከጥንቱ የአገራችን ርዕሰ ከተማ ከአክሱም ነቅለው የወሰዱትን ሃውልት ለመመለስ በመስማማታቸውና ሦስተኛው የአዋሽን ወንዝ ቆቃ ላይ በመገደብ የኤሌትሪክ ኃይል ማመንጫ በመሥራታቸው እንደሆነ ይታወሳል።

በዚህ አጋጣሚ ለአንባቢ መግለፅ ያለብኝ ኢጣሊያኖች በእብሪትና በህገወጥነት በጦር ኃይል በመውረር ያደረሱብንን ከፍ ያለ ጉዳትና በደል ለመካስ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ህዝብ ማንነት በመገንዘባቸውና በአደረባቸው አክብሮት ለኢትዮጵያ ህዝብ ክብር ይመጥናል ያሉትን ውብና ታላቅ የኢጣሊያ ህዝብ ቤተ መንግሥት ከሰጡን በኋላ በጊዜው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አማካሪዎች የነበሩ ደካማ ሰዎች «የኢትዮጵያ አምባሳደር ግርማዊነታቸው በአዲስ አበባ ከሚኖሩበት እጅግ በላቀና በተዋበ ቤተመንግሥት ውስጥ መኖር አይገባውም» በማለት ንጉሡን አሳስተው ቤተመንግሥቱ እንዲሸጥ በማድረግ የኢጣሊያ ህዝብ ምክር ቤት መማክርትና የኢጣሊያ መንግሥት አመራር አካላት ተስማምተው በህብረት ከሰጡን ከፍ ያለ ግምትና ከፍ ያለ የአክብሮት ሥፍራ የኢትዮጵያን ህዝብ አውርደው በመጣል ለአጉል ዝቅተኛ ግምትና ለመናቅ ዳርገውናል። ቤተ መንግሥቱ የተሸጠበት ገንዘብ ለኢትዮጵያ መንግሥትና ህዝብ አንዳችም የሚፈይደው ነገር አልነበረም።

ቤተመንግሥቱ የተሰጠው የአፄ ኃይለሥላሴን ጉብኝት ምክንያት በማድረግ ለሚወክሉትየኢትዮጵያ ህዝብ እንጂ በግል ለንጉሡ የተሰጠ ሥጦታ አልነበረም።

የኢትዮጵያን መንግሥትና ህዝብ የሚወክለው አምባሳደርና የኤምባሲው ኢትዮጵያዊያን ሠራተኞች ለመሥሪያና ለመኖሪያ ቤትነት ቢገለገሉበት ችግሩ አይታየኝም።

የንጉሡ አማካሪዎች ትልቅ ችግር ሆኖ የታያቸው በማዕረግ ፕሮቶኮልና እንዲሁም በሥልጣኑ ከእነሱ በታች የሆነው አምባሳደር የሚኖርበት ንጉሡ አፄ ኃይለሥላሴ በአዲስ አበባ ከተማ ከሚኖሩበት ቤተ መንግሥት የላቀና የተዋበ መሆኑ የንጉሡን ክብር ዝቅ የሚያደርግነው በማለት አስበው ከሆነ ቤተ መንግሥቱን በሮም ከተማ የኢትዮጵያ ህዝብ የታሪክ መዘክር በማድረግ የረጂም ጊዜ በነፃነት የመኖር ህልውናችን፣ የጥንታዊ ሥልጣኔያችንና የረጂም ዘመን አይበገሬ ታጋይነታችንን ለኢጣሊያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ሮምን ወይንም ኢጣሊያንን ለሚጎበኙ የዓለም ህዝቦች በማሳወቅ ከሚኖረው የታሪክ ፋይዳ ይልቅ ምናልባት እነኛ ደካማ የንጉሡ አማካሪዎች ከኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክና ክብር በላይ ግምት የሰጡት ለገንዘብ ግኝት ከሆነም ኢጣሊያኖች በበኩላቸው ቤተ መንግሥታቸውን ለኢትዮጵያ ህዝብ በመስጠታቸው የሚኖረውን የታሪክ ፋይዳ በመገንዘብ የሰጡንን ቤተመንግሥት መልሰን ለእነሱው በመሸጥ ራሳችንን በማዋረድና በመቅለል ሳንናቅ ተከብረን የታሪክ ቤተ መዘክሩን ለዘላለም የማያቋርጥ የገንዘብ ምንጭ ማድረግ ይቻል ነበር ካልኩ በኋላ ወደ ተነሳሁበት ርዕስ ወደ ብሄራዊ የምርት ዘመቻው እመለሳለሁ።

በዚህ ጊዜ ውስጥ የኢጣሊያ መንግሥት ብቻ ሳይሆን የስዊድን፣ የሕንድ፣ የጃፓንና የሆላንድ ወዘተ መንግሥታት ድርጅቶች ግለሰቦችና የዓለም ባንክ በገንዘብ

ብድርና ስጦታ፣ በጋራ ልማትና በቴክኒክ አገልግሎት ድጋፍና ትብብር አድርገውልናል።

ምዕራፍ ሃምሳ አንድ

አገራችን ለማዕድን ፍለጋ፣ ለውሃ ጥናት ልማት ለዘመናዊ የግብርና ልማትና ለኢንዱስትሪ ግንባታ የተንቀሳቀሰችበት ጊዜ።

ከ1950 ዓ.ም መባቻ ጀምሮ እስከ 1961 ዓ.ም መገባደጃ ድረስ በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ አገራችን ለማዕድን ፍለጋ፣ ለውሃ ጥናት ልማት፣ ለዘመናዊ የግብርና ልማትና ለኢንዱስትሪ ግንባታ የተንቀሳቀሰችበት ጊዜ ነበር ለማለት ይቻላል።

ይህ የኢኮኖሚ ግንባታ መልካም ጅምር በጥቂቱም ቢሆን ለሥራ ፈላጊ ወገኖቻችን የሥራ ግኝት፣ ለህዝቡም እንዲሁ በጥቂቱ የኑሮ መሻሻልና ለኢኮኖሚው ዕድገት ከፍ ያለ ተስፋ የፈነጠቀ ሁኔታ ለአሥር ዓመታት ያህል እንኳ ርቆ ሳይሄድ ከ1961 ዓ.ም መጀመሪያ ጀምሮ የተለያዩ ተከታታይ የሆኑና በኢኮኖሚው ላይ ጥላቸውን ያጠሉ ቀውሶች ስለገጠሙን የተጀመረው የኢኮኖሚ ዕድገት ወደፊት መራመድ አቅቶት አዘቅዝቆ ወደ ኋላ መሄድ ጀመረ።

እነኝህን ከአገራችን ውስጥ የመነጩ ብቻ ሳይሆኑ ከአካባቢያችንና ከዓለም ዓቀፉ የወቅቱ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችጋር የተሳሰሩና ብዙ ፈርጅ ያላቸውን ችግሮች በኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ አንድ መግቢያ የአብዮቱ መቃረቢያ፣ ዋዜማና አጥቢያ ወዘተ በማለት በዝርዝርና በጊዜ ቅደም ተከተል የገለፅኳቸው ቢሆንም ቅፅ አንድን አግኝተው ለማንበብ ላልቻሉ አንባቢዎች ግንዛቤ ከዚህ እንደሚከተለው ቢያንስ ጠቅለል ባለሁኔታ አሳጥሬ በድጋሚ መግለፅ ጠቃሚ ይመስለኛል።

1ኛ የኛ ትውልድ አይቶት በማያውቀው ሁኔታ ለተከታታይ ዓመታቶች ያላቋረጠ የዝናብ እጥረትና ድርቅ የኤርትራን፣ የትግራይን፣ የወሎን፣ የአፋርን አስተዳደር፣ ከፊል ሸዋን በተለይም የሰሜኑንን ክልልና የሐረርጌን ክፍለ ሃገራት ስለገጠማቸው የእህል እጥረትና የከብቶ ግጦሽ እጦት፣ ርሀብና ችጋር በመፈጠሩ ምክንያት በሰዎችና በእንስሶች ላይ ሞትን ሲያስከትል በተለይ በወሎና በትግራይ ክፍለ ሃገራት ነዋሪ በሆኑ አያሌ ወገኖቻችን ላይ ያደረሰው እልቂት ዓለምን እንዳስደነገጠና እንዳስለቀሰ ይታወሳል።

2ኛ አረቦች የነዳጅ ዘይትን ከእሥራኤል ጋር ለሚያደርጉት ትግል እንዲረዳቸው በማለት በዓለም የነዳጅ ዘይት ዋጋ ላይ የፈጠሩት የዋጋ ማናርና ብሎም በነዳጅ ዘይት የገበያ አቅርቦት ላይ የመጠን ማዕቀብ ማድረጋቸው በዓለም ፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ላይ ከፍ ያሉ ቀውሶችን ሲያስከትል የሲዊዝን ቦይ ወይንም የባሕር መንገድ መዝጋታቸው በአፍሪካ ቀንድ አገሮች ላይ በአጠቃላይ በአገራችን በኢትዮጵያ ላይ በተለይ በቡሀ ላይ ቆረቆር እንዲሉ ታላቅና ውስብስብ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ላይ በወደቅንበት ጊዜ አረቦች አሰልጥነው፣ አደራጅተውና አስታጥቀው

ያዘመቱብን የኤርትራ ገንጣዮችና እንዲሁም ተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት እያሰረገ ወደ አገራችን የሚያስገባቸው ሽብር ፈጣሪዎች የአገራችንን ሠላምና ፀጥታ እንደ ኢኮኖሚው ክፉኛ በማቃወስ በአገራችን ሰሜን፣ ምሥራቅና ደቡብ ክልሎች ስለሚወጉን ከፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ወዲህ የኢትዮጵያ ህዝብ ሠላምና ፀጥታ ያጣበት ጊዜ ነበር።

ጉልተኞችና ፊውዳል የመሬት ከበርቴዎች በሚያደርሱበት በደልና ገደብ አልባ ምዝበራ በእጅጉ የተሰቃየው የኢትዮጵያ ገበሬ፣ ተፈጥሮ ባደረሰበት ቀውስና የተለያዩ ችግሮች ምክንያት እንደ ወትሮው የኢትዮጵያን ህዝብ ሊመግብ ቀርቶ ራሱ በድህነት ከመሰቃየት አልፎ በምግብ እጦት በሚሞትበት ጊዜ የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት «በአገራችን ምንም ዓይነት ድርቅና የእህል ችግር የለም። የሌለውን ነገር እየፈጠሩ በኢትዮጵያ ድርቅ እንደገባና የእህል እጥረት እንደተፈጠረ አድርገው የሚያወሩና የሚያስወሩ፣ በአገሪቱ የውጭ ጠላቶች የተገዙ አንዳንድ ምንደኛ ግለሰቦች ናቸው» በማለት በብዙሃን ማሰራጫዎች በመለፈፍ ከውጪው ዓለም ህዝብ ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያም ህዝብ ርሀቡን በመደበቁ ቀውሱ ከኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግርነት አልፎ ወደ ፖለቲካና ወደ ጠቅላላ ህዝባዊ አመፅ ተሸ ጋገረ።

በአገራችን በኢትዮጵያ በተከሰተው ከባድ የአየር ንብረት ቀውስ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ፣ በአገሪቱ የተለያዩ ማዕዘናት የተጀመረው የብሄረሰቦች ንቅናቄ፣ በአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ፣ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ወዘተ የተጀመረው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ፣ ራሳቸውን «ጀብሐና ሻዕቢያ» ብለው የሚጠሩ አገር ገንጣዮች በኤርትራ በሚያካሂዱት የትጥቅ አመፅ ወዘተ የተወጠረው የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በአገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በአገሪቱ ላይ የደረሰውን ከባድ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ያቃልልኛል ብሎ በማመን የነዳጅ ዋጋ መጨመርና በተለይም በህግ ያወጀው የቁጠባ ኢኮኖሚ ምንም ዓይነት ፋይዳ ሳያስገኝ እንደውም ተጨማሪ ችግር በመሆን የህዝቡን ቁጣ በማባባስና በማቀጣጠል የአገሪቱን የፖለቲካ ትኩሳት በበለጠ አጋለው።

መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከዳር እስከዳር ትዕግስቱ በመሟጠጡና ቁጣው አፍ ገደፉን አልፎ በመፍሰሱ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ ማህበራዊ አብዮት ፈነዳ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ያስታወስ እንደሆነ አብዮታዊው ደርግ ራሱን አቋቁሞ ህልውናውን ካሳወቀ በኋላ ቀዳሚና የመጀመሪያ አብዮታዊ ተልዕኮው ወይንም ተግባሩ አድርጎ የወሰደው ርምጃ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት የደበቀውን ርሐብ ማጋለጥ ነበር።

አገራችን ባላት ብዙሃን ማሰራጫዎች ሁሉ በአገራችን ላይ በአጠቃላይ በትግራይና በወሎ ክፍለ ሃገራት በተለይ ደረሰ የተባለውን ርሃብና አደረሰ የተባሉትን ጉዳቶች ለህዝቡ በማስረዳት የሚቻለንን ሁሉ ብንልም ከኢትዮጵያ ህዝብ ከፊሉ ማለት ይቻላል

የነበረው ግምትና ግንዛቤ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ለማጥላላት የምንጠቀምበት ፕሮፖጋንዳ አድርጎ ነበር የተመለከተው።

በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በአጠቃላይ የወሎ ክፍለ ሃገር ነዋሪ በሆነው ህዝብ ላይ በተለይ የደረሰውን እጅግ አሰቃቂ የሰው ልጅ እልቂት ለኢትዮጵያ ህዝብና ለውጪው ዓለም ህዝብ ለማሳየት የኢትዮጵያ አብዮታዊያን የብሪታኒያ ዜጋ የሆነውን ጋዜጠኛ ጆናታን ዲምቢልቢይ ኢትዮጵያ በማስገባትና በስውር ወደ ወሎ ክፍለ ሃገር በመውሰድ ያስቀረፁት ተንቀሳቃሽ ፊልም ነው የረዳን።

ለ1967 ዓ.ም የዘመን መለወጫ አጥቢያ ምሽት ለንጉሡ፣ ለአዲስ አበባ ከተማና አካባቢው ህዝብ ፊልሙን ባሳየንበት ጊዜ ነው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪና የአካባቢው ህዝብ የወሎን ክፍለ ሃገር ነዋሪ ህዝብ አስደንጋጭና እጅግ አሰቃቂ እልቂት ከተመለከተ በኂላ ነው በቂ ግንዛቤ ሊያገኝና ሊያምነን የቻለው።

የቴሌቪዥን ትዕይንት ለሚደርሰው የአዲስ አበባ ከተማና ለአካባቢው ነዋሪ ህዝብ ብቻ በማሳየት ሳንወሰን የደርግ አባልና በኂላ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች የፖለቲካ ፓርቲ የፖለቲካ ቢሮ አባል በሆነው በጓድ ለገሠ አስፋው በሚመራ የደርግ ቡድን አማካኝነት ከክፍለ ሃገራት ከተሞች ጀምሮ በመላው የአገሪቱ አውራጃዎችና ወረዳዎች ነዋሪ ህዝብ ካሳየን በኂላ ነው መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ያንን እጅግ አስደንጋጭና እጅግ አሰቃቂ የወገኑን እልቂት ሊረዳ የቻለው።

የኢትዮጵያን ረሃብና የወሎን ህዝብ እልቂት ለመላው የዓለም ህዝብ በማሳየት የጆናታን ዲንቢልቢይን ውለታ፣ ታሪካዊና ሰብአዊ አስተዋፅኦ ለመግለፅ ተንቀሳቃሽ ፊልሙን ለመመልከት የቻሉ የሰው ልጆች ሁሉ በእጅጉ አዘኑ፣ አነቡ፣ አለቀሱ ከማለት የተሻሉ ቃላቶች ላገኝ አልቻልኩም።

ለማጠቃለል፤ ከ1961 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1973 ዓ.ም ድረስ ያላቋረጠ ተከታታይ የአየር ንብረት ቀውስ፣ በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ የነበረው የዓለም ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች ጋር በተያያዘና ከአገር ውስጥ በመነጩ የተለያዩ ባለ ብዙ ፈርጅ ውስብስብ ችግሮች የኢትዮጵያ ህዝብ በሚሰቃይበት ጊዜ በጎ አድራጊ ባዕዳን የሚመፀውቱንን እህል ከማዳረስ በስተቀር ሌላ አንዳችም አገራዊ መፍትሔ ለመሻትና ኢኮኖሚያዊ እርምጃ ለመውሰድ እንዳንችል፣ ጠላቶቻችን ባወጁብን ጦርነት በመወጠራችን በቅድመ አብዮት በአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት በድህረ አብዮት በአብዮታዊው መንግሥት ምንም ዓይነት ኢኮኖሚያዊ እርምጃ ለመውሰድ ባለመቻሉ ከአገሩ ጠላቶች፣ ከአንድነቱና ከአብዮቱ ፀሮች ጋር በጦር ሜዳ በመፋለም ላይ ላለው አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊታችን ቀለብ ማቅረብ የማንችልበት ሁኔታ ላይ ስለደረስን ለመጀመሪያ ጊዜ ከጦር ሜዳው ፍልሚያ ጋር በተጓዳኝ በኢኮኖሚው ችግራችን ላይ በማተኮር መላውን መንግሥታዊ ተቋሞች፣ መላውን ህዝባዊ ድርጅቶች ከአርሶ

አደሩና ከሠራተኛው መደብ ጋር ያስተባበርና ያቀናጀ ሁለገብ ብሄራዊና አብዮታዊ የምርትዘመቻ በ1973 ዓ.ም መጀመሪያ ለማወጅ አቀድን፡፡

በአብዮታዊት ኢትዮጵያ የህፃናት አምባ ውስጥ የሚያድጉ ህፃናት አያያዝና እንክብካቤ ይህንን ይመስል ነበር፡፡

ምዕራፍ ሃምሳ ሁለት

የዘመቻው መርህ ወይም ስትራቴጂ

ሁለገብ ብሄራዊና አብዮታዊ የምርት ዘመቻው መርህ ወይንም ስትራቴጂ በሰሜን ኢትዮጵያ ለአንድነታችንና ለአብዮታችን ደህንነት መዋጋት በደቡብ ኢትዮጵያ ማምረት ሲሆን ለምርት ዘመቻው ተግባራዊነት የሚበጁ ቅድመ ሁኔታዎች በቅደም ተከተል የተደረጉ መሰናዶዎችና ዝግጅቶች ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ፡-

ሀ) የሰው ልማት

ለአምስት ዓመታት ያህል ጊዜ ለማከናወን ለታቀደው የምርት ዘመቻ ብቻ ሳይሆን እንደውም በአመዛኙ ከአምስት ዓመታት በኋላ በአብዮቱ ዓላማና የፖለቲካ ፕሮግራም መሠረት ለሚጀመረው መደበኛ የረጂም ጊዜ ሰፊ የአገር ልማትና ግንባታ ከሚታሰቡ ቅድመ ሁኔታዎች አንዱ፣ ዋናውና የመጀመሪያው የሰው ልማት ሲሆን ይሄውም በሃገር ውስጥ ያሉን ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መጠንና አቅም በፈቀደልን መጠን ጥቂቶቹን በአገር ውስጥ በርካታዎችን ማለትም በሺህ የሚቆጠሩትን ወደ ተለያዩ ወዳጅ ሶሻሊስት አገሮች ማለትም ወደ ሶቪየት ህብረት፣ ህዝባዊት ቻይና፣ ምሥራቅ ጀርመን፣ ቼኮዝሎቫኪያ፣ ዩጎዝላቪያ፣ ቡልጋሪያ፣ሐንጋሪ፣ ሆላንድ፣ ኩባ፣ ሩማኒያና እንዲሁም ወደ ሌሎችም ወዳጅና ኢትዮጵያን ለመርዳት በጎ ፈቃድ ላላቸው አገሮች ማለትም ወደ ሕንድ፣ ሜክሲኮ፣ ኢጣሊያና ፈረንሳይ ወዘተ ወጣቶቻችን ከዚህ ግርጌ የተገለፁትን የተለያዩ ከፍተኛ ትምህርቶች እንዲቀስሙ መላክ ነበር፡፡

በዚህ አጋጣሚ ለአንባቢ መግለፅ ያለብኝ በኛ የምርት ዘመቻ ወቅት በፈረንሳይ የፖለቲካ ሥልጣን የነበረው ሶሻሊስት ፓርቲው ከመሆኑ ጋር ፈረንሳይ የአውሮፓ የኢኮኖሚ ማህበር መሪ በመሆኗ አገራቸውን ወክለው የአውሮፓ ኢኮኖሚ ኮሚሽን ኮምሽነር የነበሩት የኢትዮጵያ ወዳጅና የአብዮታችን ደጋፊ ሚስተር ቸስን የማህበሩን አባል ሃገራት አስተባብረው ሦስት መቶ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለዘመቻው ማስፈፀሚያ እርዳታ ያደረጉልን ከመሆናቸው በተጨማሪ ፈረንሳይ ለከፍተኛ ትምህርት ወጣቶቻችንን በመቀበል ተባብራናለች፡፡

በአገር ውስጥም ሆነ ወደ ጠቀስኳቸው ወዳጅ አገሮች ሄደው እንዲማሩ የላክናቸው ወጣቶች በአገሪቱ የሰለጠነ የሰው ኃይል የመጠንና የዓይነት ፍላጎታችን ስሌት መሰረት እንዲማሯቸው የመረጥናቸው ሞያዎች ወይንም የትምህርቶቹ ዓይነቶች ከዚህ ግርጌ የተመለከቱት ነበሩ፡፡

1) የተለያዩ የሰውና የእንስሶች ህክምና ሞያዎች
2) የተለያዩ የግብርና ሞያዎች
3) የሲቪል፣ የመካኒካል፣ የኤሌትሪካል፣ የኤሌትሮኒክ፣ የኬሚካል፣ የሃይድሮሊክ፣ የኤሮኖቲካል ወዘተ ምህንድስናዎችና በጂኦሎጂ፣ በሜትሮሎጂና በሁለገብ ዲዛይን ወይንም ንድፍ፣ በአርክቴክትና በከተማ ፕላን ሥራዎች እንዲሰለጥኑ ነው።

ለ) ለዘመቻው የእቅድ ሥራና እንዲሁም አፈፃፀም የሰለጠነ የሰው ኃይልና ድርጅታዊ አቅምን የመገንባት መሰናዶ:-

ለብሄራዊና አብዮታዊ የትምህርት ዘመቻው አስፈላጊ ጥናቶችን በማድረግ በእቅድ ዝግጅቶችና ብሎም ለዘመቻው ተግባራዊነት በሃላፊነትና በመሪነት ይሰሩ ዘንድ ከዚህ ግርጌ የተመለከቱትን መንግሥታዊ ተቋማት አቋቋምን።

1) የአገራቱ አርሶ አደሮች አደራጅ፣ አማካሪና መሪ የሆነ የግብርና ሚንስቴር
2) የቡናና የሻይ ቅጠል፣ የአትክልት፣ የፍራፍሬና የቅመማ ቅመን ልማት ሚንስቴር
3) ሁለገብ የመንግሥት እርሻ ሚኒስቴር
4) ብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ኮሚሽን
5) ከቀድሞው የማዕድን ሚኒስቴር በመነጠል እራሱን የቻለ የውሃ ልማት ኮሚሽን
6) የኪራይ ቤቶች አስተዳደርና የከተማ ልማት ሚኒስቴር
7) የመሰረተ ልማቶች ግንባታ ወይንም የኮንስትራክሽን ሚንስቴር
8) የምርት ዘመቻውን በማዕከልነት የሚመራና የሚቆጣጠር፣ የዘመቻውን ጠቅላላ እቅድ የሚነድፍና ለአፈፃፀሙ ዕያሄ ተግባሮችን የሚያወጣ፣ በውስጡ በርካታ የተለያዩ የሥራ ዘርፎች ያሉትና የምርት ዘመቻ መምሪያ በመባል የሚታወቅ ተቋም አቋቋምን።
9) በዋናው የእቅድና የምርት ዘመቻ መምሪያ እየተመሩ ከሚሠሩባቸው ክልሎች ለማዕከላዊ እቅድ የሚያስፈልጉ ዝርዝር የአካባቢ የልማት መረጃዎችን እያሰባሰቡ ለዘመቻው መምሪያ ማዕከል ከማቅረብ ባሻገር በየበኩላቸውም ከዘመቻው መምሪያ በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት በየክልሉ የልማት እቅድ ለመንደፍ በተለያዩ ባለሞያ ግለሰቦች ቅምር የተዋቀሩ አምስት የየክልሎች እቅድ አውጭ ተቋሞች በአምስት ቀጠናዎች ማለትም፤
1) ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀጠና በሸዋ ክፍለ ሃገር አዲስ አበባ ከተማ ላይ
2) ለሰሜን ኢትዮጵያ ቀጠና በወሎ ክፍለ ሃገር ደሴ ከተማ ላይ
3) ለደቡብ ኢትዮጵያ ቀጠና በሲዳሞ ክፍለ ሃገር አዋሳ ከተማ ላይ
4) ለምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና በከፋ ክፍለ ሃገር ጅማ ከተማ ላይ
5) ለምሥራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና በሐረርጌ ክፍለ ሃገር ሐረር ከተማ ላይ አቋቋምን።

መ) የግብርና ምርምርናጥናት ተቋሞችን ስለማቋቋም

የግብርና ጥናትና ምርምር ውጤቶች የሆኑትን ሳይንሳዊ የግብርና ልማት መረጃዎችን ለየቀጠናዎች የእቅድ ተቋማትና ለብሄራዊ የምርት ዘመቻ መምሪያ ማዕከል ከማቅረብ ባሻገር በሚቆጣጠሩዋቸው የአየር ንብረት ክልሎች የተለያዩ የእህሎች፣ የአትክልቶችና ፍራፍሬዎች፣ የቅመማ ቅመም፣ የቡናና ሻይ ወዘተና የቤት እንስሳት ምርጥ ዘሮችን በቅድመ አብዮት እያመረቱና እያረቡ ለአገሪቱ አርሶ አደሮች ለማደል በሸዋ፣ በአርሲ፣ በሲዳሞ፣ በከፋና በወለጋ ክፍለ ሃገራት ሙከራ ሲያደርጉ የነበሩት ለገበሬው የሚሰጡትን አገልግሎት ከፍ እንዲያደርጉ፣ በሰው ኃይልና በገንዘብ ከማጠናከር ባሻገር የክፍለ ሃገሮችን ከተሞች አቀማመጥ ሳንከተል የግብርና የአየር ንብረት ክልሎችን በሙሉ የሚያደርሱና የሚያገለግሉ በርካታ የግብርና ምርምር ጥናትና ሥርፀት ተቋማትን በብሄራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን አመራር ሥር አቋቋምን።

ሠ) ለብሄራዊና አብዮታዊ የምርቱ ዘመቻ አርሶ አደሩን ህብረተሰብ በሙሉ ስለማንቀሳቀስና የዘመቻውን ግብና ዓላማዎች በማስረዳት ረገድ የተደረጉ ጥረቶች።

የኢትዮጵያን አርሶ አደሮች ለማደራጀት፣ ለማማከርና ለመምራት የተቋቋመው የግብርና ሚኒስቴር አባል የሆኑና በሚንስቴሩ የሚመሩ የተለያዩ የግብርና ሞያ ያላቸው የግብርና ልማት አማካሪና መሪ የሆኑ ምሁራን ቡድኖች በመላው ኢትዮጵያ ከክፍለ ሃገራት እስከ ወረዳዎች አስተዳደር ድረስ በቋሚነት ለገበሬው ንቃት፣ ትጋት፣ ምርታማነትና ለዘመቻው ጥራት እንዲሰሩ አሰማራን።

ረ) የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን በተመለከተ፡-

ሌሎቹን ግንባታዎችንም ማለትም መሰረተ ልማቶችንም በተመለከተ በዘመቻው መከናወን የነበረባቸው አያሌ የንባታ ተግባሮች ስለነበሩ የመሰረተ ልማት ግንባታው ወይንም (የኮንስትራክሽን) ሚኒስትራችን ጓድ ካሣ ገብሬ ለተለያዩ ሕንፃዎች፣ የየብስ ተሽከሪካሪ የተለያዩ መንገዶች፣ ድልድዮች፣ የመስኖ እርሻ ግድቦች፣ የአውሮፕላን ማረፊያዎች፣ ለወደቦች ወዘተ በተለያዩ ክልሎች ለተለያዩ የሥራ መስኮች የተለያዩ የግንባታ ብርጌዶችን አቋቁሞ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ የአገር መከላከያ ሚኒስቴርም ራሱን ችሎ የጦር መኖሪያ ሠፈሮችን፣ የጦር ማሰልጠኛ ተቋሞችን፣ ወታደራዊ አገልገሎት የሚሰጡ የአውሮፕላን ሜዳዎችንና የመከላከያ ኢንዱስትሪዎችን ይገነባ ዘንድ በምድር ጦር አቋም ውስጥ ከነበሩት ቀዋሚና የሥራ ምህንድስና ክፍሎች የተለየና መላውን የጦር ኃይሎች የሚያገለግል አንድ የመሰረተ ልማት ግንባታ ወታደራዊ ተቋም አቋቋምን።

ሸ) የብሄራዊና አብዮታዊ የምርትዘመቻው እቅድ፡-

በብሄራዊና አብዮታዊ የምርት ዘመቻው በአምስት ዓመት የጊዜ ክልል ውስጥ ለሚከናወኑ የልማትና የግንባታ ተግባሮች የሚያስፈልጉትን ለጥናትና ምርምር፣

ለልማትና ግንባታ ተግባሮች የሚሰለፉት ገንቢና አምራች ግብረ ኃይሎች ከተቋቋሙና ከተደራጁ በኋላ ለዘመቻው ተግባራዊነት የሚያስፈልጉን የመስክ መረጃዎች በሙሉና በሚገባ ተሰባስበውና ተጠናቅረው ስለነበረ የብሄራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ ማዕከሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ የዘመቻውን የተሟላ እቅድ ከተግባራዊ አፈፃፀሙ ዝርዝር ፅያሄ ተግባር ጋር አዘጋጅቶ በማቅረቡ የዘመቻው መምሪያ የልዩ ልዩ ዘርፎች ሃላፊዎችና የአገሪቱ ሚኒስትሮች በጋራ መክረው ካፀደቁት በኋላ እንደተለመደው ለመጨረሻ ውሳኔ ለደርጉ ጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ በተግባር ላይ እንዲውል ተወሰነ::

ቀ) የማኔጅመንት ኢንስቲቲዩት ስለማቋቋም:-

ከዚህ በላይ በፊደል ተራ የተገለፁትን ልዩ ልዩ አምራች፣ ገንቢዎች፣ ልዩ ልዩ አስተዳደራዊና ማህበራዊ አገልግሎቶችን የሚሰጡ መንግሥታዊ ተቋሞችን ከአቋቋምን በኋላ በመጨረሻ ያቋቋምነው የማኔጅሜንት ኢንስቲቲዩት የተባለውን ተቋም ነው::

የዚህ ተቋም መሥራች ከሆኑ ምሁራን ጓዶች ጋር ስለተቋሙ መጠሪያ ስም ስንወያይ ተቋሙ የሚቋቋምበትን ዓላማና ተግባር ወይንም ተልዕኮ በትክክልና በአንድ ቃል የሚገልፅ አማርኛ በማጣታችን የእንግሊዝኛውን ቋንቋ እንዳለ ወስደን «የማኔጅሜንት ኢንስቲቲዩት» የተሰኘ ስም ሰጠነው::

ተዘንግቶ እንዳ ከማናቸውም መንግሥታዊ ተቋማት ሁሉ ቀድሞ በመቋቋም የተቀሩትን የተለያዩ የአስተዳደር፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማትን ለማቋቋም ምክርና ቴክኒካዊ አገልግሎት መስጠት የነበረበት ተቋም ነው::

ይህ በአገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ በምርት ዘመቻው ጊዜ በዚህ የሥራ መስክ የሞያ ብቃት፣ የሥራ ልምድና የአገር ፍቅር ባላቸው በሳል ምሁራን የተቃመረ ተቋም የተቋቋመው ጥናትና ምርምር ለማድረግ በሚቻልበት ለምሁራኑ መሥሪያና መኖሪያነት በሚያመች በደብረዘይት ከተማ ያቋቋምነው ኢንስቲቲዩት በተለያዩ የመንግሥት ተቋማት ውስጥ ከሚኒስትሮች ጀምሮ በተለያዩ ተቋማትና በየሥራው ደረጃዎች አመራር የሚሰጡ ሹማምንቶች ለሚያስተዳድሩት ህዝብ፣ ለሚመሯቸው ተቋማትና ድርጅቶች ፍትሀዊ፣ ቀልጣፋና ምርታማ የሆነ ዘመናዊ አመራር ይሰጡ ዘንድ በማስተማር፣ በማማከርና ቴክኒካዊ አገልግሎት በመስጠት የሚያገለግል ተቋም ነው::

በአገራችን በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ሠፍኖ የኖረው የሥራ አመራር ድክመት፣ የአስተዳደር ጉድለት፣ በሥልጣን መባለግ፣ ዝርክርክነት፣ ብኩንነት፣ ሙስናና ሌብነት መልሶ እንዳያገረሽና ብሎም እንዳያንሰራራ በመከላከል የሥራ ብቃትን፣ ቀልጣፋነትን፣ ምርታማነትን፣ የተፋጠነ የምርት ኃይሎች እድገትን የሚያስገኝ የአሰራር ባህል፣ ደንብ፣ ዘመናዊና ሳይንሳዊ የሆነ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች

አመራር በህዝብና በገንዘብ አስተዳደር፣ በሂሳብ አያያዝና ቁጥር ሥርዓት (ሲስተም) በመፍጠር ወሳኝ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው።

የአገሪቱ ኢኮኖሚ፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂ አቅም ሲፈቅድ የአገሪቱን ጠቅላላ አስተዳደር፣ የኢኮኖሚ አመራር፣ የገንዘብ አስተዳደር፣ የሂሳብ አያያዝና ቁጥጥር ሥርዓት ወይንም ሲስተም ሜካናይዝድ በማድረግ ረገድ የመሪነት ታላቅ ድርሻ የሚኖረው ተቋም ነው።

በ) የብሄራዊና አብዮታዊ የምርት ዘመቻ ዋና ዋና ግብና ዓላማዎች፡-

ሀ) የዘመቻው ዓላማዎች

የዘመቻውን ዓላማዎች በተመለከተ ቀዳሚ ትኩረት የሰጠነው፤ 1ኛ በዘመቻው አማካኝነት ለወደፊቱና ለዘላቂው የሃገር ልማትና ግንባታን እቅዶች በብቃትና በጥራት የመሥራት ወይንም የማዘጋጀት ትምህርት ለማግኘትና ልምድ ለማካበት፤ 2ኛ ለወደፊቱ ጊዜ ወይንም ለዘለቄታው ለማያቋርጥና ሥር ነቀል ለሆነ የሃገር ልማትና ግንባታ የኢትዮጵያን ህዝብ ለማዘጋጀት፤

3ኛ በሃገራችን ምድርና ከርሠ ምድር ላይና ውስጥ ስላሉን የተፈጥሮ ሃብቶቻችን መጠንና ዓይነት የጠሩ መረጃዎችን ማግኘት ናቸው።

ለ) የዘመቻው ግቦች፡-

የምርት ዘመቻው ብሄራዊና ሁለ ገብ ነው ብንልም ከሁሉም ክፍለ ኢኮኖሚዎች፣ በድርጅት፣ በሰው ኃይል ስምሪትና በገንዘብ ወጪ ከፍተኛውን ቅድሚያና እጅግ የላቀውን ድርሻ የሰጠነው ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ነው።

ለተቀሩት ማለትም ለማዕድናት ልማት፣ ለኃይል ማመንጫ፣ ለመሰረተ ልማቶችና ለኢንዱስትሪው የሰጠናቸው ትኩረት፣ የሰው ኃይል ስምሪትና የገንዘብ ድርሻቸው በሁለተኛ ደረጃ የታየ ነው።

በአንዳንድ ሰው ሠራሽ ችግሮችና በተለይም ተፈጥሮ ባመጣው የአየር ንብረት ቀውስ ምክንያት የኢትዮጵያ ህዝብ በገጠመው የእህል እጥረት ምክንያት የደረሰበትን እጅግ አሳዛኝና አሰቃቂ ጉዳት በአጣዳፊ ማስወገድ ከማስፈለጉ ሌላ፤

1ኛ አገራችን ባለችበት የእድገት ደረጃ ግብርናው የብሄራዊው ኢኮኖሚ መሪ በመሆኑ፤

2ኛ ግብርናው ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ብቸኛ ምንጭ በመሆኑ፤

3ኛ በአምስቱ የምርት ዘመቻ ዓመታት ውስጥ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የኢትዮጵያን ህዝብ የየዓመቱን የምግብ ፍላጎት ናፍጆት በአጥጋቢ ሁኔታ እንዲያቀርብ፤

4ኛ ለኢንዱስትሪዎቻችን ግብአት የሚያስፈልጉትን ጥሬ ምርቶች በብቃት እንዲያቀርብ፤

5ኛ ለውጭ ምንዛሪ ግኝት ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን በብቃት እንዲያመርት፤

6ኛ ቢያንስ ህዝባችንን ለአምስት ዓመታት የሚመግብ ብሄራዊ ተጠባባቂ እህል አምርቶ እንዲያካብትና በመጨረሻም ፤

7ኛ የአገሪቱ የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ጎልብቶ ብሄራዊ ኢኮኖሚውን የመምራቱን ሥፍራ እስከሚይዝበት ጊዜ ድረስ ለአገሪቱ የኃይል ምንጮች ግኝት፣ ለማዕድናት ልማት፣ ለመሰረተ ልማቶችና ለኢንዱስትሪዎች ግንባታ የሚውል መዋዕለ ንዋይ እንዲያፈስ ስለሚጠበቅበት ነው። እንዱን የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ሦስት የግብርና ሚኒስቴሮች ተከፋፍለው እንዲመሩትና እነሱም በእርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን፣ በውሃ ልማት ኮሚሽንና በሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን እንዲረዱ ያደረግነው።

ምዕራፍ ሃምሳ ሦስት

ለብሄራዊና አብዮታዊ የምርት ዘመቻ እቅድ ተግባራዊነት የሚያገለግሉ የግብርና መሣሪያዎች መሰናዶ

የዘመቻው ስትራቴጂ ከተወሰነና ከሰው ልማት ጀምሮ የሰው ኃይልና ድርጅታዊ አቅምን የመገንባቱ መሰናዶዎች ተጠናቀው የዘመቻውን እቅድ የማዘጋጀቱ ተግባር ከተከናወነ በኋላ በዘመቻው ዓላማና ግቦች መሠረት ዘመቻውን ተግባራዊ የሚያደርጉ የግብርና መሣሪያዎች መሰናዶ ለዘመቻው መታወጅ የመጨረሻው ሥራችን ወይንም ተግባራችን ነበር።

ወዳጅ ከሆኑ ሶሻሊስት አገሮችና እንዲሁም ከሌሎች ማረሻ ትራክተሮችንና የምርት ማጨጃና መሰብሰቢያዎችን ወዘተ የመሳሰሉ የግብርና መሣሪያዎችን ለማሰባሰብ ያቀድነው፤

እያንዳንዳቸው ወዳጅ አገሮች እንደየኢኮኖሚያቸው ጥንካሬና እንደማምረት ችሎታቸው የተለያዩ መሣሪያዎችን በረጂም ጊዜ ብድርና ክፍያ እንዲሸጡልን ሲሆን በተለይ ትልቋ ወዳጅና አጋራችን የሆነቺው ሶቭየት ህብረት የምርት ዘመቻውን የምንጀምርባቸውን ትራክተሮች በረጅም ጊዜ ብድርና ክፍያ ከመሸጥ ሌላ ኋላቀር የሆነውን ግብርና ለማዘመንና ምርታማ ለማድረግ ይቻለን ዘንድ በአገራችን ትራክተሮችን በማምረት እረገድ የምትረዳበትን፣ ከግብርና መሣሪያዎች እርዳታ ሌላ በዘመቻው መርሀ ግብር ውስጥ በተካተቱት የተለያዩ ክፍለ ኢኮኖሚዎች ማለትም፤

1ኛ በኃይል ማመንጫ፣ በማዕድን ልማትና በኢንዱስትሪዎች ግንባታ ረገድ ከእያንዳንዱ ወዳጅ አገር የምንፈልገውን የገንዘብ ብድርና የቴክኖሎጂ አቅርቦት እርዳታዎችን ያካተተ ነበር።

2ኛ ኢትዮጵያ አገራችን በኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ግንባታ እጅግ ወደ ኋላ የቀረች በመሆኗ ወዳጅ ሶሻሊስት አገሮች የኢኮኖሚ ልማትና ግንባታ ህብረት ማህበር አስተዋፅኦ ለማድረግ የምትችል ባትሆንም የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ውጤት የሆኑ የተለያዩ አያሌ የምርት ዓይነቶችን ማለትም የሥጋና የወተት ከብቶች ተዋፅኦ የሆኑ ምርቶች፣ የቡና፣ የስኳር፣ የማር፣ የጥጥ፣ የፍራፍሬ፣ የቅባት እህሎች ወዘተ ምርቶችን ለማቅረብ ስለምትችል የህብረቱ አባል እንዲያደርጉንና እያንዳንዳቸው ወዳጅ ሶሻሊስት አገሮች በገንዘብና በቴክኖሎጂ አቅርቦት ብቻ ሳይሆን በጋራ ልማትም ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚጠይቀውንና በአጠቃላይም የዘመቻውን ዓላማና ግቦች የሚተነትነውን የኢኮኖሚ ልማትና ግንባታ እቅድ ሰነድ ይዘን የዘመቻው ግንባር ቀደም ተሳታፊ ከሆኑት ዋና ዋናዎቹን የዘመቻ መምሪያ አመራር አካላት የሆኑ ጓዶችን፣ የግብርና፣ የማዕድን፣ የኢንዱስትሪና የመሰረተ ልማት ግንባታ ሚኒስትሮችን ያካተተና በኔየሚመራ የልዑካን ቡድን በመጀመሪያ የተጓዝነው ወደ

ዋናዋ አብዮታዊ አጋራችን ወደ ሶቭየት ህብረት ነበር። በዚህ ጊዜ የሶቭየት ህብረት ኮሚኒስት ፓርቲ ዋና ፀሃፊና የአገሪቱ ፕሬዝዳንት ጓድ ሊዮኔድ ብሬዥኔቭ ነበሩ።

ጓድ ብሬዥኔቭ መላውን የሶቭየት ህብረት ኮሚኒስት ፓርቲ የፖለቲካ ቢሮ አባላትን ሰብስበው ሞስኮ ከተማ በገባን ማግስት ጧት በክሬሚሊን ቤተመንግሥት ተቀበሉን።

በኔ የተመራው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ሶቭየት ህብረትንና የተቀሩትን ሶሻሊስት አገሮች የሚጎበኝበት ምክንያት በቅድሚያ በየሃገሮቹ ኢትዮጵያን በሚወክሉ አምባሳደሮቻችንና እንዲሁም አዲስ አበባ ሚገኙ የሶሻሊስት አገሮች መንግሥታት አምባሳደሮች አማካኝነት በሰፊው የተገለፀላቸው ስለነበረ የእነሱም በኩል እኛን ለማስተናገድ የሚያስ ፈልጓቸውን ቅድመ ሁኔታ አዘጋጅተው ነው የጠበቁን።

በኔ በኩል በፖለቲካ ቢሮው ስብሰባ ላይ ስለ ምርት ዘመቻው እቅድ ዝርዝር ውስጥ ብዙ ጠልቄ ሳልገባ በጣም በአጠረና በተጠቃለለ ሁኔታ ገለፃ ከአደረኩላቸው በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ ማለትም ሞስኮ በገባን ማግሥት ማለዳ በጓድ ብሬዥኔቭና በፖለቲካው ቢሮ አባላት ስለተደረገልን አቀባበል በራሴና አብረውኝ ባሉ በኢትዮጵያዊያን ልዑካን ጓዶች ስም ከአመሰገንኩ በኋላ ከዚህ የሚከተለውን ጥያቄ አቀረብኩ።

ያቀረብኩት ጥያቄ በሶቪየት ህብረት መንግሥት ውስጥ በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ለምሳሌም፦ በግብርናው፣ በኢንዱስትሪው፣ በማዕድን፣ በውሃ ልማት ወዘተ ሃላፊነት ያላቸው ሚኒስትሮች የጓድነትዎ መልካም ፈቃድ ቢሆን የሶሻሊስት አገሮች የኢኮኖሚ የጋራ ልማት ማህበር ኮሚሽን ሰብሳቢና መሪ ከሆኑት ከጓድ ባይባኮቭ ጋር ጓድ ጠቅላይ ሚኒስትር ኮስጂን የሚመሩት ቡድን ስለብሄራዊና አብዮታዊ የምርት ዘመቻ የምገልፀውን የልማትና የግንባታ እቅድ ዝርዝር ገለፃ ያዳምጡኝ ዘንድ እንዲፈቅዱልን ነበር።

ጓድ ብሬዥኔቭ መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ ጥያቄዬን ተቀብለው በሰጡት መመሪያ መሠረት ቁጥራቸው ከአስር በላይ የሆነ የሚኒስትሮች ቡድን በጠቅላይ ሚኒስትሩ መሪነት በክሬምሊን ቤተመንግሥት አንድ አነስተኛ የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ለሁለት ሙሉ ቀናት ተቀምጠው ገለፃዬን አዳመጡ። ገለፃዬን ከአበቃሁ በኋላ ጓድ ጠቅላይ ሚኒስትር ኮስጂን ከዚህ የሚከተለውን ተናገሩ።

«እጅግ ውስብስብ በሆነ የመደብ ትግል፣ ተፈጥሮ ባስከተለው ከባድ የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ሆናችሁ በተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት የተሰነዘረባችሁን ወረራ በአጭር ጊዜ ውስጥ በድል መልሳችሁ፣ ከኤርትራ ገንጣዮች ጋር በጦር ሜዳ መራር የሆነ ውጊያ እያካሄዳችሁ፣ የኢትዮጵያን ህዝብ ከመሀይምነት ጨለማ ለማውጣት

የምታካሄዱት ዐረ መሃይምነት ዘመቻ ሲያስገርመን የአገር ልማትና ግንባታ ዘመቻ ማቀዳችሁ በእጅጉ አስደንቆናል።

ሶቭየት ህብረት በምታካሂዱት ህዝባዊ አብዮትና በጓድነትዎ አብዮታዊ አመራር የምታምን ፍፁም ወዳጃችሁና አጋራችሁ ነች። ለእኛም ለእናንተም ወዳጅ የሆኑትን መላውን ሶሻሊስት አገሮች አስተባብረን ለዘመቻው ከጎናችሁ እንቆማለን።

በዘመቻው እቅድ ላይ በሚኒስትሮች ምክር ቤታችንና በጎስፕላን ኮሚሽን ከተመከረበት በኋላ መልሳችን በፖለቲካ ቢሮው ስብሰባ ላይ በጓድ ብሬዥኔቭ ይገለፅላችኋል » በማለት በጣም አስደሳች የሆነ ተስፋ ሰጡን።

«ጎስፕላን» ማለት የሶሻሊስት አገሮች የኢኮኖሚ ህብረት ልማትና የግንባታ ዕቅድ የሚያወጣ ኮሚሽን ማለት ነው።

እንደተባለው የሶቭየት ህብረት መንግሥት የሚኒስትሮች ምክር ቤትና የጎስፕላን መክረውበት የውሳኔ ሃሳባቸውን ለፖለቲካ ቢሮው እስኪያቀርቡ ድረስ የኢትዮጵያ ልዑካን በሞስኮ ከተማና በአካባቢዋ ያሉ አንዳንድ ታሪካዊ ሥፍራዎችን እንድንጎበኝ ተደርጎ ከሦስት ቀናት በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ጓድ ብሬዥኔቭ ክሬምሊን ቤተ መንግሥት ውስጥ ባለው የፖለቲካ ቢሮው የስብሰባ አዳራሽ ተቀበሉን።

ጠቅላይ ሚኒስትሩና የጎሳፕላን ኮሚሽን ሊቀመንበሩ እኛ ስለ ገለፅንላቸው የምርት ዘመቻው እቅድ በዝርዝር በሚገባ ስለ ተገለፀላቸውና ከሶቭየት ህብረት መንግሥት ብቻ ሳይሆን ከተቀሩትም ሶሻሊስት አገሮች የምንፈልገው እርዳታ ስለተነገራቸው ጓድ ብሬዥኔቭና የተቀሩትም የቢሮ አባላት የተሟላ ግንዛቤ ነበራቸው።

ጓድ ብሬዥኔቭ በእንደምን ሰነበታችሁ ጥያቄ ውይይቱን ከከፈቱ በኋላ ቢሮው ተነጋግሮ የደረሰበትን ውሳኔ ከዚህ በሚከተለው ሁኔታ አስረዱን።

«በጓድ ኮስጂን የተመራው የሚኒስትሮች ቡድን በእርስዎ ከተደረገለት ገለፃ በኋላ የምርት ዘመቻ እቅዳችሁን ዝርዝር ተመልክቶ በእቅዱ ዝግጅት የተሰማውን አድናቆት ገልፆልናል።

የሚኒስትሮች ቡድን ለእኛም በአደረገልን ገለፃ መሰረት የተረዳነው የእርስዎ የተፈተነ አብዮታዊ አመራር ችሎታ ውጤት መሆኑን ነውና በራሴና በተቀሩት ጓዶቼ ስም እንኳን ደስ ያለዎት እላለሁ።

የሶሻሊስት አገሮች በመላው በምርት ዘመቻችሁ ተሳትፎ እንድናደርግ ያቀረባችኋቸውን ጥያቄዎች በጥሞና ተመልክተናቸዋል።

ከሞስኮ ቆይታችሁ በኋላ ወደተቀሩት ሶሻሊስት አገሮችም ሄዳችሁ እዚህ ለእኛ እንደአደረጋችሁት ስለ ዘመቻችሁ ማስረዳትና የእቅዳችሁን ሰነድ በመስጠት ማነጋገር አስፈላጊና ጠቃሚ ነው።

ከእናንተ ጉብኝት በኋላ በኛ በኩል ሁሉም እንደየ አቅማቸውና እንደየ ፍላጎታቸው በጋራ ልማት የሚተባበሩበትንና ዘመቻውን የሚረዱበትን ሁኔታ ከማመቻቸትና ከማስተባበር ባሻገር በበኩላችን ከዚህ የሚከተሉትን ውሳኔዎች ወስነናል።

1ኛ በአጠቃላይ በግብርናው ልማት የምንሳተፍበትን፣ በኢንዱስትሪውና በማዕድናት ልማት የት፣ እንዴትና በምን ሁኔታ መርዳት የምንችልበትን ሁኔታዎች ኢትዮጵያ መጥቶ ከእናንተ ባለሞያዎችና ባለሥልጣኖች ጋር ዝርዝር አፈፃፀሙን የሚነጋገር አንድ ቡድን በአስቸኳይ እንልካለን።

2ኛ የግብርናውን ልማት ዘመቻ የምትጀምሩበት ጊዜ ከአገራችሁ የአየር ንብረት ወቅት ጋር የተያያዘና አስቸኳይም ስለሆነ 1000 አንድ ሺህ ትራክተሮች በእርዳታ በአስቸኳይ እንዲደርሷችሁ እናደርጋለን።

3ኛ የአገራችሁን የግብርና ኢኮኖሚ ለማዘመንና ምርታማ ለማድረግ ዘመናዊ የግብርና መሣሪያዎች እንደሚያስፈልጓችሁና በአገራችሁ የማምረት አቅም እንዲኖራችሁ የእኛም ምኞትና ፍላጎት ነው።

ይህንን ለማድረግ በቅድሚያ የምንሰጣችሁን በርካታ ትራክተሮች በሚገባ ለመንከባከብና ለመጠገን የሚያስችላችሁና ትራክተር የምትገጣጥሙበት ተቋም ከገነባንላችሁ በኋላ በጥቂት ዓመታት ውስጥ የመጠገኛና የመገጣጠሚያው ተቋም ወደ ተሟላ ኢንዱስትሪ ወይንም የማምረቻ ተቋምነት እንዲያድግ እናደርግላችኋለን » አሉን።

በጠቅላይ ሚኒስትር ኮስጂን ከተመራው የሚኒስትሮች ቡድን ጋር የሁለት ቀን ውይይት አድርገን በጨረስን ማግሥት ማለዳ በሶቭየት ህብረት ኮሚኒስት ፓርቲ መንግሥት፣ የምሥራቅ አፍሪካ የውጭ ጉዳይ ሃላፊ የሆነና ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው የሶቭየት ኤምባሲ ለረጂም ዓመታት በመስራት አማርኛ ቋንቋ የተማረ ሽራይቭ የተባለ ሰው አረፍንበት የእንግዳ ማረፊያ ቤት መጥቶ የሶሻሊስት አገሮች ኢኮኖሚ ማህበር አባላት የምሥራቅ አውሮፓ ለሶሻሊስት አገሮች ብቻ ናቸው ብሎ ስለነገረኝና ንገረው ተብሎ የተላከ መሆኑም ስለገባኝ ለሚኒስትሮች ያቀረብኩትን የማህበሩ አባል የመሆን ጥያቄ የፖለቲካ ቢሮው ስብሰባ ላይ ላነሳ አልፈለግሁም።

በጓድ ብሬዥኔቭ በተሰጠን ለጋስ ውሳኔ እኔና ልዑካኑ ብቻ ሳይሆን የተልእኮአችንን ውጤት በጉጉት በሚጠብቀው የኢትዮጵያ ህዝብ ስም ከፍ ያለ

ምሥጋና ካቀረብኩ በኋላ ወደ ተቀሩት ወዳጅ ሶሻሊስት አገሮች ለመሄድ እቅድ ያለን መሆኑን ገልጬ ተሰናበትናቸው።

ከሞስኮ ተነስተን የተጓዝነው የሶሻሊት አገሮችየ ኢኮኖሚ ማህበር አባል ወደሆኑት ማለትም፣ ወደ ቡልጋሪያ፣ ቼኮዝላቫኪያ፣ ሐንጋሪ፣ ሆላንድ፣ ምሥራቅ ጀርመን፣ ዩጐዝላቪያና ሩማኒያ ነው። ዩጐዝላቪያ፣ ሩማኒያ፣ አልባኒያ፣ ኮሪያና ኩባ የማህበሩ አባል አይደሉም።

የጎበኘናቸው የማህበሩ አባል አገሮች በሙሉ ልባዊ የወዳጅነት ስሜት ተቀብለውን ስለብሄራዊና አብዮታዊ የምርት ዘመቻችን እቅድ ገለፃ ከማድረግ ሌላ ከእያንዳንዳቸው ሃገራት የምንፈልገውን እርዳታና የልማት ትብብራቸውን ጠየቅን።

ሁሉም ለመረዳትና ለመተባበር ያላቸውን በጎ ፈቃድና ፍላጎት ከገለፁልን በኋላ ሁሉም ያሉን፣ ሞስኮ የሚገኘው የጎስፐላን ኮሚሽን በሚሰጠን የተሳትፎና የመርዳት ድርሻ ወይንም የሥራ ክፍያ መሰረት ቦታው ላይ ተገኝተን ምን፣ የትና እንዴት እንደምንተባበር ከእናንተ ባለሞያዎችና ባለሥልጣኖች ጋር የሚመካከሩ መልዕክተኞች በአስቸኳይ ወደ ኢትዮጵያ እንልካለን በማለት አሰናበቱን።

የሶሻሊስት መንግሥታት የኢኮኖሚ ማህበር አባል ያልሆነችው ወዳጃችን የዩጐዝላቪያ መሪ ማርሻል ቲቶ እንደ ሩሲያዊያኑ በፓርቲያቸው ጽህፈት ቤት የፓርቲያቸውን የፖሊቲካ ቢሮ አባላት ሰብስበው በመቀበል ለኔ የዩጐዝላቪያን ከፍተኛ የክብር ኒሻን ከሸለሙኝ በኋላ ስለምርት ዘመቻው በሰፊው ገለፃ አድርጌላቸው ዩጐዝላቪያ ከምታመርታቸው 300 ሦስት መቶ ትራክተሮችን በእርዳታ ከመስጠት በላይ ዩጐዝላቪያ ከኢትዮጵያ ጋር በማናቸውም የጋራ ልማት ለመተባበር ዝግጁ መሆኗን በመግለፅ አሰናበቱን።

የዲሞክራቲክ ጀርመን መሪ ጓድ ኤሪክ ሆኒከር 250 ሁለት መቶ ሃምሳ ትራክተሮች በእርዳታ በሰጡን ጊዜ የኢትዮጵያ ልዑካን አባል የሆኑ የግብርና ሚኒስትሮች የጀርመኖች ሥሪት ትራክተሮች ከፍተኛ የፈረስ ጉልበት ያላቸውና በቀላሉ የማይበላሹ ጥሩ ትራክተሮች ስለሆኑ ተጨማሪ ትራክተሮችን በግዥ እንድንገዛ ስለአሳሰቡኝ ተጨማሪ 500 አምስት መቶ ትራክተሮች በረጅም ጊዜ ብድርና ክፍያ እንዲሸጡልን ጠይቄ ፈቀዱልን።

ወደ ሃገራችን ከተመለስን በኋላ አሁንም የግብርና ሚኒስትሮቻችን በኢጣሊያ አገር የፊያት ኩባኒያ የሚያመርታቸው ትራክተሮች ለአገራችን አፈር የሚስማሙና በጣም ጥሩ ትራክተሮች ስለሆኑ ቢያንስ አምስት መቶ ያህል በረጂም ጊዜ ብድርና ክፍያ እንዲሸጡልን ይደረግ ብለው ባሳሰቡት መሰረት የኢጣሊያን መንግሥት ጠይቀን ፈቃደኞች ከመሆናቸው በላይ ከማንም ቀድመው ላኩልን። በዚህ ጊዜ ከኢጣሊያ መንግሥት ጋር የኢኮኖሚ የጋራ ልማትና ትብብር ኮሚሽን ነበረን።

በግዥና በስጦታ ከወዳጅ አገሮች 2550 ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ ትራክተሮች ስናገኝ ምን ጊዜም ለኢትዮጵያ በጎ አመለካከት ያለው የጃፓን መንግሥት ለመስኖ እርሻና ለመሠረተ ልማት ግንባታ የሚሆኑና ዛሬ ቁጥራቸውን በትክክል የማላስታውሳቸው በርካታ ዶዘር፣ ግሬደርና ሌሎችንም የግንባታ መሣሪያዎች በረጂም ጊዜ ብድርና ክፍያ ሸጡልን።

ምዕራፍ ሃምሳ አራት

የብሔራዊና አብዮታዊ የምርት ዘመቻ አዋጅ ብሥራትና ህዝባዊ ሠልፍ

ከሶቭየት ህብረት፣ ከዩጎዝላቪያ፣ ከዲሞክራቲክ ጀርመን፣ ከኢጣሊያና ከጃፓን የተላኩልን የልማትና የግንባታ መሣሪያዎች ተጠቃለው አገራችን ከገቡ በኋላ በ1974 ዓ.ም መጀመሪያ በመስከረም ወር የታወጀው የብሄራዊና አብዮታዊ የምርት ዘመቻ አዋጅ አብዮት አደባባያችን ላይ በተደረገ እጅግ ደማቅ ታሪካዊና ህዝባዊ ሠልፍ የታጀበ ነበር።

ከሁለት ዓመታት በፊት በ1972 ዓ.ም በውጭ ወራሪዎችና በአገር ውስጥ ገንጣዮች ላይ የተቀዳጀነውን ከጦር ሜዳ የተገኘ ወታደራዊ ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ ለማብሰር ሲባል አብዮታዊ የጦር ኃይሎቻችን ታላቅ የጦር መሣሪያና የሠራዊት የእግር ሠልፍ በአሳዩበት በአብዮት አደባባያችን፣ የኢትዮጵያ ሠራተኛ መደብ፣ አርሶ አደሮች፣ ከሴቶችና ከወጣቶች ድርጅቶች ጋር በህብረትና በቅንጅት መዶሻ፣ መጋዝ፣ ሞረድ፣ አካፋና ዶማ እንዲሁም ከባህላዊ የግብርና መሣሪያዎች ማጭድ፣ መንሽና ላይዳ ወዘተ የመሳሰሉትን በእጃቸው ይዘውና በትከሻቸው አንግበው 2,550 ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ ትራክተሮችን ከኋላቸው አስከትለው «ኢትዮጵያን እንገለባብጣታለን እናም የዳቦ ቅርጫት እናደርጋታለን» የሚል በትልቅ ሰሌዳ ላይ የተፃፈ መፈክር የያዘ አንድ ገበሬ እየመራ የታየው የብሄራዊና አብዮታዊ የምርት ዘመቻ አዋጅ ማብሰሪያ ሠልፍ የኢትዮጵያን ህዝብ በእጅጉ ያስደሰተ ታላቅ ህዝባዊ ሠልፍ ነበር።

የብሄራዊና አብዮታዊ የምርትዘመቻ መምሪያው መሪዎች፣ የመምሪያው ሠራተኞች፣ የልማትና የግንባታ ሚኒስትሮችና የዘመቻው ተሳታፊ የሆኑ የአገሪቱ ሲቪል ሹማምንቶች እንደወትሮው የህዝቡን ሠልፍ ተመልካች ሳይሆኑ ግዙፍ መፈክር ከያዘው ገበሬ በኋላ በተቀዳሚ ሚኒስትራችን በጓድ ኃይሉ ይመኑ መሪነት የሠልፉ መሪዎች ነበሩ።

ሠልፉን ከተመለከቱትና ከአደነቁትት የአገር ተወላጆችና ከባዕዳንን እንግዶች መሃከል ብዙዎቹ የመድፎችና የታንኮች ሠልፍ ባየንበት አደባባይ የትራክተሮች ሠልፍ ማየታችን የሚያመለክተው የኢትዮጵያ ህዝብ ለልማትና ለግንባታ የተነሳ መሆኑን ብቻ ሳይሆን የአገሪቱንም ሠላም መሆን ነው በማለት ተንብየው ነበር።

የዘመቻው ውጤቶች፡-

በአምስቱ ዓመታት የብሄራዊና አብዮታዊ የምርት ዘመቻው የመንግሥትና የህዝቡ ጥምር የህብረት ጥረቶች ያስገኙዋቸው ውጤቶች ከዚህ የሚከተሉትን ይመስላሉ።

ሀ) የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ በተመለከተ፡-



ከተለያዩ ወዳጅ አገሮች ከገዛናቸውና በእርዳታ ከተሰጡን ተራክተሮች በከፊል።

1) መላው የአገሪቱ አርሶ አደር ህብረተሰብ፣ የግብርና ሚኒስቴር ልዑካን በሆኑ፣ የግብርና ባለሞያ የምሁራን ቡድኖች፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን ልዑካን በሆኑ የግብርና ጥናት፣ ምርምርና ቴክኒካዊ አገልግሎት ሰጪነት፣ በምርጥ ዘር፣ በማዳበሪያና በሰብል ተባይ መከላከያ እየተረዱና በሬ ለሌላቸው ደሃና አዲስ ተቋቋሚ ገበሬዎች መንግሥት የእርሻ በሬዎችን እየገዛ በማደል መላው የአገሪቱ አርሶ አደሮች ምርታማ እንዲሆኑ ከማበረታታት ሌላ በአገሪቱ የተለያዩ ክልሎች ከምርት ዘመቻው በፊት ያልታረሱ እጻሪ መሬቶች እንዲለሙ ሲደረግ፣ በአገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የዲሞክራቲክ ኮሪያ መንግሥት በላከልን የግብርና ባለሞያዎች እርዳታ ለአገራችን አርሶ አደሮች የሩዝ ምርትን አመራረት ለማስተማር ተችሏል።

2) የመንግሥት እርሻ ሚኒስቴር ብቻውን ልዩ ልዩ የምግብ ሰብሎችን፣ ጥራጥሬና የቅባት እህሎችን የሚያመርቱ አዲስ ወይንም እጻሪ መሬቶችን ከማልማት ባሻገር በተጨማሪ የአየር ንብረት ቀውስና ጦርነት ከመኖሪያ ክልላቸው ያናጋቸውን በብዙ

መቶ ሺ.ህ የሚቆጠሩ አርሶአደሮችን በጐጃም፣ በወለጋ፣ በኢሊባቡር፣ በከፋ፣ በጋሞጎፋ፣ በአርሲ፣ በባሌና በሐረርጌ ክፍለ ሃገራት ያሰፈርናቸው ተፈናቃይ አርሶ አደሮች ራሳቸውን ችለው በራሳቸው የእርሻ በሬዎች ማረስ እስከሚችሉ ድረስ የታረሰላቸው መሬት መጠን በጠቅላላ ሲደመር ከ400.000 ከአራት መቶ ሺ.ህ ሄክታር በላይ ሲሆን ከዚ.ህ በላይ እንደገለፅኩት ዘጠና በመቶው ከዘመቻው በፊት ያልተነካ ወይንም ያልታረሰ እዳሪ መሬት ከመሆኑ ሌላ ከዚ.ህም ውስጥ 50.000 ሄክታር ለውጭ ገበያ የሚቀርብ የሌጦ ምርት ማምረቻ እርሻ በጐንደር ክፍለ ሃገር በሁመራ አውራጃ፤

3) 10,000 ሄክታር መተሐራ ለተቋቋመው ሁለተኛው የስኳር ማምረቻ ኢንዱስትሪ ግብአት ወይንም ጥሬ ምርት የሚሆን የሸንኮራ አገዳ የመስኖ እርሻ፤

4) በአዋሽ ሸለቆ በተንዳሆ ከነበረን በተጨማሪ 10,000 ሄክታር የመስኖ የጥጥ እርሻ፤

5) በኢሊባቡር ክፍለ ሃገር በጊሚራ አውራጃ በበቃ ወረዳ የለማ 10,000 ሄክታር የቡና ተክልና በዚ.ሁ ክፍለ ሃገር በጉሞሮ ወረዳ 2,000 የሻይ ቅጠል ተክል ሲለማ፤

6) በአገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ለቢራ መጥመቂ ያየሚሆን ብቅል እንዲያመርት ለተቋቋመው ፋብሪካ ግብአት የሚሆን ልዩና ምርጥ የገብስ ምርት በአርሲ ክፍለ ሃገር አርሶ አደሮች ለአምስቱ የቢራ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎቻችን ማለትም፣ ለአስመራው መሎቲ፣ ለአዲስ አበባዎቹ፣ ለቅዱስ ጊዮርጊስና ለሜታ፣ ለሐረሩና ለበደሌው ፒልሲነር ቢራ ማምረቻ ፍላጎትና ፍጆት መጠን ተመርቷል+

7) በጎጃም ክፍለ ሃገር በብር ሸለቆ በኢጣሊያኖች የቴክኒክ አገልግሎትና የገንዘብ ብድር ድጋፍ የተለያዩ የምግብ እህሎችና አደንጓሬ ወዘተ የመሳሰሉ ምርቶችን የሚያመርት 80,000 ሄክታር እዳሪ መሬት፤

8) ልዩ ልዩ የቅባት እህሎችን፣ በቆሎና በርበሬ የሚያመርት 40,000 ሄክታር የመንግሥት እርሻ፤

በኢሊባቡር ክፍለ ሃገር ጊሚራ አውራጃ በበበቃ ወረዳ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በበናና ሻይ ሚኒስቴር የለማ የቡና ተክል የመጀመሪያው ምርት፡፡

በጋምቤላ አውራጃ ከተማ በበሮ ወንዝ ላይ በአገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያን መሃንዲሶች የተገነባው እርዝመቱ 150 ሜትር የሆነው ታላቅ ድልድይ።

ለ) የማዕድናትን ፍለጋና ልማት በተመለከተ፡-

ከምርት ዘመቻው ጊዜ ውስንነትና ከገንዘብም እጥረት ሌላ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ ግንባታ በተቀዳሚነት እጅግ አስፈላጊ ናቸው ባልናቸው ማለትም፣ በወርቅ፣ በነዳጅ ዘይትና በተፈጥሮ ጋዝ፣ በብረትና ሲሚንቶ ማዕድናት ላይ ያተኮረ ዘመቻ ነው ያካሄድነው። በዚህም መሰረት-

1) በቅድመ አብዮት በአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ሲንክለር በመባል የሚጠራው የሰሜን አሜሪካ የነዳጅ ዘይት ፈላጊና ቆፋሪ ኩባኒያ በኦጋዴን ጀምሮ የተወውን ቁፈራ፣ በድህረ አብዮት በምርት ዘመቻው በሶቭየት ህብረት መንግሥት ትብብር ቁፈራው እንደገና ተጀምሮ አጥጋቢ ውጤት የተገኘበት፤

2) በሲዳሞ ክፍለ ሃገር በአፍሪካ ባንክ ብድርና በሶቭየት ህብረት መንግሥት የቴክኒክ አገልግሎት አቅርቦት ትብብር ከፍ ያለ መጠን ያለው የወርቅ ማዕድን ለምቶ ከፍ ያለ የገንዘብ ምንጭ መሆን፤

3) በዚሁ በሲዳሞ ክፍለ ሃገር በሶቭየት ህብረት መንግሥት ልዑካን ባለሞያዎች የወርቅ ማዕድን ቁፈራ በሚያካሄዱበት ጊዜ በዓለም ገበያ ተፈላጊነቱ ከአልማዝ

ወይንም ከዕንቁ በላይ እጅግ ከፍ ያለና (ታንታለም) በመባል የሚታወቅ ማዕድን መገኘት፤

4) በወለጋ ክፍለ ሃገር በሶሜን ኮሪያ መንግሥት ትብብርና ፍለጋ የተገኘ የብረት ማዕድን፤

5) በሸዋ ክፍለ ሃገር በመናገሻ አውራጃ በሙገር ወረዳ በዲሞክራቲክ ጀርመን መንግሥትና በኩባ መንግሥት የልማት ትብብር ከፍተኛ የሲሚንቶ ድንጋይ ክምችት ለምቶ ለአገሪቱ ከፍ ያለ ጥቅም በመስጠት ላይ የሚገኘው ወዘተ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹና ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

መ) የኤክትሪክ ኃይል ማመንጫዎችን ግንባታ በተመለከተ፡-

በአፍሪካ አህጉር ወደር የሌለው ከፍ ያለ የውሃ ሀብት ስለአለን ለአገራችን ኢንዱስትሪዎች ግንባታ ፍፁም ወሳኝነት ያለውን የኤሌትሪክ ኃይል ለማመንጨት ቅድሚያውን ወይንም ዋናውን ትኩረት የሰጠነው ከውሃ ለሚገኝ ኃይል ወይንም (ለኃይድሮ ኤሌትሪክ ኃይል) ሲሆን በዚህም መሰረት፤

1) በአርሲና በባሌ ክፍለ ሃገራት መካከል በመልካ ዋከና ወንዝ ላይ በሶቭየት ህብረትና በቼኮዝላቫኪያ መንግሥታት ትብብር ግድብ በመሥራት 300 ሜጋዋት የኤሌትሪክ ኃይል የማመንጨት ሥራ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተከናውኖ አገልግሎት መስጠት የጀመረው፤

2) በዲሞክራቲክ ኮሪያ መንግሥት ትብብር በሸዋና በከፋ ክፍለ ሃገራት መካከል በግቤ ወንዝ ላይ ግንባታው ወደ መጠናቀቁ ተቃርቦ የነበረው 300 ሜጋዋት የኤሌትሪክ ኃይል አመንጪ ግድብ፤

3) በኢሉባቡር ክፍለ ሃገር በጋምቤላ አውራጃ በባሮ ወንዝ ላይ በሶቭየት ህብረት መንግሥት ትብብር ግንባታው የተጀመረው 600 ሜጋዋት የኤሌትሪክ ኃይል የሚያመርት ግድብ፤

4) በጉጃም ክፍለ ሃገር በመተከል አውራጃ ከአካሄድነው የህዝብ ሠፈራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በኢጣሊያ መንግሥት ትብብር የተገነባው 12 ሜጋዋት የኤሌትሪክ ኃይል በማመንጨት ለሠፋሪ ገበሬዎችና ለአካባቢው ነዋሪ ህዝብ አገልግሎት መስጠት የጀመረው፤

5) በሸዋና በወለጋ ክፍለ ሃገራት መካከል በፊንጫ ወንዝ ላይ፣ በጉጃም ክፍለ ሃገር በጨሞጋ ወንዝ ላይ የግንባታ ዝግጅታቸው ተጠናቆ የነበረው የኤሌትሪክ ኃይል ማመንጫዎች፤

ሠ) የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ በተመለከተ፡-

የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ ግንባታ በተመለከተ ከሰሜን ኢትዮጵያ ማለትም ከኤርትራ ክፍለ ሃገር ብጀምር፤

1) ለምዕዋ ከተማ ነዋሪህ ዝብ የተቋቋመው የበረዶ ማምረቻ ፋብሪካ፤

2) በደቀመሀሪ ከተማ የተቋቋሙት የምግብ ማምረቻዎች ማለትም፣ ግዙፍ የዳቦ መጋገሪያና ማድረቂያ፣ ግዙፍ የስንዴ ዱቄት ማምረቻ ወፍጮ፣ የፓስታና የመኮሮኒ ማምረቻ ፋብሪካዎች፣

3) የጐንደር ከተማ የሥጋ ፋብሪካ፤

4) የባህር ዳር ከተማ የምግብ ዘይት ማምረቻ ፋብሪካ፤

5) በወሎ ክፍለ ሃገር በቆቦ ከተማ በቼኮዝሎቫኪያ መንግሥት ትብብር የተቋቋመው ግዙፍ የጨርቃ ጨርቅ ማምረቻ ፋብሪካ፤

6) በአሰብ የወደብ ከተማ የነበረውን ያረጀ ትንሽ የጨው ማምረቻ ማደስና ማስፋፋት፤

7) በዚያው በአሰብ ከተማ አቅራቢያ ካሌብ ብለን በሰየምነው ግማሽ ደሴት ላይ የተቋቋመው የመርከብ መገጣጠሚያ ፋብሪካ፤

8) በወለጋ ክፍለ ሃገር በበደሌ ከተማ በቼኮዝሎቫኪያ መንግሥት ትብብር የተቋቋመው ፒልስነር የቢራ ማምረቻ ፋብሪካ፤

9) በሲዳሞ ክፍለ ሃገር በአዋሳ ከተማ የተቋቋመው ሌላው ግዙፍና ዘመናዊ የጨርቃጨርቅ ማምረቻ ፋብሪካ፤

10) በሐረርጌ ክፍለ ሃገር በሐረር ከተማ የተቋቋመው የፒልስነር ቢራ ማምረቻ ፋብሪካ፤

11) በፋሽስት ኢጣሊያ የወረራ ዘመን በድሬዳዋ ከተማ የተቋቋመውን አሮጌ የጨርቃጨርቅ ማምረቻ ፋብሪካ ማዘመንና ማስፋፋት፤

12) በአርሲ ክፍለ ሃገር በአሰላ ከተማ የተቋቋመው የቢራ ብቅል ማምረቻ ፋብሪካ፤

13) በሸዋ ክፍለ ሃገር በዘዋይ ከተማ የግንባታቸው ዝግጅት የተጠናቀቀው የሴራሚክስ ውጤት የሆኑ ልዩ ልዩ መመገቢያና የመጠጫ ቁሳቁሶችና የመስተዋት ማምረቻ ፋብሪካዎች፤

14) በአዲስ አበባ ከተማ የተቋቋሙት የተለያዩ የቆዳ ውጤት ማምረቻ ፋብሪካዎች፤

15) የኢትዮጵያ ህዝብ በየክልሉ የሚያስፈልጉትን የተለያዩ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን የማቋቋም ትምህርትና ልምድ እንዲያገኝና በተለይም የዕደ ጥበብ ባለሞያዎች በዘመናዊ ዘዴና በማህበር አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን ያቋቁሙ ዘንድ የሚያበረታቱ በኢግዚቢት መልክ እንዲመለከቷቸውና ትምህርት እንዲቀስሙ ለማድረግ በሕንድ መንግሥት ትብብር በአዲስ አበባ ከተማ በንፋስ ስልክ አካባቢ የተቋቋሙና ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን የሚያመርቱ አስራ ሁለት አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ኮምፕሌክስ፤

16) በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ በአቃቂ ከተማ በሕንድ ከበርቴዎች ተቋቁሞ የነበረውን አሮጌ የጨርቃ ጨርቅ ማምረቻ ፋብሪካ ማዘመንና ማስፋፋት፤

17) በዚያው በአቃቂ ከተማ ለንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ለግብርናው የመስኖ ልማት የሚያገለግሉ የተለያየ መጠን ያላቸውን የውሃ ማስተላለፊያ ቧንቧዎች ለማምረት በሰሜን ኮሪያ መንግሥት ትብብር የተጀመረው ፋብሪካ፤

18) በአዲስ አበባ ከተማ ከባድ የጭነት ተሽከርካሪዎችን መገጣጠሚያ ፋብሪካ፤

19) በአዲስ አበባ ከተማ ለጊዜው የአየር መንገዳችን ጥገኛ ሆኖ ከካናዳ መንግሥት በተገኘ ላይሰንስ የተቋቋመው የአነስተኛ አውሮፕላኖች መገጣጠሚያ ፋብሪካ፤

20) በአቃቂ ከተማ ለጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች፣ ለስኳር ፋብሪካዎችና ለግብርና መሣሪያዎች የመለዋወጫ እቃዎችን፣ የብረት ውጤት የሆኑ የተለያዩ የቤት እቃዎችን ለማምረት በኢጣሊያ መንግሥት ትብብር ተቋቁሞ አገልግሎት መስጠት የጀመረው የብረታብ ረት ፋብሪካ፣

21) በሆላንድ መንግሥት ትብብር በወንጂ መተሐራ የተቋቋመው ሁለተኛው የስኳር ማምረቻ ፋብሪካ፤

22) በናዝሬት ከተማ በሶቭየት ህብረት መንግሥት ትብብር የተቋቋመው የትራክተሮች መገጣጠሚያ ፋብሪካ፤



በኢትዮጵያ አየር መንገድ የኤሮኖቲካል መሃንዲሶችና እንዲሁም በልምድ በበለፀጉ የአወስሮፕላን መካኒኮች የተገጣጠመችው የመጀመሪያዋ እሸት የተባለ ስም የተሰጣት አውሮፕላን፡፡

ረ) የመሰረተ ልማቶችን ግንባታ በተመለከተ፡-

የመሰረተ ልማቶችን ግንባታ በተመለከተ በመሰረተ ልማት ወይንም (በኮንስትራክሽን) ሚኒስቴር የተገነቡትን የኢንዱስትሪዎቹን፣ የሲቪል ምህንድስና ሥራ፣ በከተማ ልማትና በኪራይ ቤቶች አስተዳደር ሚኒስቴር የተገነቡትን አያሌ መሥሪያና መኖሪያ ቤቶች ወዘተ ግንባታዎች ሳልጨምር ነው ከዚህ ግርጌ የተመለከቱትን የተወሰኑትንና ጎላ ጎላ ያሉትን ግንባታዎች ብቻ ለመግለፅ የሞከርኩት፡፡

1) ለአገራቸው አንድነትና ለህዝባዊ አብዮቱ ደህንነት ከተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት፣ ከኤርትራ ገንጣዮችና አስገንጣዮች፣ ከቀሩት ጠባብ ብሄርተኞች፣ ከፀረ ህዝብ ፊውዳሎችና ከአምስተኛ ረድፎች ወዘተ ጋር ሲፋለሙ ቆስለው ከባድ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ጀግኖቻችን አስፈላጊው ህክምና ተደርጎላቸው ከሆስፒታል ከወጡ በኋላ ረዘም ላለ ጊዜ የሚያገግሙበት ብቻ ሳይሆን ሰው ሠራሽ አካል ተሰርቶላቸው እንደልባቸው መንቀሳቀስ እንዲችሉ ከተደረገ በኋላ ከህብረተሰቡ ጋር ተቀላቀለው እንደ አቅማቸውና ዝንባሌያቸው የተለያዩ የእጅ ሞያ

ሥልጠና ለብዙ ሺህ ጀግኖች የሚሰጥና የጀግኖች አምባ በመባል የሚታወቅ ዘመናዊና ሰፊ ተቋም ግንባታ፤

2) ለአገራቸው አንድነትና ለህዝባዊ አብዮቱ ደህንነት ሲፋለሙ ጥለው የወደቁ ጀግኖቻችን ልጆችና በአሳዳጊ እጦት የጕዳና ተዳዳሪ የነበሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ህፃናት ማሳደጊያና ማስተማሪያ የሆነ እጅግ ዘመናዊና እጅግ ሰፊ የህፃናት አምባ በመባል የሚታወቅ ተቋም ግንባታ፤

3) በመጀመሪያው በ1968 ዓ.ም ሻዕቢያ የምፅዋን ወደብና ከተማውን ከአብዮታዊ ሠራዊታችን፣ አስለቅቆ ለመውሰድና የኤርትራን ክፍለ ሃገር ከተቀሩት የኢትዮጵያ ክልሎች ጋር ያለውን ግንኙነት ለመቁረጥ በአደረገው ውጊያ ያወደመውን ከተማ፣ የጦር ሠፈሮችን፣ ልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ህንፃዎችን ወዘተ መልሶ መገንባት፤

4) በጋሞ ጎፋ ክፍለ ሃገር ርዕሰ ከተማ በአርባ ምንጭ የአገሪቱን ወጣቶች በውሃ አጠቃቀምና ልማት ወይንም (በኃይድሮሎጂ) ምህንድስና ሞያ የሚያሰለጥን በተማሪዎች መኖሪያና መመገቢያ ህንፃዎች ብቻ ሳይሆን ከማስተማሪያ ክፍሎች ሌላ ከፍተኛና እጅግ ዘመናዊ በሆነ ቤተ ምርምር የተሟላ ተቋም መገንባት፤

5) በከፋ ክፍለ ሃገር ርዕሰ ከተማ በጂማ ሐኪሞችን፣ ነርሶችንና የተለያዩ የሕክምና ባለሞያዎችን የሚያሰለጥን ሦስተኛ የሕክምና ሞያ ዩኒቨርስቲ መገንባት፤

6) በአሰብ የወደብ ከተማ፣ በባህር ዳር ከተማና በጋምቤላ አውራጃ ከተማ ማለትም ዓለም አቀፋዊ ደረጃ ያላቸው ዘመናዊ የአውሮፕላን ማረፊያዎች መሰራት፤



በቅድመ አብዮት የኢትዮጵያ ህዝብ ዘጠና ሰባት በመቶ የሚሆነው መሃይም በመሆኑ በአብዮታዊው መንግስት ከማናቸው የአገር ግንባታ በላይ ቅድሚያውንና ታላቁን ትኩረት የሰጠው ለትምህርት ቤቶች ግንባታ ነበር።

ይህ ፎቶ እንደሚያሳየው የትምህርት ቤቶችን ከህዝቡ መጠንና ፍላጎት ጋር በተመጣጠነ መገንባት ብቻ ሳይሆን ለትምህርት ቤቶቹ ህንፃ ጥራትና ዘመናዊነትን ታላቅ ትኩረት ሰጥቷል ወይም ተደርጓል።

7) የተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት በአብዮታዊ ሠራዊታችን ድል ተመትቶ ወደ አገሩ ሲሸሽ የጎዴን ዘመናዊ የአይሮፕላን ማረፊያ በጠቅላላ አገልግሎት ሰጪ ህንፃዎችንና የአየር ኃይላችንን የጦር ሠፈር በፈንጂ ከማውደም ሌላ የአውሮፕላን ሜዳውን በትራክተር አርሶት ስለሄደ አዲስ የመሥራት ያህል የተደረገው መልሶ ግንባታ፤

8) በአሰብ የወደብ ከተማ ለባህር ኃይላችንና ለአየር ኃይላችን እንዲሁም ለምድር ጦራችን ከተገነቡት የጦር ሠፈሮች ሌላ በዘርአይደረስ መታሰቢያነት የተገነባው ዘመናዊ ሆቴል፤

9) በባሌ ክፍለ ሃገር በጎባ ርእስ ከተማ የተገነባው ዘመናዊ ሆቴል፤

10) ይህንን የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ በምፅፍበት ጊዜ መጠናቸውን ወይንም ርቀታቸውን በው ለማስታወስ የተሳነኝ የመሰረተ ልማት ግንባታ ሚኒስቴር በዘመቻው ጊዜ በየክልሉ በአቋቋማቸው የመንገድ ግንባታ ብረጌዶች የሰራቸው በብዙ ሺህ ኪ/ሜትር የሚገመቱ የጥርጊያ፣ ኮረት የለበሱና በአስፋልት የተገነቡ መንገዶች፤

11) በወለጋ ክፍለ ሃገር በአሶሳ አውራጃ ከተማ የተገነባው ዘመናዊ ሆስፒታል፤

12) በኢሉባቡር ክፍለ ሃገር በጋምቤላ አውራጃ ከተማ ከአንድ ዘመናዊ ሆስፒታል ሌላ ክልሉን በከፍተኛ ደረጃ ለማልማት በነበረን እቅድ መሰረት ከአንድ ሚሊዮን ሄክታር በላይ የግብርና ልማት ጥናትና 600 ሜጋ ዋት የኤሌትሪክ ኃይል ማመንጫ ግንባታ ለሚያካሂዱ በርካታ የሶቭየት ህብረት መንግሥት ባለሞያ ልዑካኖች መሥሪያና መኖሪያ የተሰሩ ህንፃዎች፤

13) በዚሁ በጋምቤላ አውራጃ ከተማ በባሮ ወንዝ ላይ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያዊያን መሀንዲሶች የተገነባው 150 ሜትር ርዝመት ያለው ታላቅ ድልድይ፤

14) በድርቅ የተጎዳው የወሎ ክፍለ ሃገር ገበሬ በጥቂቱም ቢሆን በመስኖ እንዲያመርት በቦርከና ወንዝ ላይ የተገነባው ግድብ፤

15) የወለጋን ክፍለ ሃገር ከጎጃም ክፍለ ሃገር ጋር በዘመናዊ አስፋልት አውራ ጎዳና ለማገናኘት በአባይ ወንዝ ላይ በአገራችን የመጀመሪያ የሆነ ረጅም ድልድይ ግንባታ፤

በአገራችን በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በተቋቋመበት አላማና ውስጣዊ ይዘቱ በአፍሪካ ወደር የሌለው እና እጅግ ዘመናዊ የውሃ አጠቃቀም፣ ጥበቃ፣ ግንባታና ልማት ማሰልጠኛ፣ ምርምርምና ስርፀት የሚያደርግ ኢንስቲቲዩት መገንባት።

16) የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አካል ከሆነው የኤሌትሪክ ምህንድስና ዘርፍ በተለየና በማዕድንና በኃይል ማመንጫ ሚኒስቴር የሚመራ በርካታ ወጣቶችን በኤሌክትሪክና በኤሎትሮኒክ ምህንድስና በድግሪ ከማሰልጠን ሌላ በተጨማሪ የእነዚህ ሞያዎች ከፍ

ያለ ቤተ ምርምር ያለውና ወጣቶችን ከማስተማር ሌላ በተግባርም ልምድ እንዲበለፅጉ የተለያዩ የኤሌትሪክና የኤሎክትሮኒክ ውጤት የሆኑ እንደ ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ ወዘተ የመሳሰሉ ቁሳቁሶችን የሚያመርት ተቋም መገንባት፤

17) በአርሲ ክፍለ ሃገር በአሰላ ከተማ አቅራቢያ ገበሬዎችን በተለያዩ ደረጃዎችና ሞያዎች፣ በተለያዩ ደረጃ የህብረት እርሻዎች ከማደራጀትና ከማማከር ባሻገር የቤት ኢኮኖሚ፣ የቤት ባልትና፣ የሂሳብ አያያዝና ቁጥጥር ወዘተ የሚያስተምሩ መምህራንን የሚያሰለጥን ተቋም መገንባት፤

18) በባሌና በአርሲ ክፍለ ሃገር መካከል በአጋርፋ ወረዳ ዘመናዊ ሁለገብና ግዙፍ ገበሬዎችን የተለያዩ የግብርና ሞያዎች የሚያሰለጥን ተቋም ግንባታ፤

19) በአገራችን ርዕሰ ከተማ በአዲስ አበባ የሚቀመጡ የውጭ አገር መንግሥታት ተወካይ የሆኑ ዲፕሎማቶች የምንሰራባቸው የመሥሪያ ቤት ህንፃዎችና የምንኖርባቸው ቤቶች ፍላጎታችንን የማያሟሉና የማይመጥኑ ናቸው በማለት አብዛኞዎቹ ያላቋረጠ ስሞታ ያቀርቡ ስለነበር፤ ይህንን ችግር ለማስወገድ ተብሎ ከቦሌ አይሮፕላን ማረፊያ በስተ ምዕራብ ከአሥመራ መንገድ ጋር ገጥሞ በሚገኘው እጅግ ሰፊ ሜዳ ላይ የተንጣለሉና የተለያየ መጠንና ደረጃ ያላቸው ከሁለት መቶ በላይ የሆኑ ዘመናዊ ህንፃዎች ግንባታ በጣም ጎላ ጎላ ያሉትና ለማስታወስ የተቻሉኝ የዘመቻው ውጤቶች ናቸው::

20) በመጨረሻውም ለአንባቢያን በአብዮታዊ መንግሥታችንና በፓርቲያችን ስም ለመግለፅ የምፈልገው በፕሮፌሰር ዘውዴ በተመራ ልዩ የውሃ ጥበቃ አጠቃቀምና ልማት እንዲሁም ግንባታ ባለሞያዎች ቡድን ለአገራችን ልማትና ግንባታ የሃምሳ ዓመት እቅድ መዘጋጀቱን፤

21) በከተማ ልማትና የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ሚኒስትራችን በጓድ ተስፋዬ ማሩ የተመራው የኢትዮጵያና የኢጣሊያዊያን የከተማ ልማትና ግንባታ እቅድ ዝግጅት ባለሞያዎች ቅምር የሃምሳ ዓመት የከተማ ልማትና ግንባታ እቅድ ያዘጋጀን መሆናችንን ነው፤

ለማጠቃለል፤ የምርት ዘመቻው የሦስት ዓመት አጠቃላይ ውጤት ሲገመገም በግብርናው፣ በማዕድናቱና በኢንዱስትሪው ዘርፎች፣ በኃይል ማመንጫዎችና በመሠረተ ልማት ግንባታዎች የተደረገው ዘመቻ ሴቴ ፆታዎችን ጨምሮ በወቅቱ በአገራችን ለነበሩ ሥራ አጦችና በዘኔ ዜጎች በሙሉ ማለት ይቻላል የሥራ ዕድል በመፍጠር ሠርቶ አደሮች ከማድረግ ሌላ በተከታታይ ሦስት ዓመታት በዘመቻው ወቅት ብቻ በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍለ ሃገራት ከተሞች በአጠቃላይ፣ በአገሪቱ ርዕሰ ከተማ በአዲስ አበባበ ተለይ የግል ቤት አልባና በኪራይ ቤት ነዋሪ የነበሩትን የመከላከያ ሠራዊትና የፖሊስ ሠራዊታችንን፣



በሸዋ ክፍለ ሃገር በአዋሳ አውራጃ በእንፋሎት ኃይል ወይንም(ተርማል ኢነርጂ) ለማምረት የተጀመረ ቁፈራ::

የአገሪቱን ወዝ አደሮችና መላውን የመንግሥት ሠራተኛ እንደሚያገኙት የደመወዝ መጠን ከመንግሥት ባንኮች የረዥም ጊዜ የገንዘብ ብድር እየተበደሩ በከተማ ልማትና የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ሚኒስቴር አማካኝነት ያላአንዳች ክፍያ በነፃ የከተማ ቦታ እየተመሩና መንግሥት በሚሰጠው ነፃ የምህንድስና አገልግሎት እየተረዱ የራሳቸው

የግል መኖሪያ ቤት እንዲኖራቸው ከማድረግ ባሻገር በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ከአብዮቱ መቃረቢያ ጀምሮ ለዓመታት በሚያስደነግጥ ሁኔታ አቆልቁሎ በመውረድ ጥፁም ወድቆ የነበረውን የአገሪቱን ብሄራዊ ኢኮኖሚ መልሰን በማንሳትና በመገንባት አሥራ ሁለት በመቶ ማሳደግ ተቻለ።

ይህንን የመሰለውን ብሄራዊና አብዮታዊ አኩሪ ውጤት ለማግኘት የተቻለው በመላው የአገሪቱ ሠራተኞችና አርሶ አደሮች ወዘተ ያልተቆጠበና ያላቋረጠ የጋራ ወይንም የህብረት ጥረት ነው።

በተከታታዩ የሦስት ዓመታት የምርት ዘመቻ ወቅት ከሠራተኛው መደብና ከአርሶ አደሩ ህብረተሰብ መሀከል በምርታማነት የላቀ ውጤት ያገኙ የምርት ጀግኖች የተለያዩ ሽልማቶችና የምርት ጀግና ኒሻኖች ተሸልመዋል።

(ሀ) በማዕከላዊው ብሄራዊ የዕቅድና የዘመቻ መምሪያ ውስጥ በአመራር ላይ ከነበሩ ጓዶች፤

1ኛ የዘመቻው ማዕከል መምሪያ ምክትል ሰብሳቢ የነበረው ጓድ ኃይሉ ይመኑ፣

የዘመቻው መምሪያ የተለያዩ ዘርፎች መሪዎች ከነበሩ ጓዶች፤

2ኛ ጓድ ፋሲካ ሲደልል

3ኛ ጓድ መርስዔ እጅጉ

4ኛ ጓድ አክሊሉ

5ኛ ጓድ ተኩላ ደጀኔ

(ለ) በምርት ዘመቻው መስክ ከተሰለፉት ሚኒስትሮቻችን ፤

6ኛ የመንግሥት እርሻ ሚኒስትራችን ጓድ ዩሴፍ ሙለታ

7ኛ የግብርና ሚኒስትራችን ጓድ ገረመው ደበሌ

8ኛ የመሠረተ ልማት ግንባታ ሚኒስትራችን ጓድ ካሣ ገብሬ

9ኛ የከተማ ልማትና የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ሚኒስትራችን ጓድ ተስፋዬ ማሩ፤

10ኛ የኢንዱስትሪ ሚኒስትራችን ጓድ ተስፋዬ ዲንቃ

11ኛ የማዕድንና የኃይል ማመንጫ ሚኒስትራችን ጓድ ተከዘሸዋ አይተንፍሱ

(ሐ) ከኮሚሽነሮቻችን፤

12ኛ የውሃ ልማት ኮሚሽነራችን ጓድ ዓለም

13ኛ የእርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽነራችን ጓድ ሽመልስ አዱኛ

(መ) በተፈጥሮ የአየር ንብረት ቀውስና በጦርነት ምክንያት ከመኖሪያ ክልላቸው የተፈናቀሉ ወገኖቻችንን በሰም ምድር ላይ በማሥፈር መልሶ በማቋቋምና ምርታማ ይሆኑ ዘንድ የሚያስፈልጋቸውን እርዳታ በመስጠት፣ በማደራጀት፣ ለምርት ዘመቻው በማትጋትና አመራር በመስጠት ታላቅ ሚና ከተጫወቱ የክፍለ ሃገር አስተዳዳሪ ጓዶቻችን መካከል፤

14ኛ ጓድ ካሣዬ አራጋው

15ኛ ጓድ ገዛኸኝ ወርቄ

16ኛ ጓድ ሙሉጌታ ሐጐስ

17ኛ ጓድ ስለሽ መንገሻ

18ኛ ጓድ ዘለቀ በየነ

19ኛ ጓድ አሊ ሙሳ

20ኛ ጓድ ንጉሴ ፋንታ የአብዮታዊው ብሄራዊ የምርት ዘመቻ መሪ ኮከብ ካድሬዎች ነበሩ

ክፍል ሃያ አራት

ምዕራፍ ሃምሳ አምስት

ከጦር ሜዳው ወታደራዊ ድል በኋላ ከውስጥና ከውጭ

ጠላቶቻችን ጋር የተደረገ አዲስ የሠላም ጥረት ሠላምን ፍለጋ ወደ ካርቱም ጉዞ።

ሁለተኛው ነፃ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊታችን በአደረገው የኤርትራን ክፍለ ሃገር ከገንጣዮች ነፃ የማውጣት ዘመቻ ከአስመራ ከተማ ዙሪያ ጀምሮ ገንጣዮችን እያሳደደ በመመንጠር የሱዳን መንግሥት የአስተዳደር ክልል ድንበርተኛ በሆነው የኛ የሳህል አውራጃ ከተማ በናቅፋ ወረዳ ባሉት ድርብርብና ሠንሰለታማ ተራሮች ላይ ከሰቀልናቸው በኋላ በወንድማማቾች መሀከል በሚካሄደው ፍፁም አስፈላጊ ያልሆነ የእርስ በርስ ጦርነት ያለ አግባብ የሚፈሰው ደም ቆሞ ችግሮቻችንን በጠረጴዛ ዙሪያ ተወያይተን በፖለቲካ መፍትሄ መፍታት ይቻለን ዘንድ የሠላም ድርድር መጀመራችንን መግለፄ በአንባቢ ዘንድ ይታወሳል።

ሁለቱን ገንጣይ ድርጅቶች ማለትም በቅድሚያ ራሱን በአረቢኛ ቋንቋ «ጀብሐ» ብሎ የሚጠራውንና ቀጥሎም ከአሥር ዓመት በኋላ እንዲሁ በአረብኛ ቋንቋ ራሱን «ሻዕቢያ» ብሎ የሚጠራውን ድርጅት በአረብ ሊግ አማካኝነት የሊጉ አባል የሆኑትን መላውን የአረብ መንግሥታት በማስተባበር የፖለቲካ፣ የገንዘብና የመሣሪያ ወዘተ ድጋፍ አሰባስበው በማስታጠቅና በማደራጀት ያዘመቱብን ዋናዎቹና ግንባር ቀደሞቹ አገሮች የግብፅና የሱዳን መንግሥታት ናቸው።

የሱዳን መንግሥት ከማንም ቀድሞ ለገንጣዮች የፖለቲካ፣ የገንዘብና የመሣሪያ ድጋፍ ከመስጠት ባሻገር የኢትዮጵያ ድንበርተኛ አገር በመሆኑ የአረብ መንግሥታት በየበኩላቸው ለገንጣዮቹ የሚሰጡትን ማናቸውንም ድጋፍ እየተቀበለ የሚያከማች፣ እንደ አስፈላጊነታቸው የሚያድል ብቻ ሳይሆን፣ የገንጣዮቹ መኖሪያ፣ የጦር ማሰልጠኛ፣ በውጊያ ሲቆስሉ መታከሚያቸውና በጠቅላላ መጠለያ ምሽጋቸው በመሆኑ ኢትዮጵያን በመውጋት ረገድ የአረቦችን ሊግ ወክሎ የሚያከናውነው ፀረ-ኢትዮጵያ ተግባርና በመልክአ ምድር አቀማመጥም ያለበት ቁልፍ ሥፍራ ለሚያከናውነው ፀረ ኢትዮጵያ እኩይ ተግባሩ ያለው አመቺነት ግልፅ በመሆኑ የኤርትራ ገንጣዮች ከተቋቋሙበት ጊዜ ጀምሮ በቅድመ አብዮት በአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት፣ በድህረ አብዮት በአብዮታዊው መንግሥት ለኤርትራ ችግር ሠላማዊና ፖለቲካዊ መፍትሄ ለማግኘት ሲባል የተደረጉ ጥረቶች በሙሉ ማለት ይቻላል ከማንም በላይ እንዲረዱን በተደጋጋሚ የተለመኑት በሱዳን ህዝብ የፖለቲካ ሥልጣን ማማ ላይ ሲፈራረቁ የቆዩት የሱዳን መንግሥት መሪዎችና እንዲሁም የአመራሩ አካላት ነበሩ።

ከ1960 ዓ.ም መጀመሪያ ጀምሮ በአገራችን የተከሰተው ድርቅ በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ ካደረሰው ከፍ ያለ ጉዳት በተጨማሪ የአካባቢው የፖለቲካ ቀውስና ብሎም የስዊዝ ቦይ መዘጋት ተነባብረው በአፍሪካ ቀንድ ላይ ውስብስብ ችግሮችን በፈጠሩበት ጊዜ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ ማህበራዊ አብዮት መፈንዳት በአስከተለው የመደብና የርዕዮተ ዓለም ትግልና ብሎም በተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት የሰነዘረብንን ወረራ በመመልከት መላው አድህሮት « ኢትዮጵያ አለቀላት፣ አበቃላት፣ ልትከፋፈልና ልትፈራርስ ነው» በማለት እንደ አሟረቱ የሚታወስነው።

እንደጠላቶቻችን ትንቢትና ምኞት ባይሆንም በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ በአፍሪካ ቀንድ የነበረው ወታደራዊ የኃይል ሚዛን ወደ ጠላቶቻችን ያደላ ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ያጋደለ በመሆኑ በጦር ሜዳ የማጥቃቱ ቀደምትነት በጠላቶቻችን እጅ ስለነበረ በጣም ደካማ በሆነ አቋም ላይ ሆነን በጦር ሜዳ ከሚፋለሙን የኤርትራ ገንጣዮች ጋር የሠላም ድርድር ለማድረግ መሞከር ፋይዳ የሌለው ጉዳይ በመሆኑ በቅድሚያ ወደ ጠላቶቻችን ያመዘነውን ወታደራዊ የኃይል ሚዛን ለኛ ባደላ ሁኔታ መለወጥ ነበረብን።

ከኤርትራ ገንጣዮች በመለስ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምሥራቅ፣ በደቡብና በመሀል የአገራችን ክልሎች ሲወጉን በነበሩት ፀረ-ህዝብና ፀረ-አብዮት ድርጅቶች ላይ ማለትም በጠባብ ብሄርተኞች፣ ተስፋ ለዘውድ ፊውዳሎችና በአምስተኛ ረድፎች ላይ የማያዳግም ፍልሚያ በማድረግ ቅስማቸውን ከመስበር ባሻገር የተስፋፊውን የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት በሙሉ ከአገራችን ምድር ረግጠን ከአስወጣን በኋላ እንደሚታወቀው ፊታችንን ወደ ሰሜኑ የጦር ግምባር በማዞር ገንጣዮችን ከስምንቱ የኤርትራ ክፍለ ሃገር አውራጃዎች እየመነጠርን በማሳደድ በናቅፋ ሰንሰለታማ ተራሮችላይ እስክናንጠላጥላቸው ድረስ ውጊያው ጥቂት ወራቶችን ወሰደብን።

የአብዮት ፀር የሆኑት የዓለም አድህሮትና በተለይም ኢትዮጵያን ለመከፋፈልና ለማዳከም የሚጥሩት ታሪካዊ ጠላቶቻችን ከቅዠተ ግምታቸውና ምኞታቸው ወጥተው ኢትዮጵያ እንደገል የምትሰባበርና የምትበታተን አገር ያለመሆኗን የተገነዘቡበት ጊዜ ተፈጠረ።

በታላቋ ወዳጃችን በሶቭየት ህብረትና በተቀሩት የምሥራቅ አውሮፓ ሶሻሊስት መንግሥታት ግፊትና ትብብር ከዲሞክራቲክ የመን፣ ከፍሊስጤም ነፃ አውጭ ድርጅቶች፣ ከአልጀሪያና ከሊቢያ መንግሥታት ጋር መልካም ወዳጅነትና ጤናማ ግንኙነት ጀምረን ስለነበር በእነዚህ የአረብ መንግሥታት አማካኝነት የኤርትራን ችግር የፈጠሩትን ዋናዋቹን ጠላቶቻችንን የግብፅንና የሱዳንን መንግሥት ፀረ-ኢትዮጵያ አቋም ለማስለወጥ የማይናቅ ጥረት አደረግን።

በተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊትና በኤርትራ ገንጣዮች ላይ አንፀባራቂ ድል ተቀዳጅተን በአፍሪካ ቀንንድ የነበረውን ለጠላቶቻችን ያደላ ወታደራዊ

የኃይል ሚዛን የለወጥን ቢሆንም አገራችን ኢትዮጵያና ህዝቧ የተሟላና አስተማማኝ የሆነ ዘላቂ ሠላም አገኙ የሚያሰኝ ሁኔታ ላይ ባንገኝም በተገኘው ወታደራዊ ድል ማግሥት በመሃይምነት ላይ አገር ዓቀፍ ፀረ መሃይምነት ዘመቻ በማካሄድ ላይ እያለን በተጨማሪ አገር አቀፍ፣ ብሄራዊና አብዮታዊ የምርት ዘመቻ በማወጅ የአገራችንን ኋላ ቀር የኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ለመለወጥ ቆርጠን መነሳታችን ጠላቶቻችንን ያስገረማቸው የአገራችንን፣ የህዝባችንንና የአብዮታችንን ጥንካሬ ያስገነዘባቸው ስለነበረ በምርት ዘመቻው ብሥራት ማግሥት ነው ከውስጥም ከውጪም ጠላቶቻችን ጋር እንደገና አዲስ የሠላም ድርድር ለመጀመር ያቀድነው።

ለሠላም ፍለጋ ወደ ካርቱም ለመጓዝ ያቀድንበትን ምክንያትና ከተጓዝንም በኋላ በጊዜው የሱዳን ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት ከነበረው ከጀነራል ጃፋር ኤል ኑሜሪ ጋር ስለአደረግነው ውይይት ከመግለጼ በፊት ግብፆች የአባይን ጣፋጭ ውሃና ከኢትዮጵያ ምድር እየጠራረገ የሚወስደውን ለም አፈር በመጠቀም የሚኖሩ በመሆናቸው የኢትዮጵያ ህዝብና በኢትዮጵያ ህዝብ የፖለቲካ ሥልጣን ላይ የተፈራረቁትን ሥርወ ነገሥታት ማመስገን ሲገባቸው በተቃራኒው ፀረ ኢትዮጵያ መሆናቸው ለአንባቢ ግልፅ ስለሚመስለኝ ጠላትነታቸውንና የጥፋት መልዕክተኛነታቸውን ለመዘርዘር ብዙ ወደ ኋላ ርቄ ሳልሄድ ኤርትራን በተመለከተ ብቻ ለረጅም ጊዜ የያዙትን አቋም መግለፅ አስፈላጊ ይመስለኛል።

2ኛውን የዓለም ጦርነት በአሸናፊነት የተወጡት ሦስቱ ኃያላን መንግሥታት ማለትም የሰሜን አሜሪካ፣ የብሪታኒያ ኢምፔሪያሊስት መንግሥትና የሶቭየት ህብረት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ተሸናፊዋንና በጀርመን ሠራዊት ተይዛ የነበረቺውን የፈረንሳይ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርን በመጨመር የኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች የነበሩትን ሦስት አገሮች ማለትም የሊቢያን፣ የኤትራንና የሱማሌን የወደፊት እድል ለመወሰን በብሪታኒያ ርዕሰ ከተማ በለንደን በ1945 ዓ.ም ተሰብስበው በሚነጋገሩበት ጊዜ ፋሽስት ኢጣሊያ በጦር ኃይል ወራ ከኢትዮጵያ የንጉሠ ነገሥት መንግሥት አስተዳደር ነጥላ ቅኝ ግዛቷ በማድረግ ነፃነታቸውን ገፋ በግፍና በዘር መድሎ ረግጣ ስትገዛቸው የነበሩት የሱማሌና የኤርትራ ክልል ህዝቦች ከተፈጥሮአዊ ወገኖቻቸው ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ሊቀላቀሉ ይገባል በማለት ኢትዮጵያ ባመለከተች ጊዜ በማያገባው ጉዳይ ገብቶና ከጠላቶቻችን ሁሉ ቀድሞ የኢትዮጵያን አቤቱታ በመቃወም «የኢትዮጵያ መንግሥት እንደሚለው የሱማሌና የኤርትራ ህዝቦች በታሪክ አንዳችም ጊዜ የኢትዮጵያ አካል ስለመሆናቸው ማስረጃ ካለመኖሩ ሌላ ሶማሌዎችና ኤርትራዊያን በዘር፣ በቋንቋና በሃይማኖት የሚቀራረቡትና የሚመሳሰሉት ከአረቡ ህዝብጋር ስለሆነ ነፃነታቸውን እስኪያገኙ ድረስ ከሊቢያጋር በአረብ ሊግ ሞግዚትነት ሥር ሊቆዩ ይገባል» ሲል ያሳሰበው የግብፅ መንግሥት ነበር።

የኢጣሊያ መንግሥት ቅኝ ግዛቶች የነበሩትንና ከጦርነቱ በኋላ በብሪታኒያ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ወታደራዊ አስተዳደር ሥር የሚገኙትን የሊቢያን፣

የሱማሌንና የኤርትራን ህዝቦች እድል ለመወሰን የተሰበሰቡት የአራቱ ኃያላን መንግሥታት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ተባብረውና ተስማምተው አንድ ውሳኔ ላይ መድረስ ተስኖአቸው ጉዳዩን ለተባበሩት መንግሥታ ጉባዔ አሸጋገሩት።

የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑካን ለጊዜው የሱማሌን ጉዳይ ቀዝቀዝ አድርጎ በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ መድረክ ላይ በተለይ የኤርትራን ህዝብ ነፃነትና ብሎም ከወገኑ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር መልሶ ይቀላቀል ዘንድ ረዥም ጊዜ የወሰደና እልህ አስጨራሽ የሆነ የፖለቲካ ትግል በአካሄደበት ጊዜ ዳግም በጊዜው ነፃነታቸውን አግኝተው የተባበሩት መንግሥታት ማህበር አባል የሆኑት ፓኪስታንን የመሰሉ የእስላምና የአረብ መንግሥታትን በማስተባበር የኤርትራን ጉዳይ እንደ ራሱ ጉዳይ አድርጎ ከኢጣሊያ ጋር የተቃወመንና በፅኑ የታገለን የግብፅ መንግሥት ነበር።

እንደእውነቱከሆነ ከአረቡዓለም የኢትዮጵያንህዝብታሪክናማንነት ከግብፆችየተሻለየሚያውቅአልነበረም። የግብ ፃዊያንውሸት፣ ጥላቻናተቃውሞ የሚመነጨው ኢትዮጵያን ለማዳከም ካላቸው ፅኑፍላጎትና እስትራቴጂነው።

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ታህሳስ 2/1950 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት አምስተኛ ጠቅላላ ጉባዔ የኤርትራ ክፍለ ሃገር ህዝብ ከወገኑ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በፌደሬሽን ትስስር መልሶ እንዲዋሀድ እጅግ ከፍ ባለ የድምፅ ብልጫ በሰጠው ውሳኔ መሰረት ፌደሬሽኑ ከተቋቋመ በኋላ የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ፌደሬሽኑን ሊያፈርስ አቅዷል፣ እያፈረሰም ነው ወዘተ በማለት መንግሥታችንን አዝወትረው ከሚከሱትና አያሌ አሉባልታዎችን ከሚያናፍሱት ከፈረንሳይ፣ ከእንግሊዝና ከሰሜን አሜሪካ በአሥመራ ከተማ ከተወከሉ ቆንሲል ጀነራሎችና በአዲስ አበባ ከተማ ከነበሩ የእነኝሁ መንግሥታት አምባሳደሮች ጋር በማበር የግብፅ መንግሥት ራሱን አንቱ ብሎና በማያገባው ጉዳይ ገብቶ ፀረ-ኢትዮጵያ አሉባልታዎችን አራማጅና ከሳሽ ከመሆን ባሻገር ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌደሬሽን መዋሃዷን ይቃወሙ የነበሩ በኤርትራ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪ ከነበሩና አገራቸውን ጥለው ወይንም ከድተው ለወጡ አክራሪ ፀረ-አንድነት ግለሰብ ስደተኞች የፖለቲካ ጥገኝነት በመስጠት የኢትዮጵያን ህዝብ በጐሣና በሃይማኖት ለመከፋፈል ገንጣዮችን የሚቀሰቅስ ስበትና ለፀረ አንድነት አመፅ የሚያነሳሱበት ቋሚ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነ የራዲዮ ፕሮፖጋንዳ የሚያሰራጩበት ፕሮግራም በካይሮ ከተማ አቋቋሙላቸው።

በመጨረሻም የረጂም ዘመን ኢትዮጵያን የማዳከም ስትራቴጂካዊ እቅዳቸው ሠምሮላቸው የኤርትራ ነፃ አውጭ ነኝ የሚለውን ወይንም በአረብኛ ቋንቋ ራሱን «ጀ.ብ.ሐ» ብሎ የሚጠራውን አገር ገንጣይ ድርጅት የፖለቲካ አመራር አካላትን መሥርቶና ተዋጊ ሠራዊት አደራጅቶ አዘመተብን።

በዚህ የመጽሐፉ ክፍል ምዕራፍ ሃምሳ አምስት መግቢያ እንደገለፅኩት የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ሱዳኖች የራሳቸውን ጥቅምና ብሄራዊ ደህንነት ያልተገነዘቡ

ወይም ራሳቸውን ለአደጋ አሳልፈው የሰጡ የአረቦች መሣሪያ እንጂ የኤርትራን ችግር ፈጣሪና መሪ የግብፅ መንግሥት መሆኑን ስለሚያውቅ በቅድሚያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራችን በነበሩት በአቶ አክሊሉ ኃብተ ወልድ በኋላ በአቶ ከተማ ይፍሩ አማካኝነት በመጨረሻም አፄ ኃይለሥላሴ ራሳቸው በዚህ ጊዜ የግብፅ መሪ ለነበረው ለፕሬዝዳንት ጋማል አብደል ናስር የሚካሄደው ፀረ-ሠላም ሴራ ሁለቱን የረዥም ጊዜ ወዳጅና ጎረቤት አገሮች ጨርሶ የማይጠቅም ብቻ ሳይሆን አብረን ቃል ኪዳን የገባንለት የአፍሪካን አንድነት ድርጅት ቻርተር መርህ የሚፃረር ጥፋት ስለሆነ እንዲያቆም ቢጠይቁት የጥፋት ተግባሩን ለማቆም ፈቃደኛ ሆኖ አልተገኘም።

ከዚህ ተደጋጋሚ የሠላም ጥረት በኋላ ነው የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት አረብ ነን በሚሉት የሰሜን ሱዳን ህዝብና መሪዎቻቸው እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ ነፃነታቸውንና ሰብአዊ ክብራቸውን ተገፈው በሃይማኖትና በዘር መድሎ የሚበደሉትን ደቡባዊ ሱዳኖች ነፃ የሚያወጣ የፖለቲካ ድርጅት ማቋቋምና አረቦች በሚገባቸው ቋንቋ ማናገር ግድ የሆነው።

የደቡብ ሱዳንን ህዝብ ከአረቦች የባርነት አገዛዝ ነፃ በማውጣት በኢትዮጵያ መንግሥት ድጋፍ የተቋቋመው የፖለቲካ ድርጅት በዲንቃ ብሄረሰብ ቋንቋ «አኛኛ» በመባል ነው የሚጠራው።

"አኛኛ" ማለት በደቡብ ሱዳን ሰፊ ክልል ውስጥ በብዛት የሚኖር መርዘኛና ተናዳፊ እባብ ወይንም «ኩብራ» ማለት ነው።

ምዕራፍ ሃምሳ ስድስት

አረቦች እስራኤልን የሚወጉበት መሣሪያ ለማግኘት

የተጠቀሙበት ስልትና የፖለቲካ ወረት።

2ኛው የዓለም ጦርነት ከአከተመ በኋላ የጦርነቱ ዋና ሰለባ የሆኑት የአውሮፓ አገሮች ብቻ ሳይሆኑ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ቀውሱየ ጎበኛቸው በደቡብ አሜሪካ፣ በእስያ፣ በአፍሪካና በማዕከላዊው ምሥራቅ ክልሎች የሚገኙትም ታዳጊ አገሮች ኢትዮጵያን ጨምሮ በተለያዩና ውስብስብ በሆኑ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የሽግግር ጊዜ ውስጥ የገቡበት ጊዜ ነበር።

በተለይ በደቡብ አሜሪካ፣ በእስያ፣ በአፍሪካና በማዕከላዊው ምሥራቅ ክልሎች ውስጥ ከሚገኙ አገሮች አብዛኛዎቹ ማለት ይቻላል የአውሮፓ የቅኝግዛት ኃይሎች በጦርነቱ የመዳሸቃቸውን አጋጣሚ በመጠቀም ከቅኝ ተገዥነት ቀንበር ለመውጣትና ነፃነታቸውን ለመቀዳጀት በተለያዩ ሁኔታ ማለትም እንደአስፈላጊነቱ የትጥቅ ትግልና የፖለቲካ ድርድር የጀመሩበት ጊዜ ነበር።

በዚህ ጊዜና ሁኔታ ውስጥ የነበረው የማዕከላዊው ምሥራቅ ክልል ወይንም የአረቡ ዓለም በአጠቃላይ የግብፆች ሁኔታ በተለይ ይበልጥ የተወሳሰበ የተለያዩና በእጅጉ ተፃራሪ የሆኑ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በርካታ አንጃ የፖለቲካ ድርጅቶች የተፈጠሩበት ጊዜ ነበር።

በአዲስ መልክ የተፈጠረው የአረብ ብሄርተኝነት፣ የእስልምና እምነት አክራሪ የሆነው የእስላም ወንድማማቾች ድርጅት፣ የተለያዩና ግራ ዘመም የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች መፈጠርና የኰሚኒስቶች ህቡዕ እንቅስቃሴ፣ ኰፕቲክ ክርስቲያኖች ደህንነታቸውንና ህልውናቸውን የሚያስከብርላቸው የራስ ገዝ አስተዳደርና ሲሶ የመንግሥት ሥልጣን እንዲሰጣቸው የሚጠይቅ ንቅናቄና መላውን የአረብ ህዝብ የሚያሰባስብ የአረብ ሊግ መፈጠር፤

በአረብ ሊግ መድረክ አማካኝነት ዐረ-አይሁድና ፀረ- ኢምፔሪያሊስት አቋም እየተጠናከረ መሄድ፣ የግብፅ አብዮት መፈንዳት፣ በግብፆች ቅስቀሳና መሪነት የአረብ ሶሻሊዝም በተሰኘ ርዕዮተ ዓለም የአረብ ሶሻሊስቶች አንድነት «Arb socialite union» የተባለ መንግሥታዊ አንድነት ለመፍጠር የተደረጉ ጥረቶች በማዕከላዊው ምሥራቅ ክልል መሰረታዊ የፖለቲካ ለውጦችን አስከትለዋል።

በኮሎኔል ጋማል አብደል ናስር መሪነት ተመሥርቶ የግብፅ ነፃ የጦር መኰንኖች ንቅናቄ በመባል የሚታወቀው የፖለቲካ ድርጅት በተመራው የግብፅ ህዝብ አብዮት አርአያነት በአጭር ጊዜ ውስጥና በተከታታይ በኢራቅ፣ በሶሪያ፣ በየመን፣

በአልጀሪያ፣ በሊቢያ፣ በሶማሌና በሱዳን የጦር መኰንኖች እያመፁ በየአገራቸው መንግሥታቸውን በመፈንቅለ መንግሥት እየገለበጡ የፖለቲካ ሥልጣን ያዙ።

የኢራቅና የሶሪያ ወታደራዊ መንግሥታት የምናራምደው ወይንም የምንመራው በአረብ ሶሻሊስት ሥርዓት ነው ሲሉ፣ በሊቢያዊያን በኩል «አብዮታችን አረንጓዴው አብዮት ነው። አረንጓዴው አብዮት፣ የካፒታሊዝምንም፣ የሶሻሊዝምንም ሥርዓተ ማህበር ብቻ ሳይሆን የፓርቲ አመራርንም አይቀበልም» የሚሉ ናቸው።

የአብዮቱ መሪ ኰሎኔል ሙአምር ጋዳፊ ራሱ የፈለሰፈው ንድፈ ሃሳብ የሚመራ ጠንካራ ፀረ-አይሁድና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት የሆነ የአረብ ብሄርተኝነት ሪዮት ነው።

በአረንጓዴው አብዮት ንድፈ ሃሳብ የሚመራውና «ጀማህሪያ» በመባል የሚታወቀው የሊቢያ መንግሥት በይዘቱም ሆነ በቅርፁ እስከዛሬ ከምናውቃቸውና በዓለም ላይ ካሉ የመንግሥት ዓይነቶች ሁሉ የተለየ ወይንም አምሳያ የሌለው አዲስ ዓይነት መንግሥት ነው። ጀማህሪያ ማለት በአማርኛ ትርጉሙ ህዝባዊ እንደማለት ይመስለኛል።

የአልጀሪያ፣ የየመን፣ የሱማሌና የሱዳን ወታደራዊ መንግሥታቶች የምንመራበት ርእዮተ ዓለም ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ነው አሉ።

ግብፅ፣ ኢራቅ፣ ሶሪያና ሱዳን በማዕከላዊው ምሥራቅና በአፍሪካ ቀንድ ክልሎች ኢትዮጵያን ጨምሮ የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች እነኝህን ክልሎች ከመውረራቸው በፊት እጅግ ረጂም በሆነ ጥንታዊ የነፃ መንግሥትነት በዓለም የሚታወቁ ብቻ ሳይሆኑ የጥንታዊው የሰው ልጅ ሥልጣኔ አጋሪና ተጋሪ ናቸው።

ከእነዚህ ከጠቀስኳቸው አገሮች ሌላ ዛሬ በማዕከላዊው ምሥራቅ፣ በሰሜን አፍሪካና በአፍሪካ ቀንድ ክልሎች የሚገኙ አረባዊ አገሮችና አረብ ነን የሚሉ የእስልምና እምነት ተከታይ መንግሥታት በሙሉ አረቦች የእስልምናን እምነት በዓለም ላይ ለማስፋፋት ለሦስት መቶ ዓመታት በአካሄዱት የመስቀል ጦርነት ወረው በያዟቸው ክልሎች ላይ ያቋቋሟቸውና ከመስቀል ጦርነት በኋላ በቅርቡ የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች የፈጠሯቸው ናቸው።

ግብፆች በዓለም ጥንታዊና በጥንታዊው የሰው ልጅ ሥልጣኔ ግንባር ቀደም ከመሆናቸው ሌላ የሚኖሩበት የመልክአ ምድር አቀማመጥ የህንድ ውቅያኖስን፣ ቀይ ባህርን፣ የሜዲትራኒያን ባህሮችና የውሃ መንገዶች አገናኝ የሆነው የስዊዝ ቦይ «ስዊዝ ካናል» ስትራቴጂካዊ አቀማመጥ የግብፅን ህዝብ በተለያዩ ጊዜያቶች በዓለም የተለያዩ ክልሎች ኃይል አግኝተው የተነሱ ኃያላን መንግሥታትና የቅኝ ግዛት ኃይሎች ጥቃትና ወረራ ሰለባ አድርገውታል።

ባለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት ውስጥ የግብፅ ህዝብ ቋንቋውና ሃይማኖቱ ሦስት ጊዜ ተለዋውጠዋል። ዛሬ ግብፃዊ የሚባለው ህዝብ ጥንታዊው የግብፅ ህዝብ አይደለም። አረቦች፣ ግሪኮች፣ ሮማዊያን፣ ፐርሺያዎች፣ ቱርኮች፣ ፈረንሳዮችና እንግሊዞች በወረራ ተፈራርቀውበታል።

ባለፈው አንድ ሺህ ዓመታት ውስጥ የግብፅ ህዝብ የተሟላ ነፃነትና የተረጋጋ ሠላማዊ ህይወት ኖሮት ከራሱ ወይንም ከግብፅ ህዝብ አብራክ በወጡ የአገር ተወላጅ መሪዎች የተመራው ከአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ አመት አጋማሽ ጀምሮ በኰሎኔል ጋማል አብደል ናስር ነው።

በአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች እጅግ ረጂም ለሆነ ጊዜ የተገፈፉትን ነፃነትና በአይሁዶች የተረገጠውን የአረቦች ኩራት ለማደስ ወይንም መልሰው ለመገንባት እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1952 ዓ.ም የተንቀሳቀሱት የግብፅ መኰንኖች ዓላማዎች ከዚህ ግርጌ የተመለከቱት ነበሩ።

1ኛ የብሪታኒያ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት አሻንጉሊት የነበረውን ፊውዳላዊ የዘውድ መንግሥት ለአንዴና ለመጨረሻ ማስወገድ፤

2ኛ የሶሻሊስቱን ዓለም በአጠቃላይ ታላቋን የሶቭየት ህብረት መንግሥት በተለይ የአረቡ ዓለም የትግል አጋር በማድረግ እስራኤሎችን ከምድረ ገፅ ለማጥፋት የሚያስችል የአረቦች የጋራ የመከላከያ ኃይል ለመገንባት የሚያስችል በቂና ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ለማግኘት የአረብ ብሄርተኝነትን የሶሻሊዝም ካባ ማልበስ፤

3ኛ በሶሻሊስት የኢኰኖሚ መርህ መሰረት (ሀ) በቅድሚያ በፈረንሳይና በእንግሊዝ መንግሥታት የጋራ ይዞታነት የተያዘውን የአሌክሳንድሪያን ወደብና የመርከቦች መተላለፊያ የሆነውን የስዊዝ ቦይ (የስዊዝካናል) በመውረስ የግብፅ መንግሥት ይዞታ ማድረግ፤

ለ) የገጠሩን የእርሻ መሬት፣ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶችን፣ ኢንዱስትሪዎችን፣ ባንኮችንና ማናቸውንም የገንዘብ ድርጅቶች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የህዝብ ይዞታ የማድረግ እርምጃዎች ዋና ዋናዎቹ ነበሩ።

የግብፅ አብዮታዊ መኰንኖች የወሰዱት አብዮታዊ እርምጃ በወቅቱ በአረቡ ህዝብ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ አገራት ህዝቦች አድናቆትን ሲያተርፉ በፕሬዝዳንት ጋማል አብደል ናስርና በግብረ አበሮቹ የንቅናቄው አመራር አካል አባሎች እንደ ተጠበቀው የሶሻሊስት አገሮች በአጠቃላይና በተለይ የታላቋን የሶቭየት ህብረት ልባዊ ድጋፍ አገኘ።

በቅድሚያ ወደ ግብፅ ብሎም ከዚህ በላይ ወደ ጠቀስኳቸው አገሮች ማለትም ወደሶሪያ፣ ኢራቅ፣ አልጀሪያ፣ የመን፣ ሊቢያ፣ ሶማሌና ሱዳን የሶቭየት ህብረት ሥሪት ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች በገፍ መጉረፍ ጀመሩ።

ምዕራፍ ሃምሳ ስባት

"አኛኛ" በመባል የሚታወቀው የደቡብ ሱዳን ህዝብ ነፃ አውጭ የፖለቲካ ድርጅት መቋቋም።

የሱዳን ህዝብ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የመረጠውን መንግሥት በወታደራዊ መፈንቅ ለመንግሥት ገልብጦ በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ሥርዓት ነው የምመራው ያለውን ጀነራል ጃፋር ኤል ኑሜሪን ዋና መሣሪያቸው በማድረግና የተቀናትን አረባዊ መንግሥታት አስተባብረው የሱዳንን ምድር በመጠቀም ግብፆች ራሱን «የኤርትራ ህዝብ ነፃ አውጭ» ወይም በአረብኛ ቋንቋ «ጀብሐ» ብሎ የሚጠራውን ገንጣይ ድርጅት አደራጅተው ያዘመቱብን የሶቭየት ህብረት መንግሥትን ሥሪት ዘመናዊ የጦር መሣሪያ በገፍ ስለታጠቁ ራሳቸውን የማዕከላዊው ምሥራቅ ክልል ብቸኛ ኃይልና የአረቡ ዓለም መሪ በማድረግ እጅግ በናጠጡበት ጊዜ ነው።

ከዚህ በላይ ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት በአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት በኩል ግብፆችና ሱዳኖች ህገወጥ ከሆነው ኢትዮጵያን የማጥቃት የእብሪት ተግባራቸውን እንዲያቆሙ በተደጋጋሚ ቢጠየቁ ፈቃደኞች ባለመሆናቸው ከደቡብ ሱዳን ህዝብ መሀከል ለውትድርና አገልግሎት የደረሱ ወጣቶችን በመመልመል በጀነራል ጆሴፍ ላጉ መሪነት የደቡብ ሱዳን ህዝብ ነፃ አውጭ የሆነ ድርጅት በደቡብ ሱዳን ህዝብ አጠራር «አኛኛ» በመባል የሚታወቀውን ተዋጊ ኃይል በኢትዮጵያ ምዕራባዊ ክልል በሱዳን መንግሥት ግዛት ዳርቻ ማቋቋም ተቻለ።

በሰሜን አሜሪካና በእሥራኤል መንግሥታት ትብብር ዘመናዊ ትጥቅ የታጠቀውና በዘመናዊ የደፈጣ ውጊያ ሥልት በሚገባ የሰለጠነው ነፃ አውጭ ሠራዊት ከኢትዮጵያና ከሱዳን መንግሥታት ድንበር እየተንደረደረ በመላው የሱዳን መን ግሥት ደቡባዊ ክልል ጠልቆ በመግባት በአካሄደው ብርቱ ውጊያ የጀነራል ጃፋር ኤልኑሜሪን የመከላከያ ሠራዊትና መላውን የመንግሥቱን ዐጥታ አስከባሪ ኃይሎች በሚያስደንቅ ጀግንነትና በተራቀቀ የውጊያ ሥልት እየደመሰሰ አብዛኛውን የሱዳን መንግሥት ደቡባዊ ክልል ተቆጣጠረ።

የመንግሥቱ ሠራዊት አኛኛን ከመሰለ የሰለጠነ ጉሪላ ጋር ለመዋጋት የሚያስችለው መሰናዶና ብቃት ስለአልነበረው እና ደቡባዊው ክልል በደን የተሸፈነ ምድር ለጉሪላው ንቅናቄ አመቺ ስለሆነ በደረሰበት ከፍተኛ የሞትና የመቁሰል ጉዳት መቋቋም ስለተሳነው እንዲያስከብር የተሰጠውን የጥበቃ ወይንም የውጊያ ቀጣና ያለ ትዕዛዝ በሥርዓት አልበኝነት እየጣለ ወደ መሃል ሱዳን በማፈግፈጉ የአገሪቱ መሪ ጀነራል ኑሜሪና የመከላከያ ሠራዊቱ አመራር አካሎች ብቻ ሳይሆኑ መላው የወታደራዊ መንግሥት ባለሥልጣኖች ሁሉ መሽበራቸውን የተመለከቱ የሥልጣን ተቀናቃኝ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ወታደራዊውን አገዛዝና የሶሻሊስቱን ሥርዓት

ማህበር ተቃዋሚ የሆኑ አብዛኛው የህብረተሰቡ ክፍሎች ተቃውሞ ለወታደራዊው መንግሥት ህልውና አሳሳቢ በመሆናቸው ፕሬዝዳንት ጃፋር ኤልኑሜሪ ሊቋቋሟቸውና ሊወጣው በማይችል ከፍ ያለ ችግርና አጣብቂኝ ውስጥ ወደቀ፡፡

የሶሻሊስቱን ሥርዓተ ማህበር ያልተቀበለና ለመኖር ወይንም ለማደር ሲል ብቻ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ሲያገለግል የነበረውና የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት የአቶ ከተማ ይፈሩ ጓደኛና የቅርብ ወዳጅ የነበረው ዶክተር ማንሱር ካሊድ የፕሬዝዳንት ኑሜሪን እጅግ መጨነቅና መደናገጥ ከተመለከቱ በኋላ ከኢትዮጵያዊው አቻውና ጓደኛው ጋር ተገናኝተው ከዚህ የሚከተለውን ሃሳብ አቀረቡ፡፡

«ፕሬዝዳንት ኑሜሪ የአረቦች መሣሪያ በመሆን የኤርትራን ገንጣዮች መርዳቱን እንዲያቆም በተደጋጋሚ የኢትዮጵያ መንግሥት በጠየቀ ጊዜ በኛም የሱዳን መንግሥት አካል በሆን የተለያየን ቡድኖችና ግለሰቦች፣ ወዳጃችንና ጎረቤታችን የሆነውን የኢትዮጵያ ህዝብ መበደሉንና ማሳዘኑን እንዲያቆም ጠይቀነው ነበር፡፡

የአፄ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት መውጋት ከአረቡ ዓለም ጋር የሚያኖረውና በሶቭየት ህብረት መንግሥት ዘንድ የሚያስወድደው ጠቃሚ ጉዳይ ስለመሰለው ብቻ ሳይሆን፣ የኢትዮጵያ መንግሥት በአፀፋው ሊወስድ የሚችለውን እርምጃ ባለማሰብና ባለመገመት የሰራው ታላቅ ስህተት ነው፡፡

ዛሬ ወይንም በአሁኑ ጊዜ የመንግሥቱን ህልውና በሚያሳስብ ሁኔታ ከፍ ያለ ችግር ላይ የወደቀ ስለሆነ እሱን ከዚህ ስህተቱ ወይንም እብደቱ ልናወጣውና የአካባቢያችንን በአጠቃላይ የሱዳንና የኢትዮጵያን ህዝቦች የቀየ መልካም ጉርብትና ሠላም በተለይ ልናመጣ በሚያስችለን ሁኔታ ላይ እንገኛለን ብዬ አምናለሁ፡፡

እኔና አንተ አሜሪካኖችንና እሥራኤሎችን በሚስጥር ተገናኝተን ለኤርትራ ገንጣዮች የምትሰጠውን ድጋፍ አቁመህ፣ የሶሻሊስትን ሥርዓት አውግዘህ፣ ሶቭየቶቹን ከሱዳን ብታስወጣ፣ እኛም በበኩላችን ለደቡብ ሱዳን ችግር ሠላማዊ መፍትሄ ልናገኝልህና ከጎረቤትህ ከኢትዮጵያ ህዝብና መንግሥት ጋር ልናስታርቅህ ዝግጁ ነን ብላችሁ ብትነግሩት ኑሜሪ ሳያመነታ ሃሳባችሁን ስለሚቀበል ከሶቭየቶች ብቻ ሳይሆን ከናስርና ከጋዳፊም ልንነጥለውና ወደ ምዕራቡ ዓለም መልሰን ልናመጣው እንችላለን ብለን እንነገራቸው» በማለት ዶክተር ማንሱር ካሊድ ለአቶ ከተማ ይፍሩ ሃሳቡን ሲያቀርቡ በደስታ ተቀብለው ሁለቱ ሰዎች እንደተባለው አሜሪካኖችና እስራኤሎች የቀረበላቸውን ሃሳብ በደስታ መቀበል ብቻ ሳይሆን ራሳቸውን የጉዳዩ ዋና ባለቤት ያደርጋሉ፡፡

ዶክተር ማንሱር እንዳሉት ከዚህ በኋላ ማነጋገርና ማሳመን የነበረባቸው ሁለቱን መሪዎች ማለትም ፕሬዝዳንት ኑሜሪንና አፄ ኃይለሥላሴን ነበር።

በቅድሚያ ወዳጀን አቶ ከተማን ካርቱም ጋብዤ በህብረት ለፕሬዝዳንት ኑሜሪ ሃሳባችንን ስንገልፅላቸው የሰጡን መልስ «በደቡብ ሱዳን በመካሄድ ላይ ያለውን የእርስ በርስ ጦርነት ለማቆም በሚያስችል የፖለቲካ መፍትሄ ፍፁም ተገዥ ነኝ፣ ደስታውንም አልችለውም። የምጠይቃችሁ ነገር ቢኖር ጉዳዩን እንድታጣድፉት ብቻ ነው» የሚል ነበር።

ሁለታችንም ወደ አዲስ አበባ ተመልሰን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ለማግባባትና ሠላማዊውን መፍትሄ እንዲቀበሉ ለማሳመን ያቀድነው ከአሜሪካኖችና ከእስራኤሎች የቀረበ የሠላም መፍትሄ ነው ከማለት ባሻገር ፕሬዝዳንት ጃፋር ኤል ኑሜሪ አሜሪካኖቹና እስራኤሎች ያቀረቡላቸውን የሠላም መፍትሄ በደስታ መቀበላቸውን ገልፀን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ለማግባባትና ለማሳመን ያቀድነው ከፕሬዝዳንት ኑሜሪ ጋር ካደረግነው አቀራረብ የተለየ ሲሆን የሃሳቡም አመንጪ ወንድሜ አቶ ከተማ ነው።

እንደአጋጣሚ ሆኖ በዚህ ጊዜ ውስጥ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በአፍሪካ አባትነታቸው የአፍሪካን አንድነት ድርጅት በአገራቸው ርዕሰ ከተማ በአዲስ አበባ በመመሥረታቸው፣ የአልጄሪያንና የሞሮኮን ግጭት፣ የናይጀሪያን የውስጥ የእርስ በርስ ጦርነት ለመገላገል ከአደረጉት ጥረት ሌላ ለኩንጎ ህዝብ ነፃነትና እንዲሁም ሠላም ባደረጉት አስተዋፅኦ የዓለም ሠላም የኖቤል ሽልማት እንዲያገኙ ከታጩት ጥቂት ግለሰቦች መሃከል ግንባር ቀደም ስለነበሩና ይህንንም ራሳቸው ስለሚያውቁና በታላቅ ጉጉት የሚጠብቁ መሆናቸው የታወቀ በመሆኑ፤ በሰሜን ኢትዮጵያና በደቡብ ሱዳን ክልሎች በመካሄድ ላይ ያለው አሳዛኝ የእርስ በርስ ጦርነት በሁለቱም እህትማማች አገሮችና ህዝቦች ላይ እያደረሰ ካለው ከፍ ያለ የደም መፋሰስና አያሌ የንብረት ጥፋት ባሻገር ለእርስዎ ለመስጠት የተዘጋጀው ሽልማት እንቅፋት ሊሆን እንደሚችል በማመን ነው አስቸኳይ የሠላም መፍትሄ እንዲገኝ ከአሜሪካኖችና ከእስራኤሎች ጋር መክረንና ሱዳኖችን አሳምነን በመጨረሻ ግርማዊነትዎ ዘንድ የቀረብነው። አሁንም ፈቃድዎን ለመጠየቅና ለአፈፃፀሙም መመሪያ ለማግኘት ነው በማለት ነው።

ንጉሡ እንደ ፕሬዝዳንት ኑሜሪ ወዲያው በደስታ ፈንድቀው እሽታቸውን ሳይገልፁ አሜሪካኖቹና እስራኤሎቹ በሁለታችንም በኩል ጦርነቱ እንዲቆም ለማድረግ ያቀዱት ወይንም ያቀረቡት ተጨባጭ የሠላም መፍትሄ ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ነው ያቀረቡልን።

ሊያውቁ የፈለጉትን ሁሉ ከገለፅንላቸው በኋላ የፕሬዝዳንት ኑሜሪን ሃሳብ ጠይቀውን ፈቃደኛ መሆን ብቻ ሳይሆን በጣም ደስተኛ መሆናቸውን ስንገልፅላቸው

ፈገግ ብለው የአደረጋችሁት የሠላም ጥረት የሚያስመሰግናችሁ ነው። እኛንም ደስ አሰኝቶናል። ከእንግዲህ እንደ ጀመራችሁት ጉዳይ ሳይዘገይ የሚሆነውን ሁሉ አድርጉ ሲሉ አዘዙን በማለት የሱዳን መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ዶክተር ማንሱር ካሊድ የነገሩኝ ከብዙ ዓመታት በኋላ በስደት ላይ ሆኜ ከሌላው የኢትዮጵያ ወዳጅ ከሆነው ሱዳናዊ ዶክተር ቤንጃሚን ጋር ዚምባብዌ መኖሪያ ቤቴ ሊጎበኙኝ በመጡ ጊዜ ነው።

ዶክተር ቤንጃሚን በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ ያቋቋምነውና በዶክተር ጆን ጋራንግ የተመራው የደቡብ ሱዳን ህዝብ ነፃ አውጭ ንቅናቄ በደቡባዊ አፍሪካ ተወካይ ሲሆን ዶክተር ማንሱር ካሊድ በዚህ ጊዜ በኬኒያ ናይሮቢ በተባበሩት መንግሥታት ማህበር ጽህፈት ቤት የዩኔስኮ ቅርንጫፍ ወኪል ነበር።

ሁለቱ ጓደኛሞች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ያቀዱት የሠላም ዕቅድ በሁለቱ መንግሥታት ዘንድ ማለትም በሱዳንና በኢትዮጵያ መሃከል በተግባር ይጀመር ዘንድ የወሰዱት ሁለተኛው እርምጃ ፕሬዝዳንት ጃፋር ኤል ኑሜሪ ኢትዮጵያን በመጐብኘት ምክንያት አዲስ አበባ መጥቶ አፄ ኃይለሥላሴን በመገናኘት ""በኤርትራ የተጫረውን የእርስ በርስ የሲቪል ጦርነትና ያስከተለውን ጥፋት ወጣኝ ወይንም ፈጣሪ እኔ ወይንም የኔ መንግሥት ሳይሆን ከኔ በፊት ቀድሞ ስልጣን ላይ ከነበሩ ሰዎች የተረከብኩት ችግር ነው።

በሱዳን በኩል ስለተፈፀሙት ስህተቶችና ስላስከተሉት ጥፋቶች ሁሉ ከልብ በማዘን ግርማዊነትዎን ከፍ ያለ ይቅርታ እጠይቃለሁ። ከዚህ በኋላ ከእንግዲህ ወዲያ በአስቸኳይ ችግሩን ለአንዴና ለመጨረሻ ለማስወገድ ለግርማዊነትዎ የማያዳግም ቃል እገባለሁ።

ግርማዊነትዎ እንደሚያውቀው በአገሬ በደቡብ ሱዳን የተቀሰቀሰው የትጥቅ አመፅ በንብረትና በሰው ህይወት ላይ መጠኑን ለመገመት የሚያስቸግርና እጅግ የከፋ ጥፋት እየደረሰ ስለሆነ ግርማዊነትዎ በአፍሪካ አባትነትዎ በኛ በኩል ለተፈፀመው ታላቅ ስህተት ይቅርታ በማድረግ ጥፋቱ እንዲቆምና በሁለቱ ወንድማማች ህዝቦች መሃከል ለአያሌ ምዕተ ዓመታት የቆየው መልካም ጉርብትና፣ ወዳጅነትና ሠላም ተመልሶ እንዲሰፍን ያደርጉ ዘንድ እለምናለሁ" ብለህ ተናገር ተብሎ በሁለቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ይመከርና የሱዳኑ ፕሬዝዳንት ኢትዮጵያን እንዲጎበኝ ይደረጋል።

ፕሬዝዳንት ኑሜሪ ኢትዮጵያን እንዲጎበኝ በተዘጋጀለት ፕሮግራም መሰረት አዲስ አበባ መጥቶ በሁለቱ ሚኒስትሮች እንደተመከረው ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጋር በተገናኘበት ጊዜ በአክብሮትና በትህትና አባቴ ይማሩኝ፣ ይርዱኝ በማለት ልመናውን ያቀርባል።

ሁለቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ባቀዱት መሰረት ፕሬዝዳንት ኑሜሪንና የተከተሉትን ታላላቅ የሱዳን መንግሥት ባለሥልጣኖች በአዲስ አበባ ከተማና በአካባቢዋ ባሉ የተለያዩ የመዝናኛ ሥፍራዎችን በማስጎብኘት ሱዳኖቹ ፈፅሞ ባልጠበቁት ሁኔታ የማይረሳ መስተንግዶ ከማድረግ በተጨማሪ ፕሬዝዳንቱ ከነተከታዮቻቸው በሐረር የጦር አካዳሚ የእጩ መኰንኖች መመረቂያ በዓል ላይ ከንጉሡ ጋር እንዲገኙ በማድረግ ይሸኟቸዋል።

ከፕሬዝዳንት ኑሜሪ የአዲስ አበባ ጉብኝት በኋላ ሁለቱ የአገር መሪዎች የደረሱበትን የሠላም መፍትሄ ስምምነት በተግባር የሚተረጉም ከሁለቱም አገራት የተወጣጡና ለጉዳዩ አግባብ ያላቸው ባለሥልጣኖችና እንዲሁም የተለያዩ ባለሞያዎችን ያካተተ የጋራ ኰሚቴ ተቋቁሞ በሁለቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች የጋራና የፈረቃ አመራር አንዴ አዲስ አበባ በሌላ ጊዜ ካርቱም እየተሰበሰበ በመወያየት ከዚህ የሚተከተሉትን የሠላም መፍትሄ ሃሳቦች አርቅቆ ለመሪዎቹ አቀረበ።

በሁለቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች የተመራው የሁለቱ አገራት ህብረት የሠላም ኮሚቴ ያቀረበው የሠላም መፍትሄ ረቂቅ ሃሳብ፦

ሀ) ወደ የሠላሙ መፍትሄ ሀሳብ መግቢያ

ክቡር ፕሬዝዳንት ጃፋር ኤልኑሜሪ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ግብዣ በመቀበል ለ5 ቀናት አዲስ አበባን በመጐብኘት ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጋር በተገናኙበት ጊዜ የሁለቱን አገራት ህዝቦች ጥንታዊነት፣ የረጂም ጊዜ ባለታሪክነትና መልካም ጉርብትና ከታሪክ አንፃር ብዙ ወደ ኋላ ሄደው ዳሰዋል።

የሁለቱ እህትማማች አገራት ህዝቦች ኩታገጠም በሆነ መልክአ ምድር ላይ በመኖራቸው ከአንድ ወንዝ ውሃ የሚጠጡ በመሆናቸው፣ ከሺህ ኪ/ሜትር በላይ በረዘመ የጋራ መልክአ ምድራዊ ወሰናቸው ላይ የሚኖሩትን አያሌና የተለያዩ ማህበረሰቦችና ብሄረሰቦች የታሪክ፣ የቋንቋና የባህል ትስስር በስፋት ገምግመዋል።

የአካባቢው ተስፋፊዎችና የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች አፍሪካን ለመቀራመት በተነሱበት ጊዜ ሁሉ ሁለቱ ህዝቦች አንዱ የሌላው መጠጊያና መከታ በመሆንና በመረዳዳት ያሳለፉትን ረጂም የጋራ የትግል ታሪክ አስታውሰው ተሳስረው በኖሩ ወንድማማች ህዝቦች መሀከል የጥፋት መልዕክተኛ በሆኑ ባዕዳን ጣልቃ ገብነትና ግፊት በተፈጠረው ፀረ-ሠላም ሴራ የደረሰባቸውንና በመድረስም ላይ ባለው ከፍ ያለ ጉዳት እጅግ በማዘን ከዚህ የሠላም ውል በኋላ ዳግም እንደማይደገም ቃል በመግባት ከዚህ ግርጌ በቅደም ተከተል በተመለከቱት የሠላም ውሳኔዎች ተስማምተዋል ይላል።

ፕሬዝዳንት ጃፋር ኤል ኑሜሪ ከአዲስ አበባ ወደ ካርቱም በተመለሱ ማግሥት አንድ ያልጠበቁት ከፍተኛ አደጋ ይደርስባቸዋል። የደረሰባቸው አደጋ ታሪክ ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

ሁሉቱ የኢትዮጵያና የሱዳን መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ያለውትሮአቸው አንዴ አዲስ አበባ በሌላ ጊዜ ካርቱም እየተመላለሱ በመገናኘት የሚማከሩበትን ጉዳይና ሁለቱም ከሰሜን አሜሪካና ከእስራኤል መንግሥታት ከፍተኛ ባለስጣኖች ጋር ከአደረጓቸው ግንኙነቶች ሌላ ፕሬዝዳንት ኑሜሪ በድንገትና ሳይታሰብ ኢትዮጵያን በመጎብኘት ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጋር ያደረጉትን ውይይትና የደረሱበትን የሠላም ውል ኬጂቢ. በመባል የሚታወቀው የሶቭየት ህብረት መንግሥት የውጭ አገር የሥለላ ድርጅት ጉዳዩን ሲከታተል የቆየና የሠላሙን ውል የደረሰበት ይመስላል።

የሶቭየት ህብረት መንግሥት፣ የሱዳንን ኮሚኒስት ፓርቲ፣ በሱዳን መንግሥት መከላከያ ሠራዊት ውስጥ ያሉ ተራማጅ የጦር መኮንኖችንና የሲቪሉም ህብረተሰብ፣ የማህበራዊ ሥርዓቱ ደጋፊ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን አስተባብሮ መፈንቅለ መንግሥት በማድረግ ለተወሰኑ ሠዓቶች የአገሪቱን የዜና ማሠራጫዎች፣ የቴሌቪዥንና የራዲዮ ጣቢያዎችን፣ አስፈላጊ ናቸው ያሏቸውን አንዳንድ መንግሥታዊ ተቋማት፣ መሥሪያ ቤቶችንና ባንኮችን ወዘተ በጦር ኃይል ተቆጣጥረው ፕሬዝዳንት ኑሜሪ የሱዳንን ህዝብ ማህበራዊ አብዮት ለመቀልበስ ሲያሴሩ በመገኘታቸው የአገሪቱ የጦር ኃይሎች ከሥልጣናቸው በማውረድ አብዮቱን ከቅልበሳ አድነዋል በማለት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅና የሰዓት እላፊ አዋጅ ያውጃሉ።

መፈንቅለ መንግሥቱን ያደረጉት የጦር ኃይሉ ክፍሎች ድላቸውን ባወጁ የስድስት ሰዓት ጊዜ ውስጥ በሱዳን ምክትል ፕሬዝዳንት በብ/ጀነራል አብዱል መጂድ የተመራ ሌላ የጦር ኃይሎች ክፍል፣ በሶቭየት ህብረት መንግሥትና በሱዳን ኮሚኒስት ፓርቲ ህብረት የተሞከረውን መፈንቅለ መንግሥት አክሽፈን የአማጺያኑን አመራር አካላት በቁጥጥር ሥር አውለናል በማለት አማጺያኑ የፈጠሩት ቀውስና ሥርዓተ አልበኝነት እስኪረጋጋ ድረስ የበኩላቸውን ሌላ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅና የሰዓት እላፊ አዋጅ ያውጃሉ።

የመፈንቅለ መንግሥቱ ሴራ መክሸፉን ለማስተማመን ፕሬዝዳንት ኑሜሪ ለህዝቡ ንግግር ባደረገበት ማግሥት በሱዳን የሚኖሩ የሶቭየት ህብረት መንግሥት አምባሳደርና መላው የሶቭየት ዲፕሎማቶች፣ ወታደራዊ አማካሪዎችና በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች የግንባታ ድጋፍ ሲሰጡ የነበሩ በርካታ ባለሞያዎች ሱዳንን ለቀው እንዲወጡ ይደረጋል።

የሶቭየት መንግሥት ልዑካን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሱዳን መባረር ከማንም በላይ የሰሜን አሜሪካ መንግሥት ድል ስለነበር ከማንም ቀድመው ፕሬዝዳንት ጃፋር ኤል

ኑሜሪን እንኳን ደስ አለዎት በማለት የደስታ መግለጫ መልዕክት የላኩት ዋሽንግተንና አዲስ አበባ ነበሩ።

የሶቭየት ህብረት መንግሥት ዜጎች ተጠቃልለው ከሱዳን ከወጡ በኋላ መፈንቅለ መንግሥቱን ከሶቭየቶቹ ጋር ያቀዱና ያራመዱ የጦር መኮንኖች፣ የሱዳን ኮሚኒስት ፓርቲ አመራር አካላትና መላው አባላት ለብዙ ቀናት እየታደኑ በገፍና በአሰቃቂ ሁኔታ ተረሸኑ።

ያንን እጅግ አሰቃቂ የሆነ ግድያ የተመለከቱ ሱዳናዊያንና የውጭ ዜጎች በቺሊ ኮሚኒስቶች ላይ ከደረሰው ቀጥሎ ሁለተኛውና በታሪክ ወደር የሌለው ጭፍጨፋ ብለውታል።

በካርቱም ከተማ የተፈጠረው ቀውስና ሽብር ከተረጋጋ በኋላ ለሶቭየት ህብረት መንግሥት ህፍረት፣ ለብዙ የሱዳን ዜጎች ሞት ምክንያት የሆነውን ጠንቀኛ የሠላም ውል ተግባራዊ ለማድረግ ሁለቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች መንቀሳቀስ ይጀምራሉ።

ውሳኔዎችን በተግባር ከመተርጎም አንፃር በደቡብ ሱዳን የሚካሄደውን ለነፃነት የሚደረግ የሲቪል ጦርነት በተመለከተ፤

1ኛ ደቡባዊው የሱዳን ህዝብ ከሰሜናዊው ህዝብ ጋር በእኩልነት፣ በሠላምና በመከባበር አብሮ ለመኖር ብቻ ሳይሆን ከሰሜኑ ክልል በብዙ ረገድ በእድገት ወደ ኋላ የቀረውን የደቡብን ክልል ህዝብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት የሚያፋጥን የውስጥ ራስ ገዝ አስተዳደር የ«Reginal Autonomy» ሥልጣን እንዲሰጥ፤

2ኛ ለደቡብ ሱዳን አማፂያን የነፃነት ንቅናቄ ፖለቲካዊና ወታደራዊ አመራር ሲሰጡ ለነበሩ ሹማምንት ሁሉ ከላይ እስከታች ወታደራዊ የበታች ሹማምንት ጨምሮ በነፃ አውጭው ድርጅት ውስጥ ከነበራቸው የሥራ ቦታ፣ ሥልጣንና ማዕረግ ጋር በተመጣጠነ ሁኔታ በሱዳን መንግሥት አስተዳደርና በመከላከያው ሠራዊት ውስጥ እንዲሰጣቸው ሆኖ፣ የንቅናቄው መሪ ሜ/ጀነራል ጆሴፍ ላጉ በሌፍትናንት ጀነራልነት ማዕረግ የሱዳን መንግሥት ምክትል ፕሬዝዳንትና የደቡብ ህዝብ የራስገዝ አስተዳደር ፕሬዝዳንት ሆኖ ጠቅላላው የነፃ አውጭው ንቅናቄ ምንገዙ ሠራዊት በሙሉ የሱዳን መንግሥት የመከላከያ ሠራዊት አባል እንዲሆን የሚል ሲሆን፤

በኢትዮጵያ ሰሜን በኤርትራ ክፍለ ሃገር የሚካሄደውን የመገንጠል የትጥቅ አመፅ በተመለከተ አማጺያኑ በዓይነታቸውም ሆነ በመጠናቸው የኤርትራን ክፍለ ሃገር ህዝብ ፈፅሞ የማይወክሉና በክልሉ ከሚኖር አንድ አናሳ የቤንአሚር ብሄረሰብ መሀከል የወጡና የእስልምና እምነትን ብቻ የሚከተሉ የባዕድ ምንደኞች ስለሆኑ፤

1ኛ ከሱዳን ውጭ ድርጅቱ የሚላክለት መሣሪያና ትጥቅ፣ ሥንቅና መድሃኒት፣ አልባሳት፣ ማናቸውም ቁሳቁስና ፋይናንስ በሱዳን መንግሥት በኩልና በሱዳን ምድር ወደ ኢትዮጵያ ግዛት እንዳይተላለፉ፤

2ኛ ከሱዳን መንግሥትም ሆነ የሱዳን ዜጋ በሆኑ ድርጅቶች፣ ተቋሞች፣ ግለሰቦች፣ በውልም ሆነ በግል ምንም ዓይነት ድጋፍ እንዳይሰጠው ከማድረግ ሌላ የድርጅቱ አመራር አካላት፣ የድርጅቱ ተዋጊ ሠራዊት፣ በአጠቃላይ የጀብሃ አባል የሆነ በወልም ሆነ በግለሰብ ደረጃ በሱዳን ምድር እንዳይንቀሳቀሱ፣ ሲንቀሳቀሱ ቢገኙ በሱዳን መንግሥት የመከላከያ ሠራዊት፣ የፖሊስ ሠራዊትና በመንግሥቱ የደህንነት ኃይሎች የተቀናጀ ህብረት እጃቸው ለኢትዮጵያ መንግሥት እንዲሰጥ የሚል ውል ነው።

ይህንን ለሁለቱም አገሮች ሠላምና ደህንነት ይበጃል ተብሎ የታመነበት የሠላም ውል የሁለቱ አገራት መሪዎች በፊርማቸው ከአፀደቁት በኋላ አፄ ኃይለሥላሴ የደቡብ ሱዳንን የነፃነት ንቅናቄ መሪ ጀነራል ጆሴፍ ላጉን ቤተ መንግሥታቸው አስጠርተው ከሱዳኑ መሪ ከፕሬዝዳንት ጃፋር ኤል ኑሜሪ ጋር ያደረጉትን ሰፊ ውይይትና የደረሱበትን የሠላም ውል አስረድተው «ስለሠላሙ መፍትሄና በሁለቱ አገሮች መሀከል የተደረሰበትን ውሳኔ ለንቅናቄው የአመራር አካላትና ለመላው ሠራዊት አስረድተህና ውጊያውን አቁመህ የሱዳን መንግሥት ምክትል ፕሬዝዳንትና የደቡብ ራስ ገዝ አስተዳደር ፕሬዝዳንት ሆነህ በሠላም ኑር» ብለው ይነግሩታል።

በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ ዳግም በኛ ድጋፍ ለሁለተኛ ጊዜ የተቋቋመው የደቡብ ሱዳን ህዝብ ነፃ አውጭ ንቅናቄ መሪ ዶክተር ጆን ጋራንግ በዝርዝር እንዳስረዳኝ ጆሴፍ ላጉ በታላቅ ሐዘንና ቅሬታ «የግርማዊነትዎ መንግሥት ለአሥራ አንድ ዓመታት ከፍ ያለ የትጥቅ፣ የቁሳቁስና የፋይናስ ወጪ አውጥቶ እኛ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሆኑ የደቡብ ሱዳንን ህዝብ ልጆች ህይወት ሰውተን፣ በአሸነፍንበትና ለነፃነት በተቃረብንበት ጊዜ እኛን ሳያማክሩን እንዲህ ያለ ውሳኔ እንዴት ይሰጣሉ?» ብሎ ሲጠይቃቸው ንጉሣችሁ ክፉኛ ተቆጥተው «ያልኩህን አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ አድርገህ ባትገኝ ከፕሬዝዳንት ኑሜር ጋር ሆኜ እወጋሀለው አሉት» ብሎ ነው የነገረኝ።

ይሄ ደግሞ እውነት ነው። ይህንን የሰማሁት ከዶክተር ጆን ጋራንግ ብቻ ሳይሆን ከብዙ የደቡብ ሱዳን ታጋዮች እንደበት ነው።

በዚህ ጊዜ ዶክተር ጆን ጋራንግ ወጣት የማካራሬ ዩኒቨርስቲ በመጀመሪያ ዲግሪ ተመራቂና በጀነራል ጆሴፍ ላጉ በተመራው የደቡብ ሱዳን ነፃ አውጭ ንቅናቄ ውስጥ መስመራዊ መኮንን ነበር።

አንባቢ በሱዳንና በኢትዮጵያ መንግሥት መሃከል የተደረገውን የሠላም ውል ተመልክቶ ለመረዳት እንደሚችለው በሱዳን መንግሥት በኩል የደቡብን ህዝብ ነፃ አውጭ ንቅናቄ በማያዳግምና ሊያንሠራራ በማይችል ሁኔታ ፈርሶ፣ የንቅናቄው አመራር አካላትና ጠቅላላው ሠራዊት የሱዳን መንግሥት አካል ስለሆኑ የሱዳን መንግሥትና ጠቅላላው የሱዳን ህዝብ አስተማማኝ ሠላም በማግኘት ለአሥራ አንድ ዓመታት የተካሄደ የእርስ በርስ የሲቪል ጦርነት ፈፅሞ ለመቆሙ እርግጠኛ በመሆን በሠላሙ ውል ታላቅ ድል ተቀዳጅተዋል ማለት ይቻላል።

በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ከሠላሙ ውል እንደሚጠበቀው ከሱዳን መንግሥት ግዛት ውጭም ሆነ በሱዳን ውስጥ ራሱን «ጀ.ብ.ሐ» ብሎ በሚጠራው ገንጣይ ድርጅት ምንም ዓይነት እርዳታ እንዳያገኝ፣ የጀብሐ አባላት በወልም ሆነ በግለሰብ ደረጃ በሱዳን ምድር እንዳይንቀሳቀሱ ስለመደረጉ ከውሉ መንፈስና ፕሬዝዳንት ኑሜሪ ከገቡት ቃልና በሰነድ ላይ ከፈረሙት ፊርማ በስተቀር ማወቂያና መቆጣጠሪያ ዘዴ በሠላሙ ውል ሰነድ ላይ የሰፈረ ማስተማመኛ ነገር ያለመ ኖሩ ጉዳይ ተነስቶ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ለሱዳን መንግሥት ለቀረበው ጥያቄ፣ የሱዳን መንግሥት በሠላሙ ውል ሰነድ ላይ የገባውን ግዴታ ተግባራዊ ማድረጉን ለማረጋገጥ በሱዳን ምድር በየትኛውም ቦታና በማናቸውም ጊዜ፣ በሌሊትም ሆነ በቀን ብርሃን እንደፈለገ ብቻውንና ከሱዳን መንግሥት የመከላከያ ኃይሎች፣ የፖሊስ ሠራዊትና ከሃገሪቱ ብሄራዊ የደህንነት ሠራተኞች ጋር እየተገናኘና እየተማከረ በሱዳን የባህር በሮችና ወደቦች፣ በአይሮፕላን ማረፊያዎች፣ በየብስ ኬላዎች፣ መንገዶች፣ መግቢያና መውጫዎች፣ ከውጭ ወደ ሱዳን ምድር የሚገቡትን፣ ከሱዳን ምድር ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ወይንም ወደ ኤርትራ ክፍለ ሃገር የሚገቡትን ማናቸውንም ቁሳቁሶችና የጀብሐ አባላት በየህዝቡ መናኸሪያዎች ወይንም ከተሞች፣ በየሆቴሎች፣ በህዝቡ የግል መኖሪያ ቤቶችና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሁሉ በመከታተል ለመቆጣጠር የሚችል በአንድ ኢትዮጵያዊ የጦር ወይንም የፖሊስ ከፍተኛ መኰንን የሚመራ ተቆጣጣሪና መርማሪ ቡድን ተቋቁሞ ሊሠራ የሚችልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ ለማስተባበርና ለመተባበር ዝግጁ ነን የሚል ሃሳብ ቀረበ።

የኢትዮጵያ መንግሥት የደቡብ ሱዳንን ችግር አስመልክቶ ይበጃል በሚል ካአቀረበው የሠላም መፍትሄ ለሰሜን ኢትዮጵያ ችግር በሠላም መፍትሄነት ይበጃል ብሎ ያቀረበውና የሱዳን መንግሥት ተግባራዊ እንዲያደርገው የተፈለገው መፍትሄ በጣም የተለየ በመሆኑና የሠላሙ ውል ተግባራዊ መሆኑን ለማረጋገጥ የሱዳን መንግሥት ከአቀረበው ሃሳብ የተለየ ወይንም የተሻለ ሃሳብ ለማቅረብ ባለመቻሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ሃሳቡን እንዳልተቀበለ።

በሠላሙ ውል መሠረት የሱዳን ደቡባዊ ህዝብ ነፃ አውጭ ድርጅት «አኛኛ» ከኢትዮጵያ ምድር ነቅሎ በመውጣትና ወደ ሱዳን መንግሥት አስተዳደር ክልል በመግባት ለፕሬዝዳንት ጃፋር ኤል ኑሜሪ መንግሥት በሠላም ትጥቁን አስረክቦ

ከፈረሰ በኋላ የሱዳን መንግሥት ለሠላሙ ውል አስተማማኝነትና ዘላቂነት የሚበጀውን የብሄራዊ ደህንነት ጉዳይና የደቡብ ሱዳን ነፃ አውጭ ሠራዊት ከሰሜኑ የመንግሥት ሠራዊት ጋር የመዋሀዱን ጉዳይ እስኪያጠናቀቅ ድረስ የጀብሐ ሠራዊት በሱዳን ምድር የሚያደርገውን እንቅስቃሴና በኤርትራ ክልል ሲያካሄድ የነበረውን የሽብር ተግባር ለጥቂት ወራት ያቆመ መሰለ ወይም አስመሰለ።

ሱዳንን በመሰለ ሰፊ አገር ቋንቋውን በማያውቁት ህዝብ መሃከል በመዘዋወር ለጀብሐ ከተለያዩ የአረብ መንግሥታት ወደ ሱዳን የሚላከውንና ከውጭም ሆነ ከሱዳን መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ ግዛት የሚገባውን መሣሪያ፣ ትጥቅና ሥንቅ፣ አልባሳት፣ መድሃኒትና ቁሳቁስ ሁሉ አምስት ሰዎች ያሉት የኢትዮጵያ ቡድን ካርቱም በሚገኘው የኢትዮጵያ አምባሳደር፣ በኤምባሲው ኢትዮጵያዊ ሠራተኞች፣ በወታደራዊ አታሼውና በጥቂት የሱዳን መንግሥት የደህንነት ጥበቃ ሰዎች የግብር ይውጣ እርዳታ በመከታተልና በመቆጣጠር የጀብሐ ንቅናቄ ሊገታ ይችላል ማለት ዘበት ነበር።

ፕሬዝዳንት ጃፋር ኤልኑሜሪና የመንግሥቱ ባለሥልጣኖች የእነሱን ሠላምና ደህንነት ለማግኘት ሲሉ የበኩላቸውን ግዴታ ይወጣሉ ተብሎ በኢትዮጵያዊያን በኩል እንዲታመን ያደጋጁን መሆናቸውን አንባቢ ይረዳል ብዬ እገምታለሁ።

መገመት ብቻ ሳይሆን በሁለቱ መንግሥታት መሃከል የተደረገው የሠላም ውል በሱዳኖች በኩል በሀቅ የታዬ ልባዊ ውል ሳይሆን ፋይዳ የሌለው ባዶ ወረቀት መሆኑን ከዚህ እንደሚከተለው በሂደት እንረዳለን።

በሱዳን መንግሥትና በጀብሐ መሃከል በሱዳን መንግሥትና የጀብሐ አደራጅና አዝማች በሆኑት አረባዊያን መንግሥታትና እንዲሁም በጀብሐና በአረባዊያን መንግሥታት መሀከል ከኢትዮጵያ መንግሥት የተሰወረ የረቀቀ ሸፍጥና ሴራ የተጎነጎነ ስለመሆኑ አያጠያይቅም።

ከሱዳን መንግሥት የአስተዳደር ክልል ውጭና ከሱዳን መንግሥት ለጀብሐ የሚሰጠው ማናቸውም ዓይነት የቁሳቁስና የገንዘብ ድጋፍ የጀብሐ አመራር አካላትና የጀብሐ ሠራዊት በሱዳን ምድር መንቀሳቀሳቸውን የሚገታና የሚያቆም ምንም ዓይነት እርምጃ በሱዳን መንግሥት አልተወሰደም።

የጀብሐን እንቅስቃሴ በሱዳን እንዲከታተልና እንዲቆጣጠር ተብሎ ካርቱም ከተማ ላይ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ቡድን የፈየደው አንዳችም ነገር አልነበረም።

በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ በኢትዮጵያ የነበረው የሠላምና ፀጥታ ችግር «ጀብሐ» ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል የጀመረው የትጥቅ አመፅ ብቻ ሳይሆን በሲዳሞ፣ በባሌና በሐረርጌ ክፍለ ሃገራት ውስጥ ጠባብ ብሄርተኞችና የተስፋፊው የሱማሌ

መንግሥት ምንደኞች ከሚካሄዱት የሽብር ተግባር ሌላ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በሃገር ውስጥና በ ውጭ ሃገር በተለይም በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰበት ጊዜ ነበር።

ተማሪው መሬት ላራሹ በማለቱ፣ ፍትሀዊና ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር በመጠየቁ ብቻ ፋሽስታዊው የአፄ ኃይለሥላሴ ፊውዳል መንግሥት በአገሪቱ ወህኒ ቤቶች እያጎረና እየገደለም ነው በማለት ተማሪው በብዛት በተደራጀባቸው የዓለም ክፍሎች ማለትም በሃገር ቤት፣ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ወዘተ የመንግሥቱ ቁንጮ የሆኑትን ንጉሥ በዓለም ፊት ስላጋለጣቸው ብዙ የጠበቁትና በእጅጉ የጓጉለት የኖቤል ሽልማት የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ።

የሱዳንና የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች አቶ ከተማ ይፍሩና ዶክተር መንሱር ካሊድ ከኖቤል ሽልማት ጋር ያያይዙት የሠላም ውል ለሱዳን መንግሥት በሚገባ ሠርቶና ጠቅሞ በኢትዮጵያ በኩል ፋይዳ ቢስ ሆኖ በመክሸፉ በኤርትራ የጀብሐ የሽብር ተግባር እንደገና በገሐድ ከመቀጠሉ ሌላ ራሱን «የኤርትራ ህዝብ ነፃ አውጭ ግንባር» ወይንም በአረብኛ ቋንቋ «ሻ.ዕ.ቢ.ያ» ብሎ የሚጠራ ሌላ ገንጣይ ድርጅት ተጨመረ።

በኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ አንድና በዚህም በቅፅ ሁለት በየአጋጣሚው እንደገለፅኩት በስዊዝ ቦይ መዘጋት ምክንያት የኢትዮጵያ የውስጥና የውጭ ንግድ በአስደንጋጭ ሁኔታ አሽቆልቁሎ መውረድ፣ የነዳጅ ዘይት አምራች የሆኑ አረባዊ መንግሥታት እስራኤልንና የእስራኤል ደጋፊ የሆኑትን ምዕራባዊ መንግሥታት ለመበቀል ሲሉ በነዳጅ ዘይት ዋጋ ላይ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ ማድረጋቸውና በዚሁ የጊዜ ክልል ውስጥ በኢትዮጵያ የተከሰተው የአየር ንብረት ቀውስ በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ ባደረሰው ከፍ ያለጉዳት ምክንያት የግብርናው ምርት የቀነሰበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮት መቃረቢያ ስለነበረ የፕሬዝዳንት ጃፋር አል ኑሜሪ ክህደትና ሸፍጥ በኤርትራ እየተባባሰ ለሄደው ችግር ምንም ዓይነት መፍትሄ ማግኘት ባልተቻለበት ጊዜ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮት ፈንድቶ አፄ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣናቸው ወረዱ።

በአፄ ኃይለ ሥላሴና በፕሬዝዳንት ጃፋር ኤል ኑሜሪ መሃከል የኢትዮጵያን ሰሜናዊ ክልልና የሱዳንን ደቡባዊ ክልል የሲቪል ጦርነት ለማቆም የተደረገው ጥረትና የተገኘው ውጤት የጠቀመውና ያስደሰተው ሱዳኖችንና አሜሪካኖችን ብቻ ሆኖ ቀረና በድህረ አብዮት ሁሉንም ችግር አብዮታዊው መንግሥት ተረከበ።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘውዳዊ መንግሥት ከሥልጣን በወረደ ማግሥት የተተካው አዲሱ አብዮታዊ መንግሥት ለቅርብና ለሩቅ ጉረቤቶቻችን፣ ለአብዛኛው የአፍሪካ መንግሥታትና ለሌሎችም ከአፍሪካ አህጉር ውጭ በዓለም የተለያዩ ክልሎች ለሚኖሩ ወዳጅ አገሮች በኢትዮጵያ ሥርነቀል የሆነ ማህበራዊ የፖለቲካ ሥርዓት

ለውጥ ያስፈለገበትን ምክንያት ለማስረዳትና ወዳጅ ከሆኑ ከሁሉም አገሮች ጋር አገራችን የነበራትን የቆዬ መልካም ጉርብትና፣ ግንኙነትና ወዳጅነት በበለጠ ለማጠናከር ያላትን ፍላጎት የሚያስረዱ በርካታ መልዕክተኞች ወደ ተለያዩ አገሮች ስንልክ በቅድሚያ ከበርካታው ልዑካን የተለየ መልዕክት ይዞ በፕሬዝዳንት ጃፋር ኤልኑሜሪ ወደ ሚመራው የሱዳን መንግሥት የሄደው በደርግ ም/ሊ.ቀ መንበር በጓድ ሻለቃ አጥናፉ አባተ የተመራ ከፍተኛ የልዑካን ቡድን ነበር።

ጓድ ሻለቃ አጥናፉ አባተ የተላከው አብዮታዊት ኢትዮጵያ የምትመራበትን የውጭግንኙነት መርህ ማለትም ከሁሉም መንግሥታት ጋር በሠላም አብሮ የመኖር፣ የመልካም ግንኙነት፣ የመልካም ጉርብትና መርሆ ለማስረዳት ብቻ ሳይሆን፣ በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ በፕሬዝዳንት ጃፋር ኤል ኑሜሪና በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥታት መሃከል፣ የኢትዮጵያን ሰሜናዊ ክልልና የሱዳንን ደቡባዊ ክልል የሲቪል ጦርነት በማቆም በሁለቱ ጐረቤታማ አገሮች መሃከል ለረዥም ጊዜ የቆየውን ወዳጅነትና መልካም ጉርብትና መልሶ ለማደስና ለመገንባት ብዙ የተደከመበት የሠላም ውል ያገለገለው የሱዳንን መንግሥት ብቻ ሆኖ የሱዳን መንግሥት ለሰላሙ ውል የገባውን ግዴታ ባለመወጣት በፈፀመው ክህደት ምክንያት ኤርትራ ተብሎ የሚጠራውን ክፍለ ሃገራችንን ከኢትዮጵያ እንዲገነጥሉ በተለያዩ ጊዜና በተከታታይ እድምተኞቻችሁ ከሆኑት የአረብ መንግሥታት ጋር በመመሳጠርና በመተባበር አደራጅታችሁ ያዘመታችሁብን ሁለት ገንጣይ ድርጅቶች እስከ ዛሬ የኢትዮጵያን ህዝብ ሠላምና ፀጥታ በእጅጉ ከማወክ ባሻገር በእርስ በርስ ጦርነት የኢትዮጵያዊያን ደም ሲፈስ እየተመለከታችሁ በመደሰት በሠላም ለመኖር አትችሉም ብሎ ለፕሬዝዳንት ኑሜሪ እንዲያሳውቅ ስለነበር የአብዮታዊውን መንግሥት መልዕክት በግልፅነትና በምሬት አቅርቧል።

ጓድ አጥናፉ ያቀረበውን የኢትዮጵያ መንግሥት ስሞታ ያዳመጠው የሱዳኑ ፕሬዝዳንት በተለመደው ውሸትና ኃላፊነት በጎደለው ስሜት የሰላሙን ውል ግዴታችንን በበኩላችን በሚገባ ተወጥተናል በማለት የእኛን ስሞታ ስላስተባበለ ጓድ ሻለቃ አጥናፉ «አዲሱ የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት ፍላጎትና ዓላማ ወንድም ከሆነው የሱዳን ህዝብ ጋር በመልካም ጉርብትናና በሠላም አብሮ ለመኖር ነው። እናንተ እየሠራችሁ ያላችሁትን ስህተትና ታላቅ ጥፋት እኛም እንድንደግመው አታስገድዱን» በማለት ለሱዳኖች ብርቱ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ነው የኢትዮጵያንን ልዑካን መርቶ ወደ አገሩ የተመለሰው።

ጓድ ሻለቃ አጥናፉ አባተ ከሱዳን ተልዕኮው እንደተመለሰ የሱዳንን መንግሥት የአመራር አካላት በተመለከተ የታዘበውንና በተለይም የፕሬዝዳንቱን መልስ ለደርጉ ጉባዔና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በገለፀልን ጊዜ በሱዳን ላይ ከፍ ያለ ቁጣ ቀስቅሶ ነበር።

ጓድ ሻለቃ አጥናፉ ለፕሬዝዳንት ኑሜሪ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ በአስቸኳይ በተግባር መተርጎም የሁላችንም ፍላጎት ቢሆንም የአገራችን ውስጣዊ ባለ ብዙ ፈርጅ ውስብስብ ችግሮችና ውጥረቶች ያላስቻሉን ሲሆን በዚሁ ጊዜ ውስጥ ማለትም በ1969 ዓ.ም የተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት የጦር ኃይል ወረረን።

የሱዳን መንግሥት አመራር አካላት ጓድ ሻለቃ አጥናፉ በሰጣቸው ማስጠንቀቂያ የሰጉ ይመስላል ደቡባዊ ሱዳኖች በደቡብ ሱዳን ክልል የሚያደርጉትን ማናቸውንም እንቅስቃሴና በተለይም ከእኛ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለመግታት ከኢትዮጵያ ጋር በሚያዋስኗቸው የጠረፍ ከተሞች ማለትም በከሰላ፣ በሁመራ፣ በአብደራፊ፣ በመተማ፣ በአሶሳና በአኮቦ ወዘተ በአየር ኃይል የተደገፉ በርካታ ሜካናይዝድና እግረኛ ሠራዊት አቅርበው ድንበሩን ከማጠር ባሻገር ራሱን የኢትዮጵያ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ህብረት ብሎ የሚጠራውንና በነልዑል ራስ መንገሻ ስዩም እና በነጀነራል ነጋ ተገኝ የሚመራ የፊውዳሎች ጥርቅም የሆነ ፀረ ህዝብና ፀረ አብዮት ድርጅት ሠራዊት በሱዳን ምድር አደራጅተው በሰሜን ምዕራብ የአገራችን ክልል አዘመቱብን።

በሱዳኖች ሸፍጥና ክህደት ፍሬ አልባ የሆነ የሠላም ውል።

ምዕራፍ ሃምሳ ስምንት

በድህረ አብዮት በአብዮታዊው የኢትዮጵያ መንግሥት የተደገፈ የደቡብ ሱዳን ህዝብ ነፃ አውጭ ድርጅት መቋቋም፡፡

የአንድነታችንና የአብዮታችን ፀሮች የሆኑ ጠላቶቻችንን በሰሜን እየተከላከልን በምሥራቅ ማጥቃት በሚለው የደርግ የውጊያ ስትራቴጂ መሰረት የተስፋፊውን የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት መልሶ ለማጥቃት ያስፈለገን የውጊያ መሰናዶና ከኢትዮጵያ ምድር ረግጦ ለማስወጣት የተደረገው ውጊያ ሰባት ወር ያህል ጊዜ ወሰደብን፡፡

ቀደም ብዬ ለአንባቢ እንደገለፅኩት የኤርትራን ክፍለ ሃገር ከገንጣዮች የማፅዳቱ ውጊያ ስምንተኛው የክፍለ ሃገሩ የመጨረሻው የሳህል አውራጃ ከተማ የሚገኝበት በናቅፋ ተራሮች ጥግ በደረሰ ጊዜ ከ1966 ዓ.ም መጀመሪያ ጀምሮ በየዓመቱና በተለያዩ ሰው ሠራሽ ችግሮችና የተፈጥሮ የአየር ንብረት ቀውስ ምክንያት አቆልቁሎ መውረድ የጀመረው ጠቅላላ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ከ1970 እስከ 1972 ዓ.ም እጅግ አሳሳቢ በሆነ ሁኔታ ላይ ደርሶ ለመከላከያ ሠራዊታችን የሚቀርብ ቀለብ እስከማጣት ደረጃ ስለደረስን ይህንን ሁኔታ በአስቸኳይ ለመለወጥ እንደሚታወቀው ከውጊያው ፊታችንን ወደ ብሄራዊና አብዮታዊ አገር አቀፍ የምርት ዘመቻ ማዞር በመገደዳችን በፕሬዝዳንት ጃፋር ኤልኑሜሪ የሚመራው የሱዳን መንግሥት የአረቦች አባሪና ተባባሪ መሣሪያ ሆኖ ስለሚያኪያሄዱብን የእጅ አዙር ጦርነት፣ ጓድ ሻለቃ አጥናፉ በሰጣቸው ማስጠንቀቂያ መሰረት እነሱ በሚገባቸው ቋንቋ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ አልቻልንም ነበር፡፡

ገንጣዮችን ከኤርትራ ምድር ለማፅዳት የተጀመረው ዘመቻ በሳህል አውራጃ ናቅፋ ተራሮች ጥግ ደርሶ በደቡብና በምሥራቅ እንዲሁም በሰሜንም አንፃራዊ ሠላም አግኝተን በነበረበት ጊዜ በሱዳን መንግሥት ላይ እኛ ምንም ዓይነት በደል ሳንፈፅም ለአረቦች መሣሪያ ሆኖ በአገራችን ሰሜናዊ ክልል ለኤርትራ ገንጣዮች ድጋፍ በመስጠት ለሚያደርስብን ጥቃት አፀፋ በደቡብ ሱዳን የመንግሥቱ ተቃዋሚ የሆኑትን ታጋዮች በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በማስታጠቅ መበቀል ያለብን አሁን ነው የሚል ጥያቄ በደርግ ጠቅላላ ጉባዔና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተነስቶ ብዙ ውይይት ከተደረገበትና በአስቸኳይ ወደ በቀል እርምጃ እንድናመራ ከፍ ያለ ግፊት ተደርጎ ጉዳዩን ያዘገየነው እኔና በአመራር ላይ የነበሩ ጥቂት ጓዶች ነበርን፡፡

በደቡብና በምሥራቅ የአገራችን ክልሎች ወራሪው የሱማሌ መንግሥት የጦር ኃይል ተሸንፎ ቢባረርም በአልሞት ባይ ተጋዳይነትና በተለይም አብዮታዊ ሠራዊታችን በጠቅላላ ኃይሉ በሰሜን ገንጣዮች ላይ እንዳያተኩር ለማድረግና ኃይላችንን ለመከፋፈል በደቡብ ናበምሥራቅ የአገራችን ክልሎች እንደተለመደው

ሠርጎገብ ሽብር ፈጣሪዎቹን እየላከ በውጊያ ያገኘነውን አንፃራዊ ሠላም ማደፍረስ ህዝቡን መልሰን ለማቋቋምና በጦርነቱ የፈረሱትን ወታደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ግልጋሎት ሰጪ ተቋማትን መልሰን ለመገንባት የምናደርጋቸውን ጥረቶች በማወክ ላይ ያለበት ጊዜ ከመሆኑ በላይ የሰሜኑ የነፃ ማውጣት ወታደራዊ ዘመቻ በተሟላ ድል አላጠናቀቅንም ነበር።

እንደሚታወቀው አገራችንን ከገጠሟት አያሌ ሰው ሰራሽ ችግሮች ባሻገር ተፈጥሮም እየታገለን ስለነበር በአደገኛ ሁኔታ የወደቀውን የአገራችንን ኢኮኖሚ መልሰን በማንሳት ለመለወጥ የተዘጋጀንበት ብሄራዊና አብዮታዊው የምርት ዘመቻ የሚጠይቀን የገንዘብ ወጭ መጠን እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ የሚያስፈልገንን ለማግኘትና የጎደለንንም ለማሟላት ከዓለም ባንክ፣ ከአውሮፓ ህብረት፣ ከወዳጅ ሶሻሊስት አገሮች፣ ከአፍሪካ ባንክና ወዳጅ ከሆነው የሊቢያ መንግሥት ከፍያ ለብድር ለመበደር የተገደድንበት ጊዜ ነበር።

በእንደዚህ ያሉ ሁኔታዎች ላይ እያለን የሱዳን መንግሥት ተቃዋሚ የሆኑ የደቡብ ሱዳን ታጋዮችን በማሰባሰብ አልብሰን፣ መግበን፣ በመጠናቸው ብዛት፣ በውጊያ ብቃት ከሱዳን መንግሥት ሠራዊት በጣም የላቀ ጥራት ኖሯቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ደቡብ ሱዳንን ከሰሜኑ ለመገንጠል የተሳካ ውጤት የሚያስገኙ የደፈጣ ውጊያ ተዋጊዎች አደራጅተንና አስታጥቀን ለማሰማራት የሚጠይቀንን የገንዘብ ወጪ ስናሰላው ከፊሉን የአገራችንን የመከላከያ በጀት የሚሻማ ሆኖ ስለተገኘ እዚህ ችግር ውስጥ ከመግባታችን በፊት ያለ ብዙ ድካምና ያለ ብዙ የገንዘብ ወጪ ከሱዳኖች ጋር ሠላም ፈጥረን የኤርትራን የሲቪል ጦርነት ለማስቆም ይቻል እንደሆን ዳግም ለአንዴና ለመጨረሻ እንሞክር ብለን እኔና ጥቂት ጓዶች ያቀረብነው ሃሳብ በአብዛኛው የመንግሥታችን አመራር ጓዶች ስለተደገፈ ብሄራዊና አብዮታዊ የምርት ዘመቻውን አብሣሪ ከሆነው ህዝባዊ ሠልፍ ማግሥት በኔ የተመራ ልዑካን በ1974 ዓ.ም በመስከረም ወር ለሠላም ፍለጋ ወደ ካርቱም ተጓዘ።

የልዑካኑ አባላት ከነበሩት መካከል ይህንን የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ ሁለት በምጽፍበት ጊዜ የማስታውሳቸው የመከላከያ ሚኒስትራችን ጓድ ሌ/ጀነራል ተስፋዬ ገብረኪዳን፣ የማዕድን ሚኒስትራችን ጓድ ኃይሉ ይመኑ፣ የአገር አስተዳደር ሚኒስትራችን ጀነራል ታዬ ጥላሁን፣ የፍርድና የፍትህ ሚኒስትራችን ጓድ አማኑኤል አምደ ሚካኤል፣ የአረብኛ ቋንቋ አስትርጓሚያችን አቶ ሲራጅና የኔ ጸሃፊ ጓድ አስካለ ቢነግዴ ነበሩ።

ለሠላም ፍለጋ ወደ ካርቱም የመጓዙን ጉዳይ በህብረት ያቀዱት የሁለቱ አገራት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮችና አምባሳደሮች ከካርቱም መንግሥት ጋር ባደረጉት ግንኙነትና በደረሱበት ስምምነት መሰረት የኢትዮጵያ ልዑካን ካርቱምን እንዲጎበኝ

የተፈለገው በሱዳን ህዝብ የነፃነት በዓል ላይ ተገኝተን የደስታቸው ተካፋይ በማድረግ ሊያስተናግዱን ባቀረቡልን ጥያቄ መሰረት ነው።

ለበዓሉ በተደረገው መስናዶና የሱዳን ህዝብ ለኢትዮጵያ ህዝብ ካለው በጎ አመለካከትና ወዳጃዊ ስሜት በተጨማሪ የኢትዮጵያን ህዝብ ብሄራዊና ዲሞክራሲያዊ አብዮት ታላቅነትና ያስመዘገባቸውን ህዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ድሎች አድናቂ ከሆኑት የአፍሪካ ህዝቦች ዋናውና ግንባር ቀደሙ ስለሆነ የመንግሥቱ መስተንግዶና የህዝቡ ወንድማዊ አቀባበል እኛ ከጠበቅነው በላይ መሆኑ አስገርሞናል።

አስተናጋጃችን የአገሪቱ ፕሬዝዳንት ራሱ እንደኛው ያየውን ነገር ያልጠበቀው ይመስላል በተፈጠረው ሁኔታ ስለተገረመ የነፃነቱ በዓል ሥርዓት ተከናውኖ በዓሉ ከተደረገበት አደባባይ ወደ አረፍንበት ቤተ መንግሥት ስንመለስ በምንሄድበት ጐዳና ግራና ቀኝ ተሠልፎ እኛን ለማየት ይጠባበቅ የነበረው መጠኑ እጅግ ብዙ የነበረ ህዝብ የኔን ስም እየጠራ በመጮሁ ምክንያት ፕሬዝዳንት ኑሜሪ «እባክህ ፈቃድህ ቢሆን የመኪናችንን የላይ ኮፈን ከፍተን እንቁምና ለህዝቡ በመታየት ለጥሪው መልስ ስጠው» ብሎ ጠየቀኝ።

ፈቃደኝነቴን ገለጨለት እንደተባለው የመኪናው ኮፈን ተከፈቶ ሁለታችንም በተጠየኩት መሰረት መለዮዬን ከራሴ ላይ አንስቼ እጄን ማውለብለብ ስጀምር ህዝቡ እንዲቆም በተሰጠው ቦታ ቆሞ ከመመልከት ፋንታ በጣም ቀርቦ ለማየት ሲል የተሰጠውን ገደብና ፀጥታ አስከባሪዎችን በኃይል ጥሶ ሲጠጋን በተፈጠረው ትርምስ ፀጥታ አስከባሪ ኃይሎች ህዝቡን ለማቆምና ለመመለስ በወሰዱት አስፈላጊ ያልሆነ የኃይል እርምጃ በብዙ ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት በመድረሱ ብትሩን ሲሸሽ በምንጓዝበት አውራ ጐዳና ዳርቻ በሚፈሰው የአባይ ጅረት ውስጥ ብዙ ሰዎች በተለይም ሴቶችና ህፃናት ሲወድቁ በማየታችን የኔና የኢትዮጵያዊያን ጓዶቼ ደስታ በቅፅበት ተለውጦ ከፍ ያለ ሃዘን ተሰማን።

ከዚህ አሳዛኝ ትርዒት ወይንም ከሱዳን ህዝብ የነፃነት በዓል አንድ ቀን በኋላ ከማግሥቱ ጧት ጀምሮ ለተከታታይ ለሁለት ቀናት እኔና ፕሬዝዳንት ኑሜሪ በኢትዮጵያዊው የአረብኛ ቋንቋ አስተርጓሚ በአቶ ሲራጅ አስተርጓሚነት ስለ ሁለቱ አገሮቻችን በሰፊውና በዝርዝር ነው የተነጋገርነው።

ፕሬዝዳንት ኑሜሪ ጥሪያቸውን ተቀብለን በነፃነት በዓላቸው ላይ በመገኘታችን ዳግም ምሥጋና አቀርቦ ለውይይታችን መክፈቻ ንግግር ከአደረገበ ኋላ እኔ እንግዳ ከመሆኔ ሌላ አገሬ ኢትዮጵያ ስለሆነች ተጠቂዋ የውይይታችንን ጊዜ አብዛኛውን የወሰድኩት እኔ ነበርኩ ማለት ይቻላል።

በመጀመሪያው ግንኙነታችን ቀን ካደረግነው ሰፊና ረዥም ውይይት በኋላ እኔ ለፕሬዝዳንት ኑሜሪ ያቀረብኩት ጥያቄ በኩታ ገጠም ድንበርተኝነታችንና

ጉርብትናችን በአያሌ ታሪክና ተፈጥሮ አድሎን ከአንድ ጅረት የመጠጣትን፣ በዘር፣ በቋንቋና በባህል የመተሳሰርን የመሰሉ በጐና ገንቢ ሁኔታዎች ተጠቅመን ከመረዳዳትና ከመተሳሰብ ይልቅ እናንተ ጐጂውንና አፍራሹን መንገድ መርጣችሁ፣ ከአረቦች ጋር በመሆን የምትወጉን ለምንድን ነው? የሚል ነበር።

ፕሬዝዳንት ኑሜሪ አንድ ቀን የወሰደ ረዥም የመናገር ቅድሚያ ለኔ በመስጠት በታላቅ ትዕግሥት ማዳመጥ ብቻ ሳይሆን ያቀረብኳቸው ስሞታዎችና ክሶች በአዎንታ ተቀብሎ በበኩሉ ሊያስረዳኝ የሞከረው ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

«በኤርትራ የተቀሰቀሰው ችግር በእኛ ደቡባዊ ክልል ከተቀሰቀሰው ችግር ጋር በጋራው የሠላም ጥረታችን አብሮ ሊከስም ሲገባው እስከዛሬ በመቆየቱ በጣም አዝናለሁ።

ባለፈውና ከእናንተ ወገን በከሸፈው የሠላም ውል የእኛን የደቡብ ሱዳንን የእርስ በርስ ጦርነት ለማቆም በኔ በኩል ያላደረኩት ነገር የለም።

በሱዳን የእርስ በርስ ጦርነት ለመወገድ መፍትሄ የሆነው ከኔ በፊት እሥልጣን ላይ የነበሩ ሰዎች የፈፀሟቸውን ስህተቶች ተገንዝቤና አምኜ ለደቡብ ህዝብ ጥያቄ አርኪና ተገቢ መልስ ይሆን ዘንድ ይሄ ጎደለው የማይባል ፍፁም የተሟላ የራስ ገዝ አስተዳደር ከመስጠትና ከደቡብ የራስገዝ አስተዳደር ጋር የሚጣጣም አዲስ ህገ መንግሥት አዘጋጅተን በዚያ ከመመራታችን ሌላ የደቡብ አማጺያንን ንቅናቄ የአመራር አካላትና መላውን ሠራዊት፣ በንቅናቄ ውስጥ ከነበራቸው ፕሮቶኮል፣ የማዕረግ ደረጃና የሥልጣን ፋካ ጋር በሚጣጣም ሁኔታ ሁሉንም ከላይ እስከ ታች በማዕከላዊው መንግሥታችን ልዩ ልዩ ተቋሞችና በመከላከያ ሠራዊታችን ውስጥ በማካተት የንቅናቄውን መሪ ጀነራል ጆሴ ፍላጉን የማዕከላዊው መንግሥታችን ምክትል ፕሬዝዳንት በማድረግ ተቃዋሚዎቻችንን አስደስተን ነው ሠላማችንን መልሰን ያገኘነው።

በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ከኤርትራ አማፂያን የሚዋጉበት ምክንያት በተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ የተቋቋመውን ፌደራላዊ አስተዳደር የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ስለአፈረሰብን ነው ማለታቸው እየታወቀ በኔ በኩል አፄ ኃይለ ሥላሴ ፌደሬሽኑን መልሱላቸው ለማለት ሳልደፍር የሚዋጉበት ምክንያት ተጠንቶና ታውቆ አስተዳደራዊ መፍትሄ ይፈለግ በማለት በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በአቶ ከተማ ይፍሩ አማካኝነት ለንጉሡ ሃሳብ አቅርቤ በንጉሡ በራሳቸው የተሰጠኝ መልስ የኤርትራ ጉዳይ ከእናንተ ችግር ጋር የማይመሳሰል በጣም የተለየ ነገር ነው። በኤርትራ ያመፁት ሽፍቶች ከአንድ አናሳ ማህበረሰብ የወጡና የኤርትራን ህዝብ ፈፅሞ የማይወክሉ ወስላቶች፣ የባዕድ ምንደኞች ናቸው።

በሠላሙ ውላችን መሰረት እኛ ከሱዳን መንግሥት የምንጠብቀው ከሱዳን ውስጥም ሆነ ከሱዳን ውጭ ምንም ዓይነት የገንዘብ፣ የመሣሪያና የቁሳቁስ ድጋፍ እንዳያገኙና በሱዳን ምድር እንዳይንቀሳቀሱ ማድረግን ብቻ ነው" አሉኝ።

በኛ በኩል ከኢትዮጵያ መንግሥት የተጠየቅነውን ሁሉ አድርገናል። ጦርነቱ የቀጠለው አማፂያኑ በሱዳን መንግሥት ስለተረዱ አይደለም።

አማፂያኑ የሱዳን ምድር ሳያስፈልጋቸው ከተለያዩ አገራት የሚያገኙትን ማናቸውንም የመሣሪያ፣ የሥንቅና የቁሳቁስድ ጋፍ የሚያስገቡባቸው በዚያው በኢትዮጵያ ብዙ በሮች አላቸው» አለኝ።

ይህንን ሲለኝ በመናደዴ ፕሬዝዳንት በጣም ነው የማዝነው እናንተ ስለ እኛ የምታውቁትን ያህል እኛም ስለ እናንተ ብዙ እናውቃለን፣ እናያለን እንሰማለንም የምታደርጉት ሁሉ ከእኛ የተሰወረ አይደለም። የካርቱም ከተማ የኢትዮጵያ ሠላም፣ አንድነትና አብዮት ፀሮች መናኸሪያ መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው።

በአሁኑ ጊዜ በተለይም ከኢትዮጵያ ህዝብ አብዮት ፍንዳታ በኋላ እናንተና ሌሎቹ ግብረ አበሮቻችሁ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ከዚህ የተሻለ ጊዜ የለም ብላችሁ ለጀብሐና ለሻዕቢያ የምትሰጡትን ሁለገብ እርዳታ እጅግ ከፍ ከማድረጋችሁ በላይ የኦሮሞ ህዝብ ነፃ አውጭ ነን፣ የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጭ ነን የሚሉትን አገር ገንጣዮችና እንዲሁም እራሳቸውን የኢትዮጵያ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ህብረት በማለት የሚጠሩ የወደቀው ሥርዓት ቅራሚ የሆኑ ተስፋ ለዘውድ ፊውዳሎችን በአገራችሁ አደራጅታችሁ በማዘመት እያስወጋችሁን በኤርትራ ክፍለ ሃገራችን አገር ገንጣዮች የሚያካሂዱት ፀረ-ሠላም፣ ፀረ አንድነትና ፀረ-አብዮት ሽብርና ጦርነት እስከዛሬ ሊቆይ የቻለው በአፄ ኃይለሥላሴ ስህተትና ድክመት ነው ብለህ ለኔ መንገር እኔንም አገሬንም መስደብ ነው።

እኛ ኢትዮጵያዊያን በስህተት፣ በጭፍን ጥላቻና በእብሪት ለምታካሂዱት ጥፋት መፍትሄው ወይንም መልሱ ሌላ ጥፋት ነው ብለን ስለማናምን የእናንተን የጥፋት ተግባር ሳንከተል በትዕግሥት ለአንዴና ለመጨረሻ የጋራ ሠላም ፍለጋ መጥተናል።

ካርቱም የመጣነው የእናንተንም የእኛንም የጋራ ሠላም ፍለጋነው። ከእንግዲህ ወዲያ መጪው ጊዜ እኛ ኢትዮጵያዊያን ስንደማ እናንተ መሳቃችሁ የሚያበቃበት ጊዜ ይሆናል።

ያሉት አማራጮች ሁለት ናቸው እናንተ የምታካሂዱብንን ጥቃት አቁማችሁ ሁለቱ አገሮቻችን ዋስትና ያለው ዘላቂ ሠላም አግኝተው መኖር ወይም ሁለቱም አገሮቻችን ማቆሚያና ማለቂያ በሌለው የጦርነት እሳት መቃጠል። የጥፋቱ

የፖለቲካ ኪስ ያለው በእናንተ እጅ ስለሆነ ምርጫውንም ለእናንተ እንተወዋለን በማለት ንግግሬን አበቃሁ።

ፕሬዝዳንት ኑሜሪ ፊቱን አኩስትሮ ለጥቂት ደቂቃዎች አትኩሮ በዝምታ ከተመለከተኝ በኋላ ፈገግ ብሎ «እንዲህ የሚያስቆጣህ ነገር የተናገርኩ አልመሰለኝም።

ላስረዳህ የሞከርኩት በአገራችሁ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የአመራር ጊዜ የተሰሩት ስህተቶች ይህንን ያህል እድሜ አግኝተውና መፍትሄ አልባ ሆነው በመቆየታቸው ለእናንተም በመሸጋገራቸው ምክንያት ነው ለማለት ነው።

አሁን በኢትዮጵያ የተደረገው አብዮታዊ ለውጥ ከፈጠረው ሁኔታ ባሻገር ከአንተ ንግግር እንደተረዳሁት አብዮታዊው መንግሥት ባለው ፅኑ የሠላም ፍላጎት በሁለቱ ጎረቤታማና እህትማማች አገሮቻችን መሃከል የነበረው መልካም ጉርብትና የማይታደስበትና ችግሮቻችንን በውይይትና በህብረት የማንፈታበት ምክንያት አይኖርም።

ለዛሬ ውይይታችንን እዚህ ላይ እናቁምና ነገ በተለመደው ሰዓት ተገናኝተን መወቃቀስ ሳይሆን ለጋራ ችግሮቻችን አንተ እንዳልከው የጋራ ሠላም ሊያስገኙ በሚችሉ መፍትሄዎች ላይ እንወያያለን» አለኝና ተለያየን።

በነጋታው ስንገናኝ ከአቀባበሉ ጀምሮ ጠቅላላ የፕሬዝዳንቱ ሁኔታ ከሰሞኑ በጣም የተለየ ነበር። የሁለተኛው ቀን ውይይታችን መግቢያ ያደረገው የንግግራችን ይዘት በሙሉ በመጀመሪያው የውይይታችን ቀን እኔ ያቀረብኩትን ክስና ወቀሳ በሙሉ በአወንታ በመቀበል «ትናንት የተናገርከው ነገር እውነት በመሆኑ ብትቆጣም የሚገባህ ነው» በማለት በመናዘዝ ዓይነት ውይይቱን ጀመረ።

ትናንት በስም የገለፅካቸው የእናንተ ተቃዋሚዎች ማለትም የኦሮሞ ህዝብ ነፃ አውጭ ነን የሚሉት፣ የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጭ ነን የሚሉትና ተስፋ ለዘውድ ያልካቸው የቀድሞ የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ባለሥልጣኖች በኔ አስተያየት ከሚያራምዱት ዓላማና ከተግባራቸው ጀምሮ በሰው ኃይላቸው መጠን፣ በትጥቃቸው ዓይነትና መጠን፣ በሰዎቹ ጠቅላላ ባህሪና በእድሜያቸው ወዘተ የሚመኙትን ለማድረግ ችሎታና ብቃት የሌላቸው ፍፁም ደካሞች ስለሆኑ እናንተን ብዙ የሚያሳስቡ ካለመሆናቸው ሌላ ከእንግዲህ ወዲያ በሱዳን ምድር መንቀሳቀስ ቀርቶ በፖለቲካ ጥገኝነት ሠላማዊ ኑሮ እንዲኖሩም አይፈቀድላቸውም። ይባረራሉ።

እናንተንም እኛንም በእጅጉ የሚያሳስቡና ለሁለቱም አገሮቻችን አቢይ ችግር ፈጣሪዎች፣ ራሳቸውን «ጀ.ብ.ሐ እና ሻዕቢያ» እያሉ የሚጠሩት ገንጣይ አማፂያን ናቸው።

እነኝህን ድርጅቶች አሳሳቢ.ና በብርቱ አስቸጋሪዎች የሚያደርጓቸው ምክንያቶች በኔ አስተያየት ከዚህ የሚከተሉት ጉዳዮች ናቸው፡፡

1ኛ ሁለቱም ገንጣይ ድርጅቶች የቆሙለት ዓላማና የሚያራምዱት አገርን የመገንጠል ተግባር ተመሳሳይ ቢሆንም በመሀከላቸው አንድነትና ህብረት የሌላቸው ብቻ ሳይሆኑ አንዱ የሌላው ጠላትና ፍፁም ተፃራሪዎች ናቸው፡፡

2ኛ ሁለቱም ገንጣይ ድርጅቶች የመላው አረብ መንግሥታት ትብብርና ሁለተናዊ ድጋፍ ስላላቸው በሰው ኃይል፣ በጦር መሣሪያና ትጥቅ፣ እንዲሁም በገንዘብና በልዩ ልዩ ቁሳቁስ የደረጁና ረጂም የውጊያ ልምድ ያካበቱ ናቸው፡፡

3ኛ በዚህም ምክንያትና ትምክህት የኢትዮጵያን የጦር ኃይል አሸንፈን ፍላጎታችንን እናሟላለን በማለት የተበቱ በመሆናቸው ከመገንጠል በመለስ ከመንግሥት ጋር የጋራ የሠላም መፍትሄ ፈፅሞ የማይፈልጉ ናቸው፡፡

4ኛ ከአረብ መንግሥታት የሚያገኙት ሁለገብ ድጋፍ ከኢትዮጵያ ህዝብ አብዮት በኋላ በሰሜን አሜሪካና በመላው ምዕራባዊ መንግሥታት ድጋፍ ይበልጥ ተጠናክሯል፡፡

ከሁሉም በላይ የሚያስገርመው ነገር የሁለቱም ገንጣይ ድርጅቶች አባሎች በሙሉ በወልና በግል ከአመራራቸው እስከ ምንዝሩ ሠራዊት እያንዳንዳቸው በሱዳን ህዝብ ውስጥ ሠርገው በመግባት በዘር፣ በቋንቋና በሃይማኖት፣ በጋብቻና በተለያዩ አያሌ ጥቅማ ጥቅሞች በመተሳሰራቸው ሁኔታው ከኔ ቁጥጥር ውጭ ሆኗል፡፡

እነዚህን ሁለት ተፃፃሪ ገንጣይ ድርጅቶች ለአንድ የሠላም ዓላማና ለአንድ የፖለቲካ መፍትሄ አስተባብሮ ከመንግሥት ጋር በጠረጴዛ ዙሪያ እንዲነጋገሩ በማድረግ ለችግሩ ሠላማዊና ፖለቲካዊ መፍትሄ ለማግኘት ሁለታችን በህብረትና በአንድነት የሚቻለንን ሁሉ ማድረግ አለብን ብዬ አስባለሁ፡፡

ፖለቲካዊና ሠላማዊ የሆነው የጋራ ጥረታችን ባይሳካ አመፃቸውን ለመግታትና ብሎም ለማቆም ወይንም ለሠላማዊ መፍትሄ ለማንበርከክ የሁለቱን አገሮቻችንን የጋራ የጦር ኃይል ለመጠቀም መቻል አለብን፡፡

ይህንን በማደርግበት ጊዜ እኔን ከውጭም ከአገር ውስጥም ከፍ ያለ ተቃውሞ ስለሚገጥመኝና ብቻዬን ስለምቆም ለምወስደው የኃይል እርምጃ የአንተን ሙሉና ሁለንተናዊ ድጋፍ ስለምፈልግ እስከ መጨረሻው ከጎኔ ለመቆምህ ቃል ግባልኝ አለኝ፡፡

ከሱዳን መሪ በተለይም ከኑሜሪ እንዲህ ያለ ቃል በመስማቱ በእጅጉ ከመገረሜ ባሻገር እውነትነቱን ለማመን ብቸገርም ለቀረበልኝ የኤርትራ ችግር መፍትሄ ፍፁም መስማማቴን ከመግለፅ ሌላ ለተግባራዊነቱም የኢትዮጵያን ህዝብና አብዮታዊ

የመከላከያ ሠራዊቱን ይገፍ እስከ መጨረሻው ከጎኑ የምሰለፍ መሆኔን ቃል ገባሁለት።

«በነገው ቀን በካርቱም ከተማ ውስጥ አንዳንድ ታሪካዊ ሥፍራዎችን ከአስጎበኘሁህ በኋላ ምሽቱ ላይ በሱዳን ህዝብ ምክር ቤት የሱዳንን ህዝብ መማክርትና የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላትን ስለምሰበስብልህ የኤርትራን ችግር በተመለከተ ለኔ የነገርከኝን በሙሉ አንድም ነገር ሳታስቀር ንግግር እንድታደርግላቸው ኃብገፍሀለሁ» አለኝ።

የሱዳን መንግሥት ለሰላሳ ዓመታት ያህል ከአረብ መንግሥታት ጋር ተባብሮ የኤርትራን ገንጣዮች በመርዳት በአገሬ ላይ ያደረሰውንና በማድረስም ላይ ያለውን አንድም ነገር ሳታስቀር ግልጥልጥ አድርገህ እንድትናገር ኃብገፍሃለሁ ማለቱ በእርግጥም ችግር ቢኖረው ነው ብዬ በማሰብ ሁለቱ አገሮቻችን በጋራ በኤርትራ ገንጣዮች ላይ ወታደራዊ እርምጃ እንዲወስዱ ሃሳብ ያቀረበልኝ እውነቱን ሊሆን ይችላል በማለት ላምነው ተገደድኩ።

እንደተጠየኩትም ጎረቤታማ የሆኑት የሱዳንና የኢትዮጵያ ህዝቦች የሚጠቅማቸው በጦርነት መፋጀት ነው ወይስ በመልካም ጉርብትና፣ በሠላምና በመረዳዳት አብሮ መኖር ነው? ከሚል ጥያቄ ተነስቼ እስከዚያች በምክር ቤታቸው አዳራሽ ቆሜ እስከተናገርኩበት ጊዜ ድረስ የሱዳን መንግሥት ከግብረ አበሮቹ ከአረብ መንግሥታት ጋር ለኤርትራ ገንጣዮች ወግኖ ያደረሰብንን ጥቃት ግልጥልጥ አድርጌ ካስረዳሁ በኋላ ንግግሬን እንዳቆምኩ አድማጮቼ ከመቀመጫቸው ተነስተው በመቆም በደማቅ ጭብጨባ ስሜታቸውን ስለገለጡልኝ ንግግሬ በሱዳን ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ መስሎኛል።

ከዚህ በኋላ በነጋታው ጧት ከፕሬዝዳንት ኑሜሪ ጋር ለአጭር ጊዜ ተገናኝተን በሰሞኑ ውይይታችን የደረስንበትን ውሳኔ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለንን እቅድና የሥራ ቅደም ተከተል መዘርዘር ወይም ሠንጠረዥ የሚያዘጋጁልን ከሁለቱ አገራት የተወጣጡ የውጭ ጉዳይ፣ የሃገር መከላከያና የአገር ደህንነት ሚኒስትሮችን ያካተተ የጋራ ኮሚቴ አዲስ አበባ ላይ ለማቋቋም ከተስማማን በኋላ በኔ በኩል ፕሬዝዳንት ጃፋር ኤልኑሜሪ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የሱዳን መንግሥት ባለሥልጣኖች ይዞ ኢትዮጵያን እንዲጎበኝ ግብዣ በማድረግ ከሥራ ጓዶቼ ጋር ወደ ኢትዮጵያ ተመለስን።

ምዕራፍ ሃምሳ ዘጠኝ

በሁለቱ አገሮቻችን መሃከል በአዲስ አበባ ከተማ የተደረገ የሠላም ውል።

በዚያው ዓመት በጥቅምት ወር ፕሬዝዳንት ኑሜሪ ያደረኩላትን ግብዣ ተቀብሎ ባለቤቱንና ምክትል ፕሬዝዳንቱን ጨምሮ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ከፍተኛ የሱዳን መንግሥት ባለሥልጣኖች እየመራ አዲስ አበባ ሲገባ እነሱ እንደ አደረጉልን ሁሉ በደማቅ አቀባበል ተቀብለን በብሄራዊ ቤተ መንግሥታችን አሳረፍናቸው።

በኢትዮጵያ ህዝብና በመከላከያ ሠራዊታችን ላይ ያደረሱትንና እያደረሱም ያሉትን ያላቋረጠ ጥቃትና ታላቅ ጉዳት ይገነዘቡ ዘንድ በሺህ የሚቆጠሩና አባቶቻቸውን በሰሜኑ የጦር ሜዳ ያጡ ህፃናትን በትምህርት እየኮተኮተ በእንክብካቤ የሚያሳድገውን የህፃናት አምባና በዚሁ በሰሜኑ የጦር ሜዳ ለአገራቸው አንድነትና ለህዝባቸው ደህንነት ከአገር ገንጣዮች ጋር ማለትም ከጀብሐና ከሻዕቢያ ጋር ሲፋለሙ ከፍ ያለ የአካል ጉዳት ስለደረሰባቸው አስፈላጊው ህክምና ከተደረገላቸው በኋላ ከሆስፒታል ወጥተው ላልተወሰነ ጊዜ በእንክብካቤ በማገገም እንደ አስፈላጊነቱ ሰው ሰራሽ አካል እየተሰራላቸው በተለያዩ የእደ ጥበብ ሞያዎች የሚሰለጥኑበትን የጀግኖች አምባ አስጎበኘናቸው።

ከህፃናትና ከጀግኖች አምባ ጉብኝት ማግሥት በብሄራዊ ቤተ መንግሥታችን የሁለቱን አገራት የውጭ ጉዳይ፣ የሃገር መከላከያና የአገር ደህንነት ሚኒስትሮችን ያካተተ ስብሰባ በማድረግ ካርቱም ከተማ ላይ የተስማማንባቸውን ስምምነቶች ወደ ተግባር መተርጎም በሚያስችሉን ጉዳዮች ላይ አንድ ቀን የወሰደ ሰፊ ውይይት በማድረግ ጠቃሚ ውሳኔዎችን በጋራ ወሰንን።

ከዚህ በኋላ በነጋታው የሚኒስትሮቹ ኮሚቴ ብቻውን ተሰብስቦ ለቀጣዩ ሥራ ዕቅድ በመንደፍ ለአፈፃፀሙም ቅደም ተከተል ያወጣበትን መዘርዝር በማቅረብ ለሁለታችን ፕሬዝዳንቶች ገለፃ በአደረገበት ጊዜ አንዳንድ እርምቶችን በማድረግ ተጨማሪ መሆን የነበረባቸውን ጉዳዮች በማከል ዝግጅቱን አፀደቅን።

በዚሁ ቀን ፕሬዝዳንት ኑሜሪን ከነባለቤቱ ከባለቤቴ ጋር በማስተዋወቅ በመኖሪያ ቤቴ የምሣ ግብዣ በብሄራዊ ቤተ መንግሥታችን የራት ግብዣ በሌላው ቀን ምሽት በብሄራዊ የትያትር አዳራሻችን አስደሳች የባህል ጨዋታ ምሽት አድርገንላቸው በነጋታው ሸኘናቸው።

ለኤርትራ ችግር ቢቻል በፖለቲካ መፍትሄ ባይቻል በወታደራዊ ኃይል መፍትሄ ለማግኘት ጥረት ይደረግ ዘንድ በአማራጭነት በፕሬዝዳንት ኑሜሪ የቀረበውን ሃሳብ ተቀብለን ለተግባራዊነቱ እቅድና የተግባር አፈፃፀሙን ቅደም ተከተል ተራ ባወጣንበት ጊዜ ሱዳኖች በቅድሚያ ሁለቱን የኤርትራ ገንጣይ ድርጅቶች ማለትም ጀብሐንና

ሻቢያን በየግልና በየተራ በመቅረብና በማነጋገር በቅድሚያ በመሀከላቸው ያለውን ልዩነትና ቅራኔ የሚወገድበትንና እርቅ የሚፈጠርበትን መፍትሄ ማግኘትና ብሎም በህብረት ለሠላም ድርድር ከኢትዮጵያመንግሥት ልዑካን ጋር ማገናኘቱ የሱዳን መንግሥት ቀዳሚ የሥራ ድርሻ መሆኑን በመገንዘብ ተማምነን ሲሆን ለፖለቲካ መፍትሄ የሚደረገው ጥረት ባይሳካ በሁለቱ አገራት የጦር ኃይሎች ህብረት የኃይል እርምጃ ለመውሰድ ተስማማን::

ለአገራችን ሠላም ግኝት፣ ለሕዝባችን አንድነትና ማህበራዊ ደህንነት ስንል ያደረግነው የዲፕሎማሲ ጥረት::

የኢትዮጵያ ልዑካን በሌሉበትና ባልተካፈለበት በሱዳን መንግሥትና በገንጣዮቹ መሃከል የሠላም ድርድሩ ስለመጀመሩ ተጀምሮም ከሆነ ስለሂደቱና ብሎም ውጤቱ አንዳችም ነገር ሳይገለፅልንና የሚኒስትሮቹ ኮሚቴ ሳይገናኝ ወይንም ሳይሰበሰብ አያሌ ወራቶች ተቆጠሩ::

በጉዳዩ በጣም በመቸገራችንና ስለ ሱዳኖች ሐቀኝነት ጥርጣሬ ስለገባን በሱዳን መንግሥት ላይ ከፍ ያለ ግፊት በማድረጋችን ለሦስተኛ ጊዜ ካርቱም ላይ የሚኒስትሮች ኮሚቴ ተገናኝቶ በተደረገው ውይይት መረዳት ወይንም መገንዘብ የቻልነው ሱዳኖቹ ማለቂያ ወይም እልባት በማያስገኝ ሁኔታ ሃቀኛ የሠላም ጥረት

ማድረግና የተገኘውንም ውጤት ወይንም ያሉበትን ሁኔታ ለኛ ለመግለፅ ያለመፈለጋቸውን ብቻ ሳይሆን ጊዜ በማባከን የሚቀልዱብን መሆናቸውን ነበር።

ይህም በመሆኑ በኛ በኩል የራሳችንን እርምጃ ለመውሰድ ወስነን በደቡብ ሱዳንና በውጪ በተለያዩ አገሮች ውስጥ ካሉ የሱዳን መንግሥት ተቃዋሚዎች ትር ግንኙነት በመፍጠር የደቡብ ሱዳንን ህዝብ ከአረቦች የባርነት አገዛዝ ነፃ የሚያወጣ የፖለቲካ ድርጅት በማቋቋምና የሱዳን መንግሥት ዋና ተቃዋሚ የሆነውን የሱዳን ኮሚኒስት ፓርቲ በሚያስፈልገው ሁሉ ለመረዳት በዝግጅት ላይ በነበርንበት ጊዜ የሱዳን መንግሥት ራሱ እኛ ያላሰብናቸውና ከሱ ያልጠበቅናቸውን ከዚህ የሚከተሉትን ከፍተኛና ታሪካዊ እርዳታዎችን አደረገልን።

የአረቦችን ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ-ሠላም ድርጊት በመቃወም ከኢትዮጵያ ህዝብ ወገኖ በኤርትራ ገንጣዮች ላይ በምወስደው ወታደራዊ እርምጃ መላው የአረብ መንግሥታት ብቻ ሳይሆኑ የሱዳን ህዝብም በከፍተኛ ደረጃ እንደሚቃወመኝ የታወቀ ስለሆነ እስከ መጨረሻው ከኔ ጎን ለመቆም ቃል ግባልኝ ብሎ የጠየቀኝ ሰው፤

1ኛ ከመላው የአረብ መንግሥታት ጋር በአጠቃላይ ከሳዑዲ አረቢያ መንግሥትና በሱም ከሚመሩት የነዳጅ ዘይት አምራች ፊውዳል መንግሥታት ጋር መክሮ በሰሜንና በደቡብ ሱዳኖች መሀከል አዲስ አበባ ላይ የተደረገውን የሠላም ውልና ለሠላሙ ተግባራዊነት ሲባል ተዘጋጅቶ ይሰራበት የነበረውን ህገ መንግሥት በመጣስ የደቡብ ሱዳንን ህዝብ የራስ ገዝ አስተዳደር መብትና ሥልጣን አፍርሶ ክርስቲያን በሆነው ህዝብ ላይ የሻሪአ ህግ አወጀ።

2ኛ ህገ መንግሥቱ መጣሱንና በክርስቲያኑ ህዝብ ላይ የሻሪአ ህግ መታወጁን በመቃወም አገር አቀፍ ሠላማዊ ሠልፍ በአደረገው በመላው የደቡብ ሱዳን ህዝብ ላይ የጦርነት አዋጅ አወጀ።

3ኛ በጦርነቱ አዋጅ መሰረትም፣ በጦር አውሮፕላኖች ቦምብ በግፍ የተደበደበውና በሱዳን የምድር ጦር ሠራዊት የተመታው ህዝብ ህይወቱን ለማዳን ወደ ጎረቤት አገራት ማለትም ወደ ኢትዮጵያ፣ ወደ ኬኒያና ወደ ዩጋንዳ አገሩን ጥሎ ሸሸ።

4ኛ ከደቡብ ሱዳን የአስተዳደር ክልሎች አንዱና ትልቁን አያሌ ከብት አርቢ ህዝብ የሚኖርበትን ከአባይ ጅረት በተጨማሪ ሌሎች ሁለት ታላላቅ ወንዞች የሚያጠጡትን እጅግ ለምና እጅግ ሰፊ የውሃ ተፋሰስ ያለውንና ጆንጎሌ በመባል የሚ ጠራውን ክልል ከዚህ በላይ ለጠቀስኳቸው የነዳጅ ዘይት አምራች የሆኑ የአረብ መንግሥታት በዘመናዊ የመስኖ እርሻ፣ የተለያዩ የምግብ እህሎችን፣ ጥራ ጥሬዎችን፣ የቅባት እህሎችንና ፍራፍሬዎችን በማምረት፣ የወተትና የሥጋ ከብቶችን በማርባት ህዝባቸውን ይመግቡ ዘንድ ከፍ ያለ መጠን ባለው ገንዘብ ለረጅም ጊዜ አከራያቸው ወይንም አኮናተራቸው።

በዚህ ሁኔታ አብዛኛውን የደቡብ ህዝብ ከርስቱና ከመኖሪያ ክልሉ ወይንም ከትውልድ አገሩ በማባረር በባዕድ አገራትም እንደ አንድ ነፃ ህዝብ የኢኮኖሚም ሆነ የሰው ኃይል የሌለው ህልውና አልባ በማድረግ በድህነት አቀርቅዞ ፍፁም በማዳከም እንደፈለገ በወታደራዊ የብረት ቡጢ ለመግዛት የፕሬዝዳንት ኑሜሪን መንግሥት ያነሳሳው ዋና ምክንያት በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ በደቡብ ሱዳን ውስጥ ብቻ ከፍ ያለ መጠን ያለው የነዳጅ ዘይት በመገኘቱ ከሰሜኑ ህዝብ ጋር የማይታረቅ ቅራኔያ ለው የደቡብ ህዝብ በነዳጅ ዘይት ከብሮ ኢኮኖሚውንና የመከላከያ ኃይሉን ከሰሜኑ ህዝብ በላቀ ሁኔታ ገንብቶ በመጠናከርና እይበገሬ በመሆን ዳግም ነፃነት እንዳይጠይቅና ለነፃነቱ የመታገል አቅም እንዳይኖረው ለማድረግ ሲሆን ፕሬዝዳንት ጃፋር ኤልኑሜሪ የሸሪአ ህግ በደቡብ ህዝብ ላይ ያወጀውና ለምና ውሃ ገብ የሆነውን ክልል የሸጠው ከሁለተኛው ክህደቱ በኋላ የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት እንደማይተኛለት ስለሚያውቅ በደቡብ ህዝብና በኢትዮጵያ ላይ አረቦችን ከጎኑ ለማሰለፍ ነው።

ፕሬዝዳንት ኑሜሪ በፈፀመው ክህደት፣ ዐረ ሠላምና ዐረዲሞክራሲ ህገ ወጥ ተግባር ሌላ በሠላማዊው የደቡብ ህዝብ ላይ ጦርነት አወጆ መጨፍጨፉ በእጅጉ የተቆጡ የደቡብ ህዝብ ታጋዮችና መሪዎች አብዮታዊውን የኢትዮጵያ መንግሥት እርዳታ እንዲጠይቁ ከመሃከላቸው ሰባት ግለሰቦችን መርጠው ወደ አዲስ አበባ ላኩ።

ልዑካኖቹ በሙሉ «አኛኛ» ወይንም መርዘኛ እባብ በመባል የሚታወቀውና ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ያፈረሱት የደቡብ ሱዳን ህዝብ ነፃ አውጪ ንቅናቄ ውስጥ በተለያዩ የአመራር ደረጃ ላይ የነበሩና በአዲስ አበባው የሠላም ስምምነት መሰረት በፕሬዝዳንት ኑሜሪ ለሚመራው የሱዳን ማዕከላዊ መንግሥት ንቅናቄው እጁን ከሰጠ በኋላ በማዕከላዊው መንግሥት ውስጥ ሚኒስትሮች የነበሩና በጡረታ የተገለሉ ሦስት አዛውንቶች፣ በደቡብ የራስ ገዝ አስተዳደር ውስጥ የሁለት ክፍለ ሃገራት አስተዳዳሪ የነበሩ ሁለት ሰዎችና ከእነኝህ ከአምስቱ ሰዎች በእድሜያቸው ልጅ እግር የሆኑ ምሁራን አንደኛው በሱዳን ማዕከላዊ መንግሥት ውስጥ በውጭ ጉዳይ ሚንስቴር ምክትል ሚኒስትር የነበረና ሌላው በሱዳን መንግሥት የምድር ጦር ሠራዊት ውስጥ የሠራዊቱ የትምህርትና የዘመቻ ጉዳይ ዳይሬክተር፣ በኢኮኖሚ የዶክትሬት ድግሪ ያለው፣ በፖለቲካ የበሰለ ግራ ዘመም፣ በወታደራዊ ችሎታው የታወቀና በኋላ ማለትም በጊዜ ሂደት የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት ያቋቋመው ነፃ አውጪ ንቅናቄ መሪ የሆነው ኮሎኔል ጆን ጋራንግ በጠቅላላው ሰባት ሰዎች ነበሩ።

ከደቡብ ሱዳን ርዕሰ ከተማ ከጁባ ከአንድ ሳምንት በላይ በእግራቸው ተጉዘው ኢሉባቡር በምንለው ክፍለ ሃገራችን አውራጃ ጋምቤላ የገቡት ነፍሰ ጡር የነበረችውን ሩቤካ የምትባለዋን የዶክተር ጆን ጋራንግ ባለቤት ይዘው ነው።

የአውራጃው የፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን ጸሃፊ የነበረው ጓዳችን ጋምቤላ መድረሳቸውንና የመጡበትን ምክንያት ስለ አሳወቀን ሄሊኮፕተር ተልኮላቸው ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ተደረገ።

የተቀበላቸው ምክትል ፕሬዝዳንታችን ጓድ ፍስሃ ደስታ ሰዎቹ እጅግ መጎሳቆላቸውንና በአደረጉት ረጂም የእግር ጉዞ በጣም መድከማቸውን የገለጠልኝ ከመሆኑ ሌላ የመጡበት ወቅት በአገራችን ክረምት በሐምሌ ወር ውስጥ በመሆኑ አዲስ አበባ ስለሚቀዘቅዝ በናዝሬት ከተማ ውስጥ በሚገኝ የእንግዳ ማስተናገጃችን እንዲያርፉ አደረግን።

የሕክምና አገልግሎት እየተሰጣቸውና በምቾትም ረገድ አስፈላጊው እንክብካቤ እየተደረገላቸው ከድካማቸው ከአገገሙ በኋላ አስተናጋጅና የሥራ ባልደረባ ባደረግንላቸው በሃገር ደህንነት ሚኒስትራችን በጓድ ተስፋዬ ወልደ ሥላሴና በጦር ኃይሎች ምክትል ኤታ ማዦር ሹም በጓድ ጀነራል መስፍን ገብረ ቃል አቅራቢነት በጽህፈት ቤቴ ተቀበልኳቸው።

እነኝህ ከፍ ያለ በደልና ጥቃት የደረሰባቸው አሳዛኝ አፍሪካዊ ወንድሞቻችን ወደ እኛ የመጡበትን ምክንያት ስለምናውቅና ይህንን የመሰለውን አጋጣሚ ስንጠብቀው ስለነበረ የሚጠይቁንን እርዳታ ለመስጠት ዝግጁ ነበርን።

ከጽህፈት ቤቴ ጋር በተያያዘችው አነስተኛ የደርግ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መሰብሰቢያ ክፍል ውስጥ ተቀብዬ እንኳን ወደ አገራችን መጣችሁ በማለት ሁሉንም ጨብጬ እንዲቀመጡ በማድረግ እንደፍላጎታቸው ቀዝቃዛ መጠጦች፣ ሻይና ቡና ከተስተናገዱ በኋላ የመጡበትን ምክንያት በመጠየቅ ምን እንታዘዝ ወይንም ምን መርዳት እንችላለን የሚል ጥያቄ አቀረብኩላቸው።

ሰባቱም ከኔ ፊት ለፊት በስተግራ መደዳውን ከነጓድ ተስፋዬና መስፍን ትይዩ ተቀምጠው ስለነበረ መሃላቸው የተቀመጡትና በፕሮቶኮል ብቻ ሳይሆን በእድሜም አንጋፋ የሆኑት አዛውንት አገራችን ከደረሱበት ጊዜ ጀምሮ ስለተደረገላቸው አቀባበልና እንክብካቤ ምስጋና ከአቀረቡ በኋላ የሱዳንን ህዝብ ታሪክ በአጠቃላይ ጠቅለል አድርገው በአጭሩ የደቡብ ሱዳንን ህዝብ ውስብስብ ታሪክ ሰፋ አድርገው የደረሰባቸውን አሳዛኝ ገጠመኞች ካስረዱኝ በኋላ አገራቸውን ጥለው ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ያስገደዳቸውን ሁኔታና በደቡብ ሱዳን ህዝብ አመራር አካላት የተሰጣቸውን ተልዕኮ አስረዱኝ።

ሦስቱ አዛውንቶች እየተፈራረቁ ስለአገራቸው ከአስረዱኝ በኋላ ታዲያ ምን ይበጃል? ምን ለማድረግ አስባችኋል? እኛስ ምን መርዳት እንችላለን የሚል ጥያቄ አቀረብኩላቸው።

«በሰሜን ሱዳን አረባዊና እስላማዊ አገዛዝ ለአያሌ ዘመናት መረገጣችን፣ መዋረዳችን፣ መሰቃየታችንና ስንገደል መኖራችን አንሶ እነሆ ዛሬ የፕሬዝዳንት ጃፋር ኤል ኑሜሪ መንግሥት የጦር ኃይል የደቡብን ህዝብ በሙሉ ሲቪል ወታደር፣ ሴት፣ ወንድ፣ ህፃን፣ ሽማግሌ ሳይል በግፍና በገፍ ህዝባችንን ስለፈጀውና የቀረውንም አብዛኛውን ወደ ጎረቤት አገሮች ስለአባረረው በእኛና በኑሜሪ መንግሥት፣ በኛና አረብ ነኝ በሚለው በሰሜኑ ህዝብ መሀከል የተፈጠረው ቅራኔ ፈፅሞ የማይታረቅበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

ራሱን የመከላከል አቅም የሌለውን ህዝባችንን በጦር ኃይል ከመፍጀት ባሻገር የቀረውንም ህዝብ ከአገሩ እያስወጣ አገር አልባ አድርጎት ወደ ባዕድ አገር እየተሰደደ በመሆኑ ለአገሩ፣ ለመሬቱ፣ ለነፃነቱ ገድሎ ለመሞት የቆረጠ ህዝብ ነው።

ይህንን ህዝብ አደራጅተንና አስታጥቀን ልናታግለውና ልንመራው ወስነን ነው እርዳታ ለማግኘት ወደ ኢትዮጵያ የመጣነው።

የክቡርነትዎን መንግሥት የምንጠይቀው ሰባት ሺህ ሰው ወይንም ሰባት ሻለቃ ተዋጊ ጦር ለማሰልጠን፣ ለማደራጀትና ለማስታጠቅ እንዲረዳን ነው» አሉ።

ብዙ ላለማስቸገር ሲሉ በይሉኝታ ያቀረቡት ጥያቄ እንጂ የሱዳንን መንግሥት የጦር ኃይል ለመውጋት ሰባት ሻለቃ ጦር ፈፅሞ እንደማይበቃቸው እናውቃለን።

የምናደራጅላቸውን ተዋጊ ሠራዊት ቁጥር ሳንመጥን አገራችን ኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ ሠላም አልባ ሆና ከውስጥና ከውጭ ጠላቶቿ ጋር በመዋጋት ላይ የምትገኝ አገር ብትሆንም እናንተ በአረቦች ጥቃት፣ ውርደትና ስደት ደርሶባችሁ ዝም ብለን ማየት አይቻለንም።

ባለን አቅምና ችሎታ ከጎናችሁ ተሰልፈን እንረዳችኋለን። በዚህ ታሪካዊ አጋጣሚ በጥብቅ ልናሳስባችሁ የምንፈልገው አንድ ነገር አለ።

በአገራችን አባባል የነብርን ጭራ አይዙም ከያዙም አይለቁም ይባላል። ኢትዮጵያዊያን ይህንን ለምን እንደምንል እንደሚገባችሁ አልጠራጠርም። የምትዋጉበትን ዓላማ ህጋዊነትና ትክክለኛነት አምነንበት ከጎናችሁ ለመሰለፍ ወስነናል። ሁላችንም ልንገነዘብ የሚገባን የምንዋጋው ከሱዳን መንግሥት የጦር ኃይሎች ጋር ብቻ ሳይሆን የሻሪአ ህግ ተከታይና ደጋፊ ከሆኑትና አገራችሁን በገንዘብ ከገዙት መላው የአረብ መንግሥታት ጋር ጭምር መሆኑን ነው።

ለአኩሪ ድል በሚያበቃን ሁኔታ በፍፁም ጀግንነትና ቆራጥነት ተዋግተን እነኝህን አረቦች የምናበረክክ ካልሆነ ውጊያውን ባንጀምረው ነው የሚሻለው አልኳቸው።

«ህዝባችን የተዋረደ፣ የተቀጠቀጠ፣ ክብርና ነፃነቱን ብቻ ሳይሆን አገሩን መሬቱንና ህልውናውን ያጣ ስለሆነ በእንዲህ ያለ ሁኔታ ከመኖር ጠላቶቹን እየገደለ ለመሞት የቆረጠ ህዝብ ነው። ላናሳፍራችሁ ቃል እንገባለን» በማለት ሁሉም በተራ ቃሉን እየተቀባበሉ ደገሙት።

በገባችሁልን ቃልመሰረት እንደተርብ እንደምትዋጉና እንደምናሸንፍ እንተማመንባችኋለን ከአሁን ጀምሮ ወደ ተግባር በማምራት ሥራ መከፋፈል ይኖርብናል።

በኛ በኩል የጦር መሣሪያዎችን፣ ትጥቅና አልባሳትን፣ የሠራዊቱን ማሰልጠኛ ሥፍራና አሰልጣኞችን ወዘተ ስናዘጋጅ እናንተ ነፃ አውጪውን ሠራዊት የምትመሩበትን፣ ህዝቡን የምትቀሰቅሱበትንና የምታንቀሳቅሱበትን በአጠቃላይ የትግሉን ዓላማና ተግባር በግልፅ የሚያስረዳ የፖለቲካ ፕሮግራም አዘጋጁ ብዬ አሰናበትኳቸው።

ለእንግዶቻችን የናዝሬትን ከተማ ለማረፊያነት የመረጥነው በደቡብ ሱዳን የአየር ንብረቱ በጣም ሞቃት በመሆኑና በኢትዮጵያ ደግሞ በተለይም አዲስ አበባ በጣም ቀዝቃዛ በሆነበት የክረምት ጊዜ በሐምሌ ወር ውስጥ ስለመጡና የአዲስ አበባን ቅዝቃዜ ስለማይችሉ በሸዋ ክፍለ ሃገር ሞቃታማ የሆነውን ሥፍራ በመምረጥ ነው።

እንግዶቻችን የፖለቲካ ፕሮግራማቸውንና የተለያዩ የትግል መመሪያ ደንቦችን ማዘጋጀትና ለሚያካሂዱትም ትግል በመሃከላቸው የሥራ ድርሻ ክፍፍል ማድረግ ሲጀምሩ የፖለቲካ አመለካከት ልዩነቶች ብቻ ሳይሆኑ የሥልጣን ሽሚያም ተፈጥሮ ሥራቸውን ከመሥራት ፋንታ በመጨቃጨቅ ጊዜ የሚያባክኑ መሆናቸው ታወቀ።

ዶክተር ጆን ጋራንግ የፖለቲካ ብስለት ያለው በህብረተሰብአዊ ሥርዓተ ማህበር የሚያምን ትጉህ ሠራተኛ ብቻ ሳይሆን የወታደራዊ አመራር ብቃት ያለው ሰው በመሆኑ ከተቀሩት የልዑካኑ አባላት ጋር ናዝሬት ከተማ ተቀምጦ ጊዜ ማባከኑን ስለጠላው ሽማግሌዎቹ የፖለቲካ ፕሮግራሙን እስኪያዘጋጁ እኔ ጋምቤላ በመሄድ እዚያ ካሉት ስደተኛ የጦር መኮንኖች ጋር ተዋጊውን ሠራዊት የመመልመሉንና የማደራጀቱን ሥራ እንድጀምር ፈቃዳችሁ ሆኖ እርዱኝ በማለት ጀነራል መስፍንን አስፈቅዶ ከኢትዮጵያዊያኑ አሰልጣኝ መኮንኖች ጋር በቅንጅት ተዋጊዎችን የማሰልጠኑ ተግባር ተጀመረ።

የፖለቲካ ፕሮግራም ለማዘጋጀት ናዝሬት በቀሩት ልዑካን መካከል የተፈጠረውን ልዩነት በመሸንገል በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ባለው በአዲሱ ብሄራዊና ዲሞክራሲያዊ አብዮት መርህ ላይ ተመስርተው የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን እንዲያዘጋጁ ያቀረብንላቸውን አስታራቂ ሃሳብ ተቀብለው ጥሩ ፕሮግራም አዘጋጁ።

የሥራ ክፍፍልንና ድርጅታዊ መዋቅርን በተመለከተ አንድ ከፍተኛ የነፃ አውጪው ድርጅት የጋራ አመራር ማዕከል በዋናው የአመራር ማዕከል ሥር የፖለቲካ ጉዳይ መምሪያ ዘርፍ፣ የወታደራዊ ጉዳይ መምሪያ ዘርፍ፣ የአስተዳደርና የሎጀስቲክ መምሪያ ዘርፍ ፈጥረው ልዑካኑን እየመሩ የመጡት አዛውንት የነፃ አውጪው ድርጅት መሪ፣ ዶክተር ጆን ጋራንግ የድርጅቱ ምክትል መሪና የተዋጊው ሠራዊ ትእዛዥ ሆኖ ውጊያው ተጀመረ።

የደቡብ ሱዳን ህዝብ ነፃ አውጭ ሠራዊት ተቋቁሞ በሱዳን መንግሥት ሠራዊት ላይ ወታደራዊ ድሎችን እየተቀዳጀ መሆኑን ከተለያዩ የዜና ማሰራጫዎች የሰሙ የደቡብ ሱዳን ተወላጅ የሆኑ የተለያዩ ሞያ ያላቸው አያሌ ምሁራን ከሱዳን ውስጥና ከሱዳን ውጭ እየመጡ ድርጅቱን በብዙ ረገድ አጠናከሩት።

የፕሬዝዳንት ኑሜሪ መንግሥት ኢትዮጵያ በደቡብ ሱዳን ያሉ የመንግሥቱን ተቃዋሚዎች አደራጅታ ለበቀል ታዘምትብናለች በሚል ሥጋት ብቻ ሳይሆን በሰላዮቹ አማካኝነት የደቡብ ሱዳን ነፃ አውጪ ድርጅት መቋቋሙን ያወቀ ይመስላል የሁለቱን አገሮች ድንበር በበርካታ ሠራዊት አጠረው።

ነፃ አውጪው የደፈጣ ውጊያ ተዋጊው ሠራዊት ጠረፍ ጠባቂ ሠራዊት ባልጠበቀውና ባልታሰቡ አቅጣጫዎች ድንበሩን እየጣሰ ወደ ሱዳን ግዛት ጠልቆ በመግባት የመንግሥቱን ሠራዊት ከኋላው ዞሮ በመቁረጥ ከበበው።

የፕሬዝዳንት ኑሜሪ መንግሥት ሠራዊቱን ከከበባው ለማውጣትና ሥንቅ ለማቅረብ ስለተሳነው ከፍ ያለ ችግር በመፈጠሩ ሠራዊቱ ሥንቁን ጨርሶ ከመራቡ ሌላ ጥይቱንም ተኩሶ ጨረሰ።

የደቡብ ሱዳን ተወላጅ የሆኑ የሠራዊቱ አባላት ከነፃ አውጭው ሠራዊት ጋር ሲቀላቀሉ የተቀሩት በመበታተን ወደ ሰሜን ኮበለሉ።

በተቀሩትም የመንግሥቱ ጠረፍ ጠባቂ ሠራዊት ላይ ተመሳሳይ ጥቃትና ውድቀት ይደርሳል ብሎ በመስጋት የሱዳን መንግሥት በጠረፍ ላይ ያሰማራውን ጦር በማንሳቱ ጠረፉ በሙሉ በነፃ አውጭው ሠራዊት ቁጥጥር ስር ሆነ።

የደቡብ ሱዳን ህዝብ ነፃ አውጭ ሠራዊት አዛዥ ዶክተር ኰሎኔል ጆን ጋራንግ በአጭር ጊዜ ውስጥ በተራቀቀ የደፈጣ ውጊያ ስልት ካስገኘው የጦር ሜዳ ድል ባሻገር ለንቅናቄው በሚያደርገው ሁለገብ አስተዋፅኦ የተደነቁ መኮንኖች ባቀረቡት ሃሳብና በሰጡትም ከፍተኛ ድምፅ ከሠራዊት መሪነቱ በተጨማሪ የነፃ አውጭው ድርጅት ዋና መሪ አድርገው መረጡት።

ነፃ አውጭው ሠራዊት በተከፈተለት መንገድ በየአቅጣጫው ወደ ሱዳን የተለያዩ ክልሎች እየተንቀሳቀሰ በመንግሥቱ ሠራዊት ላይ ድንገተኛና ያልተጠበቀ ጥቃት መሰንዘሩን አዘውተረ።

የሱዳን መንግሥት በርካታ ሠራዊት አሰማርቶ በአየር ኃይል የተረዳ መጠነ ሰፊ የመልሶ ማጥቃት ውጊያ በመሰንዘሩ በሁለቱም ሠራዊት ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ቢደርስም የመንግሥቱ ሠራዊት ነፃ አውጭውን ሠራዊት ወደ ኋላው ለመግፋትና የቦታ ይዞታውን ለማሻሻል ሳይችል በመቅረቱና የማጥቃቱ ተግባር ላልተወሰነ ጊዜ ተገቶ በመቆሙ በሁለቱም ሠራዊቶች መሀከል መፋጠጥ ሆነ።

በመጀመሪያዎቹ የውጊያ ምዕራፎች በተገኙት ውጤቶች ተደስተን በኛ በኩል የሠራዊቱን ተከታታይ ሥልጠናና የሎጀስቲክ አቅርቦቱን በየጊዜው ከማሻሻልና የሠራዊቱን ሞራልና የአጥቂነት ስሜት ከመገንባት ሌላ በየስድስት ወራት 10000 አሥር ሺህ ተዋጊ በማሰልጠን በአራት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ 80,000 ሰማኒያ ሺህ ሠራዊት አሰማራን።

የደቡብ ክልል በጠቅላላ ማለት ይቻላል በውሃ ሃብት የታደለ በደን የተሸፈነና ለነፃ አውጪው ሠራዊት ለምግብነት የሚያገለግሉ አያሌ የዱር አራዊት የሚርመሰመሱበት አገር ነው።

ከሰሜኑ ደረቅና አሸዋማ ምድር የሚመጣው የመንግሥቱ ሠራዊት ሊቋቋም አለመቻል ብቻ ሳይሆን ከፍ ያሉና ተደጋጋሚ ሽንፈቶች ስለደረሱበት ሠራዊቱ ፕሬዝዳንት ኑሜሪን በመፈንቅ ለመንግሥት ከሥልጣን አውርዶ ጀነራል ስዋር ደሐብ የሚባል መኰንን ተካ።

የአዲሱ ወታደራዊ መንግሥት አመራር አካላት አገርን የማስተዳደርና የፖለቲካ አመራር ልምድ የሌላቸው በመሆናቸው ህዝቡና የመከላከያ ሠራዊቱ ከእነሱ የጠበቁትን ሊያሟሉና የአገሪቱን የተለያዩ ባለብዙ ፈርጅ ችግሮች ሊያቃልሉ ቀርቶ የሚያውቁት ወታደራዊ አመራሩም አልተሳካላቸውም።

መንግሥትና ደጋፊዎቹ ተዳክመው በመገኘታቸው ወታደራዊውን መንግሥት የሚቃወሙ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተለይም የእስልምና ወንድምማማቾች ማህበር ስለተጠናከሩና ህዝቡም ስለ ደገፋቸው በደቡብ ህዝብ ነፃ አውጪ ሠራዊትና በመንግሥቱ ሠራዊት መካከል ፍልሚያው በተጧጧፈበት ጊዜ በህዝብ ምርጫ የጀነራል ስዋር ደሐብን ወታደራዊ መንግሥት በሲቪል መንግሥት ተተካ።

የሲቪሉ መንግሥት በእስልምና አክራሪ ኃይሎች የሚመራ ስለነበረ ከጦርነቱ ሌላ በእስልምና አክራሪዎችና በተቀሩት የህብረተሰብ ክፍሎች መሀከል ከፍ ያለ ትግልና የማይታረቅ ቅራኔ ተፈጠረ።

በሚያስደንቅ ጀግንነትና በጥሩ የደፈጣ ውጊያ ሥልት የሚዋጋው የደቡብ ሱዳን ህዝብ ነፃ አውጭ ሠራዊት በድል አድራጊነት እየተንቃነቀ የደቡብ ሱዳን ህዝብ ይዞታ ነው የሚባለውን አብዛኛውን ምድር ተቆጣጥሮ ወደ ክልሉ ርዕሰ ከተማ ወደ ጁባ ሲቃረብ በሰሜን ሱዳን ሽብር ተፈጠረ።

የእስልምና እምነት አክራሪ በሆነውና ሰዲቅ አልመሃዲ በመባል የሚታወቀው ግለሰብ የሚመራው የሱዳን የሲቪል መንግሥት በጠቅላይ ሚኒስትሩ እየተመራ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት «እስከ ዛሬ በሱዳን ህዝብ የፖለቲካ ሥልጣን ማማ ላይ የተፈራረቁት ግለሰቦችና የአመራር አካላት በሙሉ የኤርትራን ገንጣዮች በመረዳት የኢትዮጵያን መንግሥትና ህዝብ መበደላቸው ታላቅ ስህተት ነው። የኛ መንግሥት ይህንን ታላቅ የጥፋት ተግባር በዕነ በማውገዝ የኢትዮጵያን መንግሥትና ህዝብ ታላቅ ይቅርታ ይጠይቃል።

በሁለቱ እህትማማች አገሮች ውስጥ የሚካሄደውን አሳዛኝ የእርስ በርስ ጦርነት አቁመን በሠላምና በመልካም ጉርብትና አብረን ለመኖር የሚያስችሉንን ሁኔታዎች በጋራ ለመፍጠር በሚቻልባቸው ሁኔታዎች ላይ ለመነጋገር መጥተናል» አሉን።

በብዙ መቶ ሺህ ዜጎች ላይ ሞትና ጉዳት ያደረሰውን የሠላሳ ዓመታት የሲቪል ጦርነት ልናቆም መጥተናል በማለት አቃለውና አቅልለው በመናገራቸው ተገርመናል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ሰዲቅ አል መሃዲና ተከታዮቹ አዲስ አበባ መጥተው ይሄንን ሲሉን ጀብሐ በአብዮታዊው ሠራዊታችንና በሻዕቢያ ተመትቶ ከትግሉ ሜዳ የወጣ ሲሆን ሻዕቢያ ታላቅ ጉዳት ደርሶበት በመሸሽ በሣህል አውራጃ በናቅፋ ወረዳ ተራሮች ላይ ለመከላከል የመጨረሻ ምሽጉን መሽጎ በተቀመጠበት ጊዜ ነው።

በኛ በኩል የተሰጣቸው መልስ እስከ ዛሬ በሱዳን ህዝብ የፖለቲካ ሥልጣን ማማ ላይ የተፈራረቁት መንግሥታት ካደረሱብን ጥቃት ባሻገር የታዘብነው አንዳቸውም አንድም ጊዜ ቃላቸውን ያለማክበራቸውን ስለሆነ እናንተም የምትሉትን ስለማድረጋችሁና የገባችሁትን ቃል ተግባራዊ ታደርጋላችሁ ብለን ለማመን እንቸገራለን።

የኤርትራ ገንጣዮች በማካሄድ ላይ ያሉትን ዐረ-አንድነት ጦርነት እናንተ አቁሙትና ውጤቱ ካማረ እኛም በደቡብ ሱዳን ተመሣሣይ እርምጃ እንወስዳለን የሚል ነው።

የእስልምና እምነት አክራሪው በሱዳን ጠቅላይ ሚኒስትር የተመራው ልዑካን ከአዲስ አበባ ወደ ካርቱም ሲመለስ ዛሬ ማለትም እኔ ይህንን የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ በምፅፍበት ጊዜ በሱዳን ህዝብ የፖለቲካ ሥልጣን ላይ ያለው ጀነራል በሽር በወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት የሲቪሉን መንግሥት ገልብጦ ሥልጣን ያዘ።

ምዕራፍ ስልሣ

የደቡብ ሱዳን ህዝብ ነፃ አውጭ ንቅናቄ የተመሰረተበትን

የአዲስ አበባ ከተማን ትቶ ወደ ናይሮቢ. ኬኒያ መሄድ።

ከ1970 ዓመተ ምህረት ጀምሮ እስከ 1975 ዓመተ ምህረት ድረስ ያሉት ዓመታት የኢትዮጵያ ህዝብ የአብዮት ዐሮች ያወጁበትን ጦርነት ተከላክሎ ወደ አጥቂነት በመሸጋገር አብዮቱ የመጣባቸው የአሮጌው ሥርዓት ቅሪቶች፣ መሳፍንት፣ መኳንንትና ፊውዳል የመሬት ከበርቴዎች አብዮቱን መቀልበስ የሚቻላቸው መስሎአቸው የጀመሩትን የትጥቅ አመፅ መልሶ በማያንሰራራበት ሁኔታ ድባቅ የመታበት፣ ራሱን «የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ» በማለት የሚጠራውና በስም የአብዮት ካባ ደርቦ በተግባር ከዐረ ህዝቦች ጋር ተሰልፎ አብዮት የወጋውን አምስተኛ ረድፍ ድርጅት የቀጣበት፤

በተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ተቀጥረው መሣሪያ በመሆን አገራቸውንና ወገናቸውን የኢትዮጵያን ህዝብ መውጋት የጀመሩ ኋላ ቀር ጠባብ ብሄርተኞች ሲያካሂዱ የነበረውን ዐረ አንድነትና ፀረ አብዮት የትጥቅ አመፅ ያመከነበት፤

የተስፋፊውን የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ረግጦ ከኢትዮጵያ ምድር ያስወጣበት፤

በኤርትራ ክፍለ ሃገራችን ግንባር ቀደም የአረቦች ቅጥረኛና የጥፋት መልዕክተኛ በመሆን አገር ለመገንጠል የትጥቅ አመፅ የጀመረውንና ራሱን በአረብኛ ቋንቋ «ጀብሐ» ብሎ የሚጠራውን ድርጅት መልሶ በማያንሰራራበት ሁኔታ ደምስሶን ከትግሉ ውጭ ያደረግንበትና፤

ሻዕቢያን ከመላው የኤርትራ ምድር መንጥረን በማሳደድ በሣህል አውራጃ በናቅፋ ወረዳ ተራሮች ላይ በመመሸግ ህልውናውን ለማቆየት የመጨረሻውን የአልሞት ባይ ተጋዳይነት የመከላከል ውጊያ እንዲዋጋ ያደረግንበት ጊዜ ነበር።

ይህ ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝብ በታጋይ አብዮታዊ ሠራዊቱ የኮራበትና በእጅጉ የተደሰተበት ጊዜ ሲሆን በአንፃሩ ኢትዮጵያ ከእንግዲህ አለቀላት አበቃላት እያሉ ሲያሟርቱ የነበሩ የውስጥና የውጭ ጠላቶቻችን በሙሉ በሃፍረት አንገታቸውን የደፉበት ጊዜ ነበር።

በመላው ኢትዮጵያ የሚካሄደው የመደብ፣ የርዕዮተ ዓለም ትግልና በየጦር ግንባሩ የሚካሄደው የትጥቅ ፍልሚያ እንደቀጠለ ሆኖ ከ1975 እስከ 1980 ድረስ ባሉት ዓመታት ውስጥ በመሃይምነት ላይ አገር ዓቀፍ አብዮታዊ ዘመቻ በማካሄድ

ከጠቅላላው መሃይም የኢትዮጵያ ህዝብ ስልሳ በመቶውን ከመሃይምነት ጨለማ ነፃ ያወጣንበት ጊዜ ነበር።

በዚሁ ጊዜ ውስጥ በመሃይምነት ላይ ከሚካሄደው ዘመቻና በአገሪቱ የተለያዩ ማዕዘናት ከሚካሄደው ከጦር ሜዳው ፍልሚያ ጋር በተጓዳኝና በአገር አቀፍ ደረጃ ብሄራዊና አብዮታዊ የምርት ዘመቻ አውጀን አቆልቁሎ ወርዶ የነበረውን የአገራችንን ኢኮኖሚ ከወደቀበት በማንሳት የግብርናና የማዕድን ውጤቶች የሆኑ ምርቶችን በማምረትና በሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ማለትም በኢንዱስትሪው፣ በመሰረተ ልማቶች ወዘተ አገራችንን በመገንባት አሥራ ሁለት በመቶ ጠቅላላ የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገባችን ወዳጆቻችን ብቻ ሳይሆኑ ጠላቶቻችንም ያወጁብንን ጦርነት እየተከላከልን የተገኘ የኢኮኖሚ ዕድገት በመሆኑ በእጅጉ ተገረሙ።

በአገር ውስጥ በተለያዩ ግንባሮች የሚካሄዱት ፍልሚያዎች በኢኮኖሚውና በተለያዩ ማህበራዊ ዘርፎች የሚካሄዱት የአገር ልማትና ግንባታዎች እየተካሄዱ ሳለ በጎረቤታችን በሱማሌ መንግሥትና የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት በሚረዳቸው ሦስት የሱማሌ ህዝብ ነፃ አውጭ ግንባሮች በተለያዩ ቀጠናዎች በህብረት የሚያካሂዱት ዐረ ዚያድ ባሬ ውጊያ ስኬታማ ሆኖ የመንግሥቱን የአስተዳደር፣ የመከላከያና የብሄራዊ ደህንነት ተቋማትን በሙሉ አፈራርሰው አገሪቱን በመከፋፈል ተቆጣጠሩ።

ሦስቱ የሱማሌ ህዝብ ነፃ አውጭ ግንባሮች አገሪቱን ከፋፍለውና ተከፋፍለው በሰሜን፣ በመሀሉ ሱማሌና በደቡብ የተለያዩ ሦስት የአስተዳደር ክልሎችን ፈጥረው መምራትጀመሩ።

እጅግ ጀብደኛውና ተስፋፊው የፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ መንግሥት «ታላቋ» የሚላትን አዲስ ሱማሌ በአጎራባች አገሮች ኪሣራ ለመገንባት የነበረውን ምኞትና ብሎም ወረራ ደግፈው የኢትዮጵያን ህዝብ አብዮት ለማዳፈን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያን ለመከፋፈል ያደረጉት ጥረት ፋይዳ ቢስ ሆኖ በውርደትና በሽንፈት መምከን በእጅጉ ያስቆጣቸው የአካባቢው ዐረ ኢትዮጵያ የሆኑ፣ አድህሮት የኢትዮጵያ ኮሚኒስቶች የሶቭየት ህብረትን መንግሥት መልሰው ወደ ሱማሊያ ሊያመጡብን ነው በማለት መሪያቸውና ጌታቸው ለሆነው የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት መጮህ ጀመሩ። በዚሁ ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት የሚታገዘው የደቡብ ሱዳን ህዝብ ነፃ አውጭ ሠራዊት ደቡባዊ ነው የሚባለውን የሱዳን መንግሥት የአስተዳደር ክልል በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ የደቡቡን ክልል ርዕሰ ከተማ ጁባን ከበበ።

የደቡብ ሱዳን ህዝብ ነፃ አውጭ ሠራዊት በአደረሰበት ከባድ ጉዳት የመንግሥቱ ሠራዊት ፍፁም መዳከሙን ያስተዋሉና በተመሳሳይ ሁኔታ አረቦች ነን ከሚለው ጨቋኝና ዘረኛ መንግሥት ተነጥለው ነፃ ለመሆን የአርነት ትግል የጀመሩት የኑባና

የዳርፉር ክልል ህዝቦች ነፃ አውጭ ሠራዊቶች በመንግሥቱ ሠራዊት ላይ ሌላና ያልተጠበቀ ጥቃት በህብረት ሠንዝረው የተወሰነ መሬት ከመቆጣጠራቸው ባሻገር ከባድ ጉዳት አደረሱ።

የጥቃቱ ሰለባ በመሆን ተደጋጋሚ ውድቀት የደረሰበት የሱዳን መንግሥት የመከላከያ ሠራዊት በጀነራል ሰዋር ደሐብ መሪነት የፕሬዝዳንት ጃፋር ኤልኑሜሪን መንግሥት ከገለበጠ በኂላ በተፈጠረው አገር አቀፍ ሁለንተናዊ ቀውስ ምክንያት በሁለት ዓመታት ውስጥ በተከታታይ አንዱ ሌላውን በመገልበጥ የኑሜሪ፣ የሰዋር ደሐብ፣ የሰዲቅ አልመሃዲና የበሽር መንግሥት ተቀያየሩ።

ረጂም ድርጅታዊ ህልውና ያለውና በጥቁር አፍሪካ ብቸኛና አንጋፋ የሆነው የሱዳን ኮሚኒስት ፓርቲ የፕሬዝዳንት ኑሜሪ መንግሥት ሶቪየቶችን ከአገሩ ባስወጣበት ጊዜ ክፉኛ በመመታቱ ራሱን ከልሎ በህቡዕ ከሚንቀሳቀስበት ሁኔታ በመውጣት መሪዎቹ ወደ አዲስ አበባ መመላለስ በማዝውተራቸው ለዘመናት ፀረ ኢትዮጵያ ግንባር ፈጥረው በሱዳን መንግሥት መሣሪያነት ሲያጠቁን የኖሩ የአረብ መንግሥታት «ኢትዮጵያ የሱዳንን ህዝብ እንደ ሱማሌ ህዝብ ልታፈራርስ ነው፣ የእስልምና እምነትን አጥፍታ በሱዳን የኮሚኒስት ሥርዓት ልትፈጥር ነው» ብለው በመሸበር የሱዳንን ህዝብም አሸበሩት።

የአረቦቹን ጩኸት የሚጋራ ብቻ ሳይሆን መላውን የአረብ አድህሮት የሚመራው የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት «የአፍሪካ ቀንድ በሙሉ በኢትዮጵያ ቁጥጥር ሥር መሆኑ ነው» በማለት የአረቦችን ጩኸት ከማስተጋባት ባሻገር «በህብረትና በፍጥነት አስቸኳይ ርምጃ ወስደን ይህንን ሁኔታ መለወጥ ብቻ ሳይሆን ኤርትራን በመገንጠል አብዮቱን አዳፍነን አብዮታዊውን መንግሥት መጣል ነው መፍትሄው» በማለት አፅናናቸው።

በአንባቢዎች ዘንድ ይታወስ እንደሆነ በ1970 ዓ.ም መጀመሪያ የአፄ ኃይለሥላሴን ፊዊዳላዊ የዘውድ መንግሥት ገርስሰን አገራችን ኢትዮጵያ የምትመራበት የእድገት አቅጣጫ ህብረተሰብአዊ የሆነ ሥርዓት ወይንም «ሶሻሊዝም» ነው ብለን የገጠሩን የእርሻ መሬት የጉልተኞችና የመሬት ከበርቴዎች ገባር፣ ጪሰኛና ሎሌ ለነበረው ደሃ ገበሬ ይዞታ የሚያደርገውን የመሬት አዋጅ በአወጅን ማግሥት የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት መሪ የነበረው ፕሬዝዳንት ጂሚ ካርተር የመንግሥቱን የውጭ ስለላ ድርጅት አመራር አካላትና በአሜሪካ ስለ ኢትዮጵያ ያውቃሉ የሚባሉ ጥቂት አሜሪካዊ ግለሰቦችን ሰብስቦ «በማይታመንና ባልተጠበቀ ሁኔታ በፍጥነት በመራመድ ላይ ያለውን የኢትዮጵያ አብዮት ከዚህ በላይ ሳይሄድና ብዙ ሳይጠነክር በእንጭጩ መግደል የሚቻለን ከውስጥ ወይስ ከውጭ?» በተሰኙ የአብዮት ቅልበሳ አማራጮች ላይ ሲወያዩ እንደነበር በወቅቱ ለኢትዮጵያ ህዝብ ገልጠናል።

አሜሪካኖች በሁለት የአብዮት ቅልበሳ ሥልት ከተወያዩ በኋላ የደረሱበት ውሳኔ «አብዮቱን የሚመራው ደርግ የተወጣጣው ከመለዮ ለባሹ መሃል በመሆኑ የመላው የጦር ኃይሎች አባላት ድጋፍ ስለ አለው ያለ ወታደሩ ድጋፍና መሣሪያነት በአሁኑ ጊዜ ደርግን ከውስጥ ለመጣል ስለማይቻል ብርቱና ያልተቆጠበ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያለብን ከውስጥ የኤርትራን ገንጣዮችና የተቀሩትን ፀረ አብዮትና ፀረ መንግሥት የሆኑ የህብረተሰቡን ክፍሎች በተቻለ አስተባብረን በዋና ኃይልነት የሱማሌንና የሱዳንን መንግሥታት በሚገባ መጠቀም ነው» ብለው ጦርነት ያወጁብን መሆናቸውን የእናት ሃገር ጥሪ ባደረግንበት ጊዜ ለኢትዮጵያ ህዝብ ማስታወቃችን ይታወሳል።

በዋሽንግተን ውሳኔ መሰረት የሱማሌንና የሱዳንን መንግሥታት በዋና መሣሪያነትና በግንባር ቀደምትነት ከተለያዩ አድሐሪ የአረብ መንግሥታት ጋር በተቀናጀ ህብረት ታላቅ ፀረ ኢትዮጵያ ሴራ ወጠኑ።

የሴራው ወጣኝና አስተባባሪ የሆኑት አሜሪካኖች፣ አረቦች፣ የሱማሊዎችና የሱዳኖች ቅምር ፀረ ኢትዮጵያ ህብረት ግምባር ነው።

የኢትዮጵያ ጠላቶች ቅምር የሆነው የህብረት ግንባር ዓላማዎች ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ።

ሀ) በኢትዮጵያ፣ በኬኒያና በጅቡቲ ላይ የመስፋፋት ፅኑ ዓላማ ያለው ብቻ ሳይሆን በጦር ኃይል ግንባታም ረገድ በቂ ዝግጅት ያለውን የፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬን መንግሥት በመርዳት አጎላብተን በመገፋፋት ኢትዮጵያን በማስወረር አለኝታዎቼ ናቸው የሚላቸውን የባሌን፣ የሲዳሞንና የሐረርጌን ክፍለ ሃገራት እንዲቆጣጠር በማድረግ፤

ለ) የአረብ ሊግን ወክሎ የኤርትራን ገንጣዮች ከማደራጀትና ለውጊያ ከማስማራት ጀምሮ ለበርካታ ዓመታት ኢትዮጵያን ሲወጋና ሲያስወጋ የቆየውን የሱዳን መንግሥት በመርዳትና በማበረታታት የኤርትራ ገንጣዮች የሚያካሂዱትን ውጊያ ከሱማሌ መንግሥት የጦር ኃይል ጋር በማቀናጀትና በማስተባበር ኤርትራን አስገንጥለን የኢትዮጵያን አብዮታዊ መንግሥት ራሱ የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲጥለው በማድረግ የሚያካሂደውን አብዮት ማዳፈን የሚሉ ነበሩ።

የጠላቶቻችን ዕቅድና ያወጁብን ጦርነት ስኬታማ ቢሆን ኖሮ አብዮቱን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ህዝብ የረጂም ጊዜ ታሪክና ህልውና ማዳፈን ነበር የሚሆነው።

ከባሌ፣ ከሲዳሞ፣ ከሐረርጌና ከኤርትራ ክፍለ ሃገራት መነጠል በኋላ ኢትዮጵያ የምንላት እናት አገራችን ስለመኖሩዋ የሚያጠያይቅ ጉዳይ ነበር የሚሆነው።

መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን የዓለም ህዝብም እንደሚያውቀው በእናት ሃገር ጥሪ የኢትዮጵያን ህዝባዊና አብዮታዊ ሠራዊት በአጭር ጊዜ ውስጥ አደራጅተን ፈጥነን በመንቀሳቀስ የአሜሪካ መንግሥትና የጥፋት ግብረ አበሮቹ የኢትዮጵያን ህዝብ ማህበራዊ አብዮት ለማዳፈንና አብዮታዊውን መንግሥት ለመጣል የሚቻለው ከውስጥ ሳይሆን ከውጭ በሚሰነዘር የኢትዮጵያ ዐሮች የህብረት ግንባር ጥቃት ነው ብለው ያወጁብንን እጅግ አደገኛ የሆነውንና የመጀመሪያውን ወይንም አንደኛውን ጦርነት አከሸፈን፡፡

የውጭና የውስጥ ጠላቶቻችን በህብረት በሰሜን፣ በምስራቅና በደቡብ ወዘተ የአገራችን ክልሎች የሰነዘሩብንን ጥቃት በመመከትና ብሎም በማሳፈር መልሰን ከጦር ሜዳው ፍልሚያ በተጓዳኝ ፊታችንንና ከፊል ኃይላችንን ወደ ሃገር ልማትና ግንባታ ከማዞር ባሻገር በኢትዮጵያ የተደራጁና ለውጊያ የተሰማሩ ሦስት የፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ፀር የሆኑ የሱማሌ ህዝብ ነፃ አውጭ ግንባሮች በህብረት የሱማሌን መንግሥት የጦር ኃይል በውጊያ አንበርክከው የሱማሌን ግዛት ወይንም ምድር ለሦስት ተከፋፍለው በተቆጣጠሩበት ጊዜ ሌላው በኢትዮጵያ መንግሥት የሚታገዘው የደቡብ ሱዳን ህዝብ ነፃ አውጭ ግንባር በበኩሉ መላውን የሱዳን ደቡባዊ ክልል በውጊያ ከመንግሥቱ ሠራዊት አስለቅቆ በመቆጣጠር የደቡብ ሱዳንን ርዕስ ከተማ ጁባን ከበበ፡፡

በዚሁ ጊዜ ውስጥ ሌሎቹ የዳርፉርና የኑባ ክፍለ ሃገራት ነዋሪ ህዝቦች ነፃ አውጭ ነን የሚሉ ተዋጊ ኃይሎች በየክልላቸው፣ በመንግሥቱ የመከላከያ ሠራዊት፣ በሃገር ደህንነት ጥበቃ ተቋማትና በዐጥታ አስከባሪ ፖሊሶች ላይ ያልተጠበቁ ድንገተኛ አደጋዎችን ጥለው ከክልላቸው በማስወጣታቸው ምክንያት በተፈጠሩ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ቀውሶች የተነሳ በሁለት ዓመታት ጊዜ ውስጥ አራት የሱዳን መንግሥታት ተቀያየሩ፡፡

የኢትዮጵያ አብዮታዊ መንግሥት የሱዳንን መንግሥት እንደ ሱማሌ መንግሥት አፈራርሶ ህዝቡን በመከፋፈል የእስልምና እምነትን ለማጥፋትና የአፍሪካን ቀንድ በሙሉ ለመቆጣጠር ተቃርቧል በማለት የተሸበሩት የአረብ መንግሥታት የሱዳን መንግሥትን ጨምሮ ጩኸት በመስማታቸው የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት «የኢትዮጵያ መንግሥት የአፍሪካን ቀንድ ለመቆጣጠር ከሚያደርገው አደገኛ ጥረት ባሻገር የመከላከያ ኢንዱስትሪዎችን በመገንባት የአገር ውስጥ ሥሪት የሆኑ የተለያዩ የጦር መሣሪያዎችን ማምረት የጀመረ በመሆኑ በጥቂት ጊዜ ውስጥ በአካባቢው የማይበገር ኃይል ሆኖ በአፍሪካ ቀንድ ብቻ ሳይሆን በምሥራቅ አፍሪካ ኮሚኒዝምን እንደሚያስፋፋ አይጠረጠርም፡፡ ይሄ አደገኛ ሁኔታ ከመፈጠሩ በፊት ተንቀሳቅሰን አስቸኳይ እርምጃ መውሰድ አለብን» በማለት እንደ ልማዱ ግብረ አበሮቹን የአረብ አድህሮት መንግሥታት አስተባብሮ በአብዮቱ ማግሥት ከአሥራ አንድ ዓመት በፊት ያወጀብንን ጦርነት ካከሸፍን በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ የኢትዮጵያን አብዮት ከውስጥ ለማጥቃትና ለመቀልበስ የሚያስችሉ አመቺ ሁኔታዎች

ተመቻችተው ይገኛሉ በማለት ከዚህ የሚከተለውን ዐረ ኢትዮጵያና ፀረ አብዮት የሆነ የጦርነት ዕቅድ አቀደ።

1ኛ የኢትዮጵያ አብዮትና የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት ፀር የሆኑትን አድህሮት ማለትም፣ የኤርትራ፣ የትግራይና የኦሮሞ ብሄረሰቦች ነፃ አውጪ ነን የሚሉትን ገንጣዮች እንደየተልዕኳቸው ክብደት በትጥቅ፣ በተለያዩ ቁሳቁሶችና በገንዘብ ስጦታ ደልሎ በማግባባት በተለያዩ የአገሪቱ ማዕዘናት ማለትም፣ ሻዕቢያና ወያኔ በጥምረት በኤርትራ፣ ወያኔ ብቻውንና በተጨማሪ በትግራይ፣ በወሎ፣ በጎንደርና በአሰብ አስተዳደር ክልሎች፣

2ኛ የኦሮሞ ብሄረሰብ ነፃ አውጪ ነኝ የሚለው ድርጅት፣ በወለጋ፣ በኢሉባቡር፣ በሱዳሞ፣ በባሌና በሐረርጌ ክፍለ ሃገራት ተሰልፈው የአገሪቱን አንድነትና የኢትዮጵያን ህዝብ ማህበራዊ አብዮት በመውጋት የአገሪቱ አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊት የጦር ክፍሎች አንዱ ሌላውን እንዳይረዳ በየክልላቸው በመውጋት ኤርትራን ገንጥለው አብዮታዊውን መንግሥት ያፈርሱ ዘንድ በትግራይ ክፍለ ሃገር በአዲግራት አውራጃ ከተማ ሰብስቦ በአንድ ዐረ ኢትዮጵያና ዐረ አብዮት ግንባር በማስተባበርና በማዋቀር ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሻዕቢያ ኤርትራን፣ ወያኔ ከእነግ ጋር አዲስ አበባን እስኪቆጣጠሩ ድረስ በራሱ አመራር ስር አማክሎ መራቸው።

3ኛ በሁለተኛው የጦርነት አዋጅ ዋናውን ሚና በመጫወት ለሦስቱም ዐረ ኢትዮጵያና ዐረ አብዮት ድርጅቶች የአረብ መንግሥታትና አሜሪካ የሚሰጡትን ጥራትና ብዛት ያላቸው የዋርሶ ሥሪት የጦር መሣሪያዎች፣ ትጥቅና ሥንቃ ስንቅ፣ መድሃኒት ወዘተ በሱዳን በኩል በሱዳን መንግሥት አቀባይነት እንዲቀርብላቸው ሲደረግ የጦርነቱ ስትራቴጂካዊ ግብ ኤርትራን በመገንጠል የአብዮታዊውን መንግሥት የሽንፈትና ብሎም የውድቀት ጎዳና መጥረግ ስለሆነ የኦሮሞ ህዝብ ነፃ አውጭ ነኝ ከሚለው ድርጅት እጅግ በላቀ ሁለገብ እርዳታ ትኩረት የተሰጠው ለሻዕቢያ እና ለወያኔ ነበር

4ኛ በፀጥታ ማስከበር ሰበብ የአሜሪካ መንግሥት በጦር ኃይል ሱማሌ ውስጥ ጣልቃ በመግባት የኢትዮጵያ መንግሥት አደራጅቶ በማሰማራት ሁለገብ ድጋፍ የሚሰጣቸውን የሱማሌ ህዝብ ነፃ አውጭ ግንባሮችን ወግቶ በመደምሰስ ዳግም በሱማሌ ምድር ዐረ ኢትዮጵያና ፀረ አብዮት የሆነ አሻንጉሊት የሱማሌ መንግሥት አቋቁሞ እንደተለመደው በሲዳሞ፣ በባሌና በሐረርጌ፣ የኦሮሞ ህዝብ ነፃ አውጭ ነኝ ከሚለው ድርጅት ጋር በህብረት የኢትዮጵያን አንደኛ አብዮታዊ ሠራዊት በውጊያ ቀስፎ የመያዝ እቅድ አቅዶ ሳለ፣ ሱማሌ ስገባ የሚገጥመኝ የሱማሌ ህዝብ ነፃ አውጭ ግንባሮች ብቻ ወይስ የኢትዮጵያ ሠራዊት ጭምር እያለ ሲያመነታ ብዙ በመዘግየቱ የሱማሌ ህዝብ ነፃ አውጭ ግንባሮች ዓለም አቀፍ የፀጥታ ማስከበር ተልዕኮ ያለው ነው የተባለውን የአሜሪካ ሠራዊት ምንም ነገር ሳይሰራ በማጣደፍ

አራውጠው በመምታት በሚያሳፍር ሁኔታ ከሱማሌ ምድር ስለ አስወጡት በኢትዮጵያ ደቡብና ምሥራቅ ክልሎች ያቀደው የጦርነት እቅድ ሳይሰራለት ቀረ ::

ጠላቶቻችን ለሁለተኛ ጊዜ ላወጁብን ጦርነት በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ከውስጥ ጥቃት ለመሰንዘር የሚያስችል ወይንም የተመቻቸነው ለማለት ያስቻላቸውና ኤርትራን ገንጥለው አብዮቱን ለመቀልበስና አብዮታዊውን መንግሥት ለመጣል ይቻለናል ብለው የተማመኑበት ምክንያት ለአገሪቱ ሠላምና አንድነት፣ ለአብዮቱ ደህንነትና ጤናማ ሂደት ብቸኛ አለኝታና መከታ በሆነው አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊታችን ድርጅታዊ ላዕላይ መዋቅር ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን ያላቸውና ሠራዊቱን የሚመሩት ከፍተኛ ጀነራል መኮንኖች የሚያዙትን ሠራዊት ለማፈራረስ ከተቀሩት የአገር ውስጥ ጠላቶችና አሜሪካ ከፈጠረው የኢትዮጵያ ጠላቶች ግንባር ጋር የተባበሩ በመሆናቸው ነው::

በአብዮቱ ፍንዳታ ማግሥት የታወጀብንን የመጀመሪያውን የውስጥ ጥቃትና የሱማሌን ወረራ ለመከላከል ቁጥሩ ወደ ግማሽ ሚሊዮን የተጠጋ አብዮታዊና ህዝባዊ የመከላከያ ሠራዊት በአደራጀን ጊዜ ይህንን ያህል ቁጥር ያለው ሠራዊት የሚመሩ አብዮታዊ የጦር መኮንኖች ለማፍራት ባለመቻላችን ተቸግረን ህብረተሰብአዊ ወይንም «ሶሻሊስታዊ» ርዕዮት የተሰረፀባቸው ባይሆኑም አገር ወዳዶች ስለሆኑ በትግሉ ሂደት እየተማሩ ስለሚነቁ አብዮትና አገር አዳኝ የሆነውን የመከላከያ ሠራዊት ይመሩልናል ብለን ከአሮጌው ሥርዓት አያሌ ነባርና ከፍተኛ መኮንኖች መካከል በአንፃራዊ አመለካከት ከመለስተኛ እድሜ ጋር የተሟላ ጤንነት ያላቸውን፣ የረጂም ጊዜ የሥራ ልምድና በወታደራዊ አመራር ብቃት አላቸው ያልናቸውን መርጠን ወሳኝነት ባላቸው ከፍተኛ የሥልጣን ሥፍራዎች ላይ ከማስቀመጥ ባሻገር አብዮታዊ ጀነራሎችና ጀግኖች እያልን በማሞካሸት እየሸለምን በተፋጠነ የማዕረግ ዕድገት ያሳደግናቸው፤ ከኢትዮጵያ ህዝብ የኑሮ ደረጃ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛው እርከን ላይ ያደረስናቸውና አብዛኛዎቹ ከኛ ከአብዮቱና ከአገሪቱ የአመራር አካላት ጓዶች በላይ ከፍ ያለ ደመወዝ የሚከፈላቸውና በአጠቃላይ አነጋገር አገሪቱ በድሎትና በእንክብካቤ የያዘቻቸው ከፍተኛ ጀነራል መኮንኖች፤ አሮጌውን የፊውዶ ቡርዧ ሥርዓት የሚናፍቁና ህብረተ ሰብአዊውን ሥርዓት በዕኑ የሚጠሉ ሆነው ግን በሰፊው ሠራዊት ውስጥ ተከልለውና የአብዮቱ ደጋፊ በመምሰል አድፍጠው እያታለሉን የቆዩትን የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት በአገራችን ውስጥ በስውር በዘረጋው የስለላ መረቡ አማካኝነት በነቂስ የሚያውቃቸው ከመሆናቸው ሌላ እነሱም በተለያዩ ዘዴዎች ራሳቸውን ያሳወቁ በመሆናቸው በህቡዕ አሰባስቦ «የኢትዮጵያ ነፃ ወታደሮች ንቅናቄ» በተሰኘ ድርጅታዊ ስም አደራጅቶ ከታወቁት አንጋፋ የአገሪቱ አንድነትና የአብዮቱ ፀሮች ከሆኑ አድሀሪ ድርጅቶች ጋር አስተባብሮ ጦርነቱን እንዲመሩለት ከገለፅኳቸው የአገሪቱ ጠላቶች ጋር ለህዝባዊ አብዮቱ ውድቀትና ለአገሪቱ ጥፋት አሰለፋቸው::

በዚህ ዐረ ኢትዮጵያና ፀረ አብዮት ጦርነት የቅንጅት አሰላለፍ «የኢትዮጵያ ነፃ ወታደሮች ንቅናቄ» ተብየው ድርጅት የአመራር አባላትና አካላት የሥራ ድርሻ፣

1ኛ ለዋሽንግተንና ለሶስቱ ገንጣይ ድርጅቶች ቋሚና የማያቋርጥ ሁለገብ የሆነ ወታደራዊ የውጊያ መረጃ መስጠት፣

2ኛ ሶስቱ ገንጣይ ድርጅቶች ማለትም፣ ሻዕቢያ ወያኔና ራሱን የኦሮሞ ህዝብ ነፃ አውጭ ነኝ የሚለው ድርጅት በህብረት በአብዮታዊ ሠራዊታችን ላይ የሚያካሂዱትን ጥቃት ማስተባበር፣

3ኛ በፍልሚያዎቹ ሜዳዎች ላይ አብዮታዊ ሠራዊታችንን ለአደጋ፣ ለሽንፈትና ብሎም ለለየለት ውድቀት የሚዳርጉትን የአመራር ሻጥሮች መስራት፣

4ኛ አገራቱ በብዙ ድካምና በብዙ ገንዘብ ከውጭ ባዕዳን አገር አስመጥታ ለአብዮታዊ ሠራዊታችን ያስታጠቀችውን እጅግ ዘመናዊ የሆኑ የተለያዩ ከባድና በርካታ መሣሪያዎችን ጠላቶቻችን ከሠራዊታችን ላይ እየገፈፉ እንዲታጠቁ ማድረግ ዋና ዋናዎቹና ግንባር ቀደም የሥራ ድርሻዎቻቸው ናቸው።

በኤርትራ ገንጣዮች ያካሄዱት አገርን የመገንጠል ውጊያ ከተጀመረበት እስከ አለቀበት ጊዜ ድረስ፣ አውቶማቲክ ጠብመንጃዎችን ከመሰሉ ቀላል መሣሪያዎች፣ ከእጅና ከጠብመንጃ ቦምቦች (ሞርተሮች) ወይንም ከአዳፍኔዎችና ከመስክ ፈንጂዎች በስተቀር አረቦች አንድም መድፍና መድፍን የመሣሰሉ ከባድ መሣሪያዎች፣ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎችንና ታንኮችን ወዘተ አልሰጧቸውም።

የተለያዩ የአየር መቃዎሚያዎችን፣ ሚሳይልና ሮኬት መወንጨፊያ መሣሪያዎችን፣ የተለያዩ ከባድ መድፎችን ተዋጊ ብረት ለበስ ተሽከረካሪዎችንና ታንኮችን ወዘተ ለበርካታ ዓመታት ሊገለገሉባቸው ከሚያስችሉ የጥይት ክምችቶች ጋር በማስረከብ ሻዕቢያ ተዋጊ አውሮፕላኖች ብቻ ሲቀሩት የተቀሩትን የመከላከያ ሠራዊታችን የታጠቃቸውን አብዛኛውን ከባድ መሣሪያዎቻችንን በማስረከብ አስታጥቀው የገነቡት የሻዕቢያ ሜካናይዝድ ሠራዊት ከ11 ዓመት በኋላ ከናቅፋ ተራሮች ወርዶ አብዮታዊ ሠራዊታችንን በራሳችን መድፎች፣ ብረትለበስና ታንኮች ወዘተ እየደበደበ በመንዳት አስመራን መልሶ ለመቆጣጠር ቻለ። በዓለም ወታደራዊ ታሪክ በራሷ መሣሪያ በጦር ሜዳ የተረታች አገር ኢትዮጵያ ብቻ ትመስለኛለች።

የምፅዋን አውራጃ፣ የአስመራንና የምፅዋን ከተሞች የሚያገናኘውን አስፋልት የየብስ ተሽከርካሪ መንገድ፣ የምፅዋን ከተማና ወደባችንን ከገንጣዮች ጥቃት ይከላከል የነበረው ጦራችን አዛዥ፣ (የምፅዋ ቴዎድሮስ) የተሰኘ ስም የተሰጠውና ወደር የሌለው ጀግና በብ/ጀነራል ተሾመ ተሰማ የተመራው ጀግና ሠራዊታችን ብቻውን በሻዕቢያ ሜካናይዝድ ጦር ተከቦ እየተደበደበ አልበገር በማለቱ "የኢትዮጵያ ነፃ

አውጭ ድርጅት" ተብዬው አባል የሆኑት፣ ብ/ጀነራል ጥላሁን ክፍሌ እና ብ/ጀነራል አሊ ሃጂ የሚባሉት የአሜሪካን ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ቅጥረኞች በዋሽንግተን ትዕዛዝ ለሻዕቢያ አድረው የሻዕቢያን ጦር እየመሩ አምጥተው (ላለቀና ዋጋ ለሌለው ውጊያ በከንቱ አትሙቱ፣ እጃችሁን ለሻዕቢያ ስጡ) በማለት በቅድሚያ በደብዳቤዎች ቀጥሎ ወደ ሠራዊታችን መከላከያ በመጠጋት ቀርበው በድምፅ ማጉያ ቢወተውቱና ክፉኛ ቢፈታተኑትም ሳይበገር ለሳምንታት በሚያስደንቅ ጀግንነት ሲዋጋ ቆይቶ የተረታው በሻዕቢያ ጦር ሳይሆን በራሳችን በኢትዮጵያ መንግሥት መድፎችና ታንኮች ጥቃት ነው::

በትግራይ የ3ኛው አብዮታዊ ሠራዊታችን የጀርባ አጥንት ወይም ደንደስ የነበረውና ስመጥር በሆኑ ጀግኖች መኮን ኖቻችን፣ በጀነራል አዲስ አግላቸው፣ በጀነራል ለገሰ አበጀ፣ በጀነራል አርአያ ዘርአይ እና በጀነራል ኃይሉ ከበደ የተመራው 604ኛው ኮር ጀግና ሠራዊት ሽሬ እንዳስላሴ ላይ የፈረሰው በወያኔ ኃይል ሳይሆን በራሳችን ከባድ መሣሪያዎችና ታንኮች ተደብድቦ ነው::

ይህ የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ ሁለት አብዮታዊ ሠራዊታችን በሰሜን ኢትዮጵያ ከኢትዮጵያ ፀሮች ጋር ያደረገውን የመጨረሻ ትግል የምተርክበት ቅፅ ባለመሆኑ እንጂ ከዚህ በላይ በጥቂቱ የገለፅኳቸውን ስለመሳሰሉ እጅግ አስቆጪ፣ እጅግ አሳፋሪ ድርጊቶች ብዙ ማለት ይቻላል::

ሻዕቢያ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም "የኢትዮጵያ ነፃ መኮንኖች ንቅናቄ" በማለት ያደራጃቸው ምንደኛ ጀነራሎቻችን ባስታጠቁት መሣሪያዎቻችን ስለተመካ አስመራን መልሶ መቆጣጠሩ ሳያረካው ቀርቶ ወያኔን አጅቦ "የኦሮሞ ህዝብ ነፃ አውጭ" ነኝ ከሚለው ሌላው ከሃዲና ቅጥረኛ ድርጅት ጋር ሶስቱም በህብረትና በዋሽንግተን መሪነት ወደ አዲስ አበባ ለመንቀሳቀስ ያስቻላቸው ሁኔታ በኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ቅፅ ሶስት በስፋትና በዝርዝር ይገለፃል::

ወያኔ ከግብረ አበሮቹ ጋር በህብረት አዲስ አበባን በተቆጣጠረ ጊዜ በብዙ ድካምና በከፍተኛ የገንዘብ ወጪ ያቋቋ ምነው የደቡብ ሱዳን ህዝብ ነፃ አውጭ ንቅናቄ አመራር አካላት በሙሉ ኢትዮጵያን ትተው ከአዲስ አበባ ወደ ናይሮቢ ከተማ ሄዱ::

የንቅናቄው ሠራዊት ጥሩ ሥልጠና የነበረውና ከፍ ያለ ተዋጊ የሰው ኃይል የነበረው ከመሆኑ ሌላ በትጥቅም መጠንና ጥራት ከሱዳን መንግሥት ሠራዊት የማይተናነስ ስለሆነ ከኢትዮጵያ መንግሥት በቋሚነት ይቀርብለት የነበረውን የጥይት አቅርቦት የዩጋንዳ፣ የዛምቢያና የዚምባብዌ መንግሥታት ኢትዮጵያን ተክተው ማቅረብ ስለቻሉ ውጊያው ሳይተጓጎል ወይንም ለቀናት እንኳን ሳያሰልስ ቀጥሎ በመጨረሻ በሱዳን ሥልጣን ላይ የወጣው የጀነራል በሽር መንግሥት በውጊያው ቢገፋ ከውድቀት በስተቀር የሚያተርፈው ነገር እንደሌለ በመረዳት በሠላም ድርድር

የደቡብ ሱዳንን ህዝብ ነፃ መንግሥት መቋቋም ለመቀበል ፈቃደኛ መሆኑን በመግለፅ ከነፃ አውጪው ንቅናቄ አመራር አካላት ጋር በኬኒያ ርዕሰ ከተማ ናይሮቢ ላይ በደረሱበት ስምምነት መሰረት የደቡብ ሱዳን ህዝብ እስላማዊና አረባዊ ነኝ ከሚለው የሱዳን መንግሥት የጭቆናና የዘር መድሎ አገዛዝ ነፃ በመሆን በራሱ መንግሥት ተመሪና ተዳዳሪ ነፃ ህዝብ ሆነ።

በሱዳን ምዕራብና ምሥራቃዊ ክልሎች የሚኖሩ የዳርፉርና የኑባ ክፍለ ሃገር ህዝቦች እንደ ደቡብ ህዝብ አረብና እስላም ነኝ በማለት የሸሪያ ህግ መስርቶ በሃይማኖትና በዘር መድሎ ጭቆና ከሚገዛቸው መንግሥት አገዛዝ ነፃ ለመውጣት የሚካሄዱትን የትጥቅ ትግል ቀጥለዋል።

ደቡብ ሱዳን ከግማሽ ሚሊዮን ካሬ ኪሎ ሜትር በላይ ስፋት ያለው፣ ምድሩ በጠቅላላ ማለት ይቻላል ለም አፈር የለበሰና ውሃ ገብ፣ በደን የተሸፈነ፣ በቤት እንስሳትና በዱር አራዊት፣ በወርቅ ማዕድንና በነዳጅ ዘይት ሀብት የታደለ አገር ስለሆነ ህዝቡ በሠላም አብሮና ተሳስቦ መኖር ከቻለና መንግሥት የህዝብ አመራርና የአገር ግንባታ አቅም ከገነባ በምሥራቅ አፍሪካ አንዱና ጠንካራ አገር እንደሚሆን አያጠያይቅም።

በአብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊታችን ትግልና መስዋዕትነት፣ በአብዮታዊ መንግሥታችን ጥረት ለብዙ ዘመናት ሲጋፉንና ሲያደሙን በኖሩት ተስፋፊ የጐረቤት ጠላቶቻችን ላይ በወሰድነው እርምጃ በማያንሰራሩበት ሁኔታ የእጃቸውን ያገኙ ስለሆነ ከእንግዲህ ወዲያ ሱማሌና ሱዳን ለአገራችን ችግርፈጣሪ ይሆናሉ ተብሎ አይታሰብም።

ወደ ፊት የወያኔን ጎጠኛ ሥርዓት አስወግደው በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥልጣን ማማ ላይ የሚቀመጡ መንግሥታት ሁሉ ከደቡብ ሱዳን መንግሥትና ህዝብ ጋር የጠበቀና የማያቋርጥ ወዳጅነት መፍጠር ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም እስከዛሬ እንደ አደረጉት ወደፊት አረቦች በአካባቢው ለመስፋፋት የሚያደርጉትን ጥረት በጋራ ለመከላከል አስተማማኝ የትግል አጋር ሊሆኑን ይችላሉና።

የቃላቶች ትርጉም

ሆርሻ- ቴክኒካዊ የፈጠራ፣ የማምረቻ፣ የእደሳና የጥገና ወዘተ የሚከናወኑበት ህንፃ ወይም ስፍራ ማለትነው።

ሉባ- ጥንታዊው የኦሮሞ ማህበረሰብ ይተዳደርበት የነበረው ገዳ በመባል የሚታወቀው የጎሳ ማህበር መዋቅር ውስጥ የመከላከያ፣ የፍርድና የአስተዳድሩን ስራ በበላይነትና በወል እንዲመሩ በጎሳው ማህበር ጠቅላላ አባላት ስብሰባ የሚመረጡ ከ40 እስከ 48 ዓመት እድሜ ያላቸው የጎልማሶች ቡድን የወል መጠሪያ ስም ነው።

ላዕላይ መዋቅር- የአንድ ድርጅት ወይም ተቋም በተለይም እኔ በተጠቀምኩበት ረገድ፣ የአንድ ፖለቲካ ሥርዓተ ማህበር፣ የአንድ ወይም የፖለቲካ ድርጅት ከፍተኛ የአመራር ማዕከል መዋቅር ሲሆን በጠቅላላ አነጋገር ፖለቲካው ማለት።

ሕቡዕ- የቃሉ ምንጭ ግዕዝ ነው። ትርጉሙ የተደበቀ ወይም የተሰወረ ማለት ነው።

ማህበረሰብ- በህብረተሰብ የእድገት ታሪክ ሂደትና ማህበራዊ አደረጃጀት፣ ከቤተሰብ፣ ከቤተዘመድ፣ ከመንደር ወይም ከጎጥ በላይ የሆነና በርካታ ጎጦችን ወይም መንደሮችን ያሰባሰበና በሦስተኛ ደረጃ የሚገኝ ማህበራዊ ድርጅት ነው።

መስመራዊ መኮንኖች- ከሻለቃ ማዕረግ በታች ላሉ የጦር መኮንኖች የተሰጠ መለያ ነው።

ቅልፈት- በኢትዮጵያ አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊት ውስጥ የበርካታ የጭነት ተሽከርካሪዎች ክትትል ወይም ጉዞ ወይም የተሽከርካሪዎች ጋተሎ ማለት ነው።

ቅምር- ጥምር፣ ቅልቅል፣ ስብስብ ወይም ስብጥር ማለት ነው።

ቡርዧ- ቃሉ ከፈረንሳይ ቋንቋ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙ ከበርቴና ገዥ መደብ ማለት ነው።

ብሄር- በህብረተሰብ የእድገት ሂደት ታሪክና ማህበራዊ አደረጃጀት ከፍተኛውና የመጨረሻው ሲሆን ይህ ቃል ከዘር፣ ከነገድና ከጎሳ መግለጫነት እጅግ የሰፋናየ ላቀ ትርጉም ያለው፣ የአንድ አገር ወይም ህዝብ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ወዘተ በጠቅላላው ሁለንተናዊ ማህበራዊ እርከንን የሚያሳይ የእድገት መግለጫና በተለያዩ የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ አያሌ ማህበረሰቦችና ብሄረሰቦችን ያካተተ ማህበራዊ ድርጅት ነው።

ብህርታዊ- የተለያዩ ወይም በርካታ ማህበረሰቦች፣ ብሄረሰቦችና የቋንቋ ቤተሰቦች የተካተቱበት ወይም የተቃመሩበት የቋንቋ ቤተሰብ ወይም ህብረተሰብ ማለት ነው።

ባለ ሌላ ማዕረግተኞች- ከመጀመሪያው የውትድርና ማዕረግ ማለትም፣ ከምክትል የአስር አልቅና ጀምሮ እስከ ሻለቃ ባሻ ድረስ ያሉትን በሌላ አነጋገር መኮንን ያልሆኑትን ወታደራዊ ሹማምንት መለያ ስም ነው።

ታህታይ መዋቅር — አንድ አገር በሚመራበት ማህበራዊ ወይም ፖለቲካዊ ሥርዓት ውስጥ ፖለቲካውን ወይም ላዕላይ መዋቅሩን የተሸከመው ወይም ለፖለቲካው መሰረት የሆነውን ኢኮኖሚውን ማለትም የመሬቱ፣ የግብርናው፣ የማዕድኑ፣ የኢንዱስትሪው፣ የገንዘቡ ወዘተ አደረጃጀት መዋቅር ማለት ነው።

የምርት ኃይሎች- አምራቹን ሰርቶ አደር ህዝብና የሚያመርትባቸውን የማምረቻ መሳሪያዎችን ያጠቃለለ የወል ስም ነው።

ጎጥ- ይህ ቃል በአብዛኛው የአገራችን ሰሜናዊ ክልል ነዋሪ ህዝብ መንደር ወይም ቀበሌ ለማለት የሚጠቀምበት ቃል ነው።

አባወራ- ቃሉ የተገኘው ከኦሮሞ ብሄረሰብ ሲሆን ትርጉሙ የቤተሰብ ሃላፊ፣ የቤተሰብ አባት ወይም አውራ ማለት ነው።

ጠገግ- የድርጅታዊ፣ መዋቅራዊ ተዋረድ፣ አስተዳደራዊ ተዋረድ ወይም የእዝ ሰንሰለት ማለት ነው።

ካድሬ- በምሁራን ዘንድ የሚታወቀው ለአንድ ልዩና ምርጥ ስራ የተመረጠ አነስተኛ የሰው ቁጥር ወይም ቡድን ማለት ሲሆን በማርክሲያዊያን ትርጉም ግን መሪ፣ አስተማሪ፣ መልካም ምሳሌና አርአያ ማለት ሲሆን፣ የሠራተኛው መደብ ግንባር ቀደም መሪ የሆኑ ድርጅቶች ወይም ፓርቲዎች አባላት ሁሉ የሚጠሩበት ስም ነው።

ግብረ-ኃይል- ይህ ቃል በወታደራዊ ተቋሞች ውስጥ ብቻ ሳይሆን በሲቪሉም ህብረተሰብ ውስጥ እንደ አስፈላጊነቱ ለተለያዩ ተግባራት ሁሉ ገብ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። በድህረ አብዮት በአብዮታዊ ሠራዊታችን ውስጥ በተለይ በሰሜኑ ውጊያ የተጠቀምንበት ወታደራዊ አደረጃጀት ነበር። ግብረ ኃይል የምንለው የጠላትን መጠንና አይነት፣ የሚዋጋበትን የመልክአ ምድር ዓይነትና ባህሬ ካመዛዘንን በኋላ ይህንን ጠላት ለመደምሰስ ይችላል ብለን በማደራጀት የምንወረውረው ወይም የምናሰልፈው የጦር ክፍል ነው። አንድ ወጥ እግረኛ ጦር ወይም ሜካናይዝድ ወይም ታንከኛ ብቻ ወይም የነኝህ ሁሉ ቅምር ሊሆን ይችላል።

ሜካናይዝድ ጦር- ቃሉ ከእንግሊዘኛ ቋንቋ የተወሰደ ሲሆን የዚህን ጦር ዓይነትና ባህሪ በትክክል የሚገልፅ ስም በአማርኛ ትርጉም ባለመገኘቱ በሠራዊታችን ውስጥ የእንግሊዝኛውን ቃል እንዳለ ስንጠቀምበት ኖረናል። አሁንም ትርጉም የተገኘለት አይመስለኝ። ሜካናይዝድ ጦር ማለት መቶ በመቶ በወታደራዊ የየብስ ተሽከርካሪዎች የሚጓዝ ሞተራይዝድ እግረኛ ጦርን፣ መቶ በመቶ በብረት ለበስ ተዋጊ ተሽከርካሪዎች

የሚንንዝና የሚዋጋ ብረት ለበስ እግረኛና የታንከኛ ጦር ቅምር ማለት ነው። ሜካናይዝድ ጦር ከፍተኛ የመንቀሳቀስ ችሎታና ከፍተኛ የተኩስ ኃይል ያለው ፀረ-እግረኛ ጦር ነው።

ዋቢ መጻህፍት

ታሪኩን ለመፃፍ ዋና መሰረት ያደረኩት ትዝታዎቼን ወይም ትውስታዎቼን ነው። ትውስታዎቼም ሁለት አይነት ናቸው። ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮት ዋዜማ ጀምሮ ከአብዮታዊ ሠራዊታችን፣ ከኢትዮጵያ ህዝብና ከኢትዮጵያ አብዮታዊያን ጋር ከአስተባባሪነት እስከ መሪነት የዋኘሁበት አብዮት በመሆኑ የተሰረፁብኝ የየእለቱ ተግባራችን ትውስታዎቼ ዋና መሰረቶች ናቸው።

ሌሎች ትውስታዎቼ፣ በቅድመ አብዮት ለረጅም ጊዜ፣ በድህረ አብዮት ለተሰወኑ ጊዜያቶች ያነበብኳቸው የተለያዩ የታሪክ፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የፍልስፍና ወዘተ መጻህፍትና ማርክሳዊ ሌኒናዊ የሆኑ አብዮታዊና ርዕዮተ ዓለማዊ መጻህፍት ናቸው።

እነኝህ መጻህፍት ከመበርከታቸውና ያነበብኩበትም ጊዜያዎች የዚያን ያህል ከመርዘማቸው በላይ መጻህፍቱ በእጀ ስለማይገኙ ያስታወስኳቸውን ጥቂቶቹንና በቅርቡ በስደት ላይ ሆኜ ያገላበጥኳቸውን ለዋቢነት ከዚህ እንደሚከተለው አቅርቢያቸዋለሁ።

በአገር ውስጥ የተዘጋጁ:-

አለቃ ታዬ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ (አዲስአበባ፣ 1964 ዓ.ም)

ላጲሶ ጌ. ደሌቦ፣ የኢትዮጵያ ረጅም የህዝብና የመንግስት ታሪክ (አዲስ አበባ፣ 1982 ዓ.ም)

ላጲሶ ጌ. ደሌቦ፣ የኢትዮጵያና የገባር ስርዓትና ጀምር ካፒታሊዝም (አዲስ አበባ፣ 1983 ዓ.ም)

ጳውሎስ ኞኞ፣ የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት (አዲስ አበባ 1980 ዓ.ም)

ተክለፃዲቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ይኩኖ አምላክ እስከ አፄ ልብነ ድንግል (አዲስ አበባ፣ 1956 ዓ.ም)

ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ልብነ ድንግል እስከ አፄ ቴዎድሮስ (አዲስአበባ፣ 1965)

ተክለፃዲቅ መኩሪያ፣ አፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት (አዲስ አበባ፣ 1981 ዓ.ም)

ተክለፃዲቅ መኩሪያ፣ አፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት (አዲስ አበባ፣ 1982)

ተክለፃዲቅ መኩሪያ፣ አፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት (አዲስ አበባ፣ 1983)

ተክለፃዲቅ መኩሪያ፣ የግራኝ አህመድ ወረራ (አዲስ አበባ፣ 1966 ዓ.ም)

ነጋድረስ አፈወርቅ፣ ዳግማዊ ምኒልክ (ሮማ፣ 1901 ዓ.ም)

አቤ ጉበኛው፣ አንድ ለናቱ (አዲስ አበባ፣ 1983 ዓ.ም)

መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አርአያ እና መዝገቡ ምትኬ፣ ጥርስ የገባች አገር (በጆን ሃዝዊይ የተፃፈ) (አዲስ አበባ፣ 1986 ዓ.ም)

ሚሊዮን ነቅንቅ፣ ትልቋ ኢትዮጵያ የብዙሃን ነገዶች ማህረሰብ የረጅም ዘመናት እድገት (በዶናልድ ሌቪን የተፃፈ) (አዲስ አበባ፣ 1993 ዓ.ም)

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ህይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ ቅፅ 1 (አዲስ አበባ፣ 1965 ዓ.ም)

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ህይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ ቅፅ 2 (አዲስ አበባ፣ 1966 ዓ.ም)

ይልማ ደሬሳ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ በአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን (አዲስ አበባ፣ 1959 ዓ.ም)

ከአገር ውጪ የተዘጋጁ፡-

Badoglio, Pietro, The war in Anyssinia (London: Methuen, 1973)

Boca, Angelo Del. The Ethiopian war, 1935-1941 (Chicago: The University of Chicago University press, 1969).

Dye, William Mc E. Moslem Egypy and Christian Ethiopia (New York: Atkin & Prout printers, 1880)

Hardie, Frank. The Abyssinian Crisis (London: B.T. Batsford, Ltd, 1974)

Makin, William J. War Over Ethiopia (London: Jarrolds Ltd, 1935)

Pankhurst, Sylvia. Counsel for Ethiopia: A Biographical Essay on Ethiopia Anti-Fascist and Anti-Colonialist History 1934-1960 (Hollywood: Tsehai Publishers, 2003)

Pankhurst, Richard #The Emperor Theodore and the Question of Foregin Artisans in Ethiopia ,; Boston University papers on Africa, V.2 African History, J.Butler, ed. (Bost on, 1966) 217-235

Skinner, Robert. Abyssinia of Today: An Account of the first Mission sent by the American Government to the Country of the Kings (1903-1904) (London: E.Arnold; New York; Longmans, Green & Co. 1960)

ትግላችን

ቅፅ ሁለት

ሌ/ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም

ጀነራል ተፈሪ የደርጉ ሊቀመንበር እኔ ነኝ ብለው ሲገልጹ ሌላው የበታች ሹም ተነስቶ ክቡር ጀነራል የደርጉ መሪ ሻለቃ መንግሥቱ እንጅ እርስዎ ያለመሆንዎ የአደባባይ ምስጢር ነውና ከእኔ በፊት የተናገረው ጓድ እንዳለው እኔም በከንቱ ወርቃማ ጊዜዎን አያባክኑ የሚል ሃሳብ አቀርባለሁ ሲል ሌሎቹም እንደዚሁ እየተነሱ ብዙ ሕገወጥ የብልግና ነገር ተናገሯቸው፡፡ ሁኔታው ሊቀመንበር ተፈሪን የሚያሳፍርና የሚያዋርድ ቢሆንም በታወቀ ትዕግስታቸው የበታች ሹማምንቱን ሃሳብ ለማስለወጥ ብዙ ሙከራ ካደረጉ በኋላ ለዛሬ እዚህ ላይ እናቁምና እናንተም ወደየሰፈራችሁ ሄዳችሁ እንደገና መክራችሁ የሚያስማማንን መፍትሔ ይዛችሁ እንደምትመለሱና ዳግም እዚሁ እንደምንገናኝ ተስፋ አደርጋለሁ በማለት ካሰናበቷቸው በኋላ ስልክ ደውለው የደረሰባቸውን ውርደት ካስረዱኝ በኋላ ሰዎቹ እኔ የምለውን ሊያዳምጡና ሊቀበሉ ቀርቶ ከኔ ጋር ለመነጋገርም ፍላጎት የላቸውምና ምን ባደርግ ይበጃል ትላለህ? ብለው ጠየቁኝ፡፡

✪ ✪ ✪ ✪ ✪ ✪ ✪ ✪ ✪

ብ/ጀነራል ተፈሪ በንቲን የደርጉ ሊቀመንበር ማድረግና ብ/ጀነራል ጌታቸው ናደውን በቅድሚያ፣ የምድር ጦር አዛዥ በኋላም የኤርትራ ክፍለ ሃገር አስተዳዳሪና የመላው የሰሜን መለዮ ለባሽ ሠራዊት አዛዥ በማድረግ ረገድ የተሰራው ታላቅ ስህተት የማንም ሳይሆን የእኔ ነበር፡፡

✪ ✪ ✪ ✪ ✪ ✪ ✪ ✪ ✪

እነ ኡስማን ሳላሕስቤ፣ እነ ረመዳን መሐመድ ኑርና እነ ተማሪ ኢሳያስ አፈወርቅ ከጀብሐ አፈንግጠው ራሱን ሻቢያ ብሎ የሚጠራውን የጀብሐ አንጃ ድርጅት ከአቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ሁለቱ ገንጣይ ድርጅቶች በሥልጣን ሽሚያ ሲዋጉ ኖረው በዚህ ጊዜ ውስጥ ማለትም በ1969-1970 ዓመታቶች የኢትዮጵያ መንግሥት ጦር በብዙ የውጊያ ግንባሮች በተወጠረበትና ተዋጊ የሰው ኃይል እጥረት በደረሰበት ጊዜ ከሱማሌ መንግሥት ጋር ተባብረው የኢትዮጵያን አብዮታዊ መንግሥት በመጣል ኤርትራን ይገነጥሉ ዘንድ ያስታረቋቸውና ያስተባበሯቸው በሰላም ፍሊጋና በእርቅ ሰበብ ጀነራል አማን መርጠው የላኳቸው የጥፋት ልዑካን ናቸው፡፡

✪ ✪ ✪ ✪ ✪ ✪ ✪ ✪ ✪

ሞያውና ብቃቱ አላቸው ተብሎ ከተሰባሰቡት መኰንኖች እኔም አንዱ ከመሆኔ ሌላ ከብርጌዱ መምሪያ መኰንኖችም አንዱ በመሆኔ በገነት ጦር ትምህርት ቤት ሻምበል ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ በኰሎኔልነት ማዕረግ የሜካናይዝዱ ብርጌድ አዛዥ በሆኑ ጊዜ በሻምበልነት ማዕረግ የቅርብ ረዳታቸው በመሆን አውቃቸዋለሁ፡፡ አለባበስ የሚያውቁ፣ ቁንንና ኩሩ፣ በጣም አጭር የማይባል አማካኝ ቁመት፣ ከላይ እስከ ታች የተደላደለና የተገነባ ሰውነት፣ ገብስማ ፀጉርና ግርማ ሞገስ ያላቸው መኰንን ናቸው፡፡ ጠቅላላ ባህሪያቸውንና ወታደራዊ አመራራቸውን ስወድ፣ የማልወድላቸው ነገር ቢኖር ጀብደኝነታቸውንና ጉረኝነታቸውን ብቻ ነበር፡፡

✪ ✪ ✪ ✪ ✪ ✪ ✪ ✪ ✪

507 ግብረ ኃይል ከሞላ ጎደል ሁለት ክፍለ ጦር ሲሆን የግብረ ኃይሉ አዛዥ ኮሎኔል ካሳ ገብረማሪያም፣ የአንደኛው ክፍለ ጦር አዛዥ ሌ/ኮሎኔል አይተነው በላይ ሲሆን የሁለተኛው ክፍለ ጦር አዛዥ ሌ/ኮሎኔል ሰይፉ ወልዴ ነበሩ፡፡ ጦሩም ሆነ መሪዎቹ ለወሬ ነጋሪ እንኳን አልተረፉም፡፡

ዋጋ 170.00 ብር